አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና

(Caacceessa Afoola Aadaa Saalaa fi Eechii Iyii Vii/Eedsii: Haala Qabatamaa Oromoo Tulamaaatiin)

በ

በጅጋ ተካ ቡኔ

2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ

የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና

(Caacceessa Afoola Aadaa Saalaa fi Eechii Iyii Vii/Eedsii: Haala Qabatamaa Oromoo Tulamaaatiin)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

በጅጋ ተካ ቡኔ

አማካሪ፡- ማሞ ሂቦ (ዶ/ር)

2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና

(Caacceessa Afoola Aadaa Saalaa fi Eechii Iyii Vii/Eedsii: Haala Qabatamaa Oromoo Tulamaaatiin)

በ

በጅጋ ተካ ቡኔ

2008 ዓ. ም.

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

የአማካሪ ሥም ፊርማ

________________________________ ________________

የውስጥ ፈታኝ

የውጭ ፈታኝ

ምሥጋና

በዚህ ጥናት ውስጥ በልዩ ልዩ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍ እና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለሥራዬ መሳካት የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጣው አማካሪየ ዶ/ር ማሞ ሂቦ ዋቤ ላደረገልኝ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ፣ የእውቀት ምክር እንዲሁም በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ያለመሰልቸት የቅርብ ሙያዊ እገዛው ስላልተለየኝ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። በፎክሎር የትምህርት ዘርፎች የጠለቀ እውቀት እንዲኖረኝ ላስተማሩኝ የኮርስ መምህራን እና ይህንን ጥናት በየደረጃው በመፈተን ገንቢ አስተያየት ለለገሱኝ ምሁራን በሙሉ ምሥጋናዬ የጎላ ነው። በሌላ መልኩ በየደረጃው ስህተቶቼን በማረምና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ጓደኞቼ እጩ ዶ/ር ፍሬሕይወት ባዩ፣ እጩ ዶ/ር ዘላለም አበበ፣ ዶ/ር ጌታቸው ዳዊ እና ዶ/ር ደስታ ደሣለኝ ምሥጋናዬ የላቀ ነው። በተመሳሳዩ የማቴሪያል እና የሙያ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ዶ/ር ጥላሁን ተሊላ፣ ዶ/ር ሙሉሰው አሥራቱ፣ ዶ/ር ዓለሙ ከሳዬ እና እጩ ዶ/ር ፀጋይ ወልደማርያም ከልብ አመሠግናለሁ። ለሥራዬ መሳካት ትብብራችሁ ላልተለየኝ የትምህርት ክፍሉ ሠራተኞም ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ።

ይህንን የትምህርት እድል እንዳገኝ መልካም ትብብር ላደረገልኝ የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በተለይም ወሳኝ ሚና ለነበረው ለአቶ መገርሳ ገለታ ያለኝ ምሥጋና ልዩ ነው። የቅርብ አለቃዬ አቶ ዲሪቢ በርባዳ ለሞራል፣ ለማቴሪያል እና ገንዘብ ድጋፍህ ምሥጋናዬ የላቀ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ከተማውን ያስተዳደራችሁ ካቢኔዎች የጀመርኩትን ትምህርት እንድገፋበት ላዳረገችሁልኝ የሞራልና የገንዘብ ድጋፍ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። በሌላ መልኩ ከለገጣፎ ሮፓክ ኢንተርናሽናል የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ድርጅት አቶ ነጋሽ ደሜ፣ አቶ ኪዳኔ ገብረመድኅን እና አቶ ሲሳይ ማሰሪያ ላደረጋችሁልኝ የላብቶፕ፣ ፕሪንተር እና የሞራል ድጋፍ ከልብ አመሠግናለሁ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጥናቴ የደረሰበትን ደረጃ በመጠየቅ የሞራል ድጋፍ ለሰጣችሁኝ አቶ ዳኜ ከበደ፣ አቶ ድንቁ አበበ፣ ዶ/ር ተሾመ ኢማና፣ አቶ ዓለማየሁ ሙለታ፣አቶ ሙሴ ሞላ፣ አቶ አስነቀ በየነ፣ አቶ መስፍን አሰፋ፣ አቶ ጫልቾ በቀለ፣ አቶ ታደሰ ዋቅሹሜ፣ ወ/ሮ ዘነበች ተሰማ፣ አቶ ጣሰው በየነ፣ አቶ ጌቱ ተፈራ፣ አቶ በልዳ አቦዬ፣ አቶ ዘሪሁን አባተ፣ አቶ ሰለሞን ሀ/ጊዮርጊስ፣ አቶ ዘየደ ሞገስ፣ አቶ ኢብራሂም አብደላ እና የመርካቶ ጓደኞቼ በሙሉ፤ (አቶ ፋንቱ አፍራሳ፣ አቶ ጌታነህ ወልደፃዲቅ፣ አቶ ብርሃኑ ዓለሙ፣ አቶ አሰፋ አረጋ፣ አሰፋ ገ/ማርያም፣ አቶ ሽበሺ ለማ ከነባለቤታችሁ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ)። በተረፈ ስማችሁን ላልጠቀስኩኣችሁ በሙሉ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

በዚህ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በዋቢ የተጠቀሱ የጽሑፍ መረጃ ባለቤቶችን አመሠግናለሁ። በተመሳሳዩ መረጃ አቀባዮቼን በሙሉ እያመሰገንኩ በተለይም በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ከፍተኛ ሚና የተጫወተው አቶ ደረጀ መኮንን በሁሉም አቅጣጫ ላደረገልኝ መልካም ትብብር ከልብ

የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሱሉልታ ወረዳ እና ከተማ አስተዳዳር ጽ/ቤቶች ሃላፊዎች እና በየሴክተሩ ያላችሁ ሠራተኞች በሙሉ ስለ መልካም ትብብራችሁ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ድጋፋችሁ ጉልህ ቦታ ለነበረው ልጆቼ ምህረት ወርቁና መሠረት በጅጋ ከነልጆቻችሁ፣ ጌታቸው ከበደና ስንታየሁ በጅጋ ከነልጆቻችሁ፣ አሰፋ ወዳጅና ጫልቱ በጅጋ፣ ተስፋዬ በጅጋ፣ ሴቴ እርገተ እና እሁቴ ፅጌ ተካ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። በተለይም አቶ ጌታቸው ከበደ፣ ኮሎኔል ሰለሞን ተካ እና ምህረት ወርቁ ላደረጋችሁልኝ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ አቶ አሰፋ ወዳጅ ከአሜሪካ ሆነህ ለጥናቴ የሚያገለግል አስፈላጊውን ማቴሪያልና ሞራል በመስጠት ላደረክልኝ ልዩ ድጋፍ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ከሁሉም በላይ ግን የትምህርት ፍላጎቴ ተሳክቶ ለዚህ እንድበቃ በመየትኛውም ጊዜ እና ሁኔታ ከጎኔ ላልተለየሽ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ሙሉነሽ ወልደፃዲቅ በቁጥር ሥፍር የማይለካ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ማውጫ

ርዕስ -- ገጽ

ምሥጋና -- i

የይዘት ማውጫ -- ii

የሠንጠረዥ፣ የካርታ እና የመዋቅር ማውጫ -- v

ዥረት ገበታ፣ የፎቶ ግራፍ እና የሞዴል ማውጫ -- vii

ምህጻረ ቃል -- viii

ሙዳየ ቃላት -- ix

አጠቃሎ/አሕጽሮተ ጥናት -- x

ምዕራፍ አንድ -- 11

1.መግቢያ -- 11

1.1የጥናቱ ዳራ.. 6

1.2የምርምሩ አነሳሽ ምክንያቶች.. 13

1.3 የምርምር ጥያቄዎች.. 15

1.4 የጥናቱ ዓላማ.. 16

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ.. 16

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች.. 16

1.5 የጥናቱ ወሰን.. 17

1.5.1 የጥናቱ ወሰን ከቦታ አኳያ.. 17

1.5.2 የጥናቱ ወሰን ከይዘት አኳያ.. 19

1.6 የጥናቱ ውስንነት.. 20

1.7 የጥናቱ ፋይዳ.. 22

ምዕራፍ ሁለት -- 23

2. ክለሳ ድርሳናት-- 23

2.1 የጽንሰ ሀሳቦች ዳሰሳ.. 24

2.1.1 የፎክሎር ምንነት.. 24

2.1.2 የፎክሎር ምደባ.. 26

2.1.3 የሥነ ቃል ምንነት እና ሚናው.. 27

2.2 የንድፈ ሀሳብ ቅኝት.. 30

2.2.1 የጤና ትምህርት ቲዮሪ.. 30

2.2.2 የወሲብ እና የግብረ-ስጋ ግንኙነት አንድነትና ልዩነት.. 32

2.2.3 የወሲብ ቲዮሪ.. 34

2.2.4 የመረጃ መተንተኛ ቲዮሪዎች.. 38

2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.. 55

2.3.1 ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እና ወሲብ የሚመለከቱ ጥናቶች.. 55

2.3.2 ኤች ኣይ ቪ /ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ጥናቶች.. 64

2.4. በጥናቱ ቦታ እና ርዕስ ላይ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ቅኝት.. 68

2. 4. 1 የጥናቱን ቦታ (ማህበረሰብ) የሚጋሩ ቀደምት ጥናቶች.. 68

2. 4. 2 ርዕሰ ጉዳዩን የሚጋሩ ቀደምት ጥናቶች.. 72

ምዕራፍ ሦስት-- 80

3. የጥናቱ ስልትና ዘዴ---80
3.1 የጥናቱ ስልት..80
3.1.1 ኣይነታዊ የምርምር አቀራረብ..80
3.1.2 መረጃ መሰብሰቢያ አመለካከት..83
3.1.3 የመረጃ ምንጮች..84
3.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች..85
3.1.5 የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ..86
3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ መሳሪያዎች እና የሥነ ምግባር መመሪያዎች 87
3.2.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች..88
3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች..94
3.2.3 የምርምር ሥነ-ምግባር መመሪያዎች...95
ምዕራፍ አራት---98
4.የጥናቱ አካባቢያዊ ዳሰሳ፣ የቱለማ ኦሮሞ ዘር ሀረግና ባህላዊ ዳራ---------------------------------98
4.1 የሱሉልታ ወረዳ መሬት አቀማመጥ...98
4.1.2 የሕዝብ ብዛት..100
4.1.3. ማህበራዊ ተቋማት..101
4.1.4 ኢኮኖሚያዊ ተቋም..103
4.2 የቱለማ ኦሮሞ የዘር ሀረግ...107
4.2.1. ቋንቋ...112
4.2.2 ሃይማኖት..114
4.3 የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ዳራ 117
4.3.1 የጋብቻ ባህል..117
4.3.3 የእሬቻ በዓል..119
4.3.4 የጥምቀት በዓል...120
ምዕራፍ አምስት --121
5. ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማቅረብ ---121
5.1 በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች..122
5.2 በምልከታ የተገኙ መረጃዎች..125
5.2.1 ተፈጥሯዊ መቼት...125
5.2.2 ተፈጥሯዊ ያልሆነ መቼት...136
5.2.3 ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች...137
5.3 በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች...139
5.4 ቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ መረጃዎች...167
ምዕራፍ ስድስት --175
6. ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ የሥነቃል መረጃዎች ምደባ እና ትንተና --------------175
6.1. ጋብቻን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባና ትንተና...181
6.2 የከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባና ትንተና..................................191
6.3 ውሽማን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና..199
6.4 ሲገባን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና..210
6. 5 እሬን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና..217

ምዕራፍ ሰባት --222

7. ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና ----------------------
222

7.1 በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ የሆኑ የኅብረተሰብ 223
ክፍሎችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና 223
7.1.1 ወጣቶች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና........224
7.1.2 ሴቶች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና........229
7.1.3 ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ........236
መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና........236
7.2 ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ 241
የሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና 241
7.2.1 የሚመክሩ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና........242
7.2.2 የሚያስጠነቅቁ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘት ምደባና ትንተና........252
7.2.3 የሚያስፈራሩ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘት ምደባና ትንተና........264
7.3 ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ 271
እንዲጋለጡ የሚያደርጉ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና 271

ምዕራፍ ስምንት --278

8.ማጠቃለያ እና ይሁንታ --285

8.1 ማጠቃለያ ....**ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.**
8.2 ይሁንታ 287

ዋቢዎች --290

የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር --307

አባሪ 1. የመስክ ምልከታ ቼክ ሊስት --

አባሪ 2. ለመጠይቅ የቀረቡ መረጃ ማሰቢሰቢያ ጥያቄዎች --

አባሪ 3. ለቃለ-መጠይቅ የቀረቡ መረጃ ማሰባሰቢያ ጥያቄዎች --

አባሪ 4. ለቡድን ተኮር ውይይት የቀረቡ መረጃ ማሰባሰቢያ ጥያቄዎች --

አባሪ 5. ልዩ ልዩ ፎቶ ግራፎች --

አባሪ 6. ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ እና ትንተና --

አባሪ 7. ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ እና ትንተና --

የሠንጠረዥ፣ የካርታ እና የመዋቅር ማውጫ ---------------------------------------ገጽ

ሠንጠረዥ 1. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ወረዳዎች/ከተሞች፣ የሕዝብ ብዛትና
የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት መግለጫ --------------------------------16

ሠንጠረዥ 2. በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መጠን ማሳያ ----------------57

ካርታ 1. የጥናቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ ---91

መዋቅር 1. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞንና በሱሉልታ የሚኖሩ

የቱለማ ኦሮሞ ዘር ሐረግ ---101

ሠንጠረዥ 3. በገላን ጎሳ ሥር የሚገኙ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች --------------------102

ሠንጠረዥ 4. በኦቦ ጎሳ ሥር የሚገኙ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች ---------------------102

ሠንጠረዥ 5. የመጫ እና የቱለማ አሮሞ ቃላት ላይ የቅጥያ አጠቀቀም ማሳያ-----------104

ሠንጠረዥ 6. በገላን ጨፌ ቱማ የእሬቻ በዓል ምርቃት -----------------------------117

ሠንጠረዥ 7. በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መግለጫ ------160

ሠንጠረዥ 8. ጋብቻን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና ---------------169

ሠንጠረዥ 9. ጋብቻን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና -------------------------174

ሠንጠረዥ 10. የከንፈር ወዳጅን የሚመለከት ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና -----178

ሠንጠረዥ 11. ከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና ------------------180

ሠንጠረዥ 12. ውሽማን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና -------------186

ሠንጠረዥ 13. ውሽማን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና -----------------------189

ሠንጠረዥ 14. ሲገባ የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና ----------------196

ሠንጠረዥ 15. ሲገባን የሚመለከቱ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ---------------------------198

ሠንጠረዥ 16. እሬን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና ---------------203

ሠንጠረዥ 17. እሬን የሚመለከቱ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ----------------------------204

ሠንጠረዥ 18. ወጣቶች በኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ

ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና --------------------------------210

ሠንጠረዥ 19. ወጣቶች በኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ

ዘፈኖች የይዘት ትንተና ---212

ሠንጠረዥ 20. ሴቶች በኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጽ

ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና ---------------------------------215

ሠንጠረዥ 21. ሴቶች በኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ

ዘፈኖች የይዘት ትንተና ---218

ሠንጠረዥ 22. ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤድስ በመጠቃታቸው ለመከላከል

መረባረብ እንዳለባቸው የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና --------

221

ሠንጠረዥ 23. ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በኤድስ መጠቃቱን

የሚገልጹ ዘፈኖች የይዘት ትንተና -------------------------------------223

ሠንጠረዥ 24. ኤድስን ለመከላከል የሚመክሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና ----
227

ሠንጠረዥ 25. ኤድስን ለመከላከል የሚመክሩ ዘፈኖች የይዘት ትንተና ----------------230

ሠንጠረዥ 26. ኤድስን ለመከላከል የሚያስጠነቅቁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና -
236

ሠንጠረዥ 27. ኤድስን ለመከላከል የሚያስጠነቅቁ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ------------243

ሠንጠረዥ 28. ሰዎች ኤድስን እንድፈሩ የሚያደርጉ

ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና -----------------------------------249

ሠንጠረዥ 29. ሰዎች ኤድስን እንድፈሩ የሚያደርጉ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ----------251

ሠንጠረዥ 30. ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ

እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና ----------
-256

ሠንጠረዥ 31. ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ

እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ----------------------
259

የኸረት ገበታ፣ የፎቶ ግራፍ እና የሞዴል ማውጫ ----------------------------------ገጽ
የኸረት ገበታ 1. የጥናቱ ምዕራፎች ርዕሰ ጉዳይ የትኩረት ጥያቄዎች--------------------3
ፎቶ ግራፍ 1. ከሱሉልታ እና ጫንጮ 2ኛና መሰናዶ ት/ቤቶች
በመጠይቅ ከተሳተፉ ተማሪዎች በካፊል------------------------------115
ፎቶ ግራፍ 2. የእሬቻ በዓል በበሾፍቱ ሆራ አርሰዲ መልካ ሲከበር--------------------119
ፎቶ ግራፍ 3. የእሬቻ በዓል በሱሉልታ ወረዳ ሞገር ሞገር መልካ ላይ እና
በገላን ከተማ ጨፌ ቱማ አቃቂ መልካ ላይ ሲከበር ---------------------
119
ፎቶ ግራፍ4. የጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ጃን ሜዳ እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ሩፋኤል
ቤተክርስቲያን ሲከበር የኦሮምኛ ዘፈኖች ክዋኔ ---------------------------121
ፎቶ ግራፍ 5. የጥምቀት በዓል በሸኖ ማርያምቤተክርስቲያን እና በጫንጮ እግዚአብሔር
ለአብ ቤተክርስቲያን ሲከበር የኦሮምኛ ዘፈኖች ክዋኔ ---------------------
122
ፎቶ ግራፍ 6. ወንድ ልጅ ሊያገባ ከቤት ሲወጣ እና ሴት ልጅ ስትዳር የጥሎሽ ሥርዓት -
123
ፎቶ ግራፍ 7. ቀብር ሥነ-ሥርዓት በለገጣፎ አባ ኪሮስ ቤተክርስቲያን ---------------124
ፎቶ ግራፍ 8. የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች በለገጣፎ በ12/02/07 ዓ.ም. -----------128
ፎቶ ግራፍ 9. የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች በለገጣፎ በ28/02/08 ዓ.ም. ------------128
ፎቶ ግራፍ 10. በቃለ መጠይቅ ዘዴ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ----------------------130

ፎቶ ግራፍ 11. የሱሉልታ እና ጫንጮ ከተማ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም -------------132

ፎቶ ግራፍ 12. ጋብቻን አስመልክቶ በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች --------137

ፎቶ ግራፍ 13. ውሽማን በሚመለከት በቃለ-መጠይቅ ላይ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ---142

ፎቶ ግራፍ 14. በሆራ አርሰዲ እሬቻ ክብረ በዓል ላይ የፎሌዎች ዘፈን ክዋኔ -----------147

መዋቅራዊ መግለጫ 1. ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች

ምደባ መዋቅራዊ መግለጫ-- 162

ሞዴል 1. የጥናቱ ማጠቃለያ ሞዴል ---262

ሞዴል 2. የሞዴሉ ማብራሪያ ---263

ምህፃረ-ቃል

AAU = Addis Ababa University

AIDS = Acquired Immun Deficiency Syndrome

CDC = US Center for Disease Control and Prevention

CSA= Central Statistical Agency

EDHS= Ethiopian Demographic Health Survey

HEARD= Health Economics and HIV/AIDS Research Division

FDRE= Federal Democratic Republic of Ethiopia

FGD= Focus Group Discussion

HLSJC = Humanities, Language Studies, Journalism and Communication

HAPCO= HIV and AIDS Preventation and ControlOffice

HIV= Human Immunodeficiency Virus

ICDR= Institute for Curriculum Development and Research

MOE= Ministry of Eduction

MOH= Ministry of Health

MPSC= Multi- Partner Sexual Contacts

OSSA= Organization for Social Services for AIDS in Ethiopia

OSSREA= Organisation for Social Science Research in Eastern and Southern Africa

STD= Sexually Transmitted Diseases

UNAIDS= United Nations Program on HIV/AIDS

UNESCO/AIDS= United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization on AIDS

WHO = World Health Organizatio

ሙዳየ ቃላት

Afoola = ሥነቃል

Ayyanaa cuuphaa = የጥምቀት በዓል

Balaa = አደጋ

Bokkuuu= በኦሮሞ ባህል በክብረ-በዓላት ጊዜ ወንዶች በእጃቸው የሚይዙት ባህላዊ ዱላ

Butii = የሴት ልጅ ጠለፋ

Dhugeeffannoo = ሚቶሎጂ (ፈጣሪ እና ተፈጥሮን መገንዘብያ መንገድ)

Dubra= ልጃገረድ

Dubrii = የአጎት/የአክስት ልጅ (ወንድ ወይም ሴት)

Fororsaa = የፎሌዎች ይዞ የሚጨፍሩበት ረዥም እንጨት/ዱላ

Hoolaa rakoo = በሠርግ ጊዜ የሚታረድ የደንብ በግ

Irradhaaba = ፈረስ ደጅ በማቆም የሚፈጸም ጋብቻ

Irreecha malkaa= የመልካ/የወንዝ እሬቻ

Irree/waarsaa) = የአጎት ልጅ (ወንድ) በጋብቻ ወቅት አብሮ የሚሆን

Jalabultii/Warsiisaa) = የሠርጉ ቀን ወር ሲቀር በሙሽርት ቤት የሚከወን የምሽት ጭፈራ

Kallacha= አባ ገዳ እና ታወቂ ሽማግሌ በግንባሩ ላይ የሚያስሩት ባህላዊ የክብር እቃ

Qaadhiimaa= እሬጮኛ

Qaammee = እንቁጣጣሽ

Qeerroo = ያላገባ ወጣት/ጎረምሳ

Safuu = ወግ / ነውር/ሥነሥርዓት

Sanyoo= ውሽማ

Sigabaa= ባል ከሞተባት ሴት ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈፀም ወንድ

Suuphoo= ያገባ ወጣት

Wadaajii= የከንፈር ወዳጅ

አጠቃሎ/አሕጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በሱሉልታ ወረዳ እና አከባቢዋ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በዚህ አከባቢ እስካሁን ድረስ በፎክሎር የትምህርት መስክ በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ ከሥነቃል አንጻር የተደረገ ጥናት የለም። በመሆኑም ይህ ጥናት የመጀመሪያ ወጥ ሥራ ነው። ጥናቱ ይዞ የተነሳው ዓላማ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን ይዘታቸውን በመተንተን፣ በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያላቸውን አዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ በመለየት፣ ለችግሮቹ መፍትሂዎቻቸውን በመጠቆም ሁሉም ሰው ራሱን ከቫይረሱ ስርጭት እንዲከላከል ማድረግ ነው።

ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ልዩ ልዩ የመረጃ ማሰበሰቢያ ዘዴዎችን (መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት) በመጠቀም እንዲሁም ከልዩ ልዩ ቦታዎች (ተፈጥሮአዊ፣ ተፈጥሮአዊ ካልሆኑ እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ) መቼቶች በቂ የሆኑ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስበዋል።

በዚሁ መሠረት በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ የሚካተቱት ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ ሲሆኑ እነዚህን አስመልክተው በርካታ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች እንዳሉ በጥናቱ ተረጋግጠዋል። ከእነዚህ ጋር ተያይዘው ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች በአብዛኛው የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር

የበኩላቸውን ሚና የሚጨወቱ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ለልቅ የግብ-ስጋ ግንኙነት የሚዳርጉ እና ለቫይረሱ ሥርጭት መባባስ ምክንያት የሚሆኑ ጥቂት የሥነቃል ዓይነቶችም መኖራቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

በቀጥታ ኤች አይ ቪ.ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ወጣቶች እና ሴቶች ለቫይረሱ ጥቃት ይበልጥ የተጋለጡ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ስለሆነም ሰዎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የማስተማር አገልግሎት አላቸው። በሌላ መልኩ የሰዎችን ወሲባዊ ፍላጎት በማነሳሳት ለግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚገፋፉ እና ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጥቃት የሚያጋልጡ ደግሞ የቫይረሱን ሥርጭት የሚያባብሱ ናቸው።

በአጠቃላይ ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ በሚል ሁለት ምዕራፎች ሥር ተመድበዋል። ከእነዚህ መካከል ከእየምዕራፉ ለትንታኔ የተመረጡት በእየርዕሰ ጉዳዮቻቸው ሥር ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ሰፊ ገለጻ እና ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል። ትንታኔው የተከናወነው በዋናነት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡበት አውድ አኳያ አውዳዊ ቲዮሪን እና የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ካለቸው ፋይዳ አንጻር ደግሞ ተግባራዊ ቲዮሪን መሠረት ያደረገ ነው። ትንታኔውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ደግሞ ሌሎች ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ደጋፊ መተንተኛ በመሆን አገልግለዋል።

ከዚሁ አንጻር እነዚህ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በሽታውን በመከላከሉ እና በመቆጣጠሩ በኩል በልዩ ልዩ መልኩ የማስተማር ሚና እንዳለቸው ሁሉ ወሲባዊ ፍላጎት በማነሳሳት ለቫይረሱ ጥቃት የሚያጋልጡ አሉታዊ ተጽዕኖአቸው በቀላሉ የሚታዩ አለመሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በመሆኑም ሰዎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ የሚያግዙ እና ለቫይረሱ የሚያጋልጡ የሥነቃል ዓይነቶች በዚህ ጥናት ውስጥ ተለይተው ተብራርተዋል። እነዚህንም በልዩ ልዩ መስኮች ለማህበረሰቡ ማስተማርያነት ማዋል እንደሚቻል በጥናቱ መደምደሚያ እና ይሁንታ ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል።

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በቱለማ ኦሮሞ፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በተለይም በሱሉልታ ወረዳ እና አከባቢዋ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ አስመልክቶ የሚነገሩና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን ሰብስቦ ከይዘታቸው አኳያ መተንተን ነው። የጥናቱ ዓላማ ርዕሱን በሚመለከት በአውንታዊ እና አሉታዊ መልኩ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን ለይቶ በመተንተን ጥናቱን መሠረት ያደረገ የመፍትሔ ሀሳቦችን መጠቆም ነው።

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተከሔዱ ቀደምት ጥናቶች ከልዩ ልዩ የጽሑፍ መረጃዎች በስፋትና በጥልቀት ተዳሰዋል። በሌላ መልኩ መረጃዎችን ከመስክ

ለመሰብሰብ የሚያግዙ እና የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን የሚረዱ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችም በስፋት ተቃኝተዋል። ከዚሁ አኳያ ቲዮሪዎቹን መሠረት በማድረግ ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተያያዥ የሆኑ በቂ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

መረጃዎቹ የተሰበሰቡት አውድን መሠረት አድርገው ሲሆን ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች እና መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። የተገኙት መረጃዎች በጽሑፍ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በድምፅ እና በምስል ተይዘዋል።

እነዚህ ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ከይዘታቸው አንጻር ተለይተው የማህበረሰቡን የሥነቃል አመዳደብ እንዲሁም የፎክሎር ምሑራንን የአከፋፋል ዲስፕሊን ባገናዘበ መልኩ በሁለት የሥነቃል ዓይነቶች ስር ተመድበዋል። እነሱም ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች (ቃል ግጥሞች) ሲሆኑ ካተከሩበት ርዕሰ ጉዳይ (ይዘት) አንጻር ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሚሉ ሁለት ዋና ዋና ርዕሶች ሥር ተዘርዝረዋል። በእያንዳንዳቸውም ሥር ከይዘታቸው አኳያ በሌሎች ንዑሳን ርዕሶች ሥር ተመድበዋል። ከተመደቡትም ውስጥ የተመረጡት በዋናነት ከአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች አኳያ የተተነተኑ ሲሆኑ ትንታኔውን ይበልጥ ግልጽ ለማድርግ ከሌሎች ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች በደጋፊነት አገልግለዋል። የቀሩት በተራ ቁጥር ቅደም ተከተል ተሰጥቷቸው በዚህ ጥናት ውስጥ አባሪ ተደርገዋል።

ከዚሁ አኳያ የጥናቱ አጠቃላይ ምዕራፎች እና በእያንዳንዱ ምዕራፍ ሥር ትኩረት የተደረገበት ዝርዝር ጉዳዮችን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የምርምር አነሳሽ ምክንያቶች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነት፣ የጥናቱ ፋይዳ በዝርዝር የቀረቡበት ነው።

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳንን የሚመለከት ሆኖ የጽንሰ ሀሳብ ደሰሳ፣ የንደፈ ሀሳብ ዳሰሳ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ያካተተ ነው። የጽንሰ ሀሳብ ደሰሳው የፎክሎር ምንነትና ምደባ፣ የሥነቃል ምንነትና ሚና የሚመለከት ነው። በንደፈ ሀሳብ ዳሰሳ ሥር የጤና ትምህርት ቲዮሪ፣ ወሲባዊ ቲዮሪዎች እና ልዩ ልዩ የመረጃዎች መተንተኛ ቲዮሪዎች በዝርዝር የተቃኙበት ነው። በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሥር ደግሞ ኤች አይ ቪ/ኤድስ

እና ወሲብን የሚመለከቱ ጥናቶች፣ በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ የተደረጉ የሥነቃል ጥናቶች እና የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚጋሩ ቀደምት ሥራዎች በዝርዝር ተዳሰዋል።

ምዕራፍ ሦስት የጥናቱን ስልት እና ዘዴ የሚመለከት ነው። የጥናቱ ስልት አይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) ስለመሆኑና ስለ መረጃው አሰባሰብ ውስጣዊና ውጫዊ አመለካከቶች የተገለጸበት ነው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት ተፈጥሯዊ፣ ተፈጥሯዊ ካልሆነ እና ከቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች መሆኑ እና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ስልት የተብራራበት ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በተመለከተ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት መሆናቸው እና መረጃውን ለማሰባሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉ መሰሪያዎች እንዲሁም የምርምር ሥነ-ምግባር መመሪያዎች በዝርዝር የተገለጸበት ሲሆን በመጨረሻም የመስክ ገጠመኝ ቀርቧል።

ምዕራፍ አራት ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ እና የማህበረሰቡ ዳራ የተቃኘበት ነው። አካባቢያዊ ዳራን በሚመለከት የሱሉልታ ወረዳ መሬት አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የተገለጸበት ነው። ማህበረሰባዊ ዳራን በሚመለከት የቱለማ ኦሮሞ የዘር ሀረግና ባህላዊ እሴት መገለጫ የሆኑ ዲርጊቶች ቀርበዋል። እነሱም በማህበረሰቡ ልዩ ልዩ የሥነቃል ክዋኔ አጋጣሚ መቼቶች የተገለጹበት ነው።

ምዕራፍ አምስት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የቀረቡበት ነው። ይህም በልዩ ልዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት) ለተነሱ ጥያቄዎች ከመረጃ አቀባዮችዎች የተገኙ መልሶች የቀረቡበት ሲሆን በምልክታ ከሥነቃል መከወኛ አጋጣሚዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በዝርዝር የተገለጹበት ነው።

ምዕራፍ ስድስት በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በሚመለከት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን አስመልክተው የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች የተመደቡበትና ከይዘታቸው አኳያ በልዩ ልዩ ቲዮሪዎች የተተነተኑበት ነው።

ምዕራፍ ሰባት ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች በሦስት ዋና ዋና ርዕሰ ርዕሰ ጉዳዮችና ሌሎች ንዑሳን ርዕሶች የተመደቡበት እና ይዘታቸው ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ማብራሪያና ትንተና የተደረገበት ነው።

ምዕራፍ ስምንት ከተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች በመነሳት የተከናወኑ ትንታኔዎችን መሠረት በማድረግ የጥናቱ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ በዝርዝር የቀረበበት ነው። በመጨረሻም ዋቢ መረጃዎች እና ልዩ ልዩ አባሪዎች ተያይዘው ቀርበዋል።

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን ዝርዝር ጉዳዮች አስመልክተው የጥናቱን ርዕስ መሠረት በማድርግ ለእያንዳንዱ ምዕራፍ የትኩረት ጥያቄዎች ቀጥለው ቀርበዋል። በመሆኑም የምዕራፎቹን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ የቀረቡትን ጥያቄዎች የሚከተለው የኀረት ገበታ የሚጠቁመን ሲሆን መልሳቸው በእየምዕራፎቹ ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል።



ዥረት ገበታ 1፡- የጥናቱ ምዕራፎች ርዕሰ ጉዳይ ትኩረት ጥያቄዎች

1.1 የጥናቱ ዳራ

ፎክሎር በዓለም ዙሪያ የበለጠ ትኩረት አግኝቶ መጠናት የጀመረው ከ1960ዎቹ በኋላ ነው (Schipper, 2000:9)። በጥናት እና ምርምር ውስጥ የፎክሎር ዘርፍ የሆነው ሥነቃል እንደ ሥነጽሑፍ ትልቅ ቦታ ማግኘት ባይችልም፣ የማህበረሰቡን ባህል በማንጸባረቅ በኩል ከፍተኛ ቦታ እንዳለው Wilson(1979:458)ይናገራል። የሥነቃልን ሚና አስመልክቶ Brunvand, (1979) እንዲህ ይላል። "Oral Literature is a sphere of interaction, needs and disire, and artistic expression with its own structures and esthetics." (PP 426). ሥነቃል በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ምኞትና ፍላጎትን፣ ቅርፅና ውበትን የምንገልጽበት ነው። ይህም ማለት ሥነቃል ከኀብረተሰቡ ተወስዶ መልሶ ለኀብረተሰቡ አገልግሎት የሚውል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ከዚህ የምንገነዘበው ፎክሎር በኀብረተሰቡ መሰተጋብር ውስጥ የሚፈጠር እና ጥበባዊ በሆነ መልኩ የኀብረተሰቡን ባህል መልሶ የሚያንጸባርቅ መሆኑን ነው። በሌላ አባባል የሰው ልጅ ምኞቱንና ፍላጎቱን የሚገልጸው የፎክሎር ዘርፍ በሆነው በሥነቃል አማካይነት በመሆኑ ሥነቃልን በማጥናት የኀብረተሰቡን ባህል፣ የኑሮ ሁኔታ፣ ጤና፣ አስተሳሰብ፣ ችግር፣ ማንነት ወዘተ … ማወቅ እንደሚቻል ያስገነዝበናል።

ሥነቃል የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያንጸባርቅ እንደመሆኑ መጠን የማይደስሳቸው ጉዳዮች የሉም። ይህንን አስመልክቶ በሥነቃል መምሪያ መግቢያ ላይ ለመጽሐፉ ዝግጅት ምን እንደ ገፋፋው ፈቃደ ከገለጻቸው ውስጥ አንደኛው ምክንያት ሥነቃልን የሚመለከት አጠቃላይ ፍላጎት በኢትዮጵያ ውስጥ እያደገ መምጣቱ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ሀገሪቱ ዛሬ ባለችበት ሁኔታ የብሄረሰቦችን ሥነቃል ሰብስቦ የማጥናት ፍላጎት እየጎላ መምጣት ነው (ፈቃደ አዘዘ፣ 1991፡ ii)። በዚህ ረገድ በአገራችን ከወሲብ ጋር ተያይዞ በሥነቃል የሚነገሩ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ የተጠኑ ጥናቶች አሉ ለማለት አያስደፍርም። ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ በሥነቃል የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች የሉም ማለት ግን አይደለም።

ሥነቃል ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በመግለጽ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠሩ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው በተለያዩ አገሮች የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚሁ አንጻር በፎክሎር የጥናት መስክ የተወሰኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች ኤች

ኤይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሥነቃል ሚና ላይ ጥናትና ምርምር አድርገው አድርገዋል (Legman, 1962[1]; HEARD,2011; Ephraim 2011)።

ከዚሁ አኳያ በዚምባቡዌ የሾና ማህበረሰብ ምሳሌያዊ ንግግሮችና አባባሎች ላይ በተደረገው ጥናትና ምርምር አስከፊውን የኤች ኤይ ቪ/ ኤድስ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጣር ረገድ ምሳሌያዊ ንግግሮች ያላቸውን አገልግሎት በEphriam, (2011) እንደሚከተለው ተገልጿል።

> Contemporary Shona societies are against sexual immorality. A proverb that warns someone who refuses to be advised is known as one who rejects advice was seen with a wound on the forehead. If one refuses to take advice about HIV and AIDS seriously, the likelihood of infection is very high. (PP. 131).

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ጠቅለል አድርገን ስናይ በዚምባቡዌ የሾና ማህበረሰብ የግለሰብ ወሲብ አፈጻጸም ከማህበረሰቡ ሥነምግባር ውጭ ከሆነ በምሳሌያዊ ንግግር አማካይነት እንደሚመከሩና ምክሩን የማይቀበል ግለሰብ በግንባሩ ላይ ቁስል እንዳኖረ መቆጠሩን የሚያስገነዝብ ነው። እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮችና አባባሎች በወሲብ ውስጥ ግላዊ ቁጥጥርና ታማኝነትን የሚያንጸባርቁ ትርጉሞችን የያዙ በመሆናቸው፤ በሽታውን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ውጤታማ ተግባራት መከናወናቸውን ያሳያል።

የሾና ባህላዊ አስተሳሰቦችን በማንጸባረቁ ረገድ ሥነቃል በተለይም ምሳሌያዊ ንግግሮች የኤች ኤይ ቪ/ ኤድስን ሥርጭት ለመግታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። በአጠቃላይ እነዚህንና መሰል የሥነቃል ዓይነቶችን ከሣይንሳዊ የሕክምና ትምህርት ጋር በማቀናጀት ዚምባቤያውያንን በማስተማር በሽታዉን ለመቆጣጠር የጎላ ዉጤት ማምጣት እንደተቻለ ጥናቱ ያመለክታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ኤች ኤይ ቪ / ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ አገር በቀሉን እውቀት ሥራ ላይ በማዋል፤ በዚምባቡዌ የሾና ምሳሌያዊ ንግግሮች ወሲብን በሚመለከቱ ትምህርታዊ ፕሮግራም የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት በተደረገው ጥረት የበሽታውን ሥርጭት በ13% መቀነስ እንደተቻለ የMungwini, (2009:126) ጥናት ያመለክታል ።

[1] The collecting of erotic folklore has only recently come to interest the world of folklore scholarship in the English-speaking countries.

ከዚህ የምንገነዘበው አገር በቀል እዉቀቶች ከዕለታዊ ሕይወት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጣር በቀላሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በደቡብ አፍሪካ ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር በተያያዘ መልኩ (እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም) የተደረገ ጥናት ችግሮችን ለመፍታት ሁለገብ የሆነ ማህበራዊና ባህላዊ አውዶችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ ያመለክታል። ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ እና ዋናው ወሲብ ነው። በመሆኑም ወሲብ በሚፈጸምበት ወቅት እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደየባህላዊ እምነቱ የሚከውናቸው ተግባራት ላይ ሰፊ ጥናት መደረግ እንዳለበት Suzanne et al, (2009) ያሳስባሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ “Oral Literature and HIV Narratives in Swaziland” በሚል ርዕስ ከድረገጽ የተገኘ መረጃ በዓለም ላይ የቫይረሱ ሥርጭት በከፍተኛ ደረጃ የሚታይበት አገር ስዋዚላንድ መሆኗን ይጠቅስና በወሲብ አፈጻጸም ላይ የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት በሥነቃል አማካይነት በማስተማር የኤች አይ ቪ/ ኤድስ አደጋን መቀነስ መቻሉን (University of KWAZULU-NATA, 2011) እንደሚከተለው ገልጿል።

> Swaziland is currently experiencing the worest HIV epidemic in the world. Over 26% of the adult population is living with HIV, and among pregnant women the age of 30 and 34 prevalence is nearly 54%. … Behaviour change on sexuality plays a crucial role in any strategy that aims to reduce HIV incidence.…One that Swazis feel is appropriate and acceptable for their culture and their lives. There is a great potential in a narrative structure which already exists in the country: Traditionally, families would gather in the evening to listen to the grandmother tell a story which touched on important events of the day, or reinforced social lessons that she felt needed addressing heard@ukzn.ac.za (Issue Biref April, 2011:1).

ትርጉም በአማርኛ

> ሲዋዚላንድ በዓለም ላይ በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ክፉኛ የተጠቃች አገር ናት። ከ26% በላይ የሆኑ ጎልማሶች ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ እድሜያቸው ከ30 — 34 የሚሆኑት ነፍሰ ጡር ሴቶች ወደ 54% ይጠጋሉ። … የኤች አይ ቪ/ ኤድስን ሥርጭት ለመቀነስ በወሲብ ላይ የባህርይ ለውጥ ማምጣት ከፍተኛ ሚና አለው። … ሲዋዚላንድውያን በሕይወታቸው ውስጥ ለባህላቸው የተለየ ቦታ ይሰጣሉ (ባህላቸውን ያከብራሉ)። በአገሪቱ ያሉት ትረካዎች ከፍተኛ ኃይል አላቸው። ማታ ቤተሰብ በሚሰበሰብበት ጊዜ ቀን ስለዋሉበት ሁኔታ፣ ወይም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ባህላዊ ተረቶች በሴት አያት ይነገራል። ይህም ማህበራዊ ጉደዮችን ለመማር ያገለግላል።

ይህም የሚያሳየን ስዋዚላንድውያን ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወሲብ ዙሪያ የባህሪይ ለውጥ አምጥቶ የቫይረሱን ሥርጭት መቀነስ መቻላቸውን ነው። ይህም የሚያሳየን ስዋዚላንድውያን ለራሳቸው ባህል ትኩረት በመስጠት ለችግሮቻችው ባህላዊ መፍትሔ መፈለግ ጋቸውንና ለዚህም ቀድሞውኑ በአገራቸው የነበሩት ሥነቃሎች ሚናቸው የጎላ መሆናቸውን ነው። ከዚሁ አኳያ በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ ስለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሚተርክ ሥነቃል በአቀራረባቸዉ መታቀብን፣ መወሰንና መጠቀምን ማዕከል ያደረጉ መሆናቸው ተገልጿል። ይህም በሥልጣኔ ሰበብ በምእራባውያን ባህል ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ ለራስ ባህል ቅድሚያ መስጠት ወሳኝ መሆኑን ያመለክታል።

እስካሁን ከቀረቡት መረጃዎች የምንረዳው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ በፎክሎር በተለይም በሥነቃል መስክ በውጭው ዓለም ጥናቶች እየተካሔዱ መሆናቸውን ነው።

በአገራችን ኤች አይ ቪ ኤድስ ከፎክሎር አኳያ የተደረገ ጥናት ስንመለከት ብዙ አሉ ለማለት አያስደፍርም። ይሁን እንጂ ኤድስ ዓለም አቀፋዊና በየትኛውም የኀብረተሰብ ክፍል ላይ በርካታ ችግሮችን እያደረሰ የሚገኝ በሽታ በመሆኑ፣ በፎክሎር የትምህርት ዘርፍ በተለይም በሥነቃል ጥናትና ምርምር ሊደረግበት ይገባል።

ከዚሁ አንጻር በኦሮሞ ኅብረተሰብ ዘንድ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስበው ቢጠኑ በሽታው እያደረሰ ያለውን አሉታዊ ገፅታ ለመለየት እና የመፍትሔ አቅጣጫ ለማሳየት የጎላ ሚና ይኖራዋል። በመሆኑም ለመግቢያ ያህል ጥናቱ የተከናወነበትን ማህበረሰብ ማንነት መግለጹ አስፈላጊ ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ ሰፊና ለም መሬት ላይ የሠፈረ፣ ዓለምን የሚገነዘብበት የራሱ አመለካከት (Dhugeeffannaa/ World view)ያለው እና በራሱ ቋንቋ ባህ ሉንና ማንነቱን የሚገልጽ ሕዝብ መሆኑን Dirribii Damisee(2009:14)ይዘረዝራል።

ኦሮሞ ከኩሽ ዝርያ የሚመደብ ሲሆን፣ በውስጡ ከአንድ ዘር የመነጩ በርካታ ቅርንጫፎች አሉት። ይህንን በተመለከተ Alamaayyoo Hayilee, (1999፡ 19) እንደሚከተለው ጽፏል።

> Oromoon saboota Kuush keessaa isa bal'aa fi uummata qabiyyee lafa guddaa irra dagaagee jiraatu. Haaluma bal'inaa fi guddina uummataan, Oromoon gosoota (dame) hedduu qaba. Isaanis- Tuulama, Macca, Arsii, Gujii, Boorana, Ittuu, Humbaana, Raayyaa, Yejjuu fi Liiban jedhamu. Kana keessaa gosni Tuulamaa isa tokkoodha. Damee Oromoo keessaa

Tuulamni gosa handhuura Itooophiyaa bakka dur Kuushitikoonni turan jedhamu lafa bal'aarra dagaagee jiraachaa turee fi ammas jiruudha.

የአማርኛ ትርጉም

> *አሮሞ ከኩሽ ዘር ውስጥ ብዙ ቁጥር ያለውና ሰፊ መሬት ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ነው። ባለው ሰፊ መሬትና የሕዝብ ቁጥር መብዛት ኦሮሞ ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። እነሱም ቱለማ፣ መጫ፣አርሲ፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ ኢቱ፣ ሁምባና፣ ራያ፣ የጁ እና ሊበን ይባላሉ። ከእነዚህ ውስጥ የቱለማ ቅርንጫፍ አንዱ ነው። ከኦሮሞ ቅርንጫፎች ውስጥ ቱለማ የኢዮትጵያ እምብርት በሆነው ድሮ ኩሾች ይኖሩበት በነበረው ሰፊ መሬት ላይ ይኖር የነበረና አሁንም እየኖረ ያለ ማህበረሰብ ነው።*

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጽሑፍ ማስረጃ እንደሚያሳየው ኦሮሞ አንድ የዘር ግንድ ያለው የኩሽ ዝርያ ሲሆን ከኦሮሞ ሚቶሎጂ አኳያ የመጀመሪያው ፍጡር ከሆነው ከሆሮ ሰባት ትውልድ በኋላ አስር ዋና ዋና የኦሮሞ አባት የሆኑ ቅርንጫፎች አሉት። እነዚህም ዋና ዋና ቅርንጫፎች በአምስት ደረጃ ይመደባሉ። እነሱም 1ኛ, ስቦና ጉና፣ 2ኛ, መጫና ቱለማ፣ 3ኛ, ሲኮና መንዶ፣ 4ኛ, ኢቱና ሁምባና፣ 5ኛ, ራያና አሴቦ ናቸው (ታቦር ዋሚ፣ 2006፡54)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር Alksander Ferenc (1988) እንደሚከተለው ገልጿል። "Oromo people have a common system of ethnogenetic myths and traditions; moreover, the particular group of this people share such traditions". ሲተረጎም የኦሮሞ ሕዝብ የጋራ ባህል እና እምነት (የዓለም አመለካከት) አለው። በሥሩ የሚገኙ ቅርንጫፎችም ይህንን ባህል ይጋሩታል። ይህም በየትኛውም ሥፍራ የሚገኙ የኦሮሞ ቅርንጫፎች በጋራ የሚያገናኛቸው እምነትና ባህል ያላቸው መሆኑን ያሳያል።

ቱለማ የሚለው ስያሜ Tuulluu (ቱሉ) ሲተረጎም ተራራ ከሚል ስም የተገኘ ነው። የቱለማ ኦሮሞ ድሮ በነበረው አከላለል፣ በደቡብ ከጉራጌ ሕዝብ ጋር፣ በምሥራቅ ከአርሲ ኦሮሞ፣ በምዕራብ ከመጫ ኦሮሞ፣ በሰሜን ከአማራ ሕዝብ ጋር፣ በሰሜን ምሥራቅ ከአፋር ሕዝብ ጋር የሚዋሰንና ሸዋ ውስጥ የሚገኝ ነው (Alamaayyoo Hayilee, 1999:xi)።

በአሁኑ ወቅት የቱለማ ኦሮሞ በኦሮሚያ ክልል፣ በአብዛኛው ሸዋ ውስጥ የሚኖር ሲሆን፣ በአዲስ አበባና ዙሪያ አምስቱም መግቢያ እና መውጫ በሮች በሚገኙ ወረዳዎችና ከተሞች (በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን) ውስጥ ይገኛል። በአምስቱ መግቢያና መውጫ በር ላይ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎች በቱለማ ኦሮሞ የተሰየሙ ናቸው። ይሄውም በሰሜን

ሰላሌ መስመር karra[2] Qirrixii (ከረ ቅሪጢ)፣ በሰሜን ምሥራቅ ደሴ መስመር karra Alloo[3] (ከረ አሎ)፣ በምዕራብ አምቦ መስመር karra Gafrsaa[4] (ከረ ገፈርሳ)፣ በደቡብ ምዕራብ ወሊሶ መስመር karra Qoree (ከረ ቆሬ[5])፣በ ምሥራቅ አዳማ መስመር karra Qaalluu (ከረ ቃሉ) በመባል እንደሚታወቁ (በኢማና፡ 2015 ውስጥ የተሊላና መርሳ፡ 2008) ጥናት ያመለክታል። ይሁን እንጂ የአማርኛ ቋንቋ ባሳደረው ተጽዕኖ ከረ ይባል የነበረው ስም "ካራ" ተብሎ መጠራት መጀመሩን ስለ ካራ አሎ ስያሜ መረጃ አቀባይ ሽማግሌዎች[6] ይናገራሉ።

በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ ምንም እንኳን በልዩ ልዩ መልኩ የአማርኛ ቋንቋ ተጽዕኖ ቢኖርበትም ባህሉን የሚያንጸባርቅበት አፋን ኦሮሞ ከአማርኛ ጋር እያደባለቀ በመጠቀም ላይ ይገኛል። ይህም ሕዝቡ ቋንቋውን መጠቀሙ እና ባህሉን በልዩ ልዩ መልኩ ማንጸባረቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ1984ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች በአፋን ኦሮሞ እየተሰራበት ሲሆን ባህሉም በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በኩል በተለያዩ መልኩ እየተንጸባረቀ ይገኛል። (አቶ መስፍን ንጉሱ፣ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ባህልና ቱሪዝም ሃላፊ፣ መጋቢት15 ቀን 2006 ዓ.ም)።

የቱለማ ኦሮሞ በሥሩ በደም (ዘር) ግንኙነት ላይ የተመሠረቱ በርካታ ጎሳዎችና የጎሳ ቤተሰቦች አሉት። ይህንን በሚመለከት በቃለ- መጠይቅ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተገኙት መረጃዎች እና ከጽሑፍ መረጃዎች ተቀናብሮ በምዕራፍ አራት ሥር በዝርዝር ቀርበዋል።

የቱለማ ኦሮሞ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እየኖረ ነው። የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ዋና ከተማዋ ፊንፊኔ (አዲስ አበባ) ነው። ልዩ ዞኑን በአራቱም አቅጣጫ የኦሮሚያ ዞኖች ያዋስኑታል። አዋሳኞቹ፡- በሰሜን፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፤ በደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፤ በምሥራቅ፣ የምሥራቅ ሸዋ ዞን፤ እንዲሁም በስተምዕራብ፤ የምዕራብ ሸዋ ዞን ናቸው።

ከፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ግብርና ልማት ጽ/ቤት የ2005 ዓ.ም. ማጠቃለያ ሪፖርት የተገኘው መረጃ የሚያሳየው የዞኑ የመሬት ስፋት 480,000 ሄክታር ሲሆን የአየር ጠባዩም

---

[2] Karra (ከረ) ማለት በአፋን አሮሞ በር ማለት ነው።

[3] ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ መስመር 15 ኪሎ ሜትር ዳገቱ ላይ ግራና ቀኝ ከፍ ያለ መሬት በር የሚመስል ቦታ ነበር። ድሮ በዚህ ቦታ ላይ አቶ አሎ ቡኔ ይኖር ስለ ነበረ karra Alloo ሲተረጎም የአሎ በር መባሉን መረጃ አቀባዮች (አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ቸሩ ሮሪሳ እና አቶ ታደሰ ደህኔ)ይነገራሉ።

[4] ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ በቡራዩ አከባቢ የሚገኝ የሐይቅ ስም ነው።

[5] Qoree (ቆሬ) በአማርኛ እሾህ ማለት ነው።

[6] አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ቸሩ ሮሪሳ እና አቶ ታደሰ ደህኔ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ለገጣፎ ።

60.12%ደጋ፣ 38.12% ወይናደጋና 23% ቆላማ ነው። ዓመታዊ የዝናብ መጠኑን በሚመለከት ዝቅተኛው 900 ሚሊ ሊትር ከፍተኛዉ 2400 ሚሊ ሊትር ሲሆን አማካዩ 1050 ሚሊ ሊትር ነው። በመሆኑም ለእርሻና ለከብት እርባታ ምቹ ነዉ። በገጠር የሚኖር ሕዝብ ዋና መተዳደሪያው ግብርና ሲሆን በሁሉም ወረዳዎች በአብዛኛዉ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ ምስር እና ሽንብራ በዋነኝነት የሚመረቱ አዝእርቶች ናቸዉ። በከተሞች አካባቢ ልዩ ልዩ ፋብሪካዎችና የግል የመኖሪያ ቤት ገንቢ ድርጅቶች ይገኛሉ። እነዚህ ድርጅቶች ለከተማ ነዋሪዎቹ በልዩ ልዩ ንግድ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ምክንያት ሆኗቸዋል። ጥቂት የሚሆኑ የከተማ ነዋሪዎች በመንግስት ስራ ላይ ይገኛሉ (በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የመሬትና አከባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት፣ እ.ኤ.አ. 2009 ዓ.ም)።

በልዩ ዞኑ ነዋሪ የሆኑ የቱለማ ዝርያ ያላቸው ጎሣዎችና የጎሣ ቤተሰቦች ተመሳሳይ ባህልና የአኗኗር ስልት አላቸው። በተለይ በባህላዊ የፍቅር ግንኙነታቸው የከንፈር ወዳጅ[7] (Wadaajii)፣ ውሽማ[8] (Sanyoo)፣ ሲገባ[9] (Sigabaa) እና "እሬ[10]"(Irree) በመሳሰሉት ባህላዊ ትውፊቶች ተመሳሳይነት እንዳላቸዉ ከልዩ ዞኑ ባህልና ቱሪዝም ሃላፊ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል (አቶ መስፍን ንጉሴ፣ መጋቢት15 ቀን 2006 ዓ.ም)። በእነዚህ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የተነሳ ለተለያዩ ተላላፊ የአባለዘርና ለቀሳፊው ኤች ኣይ ቪ /ኤድስ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚ ይኖራል።

እነዚህን አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ ለኤች አይቪ ኤድስ የሚያጋልጣቸው ሌላው ምክንያት በአዲስ አበባ ዙሪያ መገኘታቸው ነው። ከአገር አቀፍ ህዝብና ቤቶች ቆጠራ (CSA, 2011) መረጃ መሠረት አዲስ አበባ ከተማ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ቀዳሚውን ሥፍራ ትይዛለች። ከዚሁ ጋር በተያያያ ሁኔታ ከ(Ethiopian Public Health Institute Federal Ministry of Health, July, 2014:15) የተገኘው እስታስቲካዊ መረጃም የቫይረሱ ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ እንደሚበዛና በበሽታውም ይበልጥ የተጠቃው ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል መሆኑን ያመለክታል።

በመሆኑም በዚህ አካባቢ የሚኖር ኦሮሞ ከከተማው ህዝብ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች የቀረበ ግንኙነት ያለው ሲሆን በተለይ የንግድ ግንኙነቱ ከፍተኛውን ሥፍራ ይይዛል። ለምሳሌ፡-

[7] በወጣትነት እድሜ ክልል የሚገኙ ወንድ እና ልጃገረድ ከንፈር በመሳሳም የሚፈጥሩት የፍቅር ወዳጅነትን ይመለከታል።
[8] ባል ወይም ሚስት እያለው ወይም እያላት በድብቅ ከሌላ ሴት ወይም ወንድ ጋር የወሲብ ወዳጅነት መፍጠርን ይመለከታል
[9] ባሏ የሞተባት ሴት በቀድሞ ባሏ ቤት ውስጥ ገብቶ በሟቹ አልጋ (መኝታ) ላይ ወሲብ የፈጸመ ሰውን ይመለከታል።
[10] የአጎት/የአክስት ልጅ "ዱብር" የሚበላው በጋብቻ ወቅት እንደ ሚዜ ሆኖ በኋላ ላይ "ከዱብሪው" ሚስት ጋር በድብቅ ወሲብ የፈጸመ ሰው።

ለአዲስ አበባ ህዝብ፣ ምግብና የማብሰያ ማገዶዎችን የሚያቀርቡት በልዩ ዞኑ ውስጥ የሚገኙ ገበሬዎች ናቸው። ከሚያገኙት ገቢ ላይ ወደ መጠጥ ቤት ጎራ ብለው መጠጣት የተለመደ ነው። ከመጠጡ ጋር ተያይዞ በሚፈጠረዉ ጊዜያዊ ስሜት ከከተማው ሴተኛ አዳሪዎች ጋር ወሲብ ይፈጽማሉ። በባህላዊ የፍቅር ግንኙነቱ ወሲብ የሚፈጽሙባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ከመስክ የተሰበሰቡት የሥነቃል መረጃዎች ያሳያሉ። በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ባህላዊ የፍቅር ግነኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስበው ከይዘታቸው አኳያ ተተንትነዋል።

1.2 የምርምሩ አነሳሽ ምክንያቶች

ለዚህ ጥናት መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱና ዋንኛው በኢትዮጵያ ዲሞግራፊክ የጤና ዳሰሳ መረጃ መሠረት አዲስ አበባ ከፍተኛ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት የሚታይባት ከተማ መሆኗ ነው (CSA, 2011)[11]። በዚህም የተነሳ በበሽታው ይበልጥ የተጠቁት ወጣቶች በተለይም ወጣት ሴቶች መሆናቸውን በOSSREA[12] (2008) ውስጥ “The Challenges and Opportunities of Mainstreaming HIV and AIDS Intervention in Ethiopia’s Higher Education System: What Roles for Tertiary Education?” በሚል ርዕስ ሥር እንደሚከተለው ተገልጿል።

> Ethiopia is currently experiencing a generalized HIV epidemic among the overall population. … Available statistics would show that the overall infections rate in the country was about 4.4% in 2003. The situation is worse in urban areas where the estimate on infection is about 12.6%, with in the capital Addis Ababa taking its tallat 14.5%. The estimate for rural prevalence was about 2.6% … the rate of infection among multi-partener sex contact females and males attending STD clinics in Addis Ababa had reached respectively 6.7% and 1.7% (MOH 2004). … About 91% of infections occur among adults between 15 and 49 years of age (HAPCO 2004). The higest concentration of infected group for AIDS is found between 20 and 29 years of age for both sexs. Infection rates are higher among females than males between 15 and 19, which perhaps reflect the occurrence of an eariler sexual activity among young females with old male partners (Abebe Haile Gabrile, 2008: 7-8).

ሲተረጎም

> በአሁኑ ዘመን ሕዝቦቿ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከተጠቁ አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። እስታስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በ2003 ዓ.ም በአገሪቱ ካለው

[11]The Ethiopian Central Statisics Agency.
[12] Organization for Social Science Research in Eastern and Southern Africa

ሕዝብ ውስጥ በኤች ኣይቪ በሽታ ሥርጭት መጠን 4.4% ነበር። በ2004 ዓ.ም ሁኔታው እጅግ በጣም ተባብሶ በአዲስ አበባ ከተማ የበሽታው የሥርጭት መጠን 14.5% ሲገመት የገጠሩ 2.6% ነበር (MOH 2004)። በዚያ ዘመን በአዲስ አበባ ውስጥ በተላላፍ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከተጠቁ ሰዎች መካከል የሴቶቹ 6.7% ሲሆን የወንዶቹ ደግሞ 1.7% መሆኑን መረጃው ይጠቁማል። … ቫይረሱ ካለባቸው 91% የሚሆኑት ከ15 እስከ 49 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው (HAPCO 2004) ። ከእነዚህ በከፍተኛ ደረጃ የኤድስ ተጠቂ የሆኑት በሁለቱም ፆታ ዕድሜያቸው ከ20 እስከ 29 የሚገኙ ናቸው። የቫይረሱ መጠን አይሎ የሚታየው ከ15 እስከ 19 የእድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙት ወጣት ሴቶች ላይ ነው። እነዚህም በአብዛኛው የግብረሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙት ከሽማግሌዎች ጋር ነው አበበ ሀይለ ገብርኤል፣ እኤአ 2008፥7-8)።

ከዚህ የምንረዳው አዲስ አበባ ዓለም አቀፋዊ ከተማ እንደ መሆኗ መጠን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ከተማዋ የሚገቡ ሰዎች የበሽታውን ስርጭት መጠን የሚያባብሱ መሆናቸውን ነው። በሌላ መልኩ መረጃው እንደሚያሳየው በበሽታው በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ የሆኑት በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ናቸው። ወጣት ሴቶችን ይበልጥ ተጋላጭ የሚያደርጋቸው በቡና ቤቶች ውስጥ በመስተንግዶ ስም ተቀጥረው የወሲብ ንግድ ላይ መሰማራታቸው ነው።

የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ለከተማ በጣም ቅርብ መሆኑ፣ ከከተማው ማህበረሰብ ጋር በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በባህላዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ትስስር አለው። በመሆኑም በንግድ ግንኙነት ምክንያት ለበሽታው ግንባር ቀደም ተጋላጭ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለዚህ ጥናት ከ2006 እስከ 2007 ዓ.ም. ድረስ በተደረገው መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ከፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ2006 ዓ.ም የደም ምርመራ ካደረጉ 60,557 ውስጥ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የተገኘባቸው 1,095 ናቸው።[13] ይሄም በአካባቢው ያለውን የበሽታ ሥርጭት (Prevalence rate) 1·8% መሆኑን መረጃው ያሳያል። ይህ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ በወቅቱ 1·5% ከነበረው አንጻር ሲታይ የጉዳዩን አሳሳቢነት ያመለክታል። ጥናቱ ካተኮረበት የሱሉልታ ወረዳ በ2007 ዓ.ም. የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የደም ምርመራ ካደረጉት ሰዎች ውስጥ ቫይረሱ የተገኘባቸው በመቶኛ ሲሰላ በአካባቢው ያለው የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መጠን (HIV/AIDS Prevalence rate) 3.56% መሆኑን ያሳያል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከአካባቢው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ የተሰበሰቡት የሥነቃል መረጃዎች የቫይረሱ ሥርጭት መኖሩን የሚያመለክቱ

---

[13]የኦሮሚያ ልዩ ዞን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ2006 ዓ·ም አጠቃላይ ሪፖርት

ናቸው። ስለዚህ ይህ ለጥናቱ ዋንኛው አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሌሎች አነሳሽ ምክንያቶች ደግሞ ቀጣዮቹ ናቸው።

በ2008 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአፋን አሮሞ "(Aadaa Saalaa Oromoo)" የኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት በሚል ርዕስ በኦሮሚያ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ በረክ ወረዳ ላይ ትኩረት ያደረጉ የሥነቃል መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናት በአደረኩበት ወቅት ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶችም ስለነበሩ ይህንን ርዕሰ ለማሰብና በዚህ ዙሪያ ጥናት የማድረግ ውስጣዊ ፍላጎት ነበረኝ። ስለዚህ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዓለም አቀፋዊ ችግር መሆኑና እስካሁንም መፍትሔ ሳያገኝ እንደ ተዳፈነ እሳት ውስጥ ውስጡን በመሰርሰር ጥፋት እያደረሰ ስለሆነ፣ ማህበረሰቡ በተለይ ወጣቱ ሳይዘናጋ በወሲብ ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄ ከማድረግ እንዳይቦዝን እና ከበሽታ ራሱን እንዲጠብቅ ከወሲብጋር በተያያዘ ሁኔታ ባህላዊ ጉዳዮቹን በጥናት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ከዚሁ አንጻር በኦሮሚያ ክልል፣ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር አያይዘው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ በሚናገሯቸውና በሚከውኗቸው የሥነቃል ዓይነቶች ላይ እስካሁን የተካሔደ ጥናት አለመኖሩ አነሳሽ ምክንያትን የሚያጠናክር ነው። በመሆኑም የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በኅብረተሰቡ ሥነቃል ቢታገዝ የተሻለ ውጤት ይገኛል በሚል እምነት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች በማንሳት ጥናቱ ተከናውኗል።

1.3 የምርምር ጥያቄዎች

ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ ያለው ማህበረሰብ የሚናገረው የሥነቃል ዓይነቶች በጥልቀት ለመመርመር ማብራሪያ ተኮር ጥናትና ምርምር እስትራቴጂን በመከተል ትክክለኛ መረጃዎችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ጥናትና ምርምር ተደርገዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለበሽታው መስፋፋት ወይም በሽታውን ለመከላከል አስተዋፅኦ ያበረክታሉ ተብለው የሚገመቱ ጥያቄዎችም ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል። በተለይ ከወሲብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶች ለማሰባሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል።

በመሆኑም በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዝርዝር ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረቡ ናቸው።

1. በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ የሚዘወተሩ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ምን ምን ናቸው? እነዚህን አስመልክቶ የሚነገሩና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? በማን መቼና የት ይነገራሉ/ ይከወናሉ?
2. ከእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የትኞቹ ናቸው?
3. ስለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች መካከል በሽታው እንዳይስፋፋ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ወይም ስርጭቱን የሚያባብሱት የትኞቹ ናቸዉ?
4. ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች የትኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ይበልጥ ተጠቂ እንደሆኑ ይገልጻሉ?
5. እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች በሽታው እያደረሰ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊ ችግሮችን ምን ያህል አጉልተው የማሳየት አቅም አላቸው?

1.4 የጥናቱ ዓላማ

ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚነገሩ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ምስጢር የሚቆጠሩ ናቸው። ይሁን እንጂ ሥነቃል የተደበቁትን ምስጢሮች ይፋ ለማዉጣት ኃይል ስላለው፣ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በተመለከተ ማህበረሰቡ ያለውን አመለካከት ለማወቅና ለችግሩ መፍትሄ ለመፈለግ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችን ከነክዋኔያቸዉ ሰብስቦ ይዘታቸውን መተንተን ያስፈልጋል። ይሄን ለማሳካት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ እና ዝርዝር ዓለማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በቱለማ ኦሮሞ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች ከነአውዳቸው በመሰብሰብ ይዘታቸውን መተንተን፤ በሽታውን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ያላቸውን አዎንታዊ ሚና ወይም ለቫይረሱሥርጭት የሚኖራቸውን አሉታዊ ገጽታ በመለየት ለኅብረተሰቡ ማስተማሪያ እንዲሆኑ በግብአትነት እንዲያገለግሉ ማድረግ ነው።

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የቱለማ ኦሮሞን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶችን መለየትና ይዘት መተንተን፣

2. ከባህላዊ የፍቅር ግንኙቶች ጋር ተያይዞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከቱ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችን ለይቶ ማሳየት፣
3. ኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዳይስፋፋ የሚከላከሉ ወይም የሚያባብሱ የሥነቃል ዓይነቶችን ይዘት መተንተን፣
4. ኤች አይ ቪ/ ኤድስ እያደረሰ ያለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ችግሮችን መሠረት በማድረግ የሥነቃል ዓይነቶቹ የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል አቅም እንዳላቸው ማሳየት፤
5. ጥናቱን መሠረት በማድረግ የመፍትሔ ሀሳቦችን መጠቆም።

1.5 የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት ውስጥ ከጊዜ እና ገንዘብ እጥረት የተነሳ ጥናቱ የሚካሔድበት አካባቢ እና ርዕሰ ጉዳይ መወሰን የግድ ይሆናል። በመሆኑም የጥናቱ ቦታና ርዕስ ወሰን እንደሚከተለው ቀርቧል።

1.5.1 የጥናቱ ወሰን ከቦታ አኳያ

የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቀደም ሲል በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ፣ በድቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በምሥራቅ ሸዋ እና ምዕራብ ሸዋ ሥር ይተዳደር ነበር። ሆኖም ከ2000 ዓ.ም ወዲህ ቡራዩ፣ ወልመራ፣ ሙሎ፣ ሆለታ፣ ኮሎቦ (መናገሻ)፣ ተፍኪ፣ ጫንጮ፣ መልካ ቁንጡሬ፣ ዱበር፣ ለገጣፎ፣ ለገዳዲ፣ አቃቂ እና ገላን በአዲስ አበባ አካባቢ የኦሮሚያ ልዩ ዞን አስተዳደር ሥር እንዲተዳደሩ ተደርገዋል (ዲሪቢ ደምሴ፣ 2007፡ 167-168)። በዚህ መሰረት ከሰሜን ሸዋ በረክ፣ ሱሉልታና ሙሎ ወረዳዎች፤ ከደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሰበታ ሀዋስ ወረዳ፣ ከምሥራቅ ሸዋ አቃቂ ወረዳ እና ከምዕራብ ሸዋ ወልመራ ወረዳ አንድ ላይ ሆነው የኦሮሚያ ልዩ ዞን ተመሠረተ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በፊንፊኔ ዙሪያ አምስቱም በሮች የሚገኙ ከተሞች የተመሠረቱት ቀደም ሲል በወረዳዎቹ ሥር የሚታደደሩ ቀበሌዎች ራሳቸውን የቻሉ አስተዳደር ሆነው ነው። በዚሁ መሠረት ከበረክ ወረዳ የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር እና የሰንደፋ በኬ ከተማ አሰተዳደር፣ ከሱሉልታ ወረዳ የሱሉልታ ከተማ አሰተዳዳር፣ ከወልመራ ወረዳ የቡራዩ ከተማ አስተዳደር እና የሆለታ ከተማ አስተዳደር፣ ከሰበታ ሀዋስ ወረዳ የሰበታ ከተማ አስተዳደር፣ ከአቃቂ ወረዳ የገላን ከተማ አስዳደር እና የዱከም ከተማ አስተዳደር ተመሥርተዋል።

በዚህ መሠረት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን 6 ወረዳዎች እና 8 ከተሞች በድምሩ 14 የሕዝብ አስተዳደር እንዳለው ከልዩ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት 2006ዓ.ም. የተገኘ መረጃ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዞኑ ውስጥ የነበሩ የተወሰኑ ከተማ አስተዳደሮች ተጠሪነታቸዉ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንደሆነ ይነገራል[14]።

በመሆኑም የቱለማ ኦሮሞ ከሰፈረበት ሰፊ መሬት አንጻር በልዩ ዞኑ ስር የሚተዳደሩ ወረዳዎችና ከተሞችን በሙሉ የጥናቱ አካል ማድረጉ ለጥናቱ ከተወሰነለት ጊዜና ገንዘብ አኳያ አይቻልም። ስለዚህ ለጥናቱ ወሰን ማበጀቱ የግድ ይሆናል። በልዩ ዞኑ ውስጥ የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ አፋን ኦሮሞ ተናጋሪ እና ተመሳሳይ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ያለዉ በመሆኑ ጥናቱ በአንድ ወረዳ ወይም ከተማ ቢካሔድ ተመሳሳይ ውጤት ይገኛል።

ስለዚህ በዞኑ ውስጥ ካሉ ወረዳዎችና ከተሞች አንዱን መምረጥ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ከዞኑ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ2006 ዓ·ም. ከተገኘው ማጠቃለያ ሪፖርት አኳያ የሕዝብ ብዛት እና የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭትን መሠረት በማድረግ የጥናቱ ቦታ ተወስኗል።

ስለሆነም ካለው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር፣ ለአዲስ አበባ ካለው ቅርበት አኳያ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት በአካባቢው በስፋት መገኘት ከዚሁ ጋር ተያይዘው አከባቢው በሥነቃል የዳበረ በመሆኑ የሱሉልታ ወረዳና ከተማ ለጥናቱ ተመራጭ ሆኗል። በዚሁ መሠረት ጥናቱ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞንን የሚያካትት ሆኖ በሱሉልታ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ሱሉልታ ከሕዝብ ብዛት እና ከቫይረሱ ሥርጭት አንጻር የተመረጠበት ሁኔታ የሚገልጽ ሠንጠረዥ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1:- በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ወረዳዎች/ ከተሞች፣

የሕዝብ በዛት እና የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መግለጫ

ተቁ	የወረዳዉ ስም	የሕዝብ ብዛት	የበሽታው ሥርጭት በመቶኛ	የከተማዉ ሥም	የሕዝብ ብዛት	የበሽታው ሥርጭት በመቶኛ
1	ወልመራ	72,611	1·3%	ሆለታ	32,595	2·2%

[14]ከዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት በተገኘዉ መረጃ መሠረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአዲስ አበባ በቅርበት የሚገኙ ስድስት ከተሞች (ዱከም፣ ገላን፣ ሰበታ፣ ቡራዩ፣ ሱሉልታ እና ለገጣፎ-ለገዳዲ) ተጠሪነታቸዉ በቀጥታ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ሆኗል ። ቢሆንም በጥናቱ ላይ የሚያመጣው ለዉጥ የለም፤ ምክንያቱም የጥናቱ ትኩረት በገጠሩ ላይ ቢሆንም ሥነቃሉ በከተማም በገጠርም አለ። በተለይም በጥምቀት ክብረበዓል አድስ አበባን ጨምሮ በየከተማው የሚዘፍነው በአዲስ አበባ (ፊኒፊኔ) ዙሪያ የሚገኙ የቱለማ አሮሞ ነው።

2	ሱሉልታ	144,606	1·5%	ሱሉልታ	37,747	3.7%
3	ሰበታ ሐዋስ	115,554	1.0%	ሰበታ	78,885	3.5%
4	በረክ	82,078	0·2%	ሠንዳፋ በኬ	13,799	1·9%
5	አቃቂ	8,581	0·4%	ገላን	11,121	3.2%
6	ሙሎ	41,424	0·6%	ዱከም	8,069	2.1%
7				ቡራዩ	66,262	1.9%
8				ለገጣፎ ለገዳዲ	12,999	0.6%
ድምር		554,854			261,477	

በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት አጠቃላይ ሪፖርት 2006 ዓ.ም.

1.5.2 የጥናቱ ወሰን ከይዘት አኳያ

የጥናቱን ይዘት በሚመለከት የፎክሎር ጥናት መስክ የሚዳስሳቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች እንዳሉ የመስኩ ምሁራን Dorson(1972)፣ Okepewho (1992) እና ፈቃደ አዘዘ (1991) ይገልጻሉ። በዚሁ መሠረት ፎክሎር በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባል። እነዚህም ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሥነቃል ናቸዉ።

የዚህ ጥናት ትኩረት ሥነቃል ላይ ብቻ ሆኖ ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ ማህበረሰቡ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የሚናገሩትንና የሚከውኑትን ይመለከታል። ነገር ግን ከሥነቃል ዓይነቶች ብዛት የተነሳ ሁሉንም ማጥናቱ ከጊዜና ገንዘብ እጥረት አኳያ ስለማይቻል በምሳሌያዊ ንግግሮች እና በዘፈኖች ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል።

በሌላ መልኩ ከመረጃዎች መሰባሰቢያ ዘዴዎች እና ከመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻርም ወሰን ተደርገዋል። ዘዴዎቹ በመጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ላይ ትኩረት ተደርገዋል። ዝርዝር ሁኔታው በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ቀርበው በምዕራፍ አራት ውስጥ ተግባራዊ ሆነዋል። ከትንታኔ አኳያ በርካታ ቲዮሪዎች የተዳሰሱ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አብዘኞቹ በደጋፊ መተንተኛነት ሲያገለግሉ በዋና መተንተኛነት አውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች ላይ ትኩረት ተደርገዋል። ዝርዝር ሁኔታው በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ቀርበው በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት በሥራ ላይ ውለዋል።

1.6 የጥናቱ ውሰንነት

ኤች አይ ቪ/ኤድስ በዓለም ላይ የታየው እ.ኤ.አ 1980/81 ጀምሮ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ (UNAIDS, 2004[15]; Landau-Stanton & Clements, 1993: 9)[16]። የቫይረሱን ሥርጭት በተመለከተ የተካሔዱ ጥናቶች በተለይም በሽታው እያደረሰ ካለው ችግር አንጻር የተሰጠው ትኩረት ብልጭ ድርግም የሚል ዓይነት መሆኑን ይገልጻል (Menur, 2007)። ስለዚህ የበሽታው መታየት አዲስና የቅርብ ጊዜ ክስተት እንደመሆኑ መጠን ከፎክሎር አኳያ በተለይም ከሥነቃል አንጻር የተካሔዱ ጥናታዊ ሥራዎች በበቂ ሁኔታ አለመገኘታቸው በተጓዳኝ ጽሑፋዊ ቅኝት ላይ ውስንነት ነበር።

የበሽታው ሥርጭት በአብዛኛው በድብቅ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ ድብቅና ውስብስብ በሆኑ የፍቅር ግንኙነቶች ዙሪያ ጥናት ሲደረግ መረጃ ለማሰባሰብ አስቸጋሪ መሆኑን Legman(1962) ይገልጻል። በመረጃዎች አሰባሰብ ወቅት በተለይ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት ላይ ሀሳብ ከመስጠት መቆጠብ የነበረ ቢሆንም የጥናቱ ዓላማ የግለሰቦችን ታሪክ ለመጻፍ ሳይሆን ማህበረሰቡ ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሚናገረው እና በሚከውነው የሥነቃል ዓይነቶች ላይ ብቻ ትኩረት እንደሚያደርግ ተገልጾላቸዋል። ከዚሁ አንጻር የምርምሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ እንቅፋት የሚሆኑ የጎሉ ችግሮች አልተፈጠሩም። በመሆኑም በመረጃ አሰባሰብ ሂደት በጥናቱ ላይ ተፅእኖ ያሰደሩ ችግሮች አልነበሩም።

ይሁን እንጂ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በአፋን ኦሮሞ ሆኖ የጥናቱ ጽሑፍ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ በተለይ ዘፈኖችን በአማርኛ ስሜት እንዲፈጥሩ አድርጎ መተርጎሙ ላይችግር ነበር። ይህንን በሚመለከት ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ የመተርጎሙ ሥራ ከባድ መሆኑን Dundes(1980:22[17]) ይገልጻል። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፎክሎርን በመገኛ ቋንቋው አለማጥናት አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ፊቃደ አዘዘ (1991፡ 44) በዝርዝር እንደሚከተለው ገልጿል።

> የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ስሙ እንደሚያመለክተዉ ተግባሩን አልተወጣም የሚል ክስ ሲሰነዘርበት ቆይቷል። ክሱ እዉነትነት አለዉ። ነገር ግን

[15] Since the first AIDS case was diagnosed in 1981, the world struggled to come to grips with extraordinary dimensions.

[16]Because AIDS was first discovered in the early ‘80s in the United States, and there was no erlier record of it, it was assumed to be a new disease, a sudden epidemic unlike anything before in medical history.

[17] In most of the genres, the texture is the language. … The more important the textural features are in a given genre of folklore, the more difficult it is to translate an example of that genre into another language.

> [ትምህርት] ክፍሉ በተለያየ ጊዜ ለስሙ ለመብቃት ሲል የጠየቃቸዉ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ አለገኙም። … በ1970ዎቹ በጀመረዉ የሥነቃል [መሰብሰበ ሥራ]፣ ባሉት ጥቂት አባላት፣ በትግርኛ (34)፣ በጉራግኛ (32)፣ በኦሮምኛ (26)፣ በኩናምኛ (18)፣ በወላይትኛ (18)፣ በጋሞኛ (14)፣ በጊሚርኛ (13)፣ በሶማልኛ (12)፣ በሀድይኛ (11)፣ በካምባትኛ (06)፣ በድምሩ በ184 ካሴቶች ሥነቃል ሰብስቧል። ይህንን እንዲያደርግ ማንም መንግስት አላነሳሳዉም፣ አስጨንቆም አልገፈፋፋዉም። የፍላጎቱ ምንጭ ትምህርት (አካዴሚያዊ) እንጂ ፖለቲካ አልነበረም። እነዚህን ካሴቶች በተገቢዉ የሙያ እውቀት ለማጥናት የሚችል የሰዉ ኃይል ለማሠልጠን ስላልተቻለ እስከዛሬ በ[ትምህርት] ክፍሉ ተቀምጠዋል።

ከዚህ የምንረዳው በሥነቃል ላይ የሚከናወን ጥናትና ምርምር በመገኛ ቋንቋ ቢጠና የማህበረሰቡን ባህል በትክክል በማንጸባረቁ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ይህ ካልሆነ ግን በትርጉም ሥራ ውስጥ አቻዊ ፍቺ በመፈለጉ በኩል አድካሚ ከመሆኑም በላይ መረጃው የተሰበሰበበትን ማህበረሰብ ባህል በትክክል ለመግለጽ ያስቸግራል።

ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውሰጥ በአፋን ኦሮሞ የተሰበሰበውን የሥነቃል መረጃዎች ወደ አማርኛ አቻዊ ትርጉም ሲቀየር እንደ ዋናዉ ባህል ስሜት ስለማይሰጥና በዚህም የተነሳ መልዕክቱ ሊዛባ ስለሚችል ጥናቱን ውስን ያደርገዋል። እንደ አጥኚው እምነት የመገኛ ቋንቋን ወደ ጥናቱ ቋንቋ ከመተርጎም ይልቅ በመገኛ ቋንቋ ቢጻፍ[18] ባህሉን የበለጠ ይገልጻል። ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናትና ምርምር ችግሩን ለመፍታት አጠኚው ማህበረሰብ ተወላጅ በመሆኑ የትርጉሙንም ሥራ አከናውኗል። በበጀት እጥረት ምክንያት በቋንቋ ባለሙያ የማስተርጎም ሥራ ማከሔድ ባይቻልም በፍቃደኝነት ላይ በተመሠረተ መልኩ በትርጉም ሥራ የተሻለ እውቀት ያላቸው ሰዎች እንዲያዩት በማድረግ ከአጥኚው ትርጉም ጋር ተመሳክረው ተስተካክለዋል። በመጨረሻም አጥኚው ከአማካሪው ጋር በመወያየት የማስተካከል ሥራ ተካሂዶ እንዲታረም ተደርጓል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ጥረት ተደርጎም የትርጉሙ ሥራ ክፍተት የለውም ማለት አይደለም። ይህም አንዳድ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና የዘፈን ግጥሞች ከአፋን ኦሮሞ ወደ አማርኛ ሲተረጎሙ ስሜት የሚሰጡ አይደሉም። በመሆኑም ለእንደዚህ ዓይነቶቹ የሥነቃል ዓይነቶች የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የተለየ ገለጻ ተደርገዋል።

[18]አጥኚውም ጥናቱ በኦሮሚኛ ቋንቋ ቢጠና የተሻለ ስራ እንደሚሆን ያምናል። ይሄንንም ጉዳይ የሚመለከታቸውን የዩንቨርሲቲውን የስራ ሀላፊዎች አነጋግሯል። እስካሁን ግን ተጨባጭ መፍትሄ ባይገኝም ጥያቄዉ እስካለ ድረስ ለወደፊቱ መልካም ምላሽ ይኖራል የሚል ተስፋ አለኝ።

1.7 የጥናቱ ፋይዳ

ባህላዊ የፍቅር ግኑኙነቶችና መሰል ጉዳዮች በአብዛኛዉ በድብቅ የሚከናወኑና በባህል ምክንያት ፊት ለፊት የማይወያዩባቸው ናቸዉ። ግልጽ ውይይት ስለማይደረግባቸውም ሕዝቡ ለከፋ አደጋ ሊዳረግ ይችላል። በጥናቱ የተገኙት የሥነቃል ዓይነቶች ሕዝቡን ለይፋዊ ውይይት የሚጋብዙ በመሆናቸው የአገራችን ሕዝቦች በሙሉ በተለይም ጥናቱ የተካሄድበት ማህበረሰብ ተጠቃሚ ናቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳዎች አሉት።

1. የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታን ለመከላከል በጉዳዩ ላይ የተሻለ እውቀት ስለሚገኝ ይፋዊ ውይይት ለማድረግ ያገለግላል፤
2. የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ስርጭትን የሚያባብሱ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በመለየት፣ ቫይረሱን ለመከላከል እና ለመግታት የሥነቃል ዓይነቶችን በመጠቀም ሕዝብን በጤናው ዘርፍ ለማስተማር ይረዳል፤
3. ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የጥናቱ ውጤት ከፎክሎር ትምህርታዊነት አንጻር በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት በማድረግ፣ አዲሱ ትውልድ ጎጂና ጠቃሚዉን ባህላዊ እሴቶች ለይቶ ራሱን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ተከላክሎ ጤናማ ዜጋ በመሆን ለአካባቢዉ ልማት መፋጠን አስተዋጽዎ ያደርጋል፤
4. ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጣር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የጤና ፖሊሲ ለመቅረጽ በግብአትነት ሊያገለግል ይችላል፤
5. መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች በተመሳሳይ መልኩ ለሚያደርጉት ጥናታዊ ምርምር የመነሻ ሀሳብ ያገኙበታል።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ፅንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሀሳባዊ ደሰሳ እንዲሁም ተዛማጅ ጥናቶች የሚመለከቱ ጉዳዮች የተቃኙበት ነው። እነዚህም በአንድም በሌላም መንገድ ከዚህ ጥናታዊ ምርምር ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች የተዳሰሱበት ናቸው። የፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳን አስመልክቶ ስለ ፎክሎር እና ስነቃል ምንነትና ሚና በዝርዝር የቀረበበት ነው። የንድፈ ሀሳብ ዳሰሳን በሚመለከት ደግሞ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ዝምድና ያላቸው የጤና ትምህርትና የወሲብ ቲዮሪዎች እንዲሁም የመረጃ መተንተኛ ቲዮሪዎች የተቃኙበት ነው። የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በተመለከተ በኤች አይ ቪ/ ኤድስና በወሲብ አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ከስነቃል ጋር በማያያዝ በተለያዩ አገሮች የተሠሩ ተዛማጅ ጥናቶች የታዩበት ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች የተዳሰሱበትነው።

2.1 የጽንሰ ሀሳቦች ዳሰሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የተካተቱት ጉዳዮች ጥናቱ የሚከናወንበትን ዲሲፒሊን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ከጻፏቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦች ምንነትና ጠቀሜታ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህ ንዑስ ርዕስ ሁለት ጉዳዮች አሉት። የመጀመሪያው የጥናቱ ጽንሰ ሀሳብ ማዕቀፍ ዳሰሳ የተደረገበት ሲሆን ከዚሁ አንጻር ስለ ፎክሎር ምንንትና ምደባና ምሁራን ያቀረቧቸው ማብራሪያዎች የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ናቸው። የስነቃል ምንነትና ሚና በሚመለከት በዘርፉ የሚከተቱ ዓይነቶች የተዘረዘሩበት ሲሆን የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ባህላዊ ገጽታዎች በማንጸባረቁ ረገድ የሥነቃል ሚና የተብራራበት ነው።

2.1.1 የፎክሎር ምንነት

ፎክሎር[19] የሚለው ቃልም ህዝብና ልማድ የሚሉ የሁለት ጽንሰ ሃሳባዊ ቃላት ውህድ ነው (Schoemaker 1990፡3)። ህዝባዊ የሚለው ቃል ቡድናዊ የሆኑ ሰዎችን የያዘ አካል ሲሆን ልማድ ደግሞ በባህል ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው። የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ እንደ ሰው ልጅነታችን ሁላችንም በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተሳታፊዎች እንደሆን፤ ከዚህም የተነሳ አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባትና ግንኙነት መፍጠር እንደሚችል ተጽፏል። ከዚህ አገላለጽ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ፈቃደ (1998፡2) "ፎክሎር ህይወት ስለሆነ" በግለሰብም ይሁን በማህበረሰብ ደረጃ የእለት ተእለት አኗኗር ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም ነገር እንደሚያጠቃልል ያስረዳል። ከዚህ ገለፃ መነሻነት ፎክሎር የሚለው ቃል ማንኛውንም የሕዝብ ቡድን የሚመለከት ሆኖ ቢያንስ አንድ በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚገልጽ መሆን እንዳለበት እንረዳለን፡፡

በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ትምህርት፣ ሥራ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣...ወዘተ ሊሆን ይችላል (Dndes, 1965)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፎክሎር ማለት ጥበባዊ ተግባቦት ያላቸው የኅብረተሰብ ቡድን መሆኑንና በቡድኑ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ሰዎቹ የሚናገሩትን፣ የሚያደርጉትን፣ የሚሠሩትን ...ወዘተ ጉዳዮች የተመለከተ መሆኑን Ben-Amos (1971:13) ይገልጻል።

---

[19] ፎክሎር የሚለው ቃል የፈጠረው ዊሊያም ጆን ቶምስ መሆኑን ተጽፎ ይገኛል (Schoemaker 1990፡3፤ ፈቃደ 1991፡2)፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ፎክሎር የሚለውን ቃል ፈቃደ አዘዘ (2003) ለማስተማሪያነት መርጦ ባደራጀው ማቴሪያል ውስጥ (Steiner Mathisen, 1999:35) Dundesን ጠቅሶ፣ ፎክ እና ሎር በማለት ቃሉን ለሁለት በመክፈል ብያኔ ይሰጣል። ይሄም "ፎክ (folk) አንድ የጋራ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል። "በማለት ሎር (lore)ን ደግሞ "የጋራ የሆነውና ያ የሚያገናኛቸዉ እውቀት ነው፤ የጋራ እውቀቱ ምንም ይሁን ምን ሎር ይባላል።" በማለት የሚያገናቸው ዋናው ነገር የጋራ ልማድ (tradition) መሆኑን ይገልጻል። ባጭሩ ፍክሎርን የሁለት ክዋኔዎች መግለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፤ ሰዎች በዘልማድ (በባህል) የሚናገሩት እና ሰዎች በዘልማድ (በባህል) የሚተገብሩት የሰዎች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባህል ነው ማለትም ይቻላል (ፍቃደ አዘዘ፣ 1996፡ v)። ከዚህ የምንረዳው ፎክሎር ከሰዉ ልጅ ሕይወት ጋር የተያያዘ የዕለት ተዕለት ባህላዊ ጉዳዮች የሚንጸባረቅበት መሆኑን ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን እሳቤዎች በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እኤአ 2010 "Basic Texts of the 2003 Convention for the Safeguarding of the Intangible Cultural Heritage" በማለት አንድ ሰነድ አውጥቷል። በሰነዱ ውስጥ "Intangible Cultural Heritage" ተብሎ የቀረበው ጽንሰ ሀሳብ የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/92 የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ ግዙፍነት ከሌላው የሰው ልጅ እውቀት አንጻር ይመለከተዋል። "ግዙፍነት የሌለው ቅርስ ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን በዓይን ለማየት፣ በጆሮ ለመስማት የሚቻል ቅርስ ሲሆን የብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒትና ጨዋታ፣ ሥነ ቃል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ፣ የሐዘን ሥነ-ስርዓት፣ ሙዚቃ፣ ድራማና ሌሎች ተመሳሳይ ባህላዊ እሴቶች፣ ወግና ልማድን ይጨምራል" በማለት ይተረጉመዋል። በዚህ ትርጉም መሠረት ኢንታንጅብል ባህላዊ ቅርስ የማይዳሰስ የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ክዋኔ ውጤት መሆኑን እንረዳለን።

ፎክሎር አንድ ሕዝብ በማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ ውስጥ ማሕበረሰቡ የሚገኝበትን ሁኔታ በማንጸባረቁ ረገድ የተለየ ሚና እንዳለው በርካታ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህም መረጃዎች ውስጥ Dundes, (1965) ፎክሎር ያለፈውን የሚያወሳ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ የእውቀት ምንጭ በመሆኑ በዕለታዊ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ ወቅታዊ የትኩረት ጉዳዮችን በማሳየት ባህላዊና ሥነልቦናዊ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በጭንቀት

ምክንያት ድብቅ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይቀር ይፋ የማድረግ አቅም እንዳለው በፎክሎር ትንተናው ላይ ያብራራል። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ድብቅ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ዋናዉ ከወሲብ ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆኑ ይህንንም አንድ ግለሰብ የሚማረዉ ከማህበረሰቡ መሆኑንና ለዚህም የቋንቋ ሚና ከፍተኛ መሆኑን Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006) ይገልጻሉ።

በሌላ አገላለጽ Ben-Amos, (1979) ፎክሎር ማህበረሰቡ በቋንቋው አማካይነት ባህላዊ እሴቶቹን የሚገልጽበት መስታወት ከመሆኑ አንጻር የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫና በውስጡም በርካታ እሴቶችን ያካተተ መሆኑን ይናገራል። በመሆኑም ፎክሎር አገልግሎት ለሚሰጥበት ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ንብረቱ እንደመሆኑ መጠን የሕዝቦችን ልማድ፣ ወግ፣ እምነት እና ጥበቦችን ያካተተ የባህል ዘርፍ መሆኑን ገልጿል።

2.1.2 የፎክሎር ምደባ

የፎክሎር ምደባን በተመለከተ Dorson "በመስኩ የሚደረግ ምርምርን ስርዓት ለማስያዝና... መልክ ለመስጠት ሲል..." ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈለው መሆኑን ፈቃደ (1991 2-4) ይገልጻል ። እነርሱም ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል ናቸው። ዩኔስኮ ደግሞ ይህን ምደባ እንዳለ ይወስድና ሀገረሰባዊ ልማድን ለሁለት በመክፈል "Intangible Cultural Heritage" የሚለውን ጨምሮ በአምስት መድቧቸዋል። አምስተኛው "የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ" ይለዋል። ነገር ግን የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ ራሱን ችሎ የሚወጣ ሳይሆን በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘ ነው። በዚህ ጥናት ፎክሎርን በአራት አበይት ዘርፎች ከፍሎ ማየት የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በፈቃደ (1991) አራቱ አበይት የፎክሎር ዘርፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ስነቃል፡- በዚህ ምድብ የሚካተቱት የፎክሎር ዓይነቶች የሰው ልጅ ምኞቱን፣ ፍላጎቱን፣ ችግሩን፣ ደስታውን፣ ሐዘኑን፣ ደግነቱን፣ ተግባሩን ወዘተ... ሁሉ በቃሉ የሚገልጽባቸው ናቸው። እነዚህም ቃል-ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዶች፣ አፈ-ታሪኮች እና ሌሎችም በቃል የሚከወኑ ናቸው።

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፡- ይህ የፎክሎር ዘርፍ ሀገረሰባዊ ሙዚቃን፣ ዳንስንና ድራማን የሚያቅፍ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በትንፋሽ ወይም በምት አማካይነት ድምፅ የሚሰማበት የሙዚቃ አይነት ነው። ዳንስ ደግሞ የተለያዩ የሰውነት

አካላትን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ጭፈራ፣ እስክስታ፣ ዳንኪራ ወዘተ…ነው። ሀገረሰባዊ ድራማ ወይም ቴአትር በሰው ልጅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ የሚያተኩሩ ትዕይንቶችና ትረካዎች የሚታዩበት ነው። ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ዳንስና ድራማ ሦስቱ ብቻቸውን የቆሙ ሳይሆኑ በተግባር አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

ሀገረሰባዊ ልማድ፡- በዚህ የፎክሎር ዘርፍ የሚጠቃለሉት የሰው ልጅ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም ፍላጎቶቹን ለማሟላት በግልና በጋራ የሚያከናውናቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ እነዚህም የሰው ልጅ የህይወት-ዑደት (ልደት፣ ጋብቻ፣ ሞት)፣ የእምነት፣ የማህበራዊ ደረጃና ክብር መገለጫ፣ የሥርዓተ ፆታ፣ የስም አወጣጥ፣ የሰውነት አጋጌጥ፣ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት፤ ሥነ ስርዓቶች፣ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች፣ ስፖርት ወዘተ … ናቸው።

ቁሳዊ ባህል፡- በዚህ ውስጥ የሚካተቱት የሰው ልጅ በመደበኛ ትምህርት ሳይሆን በምልከታና በተግባር በሚያገኘው ልምድ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ማተሪያሎችን የሚሰራበት ክህሎት ነው። ይህም የእንጨት፣ የቆዳ፣ የሸክላ፣ የሳር፣ የብረት እና ሌሎችም የእደ ጥበብ ውጤቶችንና የአሰራር ጥበባቸውን የሚያጠቃልል ነው።

ይህ ጥናት በሥነቃል ላይ ያተኮረ በመሆኑ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖር ስለ ምንነቱና ሚናው በምሁራን የተገለጹትን እንዲሁም የተከናወኑትን ጥናቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.1.3 የሥነ ቃል ምንነት እና ሚናው

ሥነቃል በጥናትና ምርምር ውስጥ የማህበረሰቡ ባህላዊ ልዩ ልዩ ገፅታዎች አንጸባራቂ፤ የማህበረሰቡ ምኞትና ፍላጎት የሚገለጽበት እንዲሁም ሥነ ውበታዊና መዋቅራዊ የሆኑ ጉዳዮች የሚዳሰስበት እና የማህበረሰቡን አጠቃላይ አመለካከት ያካተተ መሆኑን Brunvand (1979)፣ Wilson (1979) እና Austin (1994) ያብራራሉ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፈቃደ አዘዘ፣ (1991፡ 11) ሥነቃል ማለት በቃላት አማካይነት የሚፈጠሩትን በተረት፣ በቀልድ፣ በሌጀንድ፣ በሚት፣ በዘፈን ወይም በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ በእንቆቅልሽ፣ በእንኪያስለንቲያ እና በመሳሰሉት እንዲሁም ወደዚህ የሚቀርቡትን የምንጠራበት የጥቅል ስም መሆኑን ይገልጻል ።

በማያያዝም ዘሪሁን (1992፡20) ሲያብራራ "ስነቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በማዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ

ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው” ይላል።

የስነቃልን ስያሜ በሚመለከት ተረታ-ተረቶችን፣ ሚቶችን፣ አፈታሪኮች፣ ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሽ እና ቃልግጥምን፣ ዝማሬዎችን የመሳሰሉ በቋንቋ የሚገለጹ ጥበባትን ሁሉ ጥቅል የመጠሪያ ሆኖ እንደሚያገለግልና ትርጉሙም ስነቃሉ ከሚከወንበት ዓላማና ከሚያበረክተው አገልግሎት የሚመነጭ መሆኑን ብርሃኑ (1995: 2-9) ያብራራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበረሰቡ ስለራሱ ማንነት፣ የህይወት ፍልስፍና ማህበራዊ ግንኙነት፣ ጥላቻና ፍቅሩን የሚገልጸው በሥነቃል ዓይነቶች አማካይነት መሆኑን Asafaa Tafarraa, (2004) ይናገራል።

ሥነቃል የማህበረሰቡ እውቀት መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ከአንዱ የማህበረሰብ አባል በመማር ለሌሎችም የምናስተምርበት የእውቀት ዘርፍም በመሆን ያገለግላሉ። ከዚህም ስነቃል የመሰራጨት አድማሱ ሰፊና ፈጣን እንዲሁም በየትኛውም ባህል ውስጥ በተነገረበት ቅጽበት ወደ ሌሎች የመሸጋገር ሀይል ያለው መሆኑን እንገነዘባለን። ለምሳሌ ያህል ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን እና ቀልዶችን ከታላላቆቻችን እንማራለን፤ ሌሎችንም እናስተምርበታለን። በዚህ መልኩ ሥነቃል ከአንዱ ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ የማስተማር ሚናም አለዉ (Finnegan, 1970; Mieder, 1993; Egbe, 2000; Okpewho, 2004)።

እነዚህም ተግባራት የሥነቃል ባህሪያት መሆናቸውን በመግለጽ የሥነቃልን የማስተማር ሚና አስመልክቶ የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች እምቅ በሆነ ትርጉማቸው መልዕክት የማስተላለፍ ሚናቸው የጎላ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን Finnegan፣ (1970) እና Okpewho (2004፥226) ያስረዳሉ። ስለሆነም የማህበረሰቡን አባላት የማስተማር፣ የመለወጥና የተበላሸ ባህሪይን የማስተካከል ፋይዳ አላቸው። የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባራዊ ተግባራት እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ውጤታማ ናቸው (Bascom,1954)።

ሌላው የሥነቃል ፋይዳ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ድብቅ የሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነልቦናዊ ጉዳዮችን ግልፅ ማድረጉ ነው። ድብቅ ከሆኑ ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ የፍቅር ግንኙነት ነው። የፍቅር ግንኙነቶችን በተመለከተ ድርጊቶቹ በድብቅ

የሚከናወኑ ስለመሆናቸው እንደሚከተለው ተገልጿል። “The sexes and their relations are more mysterious than settled forever. Thus they are surely correct in their assessment that sex is more vague and more mysterious than one can say.” (Sandelands, 2001:vi). ይህ ማለት ወሲብና ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ከሁሉም በላይ ምስጢራዊ መሆናቸውን የሚገልጽነው።

በድብቅ የሚከናወኑት የፍቅር ግንኙነቶች ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ከሚያጋልጡ ድርጊቶች አንዱና ዋንኛዉ ናቸው። እነዚህ ምሥጢራዊና ውስብስብ የፍቅር ግንኙነቶች በተለይም በወጣትነት ዘመን በአብዛኛዉ ጥንቃቄ በጎደለዉ ሁኔታ ስለሚከናወኑ፣ ለአባለዘር በሽታ መስፋፋት፣ ባልተፈለገ እርግዝና ለሚፈጠረው ውርጃና ለቀሳፊው የኤች አይ ቪ\ ኤድስ በሽታ የሚያጋልጡ ስለሆኑ ችግሮቹን እጥፍ ድርብ ያደርጋል (Kachingwe, 2005)።

ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በመከላከል ረገድ ከሌሎች አገሮች በተገኘ ልምድ በሴሚናር፣ በሲምፖዚየም፣ ሙዚቃ በማሰማት፣ ፖስተር በመለጠፍ ፣ ቲ-ሸርት በመልበስ፣ ወዘተ… ክዋኔዎች በኢትዮጵያ የተፈለገውን ያህል ውጤት ባለማምጣቱ በሥነቃል የመከላከሉን አማራጭነት ዳንኤል ክብረት (2003) እንደ ሚከተለው ግልጿል።

> ሕዝብ መሪዎቹ እንደማይሰሙት ማሰብ ከጀመረ ብሶቱን በማንጎራጎር ማውጣት ይጀምራል። በቀድሞ ጊዜ አንዳንድ ነገስታትና መኳንንት “እረኛ ምን ይላል” ብለው ይጠይቁ ነበር ይባላል። በየወፍጮው፣ በየወንዙ፣ በየልቅሶው፣ በየሠርጉ፣ ወዘተ … ይነገር የነበረው ሥነቃል ለዚያ ሥርዓት ማድመቂያ ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ምን ተባለ ብለው የሚያዳምጡ መኳንንት እንዲሰሙት ጭምር የሚሰነዘር ነበር። … [ዛሬም ቢሆን] ኢትዮጵያ ውስጥ የፈለገውን ያህል መግለጫ ቢሰጥ እና አዋጅ ቢወጣ፣ ሴቶች ቡና ላይ፣ ወንዶች ጠጅ ቤት ተሰብስበው ውድቅ ካደረጉት ፈረሰ ማለት ነው። ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል ኀብረተሰብ ውስጥ እንዲለወጡ የምንፈልጋቸውን ነገሮች በፖስተር እና በባነር ከማስቀመጥ ወይም 85 በመቶ ለሆነው የገጠር ወገኖቻችን በየስብሰባው ረዣዥም ንግግሮችን ሰምታችሁ ተለወጡ ከምንላቸው ይልቅ በሚገባቸው እና በለመዱት መንገድ አንነግራቸውም። በልቅሶ፣ በሠርግ፣ ውኃ ለመቅዳት ሲኬድ፣ እርሻ ላይ፣ ወፍጮ ሲፈጭ የሚነገሩትን ሥነቃሎች ኅብረተሰባችን ከመርሳት ይልቅ ከዘመን ዘመን እያሸጋገራቸው ለትውልድም ሲያደርሳቸው እያየን ለምን ይህንኑ ለኅብረተሰቡ የሚገባውን መንገድ እንደማንጠቀምበት ግራ ይገባኛል። እኛ መለወጥ አቅቶን ሕዝቡን በማይገባው መንገድ እየነገርን አልተለወጠም ብለን በሕዝቡ እናመካኛለን (ገጽ62-63)።

ከዚህ የምንረዳው ሥነቃል ማህበረሰቡን በሚመለከት የማይዳስሰው የሕይወት ዘርፍ አለመኖሩን ነው። በመሆኑም የማንነቱ መገለጫ የሆኑትን ሥነቃል ማጥናት፤ የሚጠናውን ማህበረሰብ ባህላዊና ማህበራዊ እውቀት ፈትሾ የኑሮ መማሪያ ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ

በዘርፉ የተሰማሩ ምሑራን አባባል የማህበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት በዚህ መስክ ላይ ጥናት ማድረጉ ወሳኝነት ያለው መሆኑን ያስገነዝበናል።

ይሄንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ ንድፈ ሀሳበዊ ቲዮሪዎችን መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ከዚሁ አኳያ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.2 የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

በዚህ የንድፈ ሀሳብ ዳሰሳ ርዕስ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ቀርበዋል። እነሱም ከጥናቱ ርዕስ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው የጤና ትምህርት ቲዮሪ፣ የወሲብ ቲዮሪ እና የጥናት መተንተኛ ቲዮሪዎች በዝርዝር የቀረቡበት ነው። እነዚህ ቲዮሪዎች በዚህ ጥናት ውስጥ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን አገልግሎት ላይ ውለዋል። በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የእያንዳንዳቸውን ምንነት ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.2.1 የጤና ትምህርት ቲዮሪ

እንደሚታወቀው ጤና ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን በየእለቱ በሰዎች የሠላምታ ልውውጥ ውስጥ እንሰማለን። ጤና ከሚጠበቅበት መንገድ አንዱ ጤናን ከሚያጓድሉ ነገሮች እንዲንጠነቀቅ የሚያግዘን ትምህርት ነው።

የጤና ትምህርት ቲዮሪ ማለት ሕዝቡ ለምን የግሉን፣ የቤተሰቡንና በአጠቃላይ የማህበረሰቡን ጤና እንደሚጠብቅ መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን Bensly (2009) ይገልጻል። በማያያዝም ቲዮሪ የሌለው የጤና ትምህርት፣ መሠረት እንደሌለው ቤት መሆኑን በመግለጽ የጤና ቲዮሪን መረዳትና መተግበር ፖሊሲውን ሥራ ላይ ለማዋል ዋስትና የሚሰጥ በመሆኑ የጤና ትምህርቱ በግለሰብ ተኮር የባህርይ ለውጥ ላይ መመሥረት እንዳለበት ይገልጻል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ በማህበረሰብ ተኮር የጤና አጠባበቅ ከ20 በላይ ቲዮሪዎች መኖራቸውንና ከነዚህ ቲዮሪዎች መካከል ጥቂቶቹ ተግባራዊ የማይሆኑበት ሁኔታ ሲኖር፣ ለአዳዲስ ቲዮሪዎች መፈልሰፍ በር ከፋች መሆናቸውን በመጥቀስ ካሉት ቲዮሪዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የጤና ትምህርት ትግበራ፣ የባህርይ ለዉጥ ፣ የማህበራዊ ግንዛቤ እና የግኑኝነትና ሥርጭት ቲዮሪዎች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሆናቸውን ይዘረዝራል። በማያያዝም እነዚህ ቲዮሪዎች በሕዝቡ ግንባር ቀደም ተሳታፊነት ጤናማ

የሕይወት ዑደት ያለውን ማሕበረሰብ መፍጠር በመሆኑ ለዚህም በግለሰብ ጤና አጠባበቅ ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት Bensly (2009፡ 20-35) ያብራራል ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በዓለም ላይ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ መድሃኒት ባልተገኘበት በአሁኑ ዘመን በጤና እና በግብረሥጋ ግንኙነት መካከል ያለውን የጠበቀ ግንኙነት መፈተሽ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለደስታ እና ዘር ለመተካት ብለን በምንፈጽማቸው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ላይ ራሳችንን ከአባለዘር በሽታዎች በተለይም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመከላከል ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን Brooks & Furstenbrg (1989) ያሳስባሉ። ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር ተያያዥ በሆኑ የጤና ጉዳዮች ላይ በፓትሪክ ዲክሰን ተዘጋጅተው በተስፋዬ መስፍን በተተረጎመው "ኤድስ እና እኛ" በሚል መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ይላል።

> ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ሕመሞች ለአያሌ ሺህ ዓመታት በምድራችን ነበሩ። ሕክምና እስኪገኝለት ድረስ ቂጥኝ በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ገድሎአል። ጨብጥ አሁንም በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ከመሆኑም በላይ ቀደም ሲል ይሰጡ የነበሩ መድሃኒቶችን እየተላመደ መጥቷል። ከባድ ሕመምን የሚያስከትል የብልት ላይ ምች (herpes) ትልቅ ችግር እየፈጠረ ነው፤ ብልቱ ቁስልና ሕመም ስለሚኖረው ይህ ሕመም ያለበት ሰው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረግ በጣም ያስቸግረዋል። አንዴ ሲመጣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲሄድ የሚኖርና ለዕድሜ ልክ የሚዘልቅ ሕመም ነው። የማህፀን አፍን የሚያጠቃ ካንሰር በጣም እየተስፋፋ መጥቷል። … መካንነት ወይም ልጅ መውለድ አለመቻል የብዙ እህቶቻችን ዕጣ ፋንታ ሆኗል። ይህ ሊሆን የቻለው የሴቶች እህቶቻችን ውስጣዊ ክፍል በሚጎዱ ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው በሽታዎች ምክንያት ነው። ከእነዚህም አንዱና ዋንኛው የኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ነው። ብዙ ጊዜ ጉዳቱ እስኪደርስባት ድረስ ተጠቂዋ ችግር እንዳለባት እንኳን ላታውቅ ትችላለች (2007፡ 26)።

ከላይ የቀረበው ማስረጃ ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ልዩ ልዩ የአባለ-ዘር በሽታዎች በጤናችን ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳየን ሲሆን ጤና እና የግብረ-ስጋ ግንኙነት ተያያዥነት ያላቸው መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። በሌላ መልኩ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረግ ለአባ-ለዘር በሽታዎች በተለይም ለኤች አይ ቪ የሚያጋልጥ መሆኑን ጽሑፉ ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጡ በሽታዎች ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያጠቁ ቢሆንም በተለይ ተጋላጭ የሆኑት ሴቶች መሆናቸውን ጽሑፉ ያብራራል።

አያያዞም ኤድስ በምስጢር የሚያዝ ጉዳይ መሆኑንና እየደረሰ ያለውን ጥፋት ሲያብራራ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ምክንያት የሞተ ሰው ን በካንሰር ወይም በሌላ በሽታ መሞቱ ይነገራል እንጂ እውነተኛው ምክንያት እንደማይነገርና በዚህም የተነሳ በሽታው በድብቅ እየተስፋፋ ድምፅ አልባ ገዳይ በመሆን የሰው ልጆችን በሙሉ በማጥቃት ላይ እንደሚገኝ በመጥቀስ ኤድስ በጤናው ዘርፍ የሁላችንም ችግር መሆኑን ተስፋዬ (2007፡ 19) ያስረዳል።

ከዚህ የምንረዳው የጤና ጉዳይ ዘርፈ ብዙ ስለሆነ፣ የጤና ችግሮችን በማቃለሉ በኩል በግንባር ቀድምትነት ሁሉን አቀፍ ተሳትፎን የሚጠይቅ መሆኑን ነው። ይኸውም በሽታን ለመከላከል በተለይም ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከጤና አጠባበቅ ቲዮሪዎች ባሻገር በተለይም በሥነቃል ዓይነቶች ማህበረሰቡን ማስተማሩ ለሁሉ አቀፍ ችግር መፍትሔው የሁሉም ተሳትፎ መኖር ወሳኝ መሆኑን ማሳየት ይሆናል። ከዚሁ አንጻር ከግለሰብ ጀምሮ ድርጅቶችም በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ትኩረት ያለው ምርምር ሊያደርጉበት ይገባል።

በሕይወት ዘመናችን ለደስታ እና ራሳችንንም ለመተካት ወሲብ እንፈጽማለን። ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በተስፋፋበት በአሁኑ ዘመን በጤና በኩል የሚያመጣውን ችግር ለመከላከል የወሲብ አፈጻጸማች ጤናማ መሆን ይኖርበታል። ከዚሁ አንጻር ጤና እና ወሲብ ያለቸውን ግንኙነት የሚያሳየውን የወሲብ ቲዮሪ ምንነት ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

2.2.2 የወሲብ እና የግብረ-ስጋ ግንኙነት አንድነትና ልዩነት

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታ መተላለፊያ በዋናነት የሚጠቀሰው ወሲብን አስመልክቶ ያሉ ቲዮሪዎች በዝርዝር ቀርቧል። መጀመሪያ የወሲብ ቲዮሪ ከመቅረቡ በፊት በወሲብ እና በግብረ-ሥጋ ግንኙነት መሐካል ያላውን አንድነት እና ልዩነት ማብራራት ያስፈልጋል። ለዚህም በቅድሚያ የሁለቱንም ትርጉም ማየቱ ጠቃሚ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የአማርኛ መዝገበ-ቃላት (1993: 407) “ወሲብ(ስ) በወንድ እና በሴት መካከል የሚፈፀም ፍትወተ ስጋዊ ሥራ፣ ግብረ-ስጋ። ወሲባዊ ግንኙነት፣ የግብረ-ስጋ ግንኙነት። የወሲብ ፍላጎት፣ የግብረ-ስጋ ፍላጎት። ግብረ-ስጋ (ስ) ፍትወት፣ ሩካቤ ስጋ፣ ወሲብ።” በማለት ይተርጉማል።

የወሲብ ትርጉም አስመልክተው ከድረገፅ የተገኘ መረጃ ወሲባዊነት መሠረት የሚያደርጋቸውን አራት ነጥቦችን (ነገሮችን) እንደሚከተለው ይገልጻል። ይህም፡- ፆታዊ ማንነት ማለትም በተፈጥሮ ወንድ ወይም ሴት የመሆን መገለጫ፣ ሥርዓተ ፆታዊ ሚና

(ባህልን መሠረት ያደረገ ለምሳሌ በአንዳንድ ባህሎች ወንድ ኃይለኛ ሴት ተለማማጭ እንዲሆን/ እንዲትሆን መጠበቅ)፤ ወሲባዊነት ማለትም ስሜታዊ እና አካላዊ የክስተት ግንኙነቶችን ማለትም በተመሳሳይ ፆታ፣ በተቃራኒ ፆታ ወይም ከሁለቱም ጋር ከሚደረግ የወሲብ አፈጻጸም ጋር የሚያያዝ እና በአጋሮች መካከል የሚኖር ትስስር ወይም ትውውቅ በመሳሰሉት እንደሚገለጽ WWW.k4health.org.09/15/2015 ያብራራል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ከሌላ ድረገጽ የተገኘ መረጃ ደግሞ ሰዎች ወሲባዊነትን በተለያዩ መንገዶች ማለትም ባላቸው አካላዊ አቋም፣ በአለባበስ፣ ለራሳቸው ባላቸው አስተሳሰብ፣ በሌሎች ዘንድ በሚኖር አመለካከት ወዘተ... ሊተረጉሙት ወይም ሊገልፁት እንደሚችሉ ይጠቅስና ያለግብረ-ስጋ ግንኙነት እርካታን ማግኛ መንገዶች ለምሳሌ ከንፈር ለከንፈር መሳሳም፣ ተጠጋግቶ ማውራት፣ ስጦታ መስጠት፣ የፍቅር ደብዳቤ (ግጥም) መፃፍ፣ ሙዚቃ ማዳመጥ፤ በመሳሰሉት ወሲባዊነት እንደሚገለፅ http://www.google.09/15/2015 ያስረዳል።

የግብረ-ስጋ ግንኙነት ወይም ሩካቤ ስጋ ትርጉም በተመለከተ በሴትና በወንድ መካከል ለስሜት እርካታ የሚደረግ ግንኙነት ወይም ፍቅር መሥራት ሲሆን በዚሁ ሂደት ዘር ለመተካትም የሚደረግ ነው (https://am.m.wikipedia.org>wiki April 19,2014)።

ከዚህ የምንረዳው ወሲብ እና የግብረ-ስጋ[20] ግንኙነቶችን የሚያመሳስላቸው በወንድ እና ሴት መካካል በሚኖር ሩካቤ ስጋ ግንኙነት ነው። በሁለቱ ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ወሲብ ከሩካቤ ስጋ ግንኙነት ውጭም ያሉትን ፆታዊ ግንኙነቶችን ያካትታል። ይህ ማለት ከላይ የወሲብ ትርጉም ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ውጭ ያሉትን የእርካታ ማግኛ መንገዶችንም የሚያጠቃልል ነው።

በመሆኑም ይህ ጥናት ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ውጭ ያሉትን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን ለምሳሌ ከንፈር ወዳጅንም የሚያካትት ነው። ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ ሁለቱም ቃላት አገልግሎት ላይ ውለዋል። ይሁን እንጂ ከጥናቱ ዓለማ አኳያ ሰፊ ትርጉም ያለው ወሲብ በመሆኑ ለመረጃዎች መተንተኛነት ሥራ ላይ የዋለው የወሲብ ቲዮሪ ነው። ስለዚህ የዚህን ቲዮሪ ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

[20] በዚህ ጥናት ውስጥ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማለት በወንድ ብልት እና በሴት ብልት የሚፈጸመውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ብቻ የሚመለከት ነው። ወሲባዊ ግንኙነት ማለት ደግሞ በተቃራኒ ፆታ መካካል ያለ ግብረ-ስጋ ግንኙነት ወሲባዊ እርካታ ማግኛ መንገዶችን ለምሳሌ መተሻሸትን፣ ከንፈር ለከንፈር መሳሳምን እና ልዩ ልዩ የፍቅር ስሜት መግለጫዎችን የሚያካትት ነው።

2.2.3 የወሲብ ቲዮሪ

በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የወሲብ አፈጻጸም እንደ ማህበረሰቡ ባህላዊ ሁኔታዎች የሚገለጽ ነው (O'neill፡ 1972)። ይህ ማለት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አስነዋሪ የሆነ የወሲብ አፈጻጸም ባህል በሌላኛው ማህበረሰብ ደግሞ ተቀባይነት ያለውና የሚሞገስ ሊሆን ይችላል። ይህ እንዳለ ሆኖ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ከነባሩ ባህል ውጭ በሚመጡት ተፅዕኖ ከማህበረሰቡ ባህል ያፈነገጡ ተግባራት በግለሰብ ደረጃ ይፈጸማል። ለዚህም ወሲብ ላይ ያተኮሩ ፊልሞች በወጣቶች ወሲብ አፈጻጸም ላይ ለውጥ አስከትለዋል (O'neill, 1972፡ 248)።

ከዚህ የምንረዳው እያንዳንዱ ማህበረሰብ ወሲብን የሚፈጽምባቸው ባህላዊ ሁኔታዎች ያሉ ቢሆኑም አልፎ አልፎ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከባህሉ ውጭ በሚፈጠሩት ተፅዕኖ ከማህበረሰቡ ባህል ወግና ሥርዓት ውጭ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ተግባራት መኖራቸውን ነው።

ወሲብ የሚፈጸመው የማህበረሰቡን ባህል መሠረት በማድረግ የሚከናወን ቢሆንም በወሲብ ላይ የግለሰብ ወሲባዊ ባህርይ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው (Flemming, 1997)። በተለይም በወጣትነት ዘመን የሚፈጸም ወሲብ በአብዛኛው ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ ስለሚከናወን በርካታ ወጣቶች ለኤች አይ ቪ እንደሚጋለጡ (Kachingwe et al, 2005) ይገልጻሉ።

መሠረታዊ የወሲብ ቲዮሪ እንደሚያመለክተው፣ የሁሉም ፍጥረታት የወሲብ ባህሪይ ወሲባዊ እርካታ ማግኘት እና ዘርን ለመተካት (ለመራባት) ነው። በመሆኑም በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚገኝ የሰው ልጅ በአብዛኛው ከወሲብ ውጭ አይደለም። ይሁን እንጂ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ለወሲብ የሚሰጡት ትርጉም እንደየባህላቸው የተለያየ ነው (Ember and Ember, 2003) ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወሲብ ተፈጥሯዊ መሆኑን እና ማህበራዊ ሚና እንዳለው ከወቅት ጋር በማያያዝ ጥላሁን ተሊላ (2007) እንደሚከተለው ገልጿል።

> *ጾታ ነክ ጉዳዮች ተፈጥሯዊ በመሆናቸው በየትኛውም ማሕበረሰብ ሊኖሩ የሚችሉ ናቸው። ነባር ወይም ተፈጥሯዊ የሆነው አካላዊ ተራክቦ እንደሆነው ሁሉ ከጾታ ጋር ተያይዞ የሚሰጡ ማሕበራዊ ሚናዎች አሉ። ሚናዎቹ በአለባበስ፣ በሥራ ድርሻ፣ በተሳትፎ፣ በስነልቦና እና ሌሎችም በዚያው ማሕበረሰብ ይታወቃሉ። ሆኖም ማሕበራዊ ሚናውን ጥሰው ከተሰጣቸው ገደብ የሚወጡባቸው፣ በተቃራኒ የሚቆሙባቸው፣ "አይጠሬ/ አይነገሬ" የሆኑ የጾታ ነክ ስያሜና ድርጊት እንደ ዘወትር ሰላምታ መለዋወጫ ቃላት ለአፍ የማይከብዱባቸው አጋጣሚዎች በሊሚናል ወቅት ይፈጠራል። በውዳሴም ይሁን በተግሳፅ ከወቅቱ ጋር ተያይዞ የጾታ ጉዳይ*

> በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊጠቀስ እንደሚችል ይስተዋላል። በአብዛኛው ባለጉዳዩ (Liminal Being) በሁሉም የከበራ ወቅቶች ከጾታዊ ግንኙነት የሚከለከል ይመስላል። በጉዳዩ ውስጥ እራሳቸውን አስቀምጠው የሚሳተፉት ግን በአንፃሩ የጾታዊ ግንኙነት ነክ አገላለፆችን፣ ዘፈኖችን ፣ ተረኮችን፣ ለምናልባትም በተምሳሌታዊ መልክም ይሁን፣ በምናባዊ ወይም በተግባር ለመፈፀም ካለገደብ የሚፈቀድለት መስሎም ይታያል (ገጽ 19)።

እዚህ ላይ ከጾታዊ ግንኙነት ነክ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ በዘወትር ተግባር ውስጥ በገሃድ የማይባሉ ጉዳዮች በግልፅ የሚባሉበት በማህበረሰቡ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ወቅት በዘፈን የሚገለጸውን የሚያሳይ ነው። ይህም በዘወትር ተግባር ውስጥ በገሃድ የማይባለውን አይጠሬ ወይም አይነገሬ የፆታ ነክ ስያሜን በከበራ ወቅት ወጣቶች በግልጽ ይዘፍኑበታል። አዋቂዎችም በተረት አይጠሬውን ስም ለመጥራት አያፍሩም። ከዚህ የምንገነዘበው ምንም እንኳን በመደበኛ ንግግር ወቅት ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ቃላት መጠቀም አስነዋሪ ቢሆኑም በሥነቃል መፈቀዱ ማህበረሰቡ ወሲብን በሚመለከት የሚወስንባቸው ባህላዊ ሁኔታዎች ያሉ መሆናቸውን ነው።

ወሲብ ተፈጥሯዊና ከሥነልቦና ብስለት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጉዳይ ነው። ከማህበራዊ መዋቅር ቲዮሪም አንጻር ሲታይ አንድ ግለሰብ የወሲብን ልምድ የሚማረው ከማህበረሰቡ ነው። ይህንን በሚመለከት የአንድን ጎልማሳ ወሲባዊ ባህርይ ለመረዳት ማህበራዊ መዋቅርን የማወቅ አስፈላጊነት በመጥቀስ ከተለያዩ ቲዮሪዎች አኳያ Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006) ይዘረዝራሉ። ከዘረዘሯቸው ቲዮሪዎች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሚከተሉት ናቸው። ስለሆነም ለዚህ ጥናትና ምርምር አጋዥ በመሆናቸው ተግባራቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የመሠረታዊ ፍላጎት ቲዮሪ፡- የዚህ ቲዮሪ ዋና ትኩረት ወሲብ ለሰው ልጅ ከመሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ መሆኑን የሚገልጽ ነው። የሰው ልጅ ወሲባዊ ብቃት የሚረጋገጠው በአካላዊ እድገቱና በወሲባዊ አዝግሞተ ለውጥ ውስጥ ሲሆን ወሲባዊ ባህርይ የግለሰብ ደስታን ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን ዝርያን የመቀጠል ተፈጥሯዊ ግዴታ መሆኑን የErikson (1959, 1963, 1968) ሥራ ዋቢ በማድረግ በወሲብ ውስጥ የመሠረታዊ ፍላጎት ቲዮሪ ጠቀሜታ Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006፡ 38-44) አብራርተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሰው ልጅ ወሲባዊ ፍላጎት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ የሚመጣ እና በማህበረሰቡ ባህል መሠረት የሚፈጸም መሆኑን Kantor (1999) ይገልጻል። ይህንኑ አስመልክቶ (Wolf, 1962: 175) ልጆች ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ

ወሲብን እየተለማመዱ እንደሚያድጉ ሲያስረዳ ጡትና ጣት መጥባት በወሲብ ተግባራት ውስጥ እንደሚመደቡና እያደጉም ሲሄዱ ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎችን እንደሚያነሱ ለዚህም በቤተሰብ ደረጃ ለጠየቁት ጥያቄ በቂ መልስ ካላገኙ ጉዳዩን የማወቅ ጉጉታቸው እየጨመረ እንደሚሄድና ወደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደምሻጋገሩም ያብራራል።

የእነዚህ ምሁራን ጥናቶች የሚያሳዩን የወሲባዊ ዝንባሌ ልምዳችን ቅርጽ የሚይዘው ከሚንኖርበት ማህበረሰብ አስተሳሰብ የሚመነጭ መሆኑን ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት አንድ ግለሰብ ወሲብ የሚፈጽመው ያለበትን ማህበረሰብ ባህል ተከትሎ ነው። በመሆኑም ወሲብን አስመልክተው የሚነገሩና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ከዚህ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። ይህም ማለት ወሲብን በሚመለከት ያሉትን ባህላዊ ሁኔታዎች እና ከባህሉ ያፈነገጡ ወሲባዊ ድርጊቶችም ጭምር የሥነቃል ዓይነቶቹ ምን ያህል ግልጽ እንደሚያደርጉአቸው የሚታይበት ነው።

ማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ፡- ይህ ቲዮሪ የሰው ልጅ ወሲባዊ ባህርይን ከማህበረሰቡ የሚማር መሆኑንና ይህንንም በቋንቋ አማካይነት እንደሚገለጽና ሁሉም ማህበረሰብ ባህሉን፣ ወጉን፣ እምነቱን፣ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን መሠረት የሚያደርግ የራሱ የሆነ የወሲብ አፈጻጸም ባህርይ እንዳለው (Banks and Banks (2001) ያብራራሉ። ይህም የሚያሳየን ወሲባዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የማህበረሰቡ ባህል ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ነው።

ወሲብን በሚመለከት ወንድና ሴት በማህበረሰቡ ውስጥ ማሳየት የሚገባቸው ወሲባዊ ባህሪያት አምስት የእድገት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነሱም 1) ፆታዊ የነገሮች ግንኙነት 2) ፆታዊ ማንነት 3) የፆታ ሚና 4) ወሲባዊ ችሎታን፣ እውቀትና ወግ መውረስ 5) በአውዱ ውስጥ ወሲባዊ ተሳትፎ መሆናቸውን በመጥቀስ የማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ ውስጥ የማህበረሰቡ ባህል በወሲብ አፈጻጸም ባህሪይ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው (Susan Moore & Doreen Rosenthal, 2006፡ 44-58) ያስረዳሉ።

ይህም ስለ ወሲብ በግልጽ የሚባለው (የሚነገረው) በማህበረሰቡ ቋንቋ በሥነቃል ዓይነቶች (በዘፈን፣ በቀልድ፣ በምሳሌያዊ ንግግር እና በተረት … ወዘተ) አማካይነት ነው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ወይም የባህሉን ድክመት በማሳየት እንዲሁም ከባህሉ ያፈነገጡትን በማውገዝ በኩል ከፍተኛ ሚና አላቸው (Olson, 2000)።

በተለይም የፍቅር ዘፈኖች የወሲብን ፍላጎት በማነሳሳት ከፍተኛ ጉልበት እንዳላቸው Legman (1990) ይገልጻል።

ከላይ በዘርፉ ምሑራን እንደተገለጸው በዚህ ቲዮሪ በዋናነት የሚታየው የቋንቋ ሚና ነው። የወሲብ ፍላጎት ከሚገለጽበት መንገድ አንዱ ሁለቱ የፍቅር (ወሲብ) ተፈላላጊዎች በፍቅር ዘፈን አማካይነት ስሜታቸዉን መግለጽ ነው። ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚዘፈኑ የፍቅር ዘፈኖች ስሜት ገላጭ በሆነ ቋንቋ በሚገጠሙ ግጥሞች ነው። ስለዚህ በዚህ ቲዮሪ መሠረት የፍቅር ዘፈኖቹ ወሲብን በመቀስቀስ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ወይም ባህላዊም ሆነ ከባህሉ ያፈነገጡ ወሲባዊ ድርጊቶችን በማውገዝ ከቫይረሱ በመከላከል ረገድ ያላቸው ሚና የሚገለጽበትና ትንታኔያቸውም ከዚሁ አንጻር የሚታይ ነው።

የሥነልቦናዊ ወሲባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቲዮሪ፡- ይህ ቲዮሪ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው ከጤና ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ጉዳዮች ላይ ነው። ከጤና ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለደስታ እና ዘር ለመተካት የሚፈጸም ወሲብ በተለይም ኤች አይ ቪ/ኤድስ በዓለም ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ጭንቀት እና ጥበት እየፈጠረ ነው። በዚህም የተነሳ በወሲብ ዙሪያ የሰው ልጅ የተዘበራረቀ አስተሳሰብ ለማስተናገድ መገደዱን Brooks and Furstenbrg (1989: 251); Flemming (1997) እና Kachingwe et al (2005:197) ይገልጻሉ። ይህም የሚያሳየን ወሲብ ለመፈጸም የበሽታው መኖር ጭንቀትን ሲፈጥርበት ወሲብን እንዳይተው የሰው ልጅ አመጣጡም ከዚያው በመሆኑ ለምርጫ አስቸጋሪ እንደሆነበት እንገነዘባለን።

በሥነልቦናዊ ቲዮሪ ውስጥ ወሲብ በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ የሚፈጠር ነው። ይህም አስተሳሰብ ከመወለድ ጀምሮ እስከ እለተ ሞት ድረስ የሚዘልቅ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህርይና የማንነት መገለጫ ነው። በጎልማሳነት ዘመን የወሲባዊ ሥነልቦና ተፅዕኖ የጎላ መሆኑን የSigmund Frued (1924,1935, 1950, 1953) ሥራዎችን በመጥቀስ ከሥነልቦና ይልቅ የባህላዊ ጉዳዮች ተፅዕኖ የበለጠ ሚና እንዳለው Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006) ይዘረዝራሉ።

በዚሁ መሠረት የሥነልቦናዊ ወሲባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቲዮሪ በሦስት ሞዴሎች የሚገለጹ ናቸው። እነሱም በጤና የማመን ሞዴል፣ ምክንያታዊ ትግበራ ሞዴልና የኤድስ አደጋ ቅነሳ ሞዴል ናቸው። እነዚህ ሞዴሎች በወሲብ ሰበብ በሚከሰቱ ያልተፈለገ እርግዝናና የጤና ችግሮችን ለመካላከል ጥንቃቄ ያለው ወሲብ መፈጸምን ይመለከታሉ። በተለይም እስካሁን

ድረስ መድኃኒት ያልተገኘለትን የኤድስ አደጋ ለመቀነስ ሦስት ወሳኝ ደረጃዎች ማለትም 1ኛ) በኤድስ መጠቃት መኖሩን መረዳት 2ኛ) ዝግጁነት (በኮንደም መጠቀም) 3ኛ) ኤድስን ለመከላከል በሁለቱ ተጓዳኞች ዘንድ ጥንቃቄ ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ መኖር አለበት (Susan Moore & Doreen Rosenthal 2006, 58-65)።

ከወሲብ ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ በዚህ ጥናት ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚነገሩና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ከሥነልቦናዊ ዝግጅት አኳያ የሚያስተላልፉት መልዕክቶች በሽታውን በማባባስ ወይም በመቀነስ ረገድ ያላቸው ሚና በዚህ ቲዮሪ ተቃኝተዋል።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የወሲብ ቲዮሪዎችና ሞዴሎች በዚህ ጥናት ውስጥ አስፈላጊ ናቸው። በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚንጸባረቁትን ውስብስብ የወሲብ ተግባራት ለመግለጽ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ የወሲብ ቲዮሪዎች በጋራ እና በተናጠል ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎችን ለመተንተን አገልግለዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እነዚህ መረጃዎች ከንድፈ ሀሳብ ቲዮሪዎች አኳያም ተተንትነዋል። በመሆኑም የቲዮሪዎቹን ምንነት እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.2.4 የመረጃ መተንተኛ ቲዮሪዎች

በፍክሎር ጥናት መረጃዎችን ከመሰብሰብ እስከ መጨረሻው የጥናቱ ውጤት ማጠናቀሪያ ድረስ በተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ያልፋል። ከዚሁ አንጻር በፎክሎር የመስክ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሁለት ደረጃዎች ይገለጻሉ። እነሱም፡- መረጃዎችን መለየት፣ መመደብና መተርጎም ናቸው (Dundes, 1980: 211)። ይህም ትርጓሜ (ትንታኔ) ከዘዴዎቹ ጋር ተስማሚ ከሆኑ ቲዮሪዎች አንጻር መሆን አለበት። በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየፈርጁ ተደራጅተው ተስማሚ ከሆኑ ቲዮሪዎች አኳያ መተንተን እንዳለባቸው Marshal & Rossman (2006:156) እና Creswell (2007:161) ይገልጻሉ።

በአንድ ጥናት ውስጥ ከመስክ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተለይተው ለአንባቢ ግልጽ የሆነ ትርጉም እንዲሰጡ በልዩ ልዩ ቲዮሪዎች መተንተን እንደለባቸው በጥናትና ምርምር ስልቶች ላይ የጻፉ ምሁራን እነ Dundes (1980); Marsha and Rossman (2006) እና Creswell (2007) ይገልጻሉ። ከዚሁ አንጻር ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ የመተንተኛ ቲዮሪዎች ተዳሰዋል።

በዚሁ መሠረት በልዩ ልዩ መንገዶች የተሰበሰቡት የሥነቃል መረጃዎች በዓይነታቸዉና በይዘታቸው ተለይተው ተደራጅቷል። ይሁን እንጂ በየርዕሳቸው ተለይተው የተደራጁ መረጃዎች በራሳቸዉ ገላጭ አይደሉም። በመሆኑም ምንነታቸውን፣ ቅንብራቸውንና አከዋወናቸዉን በማብራራት ፋይዳቸውንና ያላቸውን ትርጉም ከተለያዩ ቲዮሪዎች አኳያ መተንተን አለባቸው።

በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የሚንመለከተው ሥነቃልን ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ለመተንተን ከተለያዩ ምሁራን የተገኙ ንድፈ ሀሳቦች (ቲዮሪዎች) ለዚህ ስራ ጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት የቀረቡበት ነው።

እነዚህ ቲዮሪዎች በቁጥር በርከት ያሉ ቢሆኑም ባሏቸው የጋራ ጉዳዮች አንዱ በሌላኛው ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። ሥነቃል በርካታ ጉዳዮችን ስለሚዳስስ እነዚህን ቲዮሪዎች መነካካቱ አይቀርም። በሌላ መልኩ የአንዱ ቲዮሪ ድክመት በሌላኛው ጥንካሬ ሊሸፈን ስለሚችል መረጃዎችን ለመተንተን ሁሉንም እንደየአስፈላጊነታቸው መጠቀሙ የግድ ይሆናል።

በዚህ መሰረት ልዩ ልዩ የቲዮሪ ምንጮች የተዳሰሱ ሲሆን በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ እውቀቶችም ላይ ትኩረት ተደርጓል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ከእነዚሁ ቲዮሪዎች አንጻር ታይተዋል። ይህም በሥነቃል አቀራረብ አድማጭ ተመልካቹ ከሰጠው ግብረ መልስ አኳያ፣ እንዲሁም ማህበረሰቡ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቱ እና ኤች አይቪ/ኤድስ ካለው አመለካከት አንጻር የተተነተነበት መንገድ ነው። ሌላው ሥነቃሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያና ሥነቃሉን ወደ ቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍና ጠብቆ ከማቆየት አንጻር የተገለጸበት ነው። በፎክሎራዊ እውቀት ላይ ያተኩረው እይታ ደግሞ ማህበረሰቡ ለሥነቃሉ የሰጠውን አገር በቀል ትርጉማቸውን መሠረት ያደረገ ትንተና ነው። ስለዚህም የተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎች የተተነተኑት ቀደም ሲል የተገለጹ የጤናና ወሲብ ቲዮሪዎች እና ቀጥለው የተዘረዘሩ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች በተናጠል፣ እንደ አስፈላግነታቸውም በጋራ ተቀናጅተው ተግባራዊ ሆነዋል።

በዚሁ መሠረት ዓውዳዊ ቲዮሪ (Contextual theory)፣ ክዋኔ ቲዮሪ (Performance TheorY)፣ ተግባራዊ/ፋይዳዊ ቲዮሪ (Functional theory)፣ ተምሳሌታዊ ቲዮሪ (Symbolic theory)፣ ክልላዊ ቲዮሪ (Hemispheric theory)፣ የፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪ

(Pschoanalytical Folklore Theory)፣ የማሕበረሰብ እውቀት አዋቃሪያን ቲዮሪ (Social Construction of Reality theory) እና ለውጥና ቀጣይነት (Change and Continuity theory) በዚህ ጥናት ውስጥ እንዳስፈላጊነታቸው የመረጃዎች መተንተኛ ቲዮሪዎች በመሆን አገልግለዋል።

እነዚህ ቲዮሪዎች ምንም እንኳን በቁጥር ስንመለከታቸው በርካታ ቢሆኑም አንዱ ከአንዱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በመሆኑ በትንታኔ ወቅት የአንዱ ቲዮሪ ሀሳብ ሲነሳ የሌላኛውም ሀሳብ የግድ ይቀርባል። በተለይም ሥነቃል ሁለገብ በመሆኑ የማህበረሰቡን ባህል ከተለያዩ ጉዳዮዎች (ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ) አንጻር ይዳስሳል። ስለሆነም ሥነቃል ሲጠና ትንታኔዎቹን ከተለያዩ አቅጣቾዎች ማየት የግድ ይሆናል።

ለምሳሌ አንድ ሥነቃል በአውዳዊ ቲዮሪ የሚተነተን ከሆነ የክዋኔ ቲዮሪ የግድ መነሳቱ አይቀርም። ምክንያቱም ያለ ክዋኔ ብቻውን የሚኖር አውድ የለምና። በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሥነቃል ክልላዊ ቲዮሪ የሚመለከት ቢሆንና በዚህ ቲዮሪ ቢተነተን የቀጣይነትና ለውጥ ቲዮሪ የግድ መነሳቱ አይቀርም። ሌሎችም እንደዚሁ በትንታኔ ወቅት የግድ የሚጣመሩ አሉ። እያንዳንዱ ቲዮሪ ደግሞ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያንጸባርቃል። ትንታኔዎቹን በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ሥር በስፋት እንመለከተዋለን። ለዚሁ

ግንዛቤ እንዲረዳን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የእያንዳንዱን ቲዮሪ ምንነት እና አፈጻጸም ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን።

አውዳዊ ቲዮሪ፡- የዚህ ቲዮሪ አቀንቃኞች (Bascom 1954 እና Ben Amos 1993) ዋነኛ ትኩረት አንድ ፎክሎር ዘውግ የተከናወነበትን አውድ ማጉላት ነው። ቀደምት የBascom (1954) እሳቤዎችን መሰረት በማድረግ ምሁራን እንዳመለከቱት ማንኛውም ክዋኔ ሲተነተን የክዋኔው ዓውድ መገለጽ አለበት (Okpewho 1992:10፤ Ben Amos 1993:1፤ ፈቃደ 1991:37)። Jackson (1986፡4) ዓውድ በስነ ሰብ (Anthropology) ጥናት ውስጥ ላሉ ሁሉም ተመራማሪዎች ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ለሁሉም ግን ዓውድ ወሳኝ እና በተመሳሳይ መንገድ የሚያገለግል አይደለም። እንደዚሁም Sims and Stephens (2005፡137) ዓውድ የፎክሎር አንድ ቅንጣት የሚከወንበት ውስን ማህበራዊ ሁነት መሆኑን ገልጿል።

ስለዚህ የፎክሎር ጥናትና ምርምር አውድን መሠረት ያደረገ ነው ሲባል በተለይም የሥነቃል መረጃዎች ሲሰበሰቡ የሥነቃሉ ዓይነት (ምሳሌያዊ ንግግር፣ ቀልድ ተረት ዘፈን ወዘተ ... (Text)፣ የዓይነቱ ውስጣዊ ሁኔታ ወይም የቋንቋው ትርጉም (Texture) እና ሥነቃሉ የተነገረበት (የተከወነበት) አውድ (Context) ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (Dundes, 1980:20-32; Ben-Amos, 1993:210)።

ከዚሁ አንጻር የዓውዳዊ ቲዮሪ ዋና ትኩረት ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ ሁሉን አቀፍ መረጃዎች ከባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች አኳያ የከዋኙን አከዋወን ሁኔታ ከጊዜና ቦታ አንጻር የሚገለጽበት መንገድ ነው (Dorson, 1972)። በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በስፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ቲዮሪዎችና ዘዴዎችን የሚመለከት መሆኑን Ben-Amos (2006) እና Goldstein (2004) ይገልጻሉ። ይህም ተናጋሪው ሥነቃሉን በሚናገርበት ጊዜ የአቀራራብ ሁኔታ፣ የሚከውኗቸውን ድርጊቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴና የከዋኙን ልዩ ችሎታ፣ እንዲሁም የአድማጭ ተመልካቹን ግብረመልስና ስሜት የሚመለከት በአጠቃላይ በሰዎች የርስ በእርስ ግንኙነት ውስጥ የሚታዩ ጥበባዊ መገለጫዎች መሆኑን Bauman (1977) ያብራራል። በማያያዝ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን የሚያካትት መሆኑን Ben-Amos (1993፡ 210-211) ያስረዳል።

ይህንኑ በማጠናከር አውድን ከሥነቃል አንጻር ሲገልጽ ከሦስት ቁልፍ ጉዳዮች ማለትም ከከዋኙ ስብእና፣ ከመከወኛው ድባብ፣ ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ አኳያ ይመለከታል (Okepewho, 1992: 105)። እንደ እርሱ አገላለጽ የከዋኙ ስብእና የሚላቸው ግለሰቡ ይዞት የሚቀርበውን ማንኛውንም ነገር የሚያመለክት ሲሆን እነዚህም ኪናዊ ዝንባሌውን፣ ቤተሰባዊ ዳራውን፣ ግላዊ ተመክሮዎቹን እና የተከታተላቸውን ሥልጠናዎች የሚመለከቱ ናቸው። የክዋኔው ድባብ ማለት ከከዋኙ አንደበት የሚወጡትን ቴክስቶች (የሥነቃል ዓይነቶች)፣ ቴክስቱን ለመግለጽ የተጠቀማቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ከዋኙን ከበው ያሉ ታዳሚዎችና ተጽዕኗቸውን እንዲሁም በከዋኙ ስኬት ወይም ውድቀት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ያካትታል።

ባህላዊ ዓውድ፡- ባህላዊ ዓውድ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔን ከሶስት ገጽታዎች አኳያ መመልከት ማለት ነው። እነርሱም ትዕምርታዊ ትርጉም፣ ባህላዊ ተቋም ትርጉምና

የተግባቦት ሥርዓት ደንቦች ናቸው።ይህ ማለት በባህላዊ ዓውድ ውስጥ ከሚካተቱት ገፅታዎች አንዱ የባህላዊ ክዋኔው "ትዕምርታዊ ትርጉም" ነው። የባህላዊ ዓውድ ትንተና የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ትዕምርታዊ ትርጉም ምን እንደሆነ ይገልጻል። ሁለተኛው የባህላዊ ዓውድ ገጽታ "የባህላዊ ተቋም ትርጉም" ሲሆን የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ባህላዊ ተቋማትና ባህላዊ መዋቅር ውስጥ ያላቸው እሴትና ስምረት ምን እንደሆነ ማብራራት ማለት ነው። ሦስተኛው የባህላዊ ዓውድ ገጽታ ደግሞ "የተግባቦት ሥርዓት ደንቦች" መሆናቸውን Bauman (1977); Okepewho (1992) እና Ben -Amos (1993) ይገልጻሉ። በመሆኑም ዓውድን መሠረት አድርጎ የተካሔደው የዚህ ጥናት ትንተና ዋናው ጉዳይ የሥነቃል ዓይነቶቹ እንዴት የመግባቢያ ሥርዓትና ስልት ሆነው እንደሚያገለግሉና እንዴት ከሌሎች የፎክሎር ቅንጣቶች ጋር እንደሚዛመዱ ማሳየት ነው።

ማህበራዊ ዓውድ፡- እነዚሁ ምሁራን ማህበራዊ ዓውድ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔን ከሦስት ገፅታዎች አኳያ መተንተን ማለት መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያው የሥነቃል ዓይነቶቹ ከግለሰብ ህይወትና የኑሮ መሰረት ጋር የሚገናኙበትን መንገድ ሆኖ ይህም በውስጥ የተካተቱ ኢኮኖሚን፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው። ሁለተኛው የማህበራዊ ዓውድ ገፅታ የሥነቃል ዓይነቶቹ ባለቤት ማን እንደሆነ መለየትና ይህም እድሜን፣ ጾታን፣ አከባቢን፣ የኑሮ ደረጃን ወዘተ.. መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ክፍፍል ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ የሚብራራበት ነው። ሦስተኛው የማህበራዊ ዓውድ ገፅታ ወቅታዊ ሁኔታ ሲሆን ይህም ማህበረረሰቡ አሁን በዚህ ዘመን የሚገኝበት ማህበራዊ ሁኔታ የሚመለከት እና ዘመኑን ተከትለው በሚከሰቱ ተለዋዋጭ ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ የሥነቃል ዓይነቶች ክዋኔ ማህበራዊ ፋይዳ ከዘመኑ ፍላጎት አንጻር ያለበት ሁኔታ የሚተነተንበት ነው (Bauman, 1977; Okepewho, 1992; Ben-Amos, 1993)።

በዚህ ጥናት ውስጥ የሥነቃል መረጃዎቹ ከላይ የተዘረዘሩትን ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታዎችን መሰረት በማድረግ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በማህበረሰቡ ባህላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ካሳደረው አውንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ አኳያ የተተነተኑ ናቸው። ከዚሁ አንጻር ይህ ቲዮሪ ለዚህ ጥናት በዋናነት የመረጃዎች መሰብሰቢያ ዘዴና የተሰበሰቡትን መረጃዎችም መተንተኛ ሆኖ አገልግሏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የክዋኔ ቲዮሪን ዝርዝር አፈጻጸም ከዚህ በመቀጠል እናያለን።

የክዋኔ ቲዮሪ፡- ፎክሎርን ለሚያጠና ሰው ክዋኔን መመልከት ማለት ሰዎች አንድን ድርጊት እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ እንደሚለዋወጡ እና ከድርጊቱ መልእክት ጋር እንዴት እንደሚተዋወቁ መገንዘብ ማለት ነው። የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ለማጥናት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ እና የሚከተሉት እንደሆኑ Bauman, (1992፡ 5) በአርትኦቱ ውስጥ ጠቁመዋል። የመጀመሪያው ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያከናውነው ተስማምቶ ባዋቀረው ስርዓትና ደንብ መሰረት በመሆኑ ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል ሊኖረው እንደሚችል የሚያመለክት ሀሳብ ሲኖረው፣ ሁለተኛው ደግሞ ከዋኙ በተሳታፊዎች ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀመው ቋንቋ፣ የአነጋገር ለዛ እና የአከዋወን ሂደት የሚያመለክት ሀሳብ አለው።

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ አቀራረብ በሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች እንዲሁም እንደ ከዋኙና ተሳታፊው አቅም ይለያያል። በዚህ ምክንያት መልዕክቱም ስለሚለያይ የክዋኔው ደረጃ በሚቀርብበት አጋጣሚ ይወሰናል። በሌላ በኩል የከዋኙና የተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፤ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት ወቅትና ጊዜ እንዲሁም የፎክሎራዊ ጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥና የአቀራረብ ስልት ሁሉ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ በመሆናቸው ለሚከወኑበት አጋጣሚ የሚመጥኑ ሆነው መቅረብ አለባቸው።

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ማህበራዊ ዓውዶችና ግንኙነቶች እየሰፋ በመምጣቱ፤ የከዋኞችንና የታዳሚዎችን ሚና የክዋኔው ፋይዳና የሰው ልጅ የህይወት ተሞክሮዎች እንዴት እርስ በርስ እንደሚደጋገፉ ይመረምራል። ስለዚህ ክዋኔ ሰዎች አንድን ፎክሎር ቅንጣት የሚፈጥሩበት፣ የሚጋሩበትና ከቅንጣቱ ጋር የሚዛመዱበት ስልት በመሆኑ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ህይወትና ከትርጉም የሚነጠል ጉዳይ አይደለም። ክዋኔም በሥነቃል ውስጥ ሁሉም የጥበቡ አላባውያንን ያማክላል (Finnegan 1992)። ክዋኔ ድርጊት ነው። <u>ፎክሎር (ሥነቃል) ህልውና የሚኖረው ሲከወን ብቻ ነው።</u> (ሰረዝ ከራሴ ነው)። ፎክሎር ከዋኞችንና ታዳሚዎችን የሚያካትትና በክዋኔ ውስጥ ያለው የፉክክር ጉዳይም መመዝገብና መተንተን ያለበት ባህርይ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል (Dundes 2005፡389፤ Sims and Stephens 2005፡128)።

በመሆኑም በዚህ ጥናት የክዋኔ ቲዮሪ የሥነቃል ዓይነቶችን ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ከተመረጡ ቲዮሪዎች አንዱ ሲሆን አውዳዊ ትንታኔዎች በሚደረግበት ወቅት በዚህ ቲዮሪ

የተደገፈ ማብራሪያ ታክሎበታል። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የሚገለጹ ፋይዳዎች ይኖራሉ። ከዚህ አንጻር ቀጥሎ የተግባራዊ/ፋይዳዊ ቲዮሪን ንድፈ ሀሳብ እንመለከታለን።

ተግባራዊ/ፋይዳዊ ቲዮሪ፡- ይህ የሚገለጸው በማህበራዊ ህይወትና በስነ-ተፈጥሯዊ ህይወት ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት በማነፃፀር ነው። የአንድ ፍጡር መላ አካላት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ተደምረው ፍጡሩን ሙሉና ህያው የሚያደርጉት ከሆነ የየፎክሎር ክዋኔዎችም ተደምረው የከዋኙን ማህበረሰብ ህልውና ሙሉ የሚያደርጉ ተግባራዊ ፋይዳዎች አሏቸው (Radcliffe-Brown 1935: 394-397)። ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው Bascom (1954፡344-346) ያስረዳል። ከዚያም በላይ የተግባራዊ ቲዮሪ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል። ተግባራዊ ቲዮሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል (Okpewho (1992:173)። እዚህ ላይ ማንኛውንም የሚለው አባባል ተግባራዊ ቲዮሪ በማህበረሰቡ ውስጥ በግንባታ ሚና ብቻ ሳይሆን በአፍራሽ ሚናም የሚገለጽ መሆኑን ነው። የፎክሎር ተግባር የማህበረሰቡን ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ በማሸጋገር ሚና እንዳለው ሁሉ በተቃራኒም ያለውን አፍራሽ ገጽታ በሚመለከት ከድረገጽ የተገኘ የBascom (1954) ሥራ እንደሚከተለው ተገልጿል።

> The functions of folklore can be classified differently, …. Folklore operates within a society to insure conformity to the accepted cultural norms, and continuity from generation to generation through its role in education and the extent to which it mirrors culture. To extent which folklore contrast with the accepted norms and offers socially acceptable forms of release through amusement or humor and through creative imagination and fantacy, it tends to preserve the institutions from direct attack and change. (http://www.jstor.org Fri Apr 13 03 : 14:28 2007).

ከዚህ የምንገነዘበው ይህ ቲዮሪ የማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ፋይዳቸውን የሚመለከት ቢሆንም ከጠቃሚ ባህላዊ እሴት በተቃራኒ ያሉትን ጉዳዮችም የሚተነትንበት መንገድ መሆኑን ነው።

በሌላ መልኩ እያንዳንዱ የፎክሎር ቅንጣት ዘውግ (ዣነር) ለሰው ልጆች ትርጉምና አገልግሎት አላቸው። ይህም ማለት ዘውጉ ለምን ዓላማ እንደሚነገር፣ እንደሚከወንና ምን አገልገሎት እንዳለው አውድን መሠረት አድርጎ የሚገለጽበትና የሚተነትንበት መሆኑን Malinowski (1946 [1923]) ይገልጻል ። ከዚሁ አኳያ የዚህ ቲዮሪ ዋና ዓላማ አንድ ሥነቃል የተለያየ አገልግሎት እንዳለው የሚያሳይ ነው። በዚሁ ቲዮሪ መሰረትም ሥነቃል፤ የማስተማር፣ የማዝናናት፣ ባህልን የመጠበቅ፣ የመቆጣጠርና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ባህላዊ ወጎቹን የሚጠብቅበትና ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበት ነው (Bauman, 1977)።

ከዚህ አንጻር ሲታይ ተግባራዊ ቲዮሪ በልዩ ልዩ መልኮች (ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ተምሳሌታዊ ወዘተ ...) የሚገለጽ በመሆኑ የማይደስሳቸው መስኮች የሉም። ይህም ማለት በማህበረሰቡ ውስጥ የሥነቃል ሚና በልዩ ልዩ መስኮች ከሚገለጽባቸው ጉዳዮች አንዱ ፋይዳውን ማሳየት ነው። ለምሳሌ ያህል በዚህ ጥናት ውስጥ በቱለማ ኦሮሞ አንድ ምሳሌያዊ ንግግር የተነገረው ወይም አንድ ዘፈን የተዘፈነው የክዋኔው ዓላማ ለሆነ ተግባር ነው። ይህም ለማዝናናት፣ ለማስተማር፣ ለማስጠንቀቅ፣ ለማስፈራራት፣ ለማበረታታት፣ ወዘተ ... ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የማህበረሰቡን ህይወትና ባህል ለማጥናት ተግባራዊ ቲዮሪ ጠቃሚ ነው የሚለው ማብራሪያ የዚህ ጥናት ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ነው፡፡

ከዚሁ አኳያ ጥናቱ በተካሔድበት አካባቢ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ የተሰበሰቡት የሥነቃል መረጃዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ቫይረሱን ከመከላከልና ከመቆጣጠር ወይም ለቫይረሱ ሥርጭት ምክንያት ከመሆን አንጻር የሥነቃል ዓይነቶቹ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በዚህ ቲዮሪ ተቃኝቷል። ስለዚህ ተግባራዊ ቲዮሪ የሥነቃል ዓይነቶችን ተግባራትንና ፋይዳዎችን ለማብራራትና ምቹ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ከአውዳዊ ቲዮሪ ቀጥሎ ለመተንተኛነት ተመርጧል።

ተምሳሌታዊ ቲዮሪ፡- በDorson (1972) አከፋፈል ተምሳሌት በቁሳዊ ባሕል የፎክሎር ዘውግ ሥር የሚካተት ነው ሲል፣ Vitor Turner (1961) ደግሞ የማህበረሰብን እውቀት በውስጣቸው ያቀፉ ነገሮች መኖራቸውን ይጠቁማል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተምሳሌት ገላጭ የሚሆነው በቅርፁም ይሁን በይዘቱ ባዘለው ማህበረ ባህላዊ ፍቺ ጭምር እንዳለውና ቁሳዊ ብቻም ሳይሆን ረቂቅ ነገርም (Physical and Abstract) ተምሳሌትነት ሊኖራቸው እንደሚችል ጠቅሰው ተጨባጭና ረቂቅ በማለት በሁለት ይከፍላሉ። ረቂቅ ከሆኑት

ቀለማት፣ ድምፆች፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ክስተቶች፣ ወዘተ... ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, Laurence A. Basirico: (1993) ያስረዳሉ።

በአፍሪካ በተለይም በዛሚቢያ ማህበረሰብ ላይ ጥናት ያደረገው Vitor Turner (1967:19) የተምሳሌት አይነቶች ውጫዊ በሆኑ ወይም ግዑዝ ነገር ብቻ እንዳልሆነ ጠቅሶ በሰዎች ተግባራት ውስጥም ተምሳሌታዊ ጉዳዮች እንዳሉ በመግለጽ በተመለከተበት የመስክ አውድ ቁሳዊ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ ድርጊቶች፣ የማህበራዊ ግንኙነት መስመሮች፣ ክስተቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሥፍራዎች ጭምር ተምሳሌታዊ አገልግሎት ይዘው እንደተገኙ ይዘረዝራል።

ከእነዚህ ከተዘረዘሩ የተምሳሌት ዓይነቶች የምንገነዘበው ጉዳይ የነባርም ይሁን ሌሎቹ ፍቺ ስፋትና ጥልቀት ጎልቶ የሚታየው የሚነገረውና የሚከወነው የሥነቃል ዓይነት በአውድ ውስጥ ማህበራዊ እውቀቱ ያለውን ድርሻ ማሳየቱ (ማጉላቱ) ላይ ነው።

በመሆኑም የሥነቃል ተምሳሌት በቁጥሮች፣ በስሞች፣ በቀለሞች፣ በአቅጣጫዎች፣ በክስተቶች እና በቦታዎች የሚገለጽ አውዳዊ ትርጉም አላቸው። ተምሳሌታዊ ትርጉሙ እንደየ ባህሉ ስለሚለያይ ላንዱ ተምሳሌት የሆነ ለሌላው ተራ ሊሆን እንደሚችል Gusfield and Jerz (1984) ይገልጻሉ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ተምሳሌት በወካይና ተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና የሚገልጽ ሲሆን መገለጫው በቋንቋ፣ በቁሳቁስና በክዋኔ ሆኖ በውስጡም በርካታ ትርጉሞችን የያዘ ነው (Dundes, 1989:112-114)።

በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ እውቀት ውስጥ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገር ይኖራል። እነዚህ የውክልና ሁኔታዎችም በአብዛኛዉ ሜታፈሮች (Metaphors) መሆናቸውን Mills (2008) እና Bayleyegn Tasew (2009) ይገልጻሉ። ሌሎችም የሥነቃል ዓይነቶች ማህበረሰቡ እንደየሚገለገልበት ሁኔታ የሚወክሉት ጉዳይና የየራሳቸው ማህበረሰባዊ ትርጉም አላቸዉ። ለምሳሌ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የወንድና የሴት ብልትን የሚመለከቱ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች በቀጥታ ስማቸውን በመጥራት ሳይሆን በተዘዋዋሪ ሜታፈራዊ አገላለጾችን በመጠቀም ነው። ይህንን አስመልክተው ወርቅነህ ቀልቤሳ (2014) የእነ Lakoff and Johnson (1980)ጥናት ዋቢ በማድረግ ወሲባዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሜታፈርን

እንደሚከተለው ይገልጻል። “Metaphor involves a mapping between two different domains: a source domain and a target domain. The target domain is interpreted or understood in terms of the source domain. Similarly, in the field of sexuality, the taboo domain is interpreted and described in terms of non taboo domain.” Workineh Kelbessa (2014: 63).

ይህም ሜታፌር በሁለት ነገሮች ማለትም በቀጥታና በተዘዋዋሪ በሚነገር ጉዳይ መካካል ያለውን ግንኙነቶች ይመለከታል። ከዚሁ አኳያ ነውር የሆኑ ወሲባዊ ቃላት ነውር ባልሆኑ ቃላት ይገለጻሉ። ይህም በንግግር ውስጥ የሴትም ሆነ የወንድ መራቢያ አካልን በስሙ መጥራት ነውር ነው። ይሁን እንጂ ሥነቃል በምንገለገልበት ጊዜ በቀጥታ የምጠራበትም፣ የማይጠራበትም ሁኔታዎች አሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወሲባዊ ጉዳዮችን አስመልክተው የሜታፌርን አጠቃቀም ወርቅነህ እንዲህ ገልጿል።

> Most Oromo traditional singers use this mechanism to refer sexuality and refrain from naming sexual organs and sexual activites, although some singers so do. They often rely on the visible common properties of the taboo target domain and a non- taboo source domain. … For instance, the Oromo used the following metaphors to refer to female genitalia: *daabboo* furdaa (fat bread), *baqaqaa* (slit), *haro* (pond), *qabee* (gourd/container), *damma* (honey), *soogidda* (salt), and so on. … Other words reportedly used to describe the vagina are *fuchi, buqusha, luuchee, muxuruu, koshaoo, umburruu* and *dhagina dubartii/nadheenii* (women’s body). … Oromo metaphors used the penis include the following: *ejersa* (olea African) tree, *bokkuu* (the scepter of authourity), *kallachaa* (phallic ornament), *eeboo* (a spear), hororoo (ritual and marriage stick), *waddeessaa* (corida *abysinica*) tree, *jirma* (trunk of tree), and marriage stick. … Other words reportedly used to describe the penis are *qunxurroo, jamalii, bixoo seeruu* and *qasaraa*. Workineh Kelebessa, (2014: 63).

ሲተረጎም:-

> ምንም እንኳን አንዳንድ ባህላዊ ዘፋኞች በዘፈናቸው ውስጥ የሰዎችን መራቢያ አካላት በቀጥታ እየጠሩ የሚዘፍኑበት ያሉ ቢሆንም አብዛኞቹ ሜታፌር እየተጠቀሙ ይዘፍኑበታል። ለምሳሌ ኦሮሞ የሴትን መራቢያ አካል ሜታፌርን በመጠቀም ወፍራም ዳቦ፣ ስንጥቅ፣ ሸለቆ፣ መያዣ፣ ማር፣ ጨው ወዘተ በማለት ይጠራል። ትክክለኛው ስም ግን እምስ ወይም የሴት ብልት ሲሆን ይህንንም እንደየአከባቢው በልዩ ልይ ስም ይጠራል። በተመሳሳይ መልኩ ኦሮሞ የወንዱን ብልት በቀጥታ በስሙ ሳይሆን

የሚጠራው ወይራ፣ ጦር፣ ከለቻ፣ ዘንግ፣ በማለት ነው። ትክክለኛው ስሙ ቁላ ወይም የወንድ ብልት ነው።

ከዚህ የምንገነዘበው አንድን ነገር በተምሳሌታዊ ንጽጽር ለመግለጽ የሚታፈር አገልግሎት የጎላ መሆኑን ነው። ይህንን አስመልክተው በዚህ ጥናት ከመስክ ከተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎች ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚለከቱ ዘፈኖች አንዳንዶቹ ከተምሳሌታዊ የሜታፈር አገላለጽ አንጻር የቀረቡ ናቸው። እነዚህንም ከምዕራፍ ስድስት ውስጥ በዝርዝር እንመለከታለን።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከትም በርካታ ሜታፈራዊ አገላለጽ እንዳለ ምሁራን ይገልጻሉ። ከእነዚህ ውስጥ Landau-Stanton & Clements (1993: 4) ኤድስን የሚመለከቱ ዘጠኝ ሜታፈሮች መኖራቸውን በመጥቀስ ለእያንዳንዳቸዉ ምሳሌዎችን በመስጠት እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ።

> THE METAPHORS OF AIDS. At least nine metaphors have been applied to AIDS as follows:- 1. AIDS as Homosexual Illness. 2, AIDS as The Prize for Competitive Research and Economic Gain in Medical Science. 3, AIDS is Defined as Severe Opportunistic Infection and Active Illness. 4, AIDS as a Unique and Newly Created Disease. 5, AIDS as sex. 6, AIDS as Self-Inficted Illness. 7, AIDS as Malthusian Solution to Overpopulation. 8, AIDS as Romantic Death. 9, AIDS as a Spotlight for Society's Problems.

ሲተረጎም፡-

> ስለ ኤድስ ዘይቤአዊ አገላለጽ። ኤድስ ቢያንስ ዘጠኝ ዘይቤአዊ የአገላለጽ መንገዶች አሉት። እነሱም 1. ኤድስ የግብረሰዶማውያን በሽታ ነው። 2. ኤድስ በጤናሳይንስ በምርምራዊ ውድድር ሽልማትና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ማግኛ መንገድ ነው። 3. ኤድስ በአጋጣሚ የሚያጠቃ ፈጣን በሽታ ነው። 4. ኤድስ አዲስ የተፈጠረ ልዩ በሽታ ነው። 5. ኤድስ በወሲብ የሚመጣ በሽታ ነው። 6. ኤድስ ሰው በራሱ እጅ የሚያመጣ በሽታ ነው። 7. ኤድስ የሕዝብ ብዛት መቀነሻ ዘዴ ነው። 8. ኤድስ ስለ ፍቅር መሞት ነው። 9. ኤድስ የኅብረተሰብ ችግር መግለጫ ነው።

እነዚህ ዘይቤአዊ አባባሎች ኤድስን ከልዩ ልዩ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የተገለጹባቸው መንገዶች በመናቸው ሜታፈራዊ (ዘይቤያዊ) አገላለጾች በአግባቡ ተመርምረው ማህበረሰቡ ስለ ኤች አይ ቪ /ኤድስ ያለውን እውቀት በማዳበር ለዚህ አሳሳቢ በሽታ ባህላዊና

ማህበራዊ መፍትሔዎችን ለመፈለግ ማህበረሰብ ተኮር ጥናትና ምርምር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የማህበረሰቡ ፎክሎራዊ እውቀት የሚያተኩረው ማህበረሰቡ ለሥነ-ቃሎቹ የሚሰጠውን ትርጉም መሠረት በማድረግ ነው። ከዚሁ አኳያ በባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችና ቀልዶች እንዲሁም የተዘፈኑ ዘፈኖች በውስጣቸው የሚገኙት ተምሳሌቶች ከዚህ ቲዮሪ አንጻር ታይቷል። ይህ ቲዮሪ ለአውዳዊና ተግባራዊ ቲዮሪዎች አጋዥ መተንተኛ ሆኖ አገልግሏል። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በለውጥ ሂደት ውስጥ ያሉ ናቸው። ይህም ማህበረሰቡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በሚፈጥረው መስተጋብሮች ይወሰናል። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ የሚመለከት ክልላዊ ቲዮሪን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

ክልላዊ (ሂሚስፈርክ) ቲዮሪ፡- ይህ ቲዮሪ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ማህበረሰብ ከቦታው ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት፣ ወይም በሚከሰቱ ሌሎች መስተጋብሮች የተነሳ የማህበረሰቡን የዕውቀት የመዋዋስ፣ የመዋሃድ፣ የመዋዋጥ፣ የመጠናከር እንዲሁም የመዘንጋት መልኮች የሚመለከት ነው። ይህ ንድፈ ሀሳብ እንደ ፎክሎር ባለሙያው Richard Dorson (1972) በማህበራዊ እንቅስቃሴ በተለይም በታሪክ አጋጣሚና ከመልክዓ-ምድር ጋር በተያያዘ የማህበረሰብ *እውቀት* ዓይነትና ደረጃ እንዲሁም ለውጥ ይመለከታል። ንድፈ ሀሳቡ በለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚዳቀሉ፣ የሚዋዋጡ፣ የሚዘነጉና የሚጠፉ የማህበረሰብ ባህሎችን የሚመለከት ነው። በዚህ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነት የተነሳ አንዱ በአንዱ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ እና አንድ ባህል እራሱ በሂደት የሚያሳየውን ለውጥ ይመለከታል (Dorson 1972)።

ታሪካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ነባር ልማዶችን ለመለወጥ አቅሙ ስላላቸው እነዚህ ጉዳዮች በፎክሎርስቱ ሊጤኑ እንደሚገባ ያነሳል። ይህም በሥነቃል ጥናት ውስጥ "አፈ-ታሪክ" ተብለው የተተረጎሙትን (ፈቃደ አዘዘ 1991 እና ዘሪሁን አስፋው 1992) የሚመለከት ነው። በአፍ የሚገለፁ (ሥነቃልን ጨምሮ) ወይም ማህበረሰቡ እንደራሱ የዓለም እይታና ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ያሉትን ክስተቶች ከመልክዓ-ምድር ጋር አያይዞ

የሚዘፍናቸውን፣ የሚተርካቸውን፣ የሚናገራቸውን እና የሚያከናውናቸውን ተግባራዊ ጉዳይ የሚመለከት ነው።

በአጭሩ የክልላዊ ቲዮሪ ዋና ትኩረት እያንዳንዱ ማህበረሰብ ሥነቃላዊ ሀብቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚያስተላልፍ፣ እንዴት ጠብቆ እንደሚያቆያቸው እና መልሶ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንደሚያውላቸውም የሚታይበት ሲሆን አዳዲሶቹን ደግሞ እንዴት ተለማምዷቸው የራሱ እንደሚያደርጋቸው የሚመለከት ቲዮሪ ነው (Dorson, 1972)። ከዚህ አንጻር ይህ ቲዮሪ ከለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ ጋር አብረው የሚታይ በመሆኑ በትንተኔ ሂደት ውስጥ ተደጋጋፊ ናቸው።

በዚህ ጥናት ውስጥ አንዳንድ ቦታዎች ከሌሎች የበለጠ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳይ አላቸው። ለዚህም የከበራ ቦታዎች ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው። በመሆኑም በማህበረሰቡ ከበራዎች (እንቁጣጣሽ፣ ጥምቀት፣ እሬቻ፣ ሡርግ እና ለቅሶ) ላይ ከሚነገሩ እና ከሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ለምሳሌ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ዘፈኖች እና ምርቃቶች ውስጥ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ የማህበረሰቡን ሥነቃላዊ ሀብት ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፉ አኳያ ክልላዊ (ሂሚስፈርክ) ቲዮሪ ከ(Gennep Van, 1960; Turner Victor, 1967 እና Dorson 1972) ለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ ጋር ተደጋጋፊ ሆነው ለአውዳዊ ወይም ተግባራዊ ቲዮሪ መተንተኛ በማብራሪያነት አገልግለዋል። አንዳንድ ወሲብን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ከማህበረሰቡ ሥነልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። ከዚሁ አኳያ ይህንን ጉዳይ የሚመለከት ቲዮሪ ንድፈ ሀሳብ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪ፡- ይህ ቲዮሪ የፍሩድን አስተሳሰብ መሠረት ያደረገ ሲሆን በፎክሎር መስክ የወሲብ ጉዳዮችን ከሥነልቦናዊ አንጻር የሚታዩ ናቸው። በመሆኑም ወሲባዊ አካሎች በተምሳሌት የሚገለጽበት ነው። በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል በተምሳሌታዊ ቲዮሪ ሜታፊራዊ አገላለጽ ሥር እንደተገለጸው የወንድ ብልት በወይራ፣ በጦር፣ Kallacha (በከለቻ)[21]፣ Bokkuu (በቦኩ)[22]፣ ዘንግ ሲመሰል፣ የሴት ደግሞ በጎርጓዳ

---

[21] በኦሮሞ እምነት የመጀመሪያው ከለቻ ከመብረቅ ጋር ከሰማይ የወረደ ብረት ሲሆን ሌላው የመጀመሪያውን በማስመሰል ከብረት እና ከእንጨት የተሰራ ነው። ከለቻ ከለቻ አባ ገዳ እና ታዋቂ ሽማግሌ በግንባር ላይ የሚያስር ባህላዊ የክብር እቃ ነው። በመሆኑም ከለቻ ከቤት የሚወጣው ወሳኝ በሆኑ ክብረ-በዓላት ለምሳሌ በእሬቻ፣ በገዳ እና ችግሮች ለምሳሌ ድርቅ ሲከሰት እንዲዘንብ እግዚአብሔርን ለመለመን የተጣላ ሰው አልታረቅ ካላ ለማስታረቅ በጎሳ መካከል የሚፈጠርረውን ግጭት ለማስወገድ ወዘተ ... ነው። (Almaayyoo Hayilee, 2007: 221; Drribii

ነገር፣ ስንጥቅ፣ ሽለቆ፣ በመያዣ፣ ይመሰላል Workineh Kelebessa, 2014)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር የወንድ ብልት በእንጨቶች፣ በዛፍ፣ በዣንጥላ፣ በቢላ፣ በመዶሻ፣ በአይሮፕላን…ወዘተ የሚመሰል ሲሆን የሴት ደግሞ በዋሻዎች፣ በጠርሙሶች፣ በሣጥኖች፣ በበሮች፣ በቀለበቶች፣ በአትክልት ቦታዎች …ወዘተ ይመሰላሉ (Dundes, 1989)። በሌላ መልኩ ቀልድና አምልኮዎች እንዲሁም ተረቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ነዉር የሚባሉትን ከውስጠ ሕሊና (Subconscious mind) ጋር የሚያያዙ ሲሆኑ ወሲባዊ ሕልሞች የፆታ ፍላጎቶች ተምሳሌቶች መሆናቸዉ እና ከዚሁ አኳያ እስክስታ መዝለል፣ መኪና መንዳት፣ ዛፍ ላይ መውጣትና በአየር መብረር የመሳሰሉት ሕልሞች የወሲብ ፍላጎትን የሚያመለክቱ ጉዳዮች በቀጥታ ከፎክሎር ጋር ግንኙነት እንዳላቸው Dundes (1989) ገልጿል። በተለይም ፀያፍ ቀልዶች የሚባሉት ፊት ለፊት የማንናገራቸውንና አይነኬ ጉዳዮችን ለመግለጽ እንደ አንድ መንገድ የምንገለገልባቸው መሆኑን ፍሩድን ዋቢ በማድረግ ከድረገጽ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል (Dorson, 1963) [23]።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሰዎች በውስጣቸዉ የሚያስቡትንና የሚፈልጉትን ሁሉ በቀጥታ ስለማይናገሩ ሀሳባቸውንና አመለካከታቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመረዳት የሥነቃል ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የአንድ ሕዝብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ጭንቀት፣ ተስፋ፣ ምኞት፣ ሀዘንና ደስታ በአጠቃላይ ሥነልቦናዊ አስተሳሰቡ በሥነቃሉ ውስጥ ስለሚገኝ እነዚህን ምንጮች በማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከት ማወቅ እንደሚቻል ፈቃደ አዘዘ (1991፡50) ይገልጻል። ስለዚህ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ ከተጠኚው ማህበረሰብ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ከሥነልቦና አንጻር ተቃኝቷል። በመሆኑም ይህ ቲዮሪ የአውዳዊ ወይም ተግባራዊ ቲዮሪ ደጋፊ መተንተኛ ሆኖ አገልግሎት ላይ ውሏል። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የማህበረሰቡ እውቀት

Damisee, 2009: 107).

[22] ከላይ እንደ ተገለጸው የመጀመሪያው ቦኩ ከከለቻ ጋር ከሰማይ የወረደ ሲሆን ሌላው በማስመሰል የተሰራ ነው። ቦኩ ከላይ የወንድ ብልት ቅርጽ ያለው ሲሆን ከታች የሴት ብልት ምስል ያለው ዱላ ነው። ቦኩ የሥልጣን መገለጫ በመሆኑ ብክብረ በዓላት እና ችግሮች ወቅት በአባ ገዳ የሚያዝ ዱላ ነው። አባ በገዳ ምክር ቤት የተደነገገውን ሕግ ይፋ የሚያደርገው የሚወጀው ቦኩ በመያዝ ነው።(Almaayyoo Hayilee, 2007: 221; Drribii Daamusee, 2009: 106).

[23] Current Folklore Theories፡ Vl. 4, No. 1. (Feb., 1963), pp. 93-112. Stable URL; http:// www.jstor/stable/2739820. Accessed 17/02/2008 11:12

ውጤቶች ናቸው። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ አስመልክተው የማህበረሰቡ እውቀት ቲዮሪን ንድፈ ሀሳብ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የማህበረሰብ እውቀት አዋቃሪያን ቲዮሪ፡- ይህ ቲዮሪ ማህበረሰቡ በየዕለት ውሎው ከሚያከናውናቸው ተግባራት በሂደት ልማድ እየፈጠረ፣ በኋላም ተቋማትን እየገነባ የሚሄድ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ያለው እውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ ነው። በግለሰብም ሆነ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለው የእውቀት ስርጭቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር ቋንቋ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው (Berger and Luckmann, 1966)። የማህበረሰቡ እውቀት ሽግግር እውን የሚሆነው በሚያከብራቸው ልዩ ልዩ ከበራዎች በአውድ ውስጥ በሚንፀባረቅበት ወቅት ነው (Sims, and Stephens, 2005)።

ከዚህ ቲዮሪ የምንገነዘበው የሥነቃል ትንታኔ በሚከናወንበት ወቅት ከሌሎች ቲዮሪዎች ጋር አብረው የሚታይ መሆኑን ነው። ይህም ሥነቃል በማህበረሰቡ ውስጥ በየቀኑ የሚነገርና የሚከወን በመሆኑ የእውቀቱ ሥርጭት ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማሸጋገሩ አንጻር ክልላዊ ቲዮሪን የሚመለከት ሲሆን በሚያከብራቸው ልዩ ልዩ ከበራዎች አንጻር ደግሞ ከአውዳዊ ቲዮሪዎች ጋር ታያይዞ የሚታይ ነው።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በማህበረሰቡ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረበዓላት ላይ የጥናቱን ረዕሰ ጉዳይ አስመልክተው የተነገሩ እና የተከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ለአውዳዊ ቲዮሪ ወይም ተግባራዊ ቲዮሪ መተንተኛነት ከክልላዊ ቲዮሪ ጋር በተደጋጋፊነት አገልግሎት ላይ ውሏል። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በአንድ ቦታ ረግተው ያሉ ሳይሆኑ በለውጥ ሂደት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በእነዚህ ለውጦች ውስጥ በቀጣይነትም የሚገኙ ይኖራሉ። በመሆኑም የዚህን ቲዮሪ ዝርዝር ቀጥለን እንመለከታለን።

ለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ፡- በዚህ ቲዮሪ አመለካከት ማህበረሰብም ሆነ ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት፣ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ለውጥ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ለለውጡ መፋጠን የበለጠ ጎልቶ የሚጠቀስና የሚቀርብ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጉዳዮቹ ለውጡን ማስከተላቸው አይቀሬ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከስተው ከነበሩት ታሪካዊ ክስተቶች ውስጥ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች መፈጠር፣ የስልተ-ምርት እየተለወጠ መሄድ፣ የከተሜነትና ግለኝነት ኑሮ መስፋፋት ለለውጥ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው። በተለይም የአውሮፓውያን ወደ አፍሪካ መምጣት በቀጥታ በቅኝ ግዛት በያዟቸውም ሆነ በዘመኑ በነበረው የዓለም እንቅስቃሴ መንፈስ ነባሩን ሀገራዊና አካባቢያዊ ድባብ መለወጡንና እነዚህም ለውጦች በከበራዎች እንደሚገለጹ Gennep Van (1960) and Dorson (1972) አብራርተዋል።

የአውሮፓውያኑ መስፋፋት በሌሎች ማህበረሰብ ባህላዊ ጉዳዮች ላይ በአዎንታም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ተፅዕኖ ማድረጉንና በተለይም ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በአፍሪካ ማህበረሰብ ባህል ላይ ለውጥ ማስከተሉን በመጥቀስ የዛምቢያው ማህበረሰብ ነባር ሀይማኖታዊ ተቋማትና ከበራው በውጫዊ ሃይማኖት መዋጡን Turner (1967:2) ገልጿል።.

በተመሳሳይ ሁኔታ በእነዚህም ሆኑ በሌሎች ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ኢትዮጵያ ውስጥ በየጊዜው የነበሩ ለውጦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቱለማ ኦሮሞ ነባር ባህላዊ እሴቶቹ ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አልቀረም። እነዚህ በየወቅቱ የነበሩት ለውጦች በሥነቃል በተለይም በዘፈን ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። የባህላዊ ዘፈኖች መዳቀል ወይም መለወጥ አስመልክተው ወርቅነህ ቀልቤሳ (2014: 43) እንደሚከተለው ገልጿል።

> Traditional Oromo songs have been changing over centuries. Some are newly created by the singers in response new changes and influences. The Amhara, Somali, Gurage and other ethnic groups in Ethiopia and Kenya have influenced traditionadl Oromo songs.

ከዚህ የምንረዳው የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ባለው መስተጋብር ባህላዊ ዘፈኖቹ እንደሚቀየሩ ወይም ከሌላ ቋንቋ ጋር እንደሚዳቀሉ ነው። የቱለማ ኦሮሞም ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ገጽታ ከተነሳው እውነታ ውጪ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በአሁኑ ዘመን በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን አስመልክተው የሚዘፈኑ ዘፈኖች ለውጦችን ተከትለው የሚገለጹ ናቸው። በመሆኑም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎች ከዚህ ቲዮሪ አኳያ የተቃኙ ሲሆኑ ለአውዳዊ ቲዮሪ ወይም ተግባራዊ ቲዮሪ ደጋፊ መተንተኛ ሆነው አገልግለዋል።

በአጠቃላይ ከላይ በእያንዳንዱ ቲዮሪ ሥር በዝርዝር እንደተገለጸው የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ሁለገብ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው በጥናትና ምርምር ውስጥ መረጃዎቹን ለመተንተን ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር መታየት አለባቸው። ይሁን እንጂ የጥናቱ ከሚያተኮርበት ርዕሰ ጉዳይ አኳያ የተወሰኑ ቲዮሪዎች ጎልተው ይወጣሉ። ከዚሁ አንጻር በዚህ ጥናት ውስጥ የሥነቃል መረጃዎቹ አብዛኞቹ አውድን መሠረት አድርገው የተሰበሰቡ በመሆናቸው በዋናነት በአውዳዊ ቲዮሪ ተተንትነዋል። አውድ ሲነሳ ክዋኔም የግድ ስለሚኖር የክዋኔ ቲዮሪ ከአውዱ ጋር አብረው ታይቷል። በሌላ መልኩ የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚሰጡት አገልግሎት ፋይዳ (ተግባር) ስላላቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ቲዮሪም ዋና መተንተኛ ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ አውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች ዋና መተንተኛዎች ናቸው። በሌላ መልኩ ከላይ የቀረቡትን ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችን ተግባራት እንደተመለከትነው እርስ በእርሳቸው የታያያዙ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ውስጥ እንዳስፈላጊነታቸው ደጋፊ መተንተኛ ሆነው አገልግለዋል።

እስካሁን ድረስ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፎክሎር እና የሥነቃል ሚና በፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳ ውስጥ በስፋት የተገለጸ ሲሆን ይህንን የትምህርት ዘርፍ ለማጥናት የሚረዱ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችም በንድፈ ሀሳብ ዳሰሳ ተቃኝተዋል። ከእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አንጻር በቀጥታ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን ከወሲባዊ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ እስካሁን ድረስ የተካሄዱ ጥናቶችን ማየቱ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም ከተላላፊ የአባለዘር በሽታዎች በተለይም ከቀሳፊው የኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ መስፋፋት አኳያ በአውንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የሚነገሩ እና የሚከወኑ ሥነቃልን ሰብስቦ ጥናት በማድረግና ለችግሮቹ ሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ መፍትሔ መፈለጉ የግድ ይሆናል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ በወሲብ በሚተላለፉ በሽታዎች እና በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ የተሠሩ ተዛማጅ የሥነቃል ጥናቶችን እንዲሁም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋወሪ ተያያዥ የሆኑ በቱለማ ኦሮሞ እና አከባቢው የተከናወኑ ቀደምት ጥናቶችን እንቃኛለን።

2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርዕስ ሥር ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ምንነት የተገለጸ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ እና በወሲብ አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን በሚመለከት የተደረጉ ጥናቶች የተዳሰሱበት ነው። በሌላ በኩል ከስነቃል ጋር በተያያዘ ሁኔታ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ በውጭ አገር እና በአገር ውስጥ የተደረጉ ጥናቶችና በሽታውን በሚመለከት የተነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች ከልዩ ልዩ ጽሑፎች ተዳሰዋል። በመጨረሻም የጥናቱን ቦታ እና ርዕስ በሚመለከት በቱለማ አሮሞ እና አከባቢው የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ቀርበዋል።

2.3.1 ኤች አይ ቪ/ኤድስ እና ወሲብ የሚመለከቱ ጥናቶች

ኤድስ የሚለው ቃል ፍቺ " ኤድስ (ስ) በሽታን የመቋቋም ተፈጥሮአዊ ኃይልን በማዳከም ሰውነት በቀላሉ በበሽታ እንዲጠቃና ለሞት እንዲበቃ የሚያደርግ፣ ብዙውን ጊዜ በግብረሥጋ ግንኙነት አማካይነት በሚተላለፍ ቫይረስ የሚመጣ በሽታ ነው"። የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፥ 349)። በዚሁ (መዝገበ ቃለት ገጽ 253) ላይ ቫይረስ የሚለውን ቃል ከባክቴሪያ የሚያንስ ተላላፊ በሽታን የሚያስከትል ህዋስ መሆኑን ይገልጻል። በሌላ መልኩ ኤድስ የሚለው የእንግሊዝኛ ምህፃረ-ቃል ሲገለጽ AIDS (Acquireed Immuno Deficiency Syndrom) ማለት ነው። HIV ማለት ደግሞ (Human Immuno Deficiency Virus) በመባል የሚታውቅ ነው።

ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ወሲብ መሆኑ በበርከታ ጥናቶች ውስጥ ተገልጸዋል (UNESCO/AIDS: 2002; UNAIDS: 2004; National HIV/AIDS Preventation and Control Office: 2006; Susan Moore & Doreen Rosenthal: 2006; OSSREA 2008 and Mitike Molla: 2009)።

ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ እድሜ ሳይለይ፣ ድንብር ሳይከልለው በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሰው ልጅን የሚያጠቃና እስካሁንም ድረስ ክትባት ያልተገኘለት ገዳይ በሽታ መሆኑን ዓለም አቀፋዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ አኳያ እ. ኤ. አ. በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በቀረበው ዓለም አቀፋዊ የኤድስ ሥርጭት ሪፖርት መሠረት በ147 አገሮች ውስጥ 33 ሚሊዮን ሰዎች ከበሽታው ጋር ይኖራሉ። ከእነዚህ ውስጥ 67% በከፊል ሰሀራ የሚገኙ የአፍሪካ ሕዝቦች እንደሆኑና ከእነዚህም 75% ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያያዥ በሆኑ በሽታዎች መሞታቸውን UNAIDS (2008) ጥናት ያመለክታል።

ኤች አይ ቪ ከሚተላላፍባቸው መንገዶች ቀዳሚውን ሚና የሚጫወተው ልቅ የሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት ሲሆን ቫይረሱ በዓለም ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በወሲብ ዙሪያ የሰውን ልጅ ከጤና አንጻር እያስጨነቀው ይገኛል። ስለዚህ የወሲብ አፈጻጸም በጥንቃቄ ካልተከናወነ አደጋው የከፋ ነው (Landau-Stanton & Clements:1993; Scott and Duncan: 1998; Green Edward, 1999; Suzanne Leclerc-Madiala et al: 2009 and Ephraim: 2011)።

በወሲብ ከሚተላለፉ በሽታዎች እስካሁን መድሃኒት ያልተገኘለት ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሰው ልጅ ወሲባዊ እርካታ እና እርባታ ላይ ጭንቀትን እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን የሥነልቦና ተመራማሪዎች Brooks and Furstenbrg (1989: 251) ይገልጻሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ፍትህ ቶላ (2007፡ 240) ጤናን በተመለከተ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ኤች አይ ቪ እንደሚከተለው ገልጿል።

> የመጀመሪያው የኤድስ ሕመም መከሰቱ የታወቀው በ1974 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ አሜሪካን ሀገር ኒውዮርክ ከተማ በሚኖሩ ጥቂት ግብረሰዶማውያን ላይ ሲሆን ዋናው የመተላለፊያ መንገድም የግብረሥጋ ግንኙነት ነው። ኤች አይ ቪ በመጀመሪያና በመጨረሻ ደረጃ ላይ የበሽታዉ የመተላለፍ እድል ከፍ ያለ ነው። የቅርብ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በኤች አይ ቪ የተያዙ ሰዎች ኤድስ ደረጃ ላይ ለመድረስ አሥር ያህል ዓመታት ይፈጃሉ። ለዚህም የግለሰቡ ሁኔታዎች ይወስናሉ።

ከዚህ የምንገነዘበው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዋንኛው መተላለፊያ መንገድ ልቅ በሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት ሲሆን ቫይረሱ ወደ በሽታው (ኤድስ) ሳይቀየር ረዥም ጊዜ መቀየት እንደሚችል ነው። በዚህም የተነሳ ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነቱ ከቀጠለ ሳይታወቅ ሥርጭቱ የሚባባስ መሆኑን ነው። ይህንኑ አስመልክተው ኤድስ በዓለም ላይ መታየት ከጀመረበት በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ ዓለምን በፍጥነት ማዳረሱን በጤናው መስክ ላይ የተሠማሩ ተመራማሪዎች እንደሚከተለው ገልፀዋል። "AIDS has transformed into global pandemic in just a few years." (Scott and Duncan፣1998 - 9). ሲተረጎም ኤድስ በጥቂት አመታት ውስጥ ዓለምን ያዳረሰ በሽታ ነው። ይህም የሚያሳየን በሽታው በአብዛኛው የሚተላለፈው በልቅ ወሲባዊ ድርጊቶች መሆኑንና ችግሩም ሁሉንም እንደሚመለከት ነው።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ኤርሚያስ ሥዩም፣ (2006፡ 4) የወሲብ ጉዳይ ሁላችንንም የሚመለከት በመሆኑና ከዚህ ችግር ነጻ የሆነ ማንም ሰው ስለማይኖር ይህንን ዝብርቅርቅ

ያለ ሕይወት ሥርዓት ማስያዝ እና መፍትሔ ማበጀቱ ሙያዊ ግዴታ ጭምር መሆኑን ይገልጻል ።

የኤድስ ሥርጭት በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ዓለምን ያዳረሰው ቫይረሱ የተለዋዋጭነት ባህሪይ ያለዉ መሆኑን በመጥቀስ በሽታውን ለማጥፋት የማያቋርጥ ምርምር የሚጠይቅና ለተግባራዊነቱም የዜጎችን ቁርጠኝነት የሚፈልግ ስለሆነ ይህንን አስከፊ በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ግለሰብ፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ የበኩላቸዉን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው በመግለጽ፣ ቁጥጥሩን በሦስት ደረጃ Landau-Stanton & Clements (1993) ይከፋፍሉታል።

የመጀመሪያው ደረጃ አዳዲስ ሰዎች ወደ በሽታው እንዳይመጡ፣ ወሲባዊ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት ተከታታይነት ያለው ግለሰብ ተኮር ትምህርት በመስጠት ኤድስን ልክ እንደ ፈንጣጣ በሽታ ከዓለም ላይ ማጥፋት ነው። በሁለተኛ ደረጃ በበሽታው የተያዙ ሰዎች መድኃኒት እንዲወስዱና ሥነልቦናዊ ጥንካሬ እንዲኖራቸው ማበረታታትና ማስተማር ሲሆን፣ በሦስተኛ ደረጃ የበሽታውን የባህሪይ ተለዋዋጭነት ለመከላከል ቀድሞውኑ በበሽታው የተጠቁ ሰዎች ከልቅ ወሲብ እንዲታቀቡ ማስተማር መሆኑን Landau-Stanton & Clements (1993፡ 57-58) ይዘረዝራሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ኤርሚያስ ሥዩም (2006፡ 35) ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ በወሲብ ንግድ ላይ ከተሠማረች ሴት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ወሲብ እና ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት የበሽታውን አስከፊነት እንደሚከተለው ገልጻለች።

> ሽርሙጣ ብሆንም ወሲብ አልፈጽምም። ወሲብን በጣም ነው የምፈራው ወሲብን በጣም ስለምፈራ መፈጸሙን ትቻለሁ። እንደ ኤች አይ ቪ የምፈራው ነገር የለም። የሞቱትን ሽርሙጦች ስላየሁ በኤች አይ ቪ አትግደለኝ እያልኩ ነው እግዚአብሔርን የምለምነው። እግዜር በኤች አይ ቪ ከሚገለኝ በሌላ በፈለገው ቢገድለኝ ደስ ይለኛል። ጓደኛዬ የተሰቃየችውን ስቃይ እንደ እኔ ያየ የለም። ከአልጋው ጋር ተሰፍታ ነው የሞተችው ማለት ይቻላል።

ከዚህ የምንረዳው ይህች በቡና ቤት የወሲብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራች ሴት የበሽታውን አስከፊነት ተገንዝባ በወሲብ አፈጻጸም ላይ የባህርይ ለውጥ ማምጣቷን ነው። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ተላላፊ የአባለዘር በሽታዎችና የኤድስ መንስኤ ልቅ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት በመሆኑ ሥርጭቱን ለመግታት በወሲብ ላይ የባህሪይ ለዉጥ ማምጣቱ የጎላ ሚና እንዳለው በሞዛምቢክ፣ በዛምቢያ፣ በታንዛኒያና በደቡብ አፍሪካ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ (Green Edward, 1999; Suzanne Leclerc-Madiala et al, 2009; Ephraim 2011)።

በዚሁ መሠረት በአፍሪካ ያለውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ለመግታት ባህላዊና ማህበራዊ እውዶችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የወሲብ ባህርይ ላይ የጠለቀ ጥናት መደረግ እንዳለበት UNAIDS (2004) ይገልጻል።

ከዚህ አኳያ በተላላፊ በሽታዎችና ኤድስ ዙሪያ ከባህላዊ መድሃኒት አዋቂዎች ጋር የመከላከል ሥራ ተሠርቶ በ42% የበሽታው ሥርጭት መቀነሱን በታንዛኒያ 1990-1991 የተደረገው ጥናት ያመለክታል (Green Edward, 1999)። በማያያዝም የአፍሪካ አገሮች የራሳቸው የሆኑ በርካታ ባህላዊ እውዶች ያላቸው በመሆኑ፣ ወሲብን በተመለከተ ሁሉም አገሮች እንደየ ባህላዊ እምነታቸዉ የየራሳቸውን ተግባራት እንደሚያከናውኑ በደቡብ አፍሪካ ጎሳዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ይጠቁማሉ (Suzanne Leclerc-Madiala et al, 2009)።

ከወሲብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዓለም ላይ ተላላፊ የአባለዘርና ኤድስ በሽታ ሥርጭት በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱንና ለዚህም ዋና ተጋላጭ የሆኑት እድሜያቸው ከ12 እስከ 29 የሚገኙ ወጣቶች መሆናቸውን በአውስትራሊያ ከ1991 —2001 የተደረገው ጥናት ያመለክታል (Susan Moore & Doreen Rosenthal 2006, 176-177)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እ.አ.አ. በ2002 ዓ.ም. በዩኔስኮና በተባበሩት መንግስታት አማካይነት የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው በዓለም ላይ ከሚገኙ ወጣቶች ውስጥ 11.8 ሚሊዮን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 7.3 ሚሊዮን ሴቶች መሆናቸውን ይጠቅስና 6000 ያህል ወጣቶች በየቀኑ በበሽታው እንደሚያዙ UNESCO/AIDS (2002) ይጠቁማል። ከዚሁ አንጻር ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት ዓለም አቀፋዊ ሪፖርት እንደሚያሳየው እድሜያቸው ከ15-24 የሆኑ ወጣቶች በተለይም ወጣት ሴቶች በተለየ ሁኔታ የበሽታው ተጠቂዎች መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህን አስመልክቶ በተባባሩት መንግስታት የኤድስ ጥናት UNAIDS (2004: 13). እንደሚከተለው ገልጿል።

> Since the first AIDS case was diagnosed in 1981, the world struggled to come to grips with extraordinary dimensions. Now more than 20 years later, 20 million people are dead and 37.8 million people world wide are living with HIV. And still AIDS expands resentlessly, destroying people's lives and in many cases seriously damaging the fabric of societies. From these young people (aged 15-24) especially women most affected.

ሲተረጎም

> ኤድስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታየበት እ.አ.አ. 1981 ዓ.ም ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ችግሩን ለማስወገድ በሁሉም አቅጣጫ ትግል ሲያደረግ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ

> ዛሬም ከ20 ዓመት በኋላ 20 ሚሊዮን ሕዝብ በኤድስ ሞተዋል፤ 37.8 ሚለዮን የዓለም ሕዝብ ደግሞ ከቫይረሱ ጋር ይኖራል። አሁንም በኤድስ ሥርጭት ምክንያት የዓለም ኅብረተሰብ በማንኛውም መልኩ ክፉኛ እየተጎዳ ይገኛል። በተለይም እድሜያቸው ከ15 — 24 የሚገኙ ወጣት ሴቶች እጅግ በጣም እየተጎዱ ናቸው።

ከዚህ መረጃ እንደምንገነዘበው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በዓለም ላይ ከታየበት ጊዜ ጀምሮ የሥርጭት አድማሱን እያስፋፋ የሰውን ልጆች ሕይወት እየቀጠፈ መሆኑን ነው። ምንም እንኳን ከላይ የቀረበው መረጃ ጊዜው የቆየ ቢሆንም አሁንም ቢሆን የኤድስ ሥርጭት ቀንሷል በሚባልበት ዘመን ቫይረሱ ሰዎችን እየገደለ ነው። እዚህ ላይ መታየት ያለበት በቫይረሱ የሞቱትን ሰዎች ቁጥር ሳይሆን በሽታው እስካልጠፋ ድረስ እየደረሱ ያሉት ሁለገብ ችግሮች አሁንም እንዳሉ ናቸው። በተለይም በለጋ እድሜ ላይ የሚገኙትን ዜጎች እጅግ በጣም እየተጎዱ ለመምጣታቸው ዋናው ምክንያት የወሲብ ንግድ መስፋፋት መሆኑን በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ልዩ ልዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

በበአሜሪካ አገር Center for Disease Control and Prevention (CDC) በመባል የሚታወቅ ድርጅት CDC Fact Sheet በሚል ርዕሰ ጉዳይ ከአባለዘር በሽታዎች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማድረግ ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል። በዚሁ መሠረት እ.ኤ.አ. በ2013 እና 2014 ዓ.ም የቀረበው መረጃ ከአባለዘር በሽታዎች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በየዓመቱ ከተጠቁ አዳዲስ ሰዎች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ እድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣት ሴቶች መሆናቸውን CDC, (November 2015) ይገልጻል።

በአፍሪካና ደቡብ እስያ አገሮች በአብዛኛው በኤድስ የተጠቁት ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ወጣት ሴቶች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸውን Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006፡ 178-179) ይገልጻሉ። በማያያዝም ኤች ኣ ይ ቪ/ ኤድስ እያደረሰ ባለው ጥፋት በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ የሆኑት እድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ስትገልጽ እንዲህ ትላለች።

"Young women are worst affected. The peak age of infection is between 15 and 24, with a female to male ratio of two to one (2፡1) in that age group" (Paterson Gillian, 1996: ix).

ሲተረጎም ወጣት ሴቶች በግንባር ቀደምትነት የተጋለጡ ናቸው። እድሜያቸው ከ15 እና 24 መካከል የሚገኙ ወጣቶች ውስጥ የሴቶች ቁጥር ከወንዶች እጥፍ ነው።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣት ሴቶች በኤች አይ ቪ ተጠቂ መሆናቸውን Lisa et al, (2006) ይገልጻሉ። በሌላ መልኩ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሴቶች ላይ እያደረሰ ያለውን ችግር Susser Ida, (2009) ሲትገልጽ በደቡብ አፍሪካ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች ከድህነታቸው የተነሳ ኤድስን ለመከላከል ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ እንዳሉና በዚሁ የተነሳ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ሴቶች በወሲብ ዙሪያ ውስብስብ ምርጫዎች እንደሚገጥማቸው ስታብራራ፣ ልጅ ለመውለድ ከፈለጉ በሽታው የሚያሳስባቸው ሲሆን እርግዝናውን ከተከላከሉ ደግሞ ያለ ልጅ መቅረታቸው ሌላ ስጋት እንደሚሆንባቸውና በዚህ ምክንያተ ለሥነልቦናዊ ቀውስና የአዕምሮ ጭንቀት እንደሚዳረጉ ትገልጻለች።

በአገራችን ያለውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት በተመለከተ "HIV Related Estimiates and Projections for Ethiopia -2014 በሚል ርዕስ በጤና ጥበቃ ሚንስቴር የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲቲዩት ባቀረበው መረጃ መሠረት የቫይረሱ ሥርጭት በተመለከተ አሁን ያለበት ደረጃና ወደፊት ልሆን የሚችለውን መጠን አሳይቷል። በዚሁ መሠረት በበሽታው የተያዙትን፣ በቫይረሱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሞቱትንና የወደፊቱንም በመተንበይ የተሠራው እስታስቲካዊ መረጃ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የቀረበውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ 2፡- በኢትዮጵያ የኤች አይቪ/ኤድስ ሥርጭት መጠን ማሳያ (2013-2018 ዓ.ም)

(Urban+ rural) Adult(15-49) prevalence (%)	2013	2014	2015	2016	2017	2018
Total	1.2	1.1	1.1	1.0	1.0	1.0
Males	0.9	049	0.8	0.8	0.8	0.7
Females	1.5	1.8	1.3	1.3	1.2	1.2
HIVpositive population						
Total (Urban + rural)	793,705	769,602	753,o83	740,251	730,975	723,836
Males	322,004	311,555	303,597	297,356	292,631	288,697

Females	471,701	458,047	449,486	442,895	438,344	435,139
Annual AIDS Deaths						
Total (Urban + rural)	45,171	35,578	26,682	20,354	15,338	11,738
Males	17,340	14,929	11,763	8,975	6,907	5552
Females	27,831	20,649	14,919	11,379	8,431	6,186
Adult (15-49 years)	2013	2014	2015	2016	2017	2018
HIVpositive population						
Total	593,375	591,146	593,614	597,050	602,742	610,372
Males	220,783	221,384	223,015	224,988	227,818	231,339
Females	372,592	369,762	370,599	372,062	374,924	379,033
Annual AIDS Deaths						
Total	31,977	26,019	21,268	18,173	14,429	10,846
Males	10,672	10,100	9,028	7,873	6,447	5,101
Females	21,305	15,919	12,240	10,300	7,982	5,745

Ethiopian Public Health Institute Federal Ministry of Health (july, 2014:15)

ከዚህ የምንገነዘበው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መጠን እንደ አጠቃላይ መቀነሱንና የሞት መጠኑም በየዓመቱ እየቀነሰ መሄዱን ነው። ይሁን እንጂ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 49 የሚገኙ በኤች አይ ቪ የተያዙትን (HIVpositive population) ስንመለከት የቫይረሱ ሥርጭት ጨምሯል። ይህም ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያሳይ በ2014 ዓ.ም ቀነሰ እንጂ ከዚያ በኋላ በየዓመቱ እይጨመረ መሄዱን ያመለክታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በከተማ እና በገጠር ያለውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ከዚሁ የመረጃ የተገኘው እስታስቲክስ እንደሚከተለው ተገልጿል። ይኸውም እ.ኤ.አ. በ2013 ዕድሜያቸው ከ15-49 የሆኑ በከተማ ያለው የኤች አይ ቭ/ኤድስ ሥርጭት መጠን ሴት 4.6%፣ ወንድ 2.8% ጠቅላላ 3.7 ሲሆን በ2018 ደግሞ ሴት 3.2% ወንድ 2.0% ጠቅላላ 2.6% እንደሚደርስ ያሳያል። በተመሳሳዩ በገጠር ያለውን ሥርጭት ደግሞ በ2013 ሴት 0.7%፣ ወንድ 0.4 ጠቅላላ 0.6% ሲሆን በ2018 ደግሞ ሴት 0.5% ወንድ 0.3% ጠቅላላ 0.4% ይሆናል ተብለው ይገመታል (Ethiopian Public Health Institute Federal Ministry of Health july, 2014: 17-19)። ከዚህ የምንረዳው የበሽታው ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ የሚበዛ መሆኑንና በቫይረሱ በጣም እየተጠቁ ያሉት ሴቶች መሆናቸውን ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በNational HIV/AIDS Preventation and Control Office, (2006) የተደረገ አገር አቀፍ ጥናት እንደሚያሳየው እድሜያቸዉ ከ15 -49 የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶች ግንዛቤ ያላቸው ቢሆኑም፣ ለችግሩ ተጋላጮች እነዚሁ የኀብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸውን ነው። ከዚሁ አንጻር በአገራችን ያለውን የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት አስመልክተው የምሥራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ ማህበራዊ ሳይንስ ምርምር ተቋም ባደረገው ጥናት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በበሽታው ከተጠቁ አገሮች በ6ኛ ደረጃ ላይ መገኘቷን በመጥቀስ የበሽታውም ሥርጭት በከተሞች እንደሚበዛ እና በአገሪቱ ካሉ ከተሞች ውስጥ አዲስ አበባ ከፍተኛውን ድርሻ እንደምትይዝ OSSREA (2008) ይገልጻል።

በሌላ መልኩ ምትኬ ሞላ (2009) ለሦስተኛ ዲግሪ መሟያ “Preventing HIV among Yong People”በሚል ርዕስ በኖርዌ ቤረገን (Bergen) ዩኒቨርሲት ያቀረበች ጥናት በቡታጅራ ከተማና አከባቢው ማህበረሰብ ወሲባዊ ልማድና ጤና ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ የተካሔደው በ9 የገጠር እና በ1 ከተማ ላይ ሲሆን ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። የጥናቱ ትኩረት በወሲባዊ ባህርይ፣ በግብረሥጋ ግንኙነቶች በሚተላለፉ በሽታዎች እና ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር በተያያዘ ምክንያት የሞት መጠንን የሚመለከት ነበር። ቃለ-መጠይቅና ምልከታ ዘዴዎችን በመጠቀም በማዕካላዊ ደቡብ ኢትዮጵያ (ቡታጅራ ከተማና አከባቢው) ባደረገችው የመረጃ ማሰበሳብ ሥራ ከጋብቻ በፊት ወሲብ የማይፈጽሙ ልጃገረዶች 3% መሆናቸውን፣ ከአልኮል መጠጥና ጫት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወጣቶች ከጋብቻ በፊት የግብረሥጋ ግንኙነቶችን እንደሚፈጽሙ፣ ከሰባት ወጣቶች ውስጥ ስድስቶቹ በኮንደም እንደማይጠቀሙ፣ በዚህም የተነሳ 4% የሚሆኑት የወሲብ ተላላፊ በሽታዎች ምልክቶች እንደሚታይባቸው በጥናቷ አመልክታለች። ምንም እንኳን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሞቱ ወጣቶች በተመለከተ የተያዙ አስተማማኝ መረጃዎች ባይገኙም ከቤተሰብ በተገኘው መረጃ የሞት መጠኑ 0.02% ነው። ይህ ማለት ቀላል ግምት የሚሰጠው ሳይሆን በሽታው እስካልጠፋ ድረስ ማህበረሰቡን በልዩ ልዩ መልኩ የማስተማር ተግባር መቀጠል እንደለበት፣ ከጋብቻ በፊት የኤች አይ ቪ/ ኤድስ የደም ምርመራ ማድረግና የግብረሥጋ ግንኙነት አለማድረግ የሚለውን የማህበረሰቡን ባህላዊ ልማዶች መጠናከር እንደሚኖርበት፣ በኮንዶም የመጠቀም ልምድ እንዲኖር ማበረታታት እና ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆኑ የጤና ተወልዶ ትምህርት በተከታታይ መሰጠት እንዳለበት በጥናቷ የመፍትሔ ሀሳብ ውስጥ በአጽህኖት ተገልጿል (ምትኬ፣ 2009፡ 31) ፡፡

ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር በአገራችን የተወሰኑ ከተሞች የተደረገ የኤርሚያስ ሥዩም ጥናታዊ ዳሰሳ ታዳጊዎች በወሲብ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራታቸውንና እድሜያቸውም ከ11 እስከ 14 የሆኑ ሕፃናት መሆናቸውን ይገልጻል። ይሁን እንጂ ማንም ሰው ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ወይም የሌላን ሰው ፍቶተ ሥጋ ለማርካት ሲል ሕፃናትን (ተስማምተውም ቢሆን) ለወሲብ ሥራ ያነሳሳ፣ ያባበለ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የገፋፋ፣ ያቃጠረ፣ ለወሲባዊ ንግድ ንግድ ከቦታ ቦታ ያዘዋወረ ወይም በዝሙት አዳሪ ቤት ያስቀመጠ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 635 እንደምቀጣ ቢገለጽም የወንጀል ህጉ መኖሩን በመጥቀስ በሕጉ መኖር ብቻ ድርጊቱ መቆም ባለመቻሉ በርካታ ታዳጊ ወጣቶች በወሲብ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው የቫይረሱን ሥርጭት እያባባሱ መሆናቸውን ይገልጻል ኤርሚያስ (2006፡ 4)።

እስካሁን እንደተመለከትነው በማህበራዊ ዘርፍ የተደረጉ ጥናቶች በበሽታው የተጠቁትን በመግለጽና የበሽታውን መተላለፊያ መንገዶች በመጠቆም ሰዎች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ የሚረዱ ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች ከፎክሎር አንጻር በተለይም በሥነቃል ማህበረሰቡ ስለበሽታዉ ምን ይላል፣ እንዴትስ ይከላከላል፣ ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተከናወኑ ጥናቶች ጎልተው ባለመታየታቸው በዚህ ረገድ ክፍተት ይታይባቸዋል። በአገራችን በቀጥታ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የተደረጉ የሥነቃል ጥናቶች አሉ ለማለት የሚያስደፍር ነገር ባይኖርም በሌሎች ጥናቶች ውስጥ እግረ መንገድ ስለ ሥነቃል የተባሉ ጉዳዮች አሉ። ይሁን እንጂ ሥነቃልን መሠረት ያደረገ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የመከላከል ተግባራት አስመልክተው በውጭው ዓለም የተካሔዱ በርካታ ጥናቶች ሲሆን በአገራችንም ከባህላዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልኩ የጎላ ባይሆኑም በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተወሰኑ ጥናቶች አሉ። በመሆኑም ለዚህ ጥናትና ምርምር በግብዓትነት ይረዱ ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት በሥነቃል ዓይነቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶችና በሽታውን አስመልክቶ የተነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.3.2 ኤች አይ ቪ /ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ጥናቶች

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር በውጭው አገር እና በአገራችን ከቫይረሱ ጋር በተያያዘ መልኩ የተነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች የተዳሰሱበት ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ በቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የአንድን ሕዝብ ጥንተ ታሪክ ባጠናን ቁጥር ባህላዊ ምስጢሮቹን ይበልጥ እናውቃለን። ባወቅን ቁጥር ደግሞ ለችግሮቹ መፍትሔ እንደምናገኝ Fayeradnd (1998) ይገልጻል። በአፍሪካ ማህበረሰቦች ከሚነገሩና ከሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮች አጫጭር እና በቋንቋ ፈጠራ የታጀቡና ከሥነምግባር ትምህርትም ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። በመሆኑም ለማህበራዊ አገልግሎት የጎላ አስተዋጽኦ እንዳላቸው በልዩ ልዩ ምሑራን የተከናወኑ የሥነቃል ጥናቶች ይጠቁማሉ (Mieder, 1993; Egbe, 2000; Yusuf & Methangwane, 2003; Omolara & Samuel, 2012)።

ከዚሁ አንጻር ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለማስተማርና ለምክር አገልግሎት እንደሚውሉ Omolara & Samuel (2012) ይገልጻሉ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር በየት/ቤቱ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት በሥነቃል አማካይነት የማስተማሪያ ማኑዋል በማዘጋጀት የበሽታዉን አስከፊነት በማስተማር የተሳሳተ ግንዛቤ ማስወገድ እንደሚቻል Bodenstin and Gisela, (2005) ይገልጻሉ።

በፍቅር የሚፈላለጉ ሰዎች የፍቅር ስሜታቸውን ከሚገልጹበት መንገድ አንዱ በሚደረድሩት የፍቅር ዘፈን (ቃል ግጥም) ነው። በእነዚህ ዘፈኖች ዙሪያ የጠለቀ ጥናት በማድረግ የማህበረሰቡን ባህላዊ ሁኔታዎች በማወቅ የማህበረሰቡን አሰተሳሰብ መግለጽ የሚቻል መሆኑን Crowely, (1982); Legman, (1990); Okepew, (1992) and Workineh Kelbessa: 2014) ያብራራሉ።

በቻይና አገር ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት ፎክሎር ያለውን ሚና የሚገልጽ ከድረገጽ የተገኘው መረጃ "Folklore about HIV/AIDS"[24] በሚል ርዕስ በፎክሎር

[24]www.china.org.cn/china/2011-09/01/content

አማካይነት ኤች አይቪ/ኤድስን መቆጣጣርና መከላከል እንደሚቻል ጠቅሶ ለዚህም በቻይና ኤድስን በዘፈንና በመዝሙር ለመከላከል ጥረት ማድረጋቸውን ይገልጻል።

በሌላ መልኩ ኤድስን በሚመለከት በሚነገሩ ቀልዶች ላይ ከተረዘረዘሩት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል። እነሱም፡- ኤድስ ከልጃገረድ ከያዘ "የመጀመሪያ" ኤድስ፣ ከትምህርት ቤት ከያዘ "ውጤት" ኤድስ፣ በሮናልድ ሬገን ከተጠቃ ፕሬዝዳንታዊ ኤድስ እና ከዘፋኝ ከያዘ ባንድ ኤድስ ተብሎ እንደሚጠሩ Schoemaker (1990:74) ይገልጻል።

ከእነዚህ አባባሎች የምንረዳው ሁሉም ኅብረተሰብ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆኑን ነው። ለምሳሌ ያህል ኤድስ ከልጃገረድ ከያዘ የመጀመሪያ ኤድስ ይባላል የሚለው አነጋገር ግልጽ የሆነው ትርጉም የግብረሥጋ ግንኙነት አድርጋ የማታውቅ ልጃገረድ ኤድስ ሊኖርባት እንደሚችል የሚያመለክት ነው። ይህም የኤች ኣይ ቪ መተላለፊያው የግብረሥጋ ግንኙነት በማድረግ ብቻ አለመሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ቫይረሱ "የመጀመሪያ" ለመሆኑ ግን ምንም ማረጋገጫ የለም። ነገር ግን የቀልዱ መልዕክት ልጃገረድ ዘንድም ቫይረሱ ሊኖር እንደሚችል ለማሳወቅ እና ከልጃገረድ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም በኤድስ ከመያዝ ያድናል የሚሉትን ለማስጠንቀቅ ነው።

ከትምህርት ቤት ከያዘ "ውጤት" ኤድስ ይባላል የሚለው ቀልድ ግልጽ የሆነው ትርጉሙ እንደሚታወቀው አንድ ተማሪ ትምህርቱን ምን ያህ እንደተረዳ ከሚረጋገጥበት አንዱ በመመዘኛ ፈተና ነው። የፈተናውም የሚገለጸው በውጤት በመሆኑ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው ቫይረሱ ይኑርበት አይኑርበት የሚረጋገጠው በደም ምርመራ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ ምርመራ የሚገለጸው "ውጤት" በሚል ስም በመሆኑ ይህንኑ ለማመልከት የተነገረ ቀልድ ነው። ነገር ግን የቀልዱ መልዕክት ትምህርት ቤት የሚገኝ ማህበረሰብ ስለ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ አመጣጥ ግንዛቤ ያለው ቢሆንም ይህ ማለት ግን ሁሉም ከቫይረሱ ነጻ ናቸው ማለት አይደለም የሚል ትርጉም አለው። በመሆኑም በትምህርት ቤትም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ መኖሩን የሚያመለክት ቀልድ ነው።

በሮናልድ ሬገን ከተጠቃ "ፕሬዝዳንታዊ" ኤድስ ነው፤ የሚለው አባባል ቀጥተኛ ትርጉሙ በፖለተካ የክብር ስም የሆነው ፕሬዝዳንት የሚለው ቃል ለኤድስ መሰጠቱን የሚያመለክት ነው። የቀልዱ መልዕክት አገሪቱን የሚመሩ የፖላቲካ ሰዎች በያዙት አመራር የተከበሩ ቢሆኑም ከቫይረሱ ነጻ ላይሆኑ ይችላሉ የሚል ነው።

ከዘፋኝ ከያዘህ "ባንድ" ኤድስ ይባላል የሚል አባባል ቀጥተኛ ትርጉም ስናይ ባንድ የሚለው ቃል የዘፋኞችን ስብስብ የሚያመለክት ነው። የቀልዱን መልእክት ስናይ ሙዚቀኞችም ኤድስ ሊኖርባቸው ይችላል የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ አስደሳች በሆነ የመዝናኛ ቦታዎችም በቫይረሱ መያዝ አጋጣሚ እንደሚኖር ለማመልከትና በመዝናኛ ቦታዎች በሚፈጸሙ ወሲባዊ ድርጊቶች ላይ ጥንቃቄ እንዲደረግ ታስቦ የተነገረ ነው።

ከእነዚህ አባባሎች የምንረዳውው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሁሉም ቦታና በየትኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ሊኖር እንደሚችል ለማሳወቅ ነው። በመሆኑም ሰዎችን በሥራቸው፣ በጨዋነታቸው፣ በሥልጣናቸው፣ በሚሠሩበት የሥራ አካባቢ፣ … ወዘተ ብቻ አይተን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ነጻ ናቸው ወይም አይደሉም ለማለት እንደማይቻልና በማንኛውም ጊዜና ቦታ ራሳችንን ከቫይረሱ ሥርጭት ለመካላከል ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ያስገነዝቡናል።

በሌላ መልኩ ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት በተደረገው እንቅስቃሴ በአገር ውስጥ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መጽሓፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጦችና በራሪ ጽሑፎች ተዳሰዋል። በሂደቱም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሥነቃል መረጃዎች ተገኝተዋል። እነዚህም ቢሆኑ ለዚህ ጥናት አስተዋጽኦ ሰለአላቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ከእነዚህ ውስጥ "የኤድስ ፎክሎር"[25] በሚል ርእስ የተገኘው የጽሑፍ መረጃ ስለ ኤድስ ቀልድ እንዲህ ይላል። በአንድ ወቅት ኤች ኣይ ቪ በደማቸው ውስጥ ላለ ወገኖች በተቋቋመ ግብረሰናይ ድርጅት አማካይነት እርዳታ ሲሰጥ የሰሙ አንዲት ሴትዮ ለድርጅቱ ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ። ድርጅቱም ለመርዳት ኤች ኣይ ቪ በደማቸው ውስጥ ሊኖር እንደሚገባ ይነግራቸውና ሲመረመሩ ከቫይረሱ ነፃ ሆኑ። ይህን ውጤት እንደሰሙ ድንግጥ ብለው "አይ እግዜር ይህንንም እንጀራ ብለህ ትከለክለኝ? " አሉ ይባላል።

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ቀልድ ደግሞ ኮንዶምን የሚመለከት ነው። ይኸውም በአንድ አካባቢ በድህነት የሚኖሩ እናት እና ልጅ ሁሌም የሚመገቡት ሽሮ ወጥ ብቻ በመሆኑ ልጅየው ሽሮ መመገቡ ስለሰለቸው እናትየዋ ሽሮ ከማዘጋጀት እንዲቆጠቡ አስቦ "እማዬ ሽሮ ኤች ኣይ ቪ ያሲዛል ተባለ እኮ።" ሲላቸው፤ እናትየዋም "አይዞህ ልጄ በኮንዶም ትበላዋለህ።" አለችው አሉ። (ኃይለማርያም አብዲሣ፣ 2006፡ 73)።

[25] ተመስገን ምንዋጋው (2004) በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኮርስ ማሟያ ካቀረበው የተገኘ።

ከእነዚህ ሁለቱ ቀልዶች ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ከድህነትም ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑንና በኅብረተሰቡ ውስጥ የከፋ የኑሮ ችግር መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው። በተለይም የመጀመሪያውን ቀልድ ስናይ የኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ላለው ወገን የሚደረገው ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ቫይረሱ የሌለባቸው ሰውም ከችግሩ አኳያ በሽታውን የሚመኝ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለእርዳታው ሲባል ድጋፉን የሚቀበለውም ሆነ ከቫይሱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በልዩ ልዩ መልኩ እርዳታ የሚያስተባብር ክፍል የበሽታውን መኖር እንደሚመኙ አንዳንድ የጽሑፍና የሰው ማስረጃዎች ይገልጻሉ። ነገር ግን ይህ ግላዊ አመለካከት እንጂ እንደ ገዥ አስተሳሰብ የሚታይ አይደለም።

ሌላኛው ቀልድ ደግሞ ሦስት መነኮሳት ተሰብስበዉ ስለሚያወሩት የወሲብ ጉዳይ ነው። አንደኛዋ መነኩሴ፡- "ባለፈዉ ጊዜ የአባን ክፍል ሳፀዳ ምን እንዳገኘሁ ታውቃላችሁ? ብላ ትጠይቅና እራሷ መልስ ስትሰጥ፣ ብዛት ያላቸው የወሲብ መፅሔቶች ትላለች።" የቀሩት ሁለቱም በአንድነት፡- "ታዲያ ምን አደረግሻቸው?" (በመገረም ጠየቋት)። ይህኔ "ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጨመርኳቸዋ!" በማለት ትመልሳለች። ሁለተኛዋ መነኩሴ፡- "አንቺ ይህን ትያለሽ! እኔ ኮታቸዉ ኪስ ውስጥ ፓኬት ኮንዶም አላገኘሁም እንዴ!" ትላለች። ይህን ጊዜ ሶስተኛዋ መነኩሴ፡- "የሚገርም ነገር ነዉ! እና ምን አደረግሽው?" ብላ ትጠይቃለች። ሁለተኛዋ (ተጠያቂዋ) መነኩሴ፡- "ሁሉንም ቀስ አድርጌ በመርፌ በሳኳቸው!" ብላ ትመልሳለች። በዚህ ጊዜ ሶስተኛዋ መነኩሴ ራሷን ሥታ መሬት ላይ ተዘረረች (ይርጋ ደበበ፣ 2002:19-20)። የመነኮሳቱን ቀልድ ስናይ በድብቅ የሚከወን ወሲብ ለቫይረሱ እንደሚያጋልጥና በሽታው የሃይማኖት መሪዎችንም ሳይለይ ሁሉንም የሚይዝ መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነቶቹ ቀልዶች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና እያዝናኑ በማስተማር የጎላ ሚና ያላቸው በመሆናቸው በሥነቃል ዙሪያ በጥናትና ምርምር ቢደገፉ በርካታ አስተማሪ የሆኑ ጉዳዮችን ማግኘት እንደሚቻል ያመለክታል።

ከዚህ በመቀጠል ወደ ዋናው የጥናቱ ርዕሰ በመምጣት ከዚህ ጥናት ጋር ከርዕስ እና ከጥናቱ ቦታ አኳያ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶችን በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.4. በጥናቱ ቦታ እና ርዕሰ ላይ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ከጥናቱ ቦታ እና ርዕስ አኳያ የተከሄዱ ቀደምት ሥራዎች የተደሳሱበት ነው። ስለዚህ የጥናቱን አጠቃላይ ትኩረት እና ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2. 4. 1 የጥናቱን ቦታ (ማህበረሰብ) የሚጋሩ ቀደምት ጥናቶች

የቱለማ ኦሮሞ ሠፍሮ በሚገኝበት አከባቢ ከባህልና ቋንቋ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አንዳንድ ጥናቶች ተደርገዋል። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር የተዳሰሱት ከቦታ አኳያ የቱለማን ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በፎክሎር ዙሪያ ትኩረት ያደረጉት ሥራዎች ናቸው። በዚሁ መሠረት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች የተካሄዱ ጥናቶች በዝርዝር እንመለከታለን። በመሆኑም በቅድሚያ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ በቱለማ አከባቢ የተደረጉ ጥናቶችን ከነርዕሰ ጉዳያቸው እናያለን።

ታደሠ ዓለሙ "የሰላሌ ኦሮሞ የፍቅርና የሠርግ ዘፈን ግጥሞች" በሚል ርዕስ በ1974 ዓ.ም. ያደረገው ጥናት፣ አበባየሁ ደምሴ "የኦሮሞ ረገዳና ዲቺሣ ዘፈን ግጥሞች በየረርና ከረዩ አውራጃ በሚል ርዕስ በ1974 ዓ.ም. ያከናወነው ጥናት፣ መኮንን ብሩ "በመናገሻ አውራጃ በአደዓ በርጋ ወረዳ በገዳ ሥርዓት የሚዘፈኑ የኦሮሞ ዘፈኖች ይዞታዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በ1981ዓ.ም. ያካሄደው ጥናት እና ደረጀ ተሰማ "በቢሾፍቱ ከተማ የእሬቻ በዓል አከባበር ሥነ-ቃላዊ ይዘት" በሚል ርዕስ በ1998 ዓ.ም. ያደረገው ጥናት ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በቱለማ ኦሮሞ አከባቢ በፎክሎር ላይ ትኩረት ከማድረጋቸው አንጻር ለዚህ ጥናት መረጃዎችን በመስጠት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ1997 ዓ.ም ሙሉጌታ ነጋሣ፣ "በአደኣ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረ-ጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር " በሚል ርዕስ በቱለማ ኦሮሞ ፎክሎር ላይ ያተኮረ በአማርኛ ቋንቋ የተ ደረገው ጥናት ነው። ለጥናቱ ጠንካረነት የሚከተሉት ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው። ይሄም የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ቃለ-መጠይቅ እና ምልከታ ሲሆኑ ባህላዊ እና ማህበራዊ አውዶችን መሠረት በማድረግ ከልዩ ልዩ መቼቶች የተገኘ መረጃ መሆኑን ጥናቱ

ያመለክታል። ከዚሁ አኳያ በአደአ ሊበን የግጭት አፈታት "ሴረ ጉማ" በማህበረሰቡ ባህላዊ እሴቶች (በእግዞታ፣ በምርቃት፣ በመሀላና በእርግማን ወዘተ...) የሚከወን ሲሆን ከዋኔው የራሱ ተሳታፊዎች፣ መቼቶች፣ አውዶችና ትዕምርቶች እንዳሉት በጥናቱ ውስጥ ተገልጸዋል። አውዳዊ ከዋኔዎቹም በፎቶግራፍ ተደግፈው ቀርበዋል። ከመቼቶቹ ውስጥ ለእሬቻ ክብረ-በዓል ከልዩ ልዩ ቦታዎች የሚመጡት ልጆች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች በኦሮሞ የዘፈንና የጭፈራ ዓይነቶች በዓሉን እንደሚያደምቁ ተብራርቷል። በመሆኑም ጠለቅ ያለ ምርምር ከመሆኑ አንጻር የመጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም። ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችም ተገኝተውበታል።

በተያያዘ ሁኔታ በሥነ-ትምህርት ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል ስር ተከፍቶ ለነበረው የአፋን ኦሮሞ ንኡስ ዘርፍ የማስተርስ ፕሮግራም ከቀረቡ ጥናቶች ውስጥ የAbbabaa Margaa "Qaaccessa Sirba Gadaa" (የገዳ ዘፈን ትንተና) እ. ኤ. አ.በ2007 ያደረገው ጥናት እና በዚሁ ዘመን የImaanaa Bayyanaa "Qaaccessa Qabiyyee Faaruu Amantii Duudhaa Oromoo" (የኦሮሞ ሀገረሰባዊ እምነት መዝሙሮች ይዘታዊ ትንተና) ጥናት በቱለማ ኦሮሞ ሥነቃል ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በአፋን ኦሮሞ የተጠኑ ሥራዎች እንደሆኑ ይገመታል። በመሆኑም የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ሁኔታዎችን በማስተዋወቁ ረገድ ሚና የነበራቸው ሲሆን ለዚህ ጥናትም ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመስጠት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በአጠቃላይ እነዚህ ሦስቱም የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በቱለማ ኦሮሞ ላይ በማትኮራቸው ከቦታ፣ ከጥናት ዘዴያቸው፣ ከመረጃ አሰባሰብና መተንተኛ ቲዮሪያቸው አኳያ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት አላቸው። ይሁን እንጂ ካተኮሩበት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር እኔ ካደረኩት ጥናት ጋር በጣም የተለያዩ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ የትምህርት መርሐ-ግብር ማሟያነት በቱለማ ኦሮሞ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን እንመለከታለን።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ (ፎክሎር) ጉዳዮች ላይ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተደረጉ ጥናቶችን ስንመለከት የጥላሁን ተሊላ "የቱለማ ኦሮሞ መርሣ (ሊሚናል) ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም. በአማርኛ ቋንቋ የተደረገው ጥናት

በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ደረጃ በሀገር ውስጥ ከተደረጉ ጥናቶች በቱለማ ኦሮሞ ላይ ከማተኮሩ አኳያ ግንበር ቀደም ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ Desta Desalegn “A Functional Study of Tulama Oromo Oral Prose Narrative”በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ2015 እና Emana Beyene “Hist oricl Documentation and Thematic Analysis of Waqeffannaa Religion and Songs Among Tuulamaa Oromo”በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ2015) ሁለቱም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያደረጉት ጥናቶች በቱለማ ኦሮሞ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ከማተኮራቸው የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚሁ አኳያ እነዚህ ጥናቶች ካተኮሩበት ርዕስ አኳያ በቱለማ ኦሮሞ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ጉዳዮች ይበልጥ እንዲታወቁ ከማድረጋቸውም በላይ ሌሎችንም የፎክሎር ተመራማሪዎች የሚጋብዙ ናቸው። ሦስቱም በፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች በመሆናቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው እያንዳንዳቸው ባተኮሩበት ርዕስ ጉዳይ ይለያያሉ። ከዚሁ አንጻር የእያንዳንዳቸውን ርዕሰ ጉዳይ ትኩረት፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ እና መተንተኛ ቲዮሪ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የጥላሁን ጥናት ትኩረት ያደረገው “በቱለማ ኦሮሞ የመርሳ ወቅቶች” ላይ ሲሆን እነዚህም በአብዛኛው የሚገለጹት በልዩ ልዩ ከበራዎች እንደሆኑ በመጥቀስ ሁሉን የፎክሎር ዘርፎች የዳሰሰ ቢሆንም በቁሳዊ ባህሎች ላይ ያተኮረ ነው። የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎቹ ከደስታ ጋር ተመሳሳይ ሆነው የሚለየው በጉዳ ይ ምርመራ እና ሚታ ፎክሎር ዘዴዎችን በመጨመሩ ነው። የመተንተኛ ቲዮሪዎችን በሚመለከት ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችን የዳሰሰ ሲሆን በዋናነት ትኩረት ያደረገው በለውጥና ቀጣይነት እንዲሁም ተምሳሌት ቲዮሪዎች ላይ ነው። በማጠቃለያው የቱለማ ኦሮሞ መርሳ (ሊሚናል) ወቅቶች ቀጣይነታቸው የሚረጋገጠው በከበራዎች መሆኑን ይገልጻል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ቦታዎች ከከተማ መስፋፋት ጋር እና በሌሎች ምክንያቶች የቀድሞ ቦታ ለሌላ ጉዳይ እየተወሰደ መሆኑን በመጥቀስ እነዚህ ጉዳዮች ባህላዊ እውቀቶቹ እየተረሱ እንዲመጡ የሚያደርጉ ተግባራት መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። የጥላሁን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በቱለማ ኦሮሞ ላይ ትኩረት በማድረጉ፣ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች እና የመተንተኛ ቲዮሪዎች በተወሰነ መልኩ

ተመሳሳይነት አለው። ይሁን እንጂ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ፣ በዓላማ እና ውጤት ከእኔ ጋር ልዩነነት አለው።

የደስታ ደሳለኝ ጥናት "በቱለማ ኦሮሞ ተረክ" ላይ የተመሠረተ ሆኖ ተረቶችን፣ ጥንተ ታሪክን እና ጥንታዊ እምነትን የሚመለከት ነው። መረጃዎችን ያሰበሳበው በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን ማህበረሰቡ ባህላዊ ትውፊቱን ከሚያስቀጥልባቸው መንገዶች ውስጥ ልዩ ልዩ ክብረበዓላት እንዳሉት ጠቁሟል። መረጃዎችን ከአውዳዊ እና ከተግባራዊ ቲዮሪዎች አንጻር የተነተናቸው ሲሆን የሥነቃል ዓይነቶቹ ልጆችና ወጣቶች ማንነታቸውን እንዲያውቁ፣ የአእምሮ ብስለት እንዲኖራቸው፣ የማህበረሰቡን ወግና ባህል እንዲጠብቁ ለማድረግ የማስተማር አገልግሎት እንደሚሰጡ የጥናቱ ውጤትያመለክታል። በመሆኑም የደስታ ጥናት ከቦታ፣ ከመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎቹ እና መተንተኛ ቲዮሪዎች አኳያ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከዓላማ እና ውጤት አንጻር ይለያል።

የኢማና በየነ ጥናት ትኩረት "በቱለማ ኦሮሞ ዋቄፈና እምነት ክብረ-በዓላት ልማዳዊ ድርጊቶችና መዝሙሮች ታሪካዊ አመለካከት" ከፎክሎር አኳያ የሚመለከት ሲሆን ጥናቱ ኢትኖግራፊክ የሆነ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። መረጃዎቹን ያሰባሰበው በጥልቅ ቃለ-መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እና ሰነድ ምርመራ ነው። ከዋቄፈና ጋር ተያይዞ በተከበሩ እሬቻ፣ ጉማ ሥርዓት፣ ቃሉ ሥርዓት፣ አቴቴ እና ወዳጃ ክብረ-በዓላት ላይ በመገኘት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች ከነተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው በቪዲዮ ካሴት መቀረጻቸውን ጥናቱ ያመለክታል። እነዚህ መረጃዎች ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች (narrative theory, conflict theory, comparative folklore model and functionalism)አንጻር ተተንትነዋል። የዋቄፈና እምነት ልማዳዊ ዲርጊቶችና መዝሙሮች በቱለማ ኦሮሞና ሌሎችም የኦሮሞ ጎሳዎች የየዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሠላምና ደህንነትን አስተማማኝ በማድረግ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማጠናከር፣ አንድነትንና የጋራ መግባባትን በመፍጠር እንዲሁም ተከባብረውና ተቻችለው መኖርን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። የኢማና ጥናት ከላይ በሁለቱ ጥናቶች እንደተመለከትነው በተወሰነ መልኩ ከጥናቴ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በሌላው አይገናኝም።

በአጠቃላይ እነዚህ በፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ደረጃ በቱለማ ኦሮሞ ላይ የተደረጉ ጥናቶች በዋናነት የፎክሎር ዘውጎችን በመዳሰሳቸው እና ከዚህ ጥናት ጋር ባላቸው ግንኙነቶች በክለሳ ድርሳናት፣ በአጠናን ዘዴ፣ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ በንድፈ ሀሳብ ዳሰሳ እና በመተንተኛ ቲዮሪዎች መረጣ፣ ለዚህ ጥናት ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ በጣም የጎላ ነው። ይህን እንጂ በርዕስ ጉዳያቸው ሦስቱም ከዚህ ጥናት የተለዩ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ ተቀራራቢ የሆኑትን ጥናቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2. 4. 2 ርዕሰ ጉዳዩን የሚጋሩ ቀደምት ጥናቶች

በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ስር ለመጥቀስ እንደተሞከረው ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ /ኤድስን አስመልክቶ በቱለማ ኦሮሞ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ላይ ጥናቶች አልተደረጉም። በዚህ መስክ በተደረገው ጽሑፋዊ ዳሰሳ በቀጥታ ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገው በቱለማ አካባቢ የተጠኑ ሥራዎችን እስካሁን አላገኘሁትም።

ይሁን እንጂ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነት ያለው ከድረገጽ[26] የተገኘ የወርቅነህ ቀልቤሳ (2014) ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የጥናቱ ርዕስ የፍቅር ዘፈኖችን የሚመለከት ሲሆን ትኩረት ያደረገው በኦሮሚያ ክልል አምቦ፣ ቶኬ ኩታዬ፣ ኮፈሌ፣ አርሲ እና ቦረና ላይ ነው። የተሰበሰቡ የፍቅር ዘፈኖች የጋራ እና የግል በማለት በሁለት ቡድን የተመደቡ ሲሆኑ እነሱም በሴቶች የሚዘፈኑ፣ በወንዶች የሚዘፈኑ እና በሁለቱም ፆታ የሚዘፈኑ ተብለው በማብራሪያ ተደግፈው ተተንትነዋል። በትንታኔው ውስጥ ለተምሳሌታዊ እና ለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል።

ጥናቱ ከማህበረሰብ አንጻር በኦሮሞ ላይ በማተኮሩና ከርዕሰ ጉዳይ አኳያ ደግሞ የፍቅር ግንኙነት ዘፈኖች የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የቀረበ ግንኙነት አለው። ከዚሁ አኳያ ለዚህ ጥናት ተጓዳኝ ጽሑፋዊ ቅኝት የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን በመስጠት ያበረከተው አስተዋጽኦ ከሁሉም በላይ እጅግ በጣም የጎላ ነው። ይሁን እንጂ ጥናቱ ከቦታ አኳያ በቀጥታ በቱለማ ኦሮሞ ላይ አላተኮረም። ከርዕሰ ጉዳዩም አንጻር

---

[26] Council for the Development of Social Science Research in Africa, date accessed 21/11/2014.

የፍቅር ዘፈኖችን እንጂ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አላካተተም። በአጠቃላይ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ ቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን ሁሉንም አልዳሰሰም።

በመሆኑም የእኔ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ከዘፈኖችም በተጨማሪ ምሳሌያዊ ንግግሮችንም የተመለከተ ሲሆን ከማህበረሰብ አኳያ ደግሞ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል መረጃዎችን ያካተተ ነው። በሌላ መልኩ ጥናቴ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ስርጭት በስፋት በሚገኝበት አዲስ አበባ ከተማ ጋር ተያይዘው ባሉ የቱለማ ኦሮሞ ላይ በማተኮሩና በተወሰነ ቦታ ሆኖ በጥልቀት በመካሄዱ ለየት ያለ ነው።

በሌላ መልኩ ከወሲብ እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርምሮች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች ተከናውነዋል። ከእነዚህ ውስጥ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጉዳዮችን በማንሳታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ባላቸው ግንኙነት 9 የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ እና 43 የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በድምሩ 52 ጥናቶች ተዳሰዋል።

ወሲብን አስመልክተው የተደረጉ ጥናቶች ከአልኮልና አደንዛዥ ዕጽ ጋር ተያያይዞ በሚፈጸመው ልቅ ግብረ-ሥጋ ግንኙነቶች የተነሳ ላልተፈለገ እርግዝና መዳረግን፣ ለልዩ ልዩ አባለ ዘር በሽታዎችና ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ መጋለጥን እንዳስከተሉ የሚገልጹ ሲሆኑ በአንዳንዶቹ ጥናቶች ውስጥ የሥነቃል ዓይነቶች ይገኙበታል።

ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የተመለከቱ ጥናቶች ሁሉም በከተሞች የተከናወኑ ሲሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው አዲስ አበባ ነው። ይህም በዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያቶች ውስጥ እንደተገለጸው በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት አዲስ አበባ ከፍተኛውን ድርሻ መያዟን በ(OSSREA, 2008:7; CSA, 2011) የተገለጸውን ትክክለኛነት የሚያመለክት ሲሆን በሌላ መልኩ የቫይረሱን ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ መብዛቱን ከመስክ የተገኙት የሥነቃል መረጃዎችም ያሳያሉ።

የእነዚህ ጥናቶች ርዕሰ ጉዳዮችን በተመለከተ ጠቅለል በላ መልኩ ሲታዩ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ሴቶችን የሚመለከቱ፣ ከቫይረሱ ጋር በሚኖሩ አባትና እናት በሌላቸው ሕጻናት (Orphan) ላይ ትኩረት ያደረጉ እንዲሁም በወጣቶች እና ጎልማሶች ወሲባዊ ባህርይ ላይ እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶችን ያካተቱ ናቸው።

ሌሎች ጥናቶች ደግሞ የተጠቁ ሰዎችን ብዛት በማሳየት ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እያደረሰ ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ቀውሶች የሚያትቱ ናቸው። በመሆኑም በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ የተጠቁት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው።

ከእነዚህ 52 ጥናቶች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው 5 ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት እና 6 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተደረጉ ጥናቶች ናቸው። ከዚሁ አኳያ በቅድሚያ በመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተደረጉ ጥናቶችን ቀጥሎም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተካሔዱትን ጥናቶች በዝርዝር እንመለከታለን።

አብዮት ኩምሳ በ1992 ዓ.ም. "ሲ. ቪ. ኤም ከኢተዮጵያ ሬድዮ ጋር በመተባበር ከ1987 እስከ 1990 ዓ.ም. በዝሙት አዳሪዎችና በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ ያቀረባቸው ጭውውቶች" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለትያትርና ጥበባት ትምርት ክፍል ባቀረበው ጥናት በጭውውቱ ውስጥ ያሉ ገጸባህሪያት ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት የነበራቸው ሚና ተተንትነዋል።

ነብዩ ተድላ በ1993 ዓ.ም. "ሬድዮ ፋና ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሰጠው ሽፋን" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ባቀረበው ጥናት ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን መሠረት ያደረጉ የሬድዮ ፋና ፕሮግራሞች ዝግጅትና አቀራረብ ላይ ትንተና አድርጓል።

ጀቤሳ ዲልቦ በ1995 ዓ.ም. "ኤች ኣይ ቪ/ አድስን አስመልክተው በሬድዮ ፋና የተላለፉ የኦሮምኛ አዝናኝና አስተማሪ ተከታታይ ድራማዎች" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለትያትርና ጥበባት ትምርት ክፍል ባቀረበው ጥናት ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ ድራማዎች ካስተላለፉት መልዕክት አንጻር ቃኝቷል።

በ1998 ዓ.ም እስከዳር ዓለሙ " በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚነገሩ ፀያፍ ቀልዶች" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናት ነው። አጥኚዋ መረጃዎቹን ያሰባሰበችው በመጠይቅ እና በቃለ-መጠይቅ ሲሆን የወሲብ አፈጻጸምን በሚመለከት በወንዶች ላይ የሚነገሩ እና በሴቶች ላይ የሚነገሩ በማለት በሁለት ምድብ ከፍላለች። ከእነዚህ ውስጥ 29 ፀያፍ ቀልዶችን የግብረ-ስጋ ግንኙነቶች የፍላጎት አለመጣጣም፣ ከጋብቻ ውጪ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረግን አለማወቅ እና በተመሳሳይ ፆታ መካከል የግብረ-ስጋ ግንኙነት

መፍጠር በሚሉ አራት ርዕሶች በመክፈል ተንትናለች። በትንተኔዋ ውስጥ የመተንተኛ ቲዮሪ በማለት ያስቀመጠችው አቅጣጫ የለም።

የእስክዳር ጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ከወሲብ ጋር ተያያዥ ከመሆኑ እና በአዲስ አበባ ከተማ ከመደረጉ አንጻር በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ለዚህ ጥናት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በአጠቃላይ እነዚህ አራቱም የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስና የግብረ-ስጋ ግንኙነትን የሚመለከቱ ርዕሶች በመሆናቸው በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት በልዩ ልዩ መልኩ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ሌላው በርዕሰ ጉዳይ ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በ1997 ዓ.ም ሙሉቀን ኡመር "በደቡብ ክልል፣ በጌዲኦ ዞን ከኤችአይቪ ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ሥነቃል" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ነው።

ሙሉቀን መረጃዎቹን ያሰባሰበው ጥናቱ በተካሔደበት ቦታ በመገኘት ሰዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ 40 የሥነቃል መረጃዎችን ሰብስቧል። እነሱም የበሽታው ጉዳት፣ መደረግ ያለበት፣ የበሽታው ሥርጭት፣ የበሽታው ስያሜና ክስተት እንዲሁም ሌሎች በተሰኙ አምስት ክፍሎች ተመድበዋል። በእነዚህ ምድቦች ውስጥ አባባሎች፣ ቃል ግጥሞች እና ቀልዶች ተደበላልቀው ይገኙበታል።

በዚሁ መሠረት የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች በሙሉ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ካላቸው አገልግሎት አንጻር በተግባራዊ ቲዮሪ ተተንትነዋል።

የሙሉቀን ጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች መሆኑ፣ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን መከተሉ እና የመረጃ ማሰባሰቢያ ዜደዎቹም ምልከታና ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም ተግባራዊ የመተንተኛ ቲዮሪን በመጠቀሙ መረጃዎችን በመስጠት ለዚህ ጥናት ያበረከተው አስተዋጽኦ በቀላል የሚገመት አይደለም።

ይሁን እንጂ ከዚህ ጥናት ጋር ሲታይ የጥናቱ ቦታ እና ተጠኚ ማህበረሰብ በሚመለከት በጣም የተለያዩ ናቸው። ይህም የሙሉቀን በደቡብ ሕዝቦች ጌዲኦ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ቱለማ ኦሮሞ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በመሆኑም በባህል እና በቀንቋ የተለያዩ ማህበረሰቦች ናቸው። ሌላው ይህ ጥናት ከሙለቀን የሚለይባቸው ምክንያቶች በጥናቱ ዓላማ፣ በክለሳ ድርሳናት ዳሰሳ፣ በጥናት ዘዴው፣ በመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች እና መተንተኛ ቲዮሪዎች፣ ሰፊ ዳሰሳ የተደረገበት በመሆኑ ነው።

ከዚህ በመቀጠል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች ርዕሰ ጉዳያቸው ከወሲብ እና ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን እናያለን።

ስንቅነሽ አጣለ በ1997 ዓ.ም "ሙስና፣ ስደትና ኤች ኣይ/ ቪ ኤድስ ከ1990 እስከ 1996 ዓ.ም በታተሙ የአማርኛ ልቦለዶች" በሚል ርዕስ ለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረበችው ጥናት ውሰጥ ኤች ኣይ ቪ/ አዴስን በሚመለከት በጭላንጭል ልቦለድ ገጸባህሪያት ላይ ያጠነጠነ ትንተና አካሂዳለች። በዚሁ መሠረት ቫይረሱ እንዳይስፋፋ ጥንቃቄ የሚያደርጉ ገጸባህሪያት የመኖራቸውን ያህል በበቀልና በግድየለሽነት ለበሽታው ሥርጭት መባባስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ መኖራቸውን ገልጻለች። ከዚህ የምንረዳው በገሃዱም ዓለም እነዚህ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ አመለካከቶች በማህበረሰቡ ውስጥ መኖራቸውን የሚያሳይ ጥናት ነው። ከዚህ አንጻር የስንቅነሽ ጥናት መረጃዎችን በመስጠት ለዚህ ጥናት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ትዝታ አበበ እ. አ.አ 2011 ዓ.ም " Sexuality Related Behavirial Risk to HIV/ AIDS Examining the Expreience of People Abusing Home made Alchol Beverages." በሚል ርዕስ ለማህበራዊ ሳይንስ (Social Science) ትምህርት ክፍል ያቀረበችው ጥናት ያከሔደችው በሰሜን ሸዋ ዞን ጫጫ ከተማ ላይ ነው። የጥናቱ ትኩረት በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ መጠጦች (ጠላ፣ ጠጅ እና አረቄ) ባህርይን በመቀየር ለወሲብ እንደሚያነሳሱ እና ለኤች ኣይ ቪ/ አዴስ እንደሚያጋልጡ የሚገልጽ ነው። መረጃዎቹን ያሰባሰበችው ሁለት በተለያዩ ጊዜያት ባደረገችው ጥልቅ ቃለ- መጠይቅ ሲሆን በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉት እድሜያቸው ከ24 እስከ 42 የሆኑ ወንዶች ብቻ ናቸው።

መረጃ አቀባዮቿ የገለጹት ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ እንዳላቸውና በተለይም አረቄ ሲጠጡ ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ፍላጎት እንደሚነሳሳባቸውና ከቡና ቤት ሠራተኞች ጋር ልቅ የሆነ ግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደሚፈጽሙ ነው። አጥኚዋም ከእነዚህና ሌሎችም ካሰባሰበቻቸው መረጃዎች በመነሳት ባህላዊ የአልኮል መጠጦቹ ባህርይ የመለወጥ አቅም እንዳላቸውና በዚህም የተነሳ ልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት በማድረግ ለኤች ኣይ ቪ እንደሚጋለጡ በትንታኔዋ ውስጥ ገልጻለች።

ጥናቱ በቱለማ አጎራባች ወረዳ ጫጫ ከተማ በመደረጉና በተለይም በባህላዊ መጠጦች የተነሳ ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መጋለጣቸው ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ

ይመሳሰላል። በመሆኑም ለዚህ ጥናት በልዩ ልዩ መልኩ አስተዋጽኦ አለው። ይህን እንጂ ከዚህ ጥናት ጋር ከላይ በሌሎቹ ጥናቶች ውስጥ እንደተገለጸው በርከታ ልዩነቶች አሉ።

በጅጋ ተካ (የዚህ ጥናት አቅራቢ) እ.አ.አ. በ2008 ዓ.ም በአፋን ኦሮሞ "Aadaa Saalaa Oromoo Godina Shawaa Kaabaa (Salaalee), Aanaa Barrak" /የኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ሰሜን ሸዋ ዞን፣ በበረክ ወረዳ በሚል ርእስ በሥነ-ትምህርት ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል ለአፋን ኦሮሞ የማስተርስ ፕሮግራም ንዑስ ዘርፍ ባቀረበው ጥናት በተረቶች፣ ዘፈኖች እና ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ያተኮረ ሲሆን በእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱም ይገኙበታል። ከዚሁ አንጻር ለዚህ ጥናት አንዱ አነሳሽ ምክንያት መሆኑ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ተገልጿል።

ልዩነቶችን በተመለከተ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን መሠረት በማድረግ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች እንጂ የጥናቱ ዓለማ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያካተተ አይደለም። የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችም ስንመለከት የቡድን ተኮር ውይይትን ያላካተተ ነው። በጥናቱ ውጤትም ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶቹን የሚመለከቱ ሥነቃሎች ትንተና ላይ እንጅ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ አልነበሩም። በመሆኑም ይህ ጥናት እነዚህንና ሌሎችንም በርካታ ክፍተቶች የሚሞላ በመሆኑ ከቀድሞው ጥናት ይለያል።

ብዙአየሁ አየለ እ.አ.አ. 2009 ዓ.ም. "Vulnerabilty of Woman to HIV/AIDS: The Lived Experience of Woman Living with HIV/AIDS in Fiche Town." ርዕስ ለማህበራዊ ሥራ (Social Work) የትምህርት ክፍል ያቀረበችው ጥናት በኦሮሚያ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ፍቼ ከተማ ላይ ከኤች አይ ቪ ጋር በሚኖሩ ሴቶች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ጥናት ነው። ጥናቷ ዓይነታዊ ምርምር በመሆኑ መረጃዎችን ያሰባሰበችው በቦታው በመገኘት ቫይረሱ ካለባቸው ሴቶች በጥናቱ ውስጥ በኢላማ ናሙና የተካተቱትን 10 ሴቶች ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ነው። በዚህም መረጃ አቀባዮቿ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ስሰጡ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዴት እንደያዛቸው በትረካ የገለጹበት ይገኝበታል። ቡድን ተኮር ውይይትን በተመለከተ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ካለባቸው ሴቶች እና ከማህበረሰቡ ተወካዮች ጋር ውይይት በማከሔድ መረጃዎችን ሰብስባለች። ከሰበሰበቻቸው መረጃዎች ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች ይገኙበታል። የተሰበሰቡ መረጃዎችንም ከማህበረ ኢኮኖሚ እና ባህላዊ ቲዮሪዎች (Socio Economic and Cultural Theories) አኳያ ተንትናለች።

የጥናቱም ውጤት የሚያሳየው ሴቶች በቫይረሱ መያዛቸውን ያወቁት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሲሆን ይኸውም በተደጋጋሚ በሽታ በመታመማቸው ተጠራጥረው የኤች አይ ቪ ምርመራ ሲያደርጉ፣ በእርግዝና ምክንያት ሲመረመሩ፣ የትዳር ጓደኛቸው በከፍተኛ ህመም በመሞቱ በጥርጣሬ ሲመረመሩ መሆኑን በትንታኔዋ ውስጥ ገልጻለች። ከዚሁ አንጻር ጥናቷ በልዩ ልዩ መልኩ ለዚህ ጥናት የበኩሉን አስተወጽኦ አበርክቷል።

ይሁን እንጂ ጥናቷ የተካሄደበት ደረጃ፣ ርዕሰ ጉዳዩ፣ ተጠኚ ማህበረሰብ (ሴቶች ላይ ብቻ መተኮሩ) ከዚህኛው ጥናት የተለየ ነው።

ሐና ተገኝ እ.አ.አ በ2010 ዓ.ም “The Interface Between Violence Against Women and HIV/AIDS: The Experiences of HIV positive Women beneficiaries of the society for Women and AIDS in Africa- Ethiopia” በሚል ርዕስ ለፆታ ጥናት ኢንስቲዩት (Institute of Gender Studies) ትምህርት ክፍል ባቀረበችው ጥናት ውስጥ መረጃዎቹን ያሰበሰበችው በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን ከመረጃዎቹ ውስጥ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚነገሩና የሚዘፈኑ የሥነቃል ዓይነቶች ይገኙበታል። በሌላ መልኩ በስድብ፣ በማንቋሸሽና በማዋረድ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች በቫይረሱ በተጠቁ ሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደፈጠሩ ገልጻለች። በዚሁ የተነሳ በበሽታው የተጠቁ ሴቶች በተለያዩ ሁኔታዎች የሥነልቦናዊ አመለካከት ጉድለት እንደሚታይባቸው ከሥነልቦናዊ ቲዮሪ አኳያ ተንትናለች። የሐና ጥናት ከላይ ከተገለጹት ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ አኳያ ሲታይ በተሻለ ስፋትና ጥልቀት የቀረበ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ያበረከተው አስተዋፅኦ የጎላ ነው። ጥናቷ በቀጥታ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ላይ ሳይሆን ከርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቀረበ በመሆናቸው ከዚህኛው ጥናት ጋር ልዩነት አለው። ተጠኚ ማህበረሰብም በሚመለከት እንደዚሁ ልዩነት አለ።

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተካሔዱ አሥራ አንዱም ጥናቶች በተጠኑበት ደረጃ እና ባተኮሩበት ርዕሰ ጉዳይ የየራሳቸው ጠንካራ ጎኖች አላቸው። ይህን እንጂ እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው ክፍተቶች አሏቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት በዚህ ደረጃ ሲካሔድ አዲስ ከመሆኑም በላይ ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች በተሻለ ሁኔታ በስፋት እና በጥልቀት የተካሄደ በመሆኑ በሁሉም ላይ የታዩትን ክፍተቶች በመሙላት የተሻለ ውጤት የተመዘገበበት ነው።

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ በውጭው ዓለምም ሆነ በአገራችን ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ጥናቶች የሚያሳዩን በወሲብ ዙሪያ ኅብረተሰቡ ያለውን አስተሳሰብ እና አመለካከት ለማወቅ እንደሚረዱን እና ማህበረሰቡን ልናስተምርበት የምንችል አገር በቀል የእውቀት ዘርፍ መሆናቸውን ነው። በሌላ መልኩ በጥናቱ አካባቢ እና ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች በአንድ በኩል የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮችን በማስተዋወቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በሌላ መልኩ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተደረጉ ጥናቶች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ / ኤድስን በሚመለከት ለሚነገሩና ለሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ጥናት በግብአትነት ያገለገሉ ናቸው። በመሆኑም እስካሁን ድረስ የተገኙትን ጠቃሚ ሀሳቦችን በመያዝ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተግባራዊ የተደረገውን ስልት እና የዘዴዎቹን አፈጻጸም ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን።

ምዕራፍ ሦስት

3. የጥናቱ ስልት እና ዘዴ

ይህ ምዕራፍ የጥናት ስልት እና ዘዴዎቹን የሚመለከት ነው። ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት የመረጃ አይነት፣ መረጃዎቹ የተገኙባቸው መቼቶች እና መረጃዎቹን ለመሠብሰብ ስራ ላይ የዋሉ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች የቀረበበት ነው። በዚሁ መሠረት የሥነቃል መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡበት ስልት እና የዘዴዎቹ አፈጻጸም ሁኔታዎችን በዝርዝር የሚመለከት ነው። በመሆኑም የጥናቱ ስልት ዓይነታዊ (ሀተታዊ) የምርምር አቀራረብን (Qualitative Research) የተከተለ ሲሆን የመረጃዎቹ አሰባሰብ ከውስጣዊ እና ውጫዊ አመለካከት አንጻር መታየቱን የሚገልጽ ነው። ከዚሁ አንጻር መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት መቼቶች፣ ሥነ-ዘዴዎችና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች እንዲሁም የሥነምግባር መመሪያዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

3.1 የጥናቱ ስልት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የጥናቱ ስልት አይነታዊ ምርምር መሆኑ የተገለጸበት ሲሆን ይሄም ተግባራዊ የሆነው የጥናቱን አመለካከት በመቃኘት ነዉ። በዚሁ መሠረት በውስጣዊ አመለካከት (በተጠኚዎቹ ማህበረሰብ እውቀት ላይ) እና በውጫዊ አመለካከት (በዲሲፒሊኑ የምሁራን እውቀት አተያይ ላይ) የተመሠረተ የመረጃ አሰባሰብ ተግባራት ተከናውኗል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የመረጃ ምንጮች፣ መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት መቼቶች እና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ስልት በዝርዝር ቀርበዋል።

3.1.1 ኣይነታዊ የምርምር አቀራረብ

በፎክሎር መስክ የሚሰበሰቡት መረጃዎች በአብዛኛው የመጠን/ የስሌት (quantitative) ሳይሆን ዓይነታዊ/ ሀተታዊ (qualitative) ነው። በመሆኑም ይሄ ጥናት በተወሰነ መልኩ የመጠናዊ/ስሌታዊ አቀራረብ ያለው ቢሆንም በዋናነት ዓይነታዊ/ ሀተታዊ የምርምር አቀራረብ ባህሪን የተከተለ ነው። ይህም ማህበረሰቡን የሚመለከቱ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተገኙት የሥነቃል መረጃዎችን በማጣመር የተብራራበት አቀራረብ ነው። የዚህ ጥናት ስልት ተፈላጊነቱ እየጎላ የመጣው በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚካሔዱ ጥናቶች በመስክ

በሚገኙ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸውና ዘዴውም ተፈጥሯዊ፣ አሳታፊ፣ በአውድ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እና የሚገለጽ መሆኑን ምሁራን እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> Qualitative research geners have become increasingly important modes of inquiry for the social sciences and applied fields such as education, regional, planning, nursing, social work, community development, and management. Qualitative research a) is naturalistic, b) draws on multiple methods that respect humanity of participants in the study, c) focuses on context, d) is emergent and evolving, and e) is fundamentally interpretive.(Marshal & Rossman, 2006:1)።

ሲተረጎም

> አይነታዊ የምርምር ስልት ተፈላጊነቱ እጎላ የመጣው በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች በትምህርት፣ በአካባቢያዊ እቅድ፣ በጤና እንክብካቤ፣ በማህበራዊ ሥራ፣ በማህበረሰባዊ እድገት እና ሥራ አመራር መስኮች ነው። ዓይነታዊ/ ሁተታዊ ምርምር ተፈጥሯዊ፤ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ሰዎችን በጥናቱ ውስጥ የሚያሳትፍ፤ በአውድ ላይ የሚያተኩር እና የሚገለጽ ነው።

የአይነታዊ ጥናት መረጃ አሰባሰብ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተደገፈ መሆን እንዳለበት የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። በመሆኑም በዚህ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ተመራማሪ መረጃዎችን በአራት የተለያዩ ዘዴዎች መሰብሰብ እንዳለበት ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ። “Qualitative researchers typically rely on four methods for gathering information: (a) participating in the setting, (b) observing directly, (c) interviewing in depth, and (d) analyzing documents and material culture.” (Marshal & Rossman, 2006:97).

ይህ ማለት አንድ ተመራማሪ በዓይነታዊ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መረጃዎችን ለማግኘት በአራት ዘዴዎች ላይ የሚሞረኮዝ ሲሆን እነሱም በመቼቱ ውስጥ በመሳተፍ፣ በቀጥታ በመመልከት፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና ቁሳዊ ባህሉን በመመረመር ነው። ይህም በኢትኖግራፊ የአጠናን ስልት አጥኚው የማህበረሰቡን ባህል በሚገባ ለማወቅ አብረው እየኖረ በመረጃ አሰባሰቡም ውስጥ በቀጥታ መሳተፍና ጥልቅ ቃለ-መጠየቅ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ኤትኖግራፊ የአጠናን ዘዴ ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያጠና ሲሆን አመጣጡ ከሥነሰብ የትምህርት መስክ መሆኑን በመጥቀስ የአጠናን ስልቱ ተፈላጊነት እየጎላ የመጣው ከ1900ዎች ወዲህ ታወቂ ተመራማሪዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ረዥም ጊዜ ቆይተው

መረጃዎችን የመሰነድ ስልት ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምሩ መሆኑን Scott Reeves et al, (2008፡ 512). እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> Ethnography is the study of social interactions, behaviours, and perceptions that occur within groups, teams, organizations, and communities. Its roots can be traced back to anthropological studies of small, rural (and often remote) societies that were undertaken in the early 1900s, when researchers such as Bronislaw Malinowski and Alfred Radcliffe-Brown participated in these societies over long periods and documented their social arrangements and belief systems.

ሲተረጎም

> የኢትኖግራፊ አጠናን ስልት በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እነ ማሊኖዊስኪ እና ራድክልፍ በማህበረሰቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው መረጃዎችን መሰነድ በጀመሩበት ወቅት የተገኘ የማህበራዊ አጠናን ስልት ነው። በመሆኑም ኤትኖግራፍ በማህበረሰቡ ውስጥ እየተኖረ የሚጠናውን ማህበረሰብ ባህላዊ ጉዳዮችን በጥልቀት ለማወቅ እየተሳተፉ መረጃዎች የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው።

ይህ የጥናት መስክ ሦስት ዋና ዋና አላማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም 1ኛ. የሚጠናውን ሕዝብ ወግና ልማዳዊ ድርጊቶችን መግለጽ 2ኛ. እነዚህን ወጎችና ልማዶች እንዴት እንደሚከውኑ መግለጽና 3ኛ. የሕዝቡን ባህላዊ አስተሳሰቦችና ስሜቶችን መዝግቦ በግልጽ ማሳየት መሆኑን የMalinowski (1946) ሥራዎች ዋቢ በማድረግ O'reilly (2005:8) ያብራራል።

በሌላ መልኩ ይህ ጥናት በተወሰነ ማህበረሰብ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እንደመሆኑ መጠን በጉዳይ ምርመራ (Case Study) ስልት ይጠናል። በማህበረሰብ ጥናት ውስጥ ይህ ስልት ባህላዊ እሴቶች በትኩረት እና በጥልቀት በመመርመር አጉልተው የማሳየት አቅም ያለው በመሆኑ አንባቢው የማህበረሰቡን ባህል በደንብ እንዲረዳ የሚደረግበት የአጠናን ስልት ነው (Marshal & Rossman, 2006:97)።

በማህበራዊ ሳይንስ ውስጥ የጉዳይ ምርመራ የአጠናን ስልት ዓላማው ማህበረሰቡን የሚመለከቱ፡ መረጃዎችን በመሰብሰብ ያለውን እውነታ ለሌሎች ግልጽ የምናደረግበት መንገድ ነው (Best and Jems V. Kahn; 1993: 19)። ይህ የአጠናን ስልት አፈጻጸሙ ውስብስብ በመሆኑ የተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን መጠቀሙ የግድ መሆኑን ምሁራን ይመክራሉ (Marshal & Rossman, 2006:56)።

የኢትኖግራፊ አጠናን ስልት ጤናን ለሚመለከቱ በተለይም ከኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የማህበረሰቡን ውስብስብ ችግሮች በጥልቀት መርምሮ ለመፍታት ጠቃሚ የአጠናን ስልት ነው (Wolctt, 1999፡ 71)።

በመሆኑም ይህ ጥናት በባሕሪዉ ኤትኖግራፊክ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከተጠኚው ማህበረሰብ ጋር አብረው በመኖር፣ የቅርብ ግንኙነቶችን በመፍጠር እና የሕዝቡን ባህላዊ ተግባራት በጥልቀት በመመልከት እና በቀጥታም በመሳተፍ ነው። በዚህ ሂደት መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በጉዳይ ምርመራ የአጠናን ስልቱ ደግሞ በተወሰነ ማህበረሰብ ላይ ትኩረት ከማድረጉ አኳያ በቱለማ ኦሮሞ በሚነገሩ እና በሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ላይ ያተኮሩ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚሁ መሠረት የተጠኚውን ማህበረሰብ ልማዳዊ ድርጊቶች ለመከታተል አጥኚው በባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ላይ በተደጋጋሚ በመገኘት ክዋኔያቸውን ያካተቱ መረጃዎች ተሰብስቧል። ከዚህ አኳያ የሥነቃል መረጃዎቹን በማሰባሰቡ ሂደት በመመልከት ብቻ ሳይሆን በክዋኔዎቹ ውስጥ በመሳተፍም ነበር።

3.1.2 መረጃ መሰብሰቢያ አመለካከት

በፎክሎር ዘርፍ ምርምር የሚያደርግ ባለሙያ በመስክ ሥራው አማካይነት ከማህበረሰቡ ጋር መገናኘቱ የግድ ነው። በዚህን ጊዜ አጥኚው ከሁለት አንጻሮች መረጃዎችን ሊሰበስብ ይችላል። እነዚህም (Emic and etic)[27] አኳያ የሚታይ ነው። ይህም ማለት በውስጣዊ አመለካከት (Emic or insider's perspective) እና በውጫዊ አመለካከት (Etic or outers' perspective) መሠረት ያደረገ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ነው (O'reilly, 2005)።

ውስጣዊ አመለካከት፡- በዚህ አመለካከት አንድ አጥኚ የፎክሎር መረጃዎችን ለማሰባሰብ ወደ መስክ በሚሄድበት ወቅት የባህሉ ባለቤት ሕዝቡ የራሱን ባህል በሚገልጽበት መንገድ መሆን አለበት። ይህም አጥኚው ከሕዝቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሮ፣ ማህበረሰቡን በወጉ ተገንዝቦ በየዝርዝር ጉዳዮቹ መረጃዎችን መሰብሰብና ለሌላው ማሳየት ነው (O'reilly, 2005: 84)። በዚሁ መሠረት የማህበረሰቡን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የተሰበሰቡት የሥነቃል ዓይነቶች ማህበረሰቡ ስለበሽታው ካለው

---

[27] "Emic and etic, in anthropology, folkloristics, and the social science and behavioral sciences, refer to two kinds of field research done and view points obtained; from within the social group (from the prespective of the subject) and from out side (from the prespective of the observer)." https://en.m.wikpedia.org>wiki>Emic...

ሥነልቦናዊ አመለካከት አንጻር፣ ሥነቃሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያና ባህሉን ከትውልድ ወደ ትውልድ አስተላልፎ ከማቆየት አንጻር የታዩ ናቸው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ማህበረሰቡ ለሥነቃሉ ካለው አገር በቀል እውቀቶች አንጻር መረጃዎቹ የተሰበሰቡ ሲሆን የተተነተኑትም ይህንኑ አገር በቀል የሥነቃል እውቀቶችን መሠረት በማድረግ ነው።

ውጫዊ አመለካከት፡- ይህ የመረጃ አሰባሰብ ምሁራዊ አመለካከትን የሚመለከት ሲሆን አጥኚው ከሚያጠናው ዲስፒሊን ቲዮሪዎች አንጻር ትንታኔውን የሚቃኝበት አመለካከት ነው። ይህም ለውስጣዊ አመለካከት ትርጓሜ መስጠትንም ያካትታል። በዚህ አካሔድ የተመራማሪዉ ተግባር የውስጣዊ አመለካከትን ትርጓሜ ከማካተቱም በተጨማሪ ከባህሉ ውጭ ላለው አንባቢ (አድማጭ) ሊገባው በሚችል መልኩ ማሳወቅ መቻል ነው (Fetterman David,2010)። ከዚሁ አንጻር ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች የተማራማሪውንም አመለካከት አመለካከት ታሳቢ ያደረገ ነው።

በዚሁ መሠረት የተሰበሰቡት መረጃዎች ከመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻር በመስኩ ምሑራን አስተሳሰብ የተቀመሩ ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችን መሠረት ያደረገ ትንታኔ ተካሂዷል። በዚህ ትንታኔ ውስጥ በዋናነት ያገለገለው አውዳዊ ቲዮሪ ሲሆን ሌሎችም ቲዮሪዎች እንደየአስፈላጊነታቸው በደጋፊ መተንተኛነት ተግባር አገልግለዋል። የተጠኚውን ማህበረሰብ ወይም የመረጃ አቀባዮችን አመለካከት በተመለከተ ማህበረሰቡ ለሥነቃሉ ከሰጡት ትርጉም አኳያ ታይቷል። በመሆኑም ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ትንታኔ ከእነዚሁ ሁለት አመለካከቶች አኳያ የተቃኙ ናቸው። የመተንተኛ ቲዮሪዎችን በሚመለከት ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ሥር በዝርዝርዝ የቀረቡ ሲሆን በምሥራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ የተከናወኑት ትንታኔዎች ሁለቱንም አመለካከቶች ያቀፈ በመሆኑ ይህ ጥናት በተቻለ መጠን ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ የተካሄደ ነው። ከዚህ ቀጥሎ የመረጃዎቹ ምንጭ በዝርዝር እንመለከታለን።

3.1.3 የመረጃ ምንጮች

በጥናትና ምርምር ሂደት ውስጥ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ይሰበሰባሉ። እነዚህም በልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከመስክ የሚሰበሰቡ እና ከቤተመጽሐፍት፣ ከድረ ገጽ እንዲሁም ከተለያዩ ጽሑፍ በንባብ የተጠናቀሩ የመረጃዎች ምንጮች የሚመለከቱ ናቸው።

በዚሁ መሠረት ጥናቱ ከተካሄደበት ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በተለይም ከሱሉልታ ወረዳና አካባቢው ከልዩ ልዩ መቼቶች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤችአይቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስቧል። በሌላ መልኩ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ከመጽሐፍት፣ ከጥናታዊ ድርሣናት፣ ከመጽሔት፣ ከአርቲክሎች፣ ከድረ-ገጾች እና ከበራሪ ጽሑፎች በንባብ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ተካተዋል።

3.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች

በኤትኖግራፍ አጠናን ዘዴ ሦስት አይነት መቼቶችን በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ ይቻላል። እነሱም ተፈጥሯዊ መቼት (Natural Setting)፣ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ መቼት (Artificial Setting) እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት (Induced Natural Setting) በመባል ይታወቃሉ።

ተፈጥሯዊ መቼት፡- ማለት የሥነቃል ዘርፉ በተለምዶም ሆነ በባህል የሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ሲሆን አጥኚው በቦታው እና በጊዜው ተገኝቶ የተፈለጉ መረጃዎችን የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (ፈቃደ አዘዘ፣ 1991፡122)።

ተፈጥሮአዊ ያልሆነ መቼት፡- ተመራማሪው ሁሉንም የሥነቃል ዓይነቶች በተፈጥሮአዊ መቼት ብቻ ለመሰብሰብ አይችልም። ስለዚህ ከተፈጥሯዊው መቼት ውጪ መጠቀም ግዴታ ይሆናል። በመሆኑም ተፈጥሯዊ ያልሆነ መቼት ማለት ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ የተገኘበትን ጊዜና ቦታ ተጠቅሞ ተመራማሪው ሥነቃል መረጃዎችን የሚሰበስብበት ስልት ነው። ተፈጥሯዊ ባልሆነ መቼቶች ውስጥ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ሁኔታዎችን አስመልክቶ ፍቃደ አዘዘ፣ እንዲህ ይላል። "አንድ ሰው ከገጠር እከተማ መጥቶ ለአንድ ተማሪ የለቅሶ ግጥሞች ቢነግረው። ወይም አንድ ተመራማሪ እገጠር ትምህርት ቤት ሂዶ እያንዳንዱ ተማሪ የሚያውቀውን እንቆቅልሽ እክፍል ተቀምጦ እንዲፅፍለት ቢጠይቅና ቢፃፍለት፣ እነዚህ ስነቃሎች የተሰበሰቡት ከአውዳቸው ውጭ ነው ማለት ነው።" (1991፡123)።

ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት፡- ይህ ስልት በተፈጥሯአዊ መቼት ውስጥ መረጃዎችን መሰብሰብ በማይቻልበት ወቅት ጥሩ ችሎታና እውቀት ያለውን መረጃ አቀባይ በመፈለግ የተቀናበረ ተፈጥሯአዊ መቼት በመፍጠር ሥነቃልን መሰብሰብ ይቻላል (ፈቃደ

አዘዘ፣1991፡124)። ከዚህ የምንገነዘበው አጥኚው በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሳያማርጥ ሥነቃል መረጃዎችን የሚሰበስብበት ሁኔታ መሆኑን ነው።

እነዚህን የመረጃ ማግኛ ስልቶችን መሠረት በማድረግ ይህ ጥናት በተካሔደበት ቦታ ሦስቱንም መቼቶች በመጠቀም መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። በዚሁ መሠረት ከእነዚህን መቼቶች የተገኙት መረጃዎች በምዕራፍ አምስት ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል። ከዚህ በመቀጠል የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ስልትን እንደሚከተለው እናያለን።

3.1.5 የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ

በጥናትና ምርምር አካሄድ ውስጥ ከጥናቱ ዓይነት፣ የመረጃ ምንጮች እና መቼቶቹ መለየት ቀጥሎ የሚከናወነው ተግባር ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ለመስጠት የሚችሉ መረጃ አቀባዮች የተመረጡበትን ስልት መግለጽ ነው። በዓይነታዊ የጥናትና ምርምር ዘዴ ውስጥ በዕድል ከልካይ (Non Probability Sampling)የናሙና አመራረጥ ስልት መረጃ አቀባዮች ይመረጣሉ። ይህንን በሚመለከት ያዴሣ ቶሎሣ (2007፡ 77-79) ሲገልጽ፡- ዕድል ከልካይ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ዋና ባህርይ ጥናቱ ለሚመለከተው ለእያንዳንዱ ሰው ወይም ነገር በናሙናነት የመወሰድ ዕድል አለመስጠቱ ሲሆን ይህ ናሙና የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች እንዳሉትና እነሱም የአጋጣሚ፣ የግኝት፣ የኢላማ፣ የኮታ እና ጥቆማን መሠረት ያደረገ የናሙና አወሳሰድ የተሰኙ መሆናቸውን ያብራራል። ይህንኑ መሠረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ አቀባዮች በሦስት ዓይነት ናሙናዎች 181 ሰዎች (107 ወንዶች እና 74 ሴቶች ተመርጠዋል። እነሱም በኢላማ ናሙና፣ ጥቆማን መሠረት ባደረገ ናሙና እና አጋጣሚ ናሙና የተመለመሉ ናቸው። ከዚሁ አኳያ እነዚህ ናሙናዎች እንዴት ተግባራዊ እንደሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ኢላማ ናሙና፡- በአንዳንድ ጥናቶች ውስጥ በተለይም ባህላዊ ጉዳዮችን በትክክል የሚያውቁ ሰዎችን በመረጃ አቀባይነት መጠቀም የግድ ይላል። በመሆኑም በኢላማ ናሙና አጥኚው አንዳንድ ግለሰቦች በጥናቱ ቢካተቱ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል ብሎ ሲገምት ሥራ ላይ የሚውል ሲሆን በናሙና ውስጥ የሚገቡ ሰዎች ሆን ተብለው በአጥኚው የሚመረጡ ግለሰቦች ናቸው። ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ በቱለማ ኦሮሞ የምንፀባረቁ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን የሚያውቁ 28 ሰዎች (22 ወንዶች እና 6

ሴቶች) ተመርጠዋል። እነዚህን ግለሰቦች ለማወቅ የቻልኩት የአካባቢው ተወላጅ በመሆኔ ከሰዎቹ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነቶችን በመፍጠር ወዳጅነትን በመመሥረት ነው።

ጥቆማን መሠረት ያደረገ ናሙና፡- ይህ ዘዴ በመጀመሪያ አጥኚው በኢላማ ናሙና አንድ መረጃ አቀባይ ከመረጠ በኋላ በዚሁ መረጃ አቀባይነት ሌሎች መረጃ አቀባዮች እንዲጠቁሙ የሚደረግበት ዘዴ ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ በኢላማ ናሙና የተመረጡ መረጃ አቀባዮች የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶችን የሚያውቁ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙ በማድረግ እንዲሁም ለመጠይቅ የተሳተፉ ተማሪዎች የቱለማ ኦሮሞ ባህልና ሥነቃል የሚያውቁና ችሎታ ያላቸው ሰዎች እንዲጠቁሙ በማድረግ ነው። በዚሁ መሠረት 53 ሰዎች (35 ወንዶች እና 18 ሴቶች) በመረጃ አቀባይነት ተመልምለዋል።

አጋጣሚ ናሙና፡- ይህ ዘዴ ድንገታዊ እና አመቺያዊ በሚሰኙ የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎች መረጃ አቀባዮች የሚመረጡበት መንገድ ሲሆን በዋናነት በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ሰዎች ለመምረጥ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው። ከዚሁ አኳያ በጫንጮ እና በሱሉልታ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አፋን ኦሮሞ መምህራንን በመጠቀም የጥናቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ተማሪዎች ተመርጠዋል። በመሆኑም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞ የሚችሉና ባህሉን በደንብ የሚያውቁ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 50 (25 ወንዶች እና 25 ሴቶች) በድምሩ 100 ተማሪዎች መጠይቁን በመሙላት እንዲሳተፉ ተደርገዋል።

በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት ናሙና አመራረጥ የተገኙት መረጃ አቀባዮች የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች አስፈላጊ መልሶችን በመስጠት ጉልህ ተሳትፎ አድርገዋል። የሰጡት መረጃም በምዕራፍ አምስት ሥር በዝርዝር የቀረበ ሲሆን የመረጃ አቀባዮቹ ፕሮፋይል በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ አባሪ ተደርገዋል።

3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ መሳሪያዎች እና የሥነ ምግባር መመሪያዎች

የዚህ ንዑስ ርዕስ አብይ ትኩረት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች እና የሥነምግባር መመሪያዎች የሚመለከት ነው። ከዚሁ አንጻር በዚህ ጥናትና ምርምር ውስጥ መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡበት ልዩ ልዩ ዘዴዎች እና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥነ-ምግባር መመሪያዎች የሚመለከቱ ጉዳዮች በዝርዝር ቀርበዋል።

3.2.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

በፎክሎር ጥናት ውስጥ ወቅታዊውና ተመራጩ የአጠናን ዘዴ አውድን መሠረት ያደረገ ነው (Ben- Amos,1979; Dundes, 1980; Goldeistin, 1964)። ይህ ዘዴ ፎክሎሩን ከማህበረሰቡ አተገባበር ጋር በማያያዝ ከፎክሎር ቅንጣት (text) የተሟላ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ነው። ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎቹ ከ2005 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እስከ 2008 ዓ .ም መጀመሪያ ድረስ በተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ ሲከወኑ ከነአውዳቸው እንዲሁም ከአውድም ውጭ በተገኘው ጊዜ እና አጋጣሚ ሁሉ ተሰብስበዋል።

ከዚሁ አኳያ በአንድ ጥናት ውስጥ የምርምር ችግሮችን መሠረት ያደረጉ የምርምር ጥያቄዎችን በመመለስ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ እንደ ጥናቱ ባህርይ ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። በመሆኑም በቦታው በመገኘት መመልከት፣ ጥልቅ ቃለመ ጠይቅ በማድረግ ማስታወሻ መያዝና በጉዳዩ ላይ ቡድን ተኮር ውይይት በማካሄድ መረጃዎችን መሰብሰቡ ለምርምሩ ጥራት ወሳኝነት አለው (Marshal & Rossman, 2006:111)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ከመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ማካሄድ ለአንድ ጥናትና ምርምር ወሳኝ መሆኑን ICDR (1999); O’reilly (2005) እና Creswell (2007:36) ይዘረዝራሉ ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ጎን ለጎን አንድ የፎክሎር አጥኚ በማህበረሰቡ ውስጥ እየኖረ ማህበረሰቡ በሚገኝበት ሁኔታ ማጥናት እንዳለበት Ben-Amos (1979) ይገልጻል።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውሰጥ ሥራ ላይ የዋሉ አራት ዘዴዎች ሲሆኑ እነሱም መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እና ምልከታ ናቸው። ከፎክሎር ሙያ አንፃር ምልከታና ቃለመጠይቅ ዋናዎቹ ሲሆኑ በአውድ ውስጥ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው (Goldstein, 1964)። ስለሆነም ሁለቱ ከተፈጥሯዊ አውድ ጋር ተጣምረው የተተገበሩ ሲሆን የተቀሩት ለማረጋገጫነት እንደየአስፈላጊነታቸው መረጃዎችን ለማውጣጣት ያገለገሉ ናቸው። የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በስራ ላይ ማዋል የተፈለገበት ዋንኛው ምክንያት እያንዳንዱ ዘዴ የየራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳለው ስለሚታመን ነው። ከዚሁ አንጻር የመረጃዎቹን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል

ጠንካራ ጎናቸው እንዳለ የተወሰደ ሲሆን የአንዱን ድክመት በሌላኛው እንዲሟላ ተደርጓል።

በሌላ መልኩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች እንዲሁም መረጃዎቹ ሲሰበሰቡ ተግባራዊ የሆኑ ስነምግባራዊ ደንቦች ተካተዋል። ከዚሁ አኳያ በእያንዳንዱ ዘዴ ሥር የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

መጠይቅ፡- አንድ መረጃ ይሰጠናል ብለን የመረጥነውን ሰው ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎቻችን በጽሑፍ ለተጠያቂው በማቅረብ ተጠያቂውም መልሶ በጽሑፍ እንዲሰጠን የምናደርግበት የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴ ነው። በዚህ የመረጃዎች አሰበባሰብ ዘዴ አጥኚው አስፈላጊውን መረጃ አገኛለሁ ብሎ ካሰበበት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መጠይቆችን በማዘጋጀት መረጃዎችን የሚሰበስብበት ዘዴ መሆኑን ፈቃደ፣ 1991) ይገልጻል። የዚህን ዘዴ ጠቀሜታ አስመልክተው Marshal & Rossman, (2006:125) ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ። "Questionnnaires are usually tasted on small groups to determine their usefulness and, perhaps, reilaibility. … [It] is the appropeiate mode of inquiry for making inferences about a large group of people based on data drawn froma relatively small number of individuals in that group." ከዚህ የምንረዳው በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ከተወሰኑ ግለሰቦች የሚነገኙ መረጃዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ትክክለኛ ነባራዊ ሁኔታዎች የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው።

ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ ከጫንጮ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት እና ከሱሉልታ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች 100 ተማሪዎች (50 ወንዶች እና 50 ሴቶች) ተመርጠዋል። ለእነዚህ ተማሪዎች ለዓይነታዊ ጥናትና ምርምር የሚመቹ ክፍት መጠይቆችን (Open Questionnaires) በማዘጋጀት ተማሪዎቹን በማስተባበር የአፋን ኦሮሞ መምህራን እንዲተባበሩ ተደርገዋል። መጠይቆቹ ከተበተነላቸው ተማሪዎች ውስጥ 94 ተማሪዎች (48 ወንዶች እና 46 ሴቶች) ምላሽ በመስጠት ተሳትፎ አድርገዋል። በዚሁ መሠረት በዚህ የመረጃዎች አሰባሰብ ዘዴ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች ተገኝቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዚህ ዘዴ ባህሉን በደንብ የሚያውቁ የተወሰኑ መረጃ አቀባዮችም ተገኝተዋል። በመሆኑም ይህ ዘዴ ለጥናቱ መነሻነት እና አቅጣጫ ጠቋሚነት ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከተ ሲሆን ለምልከታ ቼክ ሊስት ለማዘጋጀት፣ ለቃለ- መጠይቅ እና የቡድን ተኮር

ውይይት ጥያቄዎችውስጥ የሚካተቱ ጉዳዮችን ለመወሰን አስተዋጽኦ የጎላ ነበር። በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የተጠየቁ ጥያቄዎች እና የተገኙ ምላሾች በምዕራፍ አምስት ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል።

ምልከታ፡- በማህበራዊ ሳይንስ ከመስክ ስራ ጋር በተያያዘ በአውዱ የሚከናወኑትን ባህላዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ለመመልከት በሰፊው የሚያገለግል አንዱና ጠቃሚ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ነው። ዘዴው እንደሚፈለገው የመረጃ ዓይነት የተለያየ መልክ ያለው ሲሆን አጥኚው የሰዎችን፣ የነገሮችን፣ የክስተቶችን ወዘተ … ሁኔታ፣ እንቅስቃሴ፣ ባህርይና የመሳሰሉትን በዓይኑ እየተመለከተ ያያቸውንና የተገነዘባቸውን ቁም ነገሮች የሚመዘግብበት መንገድ ነው። ይህንን በሚመለከት የፎክሎር ተመራማሪ እንዲህ ይላል። The term observation is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate (Goldstein, 1964:77).

ይህ ማለት ምልከታ በተመረጡት የጥናትና ምርምር መቼቶች በአካል በመገኘት ሁኔታዎችንና ተለዋዋጭ ዲርጊቶችና ባህሪያትን እንዳስፈላጊነቱ በአምስቱም የስሜት ሕዋሶቻችን አማካይነት የምንገነዘብበት ወይም የምንረዳበት ዘዴ ነው። በሌላ አባባል የምልከታ ዘዴ ልዩ ልዩ ቴክኒኮች አሉት። ከእነዚህም መካከል በድብቅ ወይም በግላጭ የሚደረግ ምልከታ፣ ወሰኑ የተገደበ ወይም ወሰኑ ያልተገደበ ምልከታ፣ ቀጥታ ወይም ተዘዋዋሪ ምልከታ፣ ተሳትፎ ወይም ተሳትፎ አልባ ምልከታ በመባል የሚታወቁት ተጠቃሽ ናቸው። ከእነዚህ የምልከታ ቴክኒኮች ውስጥ የተሳትፎ ምልከታ እና ተሳትፎ አልባ ምልከታን በሚመለከት የዘርፉ ምሁራን Goldestein (1964)፣ Ben Amos (1993) እና Bauman (1992) እንደሚከተለው ይገልጻሉ። ተሳትፎ አልባ (የኢ-ተሳትፎ) ምልከታ አጥኚው በባህላዊ ክዋኔ ሳይሳተፍ መረጃ የሚሰበስብበት ቴክኒክ ሲሆን የተሳትፎ ምልከታ አጥኚው በማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ በመሳተፍ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ ሥነቃል በሚከወኑባቸው ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ በመሳተፍ የቀረበው ቃል-ግጥም በማን፣ ለማን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደተከወነ የሚገልጹ ናቸው። ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ እነዚህ ቴክኒኮች እንደ አስፈላጊነታቸው ሥራ ላይ ውለዋል።

ይህ ጥናት ሲካሔድ በተሳትፎ አልባ (የኢ-ተሳትፎ) ምልከታ በባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ከበራዎች ወቅት የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች በዚህ ቴክኒክ ክዋኔዎችን አስተውሎ በማድመጥና በመመልከት መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። የተሳትፎ ምልከታ ቴክኒክን ለመጠቀም ቋንቋና ባህል እንደ ችግር ይቀርባሉ (Goldestein 1964:79)። ይህን እንጂ የማህበረሰቡ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ባገናዘበ መልኩ የፎክሎሩ ክዋኔ ሁነት ገጽታዎች በሙሉ በመረጃዎች አሰባሰብ ውስጥ መካተት እንዳለባቸው የዘርፉ በለሙያ ያስገነዝባል። ምክንያቱም ምልከታ በውስጡ የተለያዩ ክዋኔዎችን የያዘ ሲሆን፣ ይህም ድርጊቶችን በመመልከትና አስፈላጊ ሆኖ በተገኙት ውስጥም በመሳተፍ የምልከታ መረጃዎችን መሰብሰብ በመሆኑ ነው። ከዚህ አንጻር የተጠኚው ማህበረሰብ ቋንቋ ተናጋሪ እንደመሆኔ መጠን በምልከታ ወቅት ለመረጃ አሰባሰብ አስፈላጊ በሆነ አውድ ውስጥ ተሳትፎ አድረጌያለሁ።

በዚሁ መሠረት በቢሾፍቱ፣ ሞገር እና አቃቂ የተከበረውን የእሬቻ በመመልከት የሥነቃል መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። በተያያዘ መልኩ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች በተከበሩ የጥምቀት ክብረ-በዓላት ላይ በአካል በመገኘት የሥነቃል ዓይነቶች ሲከወኑ በተሳትፎ ምልከታ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። በሠርግ እና ለቅሶ ሥነ-ሥርዓቶች ላይም በመገኘት ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በስብሰባዎች፣ በገበያ ቦታዎች፣ በመሸታ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች እና በጤና ተቋማት በመገኘት ምልከታ በማድረግ የተገኙ መረጃዎችን የማሰባሰቡ ተግባር ተከናውኗል። በዚህ ዘዴ የተገኙ መረጃዎች ከድምጽ ወደ ጽሑፍ የተቀየሩ ሲሆን ፎቶግራፊቸውም ለማስረጃነት ተይዘዋል።

ቃለ-መጠይቅ፡- በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከአውድ ውጪ መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች አንዱ በሆነው ቃለ-መጠይቅ ወቅት መረጃ አቀባዮች ስለተጠየቁት ጉዳዮች እንደማህበረሰቡ አባልነታቸው ከውስጣቸው የሚገልጹበት እና የሚያስረዱበት መሆኑን ጎልድስተን ሲገልጽ እንዲህ ይላል። “This method used by field worker to obtain data about ideas or events outside the context of the interview itself through questioning persons believed or known to have that information. During the interview, the informants describe situations, materials, attitudes, or ideas from the advantage point of the insider (Goldstein, 1964፡ 77-78).” ይህ ማለት በዚህ ዘዴ የመስክ ሠራተኛው

ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ከአውዱ ውጭ መረጃዎችን የሚያገኝበት መንገድ ነው። በቃለ-መጠይቁ ወቅት የመረጃ አቀባዮች የገለጻ ሁኔታ፣ መሳሪያዎቹ፣ ዝንባሌዎቹ ወይም ሀሳቦቹ ከውስጣዊ አመለካከታቸው አኳያ የሚታዩ ናቸው። ይህ ዘዴ ስለ አንድ ባህላዊ ክዋኔ ከዋኙ ያለውን ግንዛቤ ጠይቆ መረዳትን ያመለክታል።

በቃለ-መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ስለሚጠናው ሕዝብና ርዕሰ ጉዳይ ሰዎች እንዲገነዘቡ በማድረግ አጥኚው ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ከመረጃ አቀባዩ ጋር በአካል በመገናኘት በጥያቄና መልስ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ዘዴ ነው (Julia, 2008:208)። ከዚሁ አኳያ የተጠኚው ማህበረሰብ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ሕጎችን ያገናዘቡ ጥልቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በምልከታ ወቅት ያልተሟሉ መረጃዎች መሟላት እንዳለባቸው Goldstein, (1964: 106-108) ይገልጻል።

በዚህ ጥናት ውስጥ አንዳንድ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች የተመሠረቱት በምልከታ ወቅት ከተዘፈኑ ዘፈኖች እና ከማህበራዊ ድርጊት አውዶች በመነሳት የቀረቡ ናቸው። ከዚሁ አኳያ ምልከታ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ያልተብራሩና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን መሠረት በማድረግ በዚህ ጥናት ወቅት የተገደበ እና ያልተገደበ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች እንደ ሁኔታው በማመጣጠንና በማሰባጠር ተግባራዊ ሆነዋል።

ያልተገደበ ቃለ-መጠይቅ፡- ይህ ቴክኒክ በአጥኚውና በመረጃ ሰጪው መካከል የሚካሔድ ያልተገደበ ውይይትን ያመለክታል (Goldestein 1964:109)። በዚህ ጥናት ውስጥም መረጃ ሰጪዎች ክፍት የሆኑ (Open-ended) ጥያቄዎች ተጠይቀዋል። ከሚሰጡት መልስ በመነሳት ሌሎች የማብራሪያ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል። በዚሁ መሠረት መረጃ ሰጪው በራሱ መንገድ፣ ፍጥነትና ትክክል በመሰለው ቅደም ተከተል ጥያቄዎችን መልሷል።

የተገደበ የቃለ-መጠይቅ፡- ይህን ቴክኒክ በምንጠቀምበት ጊዜ የጥያቄና መልሱ ሒደት በአጥኚው የሚመራ ነው። ይህ ማለት አጥኚው ቀድመው የተዘጋጁና ተከታታይ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ቴክኒኩ አገልግሎት ላይ የሚውለው የሚፈለገውን የመረጃ አይነት መሰረት በማድረግ ነው። መረጃ ሰጪው በሚፈለጉት መረጃዎች ላይ ብቻ አተኩሮ ያለውን እውቀት እንዲያካፍል በመደረጉ ይህ ቴክኒክ ጊዜ ከመቆጠብ አንፃር ጠቃሚ ነው።

ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ ሰጪው ለቀረቡለት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የሥነቃል መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። አጥኚው በአካባቢው ባደረገው ቆይታ በኢላማ ተኮር የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በዚህ ዘዴ ውስጥ ተሳትፈዋል በዚሁ መሠረት ከ19 ሰዎች (11 ወንዶች እና 8 ሴቶች) መረጃዎች ተሰብስበዋል።

የቡድን ተኮር ውይይት፡- ይህ ዘዴ በባህል፣ በማህበረሰብ ልማትና ትምህርት ነክ ጉዳዮች የጥናትና ምርምር ሥራ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ ሲሆን ይህም ከቡድኑ አባላት ልዩ ልዩ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ሲፈለግ በስፋት በጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው። በቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሳታፊ አባላትን ብዛት በሚመለከት Marshal & Rossman, (2006:114) እንደሚከተለው ገልጸዋል።

“The groups are generally composed of 7 to 10 people (although groups range from as small as 4 to as large as 12 who are unfamiliar with one onther and have been selected because they share certain characteristics relevant to the study's questions.” ይህ ማለት የቡድን አባላት ከ7 እስከ 10 እንደሚሆኑና አነስተኛው የቡድኑ አባላት ቁጥር ከ4 ከፍተኛው ደግሞ ከ12 እንደማይበልጡ እና እርስ በርሳቸው የማይተዋወቁ ሆኖ ሀሳብ መቀያየር የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው። በሌላ መልኩ በምልከታ ወቅት የተፈጠሩና በቃለ-መጠይቅ ዘዴም ተፈትሸው በቂ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው መረጃዎች ላይ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በቡድን ሆነው እየተወያዩና እየተረዳዱ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚደረግበት መንገድ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ይህን ሀሳብ የሚያጠናክር በሌላ አገላለጽ የቀረበው ደግሞ ይህ ዘዴ በአንድ ጊዜ ከ7 እስከ 10 የሚሆኑ አባላትን ሰብስቦ ማወያየት ከማስቻሉም በላይ ከተሳታፊዎቹ ተዓማኒነት ያላቸው መረጃዎች እንደሚያስገኝ በመጥቀስ በተለይም አካራካሪ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በሚደረግበት ወቅት ትክክለኛው መረጃ እስኪገኝ ድረስ ቢያንስ ከሁለት ጊዜ ያለነሰ ቡድን ተኮር ውይይት ሊካሄድ እንደሚገባ እና ጉዳዩ ጾታን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ የቡድን ውይይቱ ለሴቶች ለብቻ ለወንዶችም ለብቻ መሆን እንደለበት በOSSER, (2001:28) በሰፊው ተብራርተዋል።

ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መረጃ አቀባዮች በቡድን ተኮር ውይይት እንዲሳተፉ ተደርገዋል። በዚህ መሠረት 33 ሰዎች (22 ወንዶች

እና 11 ሴቶች) በአምስት ቡድን ተከፍሎ በአንድ ቡድን ውስጥ ከ5 እስከ 7 አባላት የሚገኙበት የቡድን ተኮር ውይይት አከሂዷል። የቡድኑ አደረጃጀት በጾታ ወንዶች ለብቻ፣ ሴቶች ለብቻ፣ ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ ወንዶች እና ሴቶች በጋራ ውይይቶች አድርገዋል።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች አተገባበር አስመልክተው ባሉት ችግሮች ዙሪያ እና በኤችአይቪ/ ኤድስ ተጠቂ የሆኑ የኀብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች እና በሌሎችም ተያያዥ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ በተናጠል በተደረጉ ውይይቶች የተገኙ መረጃዎችን የሚያጠናክር የቡድን ተኮር ውይይቶች ተካሂዶ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች ይበልጥ ግልጽ ተደርገዋል። በመሆኑም የውይይቱ ዓላማ ተሳክቷል።

3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በፎክሎር መስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የድምፅና ምሥል መቅረጫ መሣሪያዎች ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። አጥኚው እነዚህን መሳሪያዎች አጠቃቀሙን ማወቅና እንዳለበትና መሣሪያዎቹ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት የመረጃ ሰጪዉ ፈቃደኝነት መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት Matthews and Ross, (2010) ይገልጻሉ።

እነዚህን ተግባራት ለማከናወንና መረጃዎችን በአግባቡ ይዞ ለመመደብ እና ለመተንተን እንዲያመች የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት መቼቶች መረጃዎች ሲሰበሰቡ የድምፅ መቅጃዎች፣ የምስልና ድምፅ መቅረጫዎች፣ ዲጂታል ቪዲዮ፣ ፎቶ ካሜራ እና የማስታወሻ ደብተሮች አገልገሎት ላይ ውለዋል። ከዚሁ አኳያ በምልከታ ወቅት በክብረ በዓላት ላይ ሽማግሌዎች ሲመርቁ እንዲሁም የክብረ በዓሉ ታዳሚዎች በዓሉን ለማክበር ሲዘፍኑ ድምፃቸውን በካሴት በመቅዳትና በሚዘፍኑበትና በሚጨፍሩበት ወቅት የሚያሳዩትን ባህላዊ ድርጊቶች (ልማዶች) (Social Folk Customs)በቪ ዲዮ ካሴት በመቅረፅና ድምፃቸውን በመቅዳት መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በቅንብር ተፈጥሯአዊ መቼቶች (Induced Natural Settings) ወቅት የታዳሚዎቹ እና የአዝማሪው ዘፈን በዲጂታል ቪዲዮ እና ፎቶ ካሜራ የከዋኞቹ ምስልና ድምፅ ተቀርጿል። በተመሳሳይ መልኩ በመጠይቆች አማካይነት ከተማሪዎች የተሰበሰቡት ኦሪጂናል የጽሑፍ መረጃዎች በፋይል ተይዘዋል። በቃለ

መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ወቅትም ማስታወሻዎች የተያዙ ሲሆኑ ሥነቃሎቹ ሲነገሩና ሲከወኑ የመረጃ ሰጪዎች ድምጽ እና ምስል ተቀርጿል።

3.2.3 የምርምር ሥነ-ምግባር መመሪያዎች

የማህበራዊ ሳይንስ ጥናትና ምርምር የመስክ ሥራዎች ከተለያዩ አለማዊና መንፈሳዊ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ በጥያቄዎች አቀራረብና መረጃዎች አሰባሰብ ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። መረጃ ሰጪዎች ስማቸው እንዳይገለጽ ወይም ማንኛውም የምሥልና ድምፅ ቀረጻ እንዳይደረግ ከፈለጉ መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል። ከሰብአዊ መብት በተለይም ከኤድስ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ የስነምግባር መመሪያዎቹ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ፣ መረጃዎቹ ተጠቃለው ዘገባው በሚዘጋጅበት ወቅትም ተመራማሪው መከተል ያለበት የስነምግባር ደንብ መኖሩንና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እ.አ.አ በ1971 ዓ.ም የአጥኚዎች ስነ-ምግባር ተነድፎ ስራ ላይ መዋሉን Spradley (1980:20) ይጠቅሳል።

በመሆኑም በጥናቱ ሂደት እነዚህ እና ሌሎችም የማህበራዊ መስክ ጥናት የሥነምግባር መመሪያዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተጠኚው ማህበረሰብ ፍላጎትና ባህላዊ እሴቶች ተከብረዋል። ለመረጃ አቀባዮች ስለጥናትና ምርምሩ ዓላማ በግልፅ የተነገራቸው ሲሆን፣ ግላዊ መብቶቻቸውና ምስጢራቸውም ተጠብቋል። በሌላ መልኩ የማህበረሰቡ ተወላጅ እንደመሆኔ መጠን በመረጃዎች አሰባሰብ እና ዘገባ አቀራረብ ወቅት ደካማ ጎኖች ለመሸፈንና ያሉትን ጠንካራ ጎኖች አጋኖ ማቅረብ የሚለውን የ(Eriksen, 2002)በ(Mamo Hebo, 2006:3) ሥራ ውስጥ የተገለጸውን የሥነ -ምግባር መመሪያ በመገንዘብ የምርምሩ ሥራ ተከናውኗል። ከዚህ በመቀጠል ምርምሩ የተካሄደበትን ማህበረሰባዊና አካባቢያዊ እና ባህላዊ ዳራ ከተገኙ መረጃዎች አንጻር በዝርዝር እንመለከታለን።

3.2.4 የመስክ ገጠመኝ

ከመስክ መረጃ የማሰባሰቡ ሥራ ከአንድ ዓመት በላይ ወስዷል። ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት አንዳንድ የተጠኚው ማህበረሰብ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረበዓላት ለጥናቱ አስፈላጊ እና ወሳኝ ስለሆኑና እነሱም በዓመት አንዴ ብቻ የሚከወኑ በመሆናቸው የሚከወንበትን ጊዜ ጠብቆ ለማየት ሲባል ነው። በመረጃ አሰበሰብ ወቅት ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ አንዱ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ባህላዊ ዘፈኖችን በህብረት ሲጫወቱ ክዋኔውን

በቪድዮ እየቀረጽኩ እያለሁ አንዱ ዘፈን አውራጅ እንዴት እቀረጻለሁ በማለት ለተወሰነ ጊዜ ችግር ፈጥሮ ነበር። ይሁን እንጂ መረጃው ለትምህርታዊ ጥናት የሚውል መሆኑን በማስረዳት ችግሩ ተቃሏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ መስከረም 30 ቀን 2008 ዓ.ም በጨፌ ቱማ ገላን ከተማ በአቃቂ መልካ ላይ በተከበረው የእሬቻ በዓል ላይ መረጃዎችን በማሰባስብበት ወቅት የአገር ሽማግሌዎች[28] በቱለማ አባገዳ ለጨፌ ቱማ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው በሚል የተነሳ ቅሬታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ አስተያያታቸውን እንዳልቀርጽ ከቱለማ አባ ገዳ ጽ/ቤት የተወከለው ግለሰብ ቀረጻ እንዳይከናወን ከልክለዋል። መረጃዎቹ የፈለጉበትን አላማ ብገልጽላቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በመሆኑም ሀሳባቸውን አክብሬ ቀረጻውን በመተው ከሥነቃል ጋር ተያያዥ የሆኑ የምርቃት ክዋኔዎቹን በምልከታ ተከታትዬ በማስታወሻ ይዤለሁ።

በሌላ በኩል በሱሉልታ ወረዳ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ለቃለ-መጠይቅ እና ለቡድን ተኮር ውይይት ቀጠሮ አስይዘው በስብሰባ እና ከክፍያም ጥያቄ ጋር በተያያዘ መልኩ በቀጠሮ ቦታ ተገኝተው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኞች አልሆኑም ነበር። ይሁን እንጂ በዋና መረጃ አቀባዬ አማካይነት ተደጋጋሚ ቀጠሮ በመያዝ ወሳኝ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት እና ተፈላጊውን መረጃዎች ለማሰባሰብ ችያለሁ። በዚህም በሥነቃል ችሎታቸው ታዋቂ የሆኑትን መረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት በማሳተፍ የመረጃ ክፍተት እንዳይፈጠር አድርጌያለሁ። እዚህ ላይ በአሁኑ ዘመን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለተለያዩ ግብዓት የሚያገለግላችውን መረጃ በሚሰበስቡበት ወቅት ለመረጃ አቀባዮቻቸው ክፍያዎችን ስለሚፈጽሙላችውና ይህም በመለመዱ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ይኸው ካልተደረገላቸው መረጃ ለመስጠት ፍቃደኞች አይደሉም። ከዩኒቨርሲቲው ለጥናትና ምርምር የተሰጠው ገንዘብ ደግሞ ይህንን ያላገናዘበ ነው።

ሌላ የገጠመኝ ችግር መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በሱሉልታ ወረዳ ሞገር ቆላ ውስጥ በተከበረው የእሬቻ በዓል ላይ ተገኝቼ የሥነቃል መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሄድኩኝ ጊዜ መንገዱ እልም ያለ ገደል በመሆኑ እና መኪናው በገደሉ ላይ ተንጠልጥሎ ስለሚሄድ ካሁን

---

[28] እንደ ሽማግሌዎቹ አባባል የጥንቱ የሦስቱ ቱለማ መገናኛ ገላን አቃቂ መልካ ያለው የጨፌ ቱማ መሆኑን በመጥቀስ ለክብረ-በዓሉ ትኩረት እንዲሰጥ በየጊዜው ለቱለማ አባገዳ ጥያቄ ቢያቀርቡም ምላሻቸው አጥጋቢ ባለመሆኑ ቦታው በገላን ከተማ አስተዳደር ድጋፍ ብቻ መቆየቱን ይገልጻሉ። ከዚህ የምንረዳው እንደ ገላን ሽማግሌዎች አባባል የሦስቱ ቱለማ እሬቻ ዋናው ቦታ ገላን ያለው ጨፌ ቱማ እንጂ ቡሾፍቱ የሚገኘው ሆራ አርሰዲ አይደለም ባይ ናቸው። ይህንን በሚመለከት ትክክለኝነቱ ለማረጋገጥ ለጥናትና ምርምር የሚጋብዝ ነው።

አሁን መኪናው ይገለበጥ ይሆን የሚል ስጋት እና ጭንቀት ፈጥሮብኝ ነበር። በዚህ ሥጋት ውስጥ አልፌ በቦታው ተገኝቼ መረጃዎችን ሰብስቤ ወደ ደጋው ለመውጣት ስል ቀደም ሲል ከሌሎችም የበዓሉ ታዳሚዎች ጋር ይዞን ወርዶ የነበረው ቅጥቅጥ አይሱዙ ጥሎን በመሄዱ ሌሎች ሰዎችን ጭኖ ወርዶ የነበረውን የጭነት መኪና በዋና መረጃ አቀባዬ አማካይነት ተለምኖልኝ ተሳፍሬ ነበር። ይሁን እንጂ የተሳፈርኩበት የጭነት መኪና የበረሃውን ግማሽ መንገድ ከሄደ በኋላ በመበላሸቱ እዚያ በረሃ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ተቸገርኩ። በኋላ ላይ አንድ ሌላ በሰው የተሞላ የጭነት መኪና በመምጣቱ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች ቅድሚያ ለኔ ሰጥተውኝ ከቆላው ለመውጣት ችያለሁ። ይህም የማይረሳኝ ትዝታ ነው።

ምዕራፍ አራት

4. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳሰሳ፣ የቱለማ አሮሞ ዘር ሀረግና ባህላዊ ዳራ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ማህበረሰብ የኑሮ መሠረት እና ባህላዊ ዳራ የሚመለከቱ መረጃዎች የቀረበበት ነው። በመሆኑም ምዕራፉ ከመረጃ አቀራረብ አኳያ የጥናቱን ክፍል ያካተተ ነው። ርዕሰ ጉዳዩ ራሱን በቻለ ምዕራፍ እንዲቀርብ የተፈለገበት ምክንያት አንድ የኢትኖግራፊ ጥናት በሚደረግበት ወቅት አጥኚው በቦታው በመገኘት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ማህበረሰቡ የሰፈረበት አካባቢና ባህላዊ ዳራን ማወቁ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ማህበረሰቡ ሥነቃሉን የሚናገርባቸውና የሚከውንባቸው አጋጣሚዎች ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በመሆናቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ምዕራፉ ሦስት ርዕሶችን የያዘ ነው። እነሱም የሱሉልታ አጠቃላይ ገጽታ፣ የቱለማ ኦሮሞ የዘር ሀረግና ባህላዊ ዳራ ናቸው። የሱሉልታ አጠቃላይ ገጽታን በሚመለከት የመሬት አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት፣ ማህበራዊ እና አኮኖሚያዊ ተቋማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዝርዝር ቀርበዋል። የቱለማ ኦሮሞ የዘር ሀረግ ሥር ልዩ ልዩ ጎሳዎች፣ ቋንቋ እና ሃይማኖትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ተዘርዝረዋል። ባህላዊ ዳራ በሚመለከት የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚዎች ከጋብቻ፣ ከእንቁጣጣሽ፣ ከእሬቻ እና ከጥምቀት ክብረ-በዓላት አኳያ ዝርዝር መረጃዎች ቀርበዋል። ዝርዝሩን እንደሚከተለው እናያለን።

4.1 የሱሉልታ ወረዳ መሬት አቀማመጥ

በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ከሚገኙ 8 ከተሞች እና 6 ወረዳ ዎች ውስጥ ሱሉልታ አንዷ ናት። የሱሉልታ ወረዳ ወደ ጎጃም መሄጃ መንገድ በስተሰሜን አቅጣጫ ትገኛለች። የወረዳዋ ርዕሰ ከተማ ጫንጮ ስትሆን ከአዲስ አበባ 40 ኪሎ ሜትር ትርቃለች። ሱሉልታ በሰሜን ከውጫሌ ወረዳ እና ከያያ ጉለሌ ወረዳ፣ በደቡብ ከአዲስ አበባ ከተማ፣ በምሥራቅ ከጅዳ ወረዳ እና ከበረክ ወረዳ፣ በምዕራብ ከሙሎ ወረዳ እና ከአደኣ በርጋ ወረዳ ጋር የምትዋሰን መሆኑን ከሱሉልታ ወረዳ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ ያመለክታል (ነሐሴ 2006 ዓ.ም)።

ሱሉልታ በአሁኑ የመስተዳደር መዋቅር በወረዳና በከተማ አስተዳደር ተከፍላ ትገኛለች። የወረዳዋም ሆነ የከተማዋ ስም ሱሉልታ ነው። ወረዳዋ በወረዳ አስተዳደር የሚትመራ

ስትሆን በ23 የገጠር ቀበሌ አስተዳደርና በ3 ከተማ አስተዳደር ተዋቅራለች። ከተማዋ በካንቲባ የሚትተዳደር ስትሆን በ1 ከተማ አስተዳደርና በ3 የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ተዋቅራለች። ምንም እንኳን ሱሉልታ በአስተዳዳራዊ መዋቅሩ ከላይ በተገለጸው አኳኋን ብትከፋፈልም የሕዝቡ አኗኗር እና ባህላዊ ሁኔታዎች ተመሳሳይ በመሆኑ ጥናቱ ወረዳዋንና ከተማዋንም ያካተተ ነው። በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘ መልኩ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከወረዳው እና ከከተማው በመሆኑ መረጃዎቹ ገጠሩንና ከተማውን ያካቱቱ ናቸው። ከዚሁ አንጻር መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት የገጠሩንና የከተማውን ቀበሌዎች ያካተተ የሱሉልታ ወረዳ ካርታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ካርታ 1. የጥናቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ[29]

[29] የካርታዎቹ ቅደም ተከተል በሰዓት አቆጣጠር አቅጣጫ (Clockwise) የተቀመጠ ነው። በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን በክልሎች፣ ኦሮሚያን በዞኖች፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞንን በወረዳዎች እና ሱሉልታ ወረዳን በቀበሌዎች ተከፋፍለው የቀረቡበት ካርታዎች ናቸው። ጥናቱ እንደ አጠቃላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሆኖ ትኩረት ያደረገው በሱሉልታ ወረዳ እና ከተማ ላይ ነው።



4.1.2 የሕዝብ ብዛት

የኢትዮጵያ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንስ እ.ኤ.አ 2007 ዓ.ም. ያወጣው መረጃ የሱሉልታ ወረዳ ሕዝብ ብዛት በፆታ፣ በገጠር እና በከተማ ዘርዝሮ አቅርቧል። በዚሁ መሠረት የሕዝቡ ብዛት በገጠር ወንድ 57,092 ሴት 56,763 በድምሩ 113,855 ሲሆን በከተማ ደግሞ ወንድ 7,424 ሴት 7,721 በድምሩ 15,145 ነው። በጠቅላላው የወረዳው ሕዝብ ብዛት በገጠር እና በከተማ ወንድ **64,516** ሴት **64,484** በድምሩ **129,000** ነበር። ይሁን እንጂ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2006ዓ.ም. ለ2007 ዓ.ም. ዓመታዊ እቅድ ዝግጅት በወረዳው እና በከተማው አስተዳደር በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ በገጠር ያለው ሕዝብ ብዛት ወንድ 68,464 ሴት 68,600 ድምር 137,064 ሲሆን በከተማ ያለ ሕዝብ ብዛት

ወንድ 18,394 ሴት 19,594 ድምር 37,988 ነው። በአጠቃላይ የሱሉልታ ወረዳ ሕዝብ ብዛት ወንድ **86,858** ሴት **88,194** በድምሩ **175,052** መሆኑን ከሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (ሰኔ 2006ዓ.ም.) እና ከሱሉልታ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶች (ነሐሴ 2006 ዓ.ም.) "ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮፋይል" በሚል ርዕስ ካዘጋጁት ሰነድ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህም የሱሉልታ ሕዝብ ቁጥር ባለፉት ሰባት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በገጠር ወንድ11,372 ሴት11,837 በድምሩ በ23 ,209 የጨመረ ሲ ሆን በከተማ ወንድ 10,970 ሴት 11 ,873 በድምሩ በ22,843 ጨምሯል። በጠቅላላው በገጠር እና በከተማ ወንድ **22,342** ሴት **23,710** በድምሩ በ**46,052** መጨመሩን መረጃው ያሳያል። ይህም ሱሉልታ ለአዲስ አበባ ቅርብ እንደመሆኗ መጠን ከኢንቬስቲመንት እና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ጋር በተያያዘ መልኩ ወደዚህ አካባቢ የሕዝብ እንቅስቃሴ መኖሩን ከወረዳው እና ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ደግሞ በአዲስ አበባ የሚታየውን የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ለዚህም አካባቢ ሥጋት መሆኑን በበሽታው ዙሪያ ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ ቤት የተሰበሰቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በሱሉልታ ወረዳ አስተዳደር በኩል የተጠናከረ መረጃ ለማግኘት ባይቻልም በሱሉልታ በከተማ ያለውን የብሔር ብሔረሰብ ስብጥር ስንመለከት ኦሮሞ 73%፣ አማራ 20.8%፣ ጉራጌ 2.5%፣ ትግሬ 2.5%፣ ስልጤ 0.9% እና ሌሎች 0.1% ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በከተማ ያለውን የሃይማኖት ስብጥር ስናይ ደግሞ ኦርቶዶክስ 86.7%፣ እስላም 7.2%፣ ፕሮቴስታንት 5.8% ካቶሊክ 0.1% እና ሌሎች 0.2% መሆኑን የሱሉልታ ከተማ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮፋይል በሚል ስም ሰኔ 2006 ዓ.ም. ከተዘጋጀው መጽሔት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይህም የሚያሳየን ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የኦሮሞ ሕዝብ መሆኑን ነው።

4.1.3. ማህበራዊ ተቋማት

በሱሉልታ ውስጥ ለሕዝቡ በልዩ ልዩ መልኩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ባላቸው አንዳንድ ተቋማት ላይ መረጃዎች ተሰብስቧል። በዚሁ መሠረት በትምህርት እና በጤና ተቋማት ያሉትን ሁኔታዎች እንደሚከተለው እናያለን።

የትምህርት ተቋም፡- ትምህርት ለአንድ ሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው (ICDR, 1999)። በተለይም የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች መዝግቦ ለትውልድ ለማስተላለፍ የተማረ የሰው ኃይል ተፈላጊነቱ የጎላ ነው። ከዚሁ አንጻር በሱሉልታ ያሉትን የትምህርት ተቋማት ስንመለከት 2 የመሰናዶ ት/ቤቶች (11ኛና12ኛክፍል)፣ 4 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (9ኛና 10ኛ ክፍል)፣ 41 አንደኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ት/ቤቶች (ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል) እና 49 አንደኛ ደረጃ 1ኛ ሳይክል ት/ቤቶች (ከ1ኛ- 4ኛ ክፍል) እንዲሁም 2 የቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሉ። በእነዚህ ት/ቤቶች ወንዶች 18,806 ሴቶች 16,729 በድምሩ 35,535 ተማሪዎች በመማር ላይ እንደሉ ከሁለቱም ት/ቤቶች ጽ/ቤት የተገኙ መረጃዎች (ኅዳር፣ 2007 ዓ. ም.) ይጠቁማሉ። እነዚህ በተለያዩ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ከሚማሩት ትምህርት ጋር የአካባቢያቸውን ባህል በማንጸባረቅ ረገድ እያደረጉ ያሉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ከዚሁ አንጻር ይህ ተቋም ለዚህ ጥናት የመጠይቅ መረጃዎችን በማቀበል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው።

በመሆኑም በዚህ ጥናትና ምርምር ውስጥ በሁለቱም 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች (ጫንጮ አባገዳ እና ሱሉልታ) የሚገኙ ተማሪዎች የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የትኞቹ እንደሆኑ፣ እና ከእነዚህ ጋር ተያይዞ የሚነገሩና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን፣ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር ተያይዘው ኤድስን አስመልክቶ ያሉትን የሥነቃል መረጃዎች ከራሳቸው፣ ከወላጆቻቸውና ባህሉን ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው እንዲያቀርቡ፣ እና የባህሉና የሥነቃል ዓይነቶች የመናገር ወይም የመከወን ችሎታ ያላቸውን ሰዎች (ለመረጃ አቀባይነት ለመጠቀም) ከራሳቸው ወይም ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው ፕሮፋይላቸውን ሞልተው እንዲያቀርቡ የላኩላቸውን መጠይቆች በዘዴው ከተሳተፉት ተማሪዎች አብዛኞቹ ተማሪዎች መልስ ሰጥተዋል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በመጠይቅ ዘዴ መረጃዎች ለማግኘት በተደረገው እንቅስቃሴ የተገኘው ውጤት ትምህርት ቤቶች በርካታ ባህላዊ የሆኑ የመረጃዎች የሚገኙባቸው ምንጮች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ይህም በምዕራፍ አምስት በዝርዝር ቀርበዋል።

የጤና ተቋም፡- በሰው ልጅ ሕይወት ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ ጤንነት ዋናው ጉዳይ ነው። ይህ ጥናትና ምርምርም ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዞ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጤና ጋር የሚገናኝ ነው። በመሆኑም ከዚህ ተቋም የሚገኝ መረጃ ጠቃሚና

ወሳኝም ነው። በዚሁ መሠረት በሱሉልታ ያሉትን የጤና ተቋማት በሚመለከት ለሕዝቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ 8 ጤና ጠቢያ፣ 28 የጤና ኬላዎች እና 11 ክልኒኮች አሉ። እነዚህ ተቋማት የሕዝቡን ጤንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ከወረዳው እና ከተማ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሕዝቡን ጤና ተደራሽነት ለማስፋት በወረዳው ውስጥ አንድ አዲስ ሆስፒታል ተሠርቶ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

በዚሁ የጤና አጠባበቅ ሂደት የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ስርጭትን በሚመለከት እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ የደም ምርመራ ያደረጉት ወንድ 17,740፣ ሴት 23,213 በድምሩ 40,953 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ በደማቸው ውስጥ የኤች ኣይ ቪ ቫይረስ የተገኘው ወንድ 595 ሴት 864 በድምሩ 1,459 ናቸው። በበሽታው ከተያዙት ውስጥ መድሃኒት እየወሰዱ ካሉት መካከል ወንድ 268 ሴት 420 ድምር 688 ሲሆኑ በቫይረሱ ከተያዙት ሕይወታቸው ያለፈው ወንድ 46 ሴት 66 ድምር 112 መሆኑን ከሱሉልታ ወረዳ እና ከተማ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የተገኙት መረጃዎች (ነሐሴ፡ 2006 ዓ.ም) ይጠቁማሉ።

በዚሁ መሠረት ከተመረመሩት ውስጥ የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ የተገኘባቸው በመቶኛ ሲሰላ በአከባቢው ያለው የበሽታ ስርጭት 3.56% መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም በአካባቢው የቫይረሱ ሥርጭት መኖሩ ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያይዞ የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችም መኖራቸውን ያመለክታል። ከዚህ አንጻር የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው ከመስክ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ።

4.1.4 ኢኮኖሚያዊ ተቋም

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ባላቸው ግንኙነት ግብርናን፣ ንግድና ገበያ ልማት እና ባህልና ቱሪዝምን እንመለከታለን። ሱሉልታ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ወረዳዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ያላት ብትሆንም ከከብት እርባታ ከምታገኘው ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ውጤቶች አኳያ ከሌሎቹ ትለያለች። በሌላ መልኩ በሱሉልታ የሚገኙ ገበያዎች ለአዲስ አበባ ቅርብ በመሆናቸው ለአካባቢው ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ የጎሉ ናቸው። በሱሉልታ የሚገኙ ተፈጥሯዊ እና ባህላዊ እሴቶች በቱሪዝም መስህብ በኩል ሱሉልታን ከሌሎቹ የተለየች ያደርጉዋታል። በእነዚህ ኤኮኖሚያዊ ተቋማት ውስጥ በርካታ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች

አሉ። በመሆኑም እነዚህን ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እና የሥነቃል ዓይነቶች የመከወኛ አጋጣሚዎችን ከዚህ እንደሚከተለው እናያለን።

ግብርና፡- የሱሉልታ ወረዳ አጠቃላይ የመሬት ስፋት 109,269 ሄክታር ነው። ከዚህ ጠቅላላ የመሬት ይዞታ ውስጥ 56% ለጥ ያለ ሜዳማ መሬት፣ 36% ወጣ ገባ መሬት ሲሆን 8% ደግሞ ተራራማ ነው። የመሬቱን አገልግሎት በተመለከተ 26,662 ሄክታር ለእርሻ አገልግሎት የሚውል ምቹና ምርታማ መሬት፣ 38,720 ሄክታር ለሣር ግጦሽ አገልግሎት የሚውል፣ 15,145 ሄክታር በደን የተሸፈነ መሬት እና 28,742 ሄክታሩ ደግሞ ድንጋያማ፣ በውኃ የተሸፈነ እና በከተማ የመኖሪያ ቤቶች የተያዘ ነው። የአፈር ዓይነቱን በተመለከተ ዳለቻ አፈር 49%፣ ቀይ አፈር 24.5%፣ ጥቁር አፈር 0.5% እና 26% ልዩ ልዩ አፈር ነው።

የአየር ሁኔታው 71% ደጋ፣ 25.4% ወይናደጋ፣ እና 3.6% ቆላ ነው። የሙቀት ሁኔታን በሚመለከት 22.5 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ከፍተኛ፣ 13.43 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መካከለኛ እና 4.4 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ደግሞ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ነው። አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ 1140 ሚሊ ሊትር ሲሆን ከፍተኛው 1447 ሚሊ ሊትር እና ዝቅተኛው 834 ሚሊ ሊትር ነው።

በሌላ መልኩ ክረምት ከበጋ ዓመቱን ሙሉ ሳያቋርጡ የሚፈሱ በወረዳው ታዋቂ የሆኑ 8 ወንዞች አሉ። እነሱም ሲቢሉ፣ አሌልቱ፣ ጫንጮ፣ ጎርፉ፣ ዱበር፣ ሞገር፣ ቦሌ እና ደነባ መሆናቸውን ከወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ ይገልጻል (ነሐሴ 2006ዓ.ም.)። ከእነዚህ ወንዞች ውስጥ አንዳንዶቹ በሥነቃል የሚዘፈንባቸው እንዳሉ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከሱሉልታ ሕዝብ ውስጥ 90% የሚሆነው ኑሮው የተመሠረተው በእርሻ ላይ ነው። ከዚህ ውስጥ 51% በእህል ምርት ላይ የተሠማሩ ሲሆኑ 39% በከብት ርቢ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ይህ አሃዝ ከተሰማሩበት የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያመዝኑበትን ዘርፍ በግብርና በለሙያ ተሰልቶ የቀረበ እንጂ እርሻውንና ከብት ርቢውንም በጥምር የሚያካሂዱ አሉ። የሱሉልታ መሬት አቀማመጥ ለሁለቱም የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚዎች ምቹ በመሆኑ በሰብል ምርት ላይ የተሰማሩት ስንዴ፣ ጤፍና ገብስ በዋናነት የሚያመርቱ ሲሆን ሌሎችም ሰብሎች ባቄላ፣ አተር፣ ምስር፣ ሽንብራ፣ ጓያ፣ ተልባ፣ ኑግና ዘንጋዳ ያመርታሉ። በከብት ርቢ ላይ የተሠማሩት ደግሞ የቤት እንስሳት የቀንድ ከብቶች በተለይ የፈረንጅ

ላሞችን፣ በጎችን፣ ፍየሎችን፣ ፈረሶችን፣ በቅሎዎችን፣ አህዮችን፣ ዶሮችን የሚያረቡ ሲሆን በተለይም ከከብት ርቢ ወተትና የወተት ተዋጽኦው ይገኝበታል። በዚህ ዘርፍ ማህበረሰቡ ከሚያገኘው ጠቀሜታ ባሻገር ለአካባቢውና ለአገሪቱም አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት የ2006 ዓ.ም. ሪፖርት የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

በእነዚህ ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ውስጥ ባህላዊ ጉዳዮች ይከወንባቸዋል። ይህም ገበሬዎች የእርሻና ከብት ርቢ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በርካታ የሥነቃል ዓይነቶችን በተለይም ዘፈኖችን ለሥራቸው ማነቃቂያነት እንደሚዘፍኑ መረጃ አቀባዮች ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ (ህዳር 29 2007 ዓ.ም)ገልጸዋል። ከእነዚህ ዘፈኖች ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱም እንደሚገኙበት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በተንቀሳቀስኩበት ወቅት አረጋግጫለሁ። በመሆኑም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሥነቃል ዓይነቶች በምዳባውና ትንተና ውስጥ ተካተዋል።

ንግድና የገበያ ልማት፡- ገበያዎች ከሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ባሻገር ኅብረተሰቡን እርስ በርስ እንዲገናኙ በማድረግ የጎላ አስተዋጽኦ አላቸው። ከዚሁ አንጻር ለሱሉልታ ወረዳ በንግድ እንቅስቃሴዎች ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎት የሚሰጡ ስድስት የገበያ ቦታዎች አሉ። የገበያ ቀናቶች በጫንጮ ከተማ ማክሰኞ እና ቅዳሜ ቀን፣ በሱሉልታ ከተማ ሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ቀን፣ በዱበር ከተማ እሑድ ቀን፣ በደርባ ከተማ እሑድ ቀን፣ በኤኮ ኤፎ ባቦ ቀበሌ ሐሙስ ቀን እና የጉለሌ ደነባ ቀበሌ እሑድ ቀን በመዋል የንግድ እንቅስቃሴ ይከናወንባቸዋል። በእነዚህ ገበያዎች የአካባቢው ኅብረተሰብ እና የአዲስ አበባ ሕዝብ እንዲሁም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ነጋዴዎች ይገበያዩባቸዋል። ከእነዚህ ገበያዎች በተጨማሪ በሱሉልታ ልዩ ልዩ ንግዶች ይካሔዳሉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሆቴል ቤቶች፣ ምግብና መጠጥ ቤቶች፣ ጠላና አረቄ ቤቶች፣ ጠጅ ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ ልዩ ልዩ ሱቆች ...ወዘተ የንግድ ተቋማት ለአካባቢው ማህበረሰብ ዕለታዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ በተለይም በጠላ ቤቶች፣ በአረቄ ቤቶች እና ጠጅ ቤቶች በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች ይነገራሉ፣ ይከወናሉ። በእነዚህ መጠጥ ቤቶች አዝማሪዎች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤድስን በሚመለከት አዝናኝ የሆኑ ግን ትምህርት የሚሰጡ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ። ለምሳሌ በምልከታ ከተገኙት የዘፈን ግጥሞች የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. Lamatumaa hin deemuu karaa Alemxeenaa	እኔ አልሄድም አለምጤና ሁለተኛ፣
Kan baxxashoo bare baddaan nama seenaa	እምስ የለመደ ጫካ ስለሚያስተኛ።
2. Addisaabaa kana gommaan konkoolaate,	ከአዲስ አበባ ጎማ ተንከባሏል፣
Gara beergoo kana garaan na sodaate;	ይህን አልቤርጎ ሆዴ ፈርቷል፤
Sobaa mitii dhugumaa ,	ሀሰት አይደለም እውነት ነው፣
ganzabini keenya qinxiriitti dhumaa.	ገንዘባችን የሚያልቀው በእምስ ነው።

አዝማሪ ደሱ መገርሳ 13/03/2007 ዓ. ም በጫንጮ አቶ ከበደ ጅሩ ጠጅ ቤት

ከእነዚህ ዘፈኖች የምንረዳው ከየመጠጥ ቤቶቹ በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች የሚገኙ መሆናቸውን በዚህ ጥናት ምልከታ ሥር የተገለጸው ተግባራዊ ሆነዋል። ትንተኔያቸው ወደፊት ባሉት ምዕራፎች በሚመለከታቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሥር ቀርበዋል።

በሌላ በኩል ሱሉልታ ዘመናዊ የኢንዱስትሪ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ከማፍራቱ አንጻር በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች። እስካሁን ድረስ ባለው መረጃ መሠረት በአካባቢው የስሚንቶ፣ የጂፒሰም፣ የሃይላንድ ውኃ መምረቻ ፋብሪካዎች እና የወተትና ወተት ተዋጽኦ አግሮ ፕሮሰሲንግ አቀነባባሪ ድርጅቶች በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ ናቸው። በሌላ መልኩ አዲስ ተሠርቶ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ የመኪና መገጣጠሚያ ፊብሪካም አለ።

እዚህ ላይ የገበያ ቀናት አንዳንድ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችም የሚከወንበት መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም በየገበያዎቹ አካባቢ የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ወጣቶች (የከንፈር ወዳጆች) በእነዚህ ገበያዎች አጋጣሚ በመገናኘት የፍቅር ስሜታቸውን ይለዋወጣሉ። ስጦታም ከገበያ እየገዙ ይሰጣጣሉ። በውሽምነትም የሚፈላለጉ አንዱ የመገናኛ መንገዳቸው እነዚህ የገበያ ቀናት መሆናቸውን መረጃ አቀባዮች (ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ ወ/ሪት ሽቶ አዱኛ፣ አቶ ጉዲሣ አቤቤ እና አቶ ደረጀ መኮንን (ህዳር 29ቀን፣ 2007 ዓ.ም) ገልጸዋል። በመሆኑም በሱሉልታ የሚገኙ የገበያ ቀናት የንግድ እንቅስቃሴዎች ብቻ ሳይሆን ባህላዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችም የሚከናወንባቸው ናቸው።

ባህልና ቱሪዝም፡- የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ እሴቶችን ከቱሪስት መስህብና ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አኳያ ስንመለከት ሱሉልታ የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች አሏት። እነሱም የሞገር ቆላ፣ የቦቂ ጎልባ የተፈጥሮ ደን፣ የደርባ ፏፏቴ እና የሞገር ባግዮን አየር

ትራንስፖርት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ የአየር ትራንስፖርት ሞገር ቆላ ውስጥ 15 ኪሎ ሜትር አቋርጦ የሚሄድ የኤሌክትሪክ መስመር ሲሆን ለብርጭቆ መሥሪያ የሚሆን ማዕድን እና ለሲሚንቶ መሥሪያ የሚያገለግል ጥሬ እቃ ከቆላው ውስጥ ወደ ደጋው የሚያመላልስ በመሆኑ በሱሉልታ ካሉ ሌሎች የሲምንቶ ፋብሪካዎች (ሜድሮክ፣ አብሲኒያ እና የኢትዮ ቻይና) የተለየ ነው ። በእነዚህ ፋብረካ ውስጥ የሚገለግሉ የጉልበት ሠራተኞች ድካም እንዳይሰማቸው በባህላዊ ዘፈኖች ራሳቸውን ያበረታታሉ። ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች በቊልፍ መረጃ አቀባይ አቶ ደረጀ መኮንን አማካይነት ተሰብስበዋል።

ሌላው ለጥናትና ምርምር የሚጋብዙ አዳዲስ ግኝቶች በዚህ አካባቢ ይታያሉ። ከእነዚህም ውስጥ በሱሉልታ ወረዳ ጫንጮ ቡባ ቀበሌ የሚገኘው የኩሽ[30] ጥንታዊ መኖሪያ እና በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ቅርፅ ጥናት መገኘቷ የተረጋገጠው በሱሉልታ ከተማ ወሰርቢ ቀበሌ በተለምዶ ጨፌ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው ልዩ ቦታ የምትገኝ ወፍ[31] (White Winged Fulftail Bird) ተጠቃሽ ናቸው (የሱሉልታ ከተማ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፕሮፋይል፣ 2006)። እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች ለቱሪስት መስህብ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው። ሱሉልታንም በማስተዋወቅ የጎላ ሚና አላቸው።

ከጥናቱ ርዕስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሞጎር ወንዝ ላይ በየዓመቱ መስከረም ወር የሚከበረው የእሬቻ በዓል የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚ ቦታ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አብራርተዋል (አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ሙሉጌታ አያኔ እና ወ/ሮ ጠጅቱ ቂጠታመስከረም 27 ቀን 2007ዓ.ም.)። እኔም እዚህ ቦታ ተገኝቼ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ሰብስቤያለሁ። በዚህ ምርምር ውስጥ በምደባ እና ትንተና ውስጥ ተካተዋል።

4.2 የቱለማ ኦሮሞ የዘር ሀረግ

ከጽሑፍ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለተው የቱለማ የዘር ሐረግ በሥሩ ሦስት ዋና ዋና ጎሳዎች አሉት። ጎሳ የሚለው ቃል በዚህ አገባብ በኦሮሞ መካከል ያለውን የዘር (የደም) ግንኙነት እና የሠፈሩበትን ድንበር ለማሳየት ነው። ይህን በሚመለከት ማሞ ሂቦ (2006፡9) እንዲሚከተለው ገልጿል። "Arsii is one of the majior branches of the Oromo nation.

[30] ይህ ቦታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናትና ምርምር መጀመሩን ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ጥቅምት 2007 የተገኘ መረጃ ይጠቁማል።
[31] ይቺ ወፍ በኢትዮጵያ እና በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ብቻ የሚተገኝ ስትሆን ከኢትየጵያም በሱሉልታና አከባቢዋ ብቻ ትገኛለች። በሣር ውስጥ ተሸሎክልካ የሚትኖር ስትሆን በዓመት ውስጥ የተወሰነ ወቅት ብቻ ትገኛለች። መቼ እንደምትሄድ እና መቼ እንደምትመለስ አልታወቀም። (የሱሉልታ ከተማ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፕሮፋይል ሰኔ 2006 ዓ.ም.)።

The largest level of descent organization among the Arsii Oromo is *gosa (clan), which are territorial units in the most cases".* ሲተረጎም፡- የአርስ ከኦሮሞ ብሔር አንዱ ቅርንጫፍ ነው። በዚህ ዋና ቅርንጫፍ ውስጥ ሌሎች ጎሳዎች አሉ። በተመሳሳይ መልኩ ቱለማ ከኦሮሞ ብሔር ውስጥ አንዱና ዋና ቅርንጫፍ ሲሆን በሥሩ ሌሎች በደም ትስስር ላይ የተመሠረተ የዘር ግንኙነት ያላቸው ጎሳዎች አሉት። በዚህ መሠረት በቱለማ ኦሮሞ ሥር የሚገኙ ጎሳዎች sadeen Daacci (ሦስቱ ዳጮ)፣ jahan Bachoo (ስድስቱ በቾ) እና jahan Jillee (ስድስቱ ጂሌ) ናቸው። የዳጮ ጎሳ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን፣ በደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን፣ በፊንፊኔ (አዲስ አበባ) እና ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ይገኛል። የበቾ ጎሳ በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የጂሌ ጎሳ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ይገኛል።

የ3ቱ ዳጮ ጎሳዎች፡- 6n Galaan (6ቱ ገላን)፣ 7n Oboo (7ቱ አቦ) እና 3n Soddoo (3ቱ ሶዶ) በመባል ይታወቃሉ። 6ቱ ገላን የተባሉት ጂዳ፣ ሊበን፣ ወረጃርሳ፣ ኣቡ፣ አደኣ እና ጋዱላ ናቸው። 7ቱ አቦ ጉምብቹ፣ ጉለሌ፣ አቦሪ፣ ያያ፣ ኤካ፣ ዲገሉ እና ጋሙ ሲሆኑ 3ቱ ሶዶ ደግሞ አድቱ፣ ቱሜ እና ሊበን ናቸው።

የገላን ንዑሳን ጎሣዎች በእያንዳንዳቸዉ ሥር ሌሎች የጎሳ ቤተሰቦች አላቸው። ከዚሁ አኳያ በጂዳ ሥር፤ ኩራ፣ ጋልይ፣ ኬኩ፣ አረብሳ እና ዶዮ። በሊበን ሥር፤ ተሜ እና አቦራ፤ በኣቡ ሥር፤ ሲባ፣ አሙማ እና ኢዶሮ። በወረጃርሶ ሥር፤ ማና፣ አሙማ፣ ባቦ እና ብቶ። በአደኣ ሥር፤ ሁንዳ፣ ኢሉ እና ደኩ። በጋዱላ ሥር፤ መንደዳ፣ በዴሳ፣ ኬረጀጂ፣ ሞመጂ፣ ጄደ እና ቡሲ የሚባሉ የገላን ጎሣ ቤተሰቦች ይገኛሉ። በኦቦ ንዑሳን ጎሣዎች ሥርም እንደዚሁ ሌሎች የጎሳ ቤተሰቦች አሉ። በመሆኑም በጉምብቹ ሥር፤ ሰዮ፣ አካኮ፣ ቦነያ፣ እና መነ አብቹ። በጉለሌ ሥር፤ ረሶ፣ ፉሌሌ፣ ዳዬ፣ ሰዮ፣ አሬሌ፣ ዮያ፣ አልዬ፣ መነጉለሌ፣ ኩረቡ እና አሙማ። በአቦሪ ሥር፤ ለጉ፣ ቀሺሚ፣ እና መነቃተ። በያያ ሥር፤ ዴዴ፣ ቡየመ እና ሶሌ። በኤካ ሥር፤ ኮኖ፣ አከኮ እና መደሮ። በዲገሉ ሥር፤ አሮጂ እና ቤሮ። በጋሙ ሥር፤ ቢላ እና ሲበ የሚባሉ የኦቦ ጎሳ ቤተሰቦች አሉ። የሶዶ ጎሳም በተመሳሳይ ሁኔታ በእያንዳንዱ ንዑሳን ጎሳ ሥር ሌሎች የጎሳ ቤተሰብ ይገኛሉ። እነሱም በአድቱ ሥር፤ ሲባ፣ አባዶ፣ ኢዶሮ ሶሌ እና መሊማ። በቱሜ ሥር፤ ሂዶ እና ጉሳ። በሊበን ሥር፤ በዶ እና ሐርሙፋ በመባል የሚታወቁ የሶዶ ጎሳ ቤተሰቦች አሉ።

በተመሳሳይ መልኩ 6ቱ የበቾ ጎሳዎች በሥራቸው ሌሎች ንዑሳን ጎሳዎች ያሉ ሲሆኑ እነሱም፡- በኢሉ ሥር፤ ብሊ፣ ፋረቾ እና አሬሪ አሉ። በሜታ ሥር፤ አሙማ፣ ኩዩ፣ ወለቆ፣ ሱባ፣ ሲባ፣ ቡዩመ ኣጉ እና አከዩ ይገኛሉ። በገረሱ ሥር፤ ዳዳ፣ ገላን፣ መክፌተ፣ ቱቲ፣ አነጡሬ፣ ማልማ፣ ሊበን እና ማሞ አሉ። በዋጂቱ ሥር፤ ኢሳዋ፣ ኢዶሮ፣ ጨለንቆ፣ ገባሎ፣ አባዬ፣ ያያ፣ ዳሪሙ፣ ዴኙ እና ኢተያ ይገኛሉ። በኬኩ ሥር፤ ዱላ እና ሰሎ የሚገኙ ሲሆን በኡሩ ሥር ደግሞ ባንቱ፣ አሪሮ፣ አባዶ፣ ኘኣ፣ ዋጁ፣ አሙመ፣ ዳየ፣ ደሮ እና ኩዩ ይገኛሉ።

በ6ቱ የጂሌ ጎሳዎችም ሥር ሌሎች ንዑሳን ጎሳዎች (ቅርንጫፎች) አሉ። በዚሁ መሠረት በጎና ሥር ጃርሶ፣ ኣና፣ ናኖ፣ መሊዩ፣ ጉራ፣ አካክሌ፣ ወዩ፣ ሳጸንሳ አቦኖ፣ ኒኒ፣ ቤሬ፣ እና ጅዳ ጂሌ (ኙርጎ) ይገኛሉ። በጉሳ ሥር ሰዶ፣ ያያ፣ ዱለቾ፣ ዌያ፣ እና ሰበንሰ አሉ። በሎዮ ሥር ሲባ፣ መረዋ፣ እና ማሞ ይገኛሉ። በዋሬ ሥር ባዶ፣ ምደ፣ እና ያያ ናቸው። በሲባ ሥር አጎተ፣ ሀልቾያ፣ ብሊደ፣ ሂበን እና ወለዋን የሚገኙ ሲሆን በግንዶ ሥር ደግሞ፤ ኢዶሮ፣ ሰዮ፣ አካዩ፣ ማሩ፣ ኖኖ፣ ጉራ እና ባቦ እንደሚገኙ ዓለማየሁ ኃይሌ (1999፡ 22-26) ይዘረዝራል።

ይህ ጥናት የሚያተኩረው ከቱለማ ኦሮሞ ቅርንጫፎች በዳጪ ላይ ነው። ዳጪ በሥሩ ሌሎች ቅርንጫፎች ወይም ጎሳዎች ያሉት ሲሆን እነሱም ገላን ኦቦ እና ሶዶ መሆናቸው ከላይ ተገልጸዋል። ይህንን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የቱለማ አሮሞ የዘር ሐረግ እና በሥሩ የሚገኙ ጎሳዎችን የሚያሳይ መዋቅር እንዲሁም ጥናቱ በሚያተኮርበት በሱሉልታ የሚገኙ የገላን እና የኦቦ ጎሳዎችና የጎሳ ቤተሰብ ዝርዝር የሚገልጽ ሠንጠረዥ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

መዋቅር 1. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞንና በሱሉልታ[32] የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ዘር ሀረግ



[32] በሱሉልታ የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ከዳጭ ጎሳ ውስጥ የገላን እና የኦቦ ጎሳዎች ናቸው።

[33] ሦስት ማዕዘን ቅርጽ ወንድን የሚያመለክት ነው። በኦሮሞ ባህል የዘር ሀረግ የሚጠራው በአባት በኩል መሆኑን ያሳያል።

[34] ክብ ቅርፅ ሴትን የሚያመለክት ነው

[35] = ምልክት ጋብቻን የሚያመለክት ሲሆን ከምልክቱ ተነስቶ ቀጥ ብሎ የሚወርደው መስመር በጋብቻ የተፈጠሩ ልጆችን ያመለክታል። በዚሁ መሠረት የቱለማ ልጆች፡- በቾ፣ ዳጭ እና ጂሌ ናቸው። የዳጭ ልጆች፡- ገላን፣ አቦ እና ሶዶ ናቸው። የገላን ልጆች፡- ጂዳ፣ ሊበን፣ ኣቡ፣ ወረጃርሳ፣ አደኣ እና ጋዱላ ሲሆኑ የአቦ ልጆች ደግሞ፡- ግምቢቹ፣ ጉለሌ፣ አቦሪ፣ ያያ፣ ኤካ፣ ዲገሉ እና ጋሙ ናቸው።



ከጽሑፍ እና ከመረጃ አቀባዮች በተገኙ መረጃዎች መሠረት ተቀነባብረው የተዘጋጀ (ጥር 2007 ዓ.ም)።

ሠንጠረዥ 3. በገላን ጎሳ ሥር የሚገኙ ንዑስ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች

ተ.ቁ.	6ቱ ጋዱላ	5ቱ ጂዳ	4ቱ ወረጃርሳ	3ቱ ኣቡ	3ቱ አደኣ	2ቱ ሊበን
1	መንዳዳ	ኩራ	ማገሩ	ሲባ	ሀንዳ	ቱሜ
2	በዴሳ	ጋልይ	አሙማ	አሙማ	ኢሉ	አቦራ
3	ኬጃጂ	ኬኩ	ባቦ	ኢዶሮ	ደኩ	
4	ሞማጂ	አረቢሳ	ቢቶ			
5	ጄዳ	ዶዮ				
6	ቡሲ					

ሠንጠረዥ 4. በኦቦ ጎሳ ሥር የሚገኙ ንዑስ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች

ተ.ቁ.	10ሩ ጉለሌ	4ቱ ግምቢቹ	3ቱ ኦቦሪ	3ቱ ያያ	3ቱ ኤካ	2ቱ ዲገሉ	2ቱ ጋሙ
1	ረሳ	ሰዮ	ለጉ	ዴዴ	ኮኖ	አሮጂ	ቢላ
2	ፋሌሌ	አካኮ	ቀሺሚ	ቡየመ	አካካ	ቤሮ	ሲባ
3	ዳዮ	ቦነያ	መነቃተ	ሶሌ	መደሮ		
4	ሰዮ	መነ አብቹ					
5	አሬሌ						
6	ዮያ						
7	ኦልዬ						
8	መነ ጉለሌ						
9	ኩረቡ						

10	አሙሶ						

ከጽሑፍ እና ከመረጃ አቀባዮች በተገኙ መረጃዎች መሠረት የተዘጋጀ (ጥር 2007 ዓ.ም)።

የቱለማ ጎሳ በሠፈረባቸው የኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ የቀበሌና የወረዳ ስሞች ከእነዚህ የቱለማ ጎሳዎችና ንዑስ ጎሳዎች የተወሰዱ መሆናቸውን ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ የጉለሌ እና ኤካ ክፍለ ከተሞች፣ በኦሮሚያ ክልል ደግሞ የበቾ ወረዳ፣ የጃርሶ ወረዳ፣ የገላን ከተማ፣ የመንድዳ ወረዳ፣ ጅዳ ወረዳ፣ የሚጥቀሱ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በሱሉልታ ወረዳ እና ከተማ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቀበሌዎች ስማቸው[36] የገላንና የአቦ ጎሳ እና ጎሳ ቤተሰብ ስሞች ናቸው።

እነዚህ የቱለማ ኦሮሞ ቅርንጫፎች በሚኖሩበት አከባቢ ተመሳሳይ ቋንቋ እና ባህላዊ እምነት አላቸው። ከዚሁ አንጻር ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ በተለይም ከሥነቃል ዓይነቶች መገለጫነት አኳያ ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

4.2.1. ቋንቋ

የኦሮሞ ሕዝብ የሚግባባበት አንድ የጋራ ቋንቋ ያለው ሲሆን እሱም አፋን ኦሮሞ ይባላል። አፋን ኦሮሞ ከኩሽ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ሲሆን በአፍሪካ ውስጥ በስፋት ከሚነገሩ ከአረብኛና ሀውሳ ቋንቋዎች ቀጥለው በ3ኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን Gadaa Mebaa (1988: 9)፣ Mahdi Hamid (1995: xi) እና Dirribii Daamusee (2009: 14) ይገልጻሉ። ይህ ቋንቋ በሸዋ፣ በአርሲ፣ በሀረርጌ፣ በባሌ፣ በወለጋ፣ በኢሉ አባቦር፣ በጂማ እና በወሎ የአፍ መፍቻ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከአፍረካ ውስጥ በኬንያ፣ ከኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በደቡብ ህዝቦች ክልል እና በአማራ ክልል እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ይነገራል (Sumner: 1996)። ይህ ቋንቋ በኦሮሚያ ክልል እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በተመለከተ አፋን ኦሮሞ እና የኢትዮጵያ ቋንቋ ፖሊሲ በሚል መጽሐፍ ውስጥ እንድሚከተለው ተገልጿል።

> Naannoo Oromiyaatti afaan hojii ta'ee jira. … Afaan kun afaan barnoota sadarkaa duraa, afaan midiyaa (subqunnamtii), afaan hogbarruu, afan dhadhachaa, afan mana amantii fii yunivarsitii gargaraa keessatti immoo akka mummee qorannoo tokkotti sadarkaa digrii tokkooffaa fi lammaaffatti kennamaa jira." (Milkeessaa Miidhagaa, 2015: 16).

ሲተረጎም

[36] የጥናቱን ቦታ ከሚያሳዩ ካርታዎች ውስጥ የሱሉልታ ወረዳ ቀበሌዎችን ስም ይመልከቱ።

> አፋን ኦሮሞ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የሥራ ቋንቋ፣ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን የሕዝብ ግንኙነት ቋንቋ፣ የሥነጽሑፍ ቋንቋ እና የፍርድ ቤት ቋንቋ በመሆን አገልግሎት እየሰጠ ከመሆኑም በላይ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በዩኒቨርሲቲም ደረጃ እስከ ማስተርስ ድረስ እንደ አንድ የትምርት ዘርፍ የጥናትና ምርምር ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ከዚህ የምንገነዘበው ቋንቋው የኦሮሞን ሕዝብ ማንነት እና ባህል በማንጸባረቁ ረገድ በአሁኑ ዘመን ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ መሆኑን ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ እና በዙሪያው የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ እየተጠቀመበት ይገኛል። በመሆኑም ቋንቋው አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዲደርስና ባህሉንም ጠብቆ በማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላፉ ረገድ የጎላ ሚና ተጫውቷል። ለዚህም ሥነቃሎቹ ባህሉን በማንፀባረቁ በኩል ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አቶ ሙሉጌታ አያኔ፣ አቶ ሰይፉ መልካ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና አቶ ተስፋዬ ሁንዴ (ህዳር፡ 2007 ዓ.ም.)ይገልጻሉ።

በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ ከሌሎች የኦሮሞ ቅርንጫፎች እና በሌሎች አካባቢ ከሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ ተለይቶ ከሚታወቁበት አንዱ በአንዳንድ ቃላት በድምፅ በሚፈጥር የ"cha" (ቻ) ቅጥያ አጠቃቀሙ ነው። ለምሳሌ የመጫ ኦሮሞ ወይም በሌሎች አካባቢ የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ የ"ssa" (ሳ) ን ድምፅ ሲጠቀም፣ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ የ"cha" (ቻ)ን ድምፅ ይጠቀማል (መረጃ አቀባይ አቶ ደረጀ መኮንን ህዳር 27ቀን 2007 ዓ.ም)።

በዚህም በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ተወልዶ ያደገ አንድ የቱለማ ኦሮሞ ከሌሎች የኦሮሞ ቅርንጫፎች መለየት ይቻላል። ይህንንም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አንዳንድ ቃላትን እንደ ምሳሌ ወስደን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 5. የመጫ እና ቱለማ ኦሮሞ ቃላት ላይ ቅጥያ አጠቃቀም ማሳያ

የመጫ ኦሮሞ /በሌላ አካባቢ የሚገኝቱለማ ሲናገር	በፊንፊነኔ ዙሪያ የሚገኝ ቱለማ ሲናገር	የአማርኛ ትርጉም
Addee<u>ssa</u>	Addee<u>cha</u>	ጨረቃ
Arraage<u>ssa</u>	Arraage<u>cha</u>	ቁራ

Balleessaa	Balleechaa	ጥፋት
Eessa	Eecha	የት
Kalessa	Kalecha	ትላንትና
Keessa	Keecha	ውስጥ
Keessummaa	Keechummaa	እንግዳ
Lammeessaa	Lammeechaa	የሰው ስም
Waddeessa		Waddeecha

የእነጨት ዓይነት

Waraabessa	Waraabecha	ጅብ

ምንጭ፡- የማህበረሰቡን የቅጥያ አጠቃቀም መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ (ጥር 2007ዓ.ም)።

እነዚህ የቅጥያ (ዘዬ) እንጂ የትርጉም ልዩነት የላቸውም። ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነቱ የቋንቋ አጠቃቀም በፊንፊኔ ዙሪያ ያሉ የቱለማ ኦሮሞን የሚገልጹ ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች በሥነቃል ዓይነቶቹ ውስጥም በስፋት የሚንፀባረቁ ናቸው። ለምሳሌ በቀልዶች፣ በተረቶች፣ በዘፈኖች፣ ... ወዘተ ቱለማ የ'ቻ'ን ቅጥያ ያዘወትራል። በዚህ ጥናት ውስጥ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ያመለክታሉ። ቀጥሎ እምነቱን እንመለከታለን።

4.2.2 ሃይማኖት

ሐይማኖት የሰው ልጅ ዓለምን የሚገነዘብበት እና ስለ ሕይወት አመጣጥ የሚረዳበት መንፈሳዊ እውቀት ነው። ከዚሁ አኳያ ኦሮሞ ዓለምን የሚገነዘብበት የራሱ የሆነ እምነት ያለው ሲሆን ይህንንም በፈጣሪ እና በተፈጥሮ ይገልጻል። ይህንኑ አስመልክቶ የኦሮሞ አመለካከት Ilaalcha Oromoo በሚል መጽሐፍ ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል። "Akaakileen keenya sirna bulchiinsa ofii kan ta'e sirna Gadaatiin of bulchaa turan; akkaataa ittiin Umaa fi Umama ilaalan 'Dhugeeffannoo' (Mythology) amantaa ofii Waqeeffanaa qabu" (Dirribii Damisee, 2009: 14).

ይህ ሲተረጎም አያቶቻችን በራሳቸው የአስተዳደር ሥርዓት በገዳ ይተዳደሩ ነበር። ፈጣሪ እና ተፈጥሮን የሚመለከቱበት ሚቶሎጂ የራሳቸው የሆነ የዋቄፈና እምነት ነበራቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር የኦሮሞ ሕዝብ በፈጣሪ እና በተፈጥሮ

መካካል መኖሩንና ይህንንም በእምነቱ እንደሚገልጽ በመጥቀስ የኦሮሞን ዓለም አመለካከት ማሞ ሄቦ እንደሚከተለው ይገልጻል።

> In Oromo world-view, nature and divinits are interconnected. The interconnection is expressed at a number of customary settings. In most of the Arsi Oromo religious or ritual settings, for instance, *waaqaa* (God) and *lafa* (Land or earth) are mentioned in duality. Arsi Oromo believe human beings existed in the between God and earth. That is, human beings live on the earth and under the God. …, that is, God sees (observes) from the above and earth listens from the below. All human actions, reveals an aspect of this duality and of human position in regard to earth and God (2006፡39).

ሲተረጎም

> በኦሮሞ የዓለም አመለካከት ከፈጣሪ እና ከተፈጥሮ ጋር የተገናኙ ናቸው። እነዚህ ግንኙነቶች በበርካታ እምነታዊ አውዶች ውስጥ ይገለጻሉ። ለምሳሌ በአብዛኛው የአርሲ ኦሮሞ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክብረበዓላት ላይ እግዚአብሔር እና መሬት በአንድነት ይገለጻሉ። በአርሲ ኦሮሞ እምነት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር እና በመሬት መሐከል ይኖራል። ይህ ማለት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ሥር በመሬት ላይ ይኖራል። ይህም እግዚአብሔር ከላይ ያያል መሬት ደግሞ ከሥር ትሰማለች። የሁሉም ሰው ተግባር ከእግዚአብሔር እና ከመሬት አንጻር የሚገለጽ ነው።

ከዚህ የምንገነዘበው በኦሮሞ እምነት መሠረት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር (ፈጣሪ) ሥር እና በመሬት (ተፈጥሮ) ላይ የሚኖር መሆኑን ነው። እምነቱንም የሚገልጸው እግዚአብሔር ከላይ አይቶ መሬት ከታች ሰምታ መሆኑን በመረዳት ነው። ይህም የሚያሳየን ኦሮሞ ዓለምን የሚገነዘብበት የራሱ ሚት አመለካከት (myth) ያለው መሆኑን ነው።

ኦሮሞ በፈጣሪ እና በተፈጥሮ ላይ ያለውን እምነት በሥነቃል ውስጥ በአባባል ይገለገልበታል። ለዚህም ማረጋገጫው ይህን ጥናት ባደረኩበት አካባቢ ያሀገር ሽማግሌችን[37] ጠይቄአቸው ያገኘሁት መረጃ የኦሮሞ ሽማግሌዎች የተጣሉትን ሰዎች ሲያስታርቁአቸው Waaqaaf lafaa jedhaa araaramaa. ይህ ማለት ለእግዚአብሔር እና ለመሬት ስትሉ ታረቁ፤ ይላሉ። ከዚሁ ከእርቅ ጋር በተያያዘ መልኩ አንድ የተበደለ ሰው በእርቁ ሂደት እውነት ካልተገኘለት ጉዳዩን ለመተው ከፈለገ Waaqaai fi lafatti kennedhe. ማለት ም ለእግዚአብሔር እና ለመሬት/ ምድር ሰጥቻለሁ፤ ይላል። እነዚህ

[37] መረጃ አቀባዮች (አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ታደሰ ደህኔ፣ ሰይፉ መልካ እና አቶ ደረጀ መኮንን ኅዳር 2007ዓ.ም.)

ከጽሑፍ እና ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተገኙት መረጃዎች በየትኛውም አካባቢ የሚገኝ ኦሮሞ ዓለምን የሚመለከተው በተመሳሳይ መልኩ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

በሌላ መልኩ ኦሮሞ የክርስትና እና የእስልምና ሓይማኖቶችን ከተቀበለም በኋላም ቢሆን አብዘኛው ኦሮሞ ነባር እምነቱን አልተወም። ይህን በሚመለከት [የገዳ መልባ - Oromia] 'ኦሮሚያ' (የኦሮሚያ ሕዝብ ታሪክ) በሚል መጽሐፍ ባኃሮ ቢያንሳ (1985፡ 36) በተረጎመው ውስጥ የBartles, (1983) ሥራ በመጥቀስ እንዲህ ሲል እውነቱን ይገልጻል።

> ክርስቲያን ኦሮሞዎችም ሆኑ እስላም ኦሮሞዎች ስለመለኮት ያላቸው ባህላዊ ልማድ በሁለቱ ሃይማኖቶች መንፈሳዊ ካባ የተጻፈነ ቢሆንም መለኮታዊ አከባበራቸው ሳይቃወስ እየታሰበ ነው። አያሌ ኦሮሞዎች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ወደ "ገልማ" እየሄዱ የሚፈለግባቸውን ከበሬታ ለጎሳቸው "ቃሉ" ሲገልጹ ነበር። ይኸው ሁኔታ ከአቢሲንያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነት በሚከሄድባቸው ስፍራዎች ሁሉ ይበልጥ ተረጋግጦ የሚስተዋል ነው።

በማያያዝም ለምዕተ ዓመታት በግፍና በጭቆና ውስጥ ሲማቅቅ የኖረ ኦሮሞ መከራውን ሁሉ ተቋቁሞ ቋንቋንና ባህሉን ጠብቆ መዝለቁን እና አሁንም ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እያጎለበተ መምጣቱን፣ ለዚህም የኦሮሞ ፎክሎር እንደ ዓይነተኛ መሳሪያ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ባኃሮ ቢያንሣ (1985፡ 160) ይገልጻል ።

የገዳ ሥርዓት ባህላዊ እንቅስቃሴዎች እንዲቀጥሉ በተደረገው ጥረት ውስጥ ምንም እንኳን በርካታ ኦሮሞዎች ቢሞቱም የገዳ ሥርዓቱ በተወሰኑ የኦሮሞ ጎሳዎች ተግባራዊ ከመሆን አልተቆጠበም። ለዚህም የኦሮሞ ሥነቃል ዓይነቶች ዘፈኖች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተረቶች ወዘተ… የነበራቸው ሚና የጎላ ነው። በሌላ መልኩ በእምነታዊ ክብረበዓላት ላይ የሚዘፈኑ የኦሮሞ ባህላዊ ዘፈኖችን አስመልክተው በአንዳንድ አከባቢዎች በተለይም በሸዋ ውስጥ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተፅዕኖ የጎላ አለመሆኑ ለሥነቃሎቹ በቀጣይነት መኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ይህንን አስመልክተው ወርቅነህ ቀልቤሳ እንዲህ ይላል።

> Some Oromo were killed for trying to promote the *gadaa* system. In spite of this the Oromo *gadaa* system has been living tradition among the Borana, Guji and Gabra Oromo in sourthen Ethiopia. There have been democratic values and practices without the functioning of the political aspects of *gadaa* in some parts of Oromo lands where the people practice Orthodox Christianity and/or the indeginous Oromo religion (Workineh Kelbessa, 2014፡ 42).

ከዚሁ አንጻር የቱለማ ኦሮሞ በአብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታይ ቢሆንም ጥንታዊ እምነቱን ከአዲሱ ሀይማኖት ጋር በማዋሃድ ባህላዊ እሴቶቹን ጠብቆ ኖሯል። ይህንንም በበርካታ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ክብረበዓላት ላይ በልዩ ልዩ የሥነቃል ዓይነቶች አማካይነት እየገለጸ ይገኛል። በመሆኑም እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶችን መከወኛ አጋጣሚዎች ከባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ክብረበዓላት አኳያ ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

4.3 የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ዳራ

በሱሉልታ ወረዳ በቱለማ ኦሮሞ የሚከበሩ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ሐይማኖታዊ ክብረበዓላት ማህበረሰቡ ባህላዊ ትውፊታቸውን ጠብቆ የሚያቆዩባቸው የሥነቃል ዓይነቶች የመከወኛ አጋጣሚዎች ሲሆኑ ለማህበረሰቡም የእርስ በእርስ ግንኙነት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በሰላሌ የሚገኝ የቱለማ ኦሮሞ በሥነቃል ችሎታው በተለይም በዘፈን በጣም የታወቀ ነው (ታደሰ አለሙ፣ 1974)። በሱሉልታ የሚገኝ አሮሞ የዚሁ ቱላማ የዘር ግንድ በመሆኑ በልዩ ልዩ ክብረበዓላት ላይ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነታቸውን በሥነቃል የሚገልጽ ሲሆን ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በተለያዩ ዜማዎች የሚተቹበትም መድረክ ነው።

በመሆኑም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተገናኘ መልኩ የሥነቃል ዓይነቶቹ የሚከወኑባቸውን ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት እናያለን። ከዚሁ አንጻር ከሁሉ በፊት የሰው ልጅ መፍጠሪያ ከሆኑት አንዱና ዋንኛው ጋብቻ በመሆኑ ከዚህ በመቀጠል በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች የሚነገሩበት እና የሚከወኑበት ባህላዊ ጋብቻን በአጭሩ እንመለከታለን።

4.3.1 የጋብቻ ባህል

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር እንደሚያመለክቱት አንድ ግለሰብ ከነበረበት ማህበራዊ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገርበት ሁነቶች መኖራቸውን ነው። ከሽግግሮቹ አንዱ ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስ ነው። ይህም በጋብቻ ይገለጻል። ጋብቻ የማህበራዊ ሕይወት መሠረት እና የዜጎች መፍለቂያ ነው። ጋብቻ በተቃራኒ ፆታ መካከል ለቤተሰብ ምሥረታ እና ለሌሎችም ጠቀሜታዎች የሚመሰረት ነው።

በጋብቻ እና ቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ምርምር ካደረጉት ምሁራን ውስጥ Olson (2000:8) ጋብቻን እንዲህ ይገልጻል። " Marriage is by nature a multifaceted institution. We define marriage as the emotional and legal commitment of two people to share

emotional and physical intimacy, various tasks, economic resource". ይህ ማለት ጋብቻ በተፈጥሮ ፈረጀ ብዙ ተቋም ነው። ጋብቻ በሁለት ሰዎች መካከል ሕጋዊ መሠረት ያለውና በመተማመን የሚመሰረት ሲሆን ወሲባዊ ስሜትን ለመካፈልና ለሌሎችም የወል ጥቅሞች ሕይወት በጋራ የሚመራበት ዘዴ መሆኑን ነው። በመሆኑም ጋብቻ ሰዎች በማህበራዊ ህይወታቸው ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ሥርዓት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው።

የቱለማ ኦሮሞ ባህሉን ጠብቆ ከቆየባቸው ልማዳዊ ድርጊቶች አንዱ ጋብቻ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አቶ ተስፋዬ ሁንዴ እና አቶ ጉዲሳ አቤቤ (ጥር፣ 2007 ዓ. ም.) ገልጸዋል። የዚህን ማህበረሰብ የጋብቻ ዓይነቶች እና አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ከጥናቱ ተሳታፊዎች በቃለ-መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንዲሁም ከጋብቻ ዓይነቶች ጋር ተያይዞ በሽማግሌች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና በወጣቶች የተዘፈኑ ዘፈኖችም በርካታ ሲሆኑ ከልዩ ልዩ መቼቶች የተገኙ መረጃዎችም ተሰብስበዋል። እነሱም በምዕራፍ አምስት ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል። በመቀጠል ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ትኩረት ተሰጥተዋቸው የሚከበሩትን ክብረ-በዓላት እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

4.3.2 እንቁጣጣሽ

እንቁጣጣሽ በአፋን ኦሮሞ (Ayyaana Qaamee) በልጃገረዶች ጭፈራ ይታወቃል። በዚህ በዓል ላይ የቱለማ ኦሮሞ ልጃገረዶች በየዓመቱ ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ እንግጫ (qunni) የሚባል ሣር በመንቀል በማግስቱ ማለትም መስከረም 1 ቀን ክብረ-በዓሉን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ዘፈኖችን በልዩ ልዩ ዜማ በማዜም እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እንግጫውን በየቤቱ እየዞሩ ያድላሉ፤ ይጨፍራሉ። በዚህን ጊዜ ባለቤቶቹ እንጀራ በሰፌድ ላይ አድርገው ይሰጧቸዋል። ልጃገረዶቹም የተሰጣቸውን ቀምሰው በባህሉ መሠረት መርቀው ከዚያም እየዘፈኑ ይጨፍራሉ። ምንም እንኳን ክበረ-በዓሉ የልጃገረዶች ቢሆንም ጎሮምሶችም በዘፈኑና ጭፈራው ሰበብ አብረው ይዞራሉ። በተለይም ከልጃገረዶቹ ጓደኛ ባለፈው ዓመት ያገባች በአፋን ኦሮሞ (Barnoo) ካለች በእሷ ቤት የተለየ ቆይታ አድርገው በደንብ ይጨፍራሉ። ወንዶቹ የከንፈር ወዳጆቻቸውን ይስማሉ። በዚህ ክብረ-በዓል ቀን ልጃገረዶች እና ጎሮምሶች በነፃነት አብረው እየዘፈኑ፣ እየጨፈሩ እና እየተሳሳሙ

የሚውሉበት ቀን መሆኑን መረጃ አቀባዮች አብራርተዋል (ወ/ሮ ጠጁቱ ቂጠታ እና ወ/ሪት ሽቶ አዱኛ፣ ጥቅምት 2007)።

4.3.3 የእሬቻ በዓል

እያንዳንዱ ኅብረተሰብ ፈጣሪ አምላኩን የሚለምንበትና የሚያመሰግንበት የራሱ የሆነ የእምነት ሥርዓት አለው። የኦሮሞ ሕዝብ በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ የኩሽ ዘሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን ረዥም ዘመን ያስቆጠረ የራሱ የሆነ ባህላዊ እምነት አለው። ይህ ባህላዊ የእምነት ሥርዓት እሬቻ ይባላል። እሬቻን በሚመለከት ዓለማየሁ ኃይሌ፣ (1999፡ 79-80) እንደሚከተለው ገልጿል።

> በኦሮሞ ባህል ውስጥ ከሚገኙ የእምነት ሥርዓቶች አንዱ እሬቻ ነው። እሬቻ ማለት ምሥጋና ለአምላክ ለማቅረብ የሚከናወን ሓይማኖታዊ ሥርዓት ነው። የሚከናወነው የምልጃና የምሥጋና ተግባር በቦታና በጊዜ የተወሰነ ነው። የእሬቻ በዓል በተለያዩ ቦታዎች ሊከናወን የሚችል ቢሆንም ታላላቅ የሚባሉት ግን ሁለት ቦታዎች የሚከናወኑት ናቸው። እነዚህም የተራራ ላይ እሬቻ እና የመልካ (ወንዝ) ላይ የሚደረግ እሬቻ ናቸው።

ከዚህ የምንረዳው ይህን የእምነት የሚከተሉ ኦሮሞዎች በአንድ በተመረጠ ቦታ እና በተወሰነ ወቅት በአንድ ላይ ተሰብስበው ፈጣሪያቸውን ከሚለምኑበትና ምሥጋናቸውን ከሚያቀርቡበት ሥርዓት አንዱ የእሬቻ ክብረ-በዓል መሆኑን ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከአሁን በፊት ለኮርስ ማሟያ በእሬቻ ላይ ጥናት ባደረኩበት ወቅት በአገኘሁት መረጃ መሠረት እሬቻ ማለት እርጥብ ሣር እና አበባ በመያዝ ለእሬቻ በተመረጠ ቦታ ላይ በማስቀመጥ ለፈጣሪ ምሥጋና ማቅረብ እና ፈጣሪን መለመን መሆኑንና ይህ የእምነት ሥርዓት እግዚአብሔርን ማምለክ (Waaqeeffannaa) እንደሚባል መረጃ አቀባዮች አቶ ለማ ጉያ፣ አቶ ደስታ ገመዳ[38] እና አቶ ኩማ ኢደኤ፡ (2003) ተናግረዋል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የእምነቱን ቦታ እና ጊዜያት በሚመለከት መረጃ አቀባይ አቶ ኩማ ኢደኤ፣ (2003) እንደሚከተለው አብራርቷል።

> በኦሮሞ እምነት መሠረት እሬቻ የሚካሄድባቸው ቦታዎች ከመልካ (ወንዞች ወይም ሐይቆች) ውስጥ በተመረጠው መልካ እንዲሁም ከተራሮችም ውስጥ በተመረጠው ተራራ እሬቻ ይደረጋል እንጂ በተገኘው ወንዝ እና ተራራ የእሬቻ ሥርዓቶች እንደማይከናወኑ አስረድተዋል። በወንዞች (ሐይቆች) በዓሉ የሚከበረዉ ክረምት ከወጣ በኋላ በመስከረም ወር ሲሆን በተራራ የሚከበረው ደግሞ በመጋቢት ወር ነው። በዚሁ መሠረት የቱለማ ኦሮሞ በተመሳሳይ ወቅት በየአካባቢው እሬቻ የሚያደርግበት የየራሱ ቦታዎች ያሉት ቢሆንም ሁሉም በጋራ የሚያከብሩት

[38] እኚህ መረጃ አቀባይ በአሁኑ ሰዓት በሕይወት የሉም።

> ከሐይቅ የቢሾፍቱ ሆረአርሰዲን፣ ከተራራ ጋራ ጩቃላን (ዝቋላን) ናቸው።
> ማህበረሰቡ እነዚህን ቦታዎች የመረጠበት የራሱ ታሪካዊ ምክንያት አለው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የኦሮሞ እሬቻ ሥነሥርዓት ላይ ለሁለተኛ ዲግሪያቸው ማሟያ ጥናት ያደረጉት Hailu Ejerssaa (2009) እና Mesekerm Assaged (2009) እንዲሁም ለሦስተኛ ዲግሪ መሟያ በቱለማ ኦሮሞ ተረቶች ላይ ጥናት ያደረገው Desta Desalegn (2015) የመልካ እና የተራራ እሬቻዎች እንዳሉ በመግለጽ የእሬቻ መከበሪያ ጊዜያት የመልካው ክረምት ወራት አልፈው መስከረም ወር ውስጥ፣ የተራራው ደረቅ ወራት አልፈው በመጋቢት ወር ውስጥ መሆናቸውን ገልጸዋል። በዚህም በአቶ ኩማ ኢደኤ ሀሳብ ይስማማሉ።

በዚህ ጥናት ውስጥም በምልከታ እንዳረጋገጠው በመልካ የእሬቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች ሲነገሩ እና ሲከወኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ይህም ሽማግሌዎች በምረቃ ወጣቶች በዘፈንና በጭፈራ ክብረ በዓሉን ሲያደምቁ ታይተዋል። ይህንን በሚመለከት ከብሾፍቱ ሆረ አርሰዲ መልካ፣ ከሱሉልታ ሞገር መልካ እና ከገላን ጫፌ ቱማ አቃቂ መልካ የተሰበሰቡት መረጃዎች በምዕራፍ አምስት ውስጥ ቀርበው ተመድበዋል። ከእነዚህ የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ በሚመለከታቸው ርዕሶች ሥር ተተንትነዋል።

4.3.4 የጥምቀት በዓል

ይህ ክብረ-በዓል በቱለማ አሮሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሂዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው እና ባህላዊ ተግባራትም የሚከወንበት ነው። የጥምቀት በዓል በእምነቱ ተከታዮች ሁሉ የሚከበር ቢሆንም በተለይ ለወጣቶች ልዩ ሥፍራ አለው። ወጣቶች አዳዲስ ልብሶችን ለብሰው፣ ታጥበው፣ ተቆነጃጅተው እና አምረው ልዩ ልዩ ዜማ ያላቸውን ዘፈኖች እየዘፈኑ እና እየጨፈሩ በዓሉን እንደሚያደምቁት በታቦታት የንግስ ፕሮግራም የመስክ ምልከታ በተላያዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ ለማየት ችያለሁ። እንዲሁም መረጃ አቀባዮች አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ (ህዳር 2007 ዓ.ም.) ይህንኑ የሚያጠናክር መረጃዎችን ሰጥተዋል።

በተለይም በሰላሌ እና በሱሉልታ የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ወጣቶች በዘፈን የታወቁ በመሆናቸው ወቅታዊ የሆኑ ዘፈኖችን የማውጣት የተለየ ተሰጥኦ አላቸው። በመሆኑም በጥምቀት ክብረበዓል ላይ በርካታ እና ወቅታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና

ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ። ፖለቲካዊ ዘፈኖች የዘመኑን አስተዳደራዊ ጉድለቶችን የሚተቹና መስተካከል እንዳለባቸው የሚያሳስቡ ናቸው። እነዚህ ዘፈኖች ሥነቃል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉድለቶች በማሳየት ረገድ የጎላ ሚና እንዳላቸው በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተገለጹትን የሚያጠናክሩ ናቸው። ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ በርካታ የሥነቃል መረጃዎች በአብዛኛው የተገኙት ከዚህ ክብረ በዓል ሲሆን በሌሎች የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚዎች ከተሰበሰቡት ጋር ተበድበው በዚህ ውስጥ አባሪ ተደርገዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በልዩ ልዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ከልዩ ልዩ የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከነምንጫቸው በሚቀጥለው ምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ምዕራፍ አምስት

5. ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማቅረብ

ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ከመመደባቸው በፊት በትክክል መደራጀትና መጠናቀር አለባቸው። ይህ ማለት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለምደባ በሚያመች መልኩ አስተካክሎ ማዘጋጀት ማለት ነው። ይህም በየተሰበሰቡበት የመረጃ ማሰበሰቢያ ዘዴ ለየብቻ አደራጅቶ ማቅረብ አንዱ የመረጃ አቀራረብ ስልት ነው። በመሆኑም ይህ ምዕራፍ በመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ ማሰበሰቢያ ዘዴዎች የተገኙትን መረጃዎች ማቅረብና መግለጽ ላይ የሚያተኩር ነው። ከዚሁ አንጻር በእያንዳንዱ ዘዴ ሥር ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፣ የመረጃ ሰጪዎች ማንነት እና መረጃዎቹ የተገኙበት አውድ በዝርዝር ቀርበዋል።

እነዚህ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ በአንዱ ዘዴ የተገኘ መረጃ በሌላ ዘዴ ከተገኘው በተወሰነ መልኩ ልዩነት ቢኖረውም

በአብዛኛው ተመሳሳይነት አላቸው። ይህም ማለት መረጃ ሰጪዎቹ የተለያዩ ቢሆኑም የሥነቃል ዓይነቶቹን በተመለከተ ያላቸው እውቀት ተቀራራቢ ነው። ስለዚህ በአንዱ ዘዴ ሥር የተገለጸው መረጃ በሌለኛው ዘዴ ሥር ቢኖርም አልተደገመም። ለምሳሌ በቃለ- መጠይቅ የተገኘ መረጃ በምልከታ ዘዴ ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ የተመደበው ከሁለቱ ዘዴዎች ቀድሞ በተገኘበት በአንዱ ዘዴ ሥር ብቻ ነው። ይህም የሆነው ተመሳሳይ መረጃዎች እንዳይደጋገሙ ታስቦ ነው። ከዚሁ አኳያ በእያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙ መረጃዎችን በተናጠል መመልከቱ ጠቃሚና አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው እናያለን።

5.1 በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው መጠይቁን እንዲሞሉ የኦሮምኛ ቋንቋ ችሎታና ባህሉን ለሚያውቁ 100 ተማሪዎች ተሰጥተዋል። ከእነዚህ ውስጥ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ ከጫንጮ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት 48(24 ወንዶች እና 24 ሴቶች) እንዲሁም ከሱሉልታ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት 46 (24 ወንዶች እና 22 ሴቶች) በድምሩ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች 94 (48 ወንዶች እና 46 ሴቶች) ናቸው። በዚህ መሠረት ጥያቄቹን መሠረት በማድረግ ከእነዚህ ተማሪዎች የተገኙት ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. ተማሪዎቹ በሚኖሩበት አካባቢ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ዓይነቶችን እንዲገልጹ በተጠየቁት መሠረት የተገኙ መረጃዎች በአብዛኛው ተመሳሳይነት አላቸው። በዚሁ መሠረት በምላሹ ከተሳተፉ 94 ተማሪዎች (48 ወንዶች እና 46 ሴቶች) የተገኘው ውጤት በሱሉልታ አከባቢ በባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ሥር የሚመደቡት Wadaajii (የከንፈር ወዳጅ)፣ Sanyoo (ውሽማ)፣ Sigabaa (ሲገባ) እና Irree (እሬ) ናቸው።

ከተማሪዎች የተገኙት ምላሾች በዚህ ጥናት ምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዳራ[39] ውስጥ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ይኸውም በልዩ ዞኑ ነዋሪ የሆኑ የቱለማ ኦሮሞ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች ተመሳሳይ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እንዳላቸው በአቶ መስፍን ንጉሴ (መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ.ም.) የተሰጠ መረጃ ትክክል መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው።

[39] በዚህ ጥናት ውስጥ ምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዳራ ሥር ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ዓይነቶች የሚገልጹ የግርጌ ማስታወሻዎችን ይመልከቱ።

2. የቱለማ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን አስመልክቶ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በተመለከተ ከራሳቸው እንዲሁም ከሌሎች ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ለተጠየቁት ጥያቄ መልሳቸው ተጠቃሎ ሲታይ ባህላዊ የፍቅር ግንኙቶች በሚመለከት ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች፣ እና ቀልዶች እንደሚነገሩ እና በተለይ ዘፈኖች በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ታጅበው እንደሚዘፈኑ ገልጸዋል። ከእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተያይዥነት ያላቸው በርካታ ምሳሌያዊ ንግግሮችን እና የዘፈን ግጥሞችን በጽሑፍ አቅርበዋል። እነዚህ መረጃዎች በሌሎች የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ከተገኙት መረጃዎች ጋር ተያይዞ ከይዘታቸው አኳያ በየምድቡ ውስጥ ተካተዋል።

3.ተማሪዎቹ በሚኖሩበት አከባቢ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክተው የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች ከራሳቸው ወይም ከሚያውቁት ሰው ጠይቀው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሠረት ከሰጡት ምላሽ መካከል በቀጥታ ስለ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሚያወሱ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና በርካታ የዘፈን ግጥሞችን በጽሑፍ አቅርበዋል። እነዚህ መረጃዎች በፋይል የተያዙ ሲሆን ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተመርጠው በየምደባው ውስጥ ተካተዋል።

4. የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን እና ኤች ኣይቪ/ ኤድስ አስመልክቶ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን በሚመለከት የሥነቃል እውቀት ያላቸው ግለሰቦች የስም ዝርዝራቸውን የተላከላቸውን ቅጽ ሞልተው የ31 ሰዎች (19 ወንዶች እና 12 ሴቶች) ስም ዝርዝር አቅርበዋል። በተማሪዎች ከተጠቆሙ ሰዎች መካካል በዚህ ጥናት ውስጥ የተወሰኑትን ለቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት በመረጃ አቀባይነት ተጠቅሜባቸዋለሁ። በመሆኑም የሥነቃል እውቀት ያላቸውን መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት የተማሪዎቹ አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

በሌላ መልኩ ከተማሪዎች የተገኙት ጥቆማዎች ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ለቃለ መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ለማዘጋጀት በመነሻነት ያገለገሉ ሲሆን ለምልከታ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴም የት የት ቦታ ላይ ትኩረት ማድረግ እነዳለብኝ ጥቆማ በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በዚሁ መሠረት በእንቁጣጣሽ፣ በእሬቻ፣ በጥምቀት እና በጋብቻ ክብረ በዓላት እንዲሁም በልዩ ልዩ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ክብረ በዓላት ላይ ከሚዘፈኑ ዘፈኖች ውስጥ በርካታዎቹ

ከተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን የሚያጠናክሩና የሚያዳብሩ ናቸው። ይህም የሚያሳየን ተማሪዎቹ ከማህበረሰቡ የወጡና የባህሉ ባለቤት በመሆናቸው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የሰጡ መሆናቸውን ያሳያል። እዚህ ላይ ምንም እንኳን ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ሰዎች ባህላቸውን ይረሳሉ፤ ወይም ስለባህላቸው ብዙም ደንታ (ፍላጎት) የላቸውም የሚል አመለካከት ያለ ቢሆንም እነዚህ ተማሪዎች የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ባህል በማወቁ እና በማስተላለፉ ረገድ ያላቸው ሚና ጉልህ መሆኑን የተገኙት መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የሥነቃል ዓይነቶች ለማሰባሰብ እና በሥነቃል እውቀታቸው የተሻለ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ለማግኘት ትምህርት ቤቶች እንደ ባህል ማዕከል የሚያገለግሉ ናቸው። ከተማሪዎቹ የተገኙትን ጠቃሚ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በምልከታ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የተገኙ መረጃዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ፎቶ ግራፍ 1. በመጠይቅ ከተሳተፉ ተማሪዎች ውስጥ በስተግራ የሱሉልታ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት (10/03/ 2007)፣ በስተቀኝ የጫንጮ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት (13/03/2008 ዓ.ም)።

5.2 በምልከታ የተገኙ መረጃዎች

በዚህ ጥናት ተሳትፏዊ ምልከታ እና ኢ. ተሳትፏዊ ምልከታ ተግባራዊ የሆኑ ሲሆን ይህም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ በየመቼቶቹ ሥር ተገልጸዋል። ከእነዚህም አንዱ ተፈጥሯዊ መቼት ሲሆን እነሱም በቱለማ ኦሮሞ በሚከበሩ ልዩ ልዩ ሓይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ በዓላት ናቸው። በዚሁ መሠረት በእንቁጣጣሽ፣ በእሬቻ፣ በጥምቀት፣ በሠርግ እና በለቅሶ ሥነ-ሥርዓቶች ላይ ትኩረት ተደርገዋል። ተፈጥሯዊ ካልሆኑ መቼቶችም እንዲሁ መረጃ ተሰብስቧል። እነዚህም ት/ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ ስብሰባዎች፣ ገበያ ቦታዎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ ወዘተ… በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል። ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼትን በሚመለከት መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ሰዎችን በማስተባበር የአባቶቻችንን አድባር እናክብር በሚል ምክንያት በዓል መሰል ፕሮግራም በማዘጋጀት ነው። በፕሮግራሙ ላይ የዘፈን ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች እና አዝማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚገልጹ ዘፈኖችን በማስዘፈንና በማስጨፈር እንዲሁም አብሮ በመዝፈንና በመጨፈር ነው። በእነዚህ ሦስት መቼቶች ወስጥ በአካል ተገኝቼ፣ በመመልከት እንዲሁም በአንዳንድ መቼቶች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ጥናቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ሰብስቤያለሁ። በዚሁ መሠረት ከየመቼቶቹ የተገኙ መረጃዎች ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

5.2.1 ተፈጥሯዊ መቼት

ተፈጥሯዊ መቼት ማለት አጥኚው የሥነቃል ዓይነቶችን በተለምዶም ሆነ በባህል በሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ተገኝቶ የተፈለጉ መረጃዎች የሚሰበስብበት አውድ መሆኑ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ተገልጿል። ከዚሁ አኳያ የዘመን መለዋጫ በዓልን በሚመለከት ከእንቁጣጣሽ የልጃገረዶች ጭፈራ በተጠኚው ማህበረሰብ ቋንቋ Qaammee በመባል በሚታወቀው ክብረ-በዓል ላይ በመገኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚሁ መሠረት ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም እና መስከረም 1 ቀን 2007 ዓ.ም በለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ በመገኘት፣ ጳጉሜ 6 ቀን 2007 ዓ.ም በበረክ ወረዳ በመገኘት፣ መስከረም 1 ቀን 2008 ዓ.ም በሱሉልታ ወረዳ በመገኘት ልጃገረዶች የአዲስ ዘመን መግባትን ምክንያት በማድረግ በየቤቱ እየዞሩ እንኳን አደረሳችሁ በሚሉበት ወቅት በተጓዳኝ ለክበረ በዓሉ ጨዋታ

ከዘፈኑት ዘፈኖች ውስጥ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ የፍቅር ዘፈኖችን ከእነድምፃቸው በመቅዳት መረጃዎቹ ተሰብስቧል።

በመስከረም ወር ውስጥ በታለቅ ሥነ-ሥርዓት የሚከበር የእሬቻ በዓል (Ayyaana Irreechaa) ነው። ይህ በዓል በኦሮሚያ ክልል በልዩ ልዩ ሥፍራዎች የሚከበር ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት የሚከተሉት ናቸው። እነሱም ኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ መስከረም 25 ቀን 2007 ዓ.ም እና መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም. በቢሾፍቱ ከተማ አርሰዲ ሐይቅ (Hora Arsadii) በተከበረው ደማቅ ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘት የሽማግሌዎች ምርቃትና ልዩ ልዩ ባህላዊ ዘፈኖች ከነክዋኔያቸው በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጸዋል።

የሽማግሌዎችን ምርቃት በተመለከተ መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም ቢሾፍቱ ሆረ አርሰዲ በተከበረው እሬቻ ላይ የቱለማ አባ ገዳ በየነ ሰንብቶ ከምርቃቱ ጋር አያይዘው ከጤና ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወጣቶች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ አሳስበዋል። ከዚህ የምንረዳው የቫይረሱ ሥርጭት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚመለከት በመሆኑና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳይ በሁሉም የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ዋና አጀንዳ መሆኑን ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በዚህ በዓል ላይ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እና በልዩ ልዩ መንገድ ሰዎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ የሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች ተገኝተዋል። ለምሳሌ በአቶ በዳሳ ጉርሙ ከኤች አይ ቪ /ኤድስ እና ጤና ጋር ተያይዘው የተዘፈኑ ዘፈኖች ተጠቃሽ ናቸው። ይኸውም ሰዎች በገበያ ቀን መጠጥ በመጠጣት ከተማ በማደር በገዛ ገንዘባቸው ራሳቸውን ለበሽታ ከመዳረግ እንዲቆጠቡ በዘፈኖቹ ያስተላለፉቸው መልዕክቶች ከጥናቱ ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው። በመሆኑም በቪድዮ ከሜራ ተቀርጾ መረጃዎቹ ተያይዘዋል። የዘፈኖቹም ግጥሞች ከድምፅ ወደ ጽሑፍ ተቀይረው በምዕራፍ ሰባት ውስጥ ኤድስን ለመከላካል የሚመክሩ ዘፈኖች ሥር ተተንትኗል።

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ በሱሉልታ ወረዳ ሞገር ወንዝ (መልካ) ከተከበረው እሬቻ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፌ በቦታው ላይ በአካል

ተገኝቼ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። የተገኙት መረጃዎች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። ጉዞውን በተመለከተ የመስክ ገጠመኙ[40] ውስጥ ተገልጿል።

መስከረም 30 ቀን 2008ዓ.ም. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በገላን ከተማ አቃቂ ወንዝ (መልካ) በተከበረው Caffee Tumaa (በጨፌ ቱማ) የ6ቱ ገላን መገናኛ በሆነው የእሬቻ በዓል ላይ በመገኘት የሽማግሌዎች ምርቃትና ልዩ ልዩ የሥነቃል መረጃዎችን ከነክዋኔያቸው በቪዲዮ ካሜራ ሰብስቤያለሁ። በዚሁ መሠረት በክብረ በዓሉ ላይ በቀድሞ የቱለማ አባ ገዳ ነገሠ ነገዎ[41] እና በአገር ሽማግሌች ከቀረቡ ምርቃቶች ውስጥ የሚከተለው ይገኛል።

ሠንጠረዥ 6፡- በገላን ጨፌ ቱማ የእሬቻ በዓል ምርቃት

Hyee yaa waaq (3)	አምላክ ሆይ (3)
Waaq Odaa nabee,	የኦዳ ነቤ አምላክ፣
Waaqa Caffee Tumaa,	የጨፌ ቱማ አምላክ፣
Waaqa fincaan Tuulama sadeenii,	የሦስቱ ቱለማ አምላክ፣
Kan nagaan nu bulchite,	በሠላም ያሰደርከን፣
Nagaan nu olchi.	በሠላም አውለን።
Irraa gora nu lagi,	አቅጣጫ ከመሳት ሰውረን።
Doggoora nu lagi.	ከስህተት ሰውረን።
Biyyaa biyya ngaa nu godhi.	አገራችንን የሠላም አገር አድርግልን።
Dhibee nu lagi.	ከክፉ (ከበሽታ) ሰውረን።
Fayyaa nu kenni	ጤና ስጠን።
Xinnaa keenya nuu guddisi.	ትናንሾቹን አሳድግልን።
Guddaa keenyaa nuu bulci.	ትልልቆቹን አቆይልን።

[40] ምዕራፍ አንድ ሥር ገጽ 21 የመስክ ገጠመኝ ርዕስ ይመልከቱ።

[41] የቀድሞ የቱለማ አባ ገዳ ለገሠ ነገዎ ከአሁኑ የቱለማ አባ ገዳ በየነ ሰንበቶ በፊት የቱለማ ኦሮሞ አባ ገዳ የነበሩና ሥልጣናቸውን በሠላም ያስረከቡ ናቸው። በዕለቱ በተከበረው እሬቻ በዓል ላይ ከበዓሉ ጋር ተያያዥ የሆኑ ልዩ ልዩ ዘፈኖችን በመዝፈን የበዓሉን ታዳሚዎች ያነቃቁ ነበር። በማህበረሰቡ የተከበሩና የተወደዱ ናቸው። እሳቸው ሲነገሩና ሲጫወቱ የበዓሉ ታዳሚዎች ፊት ላይ የደስታ ስሜት ይታያል። ለጌ እያሉ ያሞግሳሉ።

Gadaan quufa gabbina.	ገዳው የጥጋብ ነው።
Biitti roobaa nagaya.	አገሩ የሠላም ዝናብ ነው።

ከዚህ ምርቃት የምንረዳው የቱለማ ኦሮሞ በላፈው ዘመን ላገኘው መልካም ነገር ምሥጋናውን ለአምለኩ የሚያቀርብበት፣ ለመጪው ደግሞ መልካም የሚላቸው ሁሉ እንዲያጋጥመውና ክፉ እንዲርቅ ምኞቱን በመግለጽ አምለኩን የሚለምንበት ሥርዓት ያለው መሆኑን ነው። ባለፈው ዘመን ለተገኘው መልካም ነገር ሁሉ ምስጋናው እንደተጠበቀ ሆኖ ለወደፊቱ ከሁሉም በላይ አገር ሠላም እንዲሆን፣ ለሕዝቡ ጤና እንዲሰጥ፣ ልጆች እንዲያድጉ፣ አዋቂዎች እንዲኖሩ ለሁሉም ፈጣሪውን ይለምናል። ለገዳ አስተዳደሩም የሠላምና የጥጋብ እንዲሆን መልካም ምኞቱን ይገልጻል። ይህም የሚያሳየን በተለይ ጤናን በተመለከተ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ነው።

በዚሁ ዕለት መስከረም 30 ቀን 2008 ዓ.ም. እኔ በገላኑ ክብረ-በዓል ምክንያት መሔድ ባለመቻሌ ቁልፍ መረጃ አቀባዬን አቶ ደረጀ መኮንን በቡራዩ ከተማ መልከ ገፈርሳ በተከበረው የአቴቴ በዓል ላይ በቦታው ተገኝቶ መረጃ እንዲያሰባስብ አድርጌለሁ። የተገኙ መረጃዎችም በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል።

ፎቶ ግራፍ 2፡- የእሬቻ በዓል አከባበር በበሾፍቱ ሆራ አርሰዲ በስተግራ (መስከረም 25 ቀን 2007 ዓ.ም.)
(በስተ ቀኝ መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም.)

ፎቶ ግራፍ 3፡- የእሬቻ በዓል አከባበር በስተ ግራ በሱሉልታ ወረዳ ሞገር ወንዝ መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

በስተቀኝ በገላን ከተማ ጨፌ ቱማ መልካ አቃቂ ላይ የቀድሞ አባ ገዳለገሠ ነገዎ (ግንባሩ ላይ ከለቻ ያደረገ) እና የአገር ሽማግሌዎች የተሳተፈበት (መስከረም 30 ቀን 2008 ዓ.ም.)

ከመስከረም ወር መጨረሻ እስከ ጥር ወር መግቢያ ድረስ በልዩ ዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ት/ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ ገበያ ቦታዎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ስብሰባዎች የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል።

በጥር ወር መግቢያ ሁለተኛው ሳምንት ውስጥ ከሚከበረው የጥምቀት ክብረ-በዓል በአፋን ኦሮሞ (Ayyaana Cuuphaa) ላይ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በ2006 ዓ.ም. እና በ2007 ዓ.ም. ነው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከተለያዩ አውዶች ነው። እነዚህም ጥር 10 ኦሮሚያ ክልል፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ በለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር የአባኪሮስ ቤተክርስቲያን የታቦት አወጣጥ (ከተራ በዓል) ሥነሥርዓት ላይ በመገኘት፣ ጥር 11 ቀን በአዲስ አበባ በርካታ ታቦታት በአንድነት ከሚወጡበት ጃንሜዳ (hurufa boonbii)[42] ፣ ጥር 12 ቀን በአዲስ አበባ [ኤ][43]ካ ክፍለ ከተማ ከሾላ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እስከ 8፡00 ሰዓት ባለው ገዜ ውስጥ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በዚሁ ዕለት 9፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ከመርካቶ አዲሱ ሚካኤል መረጃ ተሰብስቧል። ጥር 13 በአዲስ አበባ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ከሩፋኤል ቤተክርስቲያን መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በአጠቃላይ በሁለቱም ዓመት ከከተራ ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት በተደረገው የመረጃ ማሰባሰብ ተግባር በርከታ የሥነቃል መረጃዎች ተገኝተዋል። እንደየሚያተኩሩበት ርዕሰ ጉዳይ ተመድበው በዚህ ጥናት ውስጥ አባሪ ተደርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ ሰፊ የትንታኔ ሥፍራ ተሰጥቶአቸዋል።

[42] ከአጼ ምንልክ ዘመነ መንግስት በፊት ይህን ቦታ ኦሮሞ (hurfa boonbii) ብሎ ይጠራ ነበር። ስያሜውም የተገኘው በአከባቢው በአፋን ኦሮሞ boonbii የአማርኛ ትርጉሙ ጥንዝዛ የሚባል ነፍሳት በብዛት ይገኝበት ስለነበረ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ቸሩ ሮሪሳ እና አቶ ታደሠ ደህኔ ገልጿል (ጥር 2007 ዓ.ም.)።

[43] ትክክለኛው አጠራር የካ ሳይሆን ኤካ ነው። ይህ ቃል ከቱለማ አሮሞ ውስጥ በገላን አንድ የጎሳ ቤተሰብ ስም ነው። በኦሮሚያ ያሉ አንዳንድ ስሞች ወይም ፊዳል ወይም ድምፅ በመቀየራቸው የትርጉም ለውጥ ያስከትላሉ። ለምሳሌ “የካ” ማለት በአፋን ኦሮሞ “ወንጀል” ማለት ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በኦሮሚያ አንዳንድ ከተሞች ውስጥ ነባሩ ስሞች ወደ አከባቢው በመጡ ሌሎች ማህበረሰቦች የተለወጡ ናቸው። ለውጡን በተመለከተ በዚህ ጥናት ውስጥ አንዳንድ የሥነቃል ዓይነቶች በለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ የተተነተኑትም ከዚሁ አኳያ ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ ኤካ የሚለው የቋንቋው ባለቤት የሚጠራበት ትክክለኛ ስም በመሆኑ ይኸው አገልግሎት ላይ ውሏል።

ፎቶ ግራፍ 4፡-የጥምቀት ክብረ-በዓል በአዲስ አበባ ከተማ፡- በስተግራ በጃን ሜዳ (ጥር 11 ቀን 2008 ዓ.ም)

እና በስተቀኝ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን (ጥር 13 ቀን 2007 ዓ.ም)።

በሌላ መልኩ በሁለቱም ዓመት ጥር 21 ቀን ኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሸኖ ማርያም ቤተክርስቲያን ንግስ ላይ በመገኘት መረጃ ተሰብስቧል። እነዚህ መረጃዎች ከነክዋኔያቸው በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጸዋል። ዶክመንትም ተደርገዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም. እና 2008 ዓ.ም በጫንጮ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ንግስ ላይ በመገኘት በተመሳሳይ ሁኔታ መረጃ ተሰብስቧል። በእነዚህ ክብረበዓላት ላይ በአብዛኛው ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ዘፈኖች የተሰበሰቡ ሲሆን ከእነዚሁ ጋር ተያይዘው ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የተዘፈኑ ዘፈኖችም ይገኙበታል። ከእነዚህ ውስጥ ከጥናቱ ርዕስ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተያያዥነት ያላቸው በእየርዕሰ ጉዳዮቹ ሥር የተመደቡ ሲሆኑ የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ ተተንትነዋል።

ፎቶ ግራፍ 5፡- የጥምቀት በዓል አከባበር በስተቀኝ በሸኖ ማርያም ቤተክርስቲያን (ጥር 21 ቀን 2007 ዓ.ም)
እና በስተግራ የጥምቀት በዓል በጫንጮ እግዚአብሔር ለአብ ቤ/ያን (ህዳር 13 ቀን 2008 ዓ.ም)።

ሌላው መረጃ የተሰበሰበበት አውድ የሕይወት ሽግግር ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ በሆነው ጋብቻና ለቅሶ ላይ ነው። በዚሁ መሠረት የግለሰቦች ሠርግ እና የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ላይ በርካታ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስበዋል። ሠርግን የሚመለከቱ ሥነቃሎች በአብዛኛው ጋብቻ ላይ ያተኮሩ ዘፈኖች ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዘው ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ እንዲሁም አልፎ አልፎ በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ላይ ያተኮሩም ይገኙበታል።

በዚሁ መሠረት በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ከተለያዩ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ላይ በርካታ የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተለይ ሚያዚያ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አቶ ካባ ነገሰ ወንድ ልጁን ሲድር እና ሚያዚያ 25 ቀን 2007 በለገጣፎ ከተማ አቶ ጌቱ ታደሠ ሴት ልጁን ሲድር በሽምግልና ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ከዘፈኖቹ በተጨማሪ

ጋብቻን የተመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰብስቤያለሁ። ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት ውስጥ ተተንትነዋል።

ፎቶ ግራፍ 6፡- በስተግራ ወንድ ልጅ ሊያገባ ከቤት ሲወጣ ከነአጃቢዎች (ሚያዚያ 18 ቀን 2007ዓ.ም.)

በስተቀኝ ሴት ልጅ ስትዳር የጥሎሽ ሥርዓት (ሚያዚያ 25 ቀን 2007 ዓ.ም.)

የሥነቃል መረጃ የተሰበሰበበት ሌላው አውድ ከለቅሶ ቦታ ነው። በቱለማ ኦሮሞ Sirna bo'ichaa fi awwalchaa (የለቅሶ እና የቀብር ሥርዓት) የተለየ ቦታ ይሰጠዋል። ይህንንም በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት እና ከዚያም በኋላ በልዩ ልዩ መልኩ ይገልጻል። በሌላ ማህበራዊ ጉዳዮች ሞልቶለት ወይም ጊዜ አግኝተው የማይገኝ ሁሉ ከቀብር ሥርዓት ላይ አይቀርም። ሞት የሰው ልጅ ለመጨረሻ ጊዜ በአካል የሚለያይበት በመሆኑ በቱለማ ኦሮሞ ለቅሶ ለማይደርስ ሰው በምሳሌያዊ ንግግር Duutuutu warra du'aa hin dhaqne. (ለቅሶ የማይደርስ የሞተ ሰው ነው) ይባላል። ይህ ማለት ቀብር ወይም ለቅሶ የማይደርስ ሰው እንደ ሬሳ ይቆጠራል። የቅርብ ዘመዳቸው (አባት ፣እናት ወንድም ፣እህት፣ ልጅ) የሞተባቸው ሰዎች በተለያየ መንገድ ሀዘናቸውን ይገልጻሉ። ለምሳሌ ፀጉራቸውን ይላጫሉ፤

ወይም በወጣ ገባ ይቀረጣሉ። አንገታቸው ላይ ነጭ ክር ያስራሉ። ወንዶች ኮታቸውን ገልብጠው ይለብሳሉ። ጋቢ ወይም ብርድልብስ ይለብሳሉ። ጥቁር በርኔጣ ያደርጋሉ። ሴቶች ጥቁር ሻሽ ያስራሉ። ነጠላ ያደገድጋሉ። ፎጣ ከነጠላ ይለብሳሉ። ሌሎች ለቀስተኛ ሴቶች በሙሉ ነጠላቸውን ዘቅዝቀው ይለብሳሉ። በአጠቃላይ ሀዘነተኛ ከሌላ የሚለይበት አለባበስ ያለው ሲሆን ይሄን አለባበስ ያየ ማንኛውም የማህበረሰቡ ክፍል የቅርብ ዘመድ እንደሞተበት ያውቃል። (መረጃ አቀባዮች አቶ በልዳ አቦዬ፣ አቶ ቸሩ ሮሪሳ አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ ወ/ሮ ደብሪቱ ገረሱ እና አቶ ሲሳይ ማሰሪያ ታህሳስ፣ 2007 ዓ.ም.)።

የለቅሰውን ሥነሥርዓት በተመለከተ መረጃ አቀባዮች እንደተናገሩ እና አጥኚውም በምልከታ እንዳረጋገጠው ሬሳ ከቤት ከመውጣቱ በፊትና በቀብርም ቦታ ወንድ አስለቃሽ በፈረስ ላይ ሆኖ የሟቹን ዝና በግጥም እየደረደረ ቀደም ሲል የሞቱ ጓደኞቹን ስም እየጠራ የማያውቀውን ለቅሶ ደራሽ ጭምር የሀዘን ስሜት ውስጥ በሚያስገባ ዜማ ያስለቅሳል። በዚህ ጊዜ ለቀስተኞቹ እየተንጎራደዱ በሹክሹክታ ዜማ ያለቅሳሉ። አስለቃሹ ከፈረስ እስከሚወርድ ድረስ ደምፅ ከፍ አድርገው ማልቀስ በባህሉ አይፈቀድም። ምክንያቱም እየተደረደረ ያለውን የሟችን ዝና የሚገልጽ ግጥም ማዳመጥ ይጠበቅባቸዋል። አስለቃሹ ከፈረስ እንደ ወረደ ሀዘንተኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም በፊት ዘመድ አዝማድ የሞተባቸው ሰዎች እየዘለሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በዜማ ያለቅሳሉ።

ፎቶ ግራፍ 7፡- ቀብር ሥነ-ሥርዓት በለገጣፎ አባ ኪሮስ ቤ/ን ጥር 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ይህ ሁሉ የሚደረገው ሟቹ ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰናበት በመሆኑ እጅግ በጣም መሪሪ የሆነ ሀዘን ይሰማቸዋል። ከቀብሩም በኋላ ሀዘኑ የሚቀጥል ሲሆን በአከባቢው ሥርግ እንኳን ቢኖር ዘፈን አይዘፈንም። በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለመረጃ አቀባዮች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በሚመለከት የሚያውቀን ዘፈን እንዲዘፍንልኝ ተጠይቀው ሰሞኑን በአከባቢው ሰው የሞተ በመሆኑ በሀዘን ምክንያት መዝፈን እንደማይችል መረጃ አቀባዬ ገልጿል (በልዳ አቦዬ ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም.) ።

ይህ የሚያሳየን በቱለማ ኦሮሞ ለሀዘን የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን ሲሆን የአሟማቱ ሁኔታ በምንም ይሁን ሞት በሰው ልጅ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ የጎላ መሆኑ ነው። የኤች አይ ቪ/ኤድስ መኖር ደግሞ የሞት ቀጥርን ከመጨመሩ አኳያ በሀዘን ምክንያት ለደስታ የሚዘፈኑ ዘፈኖች ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ለቅሶን በሚመለከት አጥኚው ከዝምድና፣ ከጉርብትና እና ከመተዋወቅ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በልዩ ዞኑ ከተሞች እና ወረዳዎች በበርካታ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘት ችግሩ

የደረሰባቸውን ሰዎች በማጽናናት እግረ መንገድም ከጥናቱ ርዕስ ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተለይ ወጣቶች (ወንዶችም ሴቶችም) ለብዙ ጊዜ ታሞ በሕክምናም ሆነ ባህላዊ መድሃኒት ተጠቅሞ በሽታው ለሞት ካደረሳቸው በቀብራቸው ላይ አማሚቱ/አማሚቷ ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለመጠቆም በተለይ ኤድስ ወጣቶችን እየፈጀ ነው ለማለት በምሳሌያዊ ንግግር የሚከተለውን ይናገራሉ። "Kan duaa eegan jaarsaa Kan du'aa jiru dargaggeesa." ሲተረጎም "ለሞት የሚጠበቅ ሽማግሌ እየሞተ ያለ ወጣት ነው።" ይህንን የመሳሰሉ መረጃዎች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተመረጡት በምዕራፍ ሰባት ሥር ተተንትነዋል። ቀጣዩ ተፈጥሯዊ ባልሆነ መቼት የተሰበሰበ መረጃን ይመለከታል።

5.2.2 ተፈጥሯዊ ያልሆነ መቼት

ተመራማሪው ሁሉንም የሥነቃል ዓይነቶች በተፈጥሯአዊ መቼት ለመሰብሰብ በማይችልበት ወቅት ከአውዱ ውጭ በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሳያማርጥ መረጃዎችን የሚሰበስብበት ሁኔታዎች መሆኑን ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ተገልጿል። በዚህ ጥናት ውስጥ ይህን መቼት በተመለከተ በ2006 እና በ2007 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ው ስጥ የተገኘውን ጊዜና አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚሁ መሠረት ለጫንጮ አባ ገዳ እና ሱሉልታ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ት/ቤቶች ተማሪዎች የቀረቡትን መጠይቆች ለመስጠት እና ለመቀበልምልልስ በአደረኩበት ወቅት እግረ መንገድ ከመምህራንና ሠራተኞች ላይ መረጃዎን ሰብስቤያለሁ። በሌላ መልኩ በኦሮሚያ ጤና ቢሮ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘርፍ እና ከፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ጤና ጽ/ቤት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት በሚመለከት መረጃዎች ተሰብስቧል። በተመሳሳይ ሁኔታ ከሱሉልታ ወረዳና ከተማ ጤና ተቋማት ሃለፊዎች እና የጤና ባለሙያ ጋር ቅርርብ በመፍጠር ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት መረጃዎችን አግኝቻለሁ።

በኦሮሚያ ባህልና ቱሪዚም ቢሮ በመገኘት ለጥናትና ምርምሩ የድጋፍ ደብዳቤ በማጻፍ እግረ መንገድም ከጥናቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃለፊ ጋር በተደረገው የሀሳብ ልውውጥ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎች የተገኙ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በልዩ ዞኑ ውስጥ ካሉ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች በሱሉልታ ወረዳና ከተማ፣ በበረክ ወረዳና ሠንዳፌ

ከተማ፣ በለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ፣ በገላን ከተማ፣ በዱከም ከተማ፣ በሰበታ ከተማ፣ በወልመራ ወረዳና ቡራዩ ከተማ በመገኘት ከየጽ/ቤቱ ሠራተኞች እና የአከባቢው ነዋሪዎች በርከታ የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ሌላው የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚዎችና ቦታዎች የገበያ ቀናት እና ከዚሁ ጋር ተያይዘው ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጡ መጠጥ ቤቶች ናቸው። ከዚሁ አኳያ በዋናነት በሱሉልታ ወረዳ በተጨማሪም በልዩ ዞኑ ውስጥ በተለያዩ ጠጅ ቤቶች፣ ጠላና አረቄ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች እና ሆቴሎች በመገኘት መረጃ ተሰብስቧል። በተለይ በጠጅ ቤቶች ከሚዘፍኑ አዝማሪዎች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚመለከቱ በርከታ ዘፈኖች ተሰብስበዋል። ሌላው የመረጃ ምንጭ በየፋብሪካዎች የሚገኙ ሠራተኞች ከሥራቸው ጎን ለጎን በዘፈን ራሳቸውን የሚያዝናኑበት ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሱሉልታ ልዩ ልዩ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እና በለገጣፎ የተለያዩ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሥራ ላይ ተሠማርተው ከሚገኙ ሠርቶ አደሮች በርከታ የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል። እነዚህ ተግባራት የተከናወኑት በተገኘው ጊዜና አጋጣሚ ሲሆን በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ የሥነቃል መረጃዎች ከልዩ ልዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች የተገኙበት መስክ ናቸው። የተገኙት መረጃዎችም ተመድበው በሚመለከታቸው ርዕሶች ሥር ተተንትነዋል።

5.2.3 ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች

በተፈጥሯአዊ መቼት ውስጥ መረጃዎችን መሰብሰብ በማይቻልበት ወቅት ጥሩ ችሎታና እውቀት ያለውን መረጃ አቀባይ በመፈለግ የተቀናበረ ተፈጥሯአዊ መቼት በመፍጠር የሥነቃል መረጃዎች የሚሰበሰብበት አውድ ነው። ከዚሁ አንጻር በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር ልዩ ስሙ ኤካ ገዋሳ መንደረ ጎሎሌ ተብሎ በሚታወቅ ቦታ ላይ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼትን በመፍጠር የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል። ይህ ቦታ ተወልጄ ያደኩበት ሲሆን ድሮ መንደርተኞቹ በዚህ ቦታ ላይ በባህሉ መሠረት የሚበላ እና የሚጠጣ በመዘጋጀት በአንድ ላይ ተገናኝተው ሰላም እና ጤና ለመላው ቤተሰባቸው እና ለአገሩ ሁሉ እንዲሰጥ ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር። ይህም የአድባር አከባበር በመባል ይታወቃል። ይሁን እንጂ ይህ ሥነ-ሥርዓት በመሀሉ ተቋርጦ ነበርና በእኔ አነሳሽነት አብሮ አደጎቼን በማስተባበር የመጀመሪያው ዝግጅት ጥቅምት12 ቀን 2007 ዓ.ም. ተካሄዶ ነበር። በዚህ ዝግጅት ላይ ተገኝተው ምርቃት ያደረጉት የአገር

ሽማግሌዎች በዚህ ጥናት ውስጥ ብዙ ቦታ ስማቸው ይጠቀስ የነበሩ አቶ በጅጋ ሮሪሳ እና አቶ ታደሰ ደህኔ ይገኙበታል። ምርቃታቸውም ሠላምና ጤንነት ላይ ያተኮረ ሲሆን በተለይ ወጣቶች ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ራሳቸውን እንዲጠብቁ አባታዊ ምክራቸውን አስተላልፈዋል።

ሁለተኛው ዝግጅት ጥቅምት 28 ቀን 2008 ዓ.ም. የተካሄደ ሲሆን ይህ ዝግጅት በሰዎች ብዛትና በፕሮግራሙ ላይ በነበራቸው ተሳትፎ ከባለፈው ዓመት በጣም የተሻለ ነበር። በሁለቱም ዝግጅቶች ላይ ባህላዊ ዘፈን የሚያውቅ ደረጀ[44] ሹሚ (አዝማሪ) የተገኘ ሲሆን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የሚመለከቱ ዘፈኖች በመዝፈን ታዳሚዎችን አዝናንቷል። በዚህ ላይ እኔም በዘፈኑና በጭፈራው ተሳትፎ በማድረግ የሥነቃል መረጃዎችም ከነክዋኔያቸው በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጸዋል። በተለይም በሁለተኛው ዙር የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ ወቅታዊ የሆኑና ከጥናቱም ርዕስ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል መረጃዎች ተገኝተዋል። በሁለቱም ዙሮች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ለጥናቱ ተስማሚ ሆነው የተገኙት በትንታኔው ምዕራፎች ውስጥ ተካተዋል።

ፎቶግራፍ 8፡- የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች በለገጣፎ አዝማሪውና ታዳሚዎቹ በ12/02/07 ዓ.ም.

[44] አቶ ደረጀ ሹሚ የቱለማ አሮሞ ባህላዊ ዘፈኖችን በደንብ የሚያውቅ በመሆኑ በበርካታ የግለሰቦች ድግስ ላይ እየተጠራ ይዘፍናል። በመስንቆው ለዘፈኖቹ ውበት ይሸጣል። ከዘፈን ችሎታውም ሌላ የሚች ዝናን በማንሳት በድግስ ላይ የተገኙትን ዘመድ የሞተባቸውን ሰዎች ያስለቅሳል። ይህ የአርት ባለሙያ የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅ ከመሆኑም በላይ የሰዎችን ስም ከነታሪካቸው በቃሉ ያውቃል። ደስታና ሀዘን ጎን ለጎን መሆናቸውን በማሳየት ሲፈልግ ያስጨፍራል ሲፈልግ ያስለቅሳል።

ፎቶግራፍ 9፡- *የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች በለገጣፎ ታዳሚዎቹና አዝማሪው 28 ቀን 2008 ዓ.ም.*

ከዚህ በመቀጠል በመጠይቅ እና በምልክታ የተገኙትን መረጃዎች ይበልጥ ለማረጋገጥ ተጨማሪ ረጃዎችንም ለማሰባሰብ በመጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች እንደሚከተለው እናያለን።

5.3 በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ አብዛኞቹ ቃለ-መጠይቆች በፕሮግራም የተከናወኑ ሲሆን ጥቂቶቹ ግን በተገኘው ጊዜና አጋጣሚ የተካሔዱ ናቸው። በዚህ ዘዴ ውስጥ 19 (11 ወንድ እና 8 ሴት) መረጃ አቀባዮች ተሳትፈዋል። እነዚህም ከልዩ ልዩ የኅብረተሰን ክፍሎች የተሳተፉ ሲሆን፣ እነሱም ሽማግሌዎች፣ የቤት እመቤቶች፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የመንግስት ሠራተኞች፣ የጤና በለሙያዎች ወይም ኤክስፐርቶች ናቸው። ለእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የቀረቡላቸው ጥያቄዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው። ይሁን እንጂ የተለየ እውቀት[45] የሚፈልጉ ጥያቄዎች በቀጥታ ለሚመለከታቸው ባህል አዋቂ ሽማግሌዎች፣ ለጤና ባለሙያዎች እና በባህል ዘርፍ ለተሰማሩ ኤክስፐርቶች ቀርበው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

[45] በባህሉ ዙሪያ የተለየ እውቀት (የተሻለ ግንዛቤ) ያላቸው መረጃ አቀባዮች ስማቸውና መረጃውን የሰጡበት ቀንና ዓ.ም. ከሰጡት ምላሽጋር በጽሑፉ ውስጥ ተጠቅሰዋል። ማንነታቸውን በሚመለከት በግርጌ ማስታወሻ ተገልጸዋል።

በዚሁ መሠረት ጥናቱ የተካሄደበትን የቱለማ ኦሮሞ ጎሳዎች ማንነት እና የሠፈሩበትን ማወቁ በጽሑፍ የተገኙትን መረጃዎች የሚያጠናክር ከመሆኑም በላይ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ረድቷል። በመሆኑም የወረዳ ስም ሱሉልታ መባሉ እና የወረዳዋ ዋና ከተማ ጫንጮ የሚለው ስያሜ ታሪካዊ አመጣጥ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በማንሳት በቀጠይነት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ወደሚያጠነጥኑት ጥያቄዎች በመሄድ በርካታ የሥነቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል። ስለዚህ በቃለ-መጠይቁ መሠረት የመረጃ አቀባዮችን ምላሽ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንመለከታለን

በሱሉልታ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ጎሳዎች የትኞቹ እንደሆኑ እንዲገልጹ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፡-

ይህ ጥናት ባተኮረበት አካባቢ የሚገኙ የገላን እና የኦቦ ጎሳዎች መሆናቸውን፣ በሥራቸውም ሌሎች የጎሳ ቤተሰቦች እንዳሉ እና ከእነዚህ መካከል በሱሉልታ ወረዳ የሚገኙት አብቹ፣ ግምብቹ እና ኦቦሪ የሚባሉ የጎሳ ቤተሰቦች ናቸው።

በዚሁ መሠረት በሱሉልታ ወረዳ የሚገኙ አንዳንድ የቀበሌ ስሞች በጎሳ[46] ስም የተሰየሙ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ሀንዳ፣ ኤኮ፣ አደኣ፣ ግምብቹ፣ አካካ መነ አብቹ፣ ጋልይ መነ አብቹ፣ ሰዮ፣ ኘአ ደካ ቦሩ፣ ከታ ወሌሌ፣ ገለኖ ሰቦሩ፣ ጉለሌ እና ደርባ ጉለሌ በሬሳ የተባሉ ቀበሌዎች በገላን እና በኦቦ የጎሳ ቤተሰቦች ስም የተሰየሙ ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ ጎርፎ፣ ጫንጮ ከተማ፣ ድሬ ሲሎ ለገሔጦ፣ ዱበር ከተማ፣ ደርባ ከተማ የሚባሉ ቀበሌዎች ደግሞ በወረዳው ታዋቂ በሆኑ የወንዝ ስሞች የተሰየሙ ናቸው (መረጃ አቀባዮች አቶ ሙሉጌታአያኔ፣ አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና ወ/ሮ ጠጅቱ ጠታ ህዳር27፡ 2007 ዓ.ም)።

[46] ለበለጠ መረጃ የሱሉልታ ወረዳ ከርታን ይመልከቱ።

ፎቶ ግራፍ 10፡- ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ሙሉጌታ[47] አታኔ፣ አቶ ጉዲሣ[48] አቤቤ፣አቶ ደረጀ[49] መኮንን እና ወ/ሮጠጂቱ[50] ቂጠታ በሱሉልታ ወረዳ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

የወረዳ እና የዋና ከተማዋ ስያሜያቸው ከየት እንደ መነጨ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ።

[47] ሙሉጌታ አያኔ ዕድሜው 54 ነው። ተወልደው ያደጉው ሰላሌ ፍቼ አከባቢ ሲሆን ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት የሱሉልታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊ ነው። የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች (ከንፈር ወዳጅ፣ ሲገባ እሬ) ጋር ተያይዘው የሚከወኑትን ተግባራት በደንብ ያውቃል። በኢለማ ናሙና የተመረጠ መረጃ አቀባይ ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ በርከታ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ጉልህ ተሳትፎ ነበረው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ስሙ በተደጋጋሚ ተጠቀሷል።

[48] አቶ ጉዲሣ አቤቤ በሱሉልታ ወረዳ ጎርፎ ቀበሌ ውስጥ ተወልዶ ያደጉ ሲሆን አሁንም የሚኖሩት ጎርፎ ነው። የአገር ሽማግሌ በመሆናቸው በባህላዊ ጉዳዮች እውቀት አላቸው። በተለይም በሱሉልታ ውስጥ የሚገኙ ጎሳዎችን ዝርዝር በደንብ ያውቃሉ። በባህላዊ ጋብቻ ወቅት ለሽምግልና ብዙ ቦታ የሚጠሩ ናቸው። በዘህ ጥናት ውስጥ በርከታ መረጃዎችን በመስጠትም ጉልህ ተሳትፎ ነበራቸው።

[49] አቶ ደረጀ መኮንን ዕድሜው 48 ነው። ተወልደው ያደገው የሱሉልታ ወረዳ አጎራባች በሆነችው ሙሎ ወረዳ ነው። አሁን በጫንጮ አባገዳ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት የኦሮምኛ ቋንቋ አስተማሪ ነው። የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን አስመልክተው የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖችን በደንብ ያውቃል። በሱሉልታ ወረዳ ውስጥ ባህላዊ እውቀት ያላቸውን ሽማግሌዎችንም ያውቃቸዋል። በኢላማ ናሙና የተመረጠ መረጃ አቀባይ ሲሆን በዘህ ጥናት ውስጥ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ነው።

[50] ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ ዕድሜዋ 58 ነው። ተወልዳ ያደገችው በምዕራብ ሸዋ ዞን ውስጥ መሆኑን ትናገራለች። ሱሉልታ ወረዳ ውስጥ ከ30 ዓመት በላይ ኖሯለች። ጠቋሚን መሠረት ባደረገ ናሙና የተመረጠች መረጃ አቀባይ ሲትሆን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች (ከንፈር ወዳጅ፣ ጋብቻ ፣ ውሽማ፣ ሲገባ) በሚመለከት የሚከወኑትን ተግባራት በደንብ ታውቃለች። ከእነዚህ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖችንም ትችላለች። በዘህ ጥናት ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ የነበራት በመሆኗ ስሟ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል።

ይህንን አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጡ ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ሃላፊ እና ለሦስት ያገር ሽማግሌዎች ጥያቄው ቀርቦ አራቱም መረጃ አቀባዮች መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሱሉልታ ባህልና ቱሪዝም ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በመሥሪያ ቤታቸው በኩል በዳረጉት ጥናት ያገኙትን ወጤት እንደሚከተለው ገልጿል።

> Akka seenaan ibsuufi nutis qorannoon mirkaneesineetti, Sulula jechuun lafa gaareewwan jidduu jiru jechuudha. Anaan Sulultaa gaarreeniin marfamteeti argamti. Kunis aanaan Sulultaa qarqara Finfinnee gaara Inxooxxootii kaasee hanga dhufee as Caanccoo bira gahutti gaaran marfamtee argamti. Kanaafuu sululaa keecha jiraachuu ishiirraa kan ka'eedha moggasichi maqaa aanichaa Sululta kan jedhame. Kanaafuu maqaan aanaa Sulultaa teechuma lafaa irraa ka'e jechuudha.
>
> Caanccoo jechuun immoo lafa xunxunaa lafa gannaa fi bona jiidhina qabu fi yeroo hundaa magariisaa ta'eedha. Gara biraatiin caanccoo jechuun lafa doloolloo yookiin sululas bishanis qabdu jechuudha. Akkuman duratti ibsi Sululti lafa ciisaa waan ta'ee fi lafti akkanaa kuni immoo bishaan waan hin dhabneef Caancoo kan jedhu kunis teesuma lafa kanarraa uumame jechuudha. Abootii seenaa beekaniirraayis qorannee kan mirkaneessine kanuma. Obboo Mulugeetaa Ayyaanee (Sadaasa 27, bara 2007 A.L.I)

ትርጉም በአማርኛ

> *በታሪክም እንደሚነገረውና እኛም በጥናት እንዳረጋገጥነው "ሱሉላ" ማለት በተራሮች መካከል የሚገኝ መሬት ማለት ነው። ይህም የሱሉልታ ወረዳ ከአዲስ አበባ ዳር ከእንጦጦ ተራራ ጀምሮ ጫንጮ እስከሚደርስ ድረስ በተራራ ተከባ ትገኛለች። ስለዚህ በረባዳ ሥፍራ ውስጥ የምትገኝ በመሆኗ ነው ሱሉልታ የሚል ስም ያገኘችው። በመሆኑም የሱሉልታ ወረዳ ስያሜው ከመሬቱ አቀማመጥ ተነስቶ የተሰጠ ስም ነው።*
>
> *ጫንጮ ማለት ደግሞ የሚመነጭ መሬት ሆኖ ክረምትም ሆነ በጋ እርጥበት ያለው መሬት ማለት ነው። በሌላ አባባል ጫንጮ ማለት ረባዳማ ሆኖ ውኃ ያለው መሬት ማለት ነው። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ረባዳ መሬት ለጥ ብሎ የተኛ መሬት ስለሆነና እንደዚህ ዓይነት መሬት ደግሞ ውኃም ስለማያጣ ጫንጮ የሚለው ስያሜ ከመሬቱ አቀማመጥ የተገኘ ነው። ታሪክ ከሚያውቁ አባቶቻችን በጥናት ያረጋገጥነው ይህንኑ ነው። አቶ ሙሉጌታ አያኔ* (ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም)።

ይህንኑ ሃሳብ በመጠናከር የሱሉልታ ወረዳ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምሥራቅ በተራሮች የተከበበችና መሐሏ ሰፋ ያለ ሜዳማ መሬት ያላት በመሆኗ በዚሁ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ በመደመም Sululaa የአማርኛ ትርጉሙ ረባዳ

ወይም ተፋሰስ ከሚለው ሱሉልታ Sulultaa የሚል ሥያሜ የተገኘ መሆኑን እና ጫንጮ ማለት ደግሞ በአፋን ኦሮሞ xunxuna የአማርኛ ትርጉሙ እርጥብ ወይም የሚመነጭ መሬት ከሚለው Caancoo (ጫንጮ) የተሰኘ ሥያሜ የተገኘ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣አቶ ደረጀ መኮንን እና አቶ ሰይፉ[51] መልካ (ህዳር 27 ቀን፣ 2007 ዓ.ም) ገልጸዋል።

በመሆኑም ይህ መረጃ እንደሚያሳየን ለወረዳውም ሆነ ለከተማው የተሰጠው ስያሜ በአከባቢው ይኖሩ በነበሩ የቱለማ ኦሮሞ ጎሳዎች እና የጎሳ ቤተሰቦች ተፈጥሮን መሠረት በማድረግ የወጡ ስሞች መሆናቸውን መረጃዎቹ ያመለክታሉ።

ፎቶ ግራፍ 11፡- በስተቀኝ በኩል የሱሉልታ ከተማ በስተግራ በኩል የጫንጮ ከተማ (ህዳር 27 ቀን 2007)

[51] አቶ ሰይፉ መልካ ዕድሜ 74 ነው። ተወልዶ ያደገው በሱሉልታ ወረዳ ነው። ስለ ወረዳዋ እና ከተማዋ የስም አሰያየም ታሪክን ያውቃሉ። የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮችንም በደንብ ያውቃሉ። መረጃዎችን በማቀበል በዚህ ጥናት ውስጥ ጉልህ ሚና ነበረቸው።

ከዚህ በመቀጠል በማህበረሰብ ውስጥ የሚያንጸባርቁትን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ምን እንደሚባሉ እና ስለ እነሱ በሥነቃል ዓይነቶች ምን እንደሚነገሩ እና እንደሚከወኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከመረጃ አቀባዮች የተገኘውን ምላሽ እንመለከታለን፡፡

በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ የሚተገበሩ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የትኞቹ እንደሆኑ እና እነዚህን አስመልክቶ በሥነቃል ምን እንደሚነገር እና እንደሚከወን ለቀረበ ጥያቄ የተሰጡ መልሶች፡፡

ይህን ጥያቄ በተመለከተ በቃለ-መጠይቁ ከተሳተፉ መረጃ አቀባዮች የተገኙ መረጃዎች ከተማሪዎቹ መረጃ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ እነዚህም ተጠቃለው ሲቀርቡ በሱሉልታ የሚገኙ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ሥር የሚጠቃለሉት Fuudhaaf Heeruma ,ቃብቻ)፣ Wadaajii dhungachuu (የከንፈር ወዳጅን መሳም)፣ Sanyoo teeechifachuu ቀውሽማ ማስቀመጥ)፣ Sigabaa galuu (ሲገባ መግባት)እና Irree bulfachuu (እሬ ማሳደር) ናቸው (መረጃ አቀባዮች አቶ ተስፋዬ ሁንዴ፣ አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና ጠጂቱ ቂጠታ ጥቅምት፣ 2007ዓ.ም)፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስለ እነዚህ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች(ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ) ምንነት እና አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ባህሉን በደንብ ከሚያውቁ መረጃ አቀባዮች የተሰጡት መልሶች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው፡፡

1. ጋብቻን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

በቱለማ ኦሮሞ (ሱሉልታ ወረዳ) ስለሚገኙት የጋብቻ ዓይነቶችና ከጋብቻ ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ባህላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ለአገር ሽማግሌዎች ጥያቄ ቀርቦ የተገኙት መልሶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ጋብቻ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን በማህበረሰቡ ውስጥ ከባህላዊ ጋብቻ ውጭ አልፎ አልፎ ሃይማኖታዊ እና ዘመናዊ (በመዘጋጃ ቤት የሚፈጸም) የጋብቻ ዓይነቶች አሉ፡፡ በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ጥንትም የነበረ፤ አሁንም ማህበረሰቡ ውስጥ በብዛት የሚከወን መሆኑን እና ልዩ ልዩ ባህላዊ የጋብቻ ዓይነቶች መኖራቸውን የጥናቱ ተሳታፊዎች ይገልጻሉ፡፡ ይህንንም ሲያብራሩ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ በአራት እንደሚከፈል፡- እነሱም እሎኛ በመያዝ (Qaadhimannaa)፣ በጠለፋ (Butii)፣ በድንገት ፈረስ ደጅ በማቆም (Irradhaaba) እና በውርስ (Dhaala)

መሆናቸውን መረጃ አቀባዮች አቶ ተስፋዬ[52] ሁንዴ እና አቶ ደረጀ መኮንን (ህዳር 27፣ 2007 ዓ.ም.) አብራርተዋል።

ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ ጥናት እና ምርምር ያስፈልገዋል። ይሁን እንጂ ከጥናቱ ርዕስ አኳያ ከእነዚህ የጋብቻ ዓይነቶች ጋር ተያይዘው የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች ስለአሉ ለግንዛቤ እንዲረዳን የእያንዳንዱን ትርጉምና አፈጻጸሙን ከመረጃ አቀባዮች የተገኙትን መረጃዎች በአጭሩ እንደሚከተለው እናያለን።

እጮኛ በመያዝ፡- ይህ የጋብቻ ዓይነት የልጁ አባት ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌ በመላክ ለምነው ሲፈቀድላቸው በባህሉ መሠረት ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ የሚፈጸም ጋብቻ ነው። የሠርጉ ቀን ከመድረሱ በፊት አንድ ወር አስቀድሞ በልጅቷ (ሙሽራዋ) ቤት ማታ ማታ ለወጣቶቹ ብቻ በተዘጋጀ ቤት ውስጥ Jalabultii (የምሽት ዘፈንና ጭፈራ) ሥርዓት ይከናወናል። በዚህ ፕሮግራም ላይ የሙሽራዋ ጓደኞች የሆኑ ልጃገረዶች እና በቅርብም ሆነ በሩቅ ያሉ አግቢዋን የሚያውቁ ጎረምሶች በጭፈራው ይሳተፋሉ። ከንፈር ወዳጆችም ይሳሳማሉ። አብዛኛው ዘፈኖቻቸው ከጋብቻ እና ከከንፈር ወዳጅ እንዲሁም ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጋር የተያያዙ ናቸው። አልፎ አልፎ ሌሎችንም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚ (ግብርና) እና ፖላቲካ ነክ ይዘት ያላቸው ዘፈኖች ይዘፈናሉ። በተለይም ሠርጉ ሦስት ቀን ሲቀረው ከማታ ጀምሮ እስከ ንጋቱ 11፡00 ሰዓት ድርስ ሲጨፍሩ ያድራሉ። ወጣቶች ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ሙሽራዋን ለማጫወት እና በዚሁ አጋጣሚ ከንፈር በመሳሳም የፍቅር ፍላጎታቸውን ለማርካት መሆኑን መረጃ አቀባዮች አብራርተዋል (ፈተኑ ዳመሳ፤ ተማሪ ሽቶ አዱኛ፣ ተማሪ ቦንቱ ታደሰ፣ ወ/ሮ ደብርቱ ገረሱ እና አቶ ለሚ ገመቹ ሚያዚያ፣ 2007ዓ.ም)።

በሠርጉ እለት ያለው ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ አግቢው ልጅቷን ይዞ ወደ ቤት በሚገባበት ጊዜ የደንብ በግ (Hoolaa rakoo) አርዶ እና ሌሎችም መሟላት የሚገባቸው ሥርዓቶች ይከወናሉ። የደንብ በግ ታርዶላት ያገባች ሴት ትልቅ ክብር ያላትና ሕጋዊ ሚስት ናት። በባህሉ መሠረት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያገባች ሴት Nitii hoolaan rakkoo ittiqalame (nitii seeraa), niitii qeerrumma, nitii ganamaa jedhamti. ሲተረጎም የደንብ በግ የታረደላት ሚስት (የሕግ ሚስት)፣ የወጣትነት ሚስት፣ የመጀመሪያ ሚስት ትባላለች።

---

[52] አቶ ተስፋዬ ሁንዴ ዕድሜው 70 ነው። ተወልዶ ያደገው ሱሉልታ ወረዳ ውስጥ ሲሆን ባህላዊ ጋብቻን በሚመለከት በሽምግልና ብዙ ቦታ ይጠራል። ጠቋሚን መሠረት ባደረገ ናሙና የተመረጠ መረጃ አቀባይ ነው። የቱለማ ኦሮሞ የጋብቻ ዓይነቶችን እንዲሁም ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በደንብ ያውቃል። በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎችን በመስጠት ጉልህ ተሳትፎ የነበራው በመሆኑ ስሙ በዚህ ጥናት ውስጥ ተደጋግመዋል።

Niitiin rakoon fuudhan hin hiikamtu. ሲተረጎም የደንብ በግ ታርዶላት ያገቧት ሚስት አትፈታም (መረጃ አቀባዮች አቶ ተስፋዬ ሁንዴ፣ አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ እና ጠጂቱ ቂጠታ ጥቅምት፣ 2007ዓ.ም)።

ጠለፋ፡- ይህ የጋብቻ ዓይነት ወንዱ ሌሎች ጎረምሶችን ጨምሮ ሴቷን በማስገደድ የሚፈጸም ጋብቻ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ጋብቻ በሁለቱ ቤተሰብ መካካል ግጭትን የሚፈጥር እና በመጨረሻ በሽማግሌዎች እርቅ ወደ ሠላም የሚመጣ የጋብቻ ዓይነት ነው። በሌላ መልኩ በአሁኑ ዘመን በሴቷ እና ወንዱ ፍቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ስምምነት ጠለፋ ተካሂዶ በኋላ ላይ ለእርቅ ሽማግሌዎች የሚላኩበት ሁኔታዎችም እየተፈጠሩ መሆኑን መረጃ አቀበዮች[53] ገልጸዋል። ይህም የሚደረገው በአሁኑ ዘመን ጠለፋ በሕግ ስለሚያስጠይቅ እና እስርም የሚያስከትል በመሆኑ እንደ ድሮ ሴቷን አስገድዶ መጥለፍ እንደሌለ ይነገራሉ። ጠለፋ መቅረቱ ከለውጥ አኳያ ባህሉ መቀየሩን የሚያመለክት ነው። ሆኖም በሴቷ እና በወንዱ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ጠለፋ ተካሂዶ ጋብቻ መመሥረቱ ከባህላዊ እሴቱ ቀጣይነት አኳያ የሚታይ ነው።

የጥናቱ ተሳታፊዎች የጋብቻ አፈጻጸም እና ከጋብቻ ጋር ተያይዞ ያለውን ሁኔታ እንዲገልጹ ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ በቱለማ ኦሮሞ የጋብቻ ጥያቄ ቀርቦ የሠርጉ ሥነሥርዓት እስኪፈጸም ድረስ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት መኖራቸውን ይገልጻሉ። በሌላ በኩል በቱለማ ኦሮሞ የጋብቻ ሥርዓት ውስጥ ሁለቱ ተጋቢዎች በቅርብ የሥጋ ዝምድና የማይገናኙ እና የተለያየ ጎሳ አባላት መሆን እንደሚጠበቅባቸው ይጠቁማሉ። ሴቷ ከማግባቷ በፊት Dubra (ልጃገረድ) መሆን እንደሚኖርባት እንዲሁም ወንዱ ከማግባቱ በፊት Qeeroo (ያለገባ ወንድ) ይባላል። ካገባ በኋላ Suphoo እንደሚባልና ይህን በተመለከተም በርካታ የሥነቃሎች እንዳሉ አብራርተዋል። በጋብቻው እለት ሙሽሮች፣ የሙሽሮችን ቤተሰብ እንዲሁም ሚዜዎችን በሚመለከት ልዩ ልዩ ዘፈኖች ይዘፈናሉ[54]።

---

[53] (አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ አቶ ታደሰ ደህኔ አቶ ተስፋዬ ሁንዴ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ ህዳር 2007ዓ.ም)።

[54] (መረጃ አቀባዮቹ አቶ በጅጋ ሮሪሳ አቶ ታደሰ ደህኔ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም.)። እንዲሁም አቶ ጌቱ ታደሰ እና አቶ ቸሩ ሮሪሳ (ሚያዚያ 18 ቀን 2007 ዓ.ም.)።

እረዳባ፡- ይህ የጋብቻ ዓይነት የሚፈጸመው የልጅቷ ቤተሰብ ሳያስቡ በድንገት የሠርገኛ ፈረስ ደጃቸው በማቆም የሚከናወን የጋብቻ ዓይነት ነው። አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ የሚደረገው አግቢው በሥነሥርዓት የለመናትን ልጅ ሠርግ ደግሶ ለማግባት አቅሙ የማይፈቅድ ሲሆን፣ እንዲሁም ሳይለምናትም አግቢው በአቋሙ ደካማ ወይም አካለ ጎዶሎ ሲሆን፣ ወይም የልጇ ቤተሰብ ድሆች ከሆኑ በልመና ማንም ስለማይሰጥ በዚህ ዘዴ ጋብቻ የሚፈጸምበት መንገድ ነው። በዚህ የጋብቻ ዓይነት ደንብ መሠረት የሠርገኛ ፈረስ በምታገባ ሴት ቤተሰብ ደጅ ከቆመ አይከለከልም። ምክንያቱም በባህላዊ እምነቱ ለልጅቷም ሆነ ለቤተሰቦቿ መጥፎ እድል ያጋጥማል ተብሎ ስለምታሰብ ነው።

የውርስ ጋብቻ፡- ይህ የጋብቻ ዓይነት ወንድም ከሞተ የወንድሙ ልጆች በእንጀራ አባት ወይም በሲገባ እንዳይበደሉ ልጆች እንክብካቤ ለማድረግ እና የሟቹ ንብረት በሌላ ሰው እንዳይወርስ የሚፈጸም ጋብቻ ነው። በዚህም ምክንያት ወንዱ ከአንድ ሚስት በላይ ሊኖረው ይችላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኢ-ውስን ቃለ-መጠይቅ ባህላዊ የጋብቻ ፍቺ ስለ መኖሩ ለተጠየቁት አንድ መረጃ አቀባይ ሲመልሱ የተናገሩት እንዲህ ነበር።

> Aadaa Oromoo Tulamaa Keessatti nitii qeerrummaan fuudhan nitii ganamaa jedhamti. Nitiin ganamaa immoo safuu qabdi. Kanaafuu niitii qeerrummaan fuudhan hinhikan kuni safuu maleedha. Yoo rakkonillee jiraate fakenyaaf niitiin ganamaa sirumaa kan hindeenye yoo taate, odoo niitii ganamaa hin hiikin, eyyaama ishiitiin nitii biraa fuudhuu ni danda'a malee akkaa aadaa Oromoo Tulamaatitti aadaan nitii ittiin hiikan hinjiru Obboo Tasfaayee Hundee, (sadaasa 27 bara 2007).

የአማርኛ ትርጉም

> በቱለማ ኦሮሞ ባህል ውስጥ በወጣትነት ያገቧት ሚስት የመጀመሪያ ወይም የጧት ሚስት ትባላለች። የመጀመሪያ ሚስት ደግሞ Safuu[55] (ሥርዓት) አላት። ስለዚህ በወጣትነት ያገቧትን ሚስት መፍታት safuu (ነውር) ነው። ችግር እንኳን ቢኖር ለምሳሌ የመጀመሪያ ሚስቱ በጭራሽ የማትወልድ ከሆነ በመጀመሪያ ሚስቱ ፈቃድ ሌላ ሚስት ሊያገባ ይችላል እንጂ በቱለማ ኦሮሞ ባህል መሠረት ባህላዊ ፍቺ የሚባል ነገር የለም አቶ ተስፋዬ ሁንዴ (ህዳር 27፣ 2007 ዓ.ም.)።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር በኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ውስጥ ፍቺ አለመኖሩን ጌታቸው ኃይሌ (1997፡192) እንደሚከተለው ገልጿል። … "[ኦሮሞ] ግን [በ]ምንም ምክንያት ቢሆን በረኮ ያገባትን [ሚ]ስቱን ከቶ አይፈታም።" በመሆኑም ከመረጃ አቀባዩም ሆነ ከጽሁፍ የተገኘው

[55] "Safuu" በኦሮሞ ባህልና እምነት መሠረት አንድ ትርጉም ብቻ የለውም። እንደ አገባቡ ልዩ ልዩ ትርጉሞች አሉት። ይህም በምክር ሥርዓት ማክበርን፣ በማስጠንቀቅ፣ ቅሬታ ወይም ነውርን፣ መፍትሔ ለሌለው ነገር ፍርሃትን የመሳሰሉ ትርጉሞች አሉት። (Siida-ilaalcha-Waaqeffannaa... waaqeeffannaa.org 09/28/2015 97.35KB).

መረጃ በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ውስጥ ፈቺ የሌለ መሆኑን ያስገነዝበናል። በሌላ መልኩ ሥርዓት ማለት የፈጣሪ እና የተፈጥሮ ሕግ መከተል መሆኑን እና በኦሮሞ ውስጥ ይህንን መጠበቅ የመጀመሪያ ተግባር እንደሆነ Dirribii Damisee (2009: 62) ያብራራል። በመሆኑም ከመረጃ አቀባዮችም ሆነ ከልዩ ልዩ የጽሑፉ መረጃዎች እንደተገነዘብነው በኦሮሞ ባህለዊ የጋብቻ ሥርዓት ውስጥ የፍቺ ባህል አለመኖሩን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በቱለማ ኦሮሞ ከወሲብ ጋር በተያያዘ የሚከወኑም ሆኑ የሚነገሩ ነውር ጉዳዮች መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ የሥጋ ዝምድና ካለው ሰው ጋር ወሲብ መፈጸም ነውር ነው። በመደበኛ ንግግር ውስጥ የመራቢያ አካላትን በስማቸው መጥራት ነውር ነው። ስለ ጉዳዩ መግለጽ ካስፈለገ እንኳን እንዲያው በደፈና እንትኑ፣ እንትኗ ይባላል እንጂ የመራቢያ አካላት ስም አይጠሬ ናቸው።

ይሁን እንጂ በሥነቃል ውስጥ የወንድም ሆነ የሴት መራቢያ አካላት ስማቸው እየተጠራ ይዘፈንበቸዋል። ስለ ሲገባ ምንነት እና ለምን በፎሌዎች እንደሚሰደብ ባህሉን መሠረት በማድረግ ምክንያቱን በዚሁ ምዕራፍ በሲገባ ርዕሰ ጉዳይ ሥር በስፋት እንመለከታለን። ከዚህ በመቀጠል ስለከንፈር ወዳጅ የተገኘውን መረጃ እናያለን።

ፎቶ ግራፍ 12. በግራ በኩል ከግራ ወደ ቀኝአቶ በጅጋ[56] ሮሪሳ እና አቶ ታደሠ[57] ደህኔ (ሚያዚያ 18 ቀን 2007 ዓ.ም)።
በቀኝ በኩል ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ጌቱ[58]ታደሰ እና አቶ ቸሩ[59] ሮሪሳ ለገጣፎ (18/08/2007 ዓም.)።

2. የከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

ከንፈር ወዳጅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ምን እነማን ምን ተግባራትን፣ መቼ፣ እና እንዴት እንደሚፈጽሙ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት መልሶች ውስጥ በወ/ሮ ጠጅቱ ቂጠታ የተገኘ መልስ እንደሚከተለው የቀረበ ነው።

> Aadaan wadaajii dhungoo Oromoo Tuulamaa biratti bakka guddaa qaba. Wadaajii dhungoo jechuun dargaggeessii fi shamarran hidhii xuuxanii waldhunggachuun karaa fedhii jaalala isaanii ittiin bahaniidha. Wadaajii kan walii ta'uu danda'an dargaggoota fi shamarran fira dhiigguummaa walirraa hinqabneedha. Gocha kana raawwachuuf jarreen lamaanuu gaayeela kan hin godhatin ta'uu qabu. Kan waldhungatan shamarreen bakka bishaan waraabduutti, kobota, mukaa fi migira guurtutti akkasumas karaa gabaa dhaqxutti. Kanaan alattis bakka fi yeroo mijaahaa ta'e hundattu waldhungatu.
> Yaa ta'u malee yeroo waldhungatan kana maatiin isaanis ta'ee, namoonni gurguddaa isaan arguu hin qaban. Kunis safuu eegachuuf jecha. Yemmuu waldhungatan hiriyoota isnitiin ala namoonni biraa akka hin argne kan taasifamu, haala aadaatiin kan hin eeyyamamne ta'ulle, dhimma kana yeroo dargaggummaa fi shamarrummaa osoo hin dhungatin kan bira dabre hin jiru. Gaayeela booda wadaajii dhungachuun safuudha.
> Jaalala waliif qaban ibsuuf rigaa muranii walii kennu. Dhirri dubartiidhaaf urgooftuu, shashii fi naxalaa fa'a bitee kennaaf. Ishiinis immoo karameellaa, loomii fi qarshiilee hin kennitiif. Anis dur yeroo kootitti kana raawwadheetuman bira dabre Aaddee Xajjituu Qixatataa (Onkoloolleessa 29, bara 2007 A.L.I).

ትርጉም በአማርኛ

> **የከንፈር ወዳጅ ባህል በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ የታወቀ እና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው። ከንፈር ወዳጅ ማለት ጎረምሶችና ኮረዳዎች ከንፈር በመሳሳም ፍቅራቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው። የከንፈር ወዳጅ የሚሆኑት የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ወጣቶች ናቸው። የከንፈር ወዳጅ ለመሆን ሁለቱም ጾታ ያላገቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የከንፈር ወዳጆች የመሳሳሚያ አጋጣሚ ሴቷ ውኃ ስትቀዳ፣ ኩበት፣**

---

[56] አቶ በጅጋ ሮሪሳ ተወልደው ያደጉት በበረከ ወረዳ ለገጣፎ ነው። የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን (ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ሲገባ፣ ውሽማ) ጋር ተያይዘው የሚነከሩትን ሥነቃሎች በደንብ ያውቃሉ። በተለይ በምሳሌያዊ ንግግር እውቃታቸው የሚጠቀሱ ናቸው። በመሆኑም ብዙ ጊዜ በአከባቢው አቶ በጅጋ "እንዲህ አሉ" ተብለው ይነገርላቸዋል። በአከባቢ አባትነታቸው አጥኚውን ያሳደጉ ናቸው። በሥነቃል ችሎታቸው ስለሚታወቁ በኢለማ ናሙና ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ናቸው። በጥናቱ ውስጥ በርካታ መረጃዎችን በመስጠት ጉልህ ተሳትፎ ነበራቸው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ስማቸው ተደጋግሞ ተጠቅሷል።

[57] አቶ ታደሰ ደህኔ ተወልደው ያደጉት በበረከ ወረዳ ለገጣፎ ሲሆን የአቶ በጅጋ ሮሪሳ የቅርብ ጓደኛ ናቸው። እሳቸውም በሥነቃል ችሎታቸው በኢላማ ናሙና የተመረጡ መረጃ አቀባይ ናቸው።

[58] አቶ ጌቱ ታደሰ ዕድሜ 46 ነው። የአቶ ታደሰ ደህኔ ልጅ ነው። የከንፈር ወዳጅ ባህልን ከነሥነቃሎቹ ያውቃል። በኢላመማ ናሙና የተመረጠ መረጃ አቀባይ ነው።

[59] አቶ ቸሩ ሮሪሳ ዕድሜ 72 ነው። የአቶ በጅጋ ሮሪሳ ታናሽ ወንድም ሲሆኑ እሳቸውም በሥነቃል ችሎታቸው በኢላማ ናሙና የተመረጡ ናቸው።

የማገዶ እንጨት እና ስንደዶ ስትለቅም እንዲሁም ገበያ ስትሄድ ነው። ከዚህም ውጭ በማንኛውም አመቺ ጊዜና ቦታ ይሳሳማሉ።

በዚህ ወቅት ወላጆቻቸውና ማንኛውም ትላልቅ ሰዎች ማየት የለባቸውም። ይህም ባህላዊ ወጉን/ሥርዓቱን ለመጠበቅ ሲባል ነው። የቱለማ ኦሮሞ ሆኖ ከማግባቱ በፊት የከንፈር ወዳጅን ተግባር የማይፈጽም የለም። ሆኖም ከጋብቻ በኋላ ይሄንን ተግባር መፈጸም ነውር ነው።

ስጦታ መሰጣጣትን በተመለከተ መፋቂያ ቆርጠው ይሰጣጣሉ። ወንዱ ለሴቷ ሽቶ፣ሻሽና ነጠላ ይገዛላታል። ሴቷ ደግሞ ከረሜላ፣ ሎሚ እና ገንዘብ ትሰጠዋለች። እኔም ብሆን ይህንን ተግባር በጊዜዬ ፈጽሜያለሁ በማለት ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ ጥቅምት29፣ 2007 ገልጸዋል።

የከንፈር ወዳጆች መሳሳሚያ አጋጣሚ በተመለከተ ሌሎች መረጃ አቀባዮች ሲገልጹ፡- በባህላዊ ጋብቻ ጊዜ jalabultii በመባል በሚታወቅ በታጨች ልጃገረድ ቤተሰብ ዘንድ ማታ ማታ ሲጨፍሩ፣ በባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት በተለይም በእንቁጣጣሽ የልጃገረዶች ጭፈራ ወቅት ይሳሳማሉ። በጥምቀት ክብረ-በዓል ላይም ቀን ልዩ ልዩ ዜማ ያላቸውን በርካታ የፍቅር ዘፈኖች በመዝፈን አንገት ለአንገት ተያይዘው ሲጨፍሩ ውለው ከዚያም ማታ ወደ ቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ በየመንገዱ ጥግ፣ ጥግ ይዘው ነጠላ ተሻፈፍነው ከንፈር ለከንፈር በመሳሳም የፍቅር ስሜታቸውን ይገላለጻሉ። “በድሮ ዘመን የግብረሥጋ ግንኙነት ወደ መፈጸም አይሸጋገሩም ምክንያቱም በባህሉ መሠረት የከንፈር ወደጆች ወሲብ ከፈጸሙ በባህሉ **ነውር** በመሆኑ ውግዘት ይድርስባቸዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ዘመን ይህ ነውር ቀርቶ የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል።” (መረጃ አቀባዮች አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

“በአሁኑ ዘመን የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል።” የሚለው አባባል የዘመኑ ወጣቶች እንደ ድሮ ባህልን አክብረው በመሳሳም ብቻ ሳያበቁ ወደ ወሲብም እንደሚሸጋገሩ ያመለክታል።

ይህንን ባህል በማንጸባረቅ ረገድ የከንፈር ወዳጅ በመሆን የሚሳሳሙት በወጣትነት እድሜ[60] ክልል ያሉ ናቸው። ይሁን እንጂ በጥናቱ አካባቢ ግን አብዛኛውን ጊዜ ከ12 እስከ 25 ዕድሜ ክልል ያሉ በከንፈር ወዳጅነት የሚሳሰሙ መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህንኑ መሠረት በማድረግ ከ3 ወጣቶች ጋር በተካሔደ ቃለ-መጠይቅ የተገኘው መልስ ከላይ ከተጠቀሰው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት አለው። አንድ ወጣት ካንድ በላይ ከንፈር

---

[60] የWHO, (1995) መረጃ እንደሚያሳይ የወጣትነት ዕድሜ ክልል ከ15 እስከ 24 ያለውን ነው።

ወደጅ የሚኖረው ሲሆን ሴቷም ብትሆን እንደዚሁ ከአንድ በላይ የከንፈር ወዳጅ ይኖራታል። ከእነዚህ ውስጥ ግን እሱ ከልቡ የሚወዳት ወይም እሷ ከልቧ የምትወደው ይኖራል (ጋዲሳ አዱኛ መገርሳ ሁንዴ፣ ቦንቱ ታደሰ እና ፋኖሴ ጋዲሳ ህዳር 11 ቀን 2007 ዓ.ም)።

የከንፈር ወዳጅ እንዴት፣ የት እና መቼ እንደሚሳሳሙ ለቀረበለት ጥያቄ አንድ ወጣት መልስ ሲሰጥ እንደሚከተለው ገልጿል።

> Dhungoon haala addaa addaatiin bakka addaa addaatti raawwatama. Ani yemmuun dhngadhu karameellaa biteetan gamisa isaa arrabaa kootiiin afaan ishii keecha godhee, hidhii ishiidhaa xuuxee mi'eeffachaa dhungadha. Akkanatti gorora walii xuuxna. Karameellaan suni gorora mi'eessa. Haala kanaan hanga hidhiin ishii dimatuttan dhungadha.
>
> Bakkeen itti wal dhungannuu immoo eddoo bishaan waraabdutti, bakka kobota gurtuutti, bakka migira guurtutti fi bosona keechatti fa'a. yeroo heduun kan itti waldhngannu immoo gaafa qaammee ijoolleen dubaraa mana manarra deemanii qunni darban, guyyaa kabaja ayyaana masqalaa fi aduu ximqataa fa'a. Dablataanis bakka fi yeroo nutti tole hundumaa wal dhunganna. Tolosaa Marga, (Amajjii 11, bara 2007 A.L.I.)

ትርጉም በአማርኛ

> መሳሳም በተለያየ ቦታ እና ሁኔታ ውስጥ ይፈጸማል። እኔ ከረሜላ እገዛና ግማሹን በጥርሴ ሰብሬ በምላሴ አፏ ውስጥ አደርጌ ከንፈሯን መጥጬ እያጣጣምኩ እስማታለሁ። በእንዲዚህ ዓይነት ሁኔታ ከንፈሯ እስከሚቀላ ድረስ እስማታለሁ።
>
> የምንሳሳምበት ቦታ ገበያ ስትወጣ፣ ውኃ በምትቀዳበት፣ ኩበት በምትለቅምበት ስንደዶ በምትለቅምበት እና ጫካ ውስጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የምንሳሳመው በእንቁጣጣሽ፣ በመስቀል እና በጥምቀት ክብረ በዓላት ሲሆን ከዚም በተጨማሪ አመቺ በሆነ በየትኛም ጊዜ እና ቦታ እንሳሳማለን። ቶሎሳ መርጋ (ጥር 11 ቀን 2007 ዓ.ም)።

ከዚሁ ጋር በተያየዘ ሁኔታ ሁለት በታዳጊ ወጣትነት ዕድሜ ክልል የሚገኙ መረጃ አቀባዮች እንደነገሩኝ ወንዱ በ12 ዓመቱ፣ ሴቷ በ13 ዓመቷ ከንፈር መሳሳም መጀመራቸውን በመግለፅ ከላይ በወጣት ቶሎሳ የተነገረውን ሀሳብ ይጋራሉ (ወጣት ተስፋዬ ቶላ እና ወጣት ደሜ ማሩ ጥር 11 ቀን 2007 ዓ.ም)።

በሌላ መልኩ ከንፈር ወዳጅነት ባህሉን ተከትሎ ስለ መፈጸሙ ጉዳይ በሚመለከት ከንፈር በሚሳሳሙበት ወቅት የግብረሥጋ ግንኙነት ፍላጎት አይፈጠርም ወይ? ፍላጎቱ ከኖረ ደግሞ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን እንዴት ትቆጣጠራለህ/ሽ? የሚሉ ጥያቄዎች ለተወሰኑ

ወጣቶች በተናጠል ቀርቦላቸው ስማቸው እንዳይገለጽ በማሳሰብ ለጥያቄዎቹ የሰጡት ምላሾች ተቀናብረው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የመሳሳሙን ተግባር በጣም ተጠጋግተው እና ተቃቅፎ የሚከውኑት በመሆኑ በዚህን ጊዜ የወሲብ ፍላጎታቸው እንደሚያይል፣ ብልታቸውን ወደ ከንፈር ወዳጃቸው ጭን ውስጥ በማስገባት በመተሻሸት ወሲባዊ እርካታ እንደሚያገኙ ሲገልጹ አንዳንዴም የግብረሥጋ ግንኙነት እንደሚፈጽሙ አልደበቁም። ይህንን በተመለከተ ወጣት ሴቶች ሲመልሱ እያፈሩ ከላይ በወንዶቹ የተገለጸውን ተግባራት እንደሚፈጽሙ ተናግረዋል። እነዚህ ወጣቶች ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በግብረሥጋ ግንኙነት እንደሚተላለፍ እውቀቱ ያላቸው ቢሆንም የወሲብ ፍላጎታቸው በማየሉ ችግርም ቢሆን የመጣ ይምጣ በማለት የግብረሥጋ ግንኙነቱን ከመፈጸም እንደልተቆጠቡ ገልጸዋል።

በድርጊቱ ላይ ከተሳተፉ ወጣቶች የተገኘው መረጃ ቀደም ሲል መረጃ አቀባዮች አቶ ሰይፉ መልካ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ በአሁኑ ዘመን የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል በማለት የከንፈር ወዳጅነት የድሮ ባህሉን ባለመከተሉ ያሰሙት ቅሬታ እውነት መሆኑን ያሳያል። ይህም ከአውዱ የተገኘው መረጃ ባህላዊ ፍቅር ግንኙነቱ እየተለወጠ መምጣቱንና እንደዚህ ዓይነቱ ዲርጊት ደግሞ ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት በር የሚከፍት እና አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ያመለክታል።

3. ውሽማን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

ስለ ውሽማ ምንነት እንዲገልጹ ለቀረበው ጥያቄ መረጃ አቀባዮች መልስ ሲሰጡ ውሽማ ማለት አንድ ጎልማሳ ወንድ ሚስት እያለውም ሆነ ሳይኖረው ከአንዲት ባል ካላት ሴት ጋር ወይም አንድ ባለትዳር ሴት ከሌላ ወንድ ጋር በድብቅ የሚደረግ የፍቅር ግንኙነት ነው ። ግንኙነቱ አብዛኛውን ጊዜ በተግባር የሚፈጸመው በተለይም ባሏ ቤት በማይኖርበት ወቅት ሴትዋ ውሽማዋን በመጥራት ወሲባዊ ግንኙነት ይፈጽማሉ። በዚህን ወቅት ሴቷዋ እንደ ጨጨብሳ እና ገንፎ ያመሳሰሉትን ተመራጭ የሆኑ ባህላዊ ምግቦች በማዘጋጀት ለውሽማዋ ታበላለች። ይህም የውሽምነት ፍቅር ስለሚጣፍጥ የተለየ ጣፋጭ ምግብ ትመግብዋለች። እሱም ለእሷ ልዩ ልዩ አኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ነገሮች ያድርግላታል። ከልብስ መግዛት ጀምሮ ሌሎችንም እሷ የፈለገችውን ያደርግላታል። ድብቅነቱ ምናልባት ሚስቱ በውሽምነት ከተያዘችበት ባል ወይም ባሏ በውሽምነት ከተያዘባት ሚስት ይሆናል እንጂ በአካባቢው ያሉት ሰዎች ሊያውቁ ይችላሉ።

ግንኙነታቸው እየጠነከረ ከሄደ ደግሞ በሁሉም ዘንድ ሊታወቅ ይችላል። እንደዚህ ዓይነቶቹ በትዳር ላይ ከሌላ ወንድ ወይም ሴት ጋር የሚፈጸም ግንኙነት ለትዳር መፍረስ ምክንያት ይሆናል (አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ፅጌ ሁሪሳ እና ወ/ሮ አየለች ሂና፣ መጋቢት 15 ቀን 2007) ።

በሌላ መልኩ ወንዱ ሚስት እያለው ባል የሌላትን ሴት ቤት ሠርቶላት ወይም ገዝቶላት አልያም ተከራይቶላት የሚያስቀምጣት ሊሆን ይችላል። የዚህ ዓይነት ግንኙነት Sanyoo Teechifachuu (ውሽማ ማስቀመጥ) ይባላል። "የድሮ ውሽምነት ወግ እንዳለውና በድብቅም የሚከሄድ መሆኑን ይጠቅሱና በአሁኑ ዘመን የውሽምነት ግንኙነቱ አልቤርጎዎች በየከተማው በብዛት የሚገኙ በመሆናቸው እንደ ድሮ ወግ እንደሌለውና ድብቅም ሳይሆን ሁሉም በየቡና ቤቱ ማንም እያያቸው እየተዳሩ ናቸው። (መረጃ አቀበዮች አቶ ሙሉጌታ አያኔ እና አቶ ሰይፉ መልካ፣ ወ/ሮ ሊና በየነ እና አቶ ሁንዴ በዳኔ፣ ሚያዚያ፣2007)።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የዚህ ዘመን ውሽምነት ከድሮ ጋር ሲነጻጸር በችግሮች የታጠረ ነው። በድሮ ጊዜ ውሽማን ለማስቀመጥ የኢኮኖሚ አቅም የሚፈቅድ ሲሆን በሽታም ቢሆን እንደ ጨብጥ፣ ቂጥኝ፣ ከርከር እና የመሳሳሉት በቀላሉ በህክምና የሚድኑ ናቸው። በአሁኑ ዘመን እንኳንስ ውሽማ ማስቀመጥ ቀርቶ ራስንም ማስተዳደሩ ችግር ነው። በዚህ ላይ ደግሞ አቅም ያለውም ቢሆን አጅሬ ኤድስ ከያዘው ስለማይለቅ ጊዜው አስከፊ መሆኑን መረጃ አቀባዮች አቶ አበበ ጀቤሳ እና ወ/ሮ ደብሪቱ ሞረዳ (ጥር 8 ቀን 2007) ገልጸዋል።

ከእነዚህ መረጃዎች የምንገነዘበው ውሽምነት ለትዳር መፍረስ ምክንያት በመሆን በቤተስብ ውስጥ ቀውስ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት መባባስም የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ነው።

ፎቶ ግራፍ 13. በስተ ግራ በኩልከግራ ወደ ቀኝ መምህር አበበ ጃቤሳ፣ መምህርት ደብሪቱ ሞረዳ እና አጥኚው፤በስተ ቀኝ በኩል መምህር አበበ ጀቤሳ እና አጥኚው በሱሉልታ 2ኛ ደረጃናመሰናዶ ትምህርት ቤት ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም.

4. ሲገባን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

የሲገባ ምንነት እንዲያብራሩ በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ (እውቀት) ላላቸው መረጃ አቀባዮች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሲገባ ማለት አንድ ጎልማሳ የሆነ ሰው ሚስት እያለው ወይም ሳይኖረው በሏ የሞተባት ሴት ቤት ገብቶ በቀድሞ በሏ አልጋ ላይ የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመን ወንድ ማህበረሰቡ የሚጠራበት ስም ነው። ሲገባ በቱለማ ኦሮሞ ውስጥ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነት መገለጫ አንዱ ነው። ሲገባ የሚገባ ወንድ ከሴትዮዋም ሆነ ከሟች ባሏ ጋር የሥጋ ዝምድና አይኖረውም። ሲገባ መግባትም ሆነ ሲገባ ማስገባት በባህሉ የተወገዘ ነው። በተለይ ሲገባ የገባ ሰው ዘመዶችም ተወቃሽ ናቸው። ስለዚህ ሲገባ የሚገባ ወንድ ዘመዶቹንም አሰዳቢ ነው። በዚህም የተነሳ ሲገባን ዘመዶቹም እንደማይወዱት መረጃ አቀባዮች ይገልጸዋል (ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ እና አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ጣሰው በየነ እና እና አቶ ስለሽ ዳባ፣ የካቲት፣ 2007)።

ይህንን የሚያጠናክር የጥናታዊ ጽሑፍ መረጃ ሲገባ ከማህበረሰቡ ባህል ያፈነገጠ ተግባር በማከናወኑ ፎሌዎች ይሄን ተግባር የሚፈጽም ግለሰብ እናት ሳይቀር በዘፈን አማካይነት እንደሚሰድቧት Desta Desalegn, (2015:39) ገልጿል። ይህም ሲገባ በባህሉ ክብር የሌለውና የተናቀ ሰው ከመሆኑም በላይ ዘመዶቹንም አሰዳቢና ነውረኛ መሆኑን ያሳል። ምክንያቱም ባሏ የሞተባት ሴት ቤት ገብቶ ወሲብ መፈጸም ውርደት በመሆኑ በባህሉ ይወገዛል። በዚህ የተነሳ ሲገባ የገባ ወንድ በገዳ ሥርዓት ውስጥ በፎሌዎች ይሰደባል፤ ዘመዶቹንም ያሰድባል። ሲገባ ያስገባችም ሴት እንደዚሁ የውርደት ስድብ ይዘት ባላቸው ዘፈኖች ትሰደባለች።

በመሆኑም ፎሌ በገዳ ሥርዓት ውስጥ በየስምንት ዓመቱ በሚያካሔደው የዘፈን ጨዋታ የሲገባን ነጠላ ቀዳዶ Fororsaa በሚባል ፎሌዎች ይዞ በሚጨፍሩት ረዥም እንጨት ላይ አስሮ ሲገባን በማንቋሸሽ በዘፈን ሙልጭ አድርገው ይሰድቡታል። (አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ አቶ ታደሰ ጣፋ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

በገዳ ሥርዓት ውስጥ ፎሌ ሲገባን በሥነቃል እንደፈለጉ እንዲሰድቡ ወይንም የፈለጉትን እንዲያደርጉ መብት ያገኙበትን ባህላዊ ምክንያት እንዲያስረዱ በዚህ ባህል የተሻለ እውቀት ላለው ለአቶ ታደሰ ጣፋ ጥያቄው ቀርቦ ምላሹን በአፋን ኦሮሞ ሰጥቷል። አፈ-ታሪኩ ረዥም በመሆኑ ቦታ የሚፈጅ ስለሆነ የአፈታሪኩ ትርጉም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በድሮ ጊዜ ባሏ የሞተባት ሴት ቤት ገብቶ የግብረሥጋ ግንኙነት ይፈጽም የነበረ አንድ ሲገባ ነበር። አባቱ የሞተበት አንድ ትንሽ ወንድ ልጅ ደግሞ ከእናቱ ጋር ስለሚተኛ ሲገባውና እናቱ ሌሊት፣ ሌሊት ወሲብ ሲፈጽሙ ሽንት እያሸና ያስቸግራቸው ነበር። በዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ በመቸገራቸው ሲገባው የልጁን ወሸላ (ያልተገረዘ ብልት) በክር እንዲታሰር አደረገ። ከዚያም ያለምንም ስጋት ሽንት ሳይሸናባቸው አደሩ። ይሁን እንጂ ልጁ ሽንት ለመሽናት ባለመቻሉ ፊኛው ተወጥሮ ሞቶ አደረ። በማግስቱ የልጁ ቀብር ሥነ-ሥርዓት በምፈጸምበት ዕለት እና ከዚያም በኋላ "በሠላም ይጫወት የነበረ ልጅ ምን ሆኖ ሞተ?" የሚለው ሀሳብ የመንደርተኛው መነጋገሪያ ሆነ። የልጁ አሟሟት የሰዎች መነጋገሪያ መሆኑ እናትየዋን ስላስጨነቃት ጥፋቷን ለአገር ሽማግሌዎች በዝርዝር አስረዳች። የአገር ሽማግሌዎችም በጉዳዩ ላይ ከተነጋገሩ በኋላ ጉዳዩን ለገዳ ጨፌ (ምክር ቤት) አቀረቡ። ጨፌውም ሴትየዋን እና ሲገባውን አቅርቦ ሲጠይቃቸው ሲገባው በእሱ ትዕዛዝ መሠረት

የልጁ ወሸላ እንዲታሰር ማድረጉን አመነ። ከዚያም የገዳው ሸንጎ በጉዳዩ ላይ ከመከረ በኋላ ለሕጻኑ ልጅ ሞት ተጠያቂው ሲገባ በመሆኑ ልክ እሱ የሕጻኑን ልጅ ወሸላ እንዳሰረ የሲገባውም ቁላ ይቆረጥ፤ ይህንንም በገዳ ሥርዓት ውስጥ በፎሌ የእድሜ ክልል ያሉት ተግባራዊ ያድርጉ በማለት ወሰኑ። በዚህ ደንብ መነሻ በየስምንት ዓመቱ ፎሌዎች በየቤቱ እየዞሩ በሷ የሞተባት ቤት ውስጥ በቀድሞ የባሏ አልጋ ላይ የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመውን ሲገባ ሁሉ እየፈለጉ ቁላውን መቁረጥ ጀመሩ። ለረዥም ጊዜ እንደዚህ ቢደረግም ወንዶች ሲገባ መግባቱን ሴቶችም ሲገባ ማስገባቱን አልተም ነበር። በመሆኑም የገዳው ሸንጎ በጉዳዩ ላይ በድጋሚ ተወያይቶ "አንድ ሲገባ ባጠፋ ሁሉም ሲገባ መቆረጥ ስለሌለበት፣ መቁረጡ ቀርቶ የሲገባው ልብስ እየተቀደደ (እየተተለተለ) ፎሌዎች ሲጨፍሩ በሚይዙት ረጅም እንጨት (Fororsaa) ላይ ታስሮ ሲገባ የገባውን ወንድ እና ሲገባ ያስገባችውን ሴት የመራቢያ[61] አካላቸውን ስምእየጠሩ በዘፈን እየሰደቡ እንዲያሳፍሯአቸው፣ እንዲያወርዷአቸው ብሎ ውሳኔውን አሻሻለ። በተጨማሪም ባሏ የሞተባት ሴት በቀድሞ ባሏ ቤት ውስጥ ለመቆየት ከፈለገች የሟች ባሏ ወንድም በውርስ ያግባት ተብሎ የማሻሻያ ውሰኔ በገዳ ምክር ቤት ተሰጠ። ይህም የሆነበት ምክንያት የሴቷን የግብረሥጋ ግንኙነት ፍላጎት ለማሟላት እና የሟችንም ልጆች ከውጭ የመጣ ባዕድ እንዳይበድላቸው ተብሎ ነው።

በመሆኑም ከዚህ የማሻሻያ ውሳኔ በኋላ ፎሌዎች በውሳኔው መሠረት የሲገባን ልብስ እየተለተሉ ፎሮሪሳ[62] ላይ በማሰር በየመንደሩ እየዞሩ መሳደቡ ዛሬም አልቀረም። ፎሌዎች አይጠሬ የመረቢያ አካላትን እየጠሩ በሚያሸማቅቅ ሁኔታ በአሳፋሪ የዘፈን ስድቦች ሲገባን የመሳደብ መብት ያገኙት ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያት መሆኑን መረጃ አቀባይ አቶ ታደሰ[63] ጣፋ (ጥቅምት 28፣ 2006 ዓ.ም) አብራርቷል።

ይህንን አፈ-ታሪክ በተመለከተ ፎሌ የሲገባን አካል እንደማይቆርጥ ከጽሑፍ የተገኘ መረጃ እንዲህ ይላል።

---

[61] ሲገባ ያስገባች ሴት እምሷ ስምንት ሞፈር ይውጣል። የሲገባ ቁላው ስምንት ክንድ ነው ወዘተ በማለት የስድብ መዓት ያውርዳሉ።

[62] ፎሮሪሳ ማለት በገዳ ሥርዓት ውስጥ ፎሌዎች የሲገባን ልብስ (ብዙውን ጊዜ ነጠላ ነው የሚሆነው) ቀደው ወይም ተልትለው እላዩ ላይ በማሰር በእጃቸው ወደ ላይ ከፍ አድርገው የሚይዙት ረዥም እንጨት ነው። ይህንን ረዥም እንጨት (ፎሮሪሳ) በመያዝ ፎሌዎች ሲገባ የገባ ወንድ እና ሲገባ ያስገባች ሴት አይጠሬ የሰው ልጅ መራቢያ አካልን በቀጥታ ሰሙ በመጥራት (አሳፋር የሆኑ ቃለቶችን በመጠቀም) በዘፈን ይሳደባሉ። ወደ ላይ እየዘለሉም ይጨፍራሉ።

[63] አቶ ታደሰ ጣፋ ዕድሜው 51 ነው። ተወልደው ያደገው በረከ ወረዳ ኤካ ደሌ በሚባል ቀበሌ ነው። በገዳ ሥርዓት የፎሌ ጨዋታ ውስጥ ተሳትፎ ያለው በመሆኑ የሲገባን ባህል ከነ ሥነቃሉ በደንብ ያውቃል። ከአጥኚው ጋር አብሮ አደግ በመሆኑ የሥነቃል ዕውቀቱ በኢለማ ናሙና የተመረጠ መረጃ አቀባይ ነው።

> Folleen qaama namaa hin murtu. Oromoon dhiiga namaa ni safeeffata. Hin dhangalaasu. Surree isaa karaa dubaa irraa muranii itti sirbaa gabaa naanneessu. Namnni tokko muratame jechuun; nama keessaa bahe jechuudha Diirribii damissee (2009፡ 217).

ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡-

> *ፎሌዎች የሰውን አካል አይቆርጡም። ኦሮሞ የሰውን ደም ማፍሰስ ነውር መሆኑን ስለምገነዘብ አያፈስም። ሱሪውን ከኋላ ቆርጦ እየጨፈሩበት ገበያ ውስጥ ያዞራሉ። አንድ ሰው ተቆርጧል ማለት ከማህበረሰቡ ውስጥ ወጥቷል ማለት ነው ዲሪቢ ደምሴ* (2009፡ 217)።

እዚህ ላይ በአፊ ታሪክ የተነገረውና በጽሑፍ ማስረጃ የቀረበው በተወሰነ መልኩ ይፋለሳል። ይሁን እንጂ ፎሌዎች የሲገባውን ልብስ ቀዶ ፎሮርሳ በሚባል ረጅም እንጨት ላይ የተተለተለውን የሲገባ ልብስ አስሮ በዘፈን እየጨፈሩ በመሳደባቸው ላይ እና ሲገባን በማዋረዳቸው በአፊ ታሪክም ሆነ በጽሑፍ የተገኙ ማስረጃዎች ይስማማሉ። ይህንኑ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከዘፈን ጋር በተያያዘ የፎሌ ተግባር ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል።

> Foolleen seera malee nama hin sodaatu, waan jedhuu fedhe, saalfii tokko malee sirbaan ibsa, … yoo fedhe abbaa Gadaa ni faarsa (seera tolchuu irratti jabaa yoo ta'e) ykn ni abaara (seera yoo cabse). … Sadarkaa Gadaa Foollee keessatti dargaggoonni sirritti biyyas walis baru. … Dur Foolleen yeroo ajjeesu hin gaafatamu, du'us gumaa seeraan hin qabu jedhama. Hayiluu Giraany (Ebla, Bara 2015: 23).

የአማርኛ ትርጉም

> *ፎሌ ሕግን እንጂ ሰውን አይፈራም። ለማለት የፈለገውን ያላንዳች ምንተ-እፍረት በዘፈን ይገልጻል። … ከፈለገ አባ ገዳን ያሞግሳል (ህግ በማውጣት/ በማስከበር/ ጠንካራ ከሆነ)። ወይም ህግ ካለከበረ ይረግማል። … በገዳ ውስጥ በፎሌ ደረጃ የሚገኙ ወጣቶች እርስ በእርሳቸው ይተዋወቃሉ። አገራቸውንም በደንብ እንዲውያቁ ይደረጋል። … ፎሌ ድሮ ከገደለ አይጠየቅም። ከሞተም በህግ የደም ካሳ የለውም። ኃይሉ ግራኝ* (*ሚያዚያ* 2007፡ 23)።

ከዚህ የምንገነዘበው ፎሌዎች ባህሉን የሚያፋልስ ተግባር ውስጥ የተሠማራን ማንኛውንም ሰው ለማሳፈር እንደሚሳደቡ እና ይህንንም የማስፈጸም ሃለፊነት ከገዳ ሥርዓት የተሰጣቸው መሆኑን ከመረጃ አቀባዮችም ሆነ ከጽሑፍ የተገኙ መረጃዎች ይገልጻሉ።

ስለዚህ ፎሌዎች ሲገባን በዘፈን የመሳደብ መብት ያገኙት ከላይ በአፊ-ታሪክ እና በጽሑፍ እንደተገለጸው ከገዳ ሥርዓት ሲሆን በሌላ መልኩ በአፊ-ታሪኩ ውስጥ እንደተገለጸው ኦሮሞ በማህበራዊ ሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥመውን ችግር በውይይት መፍትሔ እንደሚፈልግ እና

ውሳኔውንም መልሶ በማየት መሻሻያ የሚያደርግ ሰዎችን ለመጉዳት ሳይሆን የሰዎችን ሰብአዊ መብት በመጠበቅ ከስህተታቸው እንዲማሩ ታስቦ ነው።

በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት በዕድሜ የተከፋፈለ በመሆኑ ከላይ እንደተመለከትነው ሲገባውን የመቁረጥም ሆነ የተሻሻለውን ውሳኔ እንዲያስፈጽሙ መብት የሰጠው ለፎሌዎች ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በገዳ ሥርዓት በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት የሚያከናውኑት ተግባራት ስለሚመለከታቸው ነው። ይህንኑ አስመልክቶ ከጽሑፍ የተገኘ መረጃ በገዳ ሥርዓት Foollee (Gaammee Gurguddoo) የፎሌ ጋሜ ጉርጉዶ ዕድሜ ክልል ከ16-24 መሆኑን ይጠቅስና እዚህ የዕድሜ ክልል ውሰጥ መግባታቸውን የሚገልጹት ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ክብረ በዓል ላይ ነው። በዚህ ክብረ በዓል ላይ ራሳቸውን ከማህበረሰቡም ጋር የሚያስተዋውቁ በዘፈን ነው። ፎሌዎች በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ እስፖርትን፣ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና መንፈሳዊ ተግባራትን እንደሚለማመዱና ንቁ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ Almaayoo Hayilee (1999፡ 65)፣ ታቦር ዋሚ (2006፡ 232) እና Hayiluu Giraany (2015፡ 23) ይገልጻሉ።

ከጽሑፍ የተገኙት መረጃዎች የሚያሳዩት የገዳ ሥርዓት በዕድሜ የተከፋፈለ መሆኑንና በዚህ ውስጥ ፎሌዎች ከሥርዓቱ የተሰጣቸው ሃላፊነት እና የሚያከናውኑት ተግባራት እንዳላቸው ነው። ከመረጃ አቀባዮች የተገኙትን መረጃዎች ስንመለከት በማህበረሰቡ ውስጥ ለሲገባ የተሰጠው ማህበራዊ ቦታ ዝቅተኛና የተናቀ መሆኑን እና ይህንንም ፎሌዎች በዘፈን እንደምገልጹት ነው። ይህም የሚያሳየው ባሏ ከሞተባት ሴት ጋር በቀድሞ ባሏ አልጋ ላይ ወሲብን መፈጸም በባህሉ የተወገዘ ተግባር መሆኑን ነው። ይህንን ውግዘት በማስተላለፍ በኩል ሥነቃል የጎላ ሚና እንዳለው ያሳያል። ስለዚህ ሰዎች በእንደዚህ ዓይነት ወሲባዊ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ማህበረሰቡ የሚከላከለው በሥነቃል አማካይነት መሆኑን ያመለክታል።

በመሆኑም ሥነቃል ከማህበረሰቡ ባህል የሚያፈነግጡትን በማረም እና በማስተካከከል አስጠንቅቆ የማስተማር ተግባር አለው። ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ውስጥ ሲገባን አስመልክቶ የተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶችን ሲገባ በሚል ርዕስ ሥር ተመድበው አባሪ የተደረጉ ሲሆን የተመረጡት ተተንትነዋል። ከዚህ ቀጥሎ እሬን አስመልክቶ የተገኙትን መረጃዎች እናያለን።

ፎቶ ግራፍ 14. የቱለማ ፎሌዎች በሆራ አርሰዲ እሬቻ ክብረ በዓል ላይ (መስከረም 23ቀን 2008ዓ.ም)

5. እሬን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

እሬ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና አፈጻጸሙን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ከተሳተፉት መረጃ አቀባዮች የተገኙት መረጃዎች ተጠቃለው ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በቱለማ ኦሮሞ ባህል መሠረት Irree Bulfachu (እሬ ማሳደር) ወይም Bira Ejjeta (በጋብቻ ወቅት ከሙሽራው አጠገብ መቆም) ማለት ነው። ይህም የአግቢው Dubrii (አኅት ልጅ) ከሠርጉ ጥሪ ማስተላለፍ ጀምሮ በሠርጉ ሥነ-ሥርዓት ላይ ከሙሽራው ጎን በመቆም በሠረጉ ወቅት ያለውን ልዩ ልዩ ሥነ-ሥርዓት የሚያከናውን ነው። ከዚሁ አንጻር ከሙሾራው ጋር ሆኖ እርጥብ ሣር ይዞ ሽማግሌና የልጅቷን ዘመዶች ጉልበት ይስማል። ሙሽራው በሠርጉ እለት ማከናወን የሚገባውን ሁሉ ተክቶ ያከናውናል። ሚዜን በበላይነት ይቆጣጠራል። የሠርጉ እለት ማታ በግ አርዶ እድምተኞችን ይጋብዛል። በአጠቃላይ

የሠርጉን ሥነ-ሥርዓት በበላይነት በመምራት ሁኔታዎችን ያመቻቻል (ገመቹ ዳዲ፣ ጥቅምት 15 ቀን 2007 ዓ.ም.)።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ስለ እሬ ምንነት ለቀረበለት ጥያቄ በባህሉ ውስጥ ተሳታፊ የነበረ መረጃ አቀባይ እንዲህ በማለት ገልጿል።

> Irree bulfachuu jechuun dargagganii ilmaanii wasilanii yookiin durbii walii ta'an fuudhaa fi heeruma ilaalchisuun guyyaa gaayelaas ta'ee gaayilaan booda dhimma fuudhaaf heerumaa irratti walcinaa dhaabbacuun sirna niitii ittiin fudhaniidha. … Akkaataa aadaa kanatti Irreen akka abbaa warraa lamaffaatti laalama. Guddisaa Addunyaa (Amajjii 11, bara 2007 A.L.I.).

በአማርኛ ትርጉም

> እሬ ማሳደር ማለት በወጣትነት የእድሜ ክልል የሚገኝ የአጎት ልጅ ለሌላኛው የአጎቱ ልጅ በሠርጉ ቀን እና ከሠርጉ በኋላ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አብሮ በመሆን ጋብቻ የሚፈጸምበት ሥርዓት ነው። … በዚህ ባህል መሠረት እሬ እንደ ሁለተኛ ባል ይታያል። ጉዲሳ አዱኛ (ጥር 11፣ 2007)።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን በማጠናከር የእሬን ተግባር የዘረዘረ መረጃ አቀባይ ደግሞ ስለ እሬ እንዲህ ይገልጻል። የእሬ ሌላ ስሙ ዋርሳ ሲሆን በሠርጉ ሂደት የባሏ ተወካይ ነው። በድሮ ጊዜ በጋብቻ ሥርዓት ውስጥ እሬ ትልቅ ቦታ አለው። በሌላ መልኩ እሬ (ዋርሳ) በፍቅር ግንኙነት ውስጥ እንደ ሁለተኛ ባል ይታያል። ይህም ባሏ በማይኖርበት ጊዜ በድብቅ ወሲብ ይፈጽማል። እሷም ዋርሰዋን ስለምትወድ ባሏ በሥራ ምክንያት በአከባቢው ከሌለ በድብቅ እየተገናኘች ወሲባዊ ፍላጎቷን ታጣጥማለች። እነዚህ ተግባራት በአብዛኛው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሚከወኑ ባህላዊ ዲርጊቶች ናቸው (መረጃ አቀባይ አቶ ሙሉጌታ አያኔ ህዳር 27 ቀን 2007)።

እሬ በማሳደር ከሚመሠረት ጋብቻ ጋር ተያይዞ ይፈጸማል ስለተባለው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ጉዳይ እንዲያስረዱ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው አባላት መካካል ስማቸው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት በእሬ ሥርዓት ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ በፈጸሙት የግብረ-ስጋ ግንኙነት የተነሳ የገጠማቸውን ችግር እንደሚከተለው ተርከዋል።

በመጀመሪያ ቃለ መጠይቅ የተደረገለት እድሜው 29 የሆነ ወጣት የአጎቱን ልጅ እሬ እንዲሆንለት አድርጎ ጋብቻውን ይፈጽማል። እሱም እንደዚሁ የአጎቱ ልጅ በሚያገባበት ወቅት እሬ ሆኖለት ነበር። ከጋብቻ በኋላ ሁለቱም እሬ ከሆኑላቸው ሴቶች ጋር በድብቅ

የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ይጀምራሉ። ተራኪው እንደምናገረው ከሆነ ለባህሉ ያህል አንዱ ከአንዱ ይደበቃል እንጂ ጉዳዩን ሁለቱም እንድደምፈጽሙ ይታዋወቃሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የአንደኛው ሚስት ታረግዝና ትወልዳለች። የተወለደው ልጅ ባልየውን ሳይሆን እሬውን መሠለ። በእሬውና በልጁ መልክ መመሳሰል የተነሳ ዘመዶቹ እና ጎረቤቶቹ ልጁን በእሬው ስም መጥራት ይጀምራሉ። ሕፃኑም ልጅ እያደገ ሲሄድ መልኩ ቁልጭ እሬውን ሆነ። በዚህ የተነሳ ባለታሪኩ የተወለደውን ልጅ መጥላትና ሚስቱን መደብደብ ይጀምራል። አንዳንዴ ሕጻኑ አባቴ ብሎ ሲጠጋው ልጁን ከመጥላቱ የተነሳ ይደበድበዋል። እሬ ከሆነለት የአጎቱ ልጅ ጋር እንዳይጣላ፣ አንደኛ ባህሉ ከእሬ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸምን ይፈቅዳል፣ ሁለተኛ እሱም ቢሆን እሬ ከሆነለት የአጎቱ ልጅ ሚስት ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሲፈጽም ቆይቷል። ከእሷም የተወለደው ሕጻን አባቱን እንጂ እሬውን አይመስልም። በድርጊቱ ተሳታፊ በመሆኑ የእሬን ተግባር የሚያውቅ ቢሆንም ባህሉ የፈጠረበትን ችግር አእምሮው መቀበል ባለመቻሉ አከባቢውን ለቆ በመሄድ ሌላ ሚስት አገባ። በዚህ የተነሳ የእሬ ባህል ባመጣበት ጣጣ ከሚወዳት ሚስቱ መለየቱን የገለጸው በመቆጨት ነበር (ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም.)።

ተመሳሳይ ጥያቄ የቀረበላት ሌላኛዋ መረጃ አቀባይ ባለታሪክ ጋብቻዋን በእሬ ሥርዓት የፈጸመች ስትሆን ቃለ መጠይቁ በተደረገበት ወቅት ዕድሜዋ 24 ዓመት ነው። ስሟ በዚህ ጽሑፍ ላይ እንዳይጠቀስ በማሳሰብ ጋብቻዋን በእሬ ባህላዊ ሥርዓት በመፈጸሟ የደረሰባትን ከፍተኛ ችግር የተረከችው እንደሚከተለው ነበር።

ይህች ወጣት ልጅ ጋብቻዋን የፈጸመችው የ8ኛ ክፍል ተማሪ ሆና በ16 ዓመቷ ነበር። ስታገባ በአከባቢው ባህል መሠረት በእሬ ሥርዓት አስፈላጊው ሁሉ ተሟልቶ እንዳገባችና ለባሏ ሁለት ልጆች መውላዷን ገልጻለች። የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት በለቤቷ በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ አከባቢ መሄዱንና በዚህን ወቅት የባሏም አለመኖር የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሮላት ቀደም ሲል ከእሬዋ ጋር በድብቅ ስትፈጽም የነበረውን የግብረሥጋ ግንኙነት አጠናክራ ቀጠለች። በዚህ ሂደት ከእሬዋ አረገዘች።

ባሏም ለሥራ ሄዶ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ሲመለስ ሚስት አርግዛ በመጠበቋ ይናደድና እንዴት እንዲህ ታደርጊያለሽ ብሎ በቁጣ ይጠያቃታል። በዚህን ጊዜ እሷም እንዲህ አለች። “Maalii garuu seera Irreetiin silaa dhirsa dabalataa jettaniiti na futanni mitiree?

maal rakkina qaba? Jedheen. Ani garuu homaa waan tokkollee hin beeku ture." ሲተረጎም "ምነው መቼም በእሬ ሥርዓት ተጨማሪ ባል ብላችሁ የለም እንዴ? ምን ችግር አለው አልኩት። እኔ መቼም ምንም ነገር አላውቅም ነበር።" ከዚያ እሱም ከቤቱ ወጥቶ እዚያው ቅርብ ወደሚገኘው እናቱ ቤት እንደ ሄደና እዚያም እናቱም ጉዳዩን ቀለል አድረገው ምንም ችግር እንደሌለውና በባህሉ እንደሚፈቀድ ብትነግረውም፣ እሱም ባህሉን የሚያውቅ ቢሆንም አእምሮው ባለመቀበሉ ወደ ቤቱ ሳይመለስ ቀደም ሲል ለእሱ የወለደቻቸውን ልጆቹን እንኳን ሳይጠይቅ ትቷት ወደ መጣባት ቦታ ይመለሳል።

በዚህን ጊዜ ያለውን ችግር ለእሬዋ ትናገራለች። እሬዋም ምንም ችግር እንደሌለና እንደሚረዳት ይነግራታል። እርግዝናው እየገፋ ሲመጣ በፊት ምንም ችግር የለም ይል የነበረ ሰው እሷ ወዳለችበት ቦታ ብቅ ማለት ተወ። ከወለደችም በኋላ ሳይጠይቃት ቀረ። ሰው ብትልክበትም አላውቃትም በማለት ሁለተኛ ስሙን እንዳታነሳ በላከችው ሰው በኩል ያስጠነቅቃታል። ባል ቀድሞውኑ ጥሏት ሄዷል። የባሏም ቤተሰቦች ጣል ጣል አደረጓት። እሬዋም አትድረሽብኝ አላት። ወደ ቤተሰቦቿም እንዳትመለስ፣ እነሱ አንዴ ድረዋታልና እንድትመጣበቸው አይፈልጉም። ሁኔታው ሁሉ ግራ ግብት አላት። በዚህ ጊዜ አማራጭ ብላ በወሰነችው መሠረት ቤቷን ጥላ ሦስት ልጆቿን ይዛ ወደ ከተማ ገባች።

እዚያም ጠላና አረቂ እየነገደች ሳለ ወደ መጠጥ ቤቷ ይመላለስ የነበረ ሽመግል ያለ ሰው በፍቅር ይይዛትና እንደ ውሽማ ያስቀምጣታል። በዚህ ሂደት አራተኛ ልጅ ታረግዛለች። ይህን ሲያውቅ ውሽማዋ እየራቃት ሄደ። ይህ የሆነበት ምክንያት ውሽማ ምግብ ይፈልጋልና እሷ ደግሞ ውሽማ ማብላት ቀርቶ ለራሷም የሚላስ የሚቀመስ የሌላት በመሆኑ ውሽሚው ስላረገዘች እና ለሆዱም ስላልተመቸው ተዋት። ችግሩ በጣም ተደራረበባት። በተለይም አራተኛ ልጇን ከወለደች በኋላ ችግሩ እጅግ በጣም ጠንክሮባት እሷም በመታመሚ እስከ መለመን እንደ ደረሰች ስትገልጽ አንጀት በሚበላ አነጋገር ነበር።

የሕመሙዋ ጉዳይ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በፈጸመችው የግብረሥጋ ግንኙነት የተነሳ በኤች አይ ቪ መያዟን ተጠራጥራ ባደረገችው የደም ምርመራ በእርግጥም በቫይረሱ መያዟን አወቀች። ቃለ-መጠይቅ በተደረገበት ወቅት በአንድ ግብረሰናይ ድርጅት እየተረዳች ነበር። በመጨረሻም በእሬ ጋብቻ መመሥረትን አስመልክታ የሰጠችው አስተያየት በዚህ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ለመግባት የቻለችው እሬ ባመጣባት ጣጣ መሆኑን

በማስታወስ እንዲህ ዓይነቱ ባህላዊ ተግባር በአሁኑ ዘመን እንደማያስፈግ ገልጻለች (ጥር 15፣ 2007 ዓ.ም)።

እሬን አስመልክቶ ከመረጃ አቀባዮቹ ከተገኙት መረጃዎች እንደተገነዘብነው በትዳር ውስጥ የሚከናወነው ድብቅ የፍቅር ግንኙነት ለትዳር መፍረስና ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት መስፋፋት ምክንያት መሆኑን ነው። በመሆኑም በዚህ ባህላዊ ጉዳይ ዙሪያ ራሱን የቻለ ሰፊ ጥናት ተደርጎ መፍትሔ የሚያስፈልገው መሆኑን ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ እሬን አስመልክተው የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶችም አሉ። እነሱም በምደባ የተካተቱ ሲሆኑ ከእነዚህም የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት ውስጥ በርዕሰ ጉዳዩ ሥር ተተንትነዋል።

ከዚህ በመቀጠል እስካሁን ትርጉማቸውን እና አፈጻጸማቸውን በዝርዝር የተመለከትናቸውን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች አስመልክተው የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶችን ከዚህ እንደሚከተለው እናያለን።

6. ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ ፣ ሲገባ እና እሬን አስመልክተው የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች የትኞቹ እንደሆኑ እንዲናገሩ የቀረበ ጥያቄን በሚመለከት

ይህንን ጥያቄ አስመልክቶ በቃለ-መጠይቁ ከተሳተፉ መረጃ አቀባዮች የተገኘው ምላሽ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ ተረቶች፣ ቀልዶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች መኖራቸውን ገልጸዋል። ከእነዚህ ውስጥ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ወይም እንዲዘፍኑ በተጠየቁት መሠረት አንዳንድ መረጃ አቀባዮች[64] የተወሰኑትን ተረቶች፣ ቀልዶች እና ምሳሌያዊ ንግግሮች በቃላቸው በመናገር እንዲሁም ዘፈኑን እንቅስቃሴ ጭምር በክዋኔ አሳይተዋል። ከእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች በየሚመለከታቸው ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ርዕስ ሥር ተመድበዋል። በአባሪነትም ተይዘዋል። ከተመደቡት መካከል የተመረጡት በምዕራፍ ስድስት ውስጥ ተተንትነዋል።

[64] (አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ አቶ ተስፋዬ ሁንዴ፣ አቶ ሙሉጌታ አያኔ፣ አቶ በጅጋ ሮሪሳ፣ ወጣት ኢርኮ ፈይሳ፣ ወጣት ደሜ ማሩ፣ ወጣት ተስፋዬ ቶላ፣ አቶ ቶላ ለማ፣ ወሮ ቦንቱ በዳኔ፣ አቶ አሰፋ ግርማ፣ አቶ ዲሪባ ደምሴ፣ አቶ ዓለሙ ፈይሳ፣ አቶ ደሱ መገርሳ (አዝማሪ)፣ አቶ ቢቂላ አቦ፣ አቶ ብርሐኑ ረጋሳ፣ አቶ ሲሳይ ማሰሪያ፣ አቶ ብርሐኑ ዓለሙ እና አቶ ደረጀ ቶሌራ፣ ከጥር 2006 እስከ ኅዳር 2008 ዓ.ም.)።

7. ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዞ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክተው የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶችን አስመልክቶ የቀረበ ጥያቄን በሚመለከት

ይህን ጥያቄ በሚመለከት የተገኙት መልሶች በጥቅሉ ሲታዩ በቀጥታ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ በርከታ ዘፈኖች ተሰብስበዋል። ከዘፈኖቹ ውስጥ የሚያውቁትን እንዲዘፍኑ ወይም ግጥሙን እንዲናገሩ በተጠየቁት መሠረት የተወሰኑት መረጃ አቀባዮች[65] አንዳንድ ዘፈኖችን ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በመዝፈን እንዲሁም የዘፈኖቹን ግጥም በመናገር መልስ ሰጥተዋል። በዚህ ዘዴ የተገኙ ዘፈኖች በየሚመለከታቸው ርዕስ ሥር የተመደቡ ሲሆን የተመረጡት በምዕራፍ ሰባት ውስጥ እንደየሚያተኩሩበት ይዘት ተተንትነዋል።

ምሳሌያዊ ንግግሮችን በሚመለከት በቀጥታ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ላይ የተነገሩ ጥቂት ሲሆኑ በኢ-ውስን ቃለ መጠይቅ ለተነሱ ጥያቄዎች ቀደምሲል በማህበረሰቡ ውስጥ ለሌላ ማህበራዊ ጉዳዮች ይነገሩ የነበሩትን አውዳዊ በማድረግ የተሰጡ መልሶች ናቸው። ከዚሁ አንጻር በቀጥታ ስለ ቫይረሱ የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች ባይኖሩም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ በተደረገው ውይይት ውስጥ ቀደም ሲል ለሌሎች ማህበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የተነገሩትን አውዳዊ በማድረግ ገልጸዋል።

በመሆኑም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክተው ሰዎች ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ ምክር ለመስጠት እና ምክሩን ወደ ጎን በመተው ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሚያጋልጥ መስመር ውስጥ የገቡትን ወይም ዳር ዳር የሚሉትን ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ለማስጠንቀቅ እንደሚጠቀሙበት አብራርተዋል። ከዚህ መልሳቸው በመነሳት ይህንን የሥነቃል ዓይነት በተመለከተ በቃለ መጠይቁ ወቅት በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ አንዳንድ የመወያያ ጥያቄዎች ተነስተው አውዳዊ በሆነ ሁኔታ በርካታ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተሰብስበዋል።

ለምሳሌ ያህል በአሁኑ ወቅት ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እየቀነሰ ስለሆነ ለምን ስለ ቫረሱ ይዘፈናል? ለሚል ጥያቄ ከቃለ-መጠይቁ ተሳታፊዎች ከተሰጡ መልሶች ይሚከተሉት ይገኙበታል። እነሱም "Ibiddi dibame hin dhaamu"ተረጎም "የተደፋነ እሳት

[65] (አቶ ጣሰው በየነ፣ አቶ በልዳ አቦዬ፣ አቶ ፈተኑ ዳመሳ፣ ወ/ሮ ደብሪቱ ገረሱ፣ ወ/ሮ አረጋሽ ደበሌ፣ አቶ ደረጀ ሹሚ (አዝማሪ)፣ አቶ ደረጀ በቀለ፣ ወጣት ቶሎሳ መርጋ፣ ወጣት ግርማ አበራ፣ ወጣት ዲሪባ አራርሶ፣ አቶ አለሙ ጉተማ፣ አቶ ገመቹ ዳዲ፣ አቶ ታደሠ ለማ፣ አቶ ዳባ ማረሚ፣ ወጣት ዋቄ በዳኔ፣ አቶ አሰፋ ዳርጌ፣ አቶ ታደሠ ቶላ እና ወ/ሮ ጫልቱ ንጉሴ)።

አይጠፋም።" "Bokkisaan gaafa callise rakkisa" ሲተረጎም "የሚቆጣ ዝም ያለ ለት ችግር ይሆናል።" የመሳሰሉት ናቸው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሳት የተሰበሰቡት ምሳሌያዊ ንግግሮች በምዳባው ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተመረጡት በምዕራፍ ሰባት ውስጥ በሚመለከታቸው ርዕስ ሥር ተተንትነዋል።

ከዚህ ቀጥለሎ የተተሻለ እውቀት የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አስመልክቶ በተለይ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት እና የማህበረቡን የግንዛቤ ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የጤና ባለሙያ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ እንደሚከተለው እናያለን።

8. በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ የሚከወኑ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት ጋር ተያይዞ እንዴት ይታያል? ማህበረሰቡ ስለ ቫይረሱ ግንዛቤ አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ለጤና በለሙያ ቀርቦ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው የቀረበው ነው።

በሱሉልታ ወረዳ የሚከወኑ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ እሬ እና ሲገባ መሆናቸውን ገልጸዋል። በእነዚህ ባህላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በተለይም የእሬን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ጋር በማያያዝ ባለሙያው እንደሚከተለው አብራርቷል።

> Aadaan saalaa Aanaa keenya keechati muldhatan Irree, Wadaajii, Sanyoo fi Sigabaa fa'a. Kuni akkamitti raawwataman jennee yemmuu laallu, keessumaawuu Irreen kan raawwatamu sirna fuudhaa fi heerumaa keechatti ilmaan wasiilaniititu Irree wal kadhatu. Irreen namoota firooma dhiigaa qaban jiddutti kan raawwatamuudha. Irree jechuun dhirsa lamataati. Aadaan kuni abooti, akaakilee fi abaabilee irraa kan dhufe. Dhaloonni hardhaa kunis itti fayyadamaa jira. Irreen hardhas jira. Gaheen Irree kanaa bakka dhirsi hin jirreetti akka dhirsaa ta'ee kan ishii bulchuudha.
>
> Yaa ta'u malee, fuudhaa fi heeruma keechatti tokkof tokko ta'aa; yoo ta'uu baate kondomiin fayyadamaa jennee uummata barsiisaa jirra. Yaa ta'u malee toora irree kanarratti tokkoof tokko ta'uu hin danda'amne. Ishiinis hin diddu innis Irree waan ta'eef gocha saalqunnamtii raawwachurraa duubatti hin deebi'u. Irree kan walii ta'an kuni umuriin isaanii kan walitti hiiqaniidha. Umuriin isaanii waggaa 20 hanga 30 kan ta'aniidha. Umuriin kuni immoo fedhii saalqunnamtii raawwachuuf qaamni isaanii oo'aa waan ta'eef iddoo abbaan warra hin jirreetti eeggatanii qunnamtii saalaa raawwatu.
>
> Haalli kuni immoo tamsa'ina Eechi Ayi Vii/Eedsiif isaan saaxiluu danda'a. rakkoo kana ittisuuf hawaasa abbaa aadichaa ta'e mari'achiisuun **balaa** jiru

itti ibsuudha. Kanas gara waajjira eegumsa fayyaa aanichaatiin raawwachaa jirra. Haaluma walfakaatuun aadaan Wadaajii dhungoo, Sanyoo techifachuu fi Sigabaan galuu tamsa'ina Eechi Ayi Vii/ Eedsiif karaa banaa akka jiru hawaasicha hubachiisaa jirra. Obboo Magraa Raagoo (Amajjii 11, bara 2006).

የአማርኛ ትርጉም

በወረዳችን ውስጥ የሚከወኑ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እሬ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ እና ሲገባ ናቸው። እነዚህ እንዴት እንደሚከወኑ ስናይ በተለይ እሬ በጋብቻ ሥርዓት ውስጥ የአጎት ልጆች አንዱ ለአንዱ እሬ በመሆን የሚፈጸም ነው። እሬ በወንዶች በኩል የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ነው። እሬ ማለት ለሴቷ እንደ ሁለተኛ ባል የሚታይ ነው። ይህ ባህል ከአባቶች፣አያቶች እና ቅድመ-አያቶች የመጣ ነው። የአሁኑም ትውልድ ተግባራዊ እያደረገ ነው። እሬ ዛሬም አለ። የእሬ የሥራ ድርሻ ባለቤቷ በሌለበት እንደ ባል ሆኖ ማስተዳደር ነው።

ይህን በተመለከተ በጋብቻ ውስጥ አንድ ለአንድ ሁኑ፤ ካልሆነ ኮንዶም ተጠቀሙ እያልን ሕዝቡን እያስተማርን ነው። ይሁን እንጂ በዚህ በእሬ ዙሪያ አንድ ለአንድ መሆን አልተቻለም። እሷም እምቢ አትልም፣ እሱም እሬ በመሆኑ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከማድረግ ወደ ኋላ አይመለስም። እነዚህ እርስ በርሳቸው እሬ የሚሆኑት ተመሳሳይ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ናቸው። እድሜያቸውም ከ20 እስከ 30 የሚሆኑ ወጣቶች ናቸው። በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙት ደግሞ በወሲባዊ ፍላጎት ፈጣን በመሆናቸው ባለቤቱ በሌለበት (ተደብቆ) የግብረ-ስጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ።

ይህ ደግሞ ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ስርጭት ሊያጋልጣቸው ይችላል። ይህንን ችግር ለመግታት የባህሉ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ በማወያየት ያለውን አደጋ መግለጽ ነው። ይህንንም በወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በኩል እያከናወንን እንገኛለን። በተመሳሳይ ሁኔታ የከንፈር ወዳጅነት፣ ውሽማ ማስቀመጥ እና ሲገባ መግባት ባህል ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት በር እንደሚከፍት ማህበረሰቡን እያስገነዘብን ነው። አቶ መግራ ራጎ (ጥር 11 ቀን፣ 2006 ዓ.ም.)።

ይህ የሚያሳየን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶቹ በወሲብ አማካይነት ለሚፈጠሩ በሽታዎች በተለይም ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት ሚናቸው የጎላ መሆኑን ነው። የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን በማወቁ ረገድ የማህበረሰቡ ግንዛቤ ከሞላ ጎደል ጥሩ ነው የሚባል ቢሆንም ባህላቸውን መሠረት በማድረግ ማስተማሩ አሁንም መሠራት ያለባቸው ተግባራት እንዳሉ ያስገነዝበናል። የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ በተለይ ከሥነቃል የማስተማር ተግባር አኳያ የተመረጡ የሥነቃል ዓይነቶች ትንተናን መሠረት በማድረግ በየሚመለከታቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሥር በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ በሰፊው ተብራርተዋል። በመቀጠል በቡድን ተኮር ውይይት ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

5.4 ቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ መረጃዎች

በመጠይቅ እና በቃለ-መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ እና አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የጠለቀ ግንዛቤ ለማግኘት ቡድን ተኮር ውይይት ተደርጓል። በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ውስጥ ተሳታፊዎቹ 33ሰዎች (22 ወንዶች እና 11 ሴቶች ናቸው። የቡድን ውይይቱ 5(አምስት) ጊዜ የተደረገ ሲሆን በአንድ ቡድን ውስጥ ከ5 እስከ 7 አባላት የሚገኙበት ለወንዶች ለብቻ ሁለት ጊዜያት፣ ለሴቶች ለብቻ ሁለት ጊዜያት እና ለወንዶች እና ለሴቶች በጋራ አንድ ጊዜ ውይይቶቹ ተካሂደዋል። በዚሁ መሠረት ለቀረቡ ጥያቄዎች የውይይቱ ተሳታፊዎች የሠጡት ምላሽ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች (ጋብቻ፣ የከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ) አፈጻጸማቸው በድሮ ጊዜ እና በአሁኑ ዘመን ያለው እንዴት ይገለጻል? በሚል ዋና መንደሪደሪያ ጥያቄ ዙሪያ የተሰጡ መልሶች።

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለቀረበው የመነሻ ጥያቄ በተለያዩ ጊዜያት በተካሔደው ውይይት ላይ የተሳተፉ አባላት ስለ ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ አፈጻጸም በድሮ እና በአሁኑ ዘመን ያለውን ልዩነቶች በሚመለከት የሰጡት ሀሳቦች ተጠቃለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የጋብቻን አፈጻጸም በሚመለከት በድሮ ጊዜ Qaadhimannaa (እጮኛ በመያዝ)፣ Butii (ጠለፋ)፣Irradhaaba (ድንገት ፈረስ ደጅ በማቆም)፣ Aseennaa (ሴቷ በወደደችው ወንድ ቤት ገብታ ምሰሶ መያዝ) እና Dhaala (በውርስ) የመሳሰሉ የጋብቻ ዓይነቶች መኖራቸውን ቀደም ሲል በቃለ- መጠይቅ የተገኙ መልሶች በዚህ የቡድን ውይይት ላይም ተገልጸዋል። እነዚህ የጋብቻ ዓይነቶች እያንዳንዳቸው የሚከናወኑበት ሥርዓቶች እንዳለቸውም አብራርተዋል። ከእነዚህ የጋብቻ ዓይነቶች ውስጥ የአንዳንዶቹ አፈጻጸም ከሰው ልጅ መብት አንጻር ታይተው በአሁኑ ዘመን የቀሩ መሆናቸውን ገልጸዋል። ለምሳሌ ጠለፋ ሴቷ ሳትፈልግ በግድ የሚከናወን በመሆኑ ተግባሩ በወንጀልም የሚያስጠይቅ ስለሆነ ይህ ሁኔታ በአብዛኛው መቅረቱን አስረድተዋል። በዚህ ምትክ ሴቷ በፍቃደኝነት ከወንዱ ጋር አብራ ከገባች በኋላ ሽማግሌዎች ወደ ቤተሰቦቿ እንደሚላኩና እርቅ እንደሚደረግ ገልጸዋል። ድንገት ፈረስ ደጅ በማቆም እና ሴቷ በወደደችው ወንድ ቤት ገብታ ምሰሶ በመያዝ የሚፈጸምም ጋብቻ በአሁኑ ዘመን አለ ለማለት የሚያስደፍር አለመሆኑን

በመግለጽ የውርስ ጋብቻም ቢሆን አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አለመኖሩን የውይይት ቡድኑ ተሳታፊዎች አቶ ተስፋዬ ሁንዴ፣ አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ ወ/ሮ ደሜ ቱሉ፣ አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ሙሉጌታ አያኔ፣ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ እና ጠጁቱ ቂጠታ (ኅዳር 28 ቀን 2007ዓ.ም) አብራርተዋል።

የከንፈር ወዳጅ አፈጻጸምን በሚመለከት ቀደም ሲል በቃለ-መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ወቅት እንደተጠቀሰው "በአሁኑ ዘመን ከንፈር ወዳጅነት ከላይም ከታችም ሆነዋል እና ባህሉን የተከተለ አይደለም።" በማለት ከሽማግሌዎች የተሰጠውን የቅሬታ ሀሳብ ከወጣቶቹ አስተያየት ለመቀበል ቡድን ተኮር ውይይት ተደርጓል። በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉበት አባላት የተገኘው ሀሳብ ተጠቃሎ ሲቀርብ ቀደም ሲል ከሽማግሌዎች ጋር በቃለ-መጠይቅ ከተሰጠው አስተያየት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይህንንም ከቡድኑ አባላት አንድ ወጣት እንዲህ ሲል ገልጿል።

> Ani akka yaada kootitti yeroo waldhungannu san qaama koo homaa to'achuu hin danda'u. Fedhii yeroo gabaabaa san guuttachuufan xaara jechuudha. Kanaafuu rakkoo addaa addaa keecha galuun danda'a. ulfa itti hin yaadamne uumuu yookiin dhibee addaa addaa saalqunnamtii dhaan daddarbaniif saaxilamuu dandeenya. Keechuumaawuu dhibee hanga yoonaatti qoricha hin argatin Eechi Ayi Vii/ Eedsii dhaan qabamuu dandeenyaa Abbabaa Nagaash (Amajjii 23, bara 2007 A.L I.).

የአማርኛ ትርጉም

> እኔ በበኩሌ ከከንፈር ወዳጄ ጋር በምንሳሳምበት ወቅት ራሴን መቆጣጣር አልችልም። ጥረት የማደርገው የአጭር ጊዜ ፍላጎቴን ለማሟላት ነው ። ስለዚህ የተለያዩ ችግሮች ውስጥ ልገባ እችላለሁ። ያልተፈለገ እርግዝና መፍጠር ወይም በግብረ-ስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ ልዩ ልዩ በሽታዎች ልጋለጥ እችላለሁ። በተለይም እስካሁን መድኃኒት ላልተገኘለት በሽታ በኤች አይ ቪ/ ኤድስ የመያዝ አጋጣሚ ሁሉ ይኖራል አበበ ነጋሽ (ጥር 23፣ 2007 ዓ. ም.)።

የውይይቱ ተሳታፊዎችም በአበበ ነጋሽ የቀረበውን ሀሳብ እንደሚስማሙበት ገልጸው፣ በሚሳሳሙበት ወቅት በጣም ተጠጋግቶ እና እየተሻሹ ከንፈር ለከንፈር የሚማጠጡ መሆናቸውንና በዚህ ጊዜ ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲብ እንደሚጋለጡ ገልጸዋል። ይህም

ላልተፈለገ እርግዝና እና ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ እንደሆነ የውይይቱ ተሳታፊዎች[66] ጠቁመዋል።

ከዚህ የምንረዳው ቀደም ሲል መረጃ አቀባዮቹ "በአሁኑ ዘመን የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል፣" በማለት የሰጡት አስተያየት ትክክል መሆኑንና የዘመኑ ወጣቶቹ ባህልን አክብሮ በመሳሳም ብቻ ሳያበቁ በባህሉ **ነውር** ወደ ሆነው ወሲብም እንደሚሸጋገሩ ያመለክታል። ይህ ደግሞ ወጣቶችን የበለጠ ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ያጋልጣቸዋል። ለቫይረሱም መስፋፋት የጎላ አስተዋጽኦ አለው።

ውሽማን አስመልክተው ከውይይቱ የተገኘው ሀሳብ ይህ ባህል እንዳሁኑ የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሽታ ባልተስፋፋበት ዘመን ጥሩ የፍቅር መገለጫና ልዩ ልዩ ጥቅሞችንም ያስገኝ ነበር። ይኸውም ባል ከሚስት የማያገኘውን የስሜት አለመጣጣም ከውሽማ ያገኛል። ሚስቱ መሐን ለሆነች ወንድ ልጅ እንዲያገኝ ያግዘዋል። ሚስትም እንዲሁ ከባሏ የማታገኘውን የፍቅር መጣጣም ከውሽማ ታገኛለች። በአሁኑ ዘመን ግን እንዲህ ዓይነቱ የፍቅር ግንኙነቶች እየቀሩ ናቸው። ምክንያቱም 'አጅሬው' ኤች ኣይ ቪ እንዴ ከያዘ ስለማይለቅ አብዛኛው ሰው ይፈራል። በተሞክሮ እንዳየነው ይህንን ባህል የሚያዘወትሩ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። አንዳንዶቹም የዘለዓለም በሽታ እያስተመሙ የአልጋ ቁራኛ መሆናቸውን በውይይቱ የተሳተፉ[67] መረጃ አቀበዮች ገልጸዋል። ከዚህ የምንረዳው የውሽምነት ባህል በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ፍራቻ እየቀረ መሄዱን ነው።

ሲገባን በሚመለከት በተደረገው ውይይት ባህሉ በድሮ ጊዜ በስፋት የሚከናወን ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እየቀረ መጥቷል። ለመቅረቱም አንዱ ምክንያት ባሏ የሞተባት ሴት በባሏ ቤት ከመቆየት ይልቅ ሌላ ቦታ ሄዳ ታገባለች። ከቀድሞ ባሏ የተወለዱ ልጆች ካሏትም ልጆቿን ይዛ ወይም ባሏ ዘመዶች ዘንድ ትታ ስለምታገባ በአሁኑ ዘመን የሲገባ የለም ለማለት ያስደፍራል። ይሁን እንጂ በዘፈን አልፎ አልፎ ስም ሳይጠራ በደፈናው ሲገባን ይሰድባሉ። እንደ ድሮ የሲገባን ስም ጠርተው መሳደብ ግን የለም። ምክንያቱም ተሰዳቢው ሲገባ ወይም ሲገባ ያስገባችው ሴት መብቴ ተነክቷል በማለት ፍርድ ቤት ልትከስ

[66] (ወጣት ቶሎሳ መርጋ፣ ወጣት መንግስቱ አበራ፣ ወጣት ዲሪባ አራርሶ፣ አበበ ነጋሽ፣ ተማሪ ብልሴ ያዴቻ፣ ተማሪ ቀነኒሳ እና ተማሪ ሽቶ ተስፋዬ፣ 23/05/2007 ዓ.ም)።

[67] አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ፈይሳ ዲባባ፣ አቶ አበበ ጀቤሳ፣ አቶ ጣሰው በየነ፣ ወ/ሮ ደብሪቱ ሞረዳ፣ ሊና በየነ እና ወ/ሮ አየለች ሂና (መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም)።

ትችላለች በሚል ፍራቻ ነው። ባህሉን አክብረው የማይከሱ ደግሞ በየስምንት ዓመቱ በሚደረገው የፎሌ ጭፈራ ሲገባው እንዳይሰደብ አስቀድሞ ለፎሌዎች የተለያየ መጠጥ መጋበዝና በድብቅ ነጠላ ገዝቶ መስጠት ስሙን ሳይጠሩ ሲገባ የሚለውን ቃል ብቻ በመጠቀም እንዲሳደቡ ያደርጋል። ከዚህ አኳያ በአሁኑ ዘመን ባህሉ ብዙም የማይተገበር ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የኤች አይ ቪ/ኤድስን በሽታ ፍራቻ ስላለ ባሏ የሞተባት ሴት ዘንድ መሄድ በሽታ ሊኖራት ይችላል በሚል ሰበብ ባህሉ በተወሰነ መልኩ እየቀረ መምጣቱን የውይይቱ ተሳታፊዎች[68] ይገልጻሉ።

ይህ እንደ ድሮ ሲገባው ስሙ እየተጠራ አለመሰደቡ የሚያሳየን ከሰው ልጅ መብት አንጻር በሕግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ መቅረቱን ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ባህሉ እንዳይቀር ሲገባው ለፎሌዎቹ መጋበዙ እና አስቀድሞ ነጠላ ገዝቶ መስጠቱ በጉቦ መደለሉን ያመለክታል። ከዚህ አንጻር ባህሉ በቀጣይነትና ለውጥ መካካል መኖሩን እንመለከታለን። ይህንን በሚመለከት ዝርዝር ትንታኔውን በምዕራፍ ስድስት ውስጥ እንመለከታለን።

በእሬ ሥርዓት ጋብቻን መፈጸሙ የሚያስከትል ችግር መኖር አለመኖሩን አስመልክተው ለቀረበ ጥያቄ የተገኘው ምላሽ በቃለ-መጠይቅ ወቅት በእሬ ምክንያት የደረሰውን ከትዳር የመፈናቀል ትረካን መሠረት በማድረግ እሬ በማሳደር ጋብቻ መፈጸሙ አለ የተባለውን ችግር ይበልጥ ለማረጋገጥ ሲሆን በውይይቱ የተሳተፉት ባህሉን በደንብ የሚያውቁ እና አንዳንዶቹም በእሬ ሥርዓት ጋብቻ የፈጸሙ እንዲሁም እሬ ሆነው የነበሩ ናቸው።

በዚሁ መሠረት እሬ የማህበረሰቡ ባህል በመሆኑ እና ማህበረሰቡ ደግሞ ባህሉን የፈጠረበት የራሱ ምክንያት ያለው በመሆኑ "መቅረት የለበትም።" የሚል ሀሳብ በተደጋጋሚ የቀረበ ሲሆን ከውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል አንዷ ግን ይህ ሥርዓት ከጥቅሙ ይበልጥ ጉዳቱ ስለሚያመዝን መቅረት እንደለበት ገልጻለች። ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት ያቀረበችው በአሁኑ ዘመን አስከፊ የሆነው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ እና ዋንኛው በግብረ-ስጋ ግንኙነት በመሆኑ፣ እሬ የሆነ ሰው ደግሞ እሬ ከሆነላቸው ሴቶች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ባህሉ ስለሚፈቅድለት ሴቷም ብትሆን እንደዚሁ ከብዙ ወንዶች ጋር ግንኙነቱን ስለምትፈጽም ባህሉ ለበሽታው መስፋፋት ምክንያት ስለሆነ መቅረት አለበት በማለት ተከራክራለች።

---

[68] (አቶ ታደሰ ጣፋ፣ ወ/ሮ ደሜ ቱሉ፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ አቶ በልዳ አቦዬ፣ አቶ ሰይፉ መልካ፣ ጉዲሳ አቤቤ አቶ ደረጀ መኮንን የካቲት 21 ቀን 2007 ዓ.ም)።

በዚህ ሀሳብ ዙሪያ የድጋፍ እና የተቃውሞ ሀሳቦች በሰፊው ከተንሸራሸሩ በኋላ በሴት ተሳታፊዋ የቀረበው ሀሳብ አሳማኝ ሆኖ ቀርቧል። ይሁን እንጂ የማህበረሰቡ ባህል አሁን በውይይቱ በተሳተፉት አባላት ውሳኔ መቅረት የሚችል ባለመሆኑ የማህበረሰቡ ባህል እንዲቀጥል ሆኖ ነገር ግን ከጋብቻው በኋላ በድብቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸሙ እንደተገለጸው አሁን ባለንበት ዘመን በተለይም ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት ጋር ችግሩን የሚያጎላ በመሆኑ፣ ማህበረሰቡን በስፋት ማስተማር እና በድብቅ የሚደረገውን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማስቀረት እንደሚቻል የስምምነት ሀሳብ ላይ ደርሰዋል (ጋዲሣ አዱኛ፣ ቶላ ለማ፣ ፅጌ በቀለ፣ ፋኖሴ ጋዲሣ፣ ሽቶ አዱኛ መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም.)።

ከውይይቱ ተሳታፊዎች በተገኘው መረጃ መሠረት በባህሉ ቀጣይነት እና መቅረት አለበት በሚል ሀሳብ ላይ እንደተባለው በማህበረሰቡ በቂ ውይይት ተደርጎ የሚወሰን ቢሆንም እንኳን ለተግባራዊነቱ በጉዳዩ ላይ የጠለቀ ምርምር ማድርግን ይጠይቃል።

በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ጥቃት ይበልጥ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍል የትኛው እንደሆነ ሀሳብ እንዲሰጡ የቀረበ ጥያቄ፡-

በዚህ የቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሳተፉት[69] ሁለቱንም ፆታ ያካተተ ሆኖ በዕድሜ ወጣቶች እና ሽማግሌዎች፣ ከሙያተኞች የጤና ባለሙያ፣ መምህራን፣ ገበሬዎች ነጋዴዎች እና የባህል ባለሙያ ናቸው። ውይይቱ የተደረገው ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ሲሆን ይህንን ጥያቄ በሚመለከት በቃለ-መጠይቁ ወቅት በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ የሆነውን የኀብረተሰብ ክፍል ለመለየት የተሰበሰበውን መረጃ በቡድን ውይይቱ ለማጣራት ነበር።

ከጥያቄው በመነሳት በቡድን ተኮር ውይይቱ ወቅት ሁሉም የየራሳቸውን ሀሳብ ሰጥተዋል። በዚህም አንዳንዶቹ "ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍሎች ተጠቂ ናቸው፤" በሚል ሀሳብ ሲከራከሩ አንዳንዶቹ ደግሞ "ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እየጨረሰ ያለው ወጣቶችን ነው" በማለት ምክንያቱን ጭምር አስረድተዋል። ይህም ወጣቶች ለወሲባዊ ጉዳዮች ፈጣን መሆናቸው፣ በባህላዊ ጉዳዮች በተለይ በከንፈር ወዳጅ እና በእሬ ማሰደር ግንባር ቀደም ተሳታፊ በመሆናቸው፣ እና በተለይ በአሁኑ ዘመን ወሲብ ቀስቃሽ በሆኑ ፊልሞች የተጠመዱ በአብዘኛው የተጠመዱ በመሆናቸው ወጣቶች በቫይረሱ መጎዳታቸውን በማስረጃ

[69] አቶ ደረጀ መኮንን (መምህር)፣ አቶ መግራ ራጎ (የጤና ባለሙያ)፣ ወጣት አበበ ነጋሽ (ተማሪ) ወጣት ፋኖሴ ጋዲሣ (ተማሪ)፣ ወጣት ቶሎሣ መርጋ (ገበሬ)፣አቶ አበበ ጀቤሳ (መምህር) አቶ ሙሉጌታ አያኔ(የባህል ባለሙያ)፣ አቶ ሰይፉ መልካ (ያገር ሽማግሌ) ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ (ነጋዴ) ናቸው።

አስደግፌው አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል። በሌላ መልኩ በቫይረሱ ሴቶች ይበልጥ የተጠቁ ናቸው ብለው የተከራከሩት ደግሞ ሀሳባቸውን የሚያጠናክር ማስረጃ አቅርበዋል።። ለዚህም እንደ ማስረጃ ያቀረቡት በወሲብ ንግድ ላይ በአብዛኛው ተሠማርተው የሚገኙት ሴቶች በተለይም ወጣት ሴቶች ናቸው በመሆናቸው በአብዘኛው እየተጎዱ ያሉት ሴዮች በተለይም ወጣቶች ናቸው በማለት ተከራክረዋል። በመጨረሻም ከላይ የቀረበው አማራጭ ለቡድኑ አባላት ቀርቦ ባመኑበት ላይ ሀሳብ ሰጥተዋል። በዚሁ መሠረት በቡድን ውይይቱ ለተሳተፉ ሁሉም አባላት 33(22 ወንድ እና 11 ሴት) ሲከራከሩበት በቆዩ ጉዳዮች ላይ ድምፅ እንዲሰጡ ተደርገው የተገኘው ውጤት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ የቀረበ ነው።

ሠንጠረዥ 7፡- በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መግለጫ

ተ.ቁ	በኤች አይቪ/ ኤድስ ተጠቂ የሆነ የኅብረተሰብ ክፍል	ለጥያቄው መልስ በመስጠት የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ብዛት በጾታ			የተገኘ ውጤት በ(%)
		ወንድ	ሴት	ድምር	
1.	ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቂ ስለመሆናቸው	5	2	7	21.21%
2.	ሴቶች ጠተቂ ስለ መሆናቸው	7	3	10	30.31%
3.	ወጣቶች ተጠቂ ስለ መሆናቸው	10	6	16	48.48%
	ጠቅላላ ድምር	22	11	33	100%

ከመረጃ አቀባዮች በተገኘ መረጃ መሠረት በአጥኚው የተዘጋጀ (ጥር 2008 ዓ.ም)።

ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው በኤች አይቪ/ ኤድስ እየተጠቃ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል በደረጃ ስናይ ለጥያቄው መልስ በመስጠት ከተሳተፉት 33 መረጃ አቀባዮች ውስጥ 16 ሰዎች 48.48% በማስመዝገብ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በቫይረሱ ተጠቂ መሆናቸውን ገልጸዋል። ይህንን በሚመለከት ከጽሑፍ የተገኙ መረጃዎች ወጣቶች በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተጠቁ መሆናቸውን ያመለክታል። በተለይም ምንም እንኳን የተማሩ ሰዎች የቫይረሱን ሥርጭት በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ቢሆኑም የተማሩና በከተማ አከባቢ የሚገኙ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች የወሲብ ፊልሞችን በማየት በከፍተኛ

ደረጃ ለኤድስ የተጋለጡ ናቸው (Amanuel 2007፡ 67)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በኤትዮጵያ ቴሌቪዥን አዲስ ሙግት በሚል ፕሮግራም መጋቢት 7 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው አስተያየት ወጣቶች ወሲብ ቀስቃሽ የሆኑ ፊልሞችን በማየትና በዚህም የተነሳ ልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነቶችን በመፈጸም ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የተጋለጡ መሆናቸውን ይጠቁማል። በሌላ መልኩ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭትን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉ ጥናቶች ሪፖርት የሚያሳዩት አብዛኛውን ጊዜ በቫይረሱ እየተጠቁ ያሉት ወጣቶች መሆናቸውን (Brooks & Furstendberg: 1989፣ UNAIDS: 2004; Susan Moore & Doreen Rosenthal: 2006; Abdulhamid (2008) “Feasibility of Antiretroval Drug Therapy in Ethiopia” በሚል ርዕስ በOSSREA: 2008 በተዘጋጁት ጽሑፎች ውስጥ በስፋት ተብራርተዋል።

በሠንጠረዡ ላይ እንደተገለጸው የ10 ሰዎች መልስ 31.91% በማስመዝገብ ከወጣቶች ቀጥሎ ሴቶች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን ያመለክታል። ይህን አስመልክቶ በኤች አይ ቪ/ ኤድስ እየተጠቁ ያሉት ሴቶች እንደሆኑና ከሴቶችም በተለየ ሁኔታ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ከላይ በዝርዝር የቀረቡ ዓለም አቀፋዊ ጥናቶች ይገልፃሉ። ይህም በአማኑኤል ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጸው በወሲባዊ ፊልሞች ተጽእኖ ሊሆን ይችላል። በመጨረሻም መረጃው እንደሚያሳየው የ7 ሰዎች መልስ 21.21% በማስመዝገብ ሁሉም የኀ/ሰብ ክፍሎች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆኑን ያመለክታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከላይ የተጠቀሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ ተጠቂ መሆናቸውን የሚያሳዩ ሲሆኑ የሥነቃል ዓይነቶች መረጃዎችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው። እነሱም በምዳባ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን የተመረጡት በምዕራፍ ሰባት ውስጥ በየርዕሶቹ ሥር ተተንትነዋል። ከዚህ በመቀጠል እስካሁን በልዩ ልዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ከመስክ የተገኙ የሥነቃል ዓይነቶች ምዳባና ትንተናን እናያለን።

የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ መዋቅራዊ መግለጫ

- **የሥነቃል ዓይነቶች (ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች) ምደባ**
  - ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች= 213
    - ጋብቻን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች=37
    - ከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ ሥነቃሎች =71
    - ውሽማን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች=73
    - ሲገባን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች=19
    - እሬን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች=13
  - ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች= 293



መዋቅራዊ መግለጫ 1፡- ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ መዋቅራዊ መግለጫ

ምዕራፍ ስድስት

6. ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ የሥነቃል መረጃዎች ምደባ እና ትንተና

ምደባ ዘውግን ለመተንተን ስናስብ መረጃዎችን የምናደራጅበትና የምንከፋፍልበት ስልት ነው። (Schoemaker, 1990: 236) ምደ ባን በሚመለከት እስካሁን ድረስ ሁሉንም የሚያስማማ ስልት የለም። ይህ ደግሞ ከፎክሎር ብያኔ ወጥ አለመሆን ጋር የታያያዘ ነው። ምደባን ለማከናወን ስልታዊ ገጽታዎችን፣ ርዕሰ ጉዳይን፣ የመከሰቻ አጋጣሚን፣ ተግባርን፣ አውድን፣ እንዲሁም ሀገራዊ ስያሜዎችን የአከፋፈል መስፈርቶች መሠረት አድርጎ መውሰድ የተሻለ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። ይህንን በተመለከተ Finnegan (1992: 143-145) Ben-Amos (1982: 38-46) ዘውጎችን በጭብጣቸው አጠቃሎና በተግበራቸው ከፋፍሎ መመደብ እንደሚቻል ያስረዳሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የዘውግ ፍቺና ምደባ ስለቶቹ የተለያዩ ጭብጦች ባላቸው ባህሪያት የተዋቀረና ሰዎች ስለፎክሎር ቅርጽ፣ ተግባር፣ ይዘት፣ ማህበራዊ ሥርጭት፣ ባህርይ ወይም አውዳዊ

አጠቃቀሞች ያገለግላል ብለው በሚያስቡት ነገር ውስጥ መግባት የቻለ መሆን እንዳለበት Bauman (1992:55) ይገልጻል።

መረጃዎችን መመደብ ማለት በየዘዴዎቹ ሥር የቀረቡትን እንደየሚያተኩሩበት ጉዳይ በማስተካከል ስያሜ በመስጠት፣ መመደብና ለትንተና ምቹ አድርጎ ማቅረብ ነው (ያዴሳ ቶሎሳ፣ 2007፡ 107-18)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ፈቃደ (1991፡137) ስብስብ ሳይኖር ምደባን ማሰብ እንደሌለብንና መረጃዎች ከየት ከየት መሰብሰብ እንዳለባቸው ይገልጻል። የተሰበሰቡትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ የስብስቦቹን ዓይነትና ባህርይ በመመልከትና በመመርመር በሚገኘው ግኝት ላይ ተመሥርተው መመደብ ይቻላል። እንደ ፈቃደ (1991፡ 89) አባባል ቃል ግጥሞችን ለመመደብ በእያንዳንዱ ቀን ከሚታዩ የሕይወት ክስተቶች ጀምሮ እስከ ወቅታዊና ዓመታዊ ክስተቶች ድረስ ሥርዓት ባለው መንገድ ዝርዝርራቸውን አዘጋጅተው ከርዕሱ የሚገጠሙትን ከልስፎ ማሳየት ነው ።

የሥነቃል አመዳደብን በሚመለከት ሁለት ሞዴሎች አሉ። እነሱም ሥነቃል መከፈል ያለበት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጠው አገልግሎት (ማህበረሰቡ ሥነቃሉን ከተጠቀመበት ጉዳይ) እና ከሥነቃሉ ታሪካዊ አመጣጥ አኳያ መሆን እንዳለበት በመጥቀስ ይህም አካባቢያዊ ቲዮሪን መሠረት ያደረገ መሆኑን Ben Amos, (1975a: 168)ይገልጻል። ሌላው ሥነቃልን በአካባቢ ቲዮሪ ላይ ተመስርቶ መክፈል አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ ለዚህም አንድ ግጥም ወይም ምሳሌያዊ ንግግር ሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ የተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊገኝ እንደሚችል Okepewho (1992፡ 27) ይጠቅሳል።

በእርግጥም በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ የሠርግ ዘፈኖች በጥምቀት ክብረ-በዓል ላይ፣ አንዳንድ የፎሌ ዘፈኖች በሠርግ ላይ ወዘተ … ሲዘፈኑ ታይተዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ ጊዜ ለሌላ ጉዳይ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በዚህ ጥናት ውስጥ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ ሲነገሩ ተደምጠዋል።

ከላይ የተገለጹትን አመለካከት መሠረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ ሥነቃሎቹ የተመደቡት የሁለቱንም ምሁራን አተያይ በመከተል ነው። ይኸውም ሥነቃሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጠው አገልግሎት ማለትም ከሚያነሳው ጭብጥ (ይዘት) ወይም ከሚያተኩርበት ጉዳይ አንጻር እንዲሁም ማህበረሰቡ ሥነቃሉን በሚመድብበት መንገድ የተመደቡ ናቸው። በመሆኑም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሁለት የተለያዩ የሥነቃል ዓይነቶች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ሥር ተመድበዋል። ይህንን አስመልክቶ Marshal and Rossman, (2006: 159)

እንደሚከተለው ገልጸዋል። “…the categories should be internally consistent but distinct from one another”. ይህ ማለት በአንድ ምድብ ውስጥ የተካተቱት ከይዘት አኳያ ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ በዓይነታቸው ግን አንዱ ከአንዱ ይለያል።

ከዚሁ አኳያ በአራቱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት) የተገኙ መረጃዎች እንደሚያተከሩበት ርዕሰ ጉዳይ ስያሜ ተሰጥቷቸው በይዘት ተመድበዋል። በዚሁ መሠረት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች[70] በዝርዝር ቀርበዋል። እነሱም ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች ተብሎ በሁለት የተለያዩ የሥነቃል ዓይነቶች ተከፍለዋል። በሌላ መልኩ ሁለቱ የሥነቃል ዓይነቶች ካተኮሩባቸው ይዘት አኳያ በአንድ ላይ ተመድበዋል። ለምሳሌ ጋብቻን የሚመለከቱ ሁለት የተለያዩ የሥነቃል ዓይነቶች (ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች) በአንድ ላይ ተመድበዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች በከንፈር ወዳጅ፣ በውሽማ፣ በሲገባ እና በእሬ ላይ ያተኮሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች በአንድ ላይ ተመድበዋል።

ይሄም ምደባ በሥነቃሉ ቅርፅ ሳይሆን ሥነቃሉ በሚያነሰው ጭብጥ (ይዘት) ሲሆን በዚህ ጥናት ትኩረትም ተመሳሳይነት ይዘት ያላቸውን በአንድ ላይ በማምጣት የጥናቱን ርዕስ ለመተንተን ያመቻል።

ትንተና በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለሌላው ግልጽ እንዲሆኑ ወይም በተራው ከሚታዩት በበለጠ ልዩ ልዩ ገጽታዎችን የምናሳይበትና የምናመለክትበት ስልት ነው። በትንተና ወቅት ሦስት ነገሮች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ይከናወናሉ። ይህም የተገኙትን መረጃዎች በማቅረብ መግለጽ፣ መተንተንና መተርጎምን ያካትታል።

በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ ትንተና መረጃን ወደ ግኝት የምንቀይርበት መንገድ መሆኑን Marshal & Rossman (2006:154) ይገልጻሉ። ትንተና ከገለጻ በላይ በመሆኑ የሁሉንም መረጃዎች ግንኙነት የሚመለከት ዘዴ ነው። በመሆኑም አንድ አጥኚ መረጃ በሚተነትንበት ወቅት በዋናነት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የመረጃውን ሀሳብና ጭብጥ መጠቆም መሆኑን Ben Amos, (1993) ይገልጻል።

[70] ከመስክ ከተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ በአብይ ጭብጣቸው ጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን ከሚያሰዩ ሥነቃሎች መካከል 54 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 160 ዘፈኖችበድምሩ 214 ናቸው። እነዚህም ከሚያተኩሩበት ይዘት አኳያ ጋብቻን፣ የከንፈር ወዳጅን፣ ውሽማን፣ ሲገባን እና እሬን በሚመለከቱ ሥር ተዘርዝረው በዚህ ጥናት ውስጥ አባሪ ተደርገዋል።

ስለዚህ ትክክለኛ ትንተና የሚባለው ዘውጉን በአውዱ ውስጥ የተነተነ ነው። ይህ ማለት አንድን የፎክሎር ዘውግ ለመተንተን የተሰበሰበውን የመረጃ ዓይነት (text)፣ የዓይነቱን ውስጣዊ ሁኔታ ወይም የቋንቋ ትርጉም (Texture) እና ሥነቃሉ የተነገረበት ሁኔታ ወይም የመረጃውን አውድ (Context) ትኩረት ተሰጥቷቸው በዝርዝር መታየት እንዳለባቸው Dundes (1973: 26) Ben Amos (1993:210) ያብራራሉ።

ለአውድ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ብያኔ ሰጥተዋል። ለምሳሌ Sims & Stephens አውድ አንድ ድርጊት የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ አስቀምጠዋል። ስለዚህ የአንድ ፎክ ቡድን አባላት ፎክሎርን የሚጋሩት አካላዊ መቼቶችና ማህበራዊ ሁነቶች እንዲሁም የታዳሚዎችና ከዋኞች ግንኙነት አውድን ይመሰርታሉ። በመሆኑም አውድ የሚያመለክተው በቴክስትና ክዋኔ ዙሪያ የሚገኙ ማንኛውንም የክዋኔ፣ እውነታ፣ ቁሳቁስ፣ ሁነቶችና ክስተቶችን ጭምር ነው (Sims & Stephens,2005:138)። የተለያዩ የአውድ ዓይነቶች አሉ። እነዚህን ለይቶ ማወቁ ለሚካሄደው ፎክሎራዊ ትንታኔ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ስለዚህ የአውድ ዓይነቶች መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል።

የአውድ ዓይነቶች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም ሁኔታዊ አውድ እና ባህላዊ አውድ ይባላሉ። ሁኔታዊ አውድ የሚባለው የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ባህላዊ አውድ ደግሞ በውስጡ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚቀርብበት ሰፊ ገጽታ ሲሆን፤ ክዋኔው በውስጡ የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚመራበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ስርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኙ የታሪክ ዕውቀትና የስነ-ምግባር ህግጋትን ሁሉ ያጠቃልላል (Ben-Amos,1993፡216)።

አንድ ፎክሎረኛ ከመስክ ያገኘውን መረጃ ለመተንተን ሲያደራጀ አውድን በተመለከተ ሊያተኩርባቸው የሚገባ ስድስት ነጥቦችን እንዳሉ Bauman ያስረዳል። እነሱም፡- ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ ይባላሉ (Bauman,1983፡367)። የእነዚህን አውድ ትኩረት እንደሚከተለው እንመልከታለን።

ፍቻዊ አውድ፡- የዚህ አውድ ትኩረት የሚያጠነጥነው ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ላይ ነው፡፡ ይኸውም ማህበረሰቡ ስለሚከውናቸው

ፎክሎሮች (የሥነቃል ዓይነቶች) ያለው ግንዛቤ፣ አረዳዱ፣ ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳዩ ለመረዳት ያስችለናል።

ተቋማዊ አውድ፡- በአውድ ተኮር ጥናት ሊተኮርበት ከሚገባው ውስጥ ተቋማዊ አውድ ሌላኛው ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። ጉዳዩ የሚከወንበት በባህሉ ውስጥ የት ቦታ ላይ እንደሆነ ለይተን ማስቀመጥ እንዳለብን የሚያስገነዝበን አውድ ነው። ይኸውም የሚከወኑት የት እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ ፎክሎራዊ ጉዳዩ መከወናቸው የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር ያግዛል።

የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፡- በአውድ ተኮር ጥናት ውስጥ የሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሻ ነው። ይሄም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድና አንዱን ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን ዘዴ በውስጡ ያካትታል።

ማህበራዊ መሰረት፡- ማህበራዊ መሰረት የሚባለው የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት የሚያመለክተን ነው። ይሄ ማለት የሚጠናው ፎክሎር የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ የትኛውን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ፣ በክዋኔው ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውዳዊ ትንታኔ መስጠት ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት አባላት በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሙያ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ቡድኖች ይከፈላሉ።

ግለሰባዊ አውድ፡- ግለሰባዊ አውድ የሚመለከተው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡን ሕይወት ምን እንደሚመስል ከማወቅ ላይ ነው። በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይያያዛል? ለሚል ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ላይ የሚያጠነጥን ነው። በዚህ አውድ ውስጥ የግለሰቡን የመከወን ችሎታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለግለሰቡ የሚሰጠውን ስሜት ሊጤን ይገባል። ይህም ከግለሰቡ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ እና ባህላዊ ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል።

ሁኔታዊ አውድ፡- በመጨረሻ በአውዳዊ ትንተና ውስጥ የሚነሳው ጉዳይ ሁኔታዊ አውድ ሲሆን፣ ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚከውነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ለሚለውና በማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ምላሽ የሚሰጥ ነው። ሁኔታዊ አውድ ሲባል በባህሉ የተወሰነ የአንድ ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው። በዚህ ውስጥ አካላዊ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸው የተለያዩ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓጎም የሚከናወንበት መመሪያ፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት፣ ቅደም ተከተላቸው ጭምር ያካትታል።

በትንተኔ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ቴክስት በራሱ ፍቺ ሊሰጥ የሚችል ቢሆንም በአብዛኛው ብቻውን በተሟላ መልኩ መልዕክት ለማስተላለፍ ያዳግተዋል። ቴክስቱ ያለ አነጋገር ለዛ ብቻውን መቆም አይችልም። የተሟላ ፍቺ ወይም ትርጉም ለማግኘት በአንድ በተወሰነ አውድ ሲነገር፣ ሲተረክ፣ ሲዘፈን (ሲዜም)፣ ወይም ሲከወን ብቻ ነው። ስለዚህ በተረቱ፣ በተረኩ፣ በምሳሌያዊ ንግግሩ፣ በዘፈኑ፣ ወዘተ … ውስጥ ያሉትን ነገሮች (elements) ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የሰላ ጆሮና ንቁ ዓይን ሊኖረን እንደሚገባ የዘርፉ ምሁራን Bauman, (1983); Ben Amos, (1993); Sims & Stephens, (2005) ይመክራሉ።

ስለዚህ የክዋኔን ፍቺ ለመረዳት የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ፣ እማሬያዊ ፍቺ፣ ፍካሬያዊ ፍቺ፣ ባህላዊ ፍቺና የመሳሰሉትን ለይቶ ማወቁ ግድ ይላል። ሌላው ደግሞ ከምናዳምጠው በላይ ተናጋሪውን፣ ተራኪውንና ዘፋኙን በንቃት በዓይናችን መከታተል እንዳለብን እንረዳለን። ምክንያቱም የፊት ገጽታን በመቀያየር፣ በእንቅስቃሴና በድምጽ መለዋወጥ ሳቢያ የፍች ልዩነት ስለሚያስከትሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቃላት፣ ሀረጎች፣ ዐረፍተ ነገሮችና ሥርዓተ ነጥቦች ከፍቺ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው (Ben-Amos, 1993፣14)።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ከላይ ከተዘረዘሩት የአውድ ማብራሪያዎች ጋር በተያያዘ መልኩ ከልዩ ልዩ አውዶች የተሰበሰቡ በቱለማ ኦሮሞ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች በአብዛኛው በራሳቸው የሚያስተላልፉት መልዕክት አላቸው። ጠለቅ ያለ ምርምር የሚያስፈልጋቸው ደግሞ ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት ቀርበዋል። ከዚሁ አኳያ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችንና ከእነዚህ ጋር በተያይዘ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ

የሥነቃል ዓይነቶች (ምሳሌያዊ ንግግሮችን እና ዘፈኖችን) ባህላዊ ፋይዳ ለመረዳት መሞከር የሚተላለፈውን ሀሳብ በተገቢ ሁኔታ ለመረዳት ያስችለናል።

በመሆኑም በምዕራፍ ስድስት እና ሰባት ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሚመለከት የተመረጡ የሥነቃል መረጃዎች ይዘታቸው የተተነተኑት ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ባስተሳሰረ መልኩ ነው። ይሂም እያንዳንዱ የሥነቃል ዘውግ (text) በስሙ ምሳሌያዊ ንግግር ወይም ዘፈን መሆኑ ተለይቶ፣ የዘወጉ ውስጣዊ ሁኔታ (Texture) ስለምን? ስለማን? እና ለምን? እንደሚናገር ወይም እንደሚዘፈን ታውቆ እና ዘውጉ የተገኘበት አውድ (Context) ከየት እንደሆነ ተገልጾ ተብራርቷል።

ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ በዋናነት ከአውዳዊ እና ተግባራዊ/ፋይዳዊ ቲዮሪዎች አንጻር ይዘታዊ ትንታኔ የተደረገ ሲሆን ሌሎች ልዩ ልዩ ቲዮሪዎችም በደጋፊነት አገልግሎት ሰጥተዋል። በዚሁ መሠረት የሥነቃል ዓይነቶቹ ከተገኙበት አኳያ አውዳዊ ቲዮሪን (Contextual theory)፤ እና ሥነቃሉ ለማህበረሰቡ ካለው ፋይዳ አንጻር ደግሞ ተግባራዊ/ ፋይዳዊ ቲዮሪ (Functional theory) በዋናነት መሠረት ያደረገ ትንተና ተደርጓል።

በተጨማሪ በዚህ ጥናት የተካተቱት የሥነቃል ዓይነቶች በርካታ ጉዳዮችን የሚደስሱ በመሆናቸው፣ የጤና ትምህርት ቲዮሪ (Health Education Theory)፣ የወሲብ ቲዮሪ (Sexual Theory)፣ ተምሳሌታዊ ቲዮሪ (Symbolic Theory)፣ ክልላዊ ቲዮሪ (Hemispheric Theory)፣ የፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪ (Pschoanalytical Folklore Theory) የማህበረሰብ እውቀት አዋቀሪያን ቲዮሪ (Social Constructive Theory) እና ለውጥና ቀጠይነት ቲዮሪ (Change and Continuity Theory) እንደየአስፈላጊነታቸው በደጋፊነት የመተንተኛ ቲዮሪዎች ሆነው አገልግለዋል።

በመሆኑም በየርዕሰ ጉዳዮቹ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ የተመረጡት ከይዘታቸው አንጻር ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

6.1. ጋብቻን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባና ትንተና

ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ውስጥ ጋብቻን የሚመለከቱ 37 (24 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 13 ዘፈኖች)[71] ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች አጠቃላይ ትኩረት ለአንድ

[71] አባሪ 6፡- ቢጋብቻ ሥር የተመደቡትን የሥነቃል ዓይነቶች ዝርዝር ይመልከቱ።

ማህበረሰብ መሠረቱ ቤተሰብ መሆኑንና ለዚህ ጋብቻ ወሲባዊ ፍላጎትን ለማርካት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የባልና ሚስት የጋራ ጥቅሞች እንደሚያካትት የሚገልጹ ናቸው። ይህንኑ አስመልክተው ጋብቻ ወሲባዊ ስሜትን መጋራት ብቻ ሳይሆን ሌሎች በርካታ የጋራ ጥቅሞች እንዳሉት Olson, (2000:8) ይገልጻል።

በተመሳሳይ ሁኔታ "በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው፤" የሚለውን አባባል የሚያጎሉ ናቸው። በመሆኑም አብዛኞቹ መረጃዎች የትዳርን አስፈላጊነት የሚያወሱ እና የኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታን ለመከላከል በመተማመን ላይ የተመሠረተ የአንድ ለንድ ግብረ-ስጋ ግንኙነትን የሚያበረታቱ ናቸው።

በሌላ መልኩ ከጋብቻ ውጭ የሚከናወኑ ወሲባዊ ግንኙነቶች ቅናትና እና ንቀት የሚያስከትሉ መሆናቸውን እና ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስና ለሌሎችም ልዩ ልዩ አባለዘር በሽታዎች የሚያጋልጡ እንዲሁም ለጋብቻ መፍረስና ቤተሰብ መበተን ምክንያት መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። ከዚሁ አንጻር በዚህ ሥር ከተመደቡት የሥነቃል ዓይነቶች መካከል ከጥናቱ ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው 15 (9 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 6 ዘፈኖች) ተመርጠው እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

ሠንጠረዥ 8. ጋብቻን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Haati manaa dhirsaaf kafana.	ሚስት ለባሏ ገበና ናት፡
2. "Waan jettan jedhaatii mucaa koottan Garagalaa." jette niitii dhirsaan.	‹‹የሚትለውን በልና ወደ ልጄ ልመለስ›› አለች አሉ ባሏን፡፡
3. Sireen seera nama lamaa hin baattu.	አልጋ የሁለት ሰው ደንብ አትሸከምም።
4. Ilkaan hidhii malee niitiin dhirsa malee, hin midhagdu.	ጥርስ ያለ ከንፈር ሚስት ያለ ባል አታምርም።
5. Niitii dhirsa hinqabnee fi asheeta karaarraa hundumatuu tutuqa	ፊትና የመንገድ ዳር እሸት ማንም ይነካካዋል፡፡
6. Boru boruun intala dulloomsa.	በጊዜ አላማግባት ልጅቷን ያስረጃል።
7. Boru boruun mucaa dulloomsa.	በጊዜ አላማግባት ልጁን ያስረጃል።
8. Deemsii karaa ganama hafe, fuuti ijoollummaatti hafe.	መንገድ ካሰቡ በጠዋት፣ትዳር ካሰቡ በልጅነት ።

9. Fuutii fi kajeellaan ganaman. ጋብቻና ቅልውጥ በጠዋት ነው።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቃለ-መጠይቅ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ከመረጃ አቀባዮች[72] የተገኙ ናቸው። በመሆኑም ሁሉም ከአውዳዊ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ሲሆኑ ከፋይዳቸው አንጻር በተግባራዊ ቲዮሪ ተተንትነዋል። እንዳስፈላጊነቱም በሌሎች የመተንተኛ ቲዮሪዎች ተደግፈዋል። ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በአጠቃላይ ሲታዩ የጋብቻን ክቡርነት የሚያሳዩ እና በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የጋብቻን አስፈላጊነት የሚጠቁሙ ናቸው።

ይሁን እንጂ በአጠቃለይ መልዕክታቸው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም እያንዳንዳቸው ካተኮሩበት ጉዳይ አኳያ ልዩነት አላቸው። በመሆኑም የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ተመሳሳይ የሆኑት በጋራ የተተነተኑ ሲሆን ልዩነት ያላቸው ደግሞ በተናጠል ተተንተነዋል። ዝርዝሩንም ከዚህ እንደሚከተለው እናያለን።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ባለቤት ለባሏ ገበና ሸፋኝ መሆኗን ይገልጻል። በዚህ መሠረት አባባሉ ከተነገረበት አውድ አኳያ የባለቤቷን ደካማ ጎን የምትሸፍንለት ሚስት መሆኗን የሚያመለክት ሲሆን ባል እና ሚስት ከወሲባዊ ፍላጎት ባሻገር አንዱ የሌላውን ችግር የሚሸፍኑ መሆናቸውን ያሳያል። ይህም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖላቲካዊ ጉዳዮችንም ያካትታል።

በተራ ቀጥር 2 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ በትዳር ውስጥ መሠረታዊ እና አስፈላጊ የሆነውን ወሲባዊ ፍላጎቷን በሥነቃል የገለጸችበት ነው። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚነገርበትን አውድ ስንገምት ሌሊት በመኝታ ሰዓት መሆኑን እንገነዘባለን። ይህ ጊዜ ደግሞ የእንቅልፍ ብቻ ሳይሆን በተለይ ባልና ሚስት የወሲብ ፍላጎታቸውን የሚፈጽሙበት ጊዜ ነው። ምክንያቱም በተለምዶ ባልና ሚስት የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙት ሌሊት በመሆኑ ነው። ስለሆነም የወሲብ ፍላጎቷን ባህላዊ ወጉን በተከተለ አኳኋን በጨዋ ደንብ ምሳሌያዊ ንግግር በመጠቀም የገለጸችበት መንገድ ነው። አባባሉ ወሲባዊ ፍላጎትን ከመጠቆሙም ባሻገር በሕጋዊ ጋብቻ ውስጥ ለጤናማ ዜጋ መፈጠር የጎላ ሚና እንዳለው ያመለክታል።

[72] አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶሰይፉ መልካ፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ እና አቶ ተስፋዬ ሁንዴ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም. ጫንጮ ከተማ።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የሚገኝ ምሳሌያዊ ንግግር ባልና ሚስት የሚጋቡት በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መልኩ በሥርዓትና በሕግ ተግባብተው ነው። ወሲባዊ ግንኙነታቸውን የሚፈጽሙት ደግሞ በአልጋ ላይ ነው። ምሳሌያዊ ንግግሩ አልጋው ማስተናገድ የሚችለው በሥርዓት የተጋቡትን ባልና ሚስት ብቻ ነው። ስለዚህ ይህ ሥነቃል ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ ሲታይ ከጋብቻ ውጪ የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም **ነውር** መሆኑን ያመለክታል።

በሌላ መልኩ በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ ያሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች በደጋፊ መተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ስንመለከት በወሲባዊ ቲዮሪ ይገለጻሉ። መሠረታዊ የወሲብ ቲዮሪ እንደሚያመለክተው የሁሉም ፍጥረታት የወሲብ ባህሪይ ዋና አላማዉ ወሲባዊ እርካታን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ዘርን ለመተካት (ለመራባት) መሆኑን Ember and Ember (2003) ይገልጻሉ። ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ደንብ የተደነገገ የወሲብ ሥርዓት መኖሩን የሚጠቁሙ ናቸው።

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ ያሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ያለትዳር የሚኖሩ ሴቶች ብዙ ፈተና እንደሚገጥማቸው የሚገልጹ ናቸው። 4ኛው ምሳሌያዊ ንግግር ጥርስ ያለ ከንፈር፣ ከንፈርም ያለ ጥርስ እንደማያምር ሁሉ ሴትም ያለ ባል እንደማይመቻት የሚያሳይ ነው። 5ኛው ደግሞ ባል የሌላትን ሴት ሁሉም ስለሚመኛት እንደሚጎነታትላት እና ለወሲባዊ ፍላጎት ማርኪያ ወንዶች እንደሚያስቸግሯት የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ሁለቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ ሲታዩ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ባህላዊ ወጎቹን የሚጠብቅበትና ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበት ነው (Bauman, 1977)። ለዚህም ሴቶች ትዳር መያዝ ወይም በጋብቻ ሕይወት ውስጥ መኖር እንዳለባቸው የሚገልጹ ናቸው።

ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ሲታዩ በተምሳሌታዊ ቲዮሪ ይተነተናሉ። ይኸውም ጥርስ እና ከንፈርን በባል እና ሚስት ተመሳስለው ቀርበዋል። ይህ ማለት ከንፈር የሌለው ጥርስ ገጦ ስለሚቀር ማንም ያየዋል። ይህ ደግሞ በ5ኛው ምሳሌያዊ ንግግር ላይ እንደተገለጸው ለወሲባዊ ንክኪ ያጋልጣታል። ከንፈር የሌለው ጥርስ ባዶ ሆኖ ውበት ያጣል። ውበት የሌለው ነገር ደግሞ አያምርም። በመሆኑም ሴትም ያለ ባል አታምርም ማለት ነው።

ከተራ ቁጥር 6 እስከ 9 ያሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋብቻ መፈጸም ያለበት በተወሰነ የዕድሜ[73] ክልል መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። አራቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋብቻ በወቅቱ ካልተፈጸመ ለሌላ ችግር የሚያገልጥ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። ዘርዝር ባለ መልኩ ስንመለከታቸው በ6ኛው እና 7ኛው ተራ ቁጥር ላይ ያሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ጋብቻን በወቅቱ ካልፈጸሙ እያረጁ እንደሚሄዱ እና ካረጁ ደግሞ ማንም እንደማይፈልጋቸው የሚያሳዩ ናቸው። 8ኛው የመንገድ ጉዞ በጧት ከሆነ ድካም እንደሚቀንስ ሁሉ ጋብቻም በጊዜ ከሆነ ውጤታማ መሆኑን ሲያመለክት 9ኛው ምሳሌያዊ ንግግር በተመሳሳይ መልኩ በጧት የለመነ የፈለገውን ነገር የማግኘት ዕድሉ የሰፋ እንደመሆኑ መጠን በጊዜ ያገባም ልጅ የመውለድ እና ሀብት የማፍራት ዕድሉ የሰፋ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ አራቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች የጋብቻን አስፈላጊነት የሚገልጹ እና ጋብቻ በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ መፈጸም እንዳለበት የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ ካልሆነ ግን አንድ ሰው በባህሉ መሠረት ከማህበረሰቡ ማግኘት የሚገባው ጥቅማ ጥቅሞች የሚቀሩበት መሆኑን ያሳያሉ። በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ውስጥ በዕድሜ ላይ የተመሠረቱ ደረጃዎች አሉ። በመሆኑም ጋብቻ የሚፈጸመው Raabaa doorii (ራባዶሪ)[74] ደረጃ ውስጥ ሲገባ ነው።

> Akka seera Gadaatti, namoonni kan dhalchaniifi ijoollee horatan ykn kan fuudhan yeroofi umurii murtaa'e tokkorrattidha. Kaayyoon isaas sadarkaan Gadaa abbaafi ilmaa akka wal-simuufi ijoolleen dhalattus Gadaan ala akka hin taaneef. Akka seera kanaatti namoonni kun kan fuudhan yeroo sadarkaa doorii seenan jechuudha (Almaayyoo Hayilee, 2007: 67).

ትርጉም በአማርኛ

> በገዳ ሥርዓት ደንብ መሠረት አንድ ሰው ጋብቻ በመፈጸም ልጆች ማፍራት የሚችለው በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው። ይህም የሆነበት ዋና ዓለማ የአባትና ልጅ የገዳ ደረጃ እንዳይፋለስ እና የሚወለዱ ልጆች ከገዳ ውጭ እንዳይሆኑ ነው። በዚህ ሥርዓት ወንዶች ማግባት የሚችሉት ዶሪ ደረጃ ውስጥ ሲገቡ ነው።

[73] በአከባቢው ባህል መሠረት ወንዶች ከ18 ሴቶች ደግሞ ከ15 ዓመት በላይ እንደሚያገቡ መረጃ አቀበዮች ገልጿል (አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ተስፋዬ ሁንዴ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ አቶ ጉዲሳ አቤቤ፣ አቶ ሙሉጌታ አያኔ እና አቶ ሰይፉ መልከካ ታህሳስ 2007 ዓ.ም.)።

[74] በገዳ ሥርዓት የዕድሜ ክፍፍል ዶሪ ከ32 እስከ 40 ዓመት ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶች የሚመደቡበት ነው።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር Dirribii Damissee, (2009:231) በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ውስጥ ጋብቻ የሚፈጸመው በራባዶሪ ደረጃ ከ32 እስከ 40 የዕድሜ ክልል ውስጥ መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ሰው ሚስት ማግባትና የግል ንብረት ማፍራት እንደሚጠበቅበት ይገልጻል። ይህ ካልሆነ ወደ ገዳ ደረጃ እንደማይሸጋገር ያብራራል።

ከእነዚህ የጽሑፍ መረጃዎች የሚንረዳው በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ውስጥ ጋብቻ የሚፈጸመው በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ መሆኑን ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት የገዳ ሥርዓቱ በዕድሜ ላይ የተመሠረተ ክፍፍል ያለው እና በእያንዳንዱ የዕድሜ ክልል ውስጥ መፈጸም የሚገባቸው ተግባራት በመኖራቸው ነው። ይህ ካልሆነ ግን ከማህበረሰቡ የሚገኘው ጥቅም የሚቀርበት መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ በ (Dirribii Damissee, 2009:231) ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጸው አንድ ሰው በራባ ደረጃ ካላገባ ወደ ገዳ ደረጃ አይሸጋገርም። ይህም ማለት በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ሥልጣን መያዝ የሚቻለው ዕድሜው 40 ዓመት ሲሞላ ነው። ስለዚህ ያላገባ እና ንብረት የሌለው ሰው ወይም ትዳር መሥርቶ ቤተሰቡን መምራት ያልቻለ ሰው በማህበረሰቡ ደንብ መሠረት የማስተዳደር መብት የለውም ማለት ነው። በመሆኑም በሥነቃሎቹ ውስጥ የተገለጹትም ጋብቻ በወቅቱ ካልተፈጸመ በልዩ ልዩ መልኩ የሚቀሩ ፋይዳዎች መኖራቸውን የሚጠቁሙ ናቸው።

በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ እውቀት ውስጥ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገር እንዳላቸውና እነዚህ የውክልና ሁኔታዎች በአብዛኛዉ ሜታፈሮች (Metaphors) መሆናቸውን Mills (2008) እና Bayleyegn Tasew (2009) ይገልጻሉ። ከዚሁ አንጻር እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች ከተምሳሌታዊ ቲዮሪ አንጻር ሲታዩ ከላይ እንደተብራራው ነገ ማለት ከእርጅና ጋር፣ የመንገድ ጉዞ እና ልመና ከጊዜ ጋር ተያይዞ ከሚፈጸም ጋብቻ ጋር ተመሳስለው የቀረቡ ናቸው።

በአጠቃላይ ሁሉም ምሳሌያዊ ንግግሮች ከጋብቻ ጋር የተያያዙ እና የጋብቻን አስፈላጊነት የሚገልጹ ናቸው። ከዚሁ አንጻር ጋብቻ በወቅቱ መፈጸም እንዳለበት የሚመክሩ እንዲሁም ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸሙ የግብረ-ስጋ ግንኙነቶችን የሚያወግዙ[75] ናቸው። በሌላ መልኩ ጋብቻን በወቅቱ መፈጸም ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ የሚገልጹ ሲሆኑ

[75] ከላይ በምሳሌያዊ ንግግር ውስጥ የተገለጸው "አልጋ የሁለት ሰው ደንብ አትሸከምም።" የተባለው ከጋብቻ ውጭ የሆነ ግብረ-ስጋ ግንኙነትን የሚያወግዝ አባባል ነው።

ከእነዚህ መካከል አንዱ በጋብቻ ውስጥ በመተሳሰብና አብረው በመኖር ጤናማ የሆነ ወሲብ በመፈጸም ጤናማ ዜጋን የማፍራት አስፈላጊነትን የሚያስተምሩ ናቸው።

ሠንጠረዥ 9. ጋብቻን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Silaa jala san qottaa,	መቼም ከታች እያረስክ ነው፣
Yaa Jimaa re’ee san as deebisii,	እስቲ ፍየሏን ወዲህ መልስ ጅማ፣
Sijaaladhe yoo jette,	እወድሻለሁ ካልክ
Farramii firmaadhan nabeeksisii.	አሳውቀኝ በፊርማ።
2.Yaa geeshoo hindaraarinii,	ጌሾ ሆይ አታብብ፣
Yoo daraarte baalatti hindeebituu,	ካበብክ ቅጠል ላትሆን፣
Yaa suphoo hinmaraatinii,	ከገባህ አትበድ፣
Yoo maraatte qeerrotti hindeebitu.	ብታብድም ወጣት ላትሆን
3. Ijaarii kaa yaa Jimaa,	በርታና ገንባ አንተ ጅማ፣
Hamma Finfinnee jala geechutti,	ፊንፊኔ ሥር እስክትደርስ ፣
Maraadhu kaa yaa qaadhiimaa,	በይ እንግዲ እበጅ የታጨሽ፣
Hamma dhirsa kee jala geechutti.	እስክትጋብ ከባልሽ።
4. Adurreen biddeena hin nyaatuu,	ድመት አትበላም እንጀራ ፣
Hantuuta malee	አይጥ እንጂ፣
Ani jaaldhee sindhiisuu,	አልተውሽ ወድጄ ፣
Sinfuudha malee.	አገባሻለሁ እንጂ።
5. Tiifuu qabee Ammayya tiifuu qabe,	ያካፋ ጀመረ አመያ ያካፋ ጀመረ፣
Surree baafatee boraatii gatee,	ሱሪውን አውልቆ ትራሱን እንደጣለ፣
Walittii dhiibuu qabee,	ግፊያው ተጀመረ፣
Bade kan niitii dhabee.	ያላገባ ግን ተቸገረ፡፡
6. Yaa Eedsii dhibee hundaaf gooftaa,	አጅሬ ኤድስ የበሽታዎች አውራ፣
Abbaa warraa koo manatti naaf deebiFtaa?	ቤቴ መልስልኝ የእኔን አባወራ?

እነዚህ ዘፈኖች በ2006 ዓ.ም እና በ2007 ዓ.ም. በተለያየ ቦታ በተከበረው የጥምቀት ክብረ-በዓል እና ከጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ በታዳሚ ወጣቶች ከተዘፈኑ ዘፈኖች እንዲሁምበቃለ-መጠይቅ ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ ናቸው። የስድስቱንም ዘፈኖች ግጥም መልዕክት

ስንመለከት ጋብቻ በባህሉ የተከበረ መሆኑን ያሳያሉ። ጠቅለል አድርገን እነዚህን ስድስቱንም ዘፈኖች ከመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ስንመለከታቸው መረጃዎቹ በዋናነት ከአውዳዊ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ሲሆን ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው ደግሞ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል ከሚለው የ(Okpewho (1992:173) እሳቤ አኳያ የሚታዩ ናቸው። እያንዳንዱ ዘፈን ከመልዕክታቸው አኳያ በተናጠል መተንተን ይኖርባቸዋል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለውን ስንመለከት "እወድሻለሁ ካልክ በፊርማህ አረጋግጠህ አግባኝ እንጂ ከጋብቻ ውጭ ወሲብ አልፈልግም" የሚል መልእክት አለው። የዚህን ዘፈን መልእክት ስናይ ኮረዳዋ የጋብቻ ፍላጎቷን በዘፈን የገለጸችበት ሲሆን ይህንንም የዘፈነችው የጥምቀት ክብረ-በዓል በሚከበርበት ቦታ መሆኑ ብዙውን ጊዜ ለትዳር የሚፈላለጉ ወጣቶች ለጋብቻ የሚመራረጡበት ቦታ መሆኑንም ይጠቁማል። የጋብቻ ማረጋገጫው ፊርማ በመሆኑ ይህም የሚከወነው ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት በመሆኑ እወድሻለሁ ብቻ ዋጋ ስለሌለው በትዳር መተሳሰር እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ሲታይ ደግሞ ፊርማ የፍቅር ውል (ቃል ኪዳን መተሳሰሪያ) በመሆኑ ፋይዳው ቤተሰብን ለመመሥረትና ትውልድን ለማስቀጠል ይረዳል። ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ የጋብቻ ውል   አገልግሎቱ ከፍተኛ መሆኑን ያስገነዝባል።

ተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ደግሞ ካገባህ በኋላ ከንፈር ወዳጅ እስማለሁ ብለህ አትመኝ አርፈህ ተቀመጥ የሚል ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ነው። ይህም የሚያሳየን የከንፈር ወዳጅ የሚሳመው ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊትና በተወሰነ የዕድሜ ክልል መሆኑን ሲሆን ከጋብቻ በኋላ ልጃገረድን መሳም በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ተግባር መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ ከጋብቻ በኋላ የሚኖረው የፍቅር ግንኙነት ባል ከሚስት ሚስትም ከባል ጋር ብቻ መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ነው። በመሆኑም ሥነቃሉ በጋብቻ ላይ ተደራቢ የፍቅር ግንኙነት እንዳይኖር በማስጠንቀቅ ልቅ ወሲባዊ ግንኙነቶችን የመከላከል አገልግሎት አለው።

ተራ ቁጥር 3. ቃል ግጥም ደግሞ ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ነጻነት የሚሰጥ ነው። ይህም ያላገቡ ወንዶችም ሆኑ ልጃገረዶች በባህሉ መሠረት ከንፈር በመሳሳም ፍቅራቸውን መግለጽ የሚችሉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም በባህሉ መሠረት ከንፈር

ወዳጅ የሚሳመው ከጋብቻ በፊት እንጂ ከጋብቻ በኋላ አይደለም። ስለዚህ ባል እስክታገባ ድረስ በከንፈር ዙሪያ እንደፈለግሽ መሆን ትችያለሽ የሚል መልእክት አለው።

እዚህ ላይ የማህበረሰቡ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች በዕድሜ እና በደረጃ ገደብ እንዳለው እና ከዚያ ገድብ ውጭ የሚፈጽም ካለ በሥነቃል የሚወገዝ መሆኑን እንገነዘባለን። በዕድሜ ሲባል ከንፈር ወዳጅ ለመሳም በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ መሆን የግድ ነው። በወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሆነው ጋብቻ የፈፀሙ ከሆኑ ግን ስለ ከንፈር ወዳጅ ተግባር አይከወንም። ምክንያቱም የከንፈር ወዳጅ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ሆኖ ሳያገቡ ብቻ የሚከወን ተግበር በመሆኑ ነው። በሌላ መልኩ ሽማግሌ /አሮጊት ከንፈር ወዳጅ አለው/አላት ቢባል ከባህሉ ያፈነገጠ ተግባር በመሆኑ የሚያስቅ ነው።

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ዘፈን ከጋብቻ በፊት በፍቅር አብረው ከነበረችው ልጅ ጋር የበለጠ በጋብቻ ለመተሳሰር ያለውን ምኞት የገለጸበት ነው። ይህ ዘፈን በማህበረሰቡ ውስጥ ዕጮኛ በመያዝ የሚከወን የጋብቻ ዓይነት የሚመለከት ነው። በሌላ መልኩ መሠረታዊ የወሲብ ቲዮሪ እንደሚያመለክተው የሁሉም ፍጥረታት የወሲብ ባህሪይ ወሲባዊ እርካታ ማግኘት እና ዘርን ለመተካት (ለመራባት) ነው (Ember and Ember, 2003)። በመሆኑም በየትኛዉም ጊዜና ቦታ የሚገኝ የሰው ልጅ በአብዛኛው ከወሲብ ውጭ አይደለም። ከዚህ የምንገነዘበው የማህበረሰቡ እውቅት ከወሲባዊ ቲዮሪ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ነው።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የሚገኘው ጋብቻ ከሚፈጸምበት አንዱ እና ዋንኛው ሁለቱ ተጋቢዎች የግብረ-ስጋ ግንኙነት ፍላጎታቸውን የሚረካኩበት ነው። ከማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ አንጻር ሁሉም ማህበረሰብ ባህሉን፣ ወጉን፣ እምነቱን፣ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን መሠረት ያደረገ የራሱ ወሲባዊ አፈጻጸም ባህርይ እንዳለው Banks and Banks (2001) ያብራራሉ። ከዚህ አኳያ ይህ ዘፈን ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ወሲባዊ እርካታን እንደሚያስገኝላቸው ደስታን የሚፈጥር መሆኑን የሚገልጽ ነው። በመሆኑም ያላገቡትም ወደ ጋብቻ እንዲመጡ የሚገፋፋ ነው።

ከተራ 1 እስከ 5 ያሉት ዘፈኖች ካስተላለፉት ተመሳሳይ መልዕክት እና ካላቸው ትርጉም አኳያ ስንመለከት ከፋይዳዊ ቲዮሪ የሥነቃል አጠቃላይ ተግባር አኳያ የሚተነተኑ ናቸው። ይህም የጋብቻ ቃል ክዳን መተሳሰሪያ የፍቅር ውል ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። በሌላ መልኩ ወጣቶች በከንፈር ወዳጅነት መሳሳም የሚገባቸው ወደ ትዳር ዓለም ሳይገቡ መሆን እንዳለበት እና ይህም ከግብረሥጋ ግንኙነት ውጪ ሌላውን

የወሲብ ተግባር መፈጸም እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው። ይሁን እንጂ የግብረ-ስጋ ፍላጎታቸውን ማርካት ከፈለጉ ደግሞ በጋብቻ መተሳሰር እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው። ስለዚህ ከጋብቻ ውጭ የሚደረገው የግብረ-ስጋ ግንኙነት በባህሉ ነውር መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በመሆኑም ወጣቶች ይህንን ባህል ማክበር እንዳለባቸው በማስጠንቀቅ የሚያስተምሩ ናቸው። ስለዚህ አራቱም ዘፈኖች ትንታኔያቸው ከሥነቃል የማስተማር ተግባር አኳያ የሚገለጹ ሲሆን በሌላ መልኩ ከክልላዊ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ጠብቆ ከማቆየት እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር የሚታዩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 6 ላይ የሚገኝ ዘፈን በጋብቻ ላይ ከሌላ ሴት ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ለሚፈጽም ባል የተዘፈነ ነው። ለዚህም ሚስት የበሽታዎች ሁሉ ጌታ የሆነው ኤች አይ ቪ/ኤድስን ባሏን ወደ ቤቷ እንዲመለስላት የጠየቀችበት ዘፈን ነው። ይህም ኤድስ በአንድ በኩል የማህበረሰቡ ችግር ቢሆንም በሌላ መልኩ ደግሞ ሰዎች ከልቅ ግብረሥጋ ግንኙነት እንዲጠነቀቁ ያደርጋል የሚል መልዕክት አለው።

ይህ ዘፈን ከአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪ በተጨማሪ ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች አኳያ በተምሳሌታዊ፣ በክልላዊ፣ በለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪዎች የሚታይ ነው። ይህንንም ዘርዘር ባለ ሁኔታ ስንመለከት ከተምሳሌት አንጻር የኤድስ በሽታ እንደ ጌታ መታየትና ከሁሉም በላይ የበሽታዎች ዋና ዳኛ በመሆኑ በትዳር ላይ ለሚወሰልት ባል አቤቱታ ማቅረቢያና ፍርድ የሚገኝበት መሆኑን ያመለክታል። ከክልላዊ እና ለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪዎች አኳያ ደግሞ ኤድስ ድሮ ያልነበረ በቅርብ ዘመን የመጣ በመሆኑ የቱለማ አሮሞ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ዓለም ማህበረሰብ ጋር በፈጠረው መስተጋብር የበሽታው ተጠቂ መሆኑን ያመለክታል።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተተነተኑ ዘፈኖች በቱለማ ኦሮሞ የጋብቻን አስፈላጊነት ጠንከር ባለ ሁኔታ የሚያስገነዝቡ እና ባህሉን የሚፈታተኑ ጉዳዮችን በሥነቃል ማህበረሰቡን ማስተማር እንደሚቻል ያሳዩ የሥነቃል ዓይነቶች ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ የከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ መረጃዎችን ትንታኔ እንመለከታለን።

6.2 የከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባና ትንተና

በዚህ ሥር የተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች 71 (5 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 66 ዘፈኖች)[76] ናቸው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በአራቱም የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ሲሆን በተለይ በምልከታ የተገኙት በርካታ ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች በአብዛኛው የፍቅር ስሜት መግለጫ የሆኑ አባበሎች እና ዘፈኖች ናቸው። እነሱም ከንፈር ወዳጅነት በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚፈጸም መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። ዘፈኖቹ በወጣትነት ዘመን ከንፈር መሳሳም የፍቅር መግለጫ መሆኑን፣ የከንፈር ወዳጅ ናፍቆት ሌት ተቀን እንደሚያንገበግብ የሚገልጹ እና የከንፈር ወዳጆቹ እርስ በእርሳቸው የሚሞጋገሱበት ናቸው። ይህንን በሚመለከት የሚፈቃቀሩ ሰዎች የፍቅር ስሜታቸውን ከሚገልጹበት መንገድ አንዱ የፍቅር ዘፈኖች መሆናቸውን Legman (1990)እና Okepew (1992) Workineh Kelbessa (2014) ይገልጻሉ።

በሌላ መልኩ በከንፈር ወዳጅ መካከል Safuu dubrummaa eeguu (የልጃገረድነትን ወግ ማክበር እና መጠብቅ) ግዴታ መኖሩን የሚያመለክቱም ይገኙበታል። ከልጃገረድ ጋር ወሲብ መፈጸም በባህሉ safuu (**ነውር**) መሆኑን የሚገልጹ ም ይገኙበታል። ይሁን እንጂ የዘመኑ ከንፈር ወዳጅ ከከንፈርም አልፎ ወደ ግብረ-ስጋ ግንኙነት መሄዱን በማመልከት ዲርጊቱን የሚያወግዙና መጥፎ ጎኑን በማሰየት በአሁኑ ዘመን መሳሳም ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጥ መሆኑን የሚመለከቱ ናቸው። እዚህ ላይ የዘመኑ ከንፈር ወዳጅነት የግብረ-ስጋ ግንኙነትን እንደሚያካትት በቃለ-መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች የገለጹትን በሥነቃሉም መደገሙ በመረጃ አቀባዮች እና በምልከታ ከተለያዩ አውዶች የተገኙ መረጃዎች ተመሳሳይ መሆናቸውን ያሳያሉ። በሌላ መልኩ ነባሩ ባህል እየተለወጠ መምጣቱንም ያመለክታሉ።

የከንፈር ወዳጅን አስመልክተው ከመረጃ አቀባዮች እና ከልዩ ልዩ ክብረ-በዓላት ላይ ከተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ለጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ካለቸው ቅርበት ለትንተና የተመረጡ 21(3 ምሳሌያዊ ንግግር እና 18 ዘፈኖች) ናቸው። እነሱም እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

ሠንጠረዥ 10. የከንፈር ወዳጅን የሚመለከት ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

[76] አባሪ 6፡- በከንፈር ወዳጅ ሥር የተመደቡትን የሥነቃል ዓይነቶችን ዝርዝር ይመልከቱ።

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Kan dhungoo hin beekne furrii nama faala.	አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል።
2. Qalbiin nadheenii tokko,	የሴት ልብ አንድ ናት
tokkiittiin sunuu dhungatan ni baddi.	እሷም ስትሳም ትጠፋለች።
3. Warri boruuf walabdatu,	ለነገ የሚተሳሰቡ ሰዎች፣
Dhagaa walitti walhindarbatu.	እርስ በርስ ድንጋይ አይወራወሩም።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተገኙት የከንፈር ወዳጅን በሚመለከት የሚያውቁትን ምሳሌያዊ ንግግሮች እንዲናገሩ ለመረጃ አቀባዮች ለቀረበ ጥያቄ የሰጡት መልሶች ናቸው (አቶ ደረጀ መኮንን፣ አቶ ጣሰው በየነ፣ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም.)። ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በከንፈር ወዳጅ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በመሆናቸው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ካተኮሩበት ጉዳይ አኳያ በመልዕክታቸው የተለያዩ ናቸው። በመሆኑም የእያንዳንዱ ትንተኔ በተናጠል ቀርቧል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ስንመለከት የመሳም እውቀት የሌለው ሰው ተሳሚዋን በንፍጥ እንደሚያበላሽ ይገልጻል። ስለዚህ አንድን ነገር ከማድረግ በፊት ስለ ጉዳዩ ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። የመተንተኛ ቲዮሪን በሚመለከት ምሳሌያዊ ንግግሩ በመስከ መረጃ አሰባሰብ ወቅት በቃለ-መጠይቅ የተገኘ በመሆኑ ከአውዳዊ ተዮሪ አንጻር የሚታይ ነው። ይህም የዚህን ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክት ስናይ አንድን ጉዳይ ለማከናወን በመጀመሪያ ደረጃ ስለጉዳዩ እውቀት ሊኖረን እንደሚገባ እና ይህ ካልሆነ ግን ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንደምንጎዳ ይነግረናል። በመሆኑም ከዚህ ምሳሌያዊ ንግግር የምንገነዘበው በእውቀት ላይ የተመሠረተ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያናል። ስለዚህ ይህ ሥነቃል ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ የማህበረሰቡን ወግና ባህል ማሳወቅን ይመለከታል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ ያለውን ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉም ስናይ በመሳሳም ተግባር ውስጥ ሴት ቶሎ ወደ ስሜት እንደምትገባና ከንፈሯን ለሳመ ሁሉ ልቧን እንደምትከፍት ያመለክታል። በሌላ መልኩ የልቧ ቶሎ መከፈት ከከንፈርም አልፎ ወደ ግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደምታመራ የሚያሳይ ነው። ከአውዳዊ የመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ሲታይ ሥነቃሉ የተገኘው በዚህ ጥናት ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቱ በዘመነ ኤች አይ ቪ/ኤድስ

እንዴት ይገለጻል? ከሚለው ጥያቄ ጋር ተያይዘው የተሰጠ መልስ[77] ነው። ይህም መረጃ አቀባዮቹ ከሰጡት መልስ አንጻር ድርጊቱ ለግብረ-ስጋ ግንኙነት በር የሚከፍት ተግባር ነው። ስለሆነም ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ሲታይ ሴቶች ቶሎ ብለው ወደ ግብረ-ስጋ ግንኙነት ስሜት ውስጥ እንዳይገቡ የሚያስጠንቀቅ ነው።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የሚገኘውን አባባል መልዕክት ስንመለከት ለወደፊት አብረው የሚኖሩ ሰዎች አንዱ ባንዱ ላይ ችግር ፈጣሪ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም በወጣትነት ዘመን በከንፈር ወዳጅነት አብሮ የነበሩ ወጣቶች ለወደፊቱ ኑሮአቸውም መተሳሰብ እንዳለባቸውና አንዱ አንዱን እንዳይጎዳ ጥንቃቄ የተሞላበት ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው የሚያስተምር ነው። ይህ ማለት ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው በአንዱ ሰው ላይ ድንጋይ ቢወረውር ልፈነክተው፣ ወይም በአንዱ የሰውነት አካል ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ አንድ ወንድ ወጣት የከንፈር ወዳጁን ልጃገረድ በወሲብ ስሜት ተነሳስቶ ከከንፈር አልፎ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ቢፈጽም ልጅቷን ላልተፈለገ እርግዝና ሊዳርጋት ይችላል።ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በዚህ ጥናት ምዕራፍ አምስት ውስጥ (አበበ ነጋሽ)[78] ከሰጠው አስተያየት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ሥነቃሉ የመረጃ አቀባዩን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው።

በመሆኑም ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ከማህበረሰቡ ባህል እና ወግ የሚያፈነግጡ ወይም ለማፈንገጥ ያቀበቀቡትን ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ ለማድረግ የማስተማር አገልግሎት አለው። ከዚህ በመቀጠል ከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ ዘፈኖችን መልዕክት ከትንታኔያቸው አኳያ በዝርዝር እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 11. ከንፈር ወዳጅን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Salaalee keessaa wal ar’aa motorrii,	ሰላሌ ከተማ ይሯሯጣልሞተር ፣
Xuxii nadhungadhuu,	ምጥጥ አድርገሽ ሳምኝ፣
nama gabbisaa gororrii.	በወለላው ማር ከንፈር ።

[77] በአሁኑ ዘመን የከንፈር ወዳጅነት ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል። (አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)

[78] እኔ በበኩሌ ከከንፈር ወዳጄ ጋር በምንሳሳምበት ወቅት ራሴን መቆጣጣር አልችልም። ጥረት የማደርገው የአጭር ጊዜ ፍላጎቴን ለማሟላት ነው። ስለዚህ የተለያዩ ችግሮች ውስጥ ልገባ እችላለሁ። ያልተፈለገ እርግዝና መፍጠር ወይም በግብረ-ስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ ልዩ ልዩ በሽታዎች ልጋለጥ እችላለሁ። በተለይም እስካሁን መድኃኒት ላልተገኘለት በሽታ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የመያዝ ኢጋጣሚ ሁሉ ይኖራል አበበ ነጋሽ (ጥር 23፣ 2007 ዓ. ም.)።

2. Salaalee keessaa wal hin ar'uu motorrii,	ሰላሌ ከተማ አይሯሯጡም ሞተር፣
Xuxee sindhungadhuu bashitaa fidee gororrii.	በሽታ አምጥቷልና መሳሳሙ ይቅር።
3. Bulloo soor naan jettaa,	ቡሎ ፈረስ ቀልብ ትይኛለሽ
Akkamittan sooraa farda kanaa,	እንዴት ልቀልብ ይህን ፈረስ፣
Dhungoo soomii naan jettaa,	መሳምን ተው ትይኛለሽ
Aakkamittan soomaa damma kana.	እንዴት ልተው ይህን ማር።
4. Ciwu ciwu jitte sinbirroonii,	ጭው ጭው አለች ወፊቷ፣
Aadaa duubatti hafaadhaa,	ኋላ ቀር ባህል ነውና፣
Yaa hafu dhungoon jette micayyooni.	መሳም ይቅር አለች ልጅቷ።
5. Hincabu seete hincaccabaa galbaanis	አይሰበር መሰለህ ይሰባበራል ገለባው፣
Dhungadhuu gadi nadhiisii,	ሳም አርገህ ልቀቀኝ፣
Anuma eeggataa kan biraatis,	ይጠብቃኛል ተረኛው።
6. Micayyoo xinnoo yaa maarchadisii,	አንቺ ትንሽ ልጅ መርቸዲስ፣
Dafii dhungadhuu gadi nadhiisii.	ቶሎ ሳመኝና ልመለስ።
7. Kutaa kee yaa Foolisii,	አንተ ፖሊስ ኩታህን፣
Qarqara lamaan kuula dhoofsisii,	አሰፋ ሁለቱን ጫፍ በጥለት፣
Simalee shani qabaa,	ካንተ ሌላ አሉኝ አምስት፣
Nama simalee hin qabne dorsisii.	አስፈራራ ካንተ ውጭ የሌላት።
8. Yaa saamunaa Shaggarii,	የሸገር ሣሙና ፣
Wayyaa hin addeessuu malee,	ልብስ አያፀዳም እንጂ፣
Gororrii shaggeedhaa dammaa,	የቆንጆ ሊያጭ ማር ነው፣
Nama hin macheessuu malee.	አያስክርም እንጂ።
9. Qaqallateeti yaati hundee dhangaggoo,	ቀጫጭን ሆኖ ይበቅላል የእሬት ሥር
Dammaa nadhii caala gororrii dargaggoo.	ከወለላ ማር ይበልጣል የጎረምሳ ከንፈር።
10. Dagamii asmaraan koo,	ደገም ነው አዝመራዬ፣
Guyaa sibiraan oolaa,	የቀኑማ ካንቺው ጋር ነው ውሎዬ፣
Halkan abasaan koo.	የሌሊቱ ነው እንጂ አበሳዬ።
11. Ijaarratte sinbirron,	ወፏ ቤቷን ሰራች፣
Kan baddaan ciraaroo jalli mukaa,	ከላይ በጭራሮ ከስር በእንጨት፣
Najaallattu maajettaa,	አትወጅኝም ማለትህ ከምን የመጣ ነው፣
Siifan halkan taa'ee guyyaa mugaa.	ላንተ ነው ሌሊት ሳልተኛ ቀን

	የማንቀላፋው።
12. Aqaaqiin hin ceesiisuu,	አቃቂ አያሻግርም
Suuta suuta deemii yaa Abbabaa;	ቀስ ብለህ ተሻገር አበበ፤
Waraqataa naa ergii,	ደብዳቤ ላክልኝ
Ogguman siyaadadheen nabbabaa.	አንተን ሳስታውስ እንዳነብ፤
Warqata nabbabee,	ደብደቤውን አንብቤ
Halkanii guyaa ciisa dadhabee.	ሌት ተቀን አልተኛ ተንገብግቤ፤
Waraqata yaa erbee,	ደብደቤማ ምን ልረባ፣
Obsi yaa garaa Waaqa sitti erge.	እግዜር እንደመጣብህ ቻለው ሆዴ አትባባ።
13. Abbaan Talkee torbaa,	አባ ተክሌ ሰባት ነው፣
Ttokko itti awalanii,	አንዱን ይቀብሩበታል፣
Dhibamni koo sumaa,	አለወቁልኝም እንጂ፣
Natti walaalanii.	በሽታዬ አንተው ሆነሃል።
14. Salaalee mannii hin jiruu,	ሰላሌ ውስጥ ቤት የለም፣
Maali kan Salaalee ibsaa ibsuu?	ማነው ከሰላሌ የሚያበራው እሳት?
Keechan warri akkamii?	የናንተ ቤተሰብ እንዴት ናቸው፣
Keenya akka loonii nama tiksu.	የኛዎቹማ ይጠብቁናል እንደ ከብት።
15. Rigaa namurii jettaa,	መፋቂያ ቁረጥልኝ ትላለህ፣
Akka waan rigaan hurufaa marguu,	መፊቂያ ከሜዳ እንደምገኝ ፣
Gabaa koottu naan jettaa,	ገበያ ነይ ትለኛለህ፣
Anammoo gabaa warri nanerguu.	ቤተሰብ እኔን ወደ ገበያ አይልከኝ።
16. Yaa harroota Sulultaa,	እናንተ የሱሉልታ አህዮች
maaliidhaaf odaa jala yaatanii;	ለምንድነው በአዳ ሥር የሚትሔዱ፤
Keechani zamznnii dabree,	የናንተ ዘመን አልፏል፣
keenyaa maaf qunnaadhan safartanii.	የኛን ለምንድነው በቁና የሚትሠፍሩ።
17. Sulults roobee jiraa,	ሱሉልታ አካባቢ ዘንቧል፣
safara Tulluu hindabarree malee;	አላለፊም ግን የቱሉን ሠፈር፤
Jaalala dhungoo argee,	የአልጋ ላይ ፍቅር ባላይም፣
jaalala rafuu hin agarree malee.	አይቻለሁኝ ከንፈር።
18. yaa Lataa yaa Lataa of eeggdhu intlaa,	ለታ ሆይ ለታ ሆይ አንቺ ልጅ ተጠንቀቂ ፣
Wadaajiidha jedheeti sigalaafataa.	ከንፈር ወዳጅ ነው ብሎ እንዳያበላሽሽ።

እነዚህ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 18 የተገለጹት ዘፈኖች በልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የተገኙ ናቸው። ይህም ለሱሉልታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የከንፈር ወዳጅን አስመልክተው በአካባቢያቸው የሚዘፈኑትን ዘፈኖች በጽሑፍ እንዲያቀርቡ በመጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልሶች፣ በቃለ መጠይቅ ከመረጃ አቀባዮች እና በምልከታ ወቅት ከልዩ ልዩ የሥነቃል መከወኛ አጋጣሚ ክብረ-በዓላት (እንቁጣጣሽ፣ የመስቀል እሬቻ፣ ጥምቀት እና ሠርግ) ላይ የተሰበሰቡ ናቸው።

የእነዚህን ዘፈኖች አጠቃላይ መልዕክት ስንመለከታቸው በቱለማ ኦሮሞ የከንፈር አሳሳም ባህል ዙሪያ ወጣቶች ያላቸውን የፍቅር ስሜት በዘፈን የገለጹበትን የሚያሳዩ ናቸው። ሁሉም ዘፈኖች ከመገኛቸው አኳያ በአውዳዊ ቲዮሪ ሲተነተኑ ከአገልግሎታቸው አንጻር ደግሞ በተግባራዊ ቲዮሪ ተተንትነዋል። አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ደግሞ በዲጋፊ ቲዮሪዎችም ተተንትነዋል። በዚሁ መሠረት ካላቸው ተመሳሳይነት የተወሰኑ ዘፈኖች በጥምር (በጋራ) የተገለጹ ሲሆኑ ከልዩነታቸው አኳያ ደግሞ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር በተናጠል ተተንትነዋል።

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ያሉትን የዘፈን ግጥሞች ስናይ ከንፈር ወዳጅን አስመልክቶ ተጓዳኞቹ በመሳሳም ዙሪያ ያላቸውን ስሜት በዘፈን ምልልስ የገለጹበትን የሚመለከቱ ናቸው። በተራ ቁጥር 1 ላይ የተገለጸው የዘፈን ግጥም ስንመለከት የከንፈር ወዳጁ ምጥጥ አድርጋ ብትስመው በለሃጯ እንደሚወፍር ይገልጽላታል። በተራ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ እሷ በምላሿ ችግሩን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር በማያያዝ ከንፈር መሳሳም በሽታ ማምጣቱን በመጥቀስ ከሳመችው በቫይረሱ የመጠቃት አጋጣሚ መኖሩን ስጋቷን በማሳወቅ ለመሳም ፈቃደኛ አለመሆኗን ትገልጻለች። በተራ ቁጥር 3. የዘፈን ግጥም ደግሞ እሱም በተራው በተምሳሌታዊ አነጋገር መሳምን ተው ትይኛለሽ ይህንን ማር እንዴት እተዋለሁ ይላታል። በተራ ቁጥር 4. የዘፈን ግጥም እሷም በተራዋ ዘመናዊ አስተሳሰቧን ለመግለጽ መሳሳም ኋላ ቀር ባህል በመሆኑ ይቅር በማለት በመሳሳም ዙሪያ ሲከራከሩ እናያለን። ከእነዚህ የምንገነዘበው ወጣቶቹ ቀድሞ የነበረውን ባህላዊ የፍቅር ግንኙነታቸውን እንደ ድሮ ለማከናወን በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከሰት ምክንያት ችግር የተፈጠረባቸው መሆኑን እንረዳለን። ይህም በሽታው በወጣቶች ላይ ሥጋት ማሳደሩን ይጠቁማል። የተጓዳኝ

ጥናታዊ ዳሰሳም በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እየተጠቁ ያሉ ወጣቶች መሆናቸውን ያሳያል (Lisa et al, 2006)።

ከተራ ቁጥ 5 እስከ 7 ያሉትን ስንመለከት ወጣቶቹ ከአንድ በላይ የከንፈር ወዳጅ ያላቸው መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። በመሆኑም በተራ ቁጥር 5 ዘፈን ውስጥ እንደተገለጸው ሌላ ተረኛ የሚጠብቃት በመሆኑ ቶሎ ስሞ እንዲለቃት ስትጠይቅ እሱም በተራ ቁጥር 6 ዘፈን ላይ እንደተጠቀሰው ለሌላ ተጣድፎ ቶሎ ሳሚኝና ልቀቂኝ ይላታል። በተራ ቁጥር 7 ዘፈን ደግሞ በፍቅር ዓለም ውስጥ ግጭት ሲፈጠር ካንተ/ካንቺ ሌላ አለኝ በማለት አንዱ አንዱን በዘፈን ያስፈራራል።

እነዚህ ዘፈኖች የሚያሳዩት ጓደኛዋ ከሱ ሌላ ተጨማሪ የከንፈር ወዳጅ እንዳላት ሁሉ እሱም ሌላ የከንፈር ወዳጅ ያለው መሆኑ የተገለጸበት ነው። እንደዚህ ዓይነቶቹ የፍቅር ግንኙነቶች በማህበረሰብ ውስጥ እንዳሉ በቃለ መጠይቅ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች[79] ይጠቁማሉ።

በተራ ቁጥር 8 እና 9 ላይ የሚገኙ ዘፈኖች የከንፈር ወዳጅ ጣፋጭ መሆኑን ለሀጭን ከማር ጋር አመሳስለው የተገለጸበት ነው። በእነዚህ ዘፈኖች አንዱ አንዱን በማሞጋገስ የፍቅር ስሜታቸውን ገልጸዋል። ይህም ወንዱ ለከንፈር ወዳጁ ያለውን የፍቅር ስሜት ሲገልጽ ጠጅ ከማር እንደሚሠራ እና እንደሚያሰክር ሁሉ ከንፈሯ ማር ቢሆን የማያሰክር ወይም ለጉዳት የማይሰጥ መሆኑን የገለጸበት ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ሴቷም የከንፈር ወዳጇ ለሀጭ ከወለላ ማር እንደሚበልጥ የገለጸችበት ነው። እዚህ ላይ ማር እና ለሀጭን ከማመሳሰል አኳያ በተምሳሌታዊ ቲዮሪ የሚተነተን ነው። ተምሳሌት ገላጭ የሚሆነው በቅርፁም ይሁን በይዘቱ ባዘለው ማህበረ ባህላዊ ፍቺ ጭምር እንደሆነና ቁሳዊ ብቻ አለመሆኑንና ረቂቅ ነገርም (Physical and Abstract) ተምሳሌትነት ሊኖራቸው እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ (Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, Laurence A. Basirico: 1993)። ይህም ማለት ማር ጣፋጭ እንደ መሆኑ መጠን የወጣትነት ፍቅርም ልክ እንደ ማር ጣፋጭ መሆኑን እነዚህ ዘፈኖች ያመለክታሉ።

[79] (ጋዲሳ አዱኛ መገርሳ ሁንዴ፣ ቦንቱ ታደሰ እና ፋኖሴ ጋዲሳ ኀዳር ፲ ቀን 2007 ዓ.ም)።

ከተራ ቁጥር 11 እስከ 13 ያሉ ዘፈኖች በከንፈር ወዳጅነት ፍቅር ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ቀን አብረው ቢውሉም የሌሊት አዳራቸው ለየብቻ በመሆኑ ሌሊት በናፍቆት እንቅልፍ እያጡ ማዳራቸውን የተገለጹበት ነው። በተለይም በተራ ቁጥር 12 ላይ የተገለጸው ዘፈን የፍቅር ናፍቆት ከሚገለጽበት መንገድ አንዱ ደብዳቤ በመሆኑ የተላከው ደብዳቤ ሌት ተቀን እረፍት እንደነሳት/እንደነሳው በመግለጽ የመጣውን የናፍቆት ጣጣ ከመቻል ሌላ አማራጭ እንደሌለ የተገለጸበት ነው። በማያያዝም በተራ ቁጥር 13 ላይ የሚገኘው ዘፈን በሕመም ለመያዙ/ዟ ሰበቡ የእሱ/ሷ ፍቅር መሆኑ የተገለጸበት ነው።

ከተራ ቁጥር 14 እስከ 18 ያሉ ዘፈኖች ስንመለከታቸው በተለያዩ ሁኔታዎች ይገለጹ እንጂ ተመሳሳይነት አላቸው። ይኸውም በሴቷ ወገን የቤተሰብ ቁጥጥር በዝተው ልክ እንደ ከብት የሚጠብቃአቸው መሆናቸውን በመግለጽ በወንዱ በኩል ያለውን ሁኔታ ለማወቅ የተጠየቀበት መንገድ ነው። በማያያዝም በገበያ ቀን እንኳን እንዳይገናኙ ቤተሰብ ገበያ እንደማይልካት ገልጻለች። ገበያ[80] ለከንፈር ወደጅ መገናኛ ቦታና የመሳሳሚያ አጋጣሚ ነው። (በዚህ ጥናት ውስጥ ገጽ 141 ይመልከቱ)።

በተራ ቁጥር 16 ዘፈን ላይ እንደተገለጸው የቁጥጥሩን መብዛት በመቃወም ወላጆች ድሮ የራሳቸውን ጊዜ በሚገባ ተጠቅመው የፍቅር ስሜታቸውን እንዳሳለፉ በማስታወስ አሁን የእኛን ጊዜ በስፍር አትስጡን የሚል ወቀሳ ያዘለ መልዕክት አለው። በመሆኑም የቁጥጥሩ መብዛት ወደ ግብረ-ስጋ ግንኙነት ፍላጎትም ወስዷአቸው ከከንፈር ወዳጅነትም አልፎ የመኝታ ፍቅር እንደናፈቃቸው በተራ ቁጥር 17 ላይ ያለው ዘፈን ያሳያል። ይሁን እንጂ በራሳቸው በወጣቶቹ አንደበት የቤተሰብ ቁጥጥር ለበጎ መሆኑን በከንፈር ወዳጅነት ሰበብ ልጃገረድነቷን እንዳታስወስድ በተራ ቁጥር 18 ላይ ያለው ዘፈን የማስጠንቀቂያ መልዕክቱን ያስተላልፋል።

እነዚህን ዘፈኖች በሙሉ ከመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ስንመለከታቸው በተለያየዩ አውዶች ውስጥ ይገለጹ እንጂ ባዘሉት መልዕክት ተመሳሳይነታቸው በከንፈር ወዳጅነት ዙሪያ ከባህሉ የሚያፈነግጡትን ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ በልዩ ልዩ መልኩ የሚያስተምሩ ናቸው።

---

[80] የምንሳሳምበት ቦታ ገበያ ስትወጣ፣ ውኃ በምትቀዳበት፣ ኩበት በምትለቅምበት ስንደዶ በምትለቅምበት እና ጫካ ውስጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የምንሳሳመው በእንቁጣጣሽ፣ በመስቀል እና በጥምቀት ክብረ በዓላት ሲሆን ከዚም በተጨማሪ አመቺ በሆነ በየትኛም ጊዜ እና ቦታ እንሳሳማለን። ቶሎሳ መርጋ (ጥር ፲፩ ቀን 2007 ዓ.ም)።

በመሆኑም አብዘኞቹ ዘፈኖች ባህሉን የሚገልጽ በመሆናቸው ባህሉን ከመጠበቅ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር ከክልላዊ ቲዮሪ አንጻር የሚታዩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ (በተራ ቁጥር 2 እና 4) ላይ የተገለጹት በመሳሳም ዙሪያ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ በወጣት ሴቶች ላይ የፈጠረውን ስጋት፣ ጭንቀት እና ሀዘን የሚመለከት በመሆኑ ከሥነልቦና ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። በተራ ቁጥር 17 እና 18 ላይ የተገለጹት ደግሞ ከለውጥ እና ቀጣይነት ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው።

በመሆኑም ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ የእነዚህ ዘፈኖች ፋይዳ የከንፈር ወዳጅነቱ ባህል እየተለወጠ በመምጣቱ ወጣቶች ወደ ግብረሥጋ ግንኙነት እንዳያመሩና በኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዳይጠቁ እያስጠነቀቁ የሚያስተምሩ ናቸው። በአጠቃላይ የከንፈር ወዳጅነት በዚህ ዘመን አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚጠቁሙ ናቸው። በተለይም የከንፈር ወዳጅነቱ ቀድሞ የነበረው ባህላዊ አፈጻጸሙ እየተለወጠ በሚገኝበት እና ኤድስ ባለበት ዘመን አደጋ እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው።

በመሆኑም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ዘፈኖች በሙሉ በዋናነት ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ የቀድሞውን ከንፈር ወዳጅነት ባህላዊ ወግ የሚያስተምሩ ሲሆኑ ከለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ አኳያ ደግሞ በጥንቃቄ ላይ የተመሠረተ ፍቅራዊ ግንኙነት መኖር እንዳለበት የሚያስጠነቅቁ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል ውሽማን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ትንተኔ እንመለከታለን።

6.3 ውሽማን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና

ውሽማን በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች 73 (14 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 59 ዘፈኖች)[81] ናቸው። እነሱም በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች በአንድ በኩል ድብቅ ወሲባዊ ግንኙነቶችን የሚያሞግሱ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ይሄንኑ የሚነቅፉ ናቸው። በድብቅ ወሲብ መፈጸሚያ ቦታዎች አልቤርጎዎች መሆናቸውን የሚገልጹ ሲሆን ከመረጃ አቀባዮች[82] የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። በሌላ መልኩ ከትዳር ጓደኛ ይልቅ ወሲባዊ እርካታ ከውሽማ የሚገኝ መሆኑንና ይህም ለትዳር መፍረስ ምክንያት መሆኑን የሚገልጹ ይገኙበታል። በተጨማሪም ውሽምነት ከጥቅም እና ሙስና ጋር የተያያዘ   መሆኑን የሚያመለክቱ ዘፈኖችም አሉበት።

---

[81] አባሪ 6፡- በውሽማ ሥር የተመደቡትን የሥነቃል ዓይነቶች ዝርዝር ይመልከቱ።
[82] (አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ ወ/ሮ አረጋሽ ደበሌ እና አቶ ጣሰው በየነ)።

ድብቅ ወሲብ አንዱ ሰው ከብዙ ሰዎች ጋር የሚፈጸም ተግባር በመሆኑ ለልዩ ልዩ የአባለዘር በሽታዎች እና ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት ምክንያት እንደሆነ Legman (1962)፣ Flemming (1997) እና Kachingwe (2005) ይገልጻሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከኤርሚያስ ሥዩም (2006) የተገኘውም መረጃ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው።

ከዚሁ አኳያ በውሽማ ሥር ከተመደቡት የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ለትንታኔ የተመረጡ 26 (8 ምሳሌታዊ ንግግር እና 18 ዘፈኖች) ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 12. ውሽማን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Harkaan idea sanyoon nama xixa.	በገዛ እጅ እዳ የውሽማ ቁጣ ።
2. Abeet yaa bara sanyoon dhanee, dhirsi araarsa.	ዘመነ ግልቢጦ ውሽማ ደብዳቢ፣ ባል አስታራቂ።
3. "Abeetii yaa jaalala lafa hin taane galcheeti nama salphisa." Jette intalli.	"አቤት! ፍቅር አይገቡ ቦታ አስገብቶ ሰውን ያዋርዳል።" አለች ልጂቷ።
4. "Salphoo mana ishee hin dhaqani, Mana namaati dhufti. " jette niitiin masaanuudhaaan.	‹‹የማታፍር ከቤቷ አይሔዱም፤ የሰው ቤት ትመጣለች።›› አለች ሴትዮዋ ጣውንቷን።
5. Peejoo argitee galtee dhirsa jibbite	የሰው ፔጆ አይታ፣ ባሏን ጠላች ገብታ።
6. Sanyoo argannaan dhirsa jibbite.	ውሽማ ስትይዛ ባሏን ጠላች።
7. "Afaan kee malee, afaa kee hin agarree." Jettee masaanuun.	"ምላስሽን እንጂ፣ ምንጣፍሽን አለየሁም።" አለች ጣውንቷን።
8. Daandii dhokattuu fi nadheen soofattu, Dargaggeessa ollaatuu beeka.	አሳቻ መንገድንና የምታንቋልጥ ሴትን የሚያውቅ የሰፈሩ ጎረምሳ ነው።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው በቃለ-መጠይቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከመረጃ አቀባዮች[83] የተገኙ ናቸው። እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች

[83] (አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ጠጂቱ ቂጠታ፣ አቶ አበበ ጀቤሳ እና ወ/ሮ ደብሪቱ ሞረዳ ጥር 8 ቀን 2007 ዓ.ም)።

በተለያየ አገላለጽ ይቅረቡ እንጂ አንዳንዶቹ ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም እንደየመልእክታቸው እና ትርጉማቸው ተመሳሳይነት በጋራ እና በተናጠል ተተንትነዋል። በዚሁ መሠረት በተራ ቁጥር 1 እና 2፣ 3 እና 4፣ 5 እና 6፣ ላይ ያሉት በአንድነት የተተነተኑ ሲሆኑ ተራ ቁጥር 7 እና 8 ላይ የሚገኙት ለየብቻቸው ተተንትነዋል።

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ያሉትን ስንመለከት በገዛ እጇ ያመጣችው ውሽማ እንደ ተቆጣት እንዲሁም እንደደበደባት እና ባል ደግሞ አስታራቂ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህም ከአካላዊ ወይም ሥነልቦናዊ ቅጣት አንጻር ያለውን ጉዳት ያመለክታሉ። ከዚህ የምንረዳው ሰዎች ለወሲባዊ እርካታ ብለው በገዛ ፍላጎታቸው በሚፈጽሙት ወሲባዊ ግንኙነት ለአካላዊ እና ሥነልቦናዊ ጥቃት የሚያጋልጣቸው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። በባህሉ መሠረት ባል እንጂ ውሽማ ተቆጭ ወይም ተደባዳቢ አይደለም። የሚያስገርመው ደግሞ ውሽማው ከሰው ሚስት ጋር በድብቅ የግብረሥጋ ግንኙነት ከመፈጸምም አልፎ ደብድቧት ባል አስታራቂ የመሆኑ ጉዳይ ከባህሉ ያፈነገጠ ተግባር ነው። በሌላ መልኩ እንደዚህ ዓይነቱ ተግባራት በአሁኑ ዘመን ከልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱ በሽታዎች በተለይም ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጣቸው እና ለበለጠ ጉዳት የሚዳርጋቸው መሆኑን ያመለክታል።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ የተጠቀሱትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንመለከት ውሽምነት የሚያዋርድ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ በድብቅ የሚፈጸም ወሲብ በመሆኑ ግንኙነቱ በታወቀ ጊዜ ውርደት ያስከትላል። በቃል (በንግግር) ከሚደርስ ውርደት ባሻገር አካላዊ ጉዳትም ያደርሳል። በዚህ የተነሳ በማህበረሰቡ ውስጥ በዚህ ጉዳይ በሚፈጠሩ ግጭቶች ማህበራዊ ቀውሶች ይፈጠራሉ። በሌላ መልኩ በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ባለበት ዘመን በሚያደርሰው ጉዳት ማህበራዊ ቀውሱን ያባብሳል።

በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የሚገኙትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንመለከት ውሽምነት ከኢኮኖሚያዊ እና ወሲባዊ ጥቅሞች ጋር የተያየዘ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህም ፔጆ መኪና ያለው ውሽማዋ ገንዘብ ወይም ሌላ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ስለሚሰጣት ባሏን መጥላቷን የሚያመለክት ሲሆን "ውሽማ ስታገኝ ባሏን ጠላች" የሚለው አባባል ውሽማ ወሲባዊ ፍላጎቷን ስለሚያረካላት ለባሏ ግድ የሌላት መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ውሽምነት በጋብቻ ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ያመለክታል። በሌላ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ለኤች አይ ቪ/ኤድስም ያጋልጣል።

በተራ ቁጥር 7 ላይ ያለውን ምሳሌያዊ ንግግር ስናይ ሚስት ጣውንቷን መስደቧን ነው። “ምላስሽን እንጂ ምንጣፍሽን አላየሁም።” ማለቷ ባሌን ቀምተሽ እኔን እንዳይመቸኝ አድርገሻል እና ምንም ጥቅም የለሽም ማለቷ ነው። አለመመቸቱ በወሲባዊ እርካታ ወይም በኢኮኖሚያዊ መልኩ የደረሰባትን ጉዳት የገለጸችበት ነው። ምክንያቱም ባሏ ወደ ውሽማው ስለሚያደላ ሚስቱን በመንከባከቡ በኩል ችላ ማለቱን የገለጸችበት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ጣውንቷ ምላስ እንጂ ምንጣፍ እንኳን የሌላት መሆኑኗን በመገለጽ የተሳደነችበት አባባል ነው። ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ ጣውንቷ የኤች ኣይ ቪ ቫይረስ ካለባት ባል ወደ ሚስት በሽታውን በማስተላለፉ ያመጣሽብኝ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም ማለቷ ነው።

በተራ ቁጥር 8 ላይ የተጠቀሰውን ምሳሌያዊ ንግግር ስናይ ከላይ እንደተገለጸው ውሽምነት በድብቅ የሚከናወን በመሆኑ እና በወሲባዊ እርካታም የተለየ ስሜት ስለሚሰጥ ወይም መረጃ አቀባዮቹ[84] እንዳሉት የድብቅ ፍቅር ስለሚጣፍጥ ነው።

በመሆኑም ሴትየዋ ባሏን ከምታረካበት በተለየ ሁኔታ ወሲብ ስለሚትፈጽም ይህንን ደግሞ የምታደርገው ኀረቤቷ ከሚገኝ ኀረምሳ ጋር መሆኑን ያመለክታል። ከዚሁ አኳያ ወሲባዊ እርካታን በመፍጠር ችሎታ ያላትን ሴት የሚያውቅ የኀረቤት ኀረምሳ መሆኑን ሥነቃሉ ያሳያል። ኀረምሳው ይህንን የሴቶችን የማንቋለጥ (ወሲባዊ) ችሎታ ያወቀው ከሌሎችም ሴቶች ጋር በሚፈጽመው ወሲባዊ ተግባር በመሆኑ በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የመያዙ አጋጣሚ ሰፊ ነው። ይህንንም ባል ካላት ሴት ጋር በመፈጸሙ ቫይረሱን ወደ ጋብቻ ያሳራጫል። ስለዚህ በድብቅ የሚፈጸም ወሲብ ለኤች ኣይቪ/ኤድስ ሥርጭት በር የሚከፍት መሆኑን ሥነቃሉ ያሳያል።

እነዚህን ምሳሌያዊ ንግግሮች ከመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቱ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ያለውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ገጽታ ለማወቅ በቃለ መጠይቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች በመሆናቸው በዋናነት ከአውዳዊ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። በሌላ መልኩ ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው ደግሞ ሥነቃል ለልዩ ልዩ አገልግሎት እንደሚውል ያሳያል። ይኸውም እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ቀደም ሲል ማህበረሰቡ ለሌሎች ጉዳዮች ይጠቀምባቸው

[84] (አቶ ደረጀ መኮንን፣ ወ/ሮ ፅጌ ሁሪሳ እና ወ/ሮ አየለች ሂና፣ መጋቢት 15 ቀን 2007) ።

የነበሩትን በዚህ አውድ ኤች ኣይ ቪ ኤድስን አስመልክተው የተነገሩ በመሆናቸው የምሳሌያዊ ንግግሮቹን አውድ በመቀያየር ለተለያዩ ተግባራት መገልገል እንደሚቻል ያመለክታሉ።

ስለዚህ ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ማህበረሰቡን የሚጎዱ ጉዳዮችን በመቆጣጠር የማስተማር አገልገሎት አላቸው። ስለዚህ የውሽማ ባህልን አስመልክተው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ችግሮች በመለየት ለማረም እና ከማህበረሰቡ ባህል ያፈነገጡትን ተግባራት ለመቆጣጠር እና ከስህተት ለመመለስ የሚስተማር አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል የዘፈኖቹን ትንታኔ እናያለን።

ሠንጠረዥ 13. ውሽማን የሚመለከቱ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Yaabbanneen motoobiliidhaa,	ከተሳፈሩ አውቶሞቢል ነው፣
Lafa liccisiisanitoo,	መሬት ለመሬት አስይዞ፣
Jaallanneen magaala looko	ከወደዱ ጠይም ለግላገዋን ፣
Dhirsa jibbisiisaniitoo.	በሏን አስጠልቶ።
2. Yaa micayyoo warraa Sandaafaa,	የሠንዳፋዋ ልጅ፣
Sandaafa baatee gabaadhaa,	ሠንዳፋ ገበያ የወጣችው፣
Dhoksaattan jaaladhe malee,	በድብቅ ወደድኳት እንጂ፣
Abbaan manaa ishii hamaadha.	ባለቤቷ ክፉ ነው ።
3. Ijaariin jedhe malee,	ስሪ አልኩሽ እንጂ፣
Yooman mandure diigii siin jedhee,	መቼ አፍርሺ አልኩሽ በረንዳውን፣
Najaalldhuun jedhe malee,	ውደጅኝ አልኩ እንጂ፣
Yooman dhirsa kee jibbi siin jedhe.	መቼ ጥይው አልኩ ባልሽን።
4. Qotiyyoo gaaratti ol yaaftee,	በሬዎቹን ወደ ጋራው ነድተህ፣
Maa kaloo nafcisiistaa?	ለምን ሳሩን ታስጨርሳለህ?
Jaalala torban hingunneef,	ሳምንት ለማይሞላው ፍቅር፣
Maa bultii nagachisiiftaa?	ለምን ከትዳር ታፋታኛለህ?
5. Asi hinroobne gaara robe,	እዚህ አልዘነበም ወዲያ ነው የዘነበው፣
Ganda Dabalee Birraatuu,	ከእነ ደበሌ ቢራቱ መንደር፣
Dhirsa kee daaleecha raatuu,	ባልሽ እንደሆነ አመዳም ነው፣

Gurgurtee daaran hinbaatuu,	የማሽን ልብስ ምኞትሽን፣
Hamma mashinii dharraatu.	ሽጠሽ አትወጭውም እርዛትሽን፡፡
6. Minaalee Minaaleen horii tiksaa,	ያው ምናለ ከብት ይጠብቃል፣
Hin aaree hin aare kunuu dhirsa.	እርር ድብን አለ ይህም ሆኖ ባል።
7. Yoo weeffan goobe qanbara barsiisuu,	ወይፈን ከወፈረ ቀንበር ማለማመድ፣
Niitii dhirsi inaafuu suleedha labsiisuu.	ባሏ የሚቀናባትን ሽለቆ መውሰድ።
8. Egaa ballo balloo ballo balloo,	ኧረ! ጎበዝ፣ ጎበዜዋ፣ ጎበዝዬ፣
Namichi naangore gamaaf gamanatti,	ሰውየው ጎራ አደረገኝ በየቦታው፣
Ulfina keetiif jedhee,	ይህ ሁሉ አለኝ “ለክብርሽ ነው፣”
Naa bite xajjii mandaratti,	ገዛልኝ ጠጅ ከመንደር፣
Inni hin qaana’uu, inni hin qaana’uu,	እሱ እፍረት የለውም (2)፣
Gadsiqee jeersii baafadhu jedhee daggalatii,	ጀርስ ቀሚስሽን አውልቂ አለኝ በደን፣
Lakkii yaa namaa lakkii yaa gurbaa,	ተው አንተ ሰው፣ ተው አንተ ልጅ፣
Jeersii hin baafadhu bilaasha kanatti,	አላወልቅም እንዲሁ በነፃ ቀሚሴን ፣
Maal maxxanneen kanatti saaru lagatti,	ከወንዝ ጮጎጊት እየያዘው ልብሴን፣
Qotiyyoo keenya mararaa san gurgureeti,	ተሽጦ ነው አሰዛኙ በሬያችን፣
Natti hodhisiise anatti natti hodhisiise anatti	ለኔ ያሳፋልኝ ለኔ ያሳፋልኝ ልብሱን
Yoo jaalala barbaadde boru koottu manatti,	ፍቅር ከፈለክ ነገ ና ቤት ፣
Boru koottu manatti, koottu koottu manatti.	ና ቤት፣ ነገ ና ና ቤት።
9. Akka jedhee Gamachunii,	እንዲህ አለ አሉ ገመቹ፣
Kan halkanii Waaqtuu uumee,	የሌሊቱ የእግዜር ፍቃድ ነው፣
Maalii guyyaa keennichuunii?	በቀን መስጠተሽ ለምንድነው?
10. Girmaan mana hin jiru Kabadaa malee,	ከበደ እንጂ ግርማ ቤት የለም፣
Nadheen mana diddee katamaa malee.	ከከተማ እንጂ ሴቶች ቤት አይውሉም።
11. Tolaan kana hin beekuu Dhugumaa malee,	ዱጉማ እንጂ ቶላ ይህን አያውቅም፣
Nadheen dhirsaf diddee ushummaaf malee.	ለውሽማ እንጂ ሴቶች ለባል አይሰጡም።
12. Iranumaa dhufa goommaan hin shararaa,	ከላይ እየተሽከረከረ ጎማው መጥቷል፣
Yoo markaatoo bahee achii natti gala;	መርካቶ ከወጣ ወደ እኔው ይመለሳል፣
Yoo achii galu ablee natti qaraa,	ከዚያ እንደገባ ቢላውን ይስላል፣

Ana see'eeti daa'ima too tana qalaa.	እኔን መስሎት ልጆቼን ያርዳል።
Waaqni ofii namatti hin fuudhin makaraa,	እግዜር ነው ያመጣብኝ ይህን መከራ፣
Daa'ima too tana naa qabaa mee adraa.	እነዚህን ልጆቼን ያዙልኝ አደራ።
13. Saani odoleen dhale jabbiin jala hin jirtuu,	ቡሬዋ ላም ወልዳ ጥጇዋ የለችም ከስር፣
Liqamanbarii kana nadheen isa hin didduu,	ሴቶች አምቢ አይሉም ለሊቀመበር፣
Jaluma taa'eti guba annan itiittuu.	ይጠጣል እርጎ ተቀምጦ ከስር።
14. Laqmanbariitti hin kennina qinxirii	አትስጡ እምስ ለሊቀመበር፣
Zarazareeti fixa birrii gibirii.	ዘርዝሮ ይጨርሳል የግብሩን ብር።
15. Kan calqaba marte akkamitti hodhuufi,	እንዴት ልትሰፋው ነው በጅምር
	ያዞረች፣
Kan lama jaalatte akkamitti obsuuf	እንዴትስ ልትችል ነው ሁለት
	የወደደች።
16.Qotiyyumaan qoti lafa baaftaa motii,	በበሬው እረስ አታክርም መሬቱን
Tokkichuma jaaladhu lama taataa moti.	ሁለት ላትሆኚ ውደጂ አንዱን
17. Aboote re'ee hin horee,	አቦቴ ፍየል አላረባም፣
Eeguma Aboote re'ee hin horree,	አቦቴ ምንም ፍየል አላረባም።
Tokkuma jaaldhu ,	ከሆነማ አንዱን ውደጅ፣
warra shantamaatu gurri hin tolle.	ከሃምሳ መዋሉ ለስም አይበጅ።
18. Yaa Dabalee Siyyee,	ኣይ ደበሌ ወይ ያንተ ነገር፣
Ani suman argee,	አየሁ አንተን ብቻ ፣
Nama michuun biyye.	ያለኸው ጓደኛ እንዳፈር።

እነዚህ ዘፈኖች ከተገኙበት አውድ አኳያ በዋናነት ከአውዳዊ ቲዮሪ አንጻር የሚተነተኑ ናቸው። ካስተላለፉት መልዕክት አኳያ ሲታዩ ሁሉም ዘፈኖች በትዳር ላይ ውስልትና መፈጸሙን የሚያመለክቱ ናቸው። በዝርዝር ሲታዩ ካላቸው የመልዕክት እና ትርጉም ተመሳሳይነት አንጻር በጥምር ወይም በጋራ የሚተነተኑ ናቸው። ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ያሉትን ዘፈኖች ስንመለከታቸው ባሏን እንድትጠላ በማድረግ ከሰው ሚስት ጋር ወሲብ መፈጸምን እንደ በጎ ተግባር የሚያሞግስ እና በድብቅ የወዳዳት ሴት ባሏ ክፉ መሆኑን ይገልጻሉ። እዚህ ላይ ምናልባት ባሏ ቢያውያቅ ኖሮ የሚፈጠረው

አደጋ ቀላል አለመሆኑንም ያመለክታሉ። ከእነዚህ ሁለት ዘፈኖች የምንረዳው እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ለትዳር መፍረስ ምክንያት መሆኑን ነው። ይህም መረጃ አቀባዮች[85] እንዳሉት አንዳንዴ ጊዜ የውሽምነት ፍቅር መጨረሻው ትዳር መፍታትን የሚያስከትል ነው ። በሌላ መልኩ በዚህ ወሲባዊ ውስልትና ምክንያት ለቀሳፊው ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚም ሊኖር ይችላል።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ ያሉት ዘፈኖች የውሽምነት ፍቅር የማያዛልቅ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። በዚህም የተነሳ ውሽማው "ውደጅኝ አልኩሽ እንጂ ባልሽን ጥይ አላልኩም" በማለት በትዳር ውስጥ ለሚፈጠረው አለመግባባት ተጠያቂ አለመሆኑን ይገልጻል። በማያያዝም እሷም በተራዋ ለማያዘልቅ ፍቅር ከትዳሬ አታፈናቅለኝ በማለት በሥነቃሉ መልስ ትሰጣለች። እነዚህን ዘፈኖች ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ስናያቸው ከትዳር ውጭ የሚፈጸም ወሲባዊ ግንኙነት ዘላቂነት የሌለው በመሆኑ ሰዎች ከተግበሩ እንዲቆጠቡ ጥንቃቄ ማድረግን የሚያስተምሩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የተጠቀሱት ዘፈኖች ንቀትን የሚያመለክቱ ናቸው። ይኸውም ወሽማው የሴትዮዋን ባል በመናቅ እና እንደ ሞኝ በመቁጠር ልክ እንደ ከብት ቆጥሮት ሸጣ ለራሷ ልብስ እንዲትገዛ ይመክራታል። በማያያዝም የባሏን ቅናት በማናናቅ ይህም ባል ሆኖ ይቀናል እንዴ በማለት ይደነቃል። ከዚህ የምንገነዘበው መናናቁ የመጣው አንድም የውሽማውና የባልዮው በመልክ ወይም በሥልጣን ወይም በማህበራዊ ቦታ ወይም በኢኮኖሚ ወዘተ … ደረጃ አለመመጣጠን ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ ከትዳር በመፈናቀልን ማህበራዊ ቀውስን መፍጠሩ አይቀርም።

ከተራ ቁጥር 7 እስከ 9 የሚገኙት ዘፈኖች ካላቸው ተመሳሳይ መልዕክት በአንድነት የሚታዩ ሲሆኑ በዝርዝር ሲቀርቡ በተራ ቁጥር 7 ላይ ያለው በትዳር ውስጥ ቅናት ለችግር የሚዳርግ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በተራ ቁጥር 8 ላይ የሚገኘው በድርጊት የተገለጸው ዘፈን ነው። ይሄም ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆነውን የሰውየው ተግባር በሴትየዋ አንደበት የተገለጸበተ ነው። ከዚሁ አኳያ የሰውየው ፍላጎት ውሽማውን በጫካ ውስጥ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ለማድረግ ቢፈልግም ሴትየዋ ቤት ውስጥ እንጂ ውጭ አላደርግም ማለቷ ውሽምነት ወግ ያለው በመሆኑ በየሜዳው ወሲብ እንደማይፈጸም የሚገልጽ ነው። በተራ ቁጥር 9 ላይ የተገለጸው ደግሞ ወሲብ የሚፈጸመው ሌሊት እንጂ ቀን አለመሆኑን

[85] (አቶ ደረጀ መኮንን እና ወ/ሮ ፅጌ ሁሪሳ እና ወ/ሮ አየለች ሂና መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም.)

የሚያሳይ ነው። ይህም ማህበረሰቡ በወሲብ አፈጻጸም ካለው ደንብ ውጭ የሚከወነውን ተግባር የሚያወግዘው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህንን በተመለከተ አንድ መረጃ አቀባይ የተነገረውን እዚህ ላይ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው።

> Walqunnamtii saalaa raawwachuun kanuma Waaqni uumeedha. Kun immoo ta'uu kan qabu fuudhaafi heeruma keechatti. Dhirsii fi niitiin walqunnamtii saalaa kan raawwachuu qaban immoo halkan malee guyyaa miti. Wanti guyyaa raawatamu kan hannaati. Daa'immtillee haala uumaatiin kan dhalattu halkan malee guyyaa miti. Maaliif yoo jedhame ilmi namaa yeruuma itti umame san dhalta. Kanaan ala kan guyyaa dhalattu taanaan ilma (intala) abbaa ta'uu ni mamisiisa. Obboo Abaraa Gammadaa, (Caamsaa 25 bara 2007).

ሲተረጎም

> የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረግ እግዚአብሔር የፈጠረው ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ መሆን ያለበት በጋብቻ ውስጥ ነው። ባልና ሚስት የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ያለባቸው ሌሊት ነው እንጂ ቀን አይደለም። በቀን የሚፈጸም ነገር የሌብነት ነው። ሕጻናት እንኳን በተፈጥሮ ሁኔታ የሚወለዱት ሌሊት ነው እንጂ ቀን አይደለም። ለምን ቢባል የሰው ልጅ የሚወለደው በተፈጠረበት ሰዓት ነው ። ከዚያ ውጭ ከሆነ የተወለደው/ችው ሕጻን የአባቱ ለመሆኑ/ኗ ያጠራጥራል አቶ አበራ ገመዳ (ግንቦት 25 ቀን 2007ዓ.ም)።

በተራ ቁጥር 10 እስከ 12 ላይ የቀረቡት ዘፈኖች ስንመለከት ሴቶች ከተማ መልመዳቸውን፣ ወሲብን ከውሽማ ጋር እንጂ ከባል ጋር ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን በዚህ የተነሳም ባል በመናደድ ከተማ ውሎ ሲገባ ሚስቱን ለማረድ ስለት ያለውን ቢለዋ ማዘጋጀቱን የሚገልጹ ናቸው። ይሄ የሚያሳየን ውሽምነት በድብቅ የሚከናወን ተግባር በመሆኑ ለዚህም የከተማ አልቤርጎዎች ድርጊቱን በድብቅ ለመፈጸም ምቹ መሆናቸውንም ይጠቁማል። ይህንን በድብቅ የምትፈጽም ሚስትም ለባሏ ግድ እንደሌላትና ባልም በዚህ የተነሳ በንዴት እንደሚደበድባት የሚገልጹ ናቸው። የዚህ ዓይነቱ ተግባርም ለትዳር መፍረስ ምክንያት ነው። የከተማ አልቤርጎዎች ባለትዳርን መባልጊያ ሥፍራዎች በመሆናቸው ለትዳር መፍረስ ሰበብ እንደሆኑ መረጃ አቀባዮች[86] ገልጸዋል።

በተራ ቁጥር 13 እና 14 ላይ የሚገኙ ዘፈኖች ባለ ሥልጣናት ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ ውሽማ ሊያደርጓት የፈለጓትን ሴት ፈቃደኛ ባትሆን እንኳን አስገድደው እንደሚወሽሟቸው የሚገልጹ ናቸው። ይህም በተራ ቁጥር 13 ላይ የተገለጸው ዘፈን ሴቶች

[86] አቶ ሙሉጌታ አያኔ እና አቶ ሰይፉ መልካ፣ ወ/ሮ ሊና በየነ አቶ አበበ ጀቤሳ (ሚያዚያ፣2007)።

ሊቀመንበርን እምቢ አለማለታቸው በሥልጣኑ የሚፈልጉትን ነገር እንዲፈጽምላቸው አስቦ መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን ባለ ሥልጣኑም የሚጠጣው እርጎ ሙስና መሆኑን ያሳያል። በተራ ቁጥር 14 ላይ የተገለጸው ዘፈን ደግሞ ባለሥልጣን የመንግስትን ገንዘብ ለወሲብ እርካታ የሚያውል መሆኑን የሚጠቁም ነው። በዚህም የተነሳ ያጠፋውን የመንግስት ገንዘብ ለመመለስ ሲል በያዘው ሥልጣን ጉዳዮችን በጉቦ በመፈጸም ለሙስና እንደሚጋለጥ ያሳያል።

ከተራ ቁጥር 15 እስከ 18 የሚገኙ ዘፈኖች በግብረሥጋ ግንኙነት ውስጥ አንድ ሰው ለአንድ መሆን እንዳለበትና ከዚያ በላይ ከሆነ ችግር እንደሚያስከትል የሚገልጹ ናቸው። ዘርዘር ባለ ሁኔታ ስንመለከታቸው በተራ ቁጥር 15 ላይ የተገለጸው ዘፈን ሁለት ሰው ወዳ እንዴት ልትችል ነው? የሚለው ጥያቄ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከመጠን ካለፈ ሕመም የሚያስከትል መሆኑን ያመለክታል። በተራ ቁጥር 16 ላይ የተጠቀሰው ዘፈን አንድ ሰው ሁለት ስለ ወደደ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ባህርይ መሆን ስለማይችል፣ ወሲብም የሚያምረው አንድ ሰው ለአንድ ብቻ ሲሆን በመሆኑ፣ በፍቅር ዓለም ሁለት ሰው መፈቀር እንደሌለባት ያሳያል። በተራ ቁጥር 17 ላይ ያለው ደግሞ አንዱ ብቻ ይበቃኛል ሃምሳ የወደዱትም ጥሩ ስም የላቸውም የሚል መልዕክት አለው። መልዕክቱም ከብዙ ሰዎች ጋር ወሲብ የሚፈጽም ሰው አንድም ሴሰኛ የሚል በማህብረሰቡ የተወገዘ ስም ይሰጠዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ አጅሬው ኤድስ ጠልፎ የአልጋ ቁራኛ አድርጎ መጠቋቋሚያ ያደርጋል የሚል አንድምታ አለው። በተራ ቁጥር 18 ላይ የተገለጸው ዘፈን የወሲብ ጓደኛ መብዛትና ለቁጥርም የሚታክት ሆኖ መለኪያው ሊቆጠር በማይችል አፈር መገለጹን ያመለክታል። የዚህ ዘፈን ምስጢሩ ግን የወሲብ ጓደኞቹ/ጓደኞቿ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ሞተው አፈር በልቷቸዋል የሚል ድብቅ መልዕክት ያዘለ ነው።

እነዚህን 18ቱንም ዘፈኖች ከመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው ከተገኙበት አውድ አኳያ በአውዳዊ ቲዮሪ መተንተናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ ከማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። የዚህ ቲዮሪ ዋና ትኩረት የሰው ልጅ ወሲባዊ ባህርይን ከማህበረሰቡ የሚማር መሆኑንና ይህንንም በቋንቋ አማካይነት (በፍቅር ዘፈን) እንደሚገለጽ የሚተነተንበት ነው Legman, 1990; olson 2000; Banks and Banks 2001እና Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006)። እንደዚህ ዓይነቶቹ የፍቅር ዘፈኖች በድብቅ ፍቅር የሚካሄድ ወሲብን የሚያበረታቱ

ከመሆናቸውም በላይ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን በማስፋፋት በማህበረሰቡ ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖ የጎለ መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ሲተነተኑ ውሽምነት ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ስርጭት በር የሚከፍት በመሆኑ ሰዎች ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር እንዲቆጠቡ የእያንዳንዱን ዘፈን መልዕክት መሠረት በማድረግ በምክር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የሚያስተምሩ ናቸው። በሌላ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻር ሲታዩ በጤና፣ በሥነልቦናዊ፣ በተምሳሌት፣ በክልላዊ እና በለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪዎች አንጻርም ይተነተናሉ። በዚሁ መሠረት ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን ዘፈኖች ከተወሰኑ ቲዮሪዎች አኳያ ትንታኔያቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር 7 ላይ "ወይፈን ከወፈረ ቀንበር ማለማመድ፣

ባሏ የቀናባትን ሴት ሸለቆ መውሰድ።" የሚለውን ዘፈን ከተምሳሌታዊ ቲዮሪ አኳያ ስንተትነው "የወፈረ ወይፈን" እና "ባሏ የቀናባት ሴት" እንዲሁም "ቀንበር ማለማመድ" እና "ሸለቆ መውስድ" በተምሳሌታዊ መልኩ ተገልጸዋል። የወፈረ ወይፈን ቀንበር ማለማመድ ማለት እርሻ እንዲያርስ ማድረግ ነው። ባሏ የቀናባት ሴት ሸለቆ መውስድ ደግሞ ድብቅ በሆነ ቦታ ወስዶ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ማለት ነው። ስለዚህ ሥነቃሉ ቅናት በትዳር ውስጥ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳይ ሲሆን ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚገፋፋ እና በዚህም የተነሳ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጥ መሆኑን ያመለክታል።

በተራ ቁጥር 12 ላይ የተገለጸውን ዘፈን ከሥነልቦናዊ ቲዮሪ አንጻር ሲተነተን ሚስቱ ውሽማ በመያዟ ተናዶ ሁልጊዜ ገበያ ውሎ ሲገባ በሷ ቢላዋ የሚስልባት ሴት መንፈሷ እንደተጨነቀ ያሳያል። ይህም ውሽምነት ከወሲባዊ እርካታ በሻገር የሥነልቦና ጭንቀት የሚፈጥር ነው። በማያያዝም በተራ ቁጥር 13 እና 14 ላይ ያሉት ዘፈኖች ወሲብ እና ጉቦ ተመሳስለው የተገለጹበት ነው። ይህም የሚያሳየን ሊቀመንበር ባለትዳር ሴቶችን ለወሲብ ሲፈልጋቸው እምቢ እንደማይሉት እና እንዲያውም እርጎውን እንደሚያጠጡት መገለጹ ሥልጣኑን ፈርተው ነው። ይህ ደግሞ በሥልጣን መባለግን ያመለክታል። እሱም በልዩ ልዩ መልኩ በእጁ የገባውን የመንግስት ገንዘብ ለወሲባዊ እርካታ ማዋሉ ያንን ለመተካት ከተገልጋዩ ሕዝብ ጉቦ መቀበሉ የሙስና ገጽታ መገለጫ ነው። እነዚህ ተግባራት የሚፈጸሙት በድብቅ መሆኑ ደግሞ ሰዎች ወሲብና ጎቦን በአደበባይ መፍራታቸውን

በድብቅ ግን መፈጸማቸውን ይገልጻል። ይህ የሆነው ምናልባት መረጃ አቀባዮቹ እንደገለጹት ወሲብ በድብቅ እንደሚጣፍጠው ጉቦም በምስጢር ይጠፍጥ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ያስናሳል። ምንም ይሁን ምን እነዚህ ዘፈኖች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ጉድፎች ግልጽ የሚያረጉ ናቸው።

በሌላ መልኩ እነዚህ ዘፈኖች በክልላዊ ቲዮሪ ሲተነተኑ ማህበረሰቡ ድሮ የሚተዳደርበት የገዳ ሥርዓት ቀርቶ በሊቀመንበር መመራቱ የማህበረሰቡ አስተዳደራዊ ለውጥ ባህላዊ ለውጥ ማስከተሉን ያሳያል። ይህም ከሌላ ቦታ በመጣበት ወይም በራሱ ውስጥ ባለው ለውጥ ባህላዊ ሁኔታዎችም እንደሚለወጡ ይህ ቲዮሪ ያስገነዝባል።

በሌላ መልኩ ከለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ አኳያ ሲተነተኑ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ለውጦች በርካታ ባህላዊ ለውጦችን አስከትለዋል። በተለይም ኤች አይቪ/ኤድስ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ባህሉን እንዳለ መቀጠል የማይችልባቸው ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። እነዚህ ለውጦች ከላይ በተተነተኑ ዘፈኖች ላይ በልዩ ልዩ መልኩ ተንጸባርቀዋል። ከዚህ በመቀጠል ሲገባን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶችን ትንታኔ እናያለን።

6.4 ሲገባን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና

ሲገባ ሥር የተመደቡ የሥነቃል መረጃዎች 19 (5 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 14 ዘፈኖች)[87] ናቸው። የሥነቃል ዓይነቶቹ የሚያተኩሩት ማህበረሰቡ ለሲገባ ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት የሚያንጸባርቁ ናቸው። ይህም ሲገባ ባለቤቷ በሞተባት ሴት ቤት ገብቶ ወሲብ የሚፈጽም ሰው **ነውረኛ** መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። ይሄም በገዳ ሥርዓት ውስጥ ፎሌዎች በዘፈን እንደሚሰድቡት እንዲሁም አካሉን ቢቆርጡ፣ ቢደበድቡት፣ ቢያዋርዱት ምንም መብት እንደሌለው የሚገልጹ ናቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ በአስተዳደርም ሆነ በማህበራዊ ደረጃው እንዲሁም በሃይማኖት ክብር የሚሰጠው ሰው እንኳን ቢሆን ሲገባ ገብቶ ከተገኘ በፈጸመው **ነውር** ውርደት የማይቀርለት መሆኑን የሚገልጹ ናቸው።

ከዚሁ አንጻር በዚህ ሥር ከተመደቡት የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ 13 (2 ምሳሌያዊ ንግግር እና 11 ዘፈኖች) ተመርጠው እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

ሠንጠረዥ 14. ሲገባ የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

[87] አባሪ 6፡- በሲገባ ሥር የተመደቡትን የሥነቃል ዓይነቶች ዝርዝር ይመልከቱ።

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Sigabaan daalchi hudaa daaraa,	መሰረተ ደሃ አመዳም ሲገባ፣
Akka malee jaalata fagaara.	ተወዳደሪ የለው ይህ የእምስ ገባጋባ።
2. Madaa sibiilaa malee,	ምላስ ከወጋው፣
madaa arrabaa hinfayyan.	ስለት የወጋው ይሻላል፡

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከመረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ የተገኙት ናቸው። በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለውን መሳሌያዊ ንግግር መልዕክት ስንመለከት የሲገባን ወሲባዊ ፍላጎነት ያሳያል። ይህም ሲገባ ቂጡ አመዳም መሆኑን በመጥቀስ በሚያሸማቅቅ ሁኔታ መሰደቡን ያሳያል። ይህ የሰውነት አካል የሚገኘው ከታች በመሆኑ ቃሉ ዝቅተኝነትን ያመለክታል። በሌላ መልኩ የቂጥ ተግባር ቆሻሻ ማስወገድ ስለሆነ የሲገባም ወሲባዊ ተግባር ከቆሻሻ ጋር የተያያዘ **ነውር** መሆኑንም ለማመልከት ነው። በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ለሲገባ ያለ አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ለመግለጽ ማህበረሰቡ ለስድብ ይህንን የሰውነት ክፍል መጠቀሙን ያሳያል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ደግሞ አንድ ሰው በብረት ቢፈነከት ቁሱሉ ይድናል። ነገር ግን ስድብን መዳን እንደማይቻል የሚገልጽ ነው። ይህም ፎሌዎች ሲገባን አስነዋሪ የሆኑ ቃላቶችን ተጠቅሞ እንደሚሳድቡ ያሳያል። ከዚህ ምሳሌያዊ ንግግር እንደምንገነዘበው ሲገባ በማኀበረሰቡ ዘንድ "ከሌላው እኩል ነኝ" የሚል ስሜት የማያድርበት ሲሆን መጥፎ ስሙም ለትውልድ ሲተላለፍ ይቆያል። በተለይም በባህሉ አይጠሬ የሰው ልጅ መራቢያ አካላትን ስም እየጠሩ ሲገባን መሳደባቸው ምን ጊዜም የማይረሳ መሆኑን ያመለክታል። ፎሌዎች ሲገባን ሙልጭ አድርገው እንደፈለጉ እንደሚሰድቡት ምዕራፍ አምስት ውስጥ መረጃ አቀባዮች[88] ገልጸዋል።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከተገኙበት አውድ አኳያ የተተነተኑ ሲሆን በሌላ መልኩ ከተግባራዊ ቲዮሪ የሥነቃል የማስተማር ተግባር አንጻር ከማህበረሰቡ ወግ እና ባህል

[88] የሲገባን ነጠላ ቀዳዶ Fororsaa በሚባል ፎሌዎች ይዞ በሚጨፍሩት ረዥም እንጨት ላይ አስሮ ሲገባን በማንቋሸሽ በዘፈን ሙልጭ አድርገው ይሰድቡታል። (አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ አቶ ታደሰ ጣፋ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

የሚያፈነግጡትን አስጠንቅቆ የሚያስተምሩ ናቸው። ቀጥለው ሲገባን የሚመለከቱ ዘፈኖችን ገለጻና ትንታኔ እናያለን።

ሠንጠረዥ 15. ሲገባን የሚመለከቱ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Gaaraa dhufa yaa baabura Kumbee,	የኩምቤ ባቡር ከላይ ይመጣል፣
Ati naxalaaf boocha yaa sigabaa,	አንተ ሲገባ ለነጣላ ታለቅሳል፣
Ammaa sirraa murra tuffe.	ገና እንቆርጣለን ቁላህን ።
2. Gaalee kumni hin bitu yaa Beenyaa	ሺህ አይገዛው ጋሻውን አንተ ቤኛ፣
Sigabaan ulfina hinqabdu,	ክብር የለውምና ሲገባ፣
Qeessillee mure abaan keenyaa.	ቄሱንም ቆርጧል የኛ አባባ።
3. Shoolaa jettee gabaan hoolaa,	ሾላ ደርቷል የበግ ገበያው፣
Sigabdicha tuffee irraa murra,	መቆረጥ አለበት የሲገባ ቁላው ፣
Yosan ilmoon du'aa sun nagaan oolaa.	የሙት ልጅ ሠላምን ያገኘው።
4. Eecha dhufta bulloo kaachiftee,	ከየት ትመጣለህ በቡሎ ፈረስ፣
Eecha abbaakeetii yaa sigabaa,	አንተ ሲገባ የት አባክና ፣
Daa'ima abbaa hinqabne tafkii nyaachifte.	አባት የሌላቸውን ቁንጫ አስበልተሃልና።
5. Kurupheen dhalte hadaa keessatti,	ምጻቆ ወለደች መጭ ውስጥ፣
Sigabaan harree sale gabaa keessati.	ሲገባ አህያ በዳ ገበያ ውስጥ።
6. yaa lamdii foollee,	ያ የፎሌ ለምድ
kan qarqarrii isaa lafa gahuu,	ጫፉ መሬት የሚደርሰው፣
Sigbaa alatti hidhanii,	ሲገባን ውጭ አሥሮታል፣

akkaa waraabeessi,	ጅብ
Fagaarratti dhahuu.	ቂጡን እንድገነጥለው።
7. Daamaa fardaa kan eegeen qurusaa,	ጭራው ቆረጣው ዳማ ፈረስ፣
Nadheen sigabaa huntunni nayyate buqushaa.	የሲገባ ሴት አይጡ በልቷታል እምስ ።
8. Yaa ilmoo gaangee,	ግልገሏ በቅሎ፣
lugama qabnaan imimsitee,	ልጓም ሲያዝ አስካካች፣
Waa nadheen sigabaan saluu,	ሲገባ የሚበዳቸው ሴቶች በሙሉ፣
Qinxiriin ishii moofara saddeeti liqimsite.	እምሳቸው ስምንት ሞፈር ዋጠች።
9. Foolleen galaanaa,	ፎሌ ጀግና ነው፣
damma walalati bulbulatti,	ይጠጣል የማር ወለላውን፣
Inni du’eeti ciisaa,	በሷ ሞቶ ተኝቷል፣
salphoon qinxirii gurguratti.	እሷ ትቸረችራለች እምሷን ።
10. yaa karaa dabrabiraanii,	የደብረብርሃን መንገድ፣
Nadheen sigabaa fala fiddee,	የሲገባ ሴት ጉድ፣
Oluma guurti cidhanii,	ትውጣለች ቂላ ፣
Akkuma nyaata midhanii.	ልክ እህል እንደሚበላ።
11. Yaa bishaan gaaraa	የተራራ ውሃ
gaaratti ol yaa’a jedhanii,	ይፈሳል አሉ ወደ ላይ ፣
waa nadheen sigabaa seexannii boron seenee	የሲገባን ሴቶች ከጓሮ ገብቶ ሰይጣን
dinqatti raaha jedha.	ይባዳሉ አሉ በሳሎን።

የፎሌ ዘፈኖች የገዳ ሥርዓቱን ያከበረውን ሰው የሚያመሰግኑ ናቸው። ሥርዓቱ ከሚፈቅደው ውጪ የሆኑትን ያወግዛሉ[89]። ባል የሞተባት ሴት ዘንድ ሲገባ የገባን ወንድ እና ሲገባ ያስገባችውን ሴት በስድብ ያወግዛሉ። ለምሳሌ ከስድቡ መካከል የግለሰቡን ስምና የመረቢያ አካሉን ስም በመጥራት ዖታ ነክ የሆነ ይዘት ያላቸው ስድቦችን ይሳደባሉ። በቱለማ ዘንድ የሰው ሥም በዜማ ተጠቅሶ የሚዜመው አንድም በበጎ ነገሩ የጎላ ሥራ የሠራ፣ አንድም በሠራው አስነዋሪ ተግባሩ ለተዋረደ ሰው ነው። ለሁለቱም ማህበረሰቡ ስሙን ጠቅሶ በአደባባይ በዜማ ዕውቅና ይሠጠዋል።

ከዚሁ አኳያ እነዚህ ከላይ የተገለጹ ዘፈኖች በገዳ ሥርዓት በየስምንት[90] ዓመቱ ከሚዘፈኑ የፎሌ ዘፈኖች ውጭ ማህበረሰቡ ካከበራቸው ልዩ ልዩ ክብረ-በዓላት ላይ የተሰበሰቡ ሲሆኑ የተወሰኑት በቃለ-መጠይቅ የተገኙ ናቸው። ሁሉም ዘፈኖች በገዳ ሥርዓት ውስጥ በቱለማ ኦሮሞ ሲገባ የገባ ወንድን እና ሲገባ ያስገባች ሴትን አሸማቃቂ በሆኑ ልዩ ልዩ ዜማ ባላቸው ዘፈኖች የሚሰደቡበት መሆኑን ያሳያሉ። በመሆኑም ለትንተና እንዲመች በሁለት ተከፍለዋል። እነሱም ሲገባ የገባውን ወንድ የሚመለከቱ ስድቦች እና ሲገባ ያስገባችውን ሴት የሚመለከቱ ናቸው። በዚሁ መሠረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ያሉት ሲገባ ገቢውን የሚመለከቱ ሲሆኑ ከተራ ቁጥር 7 እስከ 11 ያሉት ደግሞ ሲገባ ያስገባችውን ሴት የሚመለከቱ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው የቃል ግጥም እንደምናየው አንተ ለሚለበሰው ነጠላ ታዝናለህ ገና ቁላህን እንቆርጣለን የሚል ነው። በመሠረቱ በቱለማ ኦሮሞ ባህል የመራቢያ አካል ስም አይጠሬ ነበር። ይሁን እንጂ ከዘፈኑ ግጥም እንዳየነው የሲገባን **ነውር** ለመግለጽ አስነዋሪውን ቃል ተጠቅሞ ሲገባን በሚያሸማቅቅ መልኩ ሰድበውታል። ይህ በአንድ በኩል የሚያሳየን ሥነቃል በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን **ነውር** ሳይደብቅ ግልጽ የሚያደርግ መሆኑን ነው። ይህም ባሏ ከሞተባት ሴት ጋር በቀድሞ ባል ቤት ውስጥ ወሲብ መፈጸሙ በማህበረሰቡ የተወገዘ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ዘፈን በማህበረሰቡ ውስጥ ከሃይማኖት አኳያ ክብር ያለው ሰው እንኳን ቢሆን ሲገባ ገብቶ ከተገኘ በባህሉ ክብር እንደማይሰጠውና በፈጸመው አስናዋሪ ተግባሩ የሃይማኖት አባትም ቢሆን መቆረጡን ይገልጻል።

[89] ይህ ውግዘት ለፎሌዎች የተሰጠበትን ምክንያት በምዕራፍ አምስት ውስጥ ሲገባን በሚመለከቱ ጥያቄዎች ሥር ከመረጃ አቀባይ አቶ ታደሰ ጣፉ የተሰጠው ማብራሪያ ይገልጻል።
[90] እንደዚህ ዓይነት ዘፈኖች በማህበረሰቡ ዘንድአብዛኛውን ጊዜ ከሊሚናሊቲ (ከተወሰነ ወቅት) አንጻር የሚታዩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ ያሉት ዘፈኖች ደግሞ መረጃ አቀባይ[91] እንደገለጸ ልክ ሲገባው የሕጻኑን ቁላ አሥሮ ለሞት እንዳባቀው የሲገባውም ቁላ መቆረጥ እንዳለበት እና የሙት ልጆች በሠላም መኖር እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የተገለጹት ሲገባው በገበያ ውስጥ ከአህያ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደፈጸመ በማሳወቅ ያዋረዱበት እና በዚህ አስነዋሪ ተግባሩ በጅብ ተበልቶ ከዚህ ምድር መጥፋት እንዳለበት የሚገልጹ ናቸው። ይህም የሚያሳየው የሰው ልጅ ከእንስሳ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፍጠሩ ከተፈጥሮአዊ ሥርዓት ውጭ እንደሆነ ሁሉ ከማህበረሰቡ ባህል ውጭ የሚፈጸም ወሲባዊ ተግባር **ነውር** መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሲገባ ያስገባችው ሴት የተሰደበችበትን ዘፈኖች በዝርዝር ስንመለከታቸው ባሏ ሞቶ እሷ በእሱ ቤት ውስጥ ከሌላ ወንድ ጋር ወሲብ በመፈጸሟ የመራቢያ አከሏን ስም በመጥራት አስነዋሪ በሆኑ ስድቦች መሰደቡዋን የሚያመለክቱ ናቸው። ትንታኔያቸውንም በዝርዝር ስናያቸው እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው።

በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰው ዘፈን የመራቢያ አካሏ በዓይጥ መበላቱን የሚገልጽ ነው። ይህም በተምሳሌታዊነት የተገለጸ ሲሆን ዓይጥ በወንድ የመራቢያ አካል ጎተራን ደግሞ በሴቷ የመራቢያ አካል ተመስሎ የቀረቡ ናቸው። ይህም ዓይጥ ጎተራውን ቦርቡሮ እህል እንደሚጨርስ ሁሉ ሲገባ ያስገባች ሴትም በየጊዜው በሚትፈጽመው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሰውነቷ መመንመኑን የሚያመለክት ነው። በሌላ ሁኔታ ደግሞ በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፈው ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታም አመንምኖ ለሞት የሚያበቃ መሆኑን ለመግለጽ ነው። በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 8 ላይ የሚገኘው ዘፈን የሴትየዋ መራቢያ አካል "ስምንት ሞፈር ዋጠች" የሚለው አገላለጽ ሲገባው ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ስምንት ወንዶች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸሟን የሚያመለክት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ደግሞ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጣት መሆኑን እና ሲገባ ያስገባች ሴት ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የሚፈጽም ሰው ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ሊጠቃ እንደሚችል የሚገልጽ ነው።

በተራ ቁጥር 9 ላይ ያለው ዘፈን ባሏ የሞተባት ሴት ሲገባ ከማስገባትም አልፋ በወሲብ ንግድ ላይ መሰማራቷን የሚያመለክት ነው። በወሲባዊ ንግድ ላይ መሰማራት ደግሞ ለኤድስ ቫይረስ እንደሚያጋልጥ የሚያመለክት ነው።

[91] አቶ ታደሰ ጣፋ (ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ለገጣፎ.)።

በተራ ቁጥር 10 ላይ የሚገኝ ዘፈን ሲገባ ያስገባችውን ሴት ወሲባዊ ፍላጎት በማጋነን ከተፈጥሯዊው ውጭ መሆኗ የተገለጸበት ነው። ይህም በግብረሥጋ ግንኙነት ወቅት የወንዱን መራቢያ አካል ልክ እህል እንደሚትበላ የተገለጸበት ነው።

በመጨረሻም በተራ ቁጥር 11 ላይ የተገለጸው ዘፈን ሲገባ ያስገባች ሴት ሰይጠኖች ቤቷ ገብተው በማሎን ውስጥ ወሲብ መፈጸማቸውን የሚገልጽ ነው። ይህም ሰይጣን በክፉ ተግባር የሚወከል በመሆኑ ማህበረሰቡ ለእሷ ያለውን መጥፎ አመለካካት የሚገልጽ ሲሆን ከላይ የተገለጹት ሁሉ ተደራርበው ማንም እንዳይደርስባት የሚከለክል ነው። ይህ ክልከላ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ መልኩ ሲገለጽ ከሲገባ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ሴቶች ከበሽታ ነጻ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ ፎሌዎች እንደዚህ ዓይነቱን ዘፈኖች የሚዘፈኑት በየስምንት አመቱ ቢሆንም በማህበረሰቡ ውስጥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይዘፈናሉ። ከዚህ አንጻር እነዚህ አሥራ አንዱም ከተዘፈኑበት ዓለማ አኳያ የሚተነተኑ ናቸው። ስለሆነም ማህበረሰቡ በወሲብ ዙሪያ ባህሉን ያልተከተሉ ጉዳዮች ባጋጠሙት ወቅት ሁሉ የዚህ ዓይነት ይዘት ያላቸው ዘፈኖች ተጠቅሞ ወቅታዊ መልዕክቱን ያስተላልፋል። እነዚህ የፎሌ ዘፈኖች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት መባባስ ምክንያታዊ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው።

ከባህላዊ አውድ አንጻር በማህበረሰቡ ዘንድ ካላቸው ትዕምርታዊ ትርጉም አኳያ የሚገለጹ ሲሆን ከማህበራዊ አውድ አንጻር ደግሞ ከግለሰብ ሕይወት እና የኑሮ መሠረት ጋር ተያይዘው የሚገልገለጹ ናቸው።

በሌላ መልኩ የማህበረሰቡ ባህል በለውጥ ሂደት ውስጥ በሚገኝበት ዘመን የዘፈኖቹ ክዋኔ ማህበራዊ ፋይዳ ከዘመኑ ፍላጎት አኳያ የሚቃኙ ናቸው። በዚሁ መሠረት ከአስተማሪነታቸው አንጻር ፋይዳቸው በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ መሠረት የማህበረሰቡ ባህል የማይፈቅደውን ወሲባዊ ተግባራትን እንዳይፈጽሙ በማስጠንቀቅ የሚያስተምሩ ናቸው።

የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ጠብቆ ከማቆት አንጻር በክልላዊ ቲዮሪ ይተነተናሉ (Dorson, 1972)። በመሆኑም እነዚህ ከላይ የተገለጹት ዘፈኖች የማህበረሰቡን ሥነቃል ሀብቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፍ እና ጠብቆ ከማቆየት እንዲሁም ከባህሉ እና ወጉ የሚያፈነግጡትን በማስጠንቀቅ ለማስተማሪያነት ከማዋል አኳያ የሚታዩ ናቸው።

ዛሬ ላይ ሆነን ትላንትን እናያለን። በመሆኑም ከለውጥ እና ቀጣይነት ቲዮሪ አንጻር ሲታዩ ሲገባ የሚገባውን ወንድም ሆነ ያስገባችውን ሴት ስሟን ሳይጠሩ በደፈናው መሳደባቸው በዛሬና በትላንት መካከል ያለውን ለውጥ ያሳያል። የስድቡ መኖርና ጨርሶ አለመቅረት የባህሉን ቀጣይነት የሚያመለክት ነው።

በቀጣዩ ርዕስ ከእሬ ጋር የተያያዙ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነትን በሚመለከት የተገኙ ሥነቃሎችን ትንታኔ እንደሚከተለው እናያለን።

6. 5 እሬን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ምደባ ና ትንተና

በእሬ ሥር የተመደቡ የሥነቃል መረጃዎች 13 (6 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 7 ዘፈኖች)[92] ናቸው። ዋናው ትኩረታቸው ከእሬ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ማድረግ ባህላዊ መብት መሆኑንና በድብቅ በሚፈጸመው ወሲባዊ እርካታ እንደሚገኝ የሚያሳዩ ናቸው። ከዚሁ አኳያ በዚህ ሥር ከተመደቡት የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ 7 (3 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 4 ዘፈኖች) ተመርጠው ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትኗል።

ሠንጠረዥ 16. እሬን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Waarsaan lubbudha dhiisan cubbdha,	ዋርሳ ነፍስ ከተውት ሀጢያት
Maaltu dhiisa waarsaa ofii.	ለምንስ ይተዋል የራስ ዋርሳ ።
2. Irraaffatamaa olii irreen hin irraafatamu.	ሺህ ቢረሳ እሬ አይረሳም።
3. Abbaan qawwee qawumaan	ባለ ጠመንጃ በጠመንጃው፣
Jalalti irree dhoksumaanii.	የእሬ ፍቅር በድብቅ ነው።

እነዚህ መረጃዎች የተገኙት በቃለ መጠይቅ ነው። ሦስቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያሳዩት ከእሬ (ዋርሳ) ጋር ወሲብ አለመፈጸም እንደ ኩነኔ የሚቆጠር መሆኑን፣ እሬ ከልብ የሚወደድ በመሆኑ በጊዜ ሂደት ውስጥ እንኳን እንደማይረሳ እና የእሬ ፍቅር በድብቅ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተገለጸው ከእሬ

[92] አባሪ 6፦ በእሬ ሥር የተመደቡትን የሥነቃል ዓይነቶች ዝርዝር ይመልከቱ።

ጋር የሚደረግ የግብረ-ስጋ ግንኙነት በድብቅ[93] ነው። ድብቅነቱ ምናልባት ለባሏ ይሆናል እንጂ ማህበረሰቡ ከወሲብ አኳያ የዋርሳን ተግባር ያውቃል ማለት ነው። ባልም ቢሆን የማህበረሰቡ አካል በመሆኑ ይህንን ግንኙነት አያውቅም ለማለት አይቻልም። ምናልባት ለወጉ ያህል ብቻ ባል በሌለበት ወሲባዊ ግንኙነቱ ይፈጸም ይሆናል እንጂ ጉዳዩ የአደባባይ ምስጢር ነው ። ባልም ቢሆን ሚስቱ ዋርሳ እንዳላት ሁሉ እሱም ለሌሏዋ ዋርሳ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አንድ ሰው ለብዙዎቹ ሴቶች እሬ ስለሚሆን ሚስት ከባልና ከእሬ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ግዴታ ስለአለባት ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ አንዱን ከያዘ ብዙዎቹን በፍጥነት ማዳረስ ይችላል። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት አንዱ ምክንያ ነው።

ዋርሳ በድሮ ጊዜ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እና እንደ ሁለተኛ ባልም የሚቆጠር ነበር። ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ በሙሉ እንደ ድሮ ተቀባይነቱን አግኝቶ አለ ለማለት አያስደፍርም (መረጃ አቀባይ አቶ ሙሉጌታ አያኔ)። በመሆኑም ምሳሌያዊ ንግግሮቹ ከተገኙበት አውድ አኳያ መተንተናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከደጋፊ መተንተኛ አንጻር በክልላዊ እና በለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪዎች የሚተነተኑ ናቸው።

ይህም ማለት የማህበረሰቡ ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው (Genne van, 1960; Turner,1967; Dorson, 1972)፡ ለለውጦቹ በዋናነት የሚጠቀሱት ከሌላ ማህበረሰቦች ጋር ባለው ግንኙነቶች የማህበረሰቡ ባህል መዳቀል፣ የከተሞች መስፋፋት እና የቴክኖሎጂዎች መስፋፋት ነው። ከለውጥ እና ቀጣይነት ቲዮሪ አንጻር የእሬ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ለውጦች ለምሳሌ "ምንም ቢረሳ እሬ አይረሳም።" የሚለው ባህላዊ ለውጥን ያመለክታል። በሌላ መልኩ "ዋርሳ ነፍስ ነው ከተውት ሀጢያት ነው።" የሚለው አባባል ከባህሉ ቀጣይነት አኳያ የሚታይ ነው። በክልላዊ ቲዮሪ አኳያ ሲታዩ ደግሞ እሬን በተመለከተ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ባህላዊ እሴቶቹን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር የሚገለጹ ናቸው። በመቀጠል እሬን የሚመለከቱ ዘፈኖችን ትንታኔ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

[93] ከጋብቻ በኋላ ሁለቱም እሬ ከሆኑላቸው ሴቶች ጋር በድብቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ይጀምራሉ። ተራኪው እንደምናገረው ከሆነ ለባህሉ ያህል አንዱ ከአንዱ ይደበቃል እንጂ ጉዳዩን ሁለቱም እንድደምፈጽሙ ይታዋወቃሉ።(ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገው ዕድሜው 29 የሆነ መረጃ አቀባይ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም.)።

ሠንጠረዥ 17. እሬን የሚመለከቱ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1 Eegaa nan taphadhaa maal jedhe jaarsi Arsii Gogaan akka dhirsaa suni torana jiraa Yaa waarsaa suuta suuta hususii Takka turreeti walitti deebina nusi	እስቲ ልጫወተው ምን አለ የአርሲ ሰው፣ እዚህ ግድም አለ ያ ባል ተብዬው፣ ዋርሳ ቀስ ብለህ አውራ በሹክሹክታ፣ ትንሽ ቆይተን እንገናኛለን ወደ ማታ።
2. Gammojiin qoree qabaa Kopheen irraa deemii yaa gammachuu, Irreen ulfana qabaa Dhoksaadhan walitti loona nu lachuu.	ቆላው እሾህ አለው፣ በጫማ ሂድበት ገመቹ፣ እሬ ክብር ስላለው፡ በድብቅ ይሁን መገናኘቱ፡፡
3. Ijaaree ijaarsisee, kan Nugufni jaaltu Taaboota; Irree irree kee na boraasisii, morma kee jalaan natty dhamoota.	ገንብቶ ያስገነባል፣ ንጉስ ይወዳል ታቦት፣ እሬ ክንድህን አንተርሰኝ፣ ከአንገትህ ሥር ነው የሚበርደኝ።
4. Finfinnee bulan malee, Wasarbii buluun kuni maaluma? Barreedduu ormaatii dhiisan malee, Waarsaa ofii dhiisuun salphina.	ማደር አዲስባ እንጂ፣ ለምን ይታደር ወሰርቢ? ከተው የሰውን ቆንጆ መተው ነው፣ የራስን ዋርሳ ግን መተው ውርደት ነው።

እነዚህ ዘፈኖች በቃለ-መጠይቅ እና በምልከታ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ናቸው። የአራቱንም ዘፈኖች መልዕክቶች እንደ አጠቃላይ ስንመለከታቸው የእሬ ፍቅር ልክ እንደ ውሽማ በድብቅ የሚከናወን መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። እዚህ ላይ እሬ እና ውሽማ በድብቅ በወሲባዊ አፈጻጸማቸው ተመሳሳይ ቢሆኑም እሬ ማለት ውሽማ ማለት አይደለም። እሬ መሆን የሚችለው የባል አጎት ልጅ ሲሆን ውሽማ የሚሆነው በባል በኩልም ሆነ በሚስት ዝምድና መኖር የለበትም። ከላይ የተዘረዘሩት እሬን የሚመለከቱ ዘፈኖች በርዕሰ ጉዳያቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ካስተላለፉት መልዕክት አኳያ ይለያያሉ። በዚሁ መሠረት ተራ ቁጥር 1 እና 2 ለየብቻቸው የሚተነተኑ ሲሆኑ 3 እና 4 እንደዚሁ በአንድነት የሚታዩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰውን ዘፈን ስንመለከት ባል በአከባቢ ስላለ እሬዋ በሹክሹክታ እንዲያወራ፣ ቀስ ብሎ እንዲወጣና ማታ ተመልሶ እንዲመጣ ትነግረዋለች። ይህም የፍቅር ግንኙነታቸው በድብቅ[94] የሚከናወን መሆኑን ያመለክታል። እዚህ ላይ ከመረጃ አቀባዮችም እንደተገለጸው ድብቅነቱ ለባህሉ ወግ ያህል እንጂ ባልየውም ለሌላኛዋ ሴት እሬ ስለሚሆን እሱም እንደዚሁ በድብቅ መሄዱ የማይቀር መሆኑን ምዕራፍ አምስት ውስጥ በእሬ ርዕስ ሥር ከባለታሪኮቹ ትረካ መረዳታችን ይታወሳል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ዘፈን ቆላው እሾህ ስላለው በጫማው እንዲሄድበት በመምከር የእሬ ፍቅር ክብር ያለው በመሆኑ ግንኙነታቸው በድብቅ እንዲሆን የሚያሳስብ ነው። ይህ ዘፈን ከተምሳሌታዊ ትንተና አኳያ ሲታይ ቆላው የሴት ወይም ወንድ የመራቢያ አካል፣ እሾሁ በግብረሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታ (ኤች አይ ቪ/ኤድስ) እና ጫማው ደግሞ ኮንዶምን የሚወክል ነው። ይህም ሴትየዋ ከእሬዋና ባሏ በተጨማሪ ከሌላ ሰዎች ጋር በፈጸመችው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ምናልባት በበሽታ የመያዝ አጋጣሚ እንዳለ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ለእሬዋ ያላትን የተለየ ፍቅር ለማሳየት በበሽታው እንዳይያዝ በኮንዶም እንዲጠቀም የገለጸችበት ነው። በሌላ መልኩ ወንድየውም ቢሆን ከሌሎች ሴቶች ጋር በሚፈጽማቸው የግብረ-ስጋ ግንኙነት በሽታ ሊኖርበት ስለሚችል ሴትዮዋ ለራሷ ጥንቃቄ ለማድረግ የግብረ-ስጋ ግንኙነቱን በኮንዶም እንዲያደርግ በሥነቃል የገለጸችበት ነው።

[94] እሬ (ዋርሳ) በፍቅር ግንኙነት ውስጥ እንደ ሁለተኛ ባል ይታያል። ይህም ባሏ በማይኖርበት ጊዜ በድብቅ ወሲብ ይፈጽማል። እሷም ዋርሰዋን ስለምትወድ በሷ በሥራ ምክንያት በአከባቢው ከሌለ በድብቅ እየተገናኘች ወሲባዊ ፍላጎቷን ታጣጥማለች ሙሉጌታ አያኔ (ጥቅምት 2007ዓ.ም.)።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ የሚገኙት ዘፈኖችን ስናያቸው በአንገቱ ሥር ብርድ ስላስቸገራት እሬዋ ክንዱን እንዲያንተርሳት ስትጠይቅ በተከታዩ ዘፈን ደግሞ እሬዋ በተራው ማደር ካልቀረ ትልቁ ከተማ አዲስ አበባ ይታደራል እንጂ ወሰርቢ ትንሿ ከተማ እንዴት ይታደርባታል ይላታል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ የፈለገችውን ያህል ቆንጆ ብትሆን የሰው ቆንጆ ይተዋል እንጂ የሚወዷትን እሬ መተው እንደሌለበት ይገልጻል። ይህም የማህበረሰቡ ባህል ከእሬ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸሙን የፈቀደለት መሆኑን ያሳያል። በዋናነት ከተግባራዊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ሲተነተኑ እያዝናኑ የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ከማስተማር አንጻር የሚገለጹ ናቸው። ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች አኳያ ደግሞ ቀደም ሲል በምሳሌያዊ ንግግሮቹ ላይ የተገለጹት ለዘፈኖቹም መተንተኛነት የሚያገለግሉ ናቸው።

በአጠቃላይ እስካሁን በተመለከትናቸው የሥነቀል ይዘታዊ ትንታኔዎች ውስጥ የቱለማ አሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን አስመልክተው የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና የተዘፈኑ ዘፈኖች ልዩ ልዩ ጉዳችን በመዳሰስ በባህሉ አፈጻጸም ላይ ያሉትን ሁኔታዎች አሳይተዋል። ከዚሁ አኳያ በዋናነት በልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት የሚተላለፈውና እስካሁን መድሃኒት ያልተገኘለት ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ዓለምን እያስጨነቀ በምገኝበት በአሁኑ ዘመን ባህላዊ ድርጊቶቹን እንደቀድሞው መፈጸሙ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

በተቃራኒው ደግሞ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መኖር ምንም ትኩረት ሳይሰጥ ባህላዊ ድርጊቶቹ እንደ ድሮ መቀጠል እንዳለባቸው የሚገፋፉ ናቸው። ስለዚህ ከባህላዊ ድርጊቶች አንጻር በተዘዋዋሪ ሁኔታ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን በመከላከሉ ረገድ የበኩላቸውን ሚና የሚጨወቱ ሥነቃሎች የመኖራቸውን ያህል የቫይረሱ ሥርጭት እንዲባባስ የሚያደረጉም አሉ። ከዚሁ አንጻር ከዚህ ቀጥሎ በምዕራፍ ሰባት ውስጥ በቀጥታ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ላይ ያተኮሩ የሥነቃል ዓይነቶች ትንታኔ እንመለከታለን።

ምዕራፍ ሰባት

7. ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስመልክቶ ከመስክ ከተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች 293 (199 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 94 ዘፈኖች)[95] ናቸው። የእነዚህ ሥነቃል ዓይነቶች አጠቃላይ ትኩረት ሰዎች ስለኤች አይ ቪ/ ኤድስ በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ ጎኑ በሥነቃል እየተነጋገሩበት መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ታሪካዊ አመጣጣቸው ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የመነጩ በመሆናቸው በሽታውን አስመልክቶ ሰዎች ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ የሚረዱ ሲሆኑ በሌላ መልኩ ደግሞ ሰዎችን ለወሲብ የመገፋፋት ሚና ያላቸው ተለይተው ተመድበዋል።

ምሳሌያዊ ንግግሮቹ (አባባሎቹ) መካከል አብዛኞቹ ኤች ኣይ ቪ /ኤድስ ከመከሰቱም በፊት ሲነገሩ የነበሩ ናቸው። ይህ ማለት ኤች አይ ቪ ከመከሰቱም በፊት የነበሩና ማህበረሰቡ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ሲገለገልባቸው የነበሩ ናቸው። ይሁን እንጂ መረጃዎቹ በተሰበሰቡበት ወቅት ኤች ኣይ ቪ /ኤድስን በሚመለከት ለቀረቡ ጥያቄዎች ከአውዱ ጋር የተነገሩ እና በቫይረሱ እና በሰዎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚያሳዩ ናቸው። ዘፈኖቹን በተመለከተ አብዛኞቹ በቀጥታ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ ናቸው።

የሥነሎቹን ትኩረት ነጥቦች ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት አንጻር ሲታዩ በተለያዩ መልኮች የሚገለጹ ናቸው። ለምሳሌ ተጠቂ የሆኑ የኀብረተሰብ ክፍሎችን የሚጠቁሙ፣ ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ በምክር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት ትምህርት የሚሰጡ ሲሆኑ በተቃራኒው ደግሞ ወሲብን በማበረታታት ሰዎችን ለኤች ኣይቪ/ኤድስ እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ይገኙበታል።

በዚህ ሥር ለትንተና የተመረጡት የሥነቃል ዓይነቶች 115 (63 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 52 ዘፈኖች) ሲሆኑ እነሱም በቀጥታ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ ናቸው። ስለ ትንተና ምንነት እና ፋይዳ ምዕራፍ ስድስት ውስጥ በሰፊው የቀረበ በመሆኑ እዚህ ላይ

[95] ከመስክ ከተሰበሰቡት የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ 293 (199 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 94 ዘፈኖች ወይም ቃላዊ ግጥሞች) ናቸው። እነሱም በአባሪ ሰባት ሥር በዝርዝር ቀርበዋል።

መድገሙ አስፈላጊ አይደለም። ትንታኔዎቹም የተካሄዱት በምዕራፍ ስድስት ውስጥ የተገለጹትን የመተንተኛ ቲዮሪዎች መሠረት በማድረግ ነው።

ይህ ምእራፍ በሦስት ዋና ዋና ርእሶች የተከፋለ ሲሆን የመጀመሪያው በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በይበልጥ ተጠቂ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከት የሥነቃል ዓይነቶች ይዘታቸው የተተነተኑበት ነው። ሁለተኛው ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘታዊ ትንታኔዎችን ያካተተ ሲሆን ሦስተኛው ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ የሥነቃል ዓይነቶች የተተነተኑበት ነው።

በዚሁ መሠረት ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እና የተመረጡ የሥነቃል ዓይነቶች በየርዕሶቻቸው ሥር ተብራርተዋል። በዚሁ መሠረት ተመሳሳይ መልዕክት ያላቸው በጥምር ወይም በጋራ የተተነተኑ ሲሆን የተለየ መልዕክት ያላቸው ደግሞ በተናጠል ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ተተንትነዋል። ትንተናዎቹ በዋናነት ያተኮሩት የሥነቃል ዓይነቶቹ ከተገኙበት አውድ አኳያ በአውዳዊ ቲዮሪ የተገለጹ ሲሆን ፋይዳቸው ደግሞ ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ ተገልጸዋል። በሌላ መልኩ ካስተላለፉት ልዩ ልዩ መልዕክቶች እና ትርጉሞች አንጻር በሌሎች ደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች ተብራርተዋል። ዝርዝር ትንታናቸውም በየርዕሰ ጉዳዮቹ ሥር እንደሚከተለው ቀርቧል።

7.1 በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጎጂ (ተጠቂ) የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ስብስብ የያዘ ነው። ምሳሌያዊ ንግግሮቹ የተበሰቡት በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጠቂ የሆኑት የኅብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ ለማወቅ በቃለ-መጠይቁ ለተሳተፉ ሰዎች ለቀረበው ጥያቄ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች በምሳሌያዊ ንግግር አስደግፈው ከሰጡት ምላሽ እና በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት ከተሳታፊዎቹ የተነገሩ ናቸው። ዘፈኖቹ በአብዘኛው የተሰበሰቡት ከባህላዊ እና ሓይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ሲሆን በሌሎች አጋጣሚ መቼቶችም የተገኙ ናቸው።

በዚህ ሥር የተመደቡት የሥነቃል መረጃዎች 63 (34 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 29 ዘፈኖች) ናቸው። ርዕሱ በዋናነት የሚያተኩረው በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ተጠቂ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚጠቁሙ የሥነቃል መረጃዎችን ትንታኔ ያካተተ ነው።

በሥሩም ሦስት ንኡሳን ርእሶች አሉት። እነሱም ወጣቶች[96] በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ፣ ሴቶች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ እና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ሥር የተመረጡትን የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ትንተና እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

7.1.1 ወጣቶች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር 12 (5 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 7 ዘፈኖች)[97] ተመድበዋል። እነሱም ወጣቶች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ሲሆን ትኩረታቸው ወጣቶች በቫይረሱ እተየጠቁ መሆናቸውን የሚያሳዩ በተለይም ወጣት ሴቶች የበሽታው ሰለባ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ ናቸው። ይህንኑ አስመልክታ Paterson Gillian, (1996:ix) ኤች አይ ቪ/ ኤድስ እያደረሰ ባለው ጥፋት በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ የሆኑት ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ገልጻለች። ከመስክ የተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎችም ይህንኑ የሚገልጹ ናቸው። በዚሁ መሠረት በዚህ ሥር ከተመደቡት ውስጥ ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ጋር ካላቸው የቀረበ ግንኙነት አንጻር ታይተው 9 (4 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 5 ዘፈኖች) ለትንተና ተመርጠዋል። ስለዚህ ይዘታዊ ትንታኔአቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 18. ወጣቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ

ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Kan duaa eegan jaarsaa,	ለሞት የሚጠበቀው ሽማግሌ፣
Kan du'aa jiru dargaggeesa.	እየሞተ ያለ ወጣት ነው።
2. Dargaggeessi durii araddaa abbaa qabata,	የድሮ ጎሮምሳ የአባተን ቀዬ ይይዛል፤
inni ammaa Eedsii sodaatee baqata.	የዘመኑ ኤድስን ፈርቶ ይሰደዳል
3. "Nyaattuu na nyaatta malee,	"ከበላህ ትበላኛለህ እንጂ፣
siree niitii tootiraa addaan hin baafadhu."	አልጋዬን ከሚስቴ አልለይም።"
Jedhe gurbaan Eedsiin.	አለ ልጁ ኤድስን።

[96] ወጣቶች የሚለው ቃል ሁለቱንም ፆታዎች (ወንዶች እና ሴቶችን) ይመለከታል።
[97] አባሪ ሰባት፡- ወጣቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶችን ዝርዝር ይመልከቱ።

4. “Eedsii si sodaadhaf nitii too hin hiku, qawee Biteen si ajjeesa malee.” Jedhe mucaan.

ኤድስ ፈርቼህ ከሚስቴ አልፋታም፣ ጠመንጃ ገዝቼ እገልሃለሁ እንጂ።” አለ ልጁ።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በመስክ መረጃ አሰባሰብ በቃለ መጠይቅ ወቅት በኤች አይ ቪ/ ኤድስ እየተጠቃ ያለው የትኛው የኀብረተሰበ ክፍል እንደሆነ ለማወቅ ለቀረበ ጥያቄ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች[98] በምሳሌያዊ ንግግር በማስደገፍ ከሰጡት ምላሽ የተገኙ ናቸው። የምሳሌያዊ ንግግሮቹ መልዕክቶች ወጣቶች በኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ መጠቃታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ አራቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከማተኮራቸው አኳያ ተመሳሳይነት ስላላቸው። በመሆኑም በአንድነት ተገልጸዋል። ከሚያስተላልፉት መልዕክት አኳያ ልዩነት አላቸው። በተናጠል የተብራሩ ሲሆን ዝርዝር መልዕክታቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘውን ስንመለከት ከምሳሌያዊ ንግግሩ እንደምንረዳው መሞት ያለበት ከወጣቱ ይልቅ ቀድሞ ወደዚህ ምድር የመጣው ሽማግሌ መሆን ሲገባው እየሞተ ያለው ግን ከኋላ የመጣው ወጣቱ ትውልድ መሆኑን ይገልጻል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ደግሞ የድሮ ወጣት አግብቶ የአባቱን ቀዬ የሚይዝ ሲሆን የዘመኑ ወጣት ግን የኤድስ በሽታን ፍራቻ ላለማግባት ቀዬውን ጥሎ እንደሚሸሽ ያሳያል።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ የሚገኙት ሚስቱ የታመመችበት ወጣት በሽታዋ ምናልባት ኤድስ ይሆናል ብሎ በማሰብ፣ ኤድስ ደግሞ ገዳይ በሽታ መሆኑን በመረዳት ሞትን በመፍራት መኝታውን ከሚስቱ እንደማይለይና ትዳሩንም እንደማይፈታ ይገልጸል።

ምሳሌያዊ ንግግሮቹ የተሰበሰቡበት ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ተያይዘው ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በዋናነት በአውዳዊ ቲዮሪ የሚተነቱ ናቸው። ይኸውም መላሾቹ በቀጥታ ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ብዙም አለመኖራቸውን በመጥቀስ ቀደም ሲል ለሌሎች ጉዳዮች የተነገሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮችን ከቀረበላቸው ጥያቄ አንጻር አውዳዊ በማድረግ የተገኙ መልሶች በመናቸው ነው። ከዚህ አኳያ እያንዳንዳቸውን በተናጠል ሲታዩ የሚከተለውን መልዕክት ያዘሉ ናቸው።

[98] አቶ በጅጋ ሮሪሳ (12/02/07 ለገጣፎ)፤ አቶ ዲሪቢ በርባዳ (17/03/07 ለገጣፎ)።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር በአሁኑ ዘመን በአብዛኛው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ወጣቶችን እየጨረሰ ያለ በሽታ መሆኑን ለመግለጽ የተነገረ ነው። ይህም በተፈጥሮ ህግ መሠረት ቀድሞ መሞት ያለበት ቀድሞ ወደዚህ ምድር የመጣው መሆን ሲገባ ሽማግሌ እያለ ወጣቱ እየሞተ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የተገለጸው ምሳሌያዊ ንግግር ድሮ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከመከሰቱ በፊት ወጣቱ ትውልድ በአባቱ ደጅ ጋብቻ መሥርቶ የሚኖር ሲሆን በዚህ ዘመን ግን በቫይረሱ መኖር ምክንያት ጋብቻ መመሥረት ፈርተው አከባቢውን ለቆ መሰደዱን የሚያመለክት ነው። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ሲታይ የኤች ኣይ ቪ /ኤድስ መኖር በወጣቱ ላይ የስናልቦና ጭንቀት የፈጠረ በመሆኑ ከሥነልቦናዊ ወሲባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቲሪ አንጻር የሚተነተን ነው። ይህም ለደስታና ዘር ለመተካት የሚፈጸም ወሲብ ኤች ኣይ ቪ /ኤድስ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ጭንቀት እና ጥበት እየፈጠረ መሆኑን Brooks and Furstenbrg (1989: 251); Flemming (1997) እና Kachingwe et al (2005:197) ይገልጻሉ።

በተራ ቀጥር 3 እና 4 ላይ የሚገኙ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተነገሩበት አውድ ከላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ ሲተነተኑ ባልና ሚስት በየትኛውም የችግር ወቅት አብሮ መሆንን የሚያመለክቱ ናቸው። በመሆኑም ምንም እንኳን ኤድስ ገዳይ በሽታ ቢሆን የመጣውን ችግር አብሮ ለመጋፈጥ ለኤድስ ብሎ በወጣትነት ያገባትን ሚስቱን እንደማይፈታ የተገለጸ ነው። ይህም ወጣቶች በበሽታው ይበልጥ ተጠቂ ቢሆኑም፣ ከሆነ በኋላ ችግሩን በጋራ ለመጋፈጥ ቆረጥነትን የሚያስተምሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የተተነተኑት ምሳሌያዊ ንግግሮች ማህበረሰቡ አሁን በሚገኝበት ማህበራዊ ሁኔታ ዘመኑን ተከትለው በሚከሰቱ ተለዋዋጭ ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ምን ያህል ማህበረቡን እያነጋገረ እንደሚገኝ የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚሁ አንጻር የእነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ ለኅብረተሰቡ በልዩ ልዩ መንገዶች ትምህርታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በዚህ ረገድ ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሥነቃል ዓይነቶች የማስተማር አገልግሎት የበለጠ ለማብራራት ቀጥለው ያሉትን ዘፈኖች እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 19. ወጣቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Burtukaan too loomiin daraareeraa, of eegii yaa intaloo Eedsiin maraateeraa. Burtukaana too atii yaa dargaggoo, " ati yaa shamarree, " kana maal jetturee? Burtukaana too kan safuu hin beeknee, " jaarsaa fi jaartii jedhee, " kan addaan hinqoonne, " dhibee balaafamaaa, " kan biyyaarraa hindeemnee?	ቡርቱካኔ ሆይ ሎሚ አብቧል፣ ተጠንቀቂ አንቺ ልጅ ኤድስ አብዷል። ቡርቱካኔ ሆይ አንተ ጎሮምሳ፣ " አንቺ ኮሮዳ፣ " ይህንን ምን ትላላችሁ? ቡርቱካኔ ሆይ ይሉኝታ የማያውቅ፣ " ሽማግሌና አሮጊት ብሎ፣ " የማይለይ። " አደገኛ በሽታ " አገር የማይለቅ?
2. Dhibee barrii fidee yaa dhukkuba Eedsii, Ofeeggadhaa shamarran dargaggeessi.	የኤድስ በሽታ ዘመን ያመጣው ፣ ተጠንቀቁ ኮሮዳና ጎሮምሳው።
3. Gurbattiin nanaa, Finfinneerraan buute jeettinii, Gurbattiin nanaa, lakkii katmaa kana hinbubulni, Gurbattiin nanaa, tasa sigalaafatti Eedsinii. Gurbattiin nanaa, tasa sigalaafatti Eedsinii.	አንተ ልጅ፣ ፊንፊኔ ላይ አርፋለች ጄት፣ አንተ ልጅ፣ ተው ወደ ከተማ አትመላለስ አንተ ልጅ ድንገት ያጠፋሃል ኤድስ። አንተ ልጅ ድንገት ያጠፋሃል ኤድስ።
4. Asheete gadi cophaa, Koshmmiin asheete gadi cophaa, Yeroon gali yaa gurbaa, Gaaddifni Salaalee nama sobaa.	እሸቱ ተራገፈ፣ የኮሽም እሸት ተራገፈ፣ አንተ ልጅ ግባ በጊዜ፣ የሰላሌ ጥላ አደንዝዜ።
5. Eedsii yaa quluxaa,	ቀላወጭ ነው ኤድስ፣

Ofeeggadhaa yaa drgagoo,	ወጣቶች ተጠቀቁ ፣
Sifudhateeti bada suuta.	ይዞአችሁ እንዳይጣሩ ቀስ በቀስ ።

እነዚህ ዘፈኖች የተሰበሰቡት ማህበረሰቡ ካከበራቸው ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ላይ ሲሆን በሌሎችም ልዩ ልዩ አውዶች ይዘፈናሉ። የሁሉም ዘፈኖች አጠቃላይ መልዕክቶችን ስንመለከታቸው ወጣቶች እራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲጠብቁ በልዩ ልዩ መልኩ የማስተማር አገልግሎት ያላቸው ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ቃል ግጥም የዘፈኑትን አዝማች ስንመለከት ኤድስ ማበጁን ይጠቅስና ወጣቶች (ሴቶችም ወንዶችም) ከዚህ በሽታ እንዲጠነቀቁ ይመክራል። በመቀጠልም የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታን አስከፊነት ለመግለጽ በጥያቄ መልክ ወጣቶቹን ሽማግሌ እና አሮጊት በማለት የማይለይ ይህን አገር የማይለቅ አደገኛ በሽታን ምን ትላላችሁ? በማለት እየጠየቀ በዘፈኑ አዝማች የጥንቃቄ መልእክቱን ያስተላልፋል። ይህ ዘፈን ወጣቶች ከዚህ አስከፊ በሽታ ራሳቸውን በመጠበቅ እና በመከላከል ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ይጋብዛቸዋል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ግጥም በተመሳሳይ መልኩ ወጣቶች ከዚህ ዘመን አመጣሽ በሽታ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃል።

ከተራ ቁጥር 3 እስከ 5 የተዘረዘሩት ዘፈኖች የኤድስን አደገኛነት ይገልጹና በተለይም ወደ ከተማ መመላለስ ለበሽታው እንደሚያጋልጥ በመጥቀስ ወጣቶች በወሲብ ዙሪያ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመክራሉ።

እነዚህን አምስቱንም ዘፈኖች በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ይበልጥ የተጠቁት ወጣቶች መሆናቸውን ያመለክታሉ። ስለዚህ ወጣቶቹ በዘፈኑ ውስጥ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በማድረግ በሕይወት ዘመናቸው የማህበረሰባቸውን ድንቅ ባህላዊ እሴቶች እያከበሩ ራሰቸውን ከበሽታ እንዲከላከሉ የሚያስተምሩ ናቸው። በመሆኑም ከመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ስንመለከታቸው ከሥነቃል አጠቃላይ ተግባር አንጻር ወጣቶችን በማስጠንቀቅ የማስተማር ሚና አላቸው።

ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ በለውጥና ቀጣይነት ቲዮሪ የሚተነተኑ ሲሆን የከተሞች ማደግና ባህላዊ ጉዳዮች ለውጥ ማሳየት በተለይም የወሲብ ንግድ መስፋፋት ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መንገድ መክፈታቸውን የሚገልጹ ናቸው። ይህንን በተመለከተ

የከተሞች ማደግ እና የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት የሚያስከትሉት ለውጦች ነባሩን ሀገራዊና አካባቢያዊ ድባብ እንደሚለውጥ Gennep Van, (1960) and Dorson, (1972) ይገልጻሉ። ማህበረሰቡ ለውጡን እየተከተለ በሥነቃል ዓይነቶች ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይገልጻል። ከላይ የተዘረዘሩት ዘፈኖችም ይህንኑ በተግባር የገለጹ ናቸው።

በሌላ መልኩ እነዚህን ዘፈኖች ከጤና እና ወሲባዊ የትንተና ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው የወሲብ አፈጻጸም ጥንቃቄ ከጎደለው የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ሲሆን በተለይም ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የመጋለጡ ዕድልም የሰፋ መሆኑን Brooks & Furstenberg (1989) ይገልጻሉ። ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ቫይረስ በጣም እየተጠቁ ያሉት በወጣትነት ዕድሜ ክልል የሚገኙ በተለይም ወጣት ሴቶች ናቸው (OSSREA, 2008 and CDC, November 2015)።

በኢትዮጵያም በተደረገው ጥናት ለችግሩ ተጋላጮች ወጣቶች[99] ናቸው። በሌላ መልኩ በዚህ ጥናት ውስጥ አስመልክተው ከቡድን ተኮር የተገኘው ወጣቶች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን ያሳያል። ስለዚህ ከመስክ የተገኘው መረጃ፣ የተጓዳኝ ጽሑፋዊ ቅኝት እና የጥናቱ ውጤት ተመሳሳይ መሆናቸው የዚህን ጥናት ትክክለኝነት የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል ሴቶችን አስመልክቶ የተነገሩ የሥነቃል ዓይነቶችን እንመለከታለን።

7.1.2 ሴቶች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

በዚህ ንኡስ ርእስ ሥር የተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች 35 (21 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 14 ዘፈኖች) [100] ናቸው። የእነዚህ ሥነቃል ዓይነቶች ትኩረት ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ መስፋፋት ተጠያቂዎቹና ተጠቂዎቹ ሴቶች መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። በተለይ በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሴቶች በቫይረሱ ተጠቂ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህንን አስመልክቶ ኤርሚያስ ሥዩም፣ (2006) በአዲስ አባባ እና በሌሎችም የአገራችን ከተሞች በርካታ ሴቶች በወሲብ ንግድ ላይ መሠማራታቸውን በመጥቀስ ከሁሉም በላይ በቫይረሱ እየተጠቁ የሚገኙት ሴቶች መሆናቸውን ገልጸዋል። በሌላ መልኩ በወሲብ ንግድ

---

[99] (National HIV/AIDS Preventation and Control Office: 2006 እና Ethiopian Public Health Institute Federal Ministry of Health july, 2014)

[100] አባሪ ሰባት፡- ሴቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶችን ዝርዝር ይመልከቱ።

ላይ የተሰማሩ ሴቶች አዳዲስ ወጣት ሴቶችን ወደዚህ ንግድ እያስገቡ ያሉ በመሆናቸው ተጠያቂዎች መሆናቸውንም የሚያመለክቱ ናቸው። በዚህ ሥር የተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ሴቶች በቫይረሱ ይበልጥተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው።

በዚህ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ጋር ባላቸው የቅርብ ግንኙነት 13 (8 ምሳሌያዊ ንግግር እና 5 ዘፈኖች) ለትንታኔ ተመርጠዋል። ዝርዝር ትንታኔያቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 20. ሴቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጽ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Shaarmuxaan dullomte aqqaaxaariidha.	ሽርሙጣ ስታረጅ አቃጣሪ ትሆናለች።
2. Intalli garaa laaftu, Garaa duwwaa hin heerumtu.	ሆደ ቡቡ ልጅ፣ ባዶ ሆድ አትዳርም።
3. Durbaa fi ibbidda gara galgaati tutuqudha.	ልጃገረድና እሳት ወደ ማታ መነካካት ነው።
4. Akkana akkana taateeti dubarri nadheen taate.	እንዲህ እንዲህ ሆና ልጃገረድ ሴት ሆና ቀረች።
5. Akka bareedduun itti bultu fokkiftuun quba hinqabdu.	ቆንጆን እንዴት እንደሚታድር መልከጥፉ አታውቅም።
6. Akka ayyaana keenyaa, hallayyaarra teenya.	እንደ እድላችን። ገደል ላይ ነው መቀመጫችን።

7. Waancaan guutuun kararra teechuufi,	ተሞልቶ መንገድ ላይ ያለ ብርጭቆ እና
intalli dubrummaan magaalatti galte,	በልጃገረድነት ከተማ የገባች ልጅ
ayyaana hinqabdu.	አምላክ የላቸውም።
8. Ajjeeftu na ajjeesi malee,	ከገደልከኝ ግደለኝ እንጂ፣
sireerra na hin ciibsin,	አልጋ ላይ አታስተኛኝ፣
yaa dhukkuba baraa." Jette niitiin Eedsiin.	አንተ የዘመኑ በሽታ ። አለች ሴትዮ።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቃለ-መጠይቅ የተገኙ ሲሆን በሌላ መልኩ በማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ከሰዎች ጋር ጨዋታ ላይ እያለሁ በወሬ ወሬ ውስጥ የተሰበሰቡ ናቸው። ለምሳሌ በተራ ቁጥር 1 እና 8 ላይ የሚገኙ ምሳሌያዊ ንግግሮች ስለ ሴተኛ አዳሪ ወሬ በተነሳ ጊዜ የተገኙ ናቸው (አቶ ዲሪቢ በርባዳ ነሐሴ 16 ቀን 2006 ዓ.ም.)። ሌሎቹ በቃለ-መጠይቅ ወቅት ስለ ሴቶች ከተነገሩ ውስጥ ከጥናቱ ርዕስ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው ሆኖ የተመረጡ ናቸው። ስምንቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች በሴቶች ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ከይዘት አንጻር ተመሳሳይ ቢሆኑም ከሚያተከሩበት ጉዳይ አኳያ ተመሳሳይነትም ልዩነትም አላቸው። በመሆኑም በተናጠል እና በጋራ የሚተነተኑ በመሆናቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክት በሴተኛ አዳሪነት ተግባር ላይ በነበረች እና ከጊዜ በኋላ በእድሜ መግፋት ምክንያት የሽርሙጥናውን ሥራ በተወች ሴት ላይ ያነጣጠረ ነው። ሴትየዋ በእርጅና ምክንያት በቀጥታ የሽርሙጥናውን ተግባር ባትፈጽምም ሌሎችን በማገናኘት ሥራውን በተዘዋዋሪ እያከናወነች መሆኑን ያስገነዝበናል። ይህም የሚያሳየን አዳዲስ ወጣት ሴቶች ከወንዶች ጋር እንዲገናኙ በማድረግ የሽርሙጥናውን ሥራ እያስፋፋች እንደምትገኝ ይገልጻል። እንደዚህ ዓይነቱ አሠራር ደግሞ አዳዲስ ሰዎች በኤች ኣይ ቪ ኤድስ እንዲያዙ መንገድ ያመቻቻል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ለሁሉ ነገር አዛኝ የሆነች እና የተጠየቀችውን ሁሉ እሺ የምትል ልጃገረድ ለግብረ-ስጋ ግንኙነትም ቢጠይቋት እንቢ ስለማትል ክብረ-ንጽሕናዋን ከማስገሰሰም አልፋ ፀንሳ እንደምታገባ የሚገልጽ ነው። ከጋብቻ በፊት የግብ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም በቱለማ ኦሮሞ **ነውር**[101] ስለሆነ የተወገዘ መሆኑን በዚህ ጥናት

[101] "በድሮ ዘመን የግብረሥጋ ግንኙነት ወደ መፈጸም አይሽጋገሩም ምክንያቱም በባህሉ መሠረት የከንፈር ወደጆች ወሲብ ከፈጸሙ በባህሉ **ነውር** በመሆኑ ውግዘት ይድርስባቸዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ዘመን ይህ ነውር ቀርቶ የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል።" (መረጃ አቀባዮች አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

ምዕራፍ አምስት ውስጥ የከንፈር ወዳጅ ምንነት በተብራራበት ርዕስ ሥር መረጃ አቀባዮች መግለጻቸው ይታወሳል።

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ ያሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ልጃገረድን ማታ መነካካት ወደ ግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደሚያመራ እና እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ለልጃገረድ ክብረ-ንጽሕና መደፈር ምክንያት እንደሚሆን የሚገልጹ ናቸው። ይህም ሥርዓትን ያልተከተለ ወሲባዊ ንክኪ ላልተፈለገ እርግዝና እና ለአባለዘር በሽታዎች በተለይም ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንደሚያጋልጥ የሚያወሱ ናቸው።

ከተራ ቁጥር 5 እስከ 7 የተጠቀሱት ምሳሌያዊ ንግግሮች ወንዶች ሴቶችን ለወሲባዊ እርካታ የሚያስቸግሩዋቸው መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። በተለይ ቆንጆ የሆኑ ሴቶች ሌሊቱን ሙሉ ሥቃይ የተሞላበት የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደሚፈጸምባቸው የሚያመለክቱ ሲሆን በዚህም የተነሳ ሕይወታቸው በአስጊ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚገልጹ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በልጃገረድነታቸው ወደ ከተማ የገቡ ወጣት ሴቶች ክብረ-ንጽሕናቸውን ጠብቆ ለመቆየት የማይችሉበት አደጋ ውስጥ እንደሚገኙ የሚያመለክቱ ናቸው።

በተራ ቁጥር 8 ላይ የተገለጸው ምሳሌያዊ ንግግር በልዩ ልዩ ምክንያቶች (ከላይ በተገለጹት ሰበቦችም ሊሆን ይችላል) በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የተያዘች ሴት በሽታው ከሚያሰቃያት ሞትን መምረጧን የሚያሳይ ነው። እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በሙሉ በዋናነት ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። ይህም ከአጠቃላይ የሥነቃል ተግባር አንጻር በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚፈጸሙት የግብረ-ስጋ ግንኙነቶች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የመያዝ አጋጣሚ መኖሩን በማስጠንቀቅ የሚያስተምሩ ናቸው።

ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ስናይ ደግሞ በተራ ቁጥር 7 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር መረጃ አቀባዩ[102] እንዳለው "ተሞልቶ መንገድ ላይ ያለ ብርጭቆ እና በልጃገረድነት ከተማ የገባች ልጅ አምላክ የላቸውም።" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር በአውዱ ውስጥ እንደተነገረ ሲብራራ በጠላ የተሞላ ብርጭቆ እና ልጃገረድ ተመስለው ቀርበዋል። ይህም ከታምሳሌታዊ ቲዮሪ አንጻር ሲተነተን ሙሉውን መንገድ ላይ ያለ ብርጭቆ ድንገት ሰው በእግሩ ቢመታው ጠላውም ይደፋል ብርጭቆውም ይሰበራል። በተመሳሳይ መልኩ በልጃገረድነት ወደ ከተማ የገባች ልጅ በወሲባዊ ንክኪ ድንገት ክብረ-ንጽሕናዋ ይደፈራል። በኤች ኣይ ቪ/ኤድስም ተይዛ ትሞታለች። በመሆኑም ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በአንድ

[102] (መረጃ አቀባይ አቶ ነጋሹ ሔይ (ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ.ም)።

በኩል ወጣት ሴቶች ከወሲባዊ ንክኪ ራሳቸውን እንዲከላከሉ በሌላ መልኩ ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲጠነቀቁም ያስተምራል።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከሁሉም በላይ ሴቶች ለኤች ኣይ ቪ. ኤድስ ጥቃት ይበልጥ የተጋለጡ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። በተዛማጅ ጥናታዊ ጽሑፍ ዳሰሳ ውስጥ የተገኙ መረጃዎች ሴቶች ለቫይረሱ ተጋላጭ መሆናቸውን በመጥቀስ በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የተጠቁት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች መሆናቸውን OSSREA, (2008: 105-107) ይገልጻል። ስለዚህ ከተጠኚው ማህበረሰብ የተገኙ የሥነቃል መረጃዎችም ይህንኑ የሚያሳዩ መሆናቸው የዚህን ጥናት ትክክለኝነት የሚያረጋግጡ ናቸው። (በዚህ ጥናት ውስጥ ገጽ 161 ይመልከቱ)።

ከዚሁ አንጻር እነዚህ ስምንቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያደርሰውን ጉዳት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማየት ማህበረሰቡን ልናስተምርባቸው የምንችል መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከዚህ ቀጥለው ሴቶች በኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚያሳዩ ዘፈኖችን እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 21. ሴቶች በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1.Yaa qottoo mukattii, jaalalli hafe yaa dubartii, Eedsi bashtaan nama rarraasa mukatti.	አቤት መጥረቢያ የእንጨት መቁረጫው፣ ሴቶችን ማፍቀር ምንድነው ፋይዳው፣ ከእንጨት ያንጠለጥላል የኤድስ በሽታው።
2. Saree gurraachi lagarraa kaatee dutaa, Eedsiin hammaatee ofeegi yaa sharmuxaa.	ወንዝ ላይ እየሮጠ ይጮሃል ጥቁር ውሻ ፣ ኤድስ ከፍቷልና ተጠንቀቂ ሻርሙጣ ።
3. Yoo kurupheen laga ceetuu,	ሚዳቆ ወንዝ ስትሻገር፣

Koomeen mirgaa lafa hingeessuu,	የቀኝ ተረከዟ አይነካም መሬት ፣
Yaa haftu jaalalli Shaarmuxaa,	ይቅር የሸርሙጣ ፍቅር፣
Toeban lamaan nama hingeessuu.	ለያደርስ ለሁለት ሳምንት ።
4. Hirribaan rafaa jiraa hirriba binin shillimii,	አልተኛሁም እንቅልፍ ብንን እያልኩኝ፣
Xinnaan asgori jettaa guddaan asgori jettaa,	ሁሉንም ከመንገድ ጎራ የሚታሰኚ፣
Kan dhufe hin gaggeessituu,	የመጣውን ግን አንዱንም አትሸኚ፣
Yaa bultii balleechituu.	የሰው ኑሮ ለማጥፋት አንቺ የማትተኚ።
5. Yaa hurufa ilillee,	የእሌሌ ሜዳ፣
Barannis kaloo egeres kaloo,	አምና ከሎ ነበር፣ ያው ነው ዘንድሮም፣
Hunduu sitti irreeffataa,	ሁሉም ይሳለሙሻል፣
Maaramii Shanoo taate yaa intaloo.	ሆነሻል የሸኖ ማሪያም ።

እነዚህ ዘፈኖች በእሬቻ ክብረ-በዓል እና በጥምቀት ክብረ-በዓል ላይ የበዓሉ ታዳሚዎች በህብረት ከዘፈኑት የተገኙ ናቸው። በሌላ መልኩ ሁሉም ዘፈኖች በማህበረሰቡ ውስጥ በየትኛውም ጊዜና ቦታ በግልም በጋራም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይዘፍናሉ። የዘፈኖቹን መልዕክት ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያያዥ የሆኑና ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በተመለከተ ሴቶች የበለጠ በበሽታው ተጠቂዎች (ተጎጂዎች) መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። የእያንዳንዳቸውን ይዘት በተናጠል ስንተነትናቸው እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ዘፈን የኤድስ በሽታ እንጨት ላይ ስለሚያንጠለጥል ሴቶችን ማፍቀር ትርፉ ለኤድስ መጋለጥ መሆኑን ይገልጻል። በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ደግሞ የቫይረሱ ሥርጭትና ሰዎችን የመግደል ደረጃው ከፍ እያለ የመጣ በመሆኑ በወሲብ ንግድ ላይ የተሠማሩት ሴቶች ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃል። በተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ከሸርሙጣ ጋር የሚፈጸም ወሲባዊ ግንኙነት በገንዘብ እንጂ በፍቅር የታጀበ ባለመሆኑ ዘላቂነት የሌለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው በተራ ቁጥር 4 ላይ የሚገኘው ዘፈን ደግሞ መጠጥ የምትሸጥ ሴት ሁሉንም ከመንገድ ጎራ በሉ እያለች ስመሸባቸው እዚያው ስለምታሳድራቸው የሰዎችን ትዳር የምታናጋ መሆኗን ይገልጻል። በተራ ቁጥር 5 ላይ የሚገኝም ለሁሉም እሺ ባይ ሴት እንደ ታቦት እንደሚሳለሟት ይገልጻል። ይሄም እነዚህች ዓይነቷ ሴት በከሁሉም ጋር

የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚትፈጽም ሴት መሆኗን ያመለክታል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ደግሞ ከዕለታት አንድ ቀን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጥ መሆኑን ይገልጻል።

በአጠቃላይ የዘፈኖቹ ግልፅ ትርጉሞች እስካሁን ድረስ በተገለጸው ዓይነት መልኩ የሚታዩ ሲሆን በውስጣቸው ያዘሏቸው መልዕክቶች ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ የተጋለጡት ሴቶች መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ይኸውም ከዘፈኖቹ እንደምንገነዘበው ከሁሉም ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ሴቶች በቫይረሱ የመጠቃት ዕድላቸው ሰፊ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው።

እነዚህ ዘፈኖች የተሰበሰቡት ተጠኚው ማህበረሰብ ከሚያከብሯቸው ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ላይ እና በየትኛውም ጊዜና ቦታ በሚዘፈኑበት ወቅት የተገኙ በመሆናቸው ከአውዳዊ ቲዮሪ አኳያ ባህላዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ባገናዘቡ መልኩ ክዋኔያቸው ከጊዜ እና ቦታ አኳያ የሚገለጹ ናቸው ። ስለዚህ ትንታኔያቸውም ከዚሁ አንጻር የሚታዩ ናቸው። ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻርም ስንመለከታቸው ከላይ በምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና ውስጥ እንደተመለከትነው ሰዎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ በልዩ ልዩ መልኩ የሚያስተምሩ ናቸው።

በሌላ መልኩ ተራ ቁጥር 1 እና 4 ላይ የተጠቀሱት ዘፈኖች “ኤድስ እንጨት ላይ ያንጠለጥላል” የሚለው እና “እልተኛሁም እንቅልፍ ብንን እያልኩኝ” በማለት የተገለጹት በወሲብ ዙሪያ ጭንቀትን የሚገልጹ በመሆናቸው ከፎክሎር ሥነልቦናዊ ቲዮሪ አኳያ የሚታዩ ናቸው። ከጤና ትምህርት ቲዮሪ ውሰጥ በወሲብ ቲዮሪ ሥር በሚገኙ በመሠረታዊ ፍላጎት ቲዮሪ፣ በማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ እና በሥነልቦናዊ ወሲባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቲዮሪ አንጻርም የሚታዩ ናቸው። ይህንን አስመልክቶ የፎክሎር ሥነልቦናዊ ቲዮሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ እና አመለካከት እንደሚያሳይ Susan Moore and Doreen Rosental (2006 38-65) ይገልጻሉ። እነዚህ ቲዮሪዎች ከጤና ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በኤድስ መጠቃት መኖሩን በመገንዘብ በወሲብ አፈጻጸም ላይ መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ። በመሆኑም ዘፈኖቹ ማህበረሰቡን በተለይም ሴቶች በወሲብ ዙሪያ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚያሳስቡ ናቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ ዘፈኖች ከተዛማጅ ጥናታዊ ቅኝትም ጋር ተያያዥነት አላቸው። ዓለም አቀፋዊ ሪፖርት እንደሚያሳየው እድሜያቸው ከ15-24 የሆኑ ወጣቶች በተለይም ወጣት ሴቶች በተለየ ሁኔታ የበሽታው ተጠቂዎች መሆናቸውን UNAIDS (2004:13) ይገልጻል።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር በአፍሪካና ደቡብ እስያ አገሮች በአብዛኛው በኤድስ የተጠቁት ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ወጣት ሴቶች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸውን Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006፡ 178-179) ያብራራሉ። ስለዚህ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከመስክ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው። በዚህም የተነሳ በአንድ መልኩ ሴቶች ከቫይሱ ሥርጭት ራሳቸውን እንዲጠብቁ የጥንቃቄ መልዕክት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ በሌላ መልኩ ደግሞ ሴቶች የበሽታው ተጠቂ በመሆናቸው ወንዶች ለወሲብ እንዳይጠጓቸው የሚያስፈራሩም ይገኙበታል። ከዚህ በመቀጠል ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆነውን ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘታዊ ትንታኔን እንመለከታለን።

7.1.3 ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የተመደቡ መረጃዎች 16 (8 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 8 ዘፈኖች)[103] ናቸው። ትኩረታቸውም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ቀለም፣ ጎሳ የእድሜ ክልል ሳይገድበው ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያጠቃ በሽታ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። በመሆኑም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የቫይረሱ ተጠቂ በመሆናቸው በሽታውን ለመከላከል ሁሉም በህብረት ሆኖ ለጋራ ችግር የጋራ መፍትሔ መፈለግ እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡ ናቸው። ዝርዝር ሁኔታውን በትንታኔ ውስጥ እንመለከታለን።

ከዚሁ አኳያ በዚህ ሥር ከተመደቡ ውስጥ ለጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ተስማሚ ሆኖ የተመረጡ 10 (5ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 5 ዘፈኖች) ናቸው። እነሱም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 22. ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤድስ በመጠቃታቸው ለመከላከል መረባረብ እንዳለባቸው የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

[103] አባሪ ሰባት፡- ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በኤድስ ይበልጥ ተጠቂ መሆናቸውን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶችን ዝርዝር ይመልከቱ።

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Jirbiin wal gargaarteeti arba hiiti.	ድር ቢያብር አንበሳ ያስር።
2. Fardi kophaa kaatu hin injifatu.	ብቻውን የሚሮጥ ፈረስ አያሸንፍም።
3. Sirbilllee yoo waljalaa qaban tola.	ዘፈን እንኳን አድማቅ ሲኖር ይመቻል።
4. Waan hunda keechaa tokkummaan bayecha.	ለሁሉም አንድነት ኃይል ነው፡፡
5. Mixiin walqabattee laga ceeti.	ጉንዳን ተያይዛ ወንዝ ትሻገራለች።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተበሰቡት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጠቂ የሆኑ የኀብረተሰብ ክፍሎች መግቢያ ላይ እንደተገለጸው በቃለ-መጠይቁ እና በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት ከተሳታፊዎቹ የተነገሩ ናቸው። የአምስቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክት ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍሎች በጋራ መተባበር እንዳለባቸው የሚገልጹ ናቸው። ከተመሳሳይነታቸው አኳያ ትንታኔያቸው በጋራ የሚከወን ቢሆንም ካተኮሩበት ጉዳይ አንጻር ትርጉማቸውን በተናጠል መመልከቱ አስፈላጊ ነው። በዚሁ መሠረት እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር ምንም እንኳን ጠንካራ እንሰሳ አንበሳ ቢሆንም አቅም የሌላቸው በርካቶች አንድ ላይ ቢያብሩ ጠንካራ የተባለውን አንበሳ እንዳይነቃነቅ አድርገው ማሰር ይቻላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ እስካሁን ድረስ መድኃኒት ባለመገኘቱ በሰው ልጅ ጤና ላይ ትልቅ እንቅፋት የሆነውን ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሁሉም ሰው በመከላከሉ እና በመቆጣጠሩ መስክ ቢተባበር ችግሩን ማስወገድ እንደሚቻል ይገልጻል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰው በፈረስ ጉግስ ጨዋታ ውስጥ አባራሪ ወይም ተባራሪ የሆነ ሌላ ተወዳዳሪ ፈረስ ከሌለ ብቻውን የሚሮጥ ፈረስ አሸናፊም ተሸናፊም አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከሉ እና በመቆጣጠሩ መስክ አንድ ሰው ብቻውን የፈለገውን ያህል ጥንቃቄ ቢያደርግ በሽታውን መግታት እንደማይችል የሚያሳይ ነው።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸው በባህላዊ ጭፈራ ውስጥ አንድ ጥሩ የመዝፈን ችሎታ ያለው ሰው የሚያወርደውን ወይም የሚዘፍነውን ዘፈን የሚቀበሉ ታዳሚዎች ከሌሉ ጭፈራው ውበት ያጣል። ዘፋኙም እንደ ቁራ ብቻውን መጮህ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ

ምሳሌያዊ ንግግር አንድ ሰው ብቻውን ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን መከላከል እና መቆጣጠር አይችልም የሚል መልዕክት አለው።

በተራ ቁጥር 4 ላይ የሚገኘው ከሁሉም በላይ አንድነት አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ይህ አንድነት የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሽታን ለመከላከል ወሳኝ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር ጉንዳን አንዱ እርስ በርስ ተያይዘው ሳይነጣጠሉ ወንዝ እንደሚሻገሩ ሁሉ ይህንን አስከፊ በሽታ ሁሉም ሳይለያይ በአንድነት መከላከል እንደለብን የሚያስገነዝብ ነው።

የመተንተኛ ቲዮሪያቸውን በተመለከተ ከተነገሩበት አኳያ እስካሁን በተገለጹበት መንፈስ በአውዳዊ ቲዮሪ የሚታዩ ናቸው። ይህም “በሽታውን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት” ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ በምሳሌያዊ ንግግሮች በማስደገፍ ከተሰጠው መልስ የተገኙ በመሆናቸው የምሳሌያዊ ንግግሮቹ አውድ በተለወጠ ጊዜ የሚያስተላልፉት መልዕክትም እንደሚለዋወጥ እንመለከታለን። ይህም ማህበረሰቡ እነዚህን ሥነቃሎች ካሁን ቀደም ለሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሲጠቀምባቸው የነበረንና አሁን በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ዙሪያ ለቀረበው ጥያቄ መረጃ አቀባዮቹ በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጠቂዎች ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸውን በምሳሌያዊ ንግግሮች አስደግፈው መልስ መስጠታቸው አውዱ በተለወጠ ቁጥር የምሳሌያዊ ንግግሮቹም አገልግሎት ከአውዱ ጋር ተስማምቶ መቅረባቸውን እንገነዘባለን።

በሌላ መልኩ ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ስንመለከት ደግሞ አንድ ሥነቃል የተለያየ አውድ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች ያለው በመሆኑ እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከተነገሩበት አውድ አኳያ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚያጠናክሩ እና ኤድስን በጋራ ለመከላከል የሁሉም ህብረት እንደሚያስፈልግ የሚያስተምሩ ናቸው።

ሠንጠረዥ 23. ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በኤድስ መጠቃቱንና

መከላከልን የሚገልጹ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Eedsiin dhufe kan ilkaan kumaa,	ኤድስ መጥቷል ባለሺህ ጥርስ፣
Dhiirris dubartiinis isumaan dhumaa.	ወንድም ሆነ ሴት የሚጨርስ።
2. Fardi Boolee dhufee karra dura marsee,	በሩን ከቧል ከቦሌ የመጣ ፈረስ ፣
Dhibeen Eedsii dhufee Addunyaa dammaqsee,	ዓለምን አስጨንቋል ኤድስ ፣

Osoo Eedsii boonyuu Iboolaan numarsee.	እቦላ ከቦናል ለኤድስ ስናለቅስ ።
3. Burtukaan too loomiin daraareeraa	ቡርቱካኔ ሆይ ሎሚ አብቧል፣
of eegii yaa gurbaa Eedsiin maraateraa.	ተጠንቀቁ ወጣቶች ኤድስ አብዷል።
Burtukaana too bifa hin filatuu,	ቡርቱካኔ ሆይ መልክ አይመርጥም ፣
" sanyii hinqortuu,	" ዘር አይለይም፣
" furdaa hin sodaatuu,	" ወፍራም አይፈራ፣
" qallaas hin tuffatuu,	" ቀጭንም አይንቅም፣
" jaarsaa jaartii hin jedhu,	" ሽማግሌ አይል አሮጊት፣
" yaa nama baqadhuu,	" ሰዎች ተጠንቀቁ፣
" lubbuu kee eeggadhuu.	" ሕይወታችሁን ጠብቁ።
4. Warri tanaa gadii,	ከታች ያሉ ሰዎች፣
Aannan namaa hinqicuu gurguratee gala,	ይሸጣሉ እንጂ ለሰው አይሰጡም ወተት፣
Eedsii balleessudhaaf yaa barbaannu falaa.	ሰዎች መላ እንፈልግ ኤድስን ለማጥፋት።
5. Mee yaa lammii koo teenyeeti mala mallaa,	ወገኔ ሆይ መላ እንፈልግ እስቲ፣
Eedsii balleechuudhaaf waada waliigallaa,	እንማማልና ኤድስን ለማጥፋት ፣
Eedsii yaa farriisaa mukattan sifannisaa.	አንዴ ተባብረን እንስቀለው በእንጨት።

እነዚህ ዘፈኖች በቃለ-መጠይቅ እና ማህበረሰቡ ካከብራቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ-በዓላትም ላይ የተሰበሰቡ ናቸው። የዘፈኖቹን አጠቃላይ መልዕክት ስንመለከት ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ማጥቃቱን የሚያመለክቱ ናቸው። የእያንዳንዳቸውን መልዕክት በዝርዝር ስናያቸው ከዚህ እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ዘፈን መልዕክት በኤች አይ ቪ/ኤድስ እየተጠቁ ያሉት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች (ወንዶችም ሴቶችም) መሆናቸውን ይገልጻል። በመሆኑም ሁሉም ኅብረተሰብ በኤድስ እተጠቃ መሆኑን ይገልጻል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ዘፈን ደግሞ የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሽታ የዓለምን ህዝብ እያስጨነቀ መሆኑንና የኤድስ ችግር መፍትሔ ሳያገኝ በኢቦላ በሽታ መከበባችንን ይገልጻል። ከዚህ በመነሳት በኤድስ በሽታ እየተጠቃ ያለውሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸው ዘፈን ኤድስ ዘር፣ ቀለም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ወፍራም ወይም ቀጭን ሳይል ማንንም ከማንም ሳይለይ ሁሉንም የሚያጠቃ መሆኑን በመጥቀስ ሰዎች ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ ያስጠነቅቃል።

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ የሚገኙ ዘፈኖች ኤድስ በኅብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋት ከፍተኛ መሆኑን በመግለጽ ሁሉም ተባብረው በሽታውን ለማጥፋት ዘዴ መፈለግ እንዳለባቸው ያሳስባሉ።

ይህንን በተመለከተ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በገዳይ በሽታነቱ ቀዳሚውን ሥፍራ እንደሚይዝ እና ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ሳይለይ ሁሉንም እንደሚያጠቃ በመግለጽ በርካታ ሰዎች ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር ተያያዥ በሆኑ በሽታዎች መሞታቸውን ዓለም አቀፋዊ የኤድስ ሥርጭት ሪፖርት ያመለክታል UNAIDS (2008)፡ ይህም የሚያሳየን በክለሳ ድርሳን ደሰሳ ውስጥ በጽሑፍ የተገኙ መረጃዎች እና ከማህብረሰቡ የተሰበሰቡ የሥነቃል መረጃዎች ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው።

አምስቱም ዘፈኖች ከትኩረት አኳያ ሲታዩ ኤድስ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ መሆኑን የሚያመለክቱ ከመሆናቸው አንጻር ተመሳሳይነት አላቸው። የመተንተኛ ቲዮሪያቸውም አንጻር በተመሳሳይ መልኩ የሚገለጹ ናቸው። በመሆኑም በዋናነት ከአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች አንጻር ተተንትነዋል። ከተገኙበት አውድ አኳያ ቀደም ሲል ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ ዘፈኖች ትንተና ውስጥ እንደተገለጸው ከባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ አንጻር የሚታዩ ናቸው። በተግባራዊ ቲዮሪ ሲተነተኑ ደግሞ ካስተላለፉት መልዕክት አኳያ ከሚሰጡት የማስተማር አገልግሎት አንጻር የሚታዩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የሚገኙት ዘፈኖች ከአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች በተጨማሪ ከተምሳሌታዊ ቲዮሪ አኳያ የሚተነተኑ ናቸው። ይኸውም "ኤድስ መጥቷል ባለሺህ ጥርስ" የሚለው ስንኝ ኤድስ እና ሺህ ጥርስን በማመሳሳል የተገለጸ ሲሆን ትርጉሙም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሰውን ከያዘ ለሞት የሚያበቃ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በተመሳሳይ መልኩ "ተጠንቀቁ ሁላችሁም ኤድስ አብዷል" የሚለው ስንኝ። ኤድስ እና እብድን በማመሳሰል የተገለጸ ነው። ይህ ማለት እብድ በመንገድ ላይ ያገኘውን ሁሉ ድንጋይ በመወርወር እና ሁከት በመፍጠር ሰዎች ሠላምና መረጋጋት እንዳያገኙ እንደሚያደርግ ሁሉ ኤድስም በወሲብ መስመር ላይ ወዲያ ወዲህ የሚጓዙትን ሰዎች እየያዘ በበሽታው እንዲሰቃዩ ከማድረጉም በላይ በቫይረሱ የተያዙትን ሰዎች ጤና እንደሚያውክ የሚገልጽ ነው። ስለዚህ ሁለቱም ተምሳሌታዊ አገላለጾች ኤድስ አደጋ

የሚያደርሰው በተወሰኑ ሰዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በመሆኑ ማህበረሰቡን ለኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አለመረጋጋት የሚጋብዝ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

በሌላ መልኩ አምስቱንም ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ በፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪ ይቃኛሉ። ይኸውም የአንድ ሕዝብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ጭንቀት፣ ተስፋ፣ ምኞት፣ ሀዘንና ደስታ ሥነቃሉ ውስጥ ስለሚገኝ እነዚህን ምንጮች በማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከት ማወቅ እንደሚቻል Dundes (1989) እና ፈቃደ አዘዘ (1991፡50) ይገልጻሉ። ስለዚህ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እንደዚህ ዓይነቶቹዘፈኖች የማህበረሰቡን ጭንቀት የሚገልጹ ናቸው። ስለዚህ ማህበረሰቡ ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ ያለበት በጋራ መሆኑን ያስገነዝባሉ። ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ አንኳር የሆነውን ርዕሰ ጉዳይ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል የሥነቃል ዓይነቶች ሚና ትኩረት የሚያደርግበትን ይዘታዊ ትንተኔ እንመለከታለን።

7.2 ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ

የሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

ከተሰበሰቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ሥር የተመደቡት 200 (147 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 53 ዘፈኖች) ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሽታ እያደረሰ ካለው ችግር በመነሳት በተለያየ ዘዴ የሚያስተምሩ ናቸው። ከተግባራቸው አንጻር ሲታዩ የሰው ልጅ በቫይረሱ እንዳይጠቃ በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት እያስተማሩ ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ የሚረዱ ሲሆኑ ከሚያተኩሩበት ይዘት አንጻር የተለያዩ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው። በዚህ ሥር ከተመደቡት ውስጥ ለትንታኔ የተመረጡት 71 (40 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 31 ዘፈኖች) ናቸው። እነሱም ካተኮሩበት ጉዳይ አንጻር ይዘታቸው በልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ተደግፈው ተተንትነዋል። ትንተናው የተከናወነው በዋናነት ሥነቃሎቹ ከተሰበሰቡበት አውድ እና ካስተላለፉት መልእክት እንዲሁም ካላቸው ትርጉም አንጻር ነው።

ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በአብዛኛው በመጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡ በመሆናቸው ከተሰበሰቡበት አውድ አኳያ ተመሳሳይነት ስላላቸው በጋራ በአውዳዊ ቲዮሪ የታዩ ሲሆን ካስተላለፉት መልዕክት አንጻር ደግሞ በተግባራዊ ቲዮሪ

ተተንትነዋል። ከዚህም በተጨማሪ እንዳስፈላጊነታቸው በልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ተደግፈው ተብራርተዋል።

ዘፈኖቹ የተሰበሰቡት አራቱንም የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የካተቱ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በተለይ በምልክታ ማህበረሰቡ ካከበራቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ-በዓላት ላይ የተገኙ ናቸው። በተጨማሪም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከልዩ ልዩ አውዶች ተሰብስበዋል። ዘፈኖቹ በልዩ ልዩ ዜማዎች እና እንቅስቃሴዎች የታጀቡ በመሆናቸው በሚዘፈኑበት ወቅት የከዋኞቹ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ባከተተ መልኩ በቪድዮ ካሜራ የተሰበሰቡ በመሆናቸው ትንታኔያቸው አውድና ክዋኔን ያካተቱ ናቸው። ከዚሁ አኳያ እንደሚያተኩሩበት ርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር ትንተናቸውን እንደሚከተለው እናያለን።

7.2.1 የሚመክሩ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ የምክር አገልግሎት ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶች 80 (65 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 15 ዘፈኖች)[104] ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች አብዛኞቹ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከመከሰቱ በፊት የነበሩ ቢሆኑም በቃለ-መጠይቅ ወቅት ለቀረቡ ጥያቄዎች አውድን መሠረት በማድረግ ከመረጃ አቀባዮች የተነገሩ ናቸው። ከአጠቃላይ ትኩረታቸው አኳያ ሲታዩ ለጊዜያዊ የወሲብ ፍለጎት እርካታ ወይም ጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘት ተብሎ ሰዎች ችግር ውስጥ እንዳ ይገቡ የሚመክሩ ናቸው። በመሆኑም ወደ ወሲብ የሚገፋፉ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ለምሳሌ ከመጠጥ እና አደንዛዥ ዕፅ በመራቅ ከልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት መታቀብን፣ አንድ ለአንድ መወሰንን፣ ለወሲብ ጓዳኛ ታማኝ መሆንን እና ከአቅም በላይ ሆኖ ከተገኘ ጥንቃቄ ባለው ሁኔታ በኮንደም መጠቀምን በሚመለከት የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

ከዚሁ አንጻር በዚህ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች መካከል ለትንተና የተመረጡ 19 (14 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 5 ዘፈኖች) ናቸው። እነሱንም እንደሚከተለው እናያለን።

ሠንጠረዥ 24. ኤድስን ለመከላከል የሚመክሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Lubbuun abbaan hin eegne lama hin bultu.	ባለቤቱ ያልጠበቃት ነፍስ ሁለት ቀን አታድርም።

[104] አባሪ ሰባት፡- ሰዎች ኤድስን እንዲከላከሉ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ የሥነቃል ዓይነቶች ምድብ ሥር የተዘረዘሩትን ይመልከቱ።

2. Balaa baraa gamnatuu tara.	ከዘመኑ ችግር ብልጥ ያመልጥ።
3. Obsaan aannan goromsaati dhuga.	ታገሽ የጊደር ወተት ይጠጣል።
4. Akka baranii mitii akka baraatti bulan.	እንደለመዱት ሳይሆን እንደ ዘመኑ መኖር።
5. Bokkaa fi farda jala dheechu.	ዝናብና ፈረስ በሩቁ መሸሽ።
6. Baraa fi furguggee, gadi jedhaniti dabarfatu.	ቅዝምዝምና መጥፎ ዘመን፣ አጎንብሶ ይታለፋል።
7. Akka duriin amala gowwaati.	በድሮ በሬ ያረሰ የለም።
8. Salftaan lubbuu bulfata.	የዓይናፋር ሕይወቱ መቆየቱ።
9. Waan dabruu jettee of hidabarsni.	ለሚያልፍ ቀን እራስህን አታቃጥል።
10. Ciniinfachuurraa ciniinnachuu wayya.	ከማማጥ ጥርስ ነክሶ ማምለጥ።
11. Namatti himan malee namatti hinhidhan.	ለሰው ይነግሩታል እንጂ አይነክሩትም።
12. Maseenni okolee dide okkotee hin didu.	አልታለብ ያለች ላም ማሰሮ እምቢ አትልም
13. Nama hin gubu jedhanii, harka ibidda Keecha hin kaa'an.	አያቃጥልም ተብሎ፣ እጅ እሳት ውስጥ አይከተተም።
14. Quufan malee hin utaalan, utaalan malee hin caban.	ካልጠገቡ አይዘሉም፣ ካልዘለሉ አይሰበሩም።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በልዩ ልዩ አባባሎች ይገለጹ እንጂ ሁሉም ምክር በመስጠት ሰዎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ /ኤድስ እንዲከላከሉ የሚረዱ ከመሆናቸው አኳያ ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም ለትንተና እንዲመች ተመሳሳይ የሆኑት በአንድ ላይ ተጣምረው ተተንትነዋል። በዚሁ መሠረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ያሉት ተመሳሳይ መልዕክት ስላላቸው በአንድነት የተገለጹ ሲሆኑ ከተራ ቁጥር 11 እስከ 14 ያሉት እንደዚሁ በአንድነት ተብራርተዋል።

ከተራ ቁጥር 1-10 ያሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ሁሉም ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመካላከል እና ለመቆጣጠር እያንዳንዱ ሰው ራሱን መጠበቅ እንዳለበት ግለሰብ ተኮር የመከላከል ዘዴ ላይ ትኩረት በማድረግ በልዩ ልዩ መንገዶች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።ከዚሁ አኳያ በዝርዝር ስንመለከታቸው፡-

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ባለቤቱ ያልጠበቃት ነፍስ እድሜ እንደሌላት ይገልጻል። በተራ ቁጥር 2 ላይ ያለው ደግሞ አንድ አስቸጋሪ የሆነ ዘመን መሻገር የሚቻለው ብልጥ ሲኮን መሆኑን ይመክራል። ስለዚህ ራስን ከበሽታው ለመከላከል ብልጠት አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል። በተራ ቁጥር ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ለወሲብ ሳይጣደፉ ስሜትን በትዕግስት ማሳለፍ እንደሚቻል ይመክራል። ይህ ማለት በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እስካሁን መድሃኒት ያልተገኘለት ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ወሲብ በመሆኑ ከልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት በመታቀብ ራስን ከበሽታው መከላከል እንደሚቻል ያስተምራል። በተራ ቁጥር 4 ላይ ደግሞ “እንደ ለመዱት ሳይሆን እንደ ዘመኑ መኖር” በሚለው አነጋገር ኤች አይ ቪ/ኤድስ ባልነበረበት ዘመን ከተለያዩ ሰዎች ጋር ይፈጸም የነበረው የግብረ-ስጋ ግንኙነት በዚህ መድኃኒት ያልተገኘለት ኤድስ ባለበት ዘመን ወሲባዊ ግንኙነት ከማድረጋችን በፊት እንዲናስብበት ይመክራል። በተራ ቁጥር 5 ላይ ያለው ኤድስን ከሯጭ ፈረስ እና ከባድ ዝናብ ጋር በማመሳሰል ራስን ከበሽታው መከላከል የሚቻለው ቫይረሱ ካለበት ስፍራ ወይም የወሲብ ንግድ ካለበት ቦታ መሸሽ ብቻ የምያወጣ መሆኑን ይገልጻል።

በተራ ቁጥር 6 ላይ የሚገኘው ኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘመን ያመጣው በሽታ መሆኑን ለማሳየት በተምሳሌታዊ አገላለጽ ኤድስን እንደ ቅዝምዝም በመቁጠር በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላለመጠቃት አላስፈላጊ ከሆነ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ራስን ጋብ አድርገው ማሳለፍ ብልህነት መሆኑን ይመክራል። በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰው በወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ እንደ ድሮ ማሰብ ሞኝነት መሆኑን ይገልጻል። ይህ ማለት ድሮ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ባልነበረበት ዘመን ልብ ከወደደው ሰው ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ቢደረግ የሚያጋጥመው ግፋ ቢል በአባለዘር በሽታ መያዝ ነው ። እሱም ቢሆን በሕክምና መዳን ይቻላል። በአሁኑ ዘመን ያለውን የኤድስ በሽታ ግን መዳን አይቻልም። ስለዚህ በወሲብ ግንኙነትን እንደ ድሮ ማሰብ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን ያስገነዝባል። በተራ ቁጥር 8 ላይ የሚገኘው ዓይን አፋር በመሆን ሕይወትን ማቆየት እንደሚቻል ይገልጻል። ይህ ማለት በፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ ከወሲብ መቆጠብ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ነጻ የሚያደርግ ባህርይ መሆኑን ያሳያል። በተራ ቁጥር 9 ላይ ያለው አባባል ለሚያልፍ ነገር ራስህን አታሳልፍ ማለቱ ለሚያልፍ ወሲባዊ ስሜት ተብለው ወደ አላስፈላጊ የግብረ-ስጋ ግንኙነት አለማጣደፍን ይመክራል። በተራ ቁጥር 10 ላይ የሚገኘው ከላይ እንደተገለጸው በተመሳሳይ መልኩ ይመክራል።

ይህም ለወሲብ ተጣድፎ በኤች ኣይ ቪ ቫይረስ ተይዘው በበሽታው ከመሰቃየት ወሲባዊ ስሜትን በትዕግስት ማሳለፍ አስፈላጊ መሆኑን ይመክራል።

ከተራ ቁጥር 11 እስከ 14 የተዘረዘሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 የተዘረዘሩትን ምክሮች ለማይቀበሉ ሰዎች ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት በማሳየት ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይጓዙ ቆም ብለው እንዲያስቡ የሚመክሩ ናቸው። ዘርዘር ባለ ሁኔታ ሲተነተኑ ደግሞ በተራ ቁጥር 11 ላይ የተገለጸው በምክር አገልግሎት ውስጥ ሊሆን የሚገባውን መንገር እንጂ ነገሩን ጆሮው ላይ ማንጠልጠል እንደማይቻል የሚያስረዳ ነው። ከዚሁ ጋር የተያያዘው በተራ ቁጥር 12 ላይ የሚገኘው ደግሞ ምክርን የማይቀበል ሰው ራሱን ለጉዳት የሚያጋልጥ መሆኑን ለማሳየት አልታለብ ብላ የምታስቸግር ላም ታርዳ እንደምትባላ በተምሳሌታዊ አገላለጽ የቀረበ ነው። በመሆኑም ላምን በሰው በመመሰል ከወሲብ እንዲቆጠብ ተመክሮ አልቀበል ያለ ሰው በኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታ መያዝ እና መጨረሻው ሞት መሆኑን ለመግለጽ ነው። በተራ ቁጥር 13 ላይ ያለው ደግሞ አንድ የሚያቃጥል ነገርን ለመፈተን ተብለው እጅ ቢከተትበት የሚመጣውን ጉዳት ለማመልከት የተነገረ ነው። ይህ ማለት በአሁኑ ዘመን ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መድኃኒት ያልተገኘለት በሽታ መሆኑን በተለያዩ ጊዜ እና ቦታ እየተነገረ ባለበት ዘመን የበሽታውን ጉዳት በላመገንዘብ ወይንም ባለማወቅ ወይም ምን ይመጣል? ብለው በመናቅ ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ራሳቸውን ለሚያጋልጡ ሰዎች ምክር የተነገረ መሆኑን ያመለክታል። በመጨረሻ በተራ ቁጥር 14 ላይ ላይ የተጠቀሰው “ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ።” የሚለው አባባል ምሳሌያዊ ንግግሩ ከተነገረበት አውድ አኳያ ስናይ በአሁኑ ዘመን ሰዎች መጠጥ ጠጥተው በስካር መንፈስ ወደ ልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚጣደፉት ጥጋብ የሚያስከትለውን አደጋ ለማሳየት የተነገረ ምክር ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ 14 ምሳሌያዊ ንግግሮች በግለሰብ ላይ ያተኮሩ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው ተመሳሳይ ናቸው። በመሆኑም ከተነገሩበት አውድ አኳያ በአውዳዊ ቲዮሪ የማህበረሰቡን ባህላዊ እና ማህበራዊ አውዶችን ባገናዘበ መልኩ የሚተነተኑ ናቸው። በመሆኑም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን የመከላከላልና የመቆጣጠር ሦስቱን የ’መ’ ህጎች የሚመለከቱ ናቸው። እነሱም ወሲብ ከማድረግ ‘መታቀብ’፣ አንድ ለአንድ ‘መወሰን’፣ እና በኮንዶም ‘መጠቀም’ አስፈላጊነት ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥተው ይመክራሉ። ከዚሁ አንጻር ይህንን አስከፊ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭትን ለመከላከል

እና ለመቆጣጠር እያንዳንዱ ሰው ራሱን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከል በመምከር የሚያስተምሩ ናቸው።

ከእነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች የምንገነዘበው የማህበረሰቡን ባህላዊ ምሥጢሮች ባወቅን ቁጥር ለችግሮቹ መፍትሔ እንደምናገኝ (Fayeradnd, 1998) ከገለጸው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ስለሆነም ማህበረሰቡ ከሚናገረውና ከሚከውነው የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮች አጫጭርና በቋንቋ ፈጠራ የታጀቡ ናቸው። ከዚሁ አኳያ ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በተግባራዊ የመተንተኛ ቲዮሪ ስናያቸው የሰዎችን የተበለሸ ባህርይ ለማስተካከል እና ባህሉ ከማይፈቅደው **ነውር** ርቀው በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን መልካም ሥነ-ምግባር ለማስተማር ማህበራዊ አገልግሎታቸው የጎላ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

በተለይም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በምክር የማስተማር አገልግሎት እንደሚሰጡ Omolara & Samuel (2012) ያስረዳሉ። በመሆኑም እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በወሲብ ዙሪያ ለሚከናወኑ ተግባራት እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱን ከቫይረሱ መጠበቅ እንዳለበት የሚመክሩ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከዚህ ቀጥሎ የዘፈኖቹን ትንታኔ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 25. ኤድስን ለመከላከል የሚመክሩ ዘፈኖች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Burtukaan too loomiin daraareeraa	ቡርቱካኔ ሆይ ሎሚ ጎርምቷል፣
of eegaa hunduu Eedsiin hammaateeraa.	ሀላችሁም ተጠንቀቁ ኤድስ አብዷል።
Burtukaana too miila lama qabdaaf,	ቡርቱካኔ ሆይ ሁለት እግር አለኝ ተብሎ፣
“ muka lama hinkortu,	“ ሁለት ዘፍ አይወጣም፣
“ tokkuma jaaladhu,	“ አንዱን ብቻ ውደጅ፣
“ hamma garaa hirtuu.	“ ልብሽ ከሚከፈል።
“ qotiyumaan qotii,	“ በበሬ ብቻ እረሺ፣
“ qofforuu hinxaarinii,	“ በዶማ አትሞክሪ፣
“ tokkicha jaaladhuu,	“ አንዱን ብቻ ውደጅ
“ hundaamaraatinii.	“ ለሁሉ አትበጅ
Burtukaan too loomiin daraareeraa,	ቡርቱካኔ ሆይ ሎሚ ጎርምቷል፣
of eegaa lakkii Eedsiin hammaateeraa.	ተው ተጠንቀቁ ኤድስ አብዷል።

2. Dabbaleen tumaa tumatee ,	ካድሬ ሕግ አውጥቷል፣
Raadiyooninuu dubbatee,	ሬድዮንም ተናግሯል፣
Yoo galtee yeroodhan galii,	በጊዜ ብትገባ ይሻለል፣
Eedsiin magaala fudhate.	ኤድስ ከተማውን ወሯል።
3. Lakkii mee yaa Gilee,	ተው እስቲ አንተ ጅል፣
Ganzaba keenyaan halayyaa hinbuunu qile;	በገዛ ገንዘባችን አንግባ ገደል።
Aduu gaafa qanii gabayaa,	ልክ የገበያ እለት፣
Ganamaan si’a nutti kaasa,	ልባችን ይነሳሳል ለመሄድ፣
Yoo gadi bunuus karaan nu hin dhibuu,	ስኬድ አያስቸግር መንገዱ፣
Yoosuu nam’na raasaa,	ወዲያውኑ ይመጣል ውስዋሱ፤
Oggaa buunees badhee hin ijjennu,	ከደረስን አንቆምም ወጭ፣
Itti ol sienna mana xaasaa.	ጥልቅ ብለን ጣሳ ቤት ቁጭ ።
Lakkii mee yaa gilee.	ተው እስቲ አንተ ጅል፣
ganzaba keenyaan hallyaa hinbuunu qile.	በገዛ ገንዘባችን አንግባ ገደል።
Oggaa buunee gabaa,	ወደ ገበያ ስንሄድ፣
Mana farsootitti walgeenya;	መገናኘችን ከጠላ ቤት፤
Duutis duubaan jirti,	ሞት ይመጣል በጊዜው፣
Alamiin hamuma jireenya;	ደስታ ግን እስካሉ ነው፣
Gizee sa’aatii torbaa,	ልክ ሲሆን ሰባት ሰዓት፣
Warra abaataatitti seennaa,	ተገናኝተን ከአባተ ቤት፤
Binnee biinoo muluu,	ሙሉ ቪኖ አውርደን፣
Marsineeti biruma teteenyaa;	እንጠጣለን ዙሪያ ከበን፤
Foon lammaa fi kabadaatu qala,	ለማና ከበደ ባለልኳንዳዎቹ፣
Addumaan madaba dendeenyaa,	ለየግላችን ቀረቡልን መደቦቹ፤
Lixxee sa’aa tokko,	ከምሽቱ ልክ አንድ ሰዓት፣
Seennee warra kababuudha,	ለመሳረጊያው ከከበቡ ቤት፤
Namuu beekaaf wallaalaa hin qabuu,	ሳይለይ አዋቂ ካለአላዋቂው፣
Akkuma maxaafaa nababuudha,	ሁሉም ማነብነብ ነው፤
Ifa quufnee garaa,	እስኪበቃን ጠጣን፣
Tabbatti deema dadhabuudha,	አጅሬም መጣ ስካር፤
Machiin duubaan jirti,	ዳገቱስ እንዴት ይወጣል፣

Maayii achuma rafuudha;	እዚሁ ማደር ይበጃል፤
Yoo qabaatan fayyaa,	ካለ ጤንነቱ ፣
Katamaa tanas bulanii laaluu wayyaa.	ከተማስ ብታደር ምን አባቱ።
Yoo qabaatan fayyaa,	ካለ ጤንነቱ ፣
Katamaa tanas bulanii laaluu wayyaa	ከተማስ ብታደር ምን አባቱ።
4. Eedsii, Eedsii jedhanii,	ኤድስ፣ ኤድስ ይላሉ፣
Eedsiin nama hin koru,	ኤድስ ሰው ላይ አይወጣም፣
Kaatiikaalaa dhuguudhan dogoggoru.	ካቲካለ መጠጣት ነው ያመጣ ስህተቱን።
5. Addisaabaa kana gommaan konkoolaate,	ተንከባለለ አሉ ከአዲስ አበባ ጎማው ፣
Gara beergoo kana garaan na sodaate;	ይህን አልቤርጎ ምነው ሆዴ ፈራው፤
Sobaa mitii dhugumaa ,	ሀሰት አይደለም እውነት ነው፣
ganzabini keenya qinxiriitti dhumaa.	ገንዘባችን የሚያልቀው በእምስ ነው።

ዘፈኖቹ የተሰበሰቡት ማህበረሰቡ ካከበራቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ-በዓላት ላይ ነው። እነዚህ ዘፈኖች የምክር አገልግሎት ከመስጠታቸው አኳያ ተመሳሳይነት አላቸው። ለምሳሌ ከተራ ቁጥር 3 እስከ 5 ያሉት በከተማ አካባቢ በገበያ ቀን ከመጠጥ እና ወሲባዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው በሚከወኑ ተግባራት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። በመሆኑም ከወሲብ እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳታቸው ተመሳሳይ ስሆኑ ካስተላለፉት መልዕክት እና ካተኮሩበት ጉዳይ አንጻር ሲታዩ ግን የተለያዩ ናቸው። ከዚሁ አኳያ መልዕክታቸውን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ እያንዳንዳቸው በተናጠል ተተንትነዋል። በመሆኑም ዝርዝር ጉዳያቸውን እንደሚከተለው እናያለን።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘውን የቃል ግጥም ስንመለከት የአዝማቹ ስንኞች የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን አስከፊነት በመግለጽ እያንዳንዱ ሰው ራሱን ከበሽታው እንዲከላከል ምክር የሚሰጡ ናቸው። ይህም አንድ ሰው ሁለት እግር ስላለው በአንድ ጊዜ ሁለት ዛፍ ላይ መውጣት እንደማይችል ሁሉ በፍቅር ዓለምም ከአንድ ሰው በላይ ማፍቀር እና ወሲብ መፈጸም ለኤች ኣይ ቪ እንደሚያጋልጥ ያሳስባል። በመሆኑም ከሦስቱ የ'መ' ህጎች ውስጥ የመወሰንን አስፈላጊነት በመምከር ያስተምራል።

በተራ ቁጥር 2 ላይ ካለው ቃል ግጥም የምንረዳው በሽታውን በመከላከሉ እና በመቆጣጠሩ ረገድ የፖለቲካ ሰዎችም የበሽታው ሥርጭት መባባስ አሳስቧቸው ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት

በመስጠት ሕግ እስከ ማውጣት መድረሳቸውን ያመለክታል። በማያያዝም የብዙሃን መገናኛ ሕዝቡን በማስተማር የበኩላቸውን ድርሻ በመወጣት ላይ መገኘታቸውን ይገልጻል። በመቀጠልም የበሽታው ሥርጭት በከተማ እንደሚበዛ በመግለጽ ከከተማ በጊዜ ወደ ቤት መግባት ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ከመጋለጥ ያድናል በሚል ይመክራል።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የቀረበው ዘፈን መስከረም 25 ቀን 2007 ዓ.ም በቢሾፍቱ ሆረ አርሰዲ የእሬቻ ክብረ-በዓል ላይ የተዘፈነ ነው። የዘፈኑ አውራጅ አቶ በዳሳ ጉርሙ ዕድሜያቸው 72 ሲሆን ፀጉራቸው ሙሉ በሙሉ ሸብቷል። መልካቸው ጥቁር ሆኖ መካከለኛ ቁመት አላቸው። ነጭ ፂማቸው ከአገጫቸው በታች ረዘም ብሎ ውበት ሰጥቶታል። የዘፈኑ ታዳሚዎች አብዛኞቹ ወጣቶች ሲሆኑ ዕድሜያቸው ከአቶ በዳሳ ጉርሙ ጋር የሚቀራረቡ ጥቂት ሽማግሌዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ። አቶ በዳሳ በሚዘፍኑበት ጊዜ ከዘፈኑ ስንኞች ጋር የሚሄዱ የእጅ፣ እግርና ዓይን እንቅስቃሴያቸው ለዛ ካለው ዜማ ጋር ክዋኔውን አሳምሮታል። የዘፈኑ ተቀባዮች የዘፋኙን እንቅስቃሴ እየተከተሉ የአዝማቹን ዜማ በመደጋገም በሣቅና በፈጋግታ ታጅበው ወደ ላይ እየዘለሉ ይጨፍራሉ። ይህንን ክዋኔ አስመልክተው ዘፈኑ ተጀምሮ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ድምፅ እና ምስል በቪዲዮ ካሴት ተቀርጿል።

የዘፈኑ ትርጉም እና አጠቃላይ መልዕክት በመጠጥ መንፈስ ተነሳስተው በገዛ ገንዘባቸው ገደል በሚያስገባ ተግባራት ላይ መሰማራት እንደሌለባቸው የሚገልጽ ነው። ድርጊቱ በአንድ የገበያ ቀን የተከወነን ተግባር ከጧት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ያለውን እንቅስቃሴ በትረካ መልክ የቀረበበት ዘፈን ነው። ይህም የሚከተለውን ይመስላል።

በዘፈኑ ውስጥ እንደተገለጸው ዘፋኙ ጓደኛውን የሚመክር ነው። ይህም አንድ የገበያ ቀን ጧት የሚሸጥ ነገር (እህል፣ እንሰሳ፣ ማገዶ ወዘተ...) ሊሆን ይችላል ይዘው ወደ ገበያ ሄዱ። መንገዱም ደስ እያላቸው ምንም ሳይታወቃቸው ገበያ ደርሰው የሚሸጡትን ሸጠው፣ የሚገዙትን ገዝተው፣ ወደ ጠላ ቤት ጎራ ብለው ጠጡ። እዚያው መጠጡን እየደጋገሙ ጠጥተው "እበክህን ምን አባቱ ሞት እንደሆነ አይቀርም" እያሉ ሲገባበዙ ቆዩ። እንዲህ፣ እንዲህ እያሉ ሰባት ሰዓት ሲሆን ከጠላ ቤት ወጥተው መጠጥም ምግብም ወደሚሸጥበት አቶ አባተ ቤት ገብተው ሥጋ በመደብ ገዝተው ከበሉ በኋላ፣ ሙሉ ቪኖ አውርደው መጠጡን መኮምኮም ጀመሩ። ጊዜው እየመሸ ሲሄድ ከአቶ አባተ ግሮሰሪ ወጥተው ለመሰነባበቻ ብለው ወ/ሮ ከበቡሽ ቤት እንደገና መጠጣት ጀመሩ። ስካርም እየመጣ ሁሉም

ተናጋሪ ሆኖ አድማጭ ጠፋ። አለመደማመጡ የስካር መገለጫ መሆኑ ነው። ከዚያም ስካሩ እየጠነከረባቸው ሲሄድ ጧት ዳገቱን ወጥተው ቁልቁለቱን ወርደው ምንም የድካም ስሜት ሳይሰማቸው ወደ ገበያ የመጡ ሰዎች ማታ ላይ የመንገዱ ርቀት እና የተራራው ውጣ ውረድ በዓይነ ህሊናቸው ይታያቸው ጀመረ። በኋላም መሄድ እንደማይችሉ በማሰብ ከተማ ለማደር ወስኑ። አደሩ። ለዚህም ከላይ "በገዛ ገንዘባችን አንግባ ገደል" በማለት ይመክር የነበረው ሰው በማሳረጊያው ስንኝ "ካለ ጤንነቱ ከተማስ ቢታደር ምን አባቱ" በማለት ዘፈኑ ይተርካል።

እዚህ ላይ የዘፈኑ መልዕክት የገጠር ሰዎች በተለያየ መንገድ ያፈሩትን ንብረት ሸጠው ገንዘባቸውን ከተማ እንደሚያራግፉ እና በገዛ ገንዘባቸው ለልዩ ልዩ ችግሮች የሚዳረጉ መሆኑን በዘፈን የተገለጸበት ነው። በሌላ መልኩ ከዘፈኑ እንደተረዳነው ገበያ ለገጠሩ ማህበረሰብ ዋና የመገናኛ ቦታ ሲሆን ገበያ የሚቆመው በከተማ ውስጥ በመሆኑ እና ከተሞች ደግሞ እነዚህኑ ገበያተኞች ታሳቢ በማድረግ የመጠጥ ቤት ከፍተዋል። በእነዚህ ቤቶች የሚጠጡ የገጠር ገበያተኞችም በመጠጥ መንፈስ ተነሳስተው ለልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት እንደሚዳረጉ እና በዚህም የተነሳ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንደሚጋለጡ የሚያመለክት ዘፈን ነው።

በተራ ቁጥር 4 ላይ ያለው ዘፈንም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ለመጋለጥ የመጠጥ ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከመጠጦች ሁሉ ካቲካላ (አረቄ) በያዘው የአልኮል መጠን ከፍተኛ መሆን የማስከር እና የሰውን ልጅ ከመጠጡ በፊት የነበረ ባህርይ የመለወጥ ኃይሉ ከፍተኛ መሆኑ የተገለጸበት ነው። በመጠጥ መንፈስ የሚመጣ የባህርይ ለውጥ ለልቅ የግብ-ስጋ ግንኙነት እንደሚጋብዝ በዚሁ ግንኙነት ለሚተላለፈው በሽታ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጥ መሆኑን የሚያሳይ ዘፈን ነው።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የተገለጸው ዘፈንም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ከተማ ውስጥ አልቤርጎ ማደር መፍራቱን የሚገልጽ ነው። የዘፈኑ መልዕክት ኤድስ ከገጠር ይልቅ በከተማ ይበዛል የሚል ትርጉም አለው። በመሆኑም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት በከተማ መብዛት በገጠሩ ማህበረሰብ ላይ ምን ያህል የመንፈስ ጭንቀት በመፍጠር ላይ እንደሚገኝ የሚያስገነዝበን ነው። ስለዚህ ይህ ዘፈን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ከገጠሩ ይልቅ በከተማ ይበዛል የሚለውን የጽሑፍ ማስረጃ የሚያረጋግጥ ነው። በተጨማሪም የከተማና የገጠሩን ህዝብ ግንኙነት ምክንያትም የሚያሳይ ነው።

ይህንን አስመልክቶ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን ውስጥ "በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች እና ኤድስን የሚመለከቱ ጥናቶች በሚል ርዕሰ ጉዳይ ሥር የበሽታው ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ[105] እንደሚበዛ ሪፖርቶች ይገልጻሉ።

በሌላ መልኩ በ2006ዓ.ም. ከፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ሪፖርት የተገኘው መረጃም የቫይረሱ ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ እንደሚበዛ ያሳያል። ይህም የጥናቱን ትክክለኝነት ያረጋግጣል። ሆኖም ግን የቀረበው መረጃ ለእስታስቲክስ ግብዓትነት በከተማ እና በገጠር ያለውን የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት ያለበትን ደረጃ ለማሳየት እንጂ በገጠር ቫይረሱ የለም ማለት አይደለም። በመሆኑም የሥነቃሉ መልዕክት የከተማውም ሆነ የገጠሩ ነዋሪ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በመምከር የሚያስተምር ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አምስቱም ዘፈኖች ከተሰበሰቡበት አውድ አኳያ ሲተነተኑ ትኩረታቸው በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በልዩ ልዩ መንገዶች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው ከማህበረሰቡ ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ አንጻር የሚታዩ ናቸው። ከባህላዊ አውድ አኳያ ዘፈኖቹ የማህበረሰቡ የመግባቢያ ስልት ሆነው ማገልገላቸው እና እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው በማህረሰቡ ውስጥ ያለውን ችግር ማሳየት ከመቻላቸው አንጻር የሚታዩ ሲሆኑ ከማህበራዊ አውድ አንጻር ደግሞ ዘፈኖቹ ከግለሰብ ህይወትና የኑሮ መሰረት ጋር የሚገናኙበትን ኢኮኖሚን፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መሆናቸው ነው።

ከማህበራዊ ዓውድ ገፅታው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ማንጸባረቅ ከመቻላቸው አኳያ ደግሞ የክዋኔው ማህበራዊ ፋይዳ ከዘመኑ ፍላጎት አንጻር የተገለጸበት ነው። ይህም ማህበረሰቡ ስለ አስከፊው የኤች ኣይቨ/ ኤድስ በሽታ በሥነቃል እየተወያየበት መሆኖን የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል የኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፊያ መንገዶችን በማስገንዘብ ሰዎች ከቫይረሱ ሥርጭት ራሳቸውን እንዲከላከሉ የሚስጠነቅቁ የሥነቃል ዓይነቶችን ይዘታዊ ትንታኔ እንመለከታለን።

[105] የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት ከገጠር ይልቅ በከተማ የሚበዛ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ (National HIV/AIDS Preventation and Control Office, 2006; and Ethiopian Public Health Institute Federal Ministry of Health july, 2014: 17-19)።

7.2.2 የሚያስጠነቅቁ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘት ምደባና ትንተና

ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ የማስጠንቀቂያ መልዕክት የሚያስተላልፉ የሥነቃል ዓይነቶች 76 (57 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 19 ዘፈኖች)[106] ናቸው። እነሱም ትኩረት የሚያደርጉት ሰዎች ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሚጋለጡት ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ መሆኑን ይጠቁማሉ። አያይዘውም ኤድስ ካልነኩት ሰውን የማይነካ በሽታ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው ለኤች ኣይ ቪ ከሚያጋልጡት ቦታዎች መራቅ እንዳለበት የሚያስጠነቅቁ ናቸው።

ከዚህ አኳያ በዚህ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ለትንተና የተመረጡ 31 (18 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 13 ዘፈኖች) ናቸው። ዝርዝሩን እንደሚከተለው እናያለን።

ሠንጠረዥ 26. ኤድስን ለመከላከል የሚያስጠነቅቁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Abaatuu of mara jedhe bofti.	ተከላከል ራስህን አለ እባብ።
2. Bakka malee ejjetaniiti,	ያለ ቦታው እየቆሙ፣
Maali lafti badaan kun jedhu.	በመሬቱ ያሳብባሉ፡፡
3. Eedsii fi koreentiin qoosaa hin beekan.	ኤድስና ኤሌክትሪክ ቀልድ አያውቁም።
4. Ibiddi abbaa irra taa'e guba.	እሳት የተቀመጠበትን ሰው ያቃጥላል።
5. Ibbiddii fi Eedsiin tutuqaa hin jaalatu.	እሳትና ኤድስ ንኪኪ አይወዱም።
6. Ibiddi xuxuqaa qabu hin dhaamu.	የሚቆሰቆስ እሳት አይጠፋም።
7. Muujjalee fi dhibeen Eedsii,	ሙጃሊና የኤድስ በሽታ፣
suuta jetteeti nama lixxi.	ቀስ ብሎ ሰው ውስጥ ይገባሉ።
8. Leenci rafe waan du'e fakkaata.	የተኛ አንበሳ የሞተ ይመስላል።
9. Callisaan biyya balleesa.	ዝምተኛ አገር አጥፊ ነው።
10. Ibiddi dibame hin dhaamu.	የተዳፈነ እሳት አይጠፋም።
11. Bokkisaan gaafa callise rakkisa.	ተቆጭ ዝም ያለ ዕለት ሰው ያስጨንቃል።
12. Eedsii fi miidhagni guntuta barbaadu.	ኤድስና ቁንጅና አጎጠጎጥ ይፈልጋሉ።
13. Midhaga hawwanii midhama hindhaban.	ሲያጌጡ ይመለጡ፡፡
14. Tiisifni baduutti dakuu barte,	በአጓት መዋኘት የለመደች ዝንብ፣
danfaa seenti.	በፈላው ውስጥ ገባች።

[106] አባሪ ሰባት፡- ሰዎች ኤድስን እንዲከላከሉ የሚያስጠነቅቁ የሥነቃል ዓይነቶች ምድብ ሥር የተዘረዘሩትን ይመልከቱ።

15. Jaalalli allaatii gara raqaatti nama geessa.	የአሞራ ፍቅር ይወስዳል ከገደል።
16. Gammachuun gaaf tokkoo, gadda bara baraa ta'u danda'a.	የአንድ ቀን ደስታ፣ የዘላላም ሐዘን ልሆን ይችላል።
17. Sirbi ganamaa galgala boo'cha fida.	እዩኝ እዩኝ ማለት ኋላ ደብቁኝን ያመጣል፡፡
18. Beekaan yoo salphina jalaa bahe.	አዋቂ ማለት ከውርደት የወጡ ዕለት።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በመጠይቅ ከተማሪዎች እና በቃለ-መጠይቅ ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ ናቸው። በልዩ ልዩ አገላለጽ ይቅርቡ እንጂ አጠቃላይ መልዕክታቸው በማስጠንቀቅ ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ /ኤድስ እንዲከላከሉ የሚያግዙ ናቸው። ከዚህ አንጻር በአስተላለፉት መልዕክት ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም ለትንተና እንዲመች ተመሳሳይ የሆኑ ተጣምረው በአንድነት ተተንትነዋል። በዚሁ መሠረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ያሉት ተመሳሳይ መልዕክት ስላላቸው በአንድነት ተተንትነዋል። በሌላ መልኩ ከተራ ቁጥር 8 እስከ 11 ያሉትም እንደዚሁ በአንድነት የተገለጹ ሲሆን ከተራ ቁጥር12 እስከ 18 ያሉትም እንዲዚሁ በአንድነት ተተንትነዋል።
ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ኤድስን ከእሳት ጋር አያይዘው ሰዎች ከቫይረሱ እንዲጠነቀቁ ከማስተማራቸው አኳያ ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም እንደሚያተኩሩበት ጉዳይ ሰባቱም በተናጠል ከተብራሩ በኋላ ከተመሳሳይነታቸው አንጻር ደግሞ ከተገኙበት አውድ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በአንድነት ተተንትነዋል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ከማንኛውም አደጋ ባለቤቱ እራሱን መጠበቅ እንዳለበት የሚያስጠነቅቅ ነው። በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው የማይሆን ቦታ ሄዶ ሌላውን ከመውቀስ መጀመሪያውኑ ለይተው ማየት አስፈላጊ መሆኑን ያስጠነቅቃል። ይህም ማለት ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ቫይረስ ሥርጭት ምክንያት ከሚሆኑ ቦታዎች መቆጠብን ያስጠነቅቃል። በተራ ቁጥር 3 ላይ ያለው ኤድስን ከኤሌክትሪክ ጋር በማመሳሰል ሁለቱንም በሩቁ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው እሳት ላይ የተቀመጠ ሰው እንደሚቃጠል ሁሉ ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ራሱን ያጋለጠ ሰው ተጎጂ መሆኑን በማስገንዘብ ጥንቃቄ ማድረግን ያሳያል። በተራ ቁጥር 5 ላይ የተገለጸው ከላይ ኤድስን ከኤሌክትሪክ ጋር እንዳመሳሰለው ሁሉ እዚህ ላይ ኤድስን ከእሳት ጋር በማመሳሰል ሁለቱንም በሩቁ

መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል። በተራ ቁጥር 6 ላይ የሚገኘው ልክ እሳት ከተቆሰቆሰ እንደማይጠፋ ሁሉ ቫይረሱ ካለበት ሰው ጋር ወሲብ መፈጸም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት እንዲስፋፋ የሚያደርግ ተግባር መሆኑን ያመለክታል። በተራ ቁጥር 7 ላይ የተገለፀው ደግሞ ኤድስን ከሞጀሌ ጋር በማመሳሰል ልክ ሞጀሌ ቀስ ብላ ሰውነትን እንደምትቆጠቁጥና በሕመሟ ሰውን ሠላም እንደምትነሳ ኤድስም ወደ ሰውነት ክፍል ከገባ በኋላ ቀስ በቀስ የሰዎችን ሰውነት የሚያመነምን መሆኑን በመግለጽ ከቫይረሱ ሥርጭት ሰዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ የማስጠንቀቅ መልዕክት አለው።

እነዚህ ሰባት ምሳሌያዊ ንግግሮች የተሰበሰቡት ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የትኞቹ እንደሆኑ ተማሪዎች እና በቃለ-መጠይቅ መረጃ አቀባዮች[107] በተጠየቁበት ወቅት ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የመጣው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመሆኑ በቀጥታ በሽታውን አስመልክቶ የተባሉት ብዙ ባይሆኑም የጥያቄውን መልስ አውድ በማድረግ ቀደም ሲል ለሌሎች ጉዳዮች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር በማያያዝ መልስ የተሰጡበት ነው።

ከትንተና ቲዮሪያቸው አኳያ ስንመለከታቸው ከአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች አንጻር የሚታዩ ናቸው። ይኸውም መረጃዎቹ ከተገኙበት አውድ አንጻር ሲታዩ በአውዳዊ ቲዮሪ (Okepewho, 1992; Ben-Amos, 1993; Bauman, 1977)ከገለጹአቸው ባህላዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች አኳያ የሚታዩ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዱ ግለሰብ ከቫይረሱ እራሱን እንዲጠብቅ የሚያስጠነቅቁ ናቸው። በሌላ መልኩ ካለመጠንቀቅ የተነሳ ለሚመጣው ጉዳት ተጠያቂው ማንም ሳይሆን ባለቤቱ ራሱ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። ከዚሁ አኳያ እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዲጠብቅ በማስጠንቀቅ የሚያስተምሩ ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ ግለሰብ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመቆጣጠሩ እና በመከላከሉ ረገድ ሃለፊነትም እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ናቸው።

ካስተላለፉት መልዕክት እና ከተነገሩበት ዓላማ አኳያ ደግሞ በተግባራዊ ቲዮሪ ይታያሉ። ምክንያቱም የዚህ ቲዮሪ ዋና አላማ እያንዳንዱ የፎክሎር ቅንጣት ለሰው ልጅ ካላቸው የትርጉም አኳያ ከመቆጣጠር እና ከማስተማር አገልግሎት አንጻር የሚገለጹ ናቸው (Malinowski, 1946; Bahuman,1977) እና ፈቃደ፣1991) ። በሌላ በኩል ባህሉን ጠብቆ

[107] (ከተማሪዎች መልስ የሰጡ እና ከመረጃ አቀባዮች አቶ በጅጋ ሮሪሣ እና አቶ ታደሰ ደህኔ፣ ህዳር13 ቀን 2007 ዓ.ም.)።

ከማቆየትና ሥነቃሎቹን ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፉ አንጻር በክልላዊ ቲዮሪም ይቃኛሉ።

ከተራ ቁጥር 8-11 ያሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች በጥቅል መልኩ ሲታዩ አንድ የሌለ የሚመስል ነገር ተደብቆ ቆይተው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ብቅ ብሎ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ የለም ብለው ከመዘናጋት ጥንቃቄ ማድረግን የሚያስተምሩ ናቸው። ዘርዘር ባለ ሁኔታ መልዕክቶቹ ስናያቸው ደግሞ በተራ ቁጥር 8 ላይ ያለው የተኛ አንበሳ የሞተ እንደሚመስል ሁሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ጠፍቷል የለም፤ ለሚሉት እንዳይዘናጉ የሚያስጠነቅቅ ነው። በተራ ቁጥር 9 ላይ የሚገኘው ከላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን እያለ ጸጥ ያለ ነገር የተነሳ ዕለት ብዙ ጥፋት እንደሚያደርስ የሚያስጠነቅቅ ነው። በተራ ቁጥር 10 ላይ ያለው ደግሞ የተዳፈነ እሳት እንደማይጠፋ ሁሉ በአሁኑ ዘመን ኤድስ እየቀነሰ ነው ለሚሉት እስካልጠፋ ድረስ የበሽታው ገዳይነት የሚቀጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው። በተራ ቁጥር 11 ላይ የተገለጸው በተራ ቁጥር 9 ላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን አንድ በቁጡ ባህርይ የሚታወቅ ሰው ዝም ካለ ውስጥ ውስጡን የሚያብሰለስሉ ጉዳዮች እንዳሉት በመገንዘብ ዝምታውን በበጎ መንገድ መውሰዱ ሞኝነት የመሆኑን ያህል የኤች አይ ቪ/ኤድስ ገዳይነት እንደ ድሮ ስሙ አለመግነን በጉዳዩ ላይ ዝምታን የሚያስከትል ከሆነ ወይም ሰዎች ስለ በሽታው የማይወያዩ ከሆነ ሥርጭቱ ውስጥ ውስጡን እንደሚቀጥል የሚያስገነዝብ ነው።

ከመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ምሳሌያዊ ንግግሮቹ ከተሰበሰቡበት አውድ እና ከተነገሩበት ሁኔታዎች አኳያ ስንመለከት መረጃዎቹ በተሰበሰቡበት ወቅት በቡድን ተኮር ውይይት ላይ በኢ-ውስን ቃለ-መጠይቅ (unstructured interview) ከተሰጠው መልስ የተገኙ ናቸው። ይኸውም ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በአሁኑ ሰዓት እየቀነሰ በመምጣቱ ጉዳቱ ይህን ያህል ባለመሆኑ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መወያየቱ ምን ይጠቅማል? ተብሎ ለተሰነዘረው ጥያቄ በምሳሌያዊ ንግግሮቹ ተደግፎ ከተሳታፊዎቹ[108] የተሰጡ መልሶች ናቸው።

የእነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች አጠቃላይ መልዕክት ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በአሁኑ ዘመን እየቀነሰ መጥቷል ለሚለው አባባል ለበሽታው አስተማማኝ የሆነ መድኃኒት እስካልተገኘ ወይም ቫይረሱ ከዓለም ላይ እስካልጠፋ ድረስ መዘናጋት እንዳይኖር ከመተላለፊያ መንገዶቹ ራስን መጠበቁ ብልህነት መሆኑን የሚያስጠነቅቁ ናቸው።

[108] (አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ ወ/ሮ ጠጅቱ ቂጠታ፣ አቶ ደረጀ መኮንን እና አቶ ሙሉጌታ አያኔ፣ ህዳር፡ 2007)።

ከተራ ቁጥር 12 እስከ 18 የተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች አንድ ጥሩ ነው ብለው ያሰቡት ወይም ያደረጉት ነገር በሌላ ጎኑ ችግር ውስጥ የሚከት መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። በመሆኑም ወሲባዊ የሆኑ ግንኙነቶችን ከማከናወናችን በፊት ጥቅሙንና ጉዳቱን በማመዛዘንና ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን የሚያሳስቡ ናቸው። ከዚሁ አኳያ ካስተላለፉት መልዕክት አንጻር ተመሳሳይነት አላቸው። ይሁን እንጂ ካተኮሩበት ጉዳዮች አንጻር እያንዳንዳቸው ለየብቻ የሚገለጹ ናቸው። ስለዚህ ከተነገሩበት አውድ አኳያ ለምን እንደተባሉ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር 12 ላይ ያለው አንድት ቆንጆ ልጅ ከምትገለጽበት መንገድ አንዱ በጡቷ ነው። ለዚህም በሥነቃል ስንኝ ተቋጥሮለት "ጉች፣ ጉች ያለ ጡት" እየተባለ የሚዘፈነው። እንዲህ ዓይነቷን ልጅ ደግሞ ሁሉም ለወሲበዊ ፍላጎት ማርኪያነት ይፈልጋታል። ወሲባዊ ግንኙነቱ ደግሞ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጥ መሆኑን ለማስገንዘብ የተነገረ ሲሆን ቆንጆዎቹም ሆኑ ቆንጆ ፈላጊዎች ከወሲባዊ ግንኙነት ራሳቸውን እንዲቆጥቡ ለማስጠንቀቅ ነው። አባባሉ ከላይ እንደተገለጸው ማህበረሰቡ ቆንጆን ለወሲባዊ የፍቅር ግንኙነት መመኘቱ እና ከተሰካለትም መጎነታተሉ ስለማይቀር በርከታ ሰዎች በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ላይ ከተሰማሩ ጡት ቆንጅናን የማጉላቱን ያህል ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ያጋልጣል ማለት ነው። አባባሉ ለጥንቃቄ ያህል ነው እንጂ ቆንጆ የሆኑ ሁሉ ኤድስ አለባቸው ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም።

በተራ ቁጥር 13 ላይ የሚገኘው ከላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ይኸውም ቆንጆን የተመኘና ወደ ወሲባዊ ግንኙነት የሚያመራ ከሆነ አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጋልጦ በሽታው ጉዳት እንደሚያስከትልበት በማሳሰብ ከእንዲህ ዓይነት ተግባር እንዲቆጠብ ለማስጠንቀቅ ነው።

በተራ ቁጥር 14 ላይ የተጠቀሰው ምሳሌያዊ ንግግር የሚያመለክተው ሁልጊዜ በአሬራ መዋኘት የለመደች ዝንብ አንድ ቀን የፈላ ውኋ ወይም ከፍተኛ ሙቀት ያለው ፈሳሽ ውስጥ ገብታ ሕይወቷ እንደሚያበቃ የሚገልጽ ነው። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ከተምሳሌታዊ ቲዮሪ አንጻር ሲተነተን "ጤንነት" "ከአሬራ" ጋር፣ "የፈላ ውሃ" "ከኤደስ" ጋር እና "ሰው" "ከዝንብ" ጋር በማመሳሰል የቀረበ ነው። ይህ ማለት ድሮ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ባልነበረበት ዘመን ከውሽማ ወይም ከእሬ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ቢደረግ በጤና በኩል ለሕይወት አሲጊ የሆነ በሽታ አልነበረም። ስለዚህ ወሲባዊ ድርጊቱ በአንጻራዊ መልኩ ጤናማ ነበር

ማለት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ድሮ እንደ ተለመደ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ አደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይሄም ልክ ዝንቧ በአሬራ መዋኘት ለምዳ የፈላ ውሃ ውስጥ ጋብታ የሕይወቷ ፍጻሜ እንደ ሆነ ሁሉ የሰው ልጅም ድሮ እንደ ለመደ ልቅ ግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈጽም ከሆነ በኤድስ ተይዞ ተሰቃይቶ የሚሞት መሆኑን የሚያመለክት ነው። በአጠቃላይ በዚህ ዘመን ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈጽም ወንድ ሆነ ሴት ከዕለታት አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ መጋለጡ የማይቀር መሆኑን ለመግለጽ ነው። በመሆኑም ሰዎች ከልቅ ወሲባዊ ዲርጊት ራሳቸውን እንዲቆጥቡ የሚያስጠነቅቅ ነው።

በተራ ቁጥር 15 ላይ የሚገኘው አባባል አሞራ በአንድ ቦታ የሚረጋ ሳይሆን ወደ ተለያዩ አካባቢዎች የሚዞር ነው። በዚህ ጉዞ ውስጥ ገደሉን ሁሉ አቅርጦ ስለሚበር በአፉ ይዞት የሚጓዝ ነገር አንድ ቀን በሆነ ስህተት አፉን ሲከፍት ያ በአፉ ያለ ነገር ገደል ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ይህን ምሳሌየዊ ንግግር ከተምሳሌት አንጻር ስናይ “አሞራ” “ከሴተኛ አዳሪ” ጋር “አሞራው በአፍ የያዘ ነገር” “ከሴትየዋ የመራቢያ አካል” ጋር ተመሳስለው የቀረቡ ናቸው። አሞራው ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር በአፉ ያለው ነገር ገደል ውስጥ ከወደቀበት የትም ቀረ (ጠፋ) ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በወሲብ ንግድ ላይ የተሠማራች ሴት (ሴተኛ አዳሪ) በአንድ ቦታ ስለማትረጋ እና ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ስለምትፈጽም አንድ ቀን ለኤድስ መጋለጧ አይቀርም። ይሄም ለሕይወቷ መጥፋት ምክንያት ይሆናል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ለኑሮ ሲባል ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ ወንዱንም ሴቱንም የሚመለከት በመሆኑ አንድ ወንድ ከተለያዩ ሴቶች ጋር ወይም አንዲት ሴት ከተለያዩ ወንዶች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነትን የሚያዝወትር ከሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መጋለጡ የማይቀር ነው። በመሆኑም ማንም ሰው የመራቢያ አካሉን ይዞት ይዞራል ነገር ግን የትም ቦታ   የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈጽም/የምትፈጽም ከሆነ/ከሆነች አደጋው በሕይወት የሚመነዘር መሆኑን አውቀ ሰዎች ከእንደዚህ ዓይነት ተግባር እንዲታቀቡ ለማስጠንቀቅ የተነገረ ነው።

በተራ ቁጥር 16 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክት ለአንድ ቀን ደስታ ተብሎ በሚፈጸም ወሲብ ምናልባት ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚን ሊያስከትል እንደሚችል የሚያስጠነቅቅ ነው። ሥነቃሉ ወሲብ ለሰው ልጅ ደስታን የሚፈጥርለት

ቢሆንም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በተስፋፋበት ዘመን በወሲብ አፈጻጸም ላይ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ያስተምራል።

በተራ ቁጥር 17 ላይ ያለው ሁሌ ጭፈራ ማብዛት ለቅሶንም ሊያስከትል እንደሚችል የሚያስጠነቅቅ ነው። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ከተነገረበት አውድ አኳያ ሲታይ ወጣቶች ለወሲባዊ ግንኙነት መጣደፋቸው የወደፊት ሕይወታቸውን አደጋ ላይ መጣል እንደሚችሉ ለማስገንዘብ ነው። ስለዚህ ራስን ከልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መቆጠብ ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መጠንቀቅ መሆኑን ለመግለጽ የተነገረ ነው።

በተራ ቁጥር 18 ላይ የሚገኘው አንድ ሰው አዋቂ ነው የሚባለው ራሱን ችግር ውስጥ ከሚከቱት ነገሮች የሚጠነቀቅ ሰው መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው። በተመሳሳይ መልኩ በአሁኑ ዘመን ሰዎች ብልህ ናቸው ማለት የሚቻለው እስካሁን ድረስ መድኃኒት ካልተገኘለት ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጠንቅቆ ራሱን መከላከል የሚችል ሰው ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

እነዚህ ከተራ ቁጥር 12 እስከ 18 የተዘረዘሩት ሰባቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከወሲባዊ ግንኙነቶች ጋር የታያያዙ ናቸው። በመሆኑም ሥነቃሎቹ ከተነገሩበት አውድ አንጻር ከላይ በተገለጸው ሁኔታ አውዳዊ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። ከተግባራዊ ቲዮሪ አንጻርም ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲጠነቀቁ የማስተማር ሚና እንዳላቸውም በትንታኔው ውሰጥ ተገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ እነዚህ 18 ምሳሌያዊ ንግግሮች በአንድነት ሲታዩ በወሲባዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮራቸው ከጤና እና ወሲባዊ ቲዮሪዎች አንጻር የሚገለጹ ናቸው። ከዚሁ አኳያ በክለሳ ድርሳን ውስጥ እንደተገለጸው የወሲብ ቲዮሪ ዋና ትኩረት ወሲብ ለሰው ልጅ ከመሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ እና የግለሰብ ደስታን ለመፍጠር እንዲሁም ዝርያን ለመቀጠል የሚያገለግል መሆኑን በዘርፉ ምርምር ያደረጉ ምሁራን[109] ያብራራሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች ወሲባዊ ደስታን ለማግኘት ሲሉ በቫይረሱ እንዳይጠቁ ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ለመከላከል በወሲባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡ ናቸው። በሌላ መልኩ ከጤና ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ አኳያ ይተነተናሉ። ይህ ቲዮሪ የሰው ልጅ ወሲባዊ ባህርይን ከማህበረሰቡ የሚማር መሆኑንና ይህንንም በቋንቋ

[109] Susan Moore & Doreen Rosenthal (2006: 38-44)

አማካይነት እንደሚገለጽና ሁሉም ማህበረሰብ ባህሉን፣ ወጉን፣ እምነቱን፣ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን መሠረት የሚያደርግ የራሱ የሆነ የወሲብ አፈጻጸም ባህርይ[110] አለው። ይህም የሚያሳየን ወሲባዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የማህበረሰቡ ባህል ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ግለሰብ በግብረ-ስጋ ግንኙነት አፈጻጸም ላይ ግለሰብ ተኮር ጥንቃቄ ማድረግ እንደለበት የሚያስገነዝቡ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የዘፈኖቹን ትንታኔ ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 27. ኤድስን ለመከላከል የሚያስጠነቅቁ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Suufii yaa Suufii dhirsii kee Caancoo bule,	ሱፊ አንቺ ሱፊ ጫንጮ አደረ ባልሽ፣
Eedsiin qabamee dhufuufii.	በኤድሰ ተይዞ ልመጣልሽ።
2. Silaa Qidaamee torbanumaan buuta ,	በየሳምንቱ ቅዳሜ ገበያ ትሄዳለህ፣
ofeeggadhu eedsii kana fiddee duutaa.	ተጠንቀቅ በኤድስ ተይዘህ ትሞታለህ።
3. Eedsii yaa dhukkuba bara,	የዘመኑ በሽታ አንተ ኤድስ አጅሬ ፣
Ani sin tuquu nanxuqin adaraa.	እኔ አልደርስብህም አትድረስ ከበሬ፡፡
4. Dhukkuba Eedsii yaa tiraakoomaa,	የኤድስ በሽታ አንተ ትራኮማ፣
Achi narraa gori ani nan soomaa.	ዞር በልልኝ ወዲያ እኔ ልጹማ።
5. Yoo dhungoo barbaadde kunooti hidhinii,	መሳም ካስፈለገህ ከንፈሩ ይኸውልህ ፣
Yoo hirriiba sibarbaachise kunooti sireenii,	መኝታ ከፈለግህ አልጋው ይኸውልህ ፣
Iyyitullee hin argattu waan gara kanii,	ብትጮህ ብትፈርጥ አታገኝ ከሌላው፣
Kan nama nyaatu dhufe bineensi hamaanii.	ክፉ ጅብ መጣ አሉ ሰው አይምሬው።
6. Geeshoo baalatu daraaraa ya baala ataraa,	ጌሾ ቅጠሉ ያብባል የታለ የአተሩ ፣
Eedsii baratu maraachee ofeegi adaraa.	ኤድስ አብዷልና ለጥንቃቄ ተባበሩ።
7. Baaqeelli asheetee garbuunis addaate,	በቈላ አሽቷል ገብስ ነጥቷል፣
Eegaa yaa barataa jabbadhuu baradhuu,	እንግዲህ አንተ ተማሪ ጠንክርና ተማር፣
Dhibeerraa ofeegii Yoo jiraachuu barbaaddee.	ራስህን ከበሽታ ጠብቅ ከፈለክ መኖር ።
8. Dukkana hideemnii mandureetti buutaa,	በጭለማ አትህድ ከበረንዳ ትላተማለህ፣
Lakkii hin muddamnii dhibee Eedsiin duutaa.	ተው አትቸኩል በኤድስ ትሞታለህ።
9. Eedsii, Eedsii jedhanii Eedsiin maraataadhaa,	ኤድስ፣ ኤድስ አሉ ኤድስ እኮ እብድ
Kan of hin eegneef xannee albaasaadha.	ነው፣

[110] Banks and Banks (2001)

	ላልተጠነቀቀ ጠኔ አስቀዛኝ ነው።
10. Gammoojjii bu’an malee,	ቆላ ካልወረዱ፣
Eedsiin nama hindhiisuu du’an malee.	ኤድስ ሰውን አይለቅም ካልሞቱ።
11. Jaalanneen nadheen Addis Abaatii,	መውደድስ ካልቀረ የአዲሳባን ሴት፣
Caammaan xaqqixaqqiidha	ጫማዋ የምለው ጠቅ ጠቅ፣
Namaaf bitti carqiidha,	ለሰው ትገዛለች አሉ ጨርቅ፡፡
Yaa gurbaa carqqiin xiqimii hinqabuu;	አንተ ልጅ ምን ይጠቅማል ልብስ፣
Eegaa ofeeggadhu eedsiin hakmii hinqabuu.	ተጠንቀቅ ሐኪም የለውም ኤድስ።
12. Gurbattiin nanaa,	አንተ ልጅ፣
Finfinneerraan buute jeettinii,	አዲሳባ ላይ አረፈ አሉ ጄት፣
Gurbattiin nanaa,	አንተ ልጅ፣
lakkii katmaa kana hinbubulni,	ተው እንዳታዘወትር ከተማ ማደር፣
Gurbattiin nanaa,	አንተ ልጅ፣
Tasa sigalaafatti Eedsinii.	ድንገት ያጠፋሃል ያ ቀሳፊ ኤድስ።
13. Ijaara warra Tulluu,	የነ ቱሉን ቤት አሰራር፣
Jjala dhaabbateeti laala Qeesinii,	ከሥር ሆኖ ሊያየው ገባ ቄስ፣
Dargaggoo jedhan malee,	ወጣቱን ይላሉ እንጂ ፣
Manguddoo rafaarrafe Eedsiinii.	ሽማግሌውን ረፈረፈው ኤድስ ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ዘፈኖች የተሰበሰቡት ማህበረሰቡ ካከበራቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረበዓለት እንዲሁም በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሰዎች በቡድን እና በግላቸውም ሲዘፍኑ በተገኘው ጊዜ እና አጋጣሚ ነው።

እነዚህ ዘፈኖች ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ /ኤድስ እንዲከላከሉ የጥንቃቄ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው። በመሆኑም ካተኮሩበት ዓላማ አንጻር ሁሉም ተመሳሳይነት አላቸው። ስለዚህ ለትንተና እንዲመች ተመሳሳይ የሆኑት ተጣምረው በአንድነት ተተንትኗል። የተለየ መልዕክት ያላቸው ደግሞ በተናተል ተተንትነዋል።

ከተራ ቀጥር 1 -5 ያሉት ዘፈኖች አምስቱም ከተመሳሳይነታቸው አንጻር ለኤድስ የሚያጋልጡ አከባቢዎችን በመጠቆም፤ ኤድስን ከልዩ ልዩ ነገሮች ጋር በማመሳሰል ሰዎች ከቫይረሱ እንዲጠነቀቁ የሚያስገነዝቡ ናቸው። ካተኮሩባቸው ጭብጦች ደግሞ የእያንዳንዳቸው ትኩረት እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ሱፊ የምትባል ሴትዮ ባል ሁልጊዜ ከተማ እንደሚያድር የተገነዘበች የሱፊ ጓደኛ ሱፊ ከባሏ ጋር የምታደርገውን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ኮንዶምን በመጠቀም ጥንቃቄ እንድታድርግ የሚያሳስብ ነው። በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኝ የቃል ግጥም ቅዳሜ በየሳምንቱ በገበያ ምክንያት ወደ ከተማ የሚመላለሰውን ሰው ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዳይጋለጥ የሚያስጠነቅቅ ነው።

እነዚህ ሁለቱም ዘፈኖች ከአቶ በዳሳ ጉረሙ ኤድስ ለመከላካል ከሚመክሩ[111] ዘፈኖች ጋር ተመሳሳይነት ኣላቸው። ይህም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት የሚበዛው በከተማ መሆኑን በጉዳዩ ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት የሚያስጠነቅቁ ናቸው። በመሆኑም ከማህበረሰቡ የፈለቁ እነዚህ ዘፈኖች የችግሩን አሳሳቢነት በማስገንዘብ በወሲብ ዙሪያ ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚያስተምሩ ናቸው።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የሚገኝ ዘፈን መልዕክት የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሽታን አስከፊነት በመግለጽ ሰዎች ለበሽታው ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥንቃቄን የሚያስተምር ነው። ይህም በሽታው ድሮ ያልነበረ እና ዘመን አመጣሽ ጣጣ መሆኑን በመጥቀስ ለችግሩ ላለመጋለጥ በአልነካህም አትንካኝ አባባል በወሲብ ዙሪያ ጥንቃቄ ማድረግን የሚያመለክት ነው።

በተራ ቁጥር 4 ላይ የሚገኘው ደግሞ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን ከዓይን በሽታ ጋር በማመሳሰል አትጠጋኝ ዓይነት ማስጠንቀቂያ መልእክት አለው። ከተምሳሌታዊ ቲዮሪ አኳያ በወካይና ተወካይ መካከል ያለን ዝምድና ለመግለጽ "ትራኮማ" "በኤድስ" ተመስሎ የቀረበበት ነው። ይህም የትራኮማ በሽታ ዓይን እስከ ማጥፋት ድረስ እንደሚሄድ ሁሉ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስም ከመግደሉ በፊት   በበሽታ እንደሚያሰቃይ ይጠቁማል።

ይህንን አስመልክቶ ማህበረሰቡ ስለ ኤች አይ ቪ /ኤድስ ያለውን እውቀት ለማዳበርና ለዚህ አሳሳቢ በሽታ ባህላዊና ማህበራዊ መፍትሔዎችን ለመፈለግ ማህበረሰብ ተኮር ጥናት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን Landau-Stanton & CLements, (1993: 4-15) ይመክራሉ። ከዚህ አኳያ ይህ ዘፈን ማህበረሰቡ ለሥነ-ቃሉ ከሰጠው ትርጉም አንጻር ስንመለከት ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን ከትራኮማ በሽታ ጋር በማመሳሰል የበሽታው አስከፊነት የጎላ መሆኑን ያስጠነቅቃል። በሌላ መልኩ ደግሞ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ሃይማኖተኛ ሰው የሃይማኖቱ ደንብ

[111] በዚህ ጥናት ውስጥ ኤድስን ለመካካል ከሚመክሩ ውስጥ በተራ ቁጥር 3 ላይ (ከመረጃ አቀባይ በዳሳ ጉረሙ መስከረም 25 ቀን 2007 ዓ.ም) የተገኘውን ዘፈን ይመልከቱ።

ስለሚያስገድደው በጾም ወቅት ምግብ እንደሚጾም ሁሉ የግብረ-ስጋ ግንኙነቱንም በበሽታው ላለመያዝ መተው አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ይገልጻል።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የሚገኘው ዘፈን መልእክት ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ከሚተለላለፍባቸው መንገዶች አንዱ እና ዋንኛው ወሲብ መሆኑን በማስገንዘብ በወሲብ አፈጻጸም ላይ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ያስተምራል። የዚህን ዘፈን የመጀመሪያ እና ሁለተኛውን ስንኝ ሴቷ ለፍቅር ተጓዳኝዋ አማራጭ መስጠቷን እና ከወሲብ መገለጫ አንዱ የፍቅር መገለጫ የሆነውን መሳም እንደፈቀደችለት ያሳያል። ሦስተኛው እና አራተኛው ስንኞች ግን ብትጮህም ብታብድም በምንም ዓይነት ሁኔታ የግብረ-ስጋ ግንኙነትን አልፈቅድልህም፤ ምክንያቱም ሰው በላው አውሬ መጥቷል እና እጠነቀቃለሁ የሚል መልእክት አለው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ወሲብ ተፈጥሯዊ በመሆኑ ባንድ አልጋ ላይ ተኝተው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሳይፈጽሙ በመሳሳም ብቻ ማደሩ ከባድ ነው። ምክንያቱም መሳሳሙ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ስለሚቀሰቅስ አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ አስከፊነት ፍቅርኛሞች እንኳን አንዱ አንዱን እንድጠራጠር አድርጎ ይህን ያህል ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስገድድ መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ቫይረሱ በሰው ልጅ ወሲባዊ እርካታ እና እርባታ ላይ ጭንቀትን እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን የሥነልቦና ተመራማሪዎች Brooks and Furstenbrg(1989: 251) ይገልጻሉ።

ይህ ዘፈን ከደጋፊ የትንተና ቲዮሪ አንጻር በተምሳሌታዊ የመተንተኛ ዘዴ ይገለጻል። ይኸውም በቃል ግጥሙ ውስጥ "ኤድስ" "በጅብ" ተወክሎ ቀርቧል። በወካይ እና በተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና ስንመለከት ሁለቱም የሰው ልጅን የሚበሉ ወይም ሕይወትን የሚያጠፉ ጠላቶች በመሆናቸው ተመሳሳይነት አላቸው። የጅብን የሰው ልጅ ጠላትነት ለማሳየት ተጠኚው ማህበረሰብ ሕጻን ጥፋት ሲያጠፉ የሚያስፈራራው Bineensi sii dhufe ትርገሙ ጅብ መጣልህ እያለ ስለሆነ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ/ አመለካከት ጅብ የሰው ልጅ ፀር መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ይህ ዘፈን ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ከሰው በላው ጅብ ያመሳስላል። ስለዚህ የሰው ልጅ በቫይረሱ እንዳይጠቃ ጥንቃቄን ማድረግን የሚያስተምር ነው።

ከተራ ቁጥር 6 እስከ 10 የተዘረዘሩት ዘፈኖች በጥቅሉ ሲታዩ ሰዎች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዳይጋለጡ በማንኛውም ሁኔታዎች ውስጥ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ናቸው። ዘርዘር በላ ሁኔታ የእያንዳንዳቸውን መልዕክት ስናይ ደግሞ በተራ ቁጥር 6 ላይ

ያለው ኤድስን ከእብድ ጋር በማመሳሰል ሰዎች ከቫይረሱ እንዲጠነቀቁ ያስገነዝባል። ይህንን በተመለከተ ቀደም ሲል ኤድስ እና እብድ በተምሳሌት መገለጹ ይታወሳል። በተራ ቁጥር 7 ላይ የተገለጸው በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጠንክረው ከመማር ጎን ለጎን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ራሳቸውን እንዲጠብቁ የሚያስነጠቅቅ ነው። በተራ ቁጥር 8 ላይ የሚገኘው በጨለማ አትሂድ ከግርግዳ ትጋጫለህ ማለቱ አብዛኛውን ጊዜ የግብረሥጋ ግንኙነት የሚፈጸመው በጨለማ መሆኑን ለመግለጽ ሲሆን ከወሲብ አፈጻጸም አኳያ ደግሞ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት የሚያሳስብ ነው። በተራ ቁጥር 9 ላይ የተገለጸው ኤድስ እንደ እብድ የሚቆጠር በመሆኑ ላልተጠነቀቀ ሰው አስቀዝኖ የሚገድል መሆኑን የሚያመለክት ነው። በተራ ቁጥር 10 ላይ ያለው ዘፈን ኤድስ አንዴ ከያዘ ሰውን የማይለቅ መሆኑን እና ለሞት የሚያበቃ አደገኛ በሽታ መሆኑን የሚያስጠነቅቅ ነው።

ከተራ ቁጥር 11 እና 12 የተዘረዘሩት ዘፈኖች የቫይረሱ ሥርጭት ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ በሚገኘው አዲስ አበባ ላይ ትኩረት በማድረግ በዚህ አካባቢ በሚደረግ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ላይ ጥንቃቄ እንዲደረግ በዜማ የተገለጸ ነው። ለዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያትነት እንደተጠቀሰ በኢትዮጵያ ዲሞግራፊክ የጤና ዳሰሳ መረጃ (CSA: 2011) እና (OSSREA፡ 2008) መሠረት አዲስ አበባ ከፍተኛ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት የሚታይባት ከተማ ነች። ከዚህ አኳያ የዚህ ጥናቱ ውጤት እና በጽሑፍ የተገኙ መረጃዎች ተመሳሳይ ናቸው።

በተራ ቁጥር 13 ላይ የሚገኘው በኤች አይ ቪ/ኤድስ እያለቀ ያለው ወጣት ነው የሚለውን አባባል የሚያፈልስ እና እንዲያውም በኤድስ እያለቀ ያለው ሽማግሌ መሆኑ የሚያሳይ ነው። ይህም የሚያመለክተው በዕድሜ የገፉ ሰዎች (shuger Dadi) ወጣት ሴቶችን በገንዘብ እየደለሉ ወሲብ እንደሚፈጽሙ በክለሳ ድርሳን ውስጥ የተገለጸውን በሥነቃል የተረጋገጠነበት ነው። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በዕድሜያቸው የገፉ ሰዎች በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ላይ እንደተሰማሩ በሰፊው ይወራል። በመሆኑም ወጣቶችም ሆኑ ሽማግሌዎች ከእንደዚህ አይነቱ ተግባር እንዲቆጠቡ የሚያስጠነቅቅ ዘፈን ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ 13 ዘፈኖች ከአውዳዊ ቲዮሪ አኳያ ቀደም ሲል እንደተብራራው ከባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ አንጻር የሚታዩ ናቸው ካስተላለፉት መልዕክት አኳያ በተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ከሥነቃል አስጠንቅቆ የማስተማር ሚና አኳያ የሚታዩ ናቸው። የተግባራዊ ቲየሪ ሚናም ቀደም ሲል በሌሎች የሥነቃል ዓይነቶች ትንተና ውስጥ በሰፊው ስለተብራራ ለእነዚህም ተመሳሳይ በመሆናቸው እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።

በሌላ መልኩ ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻር ደግሞ በጤና ቲዮሪ፣ በወሲባዊ ቲዮሪ እና በፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪን መሠረት ያደረጉ ናቸው።

በዚሁ መሠረት ከጤና ቲዮሪ አኳያ በምንፈጽማቸው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ላይ ራሳችንን ከአባለዘር በሽታ በተለይም ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ለመከላከል ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን Brooks & Furstenbrg (1989) ከገለጹት አኳያ የሚታዩ ናቸው።

ከወሲባዊ ትንተና ቲዮሪ አንጻር ሲታዩም በአሁኑ ዘመን የሚፈጸም የግብረ-ስጋ ግንኙነት ወሲባዊ ፍላጎትን ማርካት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን ባህል የተከተለ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ የግለሰብ ወሲባዊ ባህርይም ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት የጎላ ሚና ያለው በመሆኑ በግለሰብ ተኮር የጤና አጠባበቅ አንጻር መታየት አለበት። ይህንን አስመልክቶ በወጣትነት ዘመን የሚፈጸም ወሲብ በአብዛኛው ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ ስለሚከናወን በርካታ ወጣቶች ለኤች ኣይ ቪ. እንደሚጋለጡ Kachingwe et al, (2005) ይገልጻሉ። ከዚሁ አኳያ እነዚህ ዘፈኖች እያንዳንዱ ግለሰብ በወሲብ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት በማስጠንቀቅ የሚያስተምሩ ናቸው።

ከፎክሎር ሥነልቦናዊ ቲዮሪ አንጻር ስተነተኑ ሰዎች በውስጣቸዉ የሚያስቡትንና የሚፈልጉትን እንዲሁም ሀሳባቸውንና አመለካከታቸውን ለመረዳት የሥነቃል ሚና ከፍተኛ መሆኑን እንመለከታለን። በመሆኑም የአንድ ሕዝብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ጭንቀት፣ ተስፋ፣ ምኞት፣ ሀዘንና ደስታ ሥነቃሉ ውስጥ ስለሚገኝ እነዚህን ምንጮች በማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከት ማወቅ እንደሚቻል ፈቃደ (1991፡50) ይገልጻል። ስለዚህ እነዚህ አሥራ ሦስቱም ዘፈኖች ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት ሰዎች ከልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት እንዲታቀቡ የሚያስጠነቅቁ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል የኤች አይ ቪ/ኤድስ መኖር በሰዎች ላይ ፍርሃት እና ጭንቀት ከመፍጠሩ አኳያ በማስፈራራት ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ የሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች ትንታኔን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

7.2.3 የሚያስፈራሩ የሥነቃል ዓይነቶች ይዘት ምደባና ትንተና

ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ የማስፈራራት ሚና ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶች 44 (25 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 19 ዘፈኖች)[112] ናቸው። እነዚህ የሥነቃል

[112] አባሪ ሰባት፡- ሰዎች ኤድስን እንዲፈሩ የሚያደርጉ የሥነቃል ዓይነቶች ምድብ ሥር የተዘረዘሩትን ይመልከቱ።

ዓይነቶች የሚያተኩሩት ሰዎች ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በመፍራት ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ የሚረዱ ናቸው። ይህም ኤድስ ልክ የሰው ልጅ ቁንጫን በጣቶቹ አሽቶ እንደምገደል ሁሉ ኤቾ ኣይ ቪ/ኤድስም ሰዎችን እንደ ቁንጫ አሽቶ እና አሰቃይቶ የሚገል በሽታ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። በሌላ መልኩ ኤድስ እንደ ሰው በላ አውሬ የሚታይ እና እንደ ሰደድ እሳት የሚፋጅ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ኤድስን እንደ ሽፍታ ነፍሰ ገዳይ በመመሰል የማስፈራራት ሚና ያላቸው ናቸው። በዚህም የተነሳ ኤድስ እስካለ ድረስ ወሲብ መፈጸም ቀርቶ ማፍቀር እና ጋብቻ መፈጽም ራሱ የሚያስፈራ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው።

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች መካከል ለትንተና የተመረጡ 21 (8 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 13 ዘፈኖች) ናቸው። ዝርዝር ትንታኔያቸውን እንደሚከተለው በዝርዝር እናያለን።

ሠንጠረዥ 28. ሰዎች ኤድስን እንድፈሩ የሚያደርጉ

ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Kan gamatti jibban gamana namatti ceeti.	በማዶ የጠሏት ወዲህ ትሻገራለች።
2. Fanxoo madaa ishiirra maqaa ishii.	ቅጥኝ ከቁሱኋ ስሟ።
3. “Du’a hin jibbine,	“ሞትን አልጠላሁም፣
sukkuummaan jibbe.” Jette tafkiin.	መታሸቱን ነው የጠላሁት።” አለች ቁንጫ
4. Obboo jijjiksaan hamma maqaati gaha.	አቶ ረፍርፍ እንደ ስሙ ጨፍጭፍ ነው።
5. Eedsiin akka ibidda saafa’aatti nama guba.	ኤድስ እንደ ቀትር እሳት ሰው ይፈጃል።
6. Bineensa mootii hin qabne.	ጌታ የሌለው አውሬ
7. Dhukkuba qoricha hin qabne.	መድሃኒት የሌለው በሽታ
8. Mukti muka caalu odaadha,	ከእንጨት የሚበልጥ እንጨትኦዳ ነው፣
Dhibeen dheebee caalu Eedsiidha.	ከበሽታ የሚበልጥ በሽታ ኤድስ ነው።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተሰበሰቡት ኤች ኣይ ቪ /ኤድስ እያደረሰ ያለውን ጥፋት በተመለከተ ለመረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ ለቀረበው ጥያቄ ከሰጡት መልሶች የተገኙ በመሆናቸው ትርጉማቸው ከተነገሩበት አውድ አንጻር የሚታይ ነው። ያስተላለፉትን

መልዕክት በጥቅሉ ስንመለከተው ማህበረሰቡ ለበሽታው ያለውን ፍራቻ የገለጸበት ነው። ስለዚህ ከተመሳሳይ ይዘታቸው አንጻር ሁሉም በአንድነት የሚተነተኑ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ ካተኮሩበት ጉዳይ አንጻር ሲታዩ የእያንዳንዱን ትርጉም በተናጠል እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለውን ምሳሌያዊ ንግግር ስናይ በማዶ የሚፈራ ነገር ወደዚህ መሻገሩ የማይቀር መሆኑን ያመለክታል። ይህም ኤች አይ ቪ/ኤድስ አመጣጡ ከውጭው ዓለም መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ መልኩ ቫይረሱ በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ወደ ራስም እንዳይመጣ ያለውን ፍራቻ የሚገልጽ ነው።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ደግሞ የአባለዘር በሽታ የሆነው ቂጥኝ ከቁሱሉ ስሙ የሚያስፈራ መሆኑን ይገልጻል። ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ በቂጥኝ የተያዘ ሰው የወሲብ ፍላጎቱ ከፍተኛ መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ ማንም በዚህ ዓይነቱ በሽታ መያዝንና ቂጥኛም መባልን ስለማይፈልግ ሥነቃሉ ፍርሃትን ያሳያል። እዚህ ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገር አንድ አባባል አለ። ይህም ሰዎች ወሲብ መፈጸምን እና ጉቦ መቀበልን በአደበባይ ይፈራሉ። ሁሉም ግን በሚስጢር ይፈጽሙታል። ይህ ነገር አንዳንድ ሰዎች "በድብቅ ወሲብ እና የሚስጥር ጉቦ ይጣፍጣል" የሚሉትን አባባል(አነጋገር) እውነት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር ቀጥተኛ ትርጉም እንደሚያሳይ ቁንጫ የፈራችው ሞትን ሰይሆን አሟሟቷን ነው። ሥነቃሉ ከተነገረበት አውድ አኳያ ያለው ትርጉም አንድ ሰው ቁንጫን አሽተው እንደሚገድል ሁሉ የኤች አይ ቪ የያዘውን ሰው አመንምኖ የሚገል መሆኑን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ይህ ዘፈን ሰዎች ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያመጣውን ስቃይ በመፍራት ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዲከላከሉ የሚያስተምር ነው።

በተራ ቁጥት 4 ላይ ያለው ኤድስ የሰው ልጅን አሰቃይቶ የሚገድል በሽታ መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህም ውሸት ሳይሆን እውነት እንደ ስሙ አደገኛ መሆኑን እና የሰውን ልጅ እንደቅጠል የሚጨፈጭፍ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በተራ ቁጥር 5 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር በተምሳሌታዊ መንገድ ኤድስን እንደ ቀትር እሳት የሚፋጅ በማስመሰል ሰዎች በሽታውን እንዲፈሩት የተነገረ ነው። ይህ ማለት የሰደድ እሳት ደረቅ እርጥብ ሳይል ያገኘውን ሁሉ አቃጥሎ

እንደሚፈጅ ሁሉ ኤድስም ማንንም ሳይለይ ያጋጠመውን ሁሉ የሚያጠቃ መሆኑን በማሳየት ይህን አስከፊ በሽታ ሁሉም እንዲፈራ እና ከልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ራሱን እንዲቆጥብ የተነገረ ነው።

ከተራ ቁጥር 6 እስከ 8 የተጠቀሱት ምሳሌያዊ ንግግሮች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። ይኸውም ኤድስ የበሽታዎች ሁሉ ጌታ ነው ሲባል እስካሁን ድረስ መድኃኒት ያልተገኘለት በሽታ መሆኑን ለማመልከት ነው። በመሆኑም በሽታ አስፈሪነት ለመግለጽ የተነገሩ ናቸው።

ከትንተና ቲዮሪ አንጻር ስንመለከታቸው ስምንቱም ምሳሌያዊ ንግግሮች የተገኙበት አውድ ቀደም ሲል ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ከተግባራቸው አንጻር ሲታዩ ከሥነቃል አጠቃላይ ተግባር አኳያ ሰዎችን ከልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት የመግታት እና የመቆጣጠር ሚና የሚጫወቱ ናቸው። በሌላ መልኩ ከፎክሎር ሥነልቦናዊ ትንተና ቲዮሪ አንፃር የቫይረሱ መኖር ጭንቀትን የሚፈጠር በመሆኑ ሰዎች በበሽታው መያዝን እንድፈሩ በማድረግ የሚያስተምሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የማስፈራራት ሚና ያላቸውን ዘፈኖች እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ29. ሰዎች ኤድስን እንድፈሩ የሚያደርጉ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Ani aramaa hinaramuu,	እኔ አረም አላርምም፣
Hammaa garbuun gau'tti,	ገብስ እስከሚደርስ፣
Ani Shaggee hin amanuu,	እኔ ቆንጆ አላምንም፣
Hamma eedsiin badutti.	እስካልጠፋ ኤድስ።
Aani dafee hin farramuu,	ቶሎ አልፈርምም፣
Hamma eedsiin badutti.	እስካልተወገደ ኤድስ።
2. Wayaan amma dhufte jinsii yaa jinsii,	አሁን የመጣ ልብስ ጂንስ ነው ጂንስ፣
Hundumatuu uffataa.	ሁሉም ሰው የምለብሰው።
Dhibeen ammaa dhufe Eedsii yaa Eedsii,	አሁን የመጣ በሽታ ኤድስ ነው ኤድስ፣
Hundumatuu sodaata.	ሁሉም ሰው የሚፈራው።
3. Wllagga yaa Lixa biiftuu,	ወለጋ የጀንበር መጥለቂያ፣

Dhagaan Gibee konkolaate,	የጊቤ ድንጋይ ተንከባለለ፣
Waldhabne yaa intala Diimtuu,	ተለያየን አንቺ ቀይ ልጅ፣
Garaan didee na sodaatee.	እኔ እንጃ ፈርቷል ሆዴ።
4. Salaale naga'aa waa bulloo yaabbatuu,	ሰላሌ ደህና ነው ይጋልባል "ቡሎን"[113]፣
Ati fayyaa qabdaa ani hin sanabatuu.	አንቺ ጤነኛ ነሽ እኔ እንጃ መሰንበቴን።
5. Abbaan Taklee naggasee,	አባ ተክሌ ነገሱ፣
Taaboota gammojiiti ta'e malee,	የቆላ ታቦት ሆነ እንጂ፣
Silaa sifudhee bade,	ወስጄሽ ሂልም ነበር፣
Situu baala doobbii ta'e malee.	ልክ እንደሳማ ቅጠል ሆንሽ እንጂ።
6. Ani shamaanee miti wayyaa sindhahuu,	ሸማኔ አይደለሁም ልብስ አልሰራልህ እኔ፣
Wannaa hardhaa keetumaa boruuf sinta'uu.	የዛሬስ ያንተው ነኝ አትጠብቅ ለነጌ።
7. Bofti miila hinqabuu garaachumaan lohaa,	እባብ እግር የለውም በሆዱ ይሳባል፣
Namni Eedsiin qabame halkuu guyyuu bohaa.	በኤድስ የተያዘ ሰው ሌት ቀን ያነባል።
8. Yaa muka baala hinqabnee maaltu koree	ቅጠል የሌለህ እንጨት ማን ይቆርጥሃል፣
Simuraa bubbeetuu siraasa malee,	ንፋስ ያወዛውዝሃል እንጂ፣
Yaa Namni Eedsiin qabamee ,	በኤድስ የተያዘ ሰው፣
mala maaliiti qaba biyyeetu sinyaata malee.	ምን መላ አለው መጨረሻው አፈር ነው።
9. Tanaa gadii xaafii calleechanii,	ከዚህ ገደማ ጤፍ ያነፍሳሉ፣
Baranammoo maal maal odeechanii,	የዘንድሮስ ወሬ መዓቱን ይላሉ፣
Eedsiin dhufee jedhanii,	ኤድስ መጣ ብለው፣
Maqaasaa biyyarra bitinnechanii.	ስሙን አዳረሱ ከዳር እስከ ዳር።
Haatii ilmoo dhabdee,	እናት ልጇን አጣች፣
Ilmoon haadha dhabdee,	ልጅም እናቱን፡፡
Sanyii ilma namaa foon irraa carrisee	የሰውን ልጅ አካል ጨረሰ አመንምኖ፣
Qa'eesi kophaatti hanbisee.	መንደሩም ሰው የለው ቀዬው ኦና ሆኖ።
10. Yaa shaashii amma dhuftee,	አሁን የመጣ ሻሽ፣
Baala zannabee baala zannabee,	ባለ ዘነብ ዘርፍ፣

[113] ቡሎ ዳሌቻ ለሆነ ፈረስ የተሰጠ ስም ነው። በቱለማ ኦሮሞ ባህል በፈረስ ግልቢያ የሚታወቁ ሰዎች ለፈረሱ እንደ አባት ሆኖ በስሙ ይጠሩበታል። ለምሳሌ ለቡሎ ፈረስ፣ አባ ቡሎ፣ ለቀይ ፈረስ አባ ዲማ፣ ለጠይም ፈረስ አባ መጋል፣ ለጥቁር ፈረስ አባ ጉራቻ …ወዘተ ይባላል።

Yaa qorcha Eedsiidha,	የኤድስ መድኃኒት፣
Baala isaa argeetan,	ቅጠሉን አግኝቼ፣
Hundee dhabee.	አጣሁት ሥሩን።
11. Sululta gubbaan manumaa,	ሱሉልታ ጋራውን ቤት ነው፣
Baranuma gaayii ta’e malee;	ዘንድሮ ታረሰ እንጂ፤
Silaa si fudhee bade,	ወስጄሽ እጠፋ ነበር፣
Eedsii tu nafseegadaay ta’e malee.	ኤድስ ነፍሰ ገዳይ ሆነ እንጂ።
12. Gammachuun loon bobbaasee,	ገመቹ ከብቶቹን አሰማርቶ፣
Qarree gubbaa cicibsee;	አስተኛቸው ከአፋፉ ላይ ፡፡
Sin fuudha yaa jaalaleetoo,	አገባሻለሁ ፍቅሪዬ፣
Eedsiin yoo biyya gadi dhiise.	ኤድስ ሲጠፋ ካገር ላይ።
13. Tiifuu, tiifuu binnaanyii,	ካፊያ፣ የካፊያ ብናኝ፣
Yaa Eedsii siifuu iblaanyii.	አንተ ኤድስ ላንተስ ይብላኝ፡፡

እነዚህ ዘፈኖች ማህበረሰቡ ካከበራቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረበዓለት እንዲሁም በልዩ ልዩ አውዶች ሲዘፍኑ በተገኘው ጊዜ እና አጋጣሚዎች የተሰበሰቡ ናቸው።

ዘፈኖቹ ሰዎች ኤች ኣይ ቪ /ኤድስ እያደረሰ ያለውን ጥፋት በመፍራት ራሳቸውን ከቫይረሱ ጥቃት እንዲከላከሉ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው። በማስፈራራት ከማስተማር አንጻር ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው። ይህን እንጂ ከትኩረታቸው አኳያ በተናጠል የተገለጹ ሰሆን ከተመሳሳይነታቸው አንጻር ደግሞ በጣምራ ተተንትነዋል።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ዘፈን ኤድስ እስከሚጣፋ ድረስ ቆንጆን እንደማያምን እና ጋብቻም ለመፈጸም ፍላጎት እንደሌለው ይገልጻል። ከዚህ የምንረዳው በመጀመሪያ ቆንጆ አላማመኑን ሲገልጽ በመቀጠል ደግሞ ይባስ ብሎ በኤድስ ምክንያት ትዳርም መያዝ አለመፈለጉን ይገልጻል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በወሲብ ዙሪያ የበሽታው መኖር በማህበረሰቡ ዘንድ የፈጠረውን ጭንቀት የሚያመለክት ነው።

በተራ ቁጥር 2 ላይ የሚገኘው ዘፈን በተመሳሳይ ሁኔታ ኤድስ የዘመኑ በሽታ መሆኑን እና ሁሉም የሚፈራው ስለመሆኑ ይገልጻል። ከዚህ የምንረዳው መጀመሪያ በግለሰብ ደረጃ ስጋት ፈጥሮ የነበረው በሽታ በሁሉም ማህበረሰብ ላይ ፍርሃት እና ጭንቀት የፈጠረ መሆኑን ነው።

ከተራ ቁጥር 3 እስከ 6 ያሉት ዘፈኖች በሁለቱም ጾታ ፍራቻን የገለጹበት ነው። ይኸውም ወንዱ ተለያየን ሆዴ ፈርቷል፤ አንቺ ደህና ነሽ እኔ መሰንበቴንም እንጃ በማለት ያለውን ስጋት ሲገልጽ፣ እሷም በሽታውን ያመጣህብኝ አንተው ራስ ስለሆንክ ለዛሬው ያንተው ነኝ እንጂ ለወዲፊቱ እኔም የለሁም በማለት ጭንቀቷን ትገልጻለች። እነዚህ ዘፈኖች መልዕክታቸው ኤች አይ ቪ/ኤድስ አንዴ ሰውን ከያዘ ለሞት የሚያበቃ መሆኑንና መለያያታቸውም እስከ መጨረሻው መሆኑን በመረዳት ፍርሃትና ጭንቀታቸውን ይገልጻሉ።

በተራ ቁጥር 7 እና 8 ላይ የሚገኙት የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ያለበት ሰው አንዴ ዳንኩ ሲል ሌላ ጊዜ በሽታው መልኩን እየቀያየረ ሕመሙ ስለማይለቀው ሌሊትም ሆነ ቀን በበሽታ እንደሚሰቃይ የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ቅጠል ያለውን ዛፍ ንፋስ እንደሚያወዛውዘው ሁሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ያለበትም ሰው በሽታው እንደሚያሰቃየውና በመጨረሻም ለሞት እንደሚያበቃው የሚገልጹ ናቸው።

በተራ ቁጥር 9 እና 10 ላይ የተጠቀሱት የዘመኑ ወሬ ሆኖ ሁሉም ስለ ኤች አይቪ/ኤድስ እንደሚያወራ እና ስሙ በዓለም ላይ ገኖ እንደሚገኝ፣ በገዳይነቱም የታወቀ በመሆኑ አንድ ቤተሰብን ጨርሶ ቀየውን ሰው አልባ ማድረጉን፣ በመሆኑም ለዚህ አስከፊ በሽታ መድኃኒት ለማግኘት በተደረገው ጥረት ሕመሙን የሚያስታግዝ ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ በዘላቂነት ኤድስን የሚያጠፋ መድኃኒት አለመገኘቱን "ለኤድስ መድኃኒት አግኝቼው ቅጠሉን አጣሁት ሥሩን።" በሚል ስንኝ እስካሁን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈዋሽ መድኃኒት ያልተገኘለት መሆኑ በዝርዝር የቀረበበት ነው።

ከተራ ቁጥር 11 እስከ 13 የተዘረዘሩት ዘፈኖች ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሁሉም በላይ አስከፊ በሽታ መሆኑ የተገለጸበት ነው። ይኸውም በወሲባዊ ቲዮሪ በየትኛዉም ጊዜና ቦታ የሚገኝ የሰው ልጅ በአብዛኛው ከወሲብ ውጭ አይደለም። ይሁን እንጂ በዚህ አስከፊ በሽታ የተነሳ ጋብቻ ለመፈጸም በሰዎች ላይ ስጋት መፈጠሩን የሚያመለክቱ ናቸው። በመሆኑም ኤድስ እስካልጠፋ ድረስ ትዳር ለመመሥረት ፍርሃት እና ጭንቀት መኖሩን የሚያመለክቱ ዘፈኖች ናቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ 13 ዘፈኖች ትንታኔያቸው በዋናነት ከተሰበሰቡበት አውድ አኳያ የሚገለጹ ናቸው። ይኸውም ኤች አይ ቪ/ኤድስ በማህበረሰቡ ላይ ካሳደረባቸው ፍርሃት እና ጭንቀት አንጻር ከባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ አኳያ የሚተነተኑ ናቸው። በመሆኑም

ማህበረቡ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ-በዓላትን በሚያከብሩበት አውዶች እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ አውዶች እንኳን ሳይቀር የቫይረሱ አስከፊነት በባህላዊ እና በማህበራዊ ሕይወታቸው ላይ ጭንቀት እና ፍርሃት ከመፈጠሩ አንጻር ሁሉም በሥነቃል እየተነጋገረበት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

ካስተላፉት መልዕክት አንጻር ደግሞ በተግባራዊ ቲዮሪ የተገለጹ ናቸው። ከዚሁ አንጻር ከተግባራቸው አኳያ ሲታዩ በማስፈራራት ሰዎችን ከልቅ ወሲባዊ ተግባር የመግታትና የመቆጣጠር ሚና አላቸው። እንደነዚህ ያሉ የሥነቃል ዓይነቶች በጎ ምግባርን በማስተማር፣ ምሥጉንና ድንቅ የሚባሉ የማህበረሰቡ እሴቶች እንዲከበሩ የሚያደርጉ ናቸው። በሌላ መልኩ **ነውር** ተግባራትን በመፈጸም ከባህሉ የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ዳር ዳር የሚሉትን በአርፈህ ተቀመጥ ግሳፄ ወደ ብዙሃኑ ባህላዊ ድርጊት እንዲመለሱ የሚያደርጉ ናቸው። በዚህ ተግባራዊ ሂደት ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሥነቃልን በመጠቀም የበሽታውን አስከፊነት በመግለጽ እያስፈራሩ ማስተማር እንደሚቻል የሚያስገነዝቡ ናቸው።

እስካሁን ድረስ በሦስት ንዑሳን ርዕሶች ሥር ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የማስተማር ሚና የነበራቸውን የሥነቃል ዓይነቶች በትንታኔ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተናል። የሥነቃል ዓይነቶቹ ከላይ በተገለፀው መልኩ የማስተማር ሚና እንዳላቸው ሁሉ ሰዎችን ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የማጋለጥ ሚና ያላቸው በመስክ መረጃ አሰባሰብ ውስጥ ተካተዋል። ከዚሁ አኳያ የእነዚህንም ትንታኔ በሚቀጥለው ርዕሰ ጉዳይ ሥር እንመለከታለን።

7.3 ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች ኣይ ቪ/ ኤደስ እንዲጋለጡ የሚያደርጉ የሥነቃል ዓይነቶች የይዘት ምደባና ትንተና

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር የተመደቡ የሥነቃል መረጃዎች 30 (18 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 12 ዘፈኖች)[114] ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ጭብጥ ሰዎችን ወደ ልቅ ወሲብ የሚገፋፉ ናቸው። ከእነዚህ አባባሎች እና ዘፈኖች መካከል ለምሳሌ “ቆንጆ እና እሸት አይታለፍም”፣ “ኤድስ ከመሸ የለም”፣ ኤድስ “በአረቄ እና በበርበሬ ይጠፋል”፣ “ከድንግል ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ከኤድስ ያድናል” ወዘተ … የሚሉ ይገኙበታል።

[114] አባሪ ሰባት፡- ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎችን ለኤድስን የሚያጋልጡ የሥነቃል ዓይነቶች ምድብ ሥር የተዘረዘሩትን ይመለከቱ።

ከእነዚህ አባባሎች ውስጥ “ቆንጆ እና እሸት አይታለፍም”፣ የሚለው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በተከሰተበት ዘመን ከጊዜው ጋር የሚሄድ አይደለም። በሌላ መልኩ “ከድንግል ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም ከኤድስ ያድናል” የሚለው ድሮ የነበረውን የማህበረሰቡን ወግና ባህል የሚጻረር ነውር ተግባር ነው።

በመሆኑም እንደዚህ ዓይነቶቹ አባባሎች ሰዎች ራሳቸውን ከቫይረሱ እንዳይጠብቁ የሚያዘናጉ እና ለበሽታው የሚያጋልጡ ናቸው። ይህን በሚመለከት ኤድስ እና እኛ በሚል ርዕስ በPatirik Dixon ተዘጋጅቶ ተስፋዬ ሥዩም፣ (2000፡30) ወደ አማርኛ በተረጎመው መጽሐፍ ውስጥ ከቫይረሱ ስለ መፈወስ በየጊዜው አዳዲስና አስደናቂ መድኃኒቶች እንደተገኙ መሰማቱን በመጥቀስ አንዳንዶቹ ከድንግል ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ማድረግ ህመሙን እንደሚያድን ማመናቸው ሙሉ በሙሉ ስህተት መሆኑን ይገልጻል። ከዚህ የምንረዳው አንዳንድ ሰዎች ስለ በሽታው የተዘባ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ነው።

ከዘፈኖቹም መካከል የሴትን ልጅ ውበት በማድነቅ ለወሲብ በማነሳሳት ሰዎች ሞትን እንኳን እንዳይፈሩ የሚያደፋፍሩ ናቸው። ይህንን አስመልክቶ Susan Moore & Doreen Rosentahal, (2006) አንዳንድ ዘፈኖች ወሲብን በመቀስቀስ ሰዎችን ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጡ እና ለቫይረሱም ሥርጭት መባባስ የጎላ ሚና እንዳላቸው ይገልጻሉ።

በዚህ ሥር ከተመደቡ የሥነቃል ዓይነቶች ውስጥ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ባላቸው የቅርብ ግኑኘት 12 (6 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 6 ዘፈኖች) ተመርጠው ከይዘታቸው አኳያ እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

ሠንጠረዥ 30. ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ

እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮች የይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Asheetaa fi bareeda bira hin dabran.	ቆንጆና እሸት አይታለፍም።
2. Afaanii fi fagaara sochoosuu barbaachisa.	አፍ እና ቂጥ ማንቀሳቀስ ይፈልጋሉ።
3. Bareednii fi qarshiin yoo jijjiiran tolti.	ቆንጆና እና ገንዘብ ስቀያይሩት ይሻላል።
4. Hantuunni bolla lamaa hin du’u.	ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም።

5. "Bakkaa dubartiin lafa guuteetti dulumitti naqabde." Jedhe jaarsi.	"ሴቶች በሞሉበት ዘመን፣ እርጂናው ተጫነኝ።" አለ ሽማግሌው።
6. "Anuu maraadhetan Itoophiyaa lixee, Nyaanni isaanii barbarree, Dhugaatiin isaanii kateedhaa." Jedhe Eedsiin.	"እኔም አብጄ ነው ኢትዮጵያ መግባቴ፣ ምግባቸው በርበሬ፣ መጠጣቸው ካቴ[115]።" አለ አሉ ኤድስ።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን በሚመለከት ለመረጃ አቀባዮች በመጠይቅ እና በቃለ-መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ከሰጡት መልስ እና በተገኘው አጋጣሚ ሰዎች ከሚናገሩት የተሰበሰቡ ናቸው። አብዛኞቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታ ወሲባዊ የሚመለከቱ ሲሆኑ አንዱ ቀደም ሲል ለሌላ ጉዳይ ሲባል የነበረ ለጥያቄው የተሰጠ አውዳዊ መልስ ነው። የመጨረሻው በቀጥታ ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ጋር የተያያዘ ነው። መልዕክታቸው ከወሲብ ጋር በተያያዘ መልኩ በአንድ አለመርጋትን የሚያበረታቱ ናቸው። ይኸውም ወሲባዊ ድርጊቶችን በማሞገስ የሰዎችን ፍላጎት በመቀስቀስ ለልቅ ግብረሥጋ ግንኙነት የሚገፋፉ እና ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ናቸው። በመሆኑም በአብዛኛው የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ለማፍረስ ከፍተኛውን ሚና የሚጨወቱ ናቸው።

ከተሰበሰቡበት አውድ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በአውዳዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪ አንጻር ይተነተናሉ። ከደጋፊ መተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ደግሞ ትኩረታቸው በወሲባዊ ጉዳዮች ላይ በመሆኑ ከወሲባዊ ቲዮሪ[116] አንጻር የሚገለጹ ናቸው። በመሆኑም ከተመሳሳይነታቸው አንጻር በጋራ የሚተነተኑ ሲሆን ትኩረት ካደረጉበት ጉዳይ አኳያ ደግሞ በተናጠል የሚታዩ ናቸው።

በዚሁ መሠረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የሚገኙት ተመሳሳይ ትርጉም ስላላቸው በአንድ ላይ የተተነተኑ ሲሆን ከተራ ቁጥር 4 እስከ 6 ያሉት ለየብቻቸው ተተንትነዋል። ዝርዝራቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ያሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች በተለያዩ አገላለጾች ይቅረቡ እንጂ መልዕክታቸው የሴቶች ቁንጅናን በማሞገስ የሰዎችን ወሲባዊ ፍላጎት የሚያነሳሱ እና ለልቅ የግብረሥጋ ግኑኝነት የሚጋብዙ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነው። ከዚሁ

[115] ለባህዊ የአልኮል መጠጥ ለአረቂ የተሰጠ ስም ነው። ሰዎች አረቄን ካቴ፣ ቁንድፍቲ፣ ብልጧ ... ወዘተ ብለው ይጠሩታል።
[116] (Susan Moore & Doreen Rosenthal, 2006)።

ጋር በተያያዘ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሊያጋልጡ የሚችሉ ናቸው። እያንዳንዳቸውን መልዕክት በተናጠል ሲታዩ እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ምሳሌያዊ ንግግር "ቀንጆ እና እሸት አይታለፍም።" በማለት ለልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት የሚያነሳሳ ነው። ይህም ቀንጆ በታየች ቁጥር ለወሲብ መጣደፍንና በአንድ አለመርጋትን ያሳያል። እንደዚህ ዓይነት አባባል በድሮ ጊዜ እንጂ በአሁኑ ዘመን ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንደሚያጋልጥ መረጃ አቀባዮች[117] ይገልጻሉ።

በተራ ቁጥር 2 ላይ ያለው "አፍ እና ቂጥ እንቅስቀሴ ይፈልጋሉ።" የሚለው አባባል አፍ ለንግግር እንደተፈጠረ ሁሉ የሴት መራቢያ አካልም በግብረ-ስጋ ግንኙነት ወቅት እንቅስቃሴ በማድረግ ለወሲብ እርካታ መዋል አለበት የሚል ትርጉም አለው። ይህ አባባል ለወሲብ የሚያነሳሳ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ወሲብን ለማጣጣም ይጋብዛል። በአፍ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ገብተው ይደቃሉ። በተመሳሳይ መልኩ ሁልጊዜ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በወሲባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የምትገኝ ሴት ለልቅ የግብረሥጋ ግንኘነት መዳረጉዋን ያመለክታል። ይህ ድርጊት ደግሞ በጥንቃቄ ካልተደረገና የእንቅስቃሴ ጣዕም ለመለየት የግብረሥጋ ግንኙነቱ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የሚቀጥል ከሆነ አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የመጋለጥ አደጋን ያስከትላል።

በተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸው ገንዘብ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ተቀያይረው ትርፍ እንደሚያመጡ ሁሉ ቆንጆን መቀያየርም ወሲባዊ እርካታን ያስገኛል የሚል ትርጉም አለው። እንዲህ ዓይነቱ አባባል ይበልጥ ለግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚያነሳሳ ነው። ይሁን እንጂ ንግዱ በሚገባ የተጠና ካልሆነ ትርፍ ሊያስገኝ አይችልም። አንዳንዴ ከፍተኛ ኪሳራም ሊያስከትል ይችላል። ልክ እንደ ንግዱ ቆንጆ መቀያየሩም ጥንቃቄ ካልተደረገበት ለአስከፊው ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሽታ ማጋለጡ አይቀርም።

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው "ሁለት ጉድጓድ ያላት ዓይጥ አንዱ ቢደፈንባት በአንዱ ትገባለች።" ከሚለው አባባል ጋር የሚያያዝ ነው። ምሳሌያዊ ንግግሩ ከተነገረበት አውድ አኳያ ለማለት የተፈለገው ሁለት የወሲብ ጓደኛ ያለው ሰው ባንዱ ባይረካ በሌላኛው መርካት ይችላል የሚል ትርጉም ያዘለ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አባባል ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ይጋብዛል። ድግግሞሹም አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ያጋልጣል።

[117] አቶ ጣሳው በየነ እና አቶ ደረጀ መኮንን (ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የተገለጸው አባባል ድሮ ያልነበሩ ቆንጆዎች አሁን በሞሉበት ዘመን የሽማግሌው የወሲብ ችሎታ መዳከሙን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ ዘመኑ እንኳንስ አርጅተው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ለመፈጸም ይቅርና የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ መኖር ለወጣቶቹም ቢሆን የሚያጓጓ አይደለም።

በተራ ቁጥር 6 ላይ የሚገኘው ኤድስ አረቄ እና በርበሬ የሚመገቡ ሰዎችን አይዝም ቢይዝም እንኳን ተቃጥሎ ይጠፋል የሚል ትርጉም አለው። ይህ አባባል "ኤድስ ከመሸ የለም" ከሚለው አነጋገር ጋር ተመሳሳይ ነው። እንዲያውም ኤድስ በአብዛኛው የሚገኘው ሌሊት ነው። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚፈጸመው ሌሊት በመሆኑ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የመጋለጡም አጋጣሚ ከቀን ይልቅ ሌሊት ይበዛል። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነቶቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሁን ካለንበት ዘመን ጋር የማይሄዱ ናቸው።

እነዚህን ስድስቱንም ምሳሌያዊ ንግግሮች ከመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻር ስንመለከታቸው ከላይ እንደተገለጸው ከተነገሩበት አውድ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር የሚታዩ ናቸው። ከዚሁ አኳያ በዋናነት ከአውዳዊ እና ከተግባራዊ ቲዮሪ አኳያ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ቀደም ሲል ከተተነተኑ የሥነቃል ዓይነቶች ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው አዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።

ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር ሲታዩ ደግሞ ከማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም አኳያ ስንመለከታቸው በአብዛኛው ቆንጆን በማሞገስ ወሲባዊ ፍላጎትን የሚቀሰቅሱ በመሆናቸው ሰዎችን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ አደገኛ አባባል ናቸው። በመቀጠል ከእነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዘፈኖችን እናያለን።

ሠንጠረዥ 31. ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎች ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

Afaan Oromootiin	የአማርኛ ትርጉም
1. Salaaleetti galanii,	ሰላሌ ተገብቶ፣
Shugguxii malee maa hidhatanii,	ሽጉጥ ነው እንጂ ምን ይታጠቃል፣
Shaggituu jaalatanii,	ቆንጆ ልጅ ወዶ፣
Dhibama garaa maa himatanii?	የሆድ በሽታ ለምን ይነገራል?

2. Yoon asumaa gadi laaluu,	ስመለከት ወደ ታች ፣
Gaangeen marfii dhibba baatti,	በቅሎ መቶ መድፍ ተጭናለች፣
Yoon siif jedhee du’e maalii,	ብሞትልሽስ ምን አለበት፣
Du’an biyyeen nama nyaatti.	ሞቼስ አፈር ብትበላኝ።
3. Osumaan qotiisa deemuu,	ስሔድ ወደ እርሻዬ ፣
Nagaraftee yaa qaccee too,	ገረፈኝ ጅራፌ፣
Yoon siif jedhee du’ee maalii,	ላንቺ ብዬ ብሞት ምን አለበት፣
Namarartuu bar nafseen too.	አልሳሳም እኮ ለነፍሴ።
4. Osumaan qotee qotuu,	ማረስ ካለብኝስ፣
Qamadii malee hin qotuu,	የማርሰው ስንዴ ነው፣
Osumaan obese, obesuu	መታገስ ብኖርብኝ አንኳን
Morma shggituu hin obsuu.	የማልታገሰው የቆንጆን አንገት ነው።
5. Hindhaamuu ibiddii kee,	አልጣፋ አለ እሳትሽ፣
Halayyaa bile jalattan dibee,	ገደል ሥር ነው ያዳፈንኩት፣
Hindhiisuu jaalala kee,	በጭራሽ አልተውም ፍቅርሽን፣
Nama jaalatee argee natti himee.	አፍቅሮ ያየ ነው የነገረኝ።
6. Yaa galabaa sinaamuu,	አላጭድህም አንተ ገለባ ፣
Akkan sinaamnee taatee,	እንዳላጭድህ ሆነሃልና፣
Yaa damma too sindhiisuu,	አልተውሽም የኔ ማር፣
Akkan sindhiifne taatee.	እንዳልተውሽ ሆነሻልና።

እነዚህ ዘፈኖች በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ አውዶች የሚዘፈኑ ናቸው። ከላይ በሰፊው እንደተብራራው የሰዎችን ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ለልቅ ለግብረሥ-ስጋ ግንኙነት የሚጋፉፉ እና ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ከመሆናቸው አኳያ ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም ተመሳሳዮቹ በጋራ የተገለጹ ሲሆን የተለየ መልዕክት ያላቸው በተናጠል ተብራርተዋል። ከዚሁ አኳያ ይዘታዊ ትንታኔያቸው እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር 1 ላይ የሚገኘው ዘፈን ቆንጆ ከወዳዱ ስለ በሽታ ማውራት አያስፈልግም የሚል ነው። ይህ የሚያሳየን ቁንጅና ለወሲብ መቀስቀሻ ምክንያት መሆኑ ነው። ይህ ዘፈን ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ጥንቃቄን አስመልክተው በተራ ቁጥር 13 ላይ

ከተጠቀሰው “ቆንጆ[118] የተመኘ ጉዳት አገኘ” ከሚል ምሳሌያዊ ንግግር ጋር ተመሳሳይነት አለው። በዚህ ዘፈን ውስጥ ምንም እንኳን የበሽታው ዓይነት ባይገለጽም ቆንጆ በመሆኗ ብቻ ስለ በሽታው መናገር እንደማያስፈልግ ይገልጻል። ምናልባት በሽታው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ቢሆን በምስጢር የመያዙ ሁኔታ ለቫይረሱ መስፋፋት በር መክፈት ይሆናል። ምክንያቱም ተናጋሪው በሽታውን ደብቆ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት በመፍጠር ሊያዛምት ይችላል።

በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የሚገኙ ዘፈኖች ከላይ ከተብራራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። ይኸውም ቆንጆን በመውደዱ እና የፈለገውን የወሲብ እርካታ በማግኘቱ ሞት እንኳን ቢሆን ለነፍሱ ምንም እንደማይጓጓ ይገልጻሉ። እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት ሰዎችን ለልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት የሚገፋፉ ናቸው። በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰውም ከእነዚሁ ዘፈኖች ጋር የሚገናኝ ሲሆን የፈለገ ነገር ቢፈጠር ከቆንጆ አንገት ሥር እንደማይወጣ በቁርጠኝነት ይገልጻል። እንዲህ ዓይነቱ ቁርጠኝነት ሰዎች ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን እንዳይፈሩት የሚያደርግ እና ለልቅ ወሲብ የሚገፋፉ ነው።

በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ ያሉት ዘፈኖችም የመጣው ቢመጣ አንቺን አልተውም የሚል መልዕክት አላቸው። ፍቅሯዋን ላለመተው ያስገደደውም አፍቅሯዋት ያየ የፍቅሯዋን ጣፋጭነት ነግሮኛል የሚል ምክንያት አለው። በመሆኑም በፍቅርሽ ስላበድኩ አልተውሽም የሚል መልእክት አለው። ከዚህ የምንረዳው የወደዳትን ልጅ ከመውደዱ በፊት ሌላም ሰው እንዲሁ ወደዷት እንደነበር ይጠቁማል። የእሷ ከሌሎችም ጋር ፍቅር መመስረት ምናልባትም ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የመጋለጥ አጋጣሚዋ ሰፊ ነው። ስለዚህ የዘፈኖቹ መልዕክት ከበሽታ መስፋፋት አንጻር ስናያቸው በአደጋ የታጠሩ ናቸው። በመሆኑም ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስን እንደ መሸሸ ቀጥ ብለው መጋፈጥና መድፈሩ ለጊዜያዊ የወሲብ እርካታ ብለው ምትክ የሌላትን ሕይወት ማጣትን ያስከትላል።

ከመተንተኛ ቲዮሪ አንጻር በሌሎቹ ትንተና ላይ እንደተገለጸው ከተገኙበት አውድ እና የሥነቃል ዓይነቶቹ ለማህበረሰቡ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የሚገለጹ ናቸው። ከደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪ አኳያ ደግሞ በወሲባዊ ቲዮሪ ይተነተናሉ። ይህም ወሲብን በመቀስቀስ

[118] ቆንጆን የተመኘ ወደ ወሲባዊ ግንኙነት ማምራቱ ስለማይቀር አንድ ቀን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ መጋለጡ ስለማይቀር ከእንዲህ ዓይነት ተግባር እንዲቆጠብ ለማስጠንቀቅ ነው። (ከገጽ 241 ማብራሪያ ላይ ለዚህ አባባል እንዲመች ተስተካክሎ የቀረበ)።

ሰዎችን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሚያደርጉ ከመሆናቸው አንጻር የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ከመጻረር እና ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መባባስ ምክንያት ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች ቀደም ሲል በ7.2. ርዕስ ሥር የተገለጹትን በምክር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጥቃት እንዲከላከሉ ከሚረዱ የሥነቃል ዓይነቶች ተቃራኒ መልዕክት ያላቸው ናቸው።

እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች የሰዎችን ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት እና በመቀስቀስ ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ይገፋፋሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ተግባራት ደግሞ በአብዛኛው ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ያፈነገጡ **ነውር** ድርጊቶችን ያካተቱ ናቸው። በመሆናቸውም ሰዎችን ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ያጋልጣሉ። ስለዚህ እነዚህ እና የመሳሰሉት የሥነቃል ዓይነቶች በመጥፎ ምሳሌነታቸው የሚጠቀሱ ናቸው። በመሆኑም ሰዎች ከልቅ ወሲባዊ ድርጊቶች እንዲርቁ አፍራሽ ሚናቸውን በማጋለጥ ማስተማሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግ ይችላሉ።

እስካሁን ድረስ የጥናቱን ርዕስ መሠረት በማድረግ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በየምዕራፎቹ ተመድበው ከእነዚህ ውስጥ የተመረጡት ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ተተንትነዋል። እንዚህን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ማጠቃለያ እና ይሁንታ ወደ ሚገለጽበት ምዕራፍ እንሸጋገራለን። ለዚህም በቅድሚያ የጥናቱን ማጠቃለያ ሞዴል እንመለከታለን።

ምዕራፍ ስምንት

8. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

8.1 ማጠቃለያ

ኤች አይ ቪ/ኤድስ በዓለም ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የሰውን ልጅ ሕይወት በመቅጠፍ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል። ይህንን አስከፊ በሽታ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በሕክምናው መስክ ያለሰለሰ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም እስካሁን ድረስ መድኃኒት ባለመገኘቱ በሰዎች አእምሮ ላይ ጭንቀት እየፈጠረ ነው። በሽታው ዓለም አቀፋዊ ችግር እንደመሆኑ መጠን መፍትሔውም በሁሉም መስክ ያልተቋረጠ ጥናትና ምርምር ማድረግን የሚፈልግ ነው። ይሄም በሁሉም የትምህርት ዘርፍ የሁሉም ሰው ርብርብ ያስፈልገዋል። በተለይም በፎክሎር የትምህርት ዘርፍ ማህበረሰቡ ከባህል ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለ ወሲባዊ ጉዳዮች በሥነቃል የሚናገራቸው ጉዳዮች በደንብ መመርመር አለባቸው። ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ እና ዋንኛው ልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ነው። እነዚህ ግንኙነቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚፈጸሙት በድብቅ መሆናቸውን የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። የሥነቃል ፋይዳውም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ድብቅ የሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነልቦናዊ ጉዳዮችን ግልፅ የማድረግ አቅም ያለው መሆኑ ነው። ሥነቃል ከወሲብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ምስጢራዊ ጉዳዮችን ይፋ የማድረግ አቅም አለው።

በድብቅ የሚከናወኑ ወሲባዊ የፍቅር ግንኙነት ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ከሚያጋልጡ ድርጊቶች አንዱና ዋንኛዉ ነው። እነዚህ ምሥጢራዊና ውስብስብ የፍቅር ግንኙነቶች በተለይም በወጣትነት ዘመን በአብዛኛዉ ጥንቃቄ በጎደለዉ ሁኔታ ስለሚከናወኑ፣ ለአባለዘር በሽታ መስፋፋት፣ ባልተፈለገ እርግዝና ለሚፈጠረው ውርጃና ለቀሳፊው የኤች አይ ቪ\ ኤድስ በሽታ የሚዳርጉ ስለሆኑ ችግሮቹን እጥፍ ድርብ ያደርጋል።

በዚህ ጥናት ውስጥ በልዩ ልዩ የመረጃ ማሰበሰቢያ ዘዴዎች ከተለያዩ መቼቶች ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በቂ የሥነቃል ዓይነቶች ተሰብስበዋል። በዚህ የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ውስጥ ከመረጃ አቀባዮች እና በጥናቱ ቦታና አከባቢ በማህበረሰቡ ከሚከበሩ ሃይማኖታና ባህላዊ ክብረ-በዓላት ላይ የተሰበሰቡት ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ዘፈኖች ናቸው። በእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች አማካይነት ማህበረሰቡ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በአውንታዊ እና በአሉታዊ መልኩ እየተነጋገረበት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

በመሆኑም የሥነቃል ዓይነቶች ከይዘታቸው አኳያ የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በሚሉ ሁለት ምዕራፎች ሥር ተመድበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው መረጃዎች ከተብራሩ በኋላ ከልዩ ልዩ ቲዮሪዎች አንጻር ተተንትነዋል። በትንታኔ ውስጥ ከጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው በተደጋጋሚ የተነሳው **ነውር** የሚል ቃል ነው። የቃሉን ምንነት ግልጽ ለማድረግ ማብራራት ያስፈልጋል። ስለሆነም የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ሥር የሚካተቱትን ጉዳዮች በመዘርዘር የእነዚህ አፈጻጸም እንዴት **ከነውር** ጋር እንደሚገናኝ እንደሚከተለው እናያለን።

ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ሥር የተዘረዘሩት ጋብቻ፣ ከንፈር ወዳጅ፣ ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ መገለጫዎች መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ጋብቻ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ በተለየ መልኩ የሚታይ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል። ይሄም ጋብቻ በውል የሚመሠረት የፍቅር ግንኙነት ከመሆኑም በላይ በሁለቱ ተጋቢ ወገኖችም መካካል ዘላቂ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነቶችን የሚፈጥር ማህበራዊ ተቋም ነው። በመሆኑም ጋብቻ ለቤተሰብ እና ማህበረሰብ መፈጠር ዋና መሠረት ነው። የከንፈር ወዳጅ ባህላዊ ወጉን ጠብቆ ከተከናወነ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸመውን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ይከላከላል። በመሆኑም ክብረ-ንጽሕናን ጠብቆ ጋብቻ ለመመሥረት የሚጠቅም ነው። በሌላ መልኩ ጋብቻን ለመመሥረት እንደ ድልድይ ከማገልገሉ አኳያ በአዎንታዊ ጎኑ የሚታይ ነው። ሌሎቹ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች (ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ) ግን በሁለቱ የፍቅር ተጓዳኞች መካካል ብቻ የሚመሠረቱ እና ዘላቂነትም የሌላቸው ናቸው። እነዚህ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ከጋብቻ ጋር በሚፈጥሩት ድብቅ የፍቅር ግንኙነቶች በጋብቻ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅእኖዎች ለጋብቻ መነጋት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው። እንደዚህ አይነቶቹ ግንኙነቶች በባህሉ የሚወገዙ **ነውር** ተግባራት ናቸው። በመሆኑም ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ያፈነገጡ ድብቅ ወሲባዊ ግንኙቶች **ነውር** በመሆናቸው ውጤታቸውም **ለነውር** የሚያጋልጡ ናቸው። እነዚህ **ነውር** ውጤቶች ልዩ ልዩ የአባለዘር በሽታዎች በተለይም ቀሳፊው ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። በሌላ መልኩ ጋብቻ ከእነዚህ **አስነዋሪ** ተግባራት ነጻ ከሆነ ለቤተሰብ እና ማህበረሰብ ብሎም አገር ግንባታ አዎንታዊ ሚናው የጎላ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል።

በመሆኑም ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው የሚነገሩ የሥነቃል ዓይነቶች በጋብቻ ላይ የሚያሳድሩት አዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታዎችን የሚያሳዩ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዘው አንዳንዶቹ ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መስፋፋት ሌሎቹ ደግሞ ለበሽታው መገታት የበኩላቸውን ሚና የሚጨወቱ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በእነዚሁ መነሻነት በቀጥታ ኤች ኣይ ቪ.ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች ለቫይረሱ ጥቃት ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚገልጹ ናቸው። ከዚሁ አንጻር ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ጥቃት እንዲከላከሉ የሚያግዙ የሥነቃል ዓይነቶች የመኖራቸውን ያህል ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ሰዎችን ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚገፋፉ እና ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲጋለጡ የሚያደርጉ የሥነቃል ዓይነቶች መኖራቸው በጥናቱ ተረጋግጠዋል።

ሥነቃል የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን በተለይ ባህላዊ ጉዳዮችን በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው እና ባህላዊ ለውጦች በተደረጉም ቁጥር ሥነቃሉም አብሮ በመለወጥ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎችን እንደሚያንጸበርቁ በዚህ ጥናት ተረጋግጠዋል። ከዚሁ አኳያ በዚህ ዘርፍ በጥናትና ምርምር ላይ የተሠማሩ ምሁራን[119] ሲገልጹ ሥነቃል ወቅታዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉድለቶች ግልጽ በማድረግ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የማስተማር ሚና አለው። በመሆኑም ሥነቃል በዚህ ተግባሩ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ የሚሸጋገር ስለሆነ ለአንድ ማህበረሰብ ሕልውና ቀጣይነትም አስተዋጽኦው የጎላ ነው።

ክልላዊ (ሂሚስፈርክ) ቲዮሪ እንደሚያመለክተው አንድ ማህበረሰብ ከቦታው ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት በሚከሰቱ መስተጋብሮች የተነሳ ቀድሞ የነበረው የማህበረሰቡ ቋንቋ እና ባህል በሌላው የመዋጥ፣ ከሌላው የመዋስ፣ ከሌላው ጋር የመዋሃድ፣ ወይም ቀድሞውኑ የነበረውን የማጠናከር ወይም ድሮ የነበረውን የመዘንጋት ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ(Dorson 1972: 44)። ከዚሁ አኳያ በፖለቲካ እና የከተሞች መስፋፋት ምክንያት ወደ ቱለማ ኦሮሞ በቋንቋው እና ባህሉ የተለየ ሌላ ማህብረሰብ በመምጣቱ በቱላማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ ለውጦች ተስተናግደዋል። እያስተናገደም ይገኛል። ከዚሁ አንጻር በጥናቱ እንደተረጋገጠው በቱለማ አሮሞ ድሮ የነበሩ አንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች በአሁኑ ዘመን አለመኖራቸው ወይም መልካቸውን ቀይሮ መነገር ወይም መከወን

[119] (Finnegan, 1970; Mieder, 1993; Egbe, 2000; Okpewho, 2004)።

ጀምረዋል። ለምሳሌ የከንፈር ወዳጅ አፈጻጸም ባህላዊ ወጉን እየለቀቀ መምጣቱን መረጃ አቀበዮች ገልጸዋል። በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ድሮ የነበሩ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች መልካቸውን እየቀየሩ መምጣታቸውንና የሥነቃል ዓይነቶችም ይህንኑ ለውጥ መከተላቸውን ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ለምሳሌ ያህል በባህላዊ ዲርጊት አፈጻጸም የከንፈር ወዳጅ ግንኙነት[120] ከላይም ከታችም መሆን በቱለማ ኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ድሮ ያልነበሩ ናቸው። እነዚህ ተግባራት ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዳጋለጣቸው በሥነቃል ዓይነቶቹ በተለይም በዘፈኖች ውስጥ ተንጸባርቋል። ስለዚህ ባህሉ ሳይሆን በልዩ ልዩ ምክንያቶች የባህሉ መቀየር ወይም መለወጥ ለችግሩ መንስኤ መሆኑን ይህ ጥናት ያሳያል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የከተሞች መመስረት፣ ወሲብ ቀስቃሽ ፍልሞች[121] እና የአልቤርጎዎች መኖር ለድብቅ ወሲባዊ ግንኙነቶች መስፋፋት ምክንያት ናቸው። በተያያዘ ሁኔታ በድብቅ ወሲብን በመፈጸም ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ወጣቶች በመሆናቸው ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ይበልጥ የተጋለጡትም እነዚሁ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸውን መረጃ አቀባዮች ገልፀዋል። ይህንን አስመልክተው ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በግንባር ቀደምትነት ተጋላጭ የሆኑና ለከፋ ችግር የተዳረጉት ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ከጽሑፍ የተገኘ ጥናታዊ[122] መረጃ ይገልጻል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በሌሎችም ባህላዊ የፍቅር ግንኙነት ዓይነቶች (ውሽማ፣ ሲገባ እና እሬ) ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከባህላዊ ለውጥ አንጻር ለቫይረሱ ሥርጭት አመቺ መንገድ የሚፈጥሩ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው። በአጠቃላይ ከመስክ የተገኙ የሥነቃል መረጃዎች የይዘት ትንተና ውስጥ እንደተገለጸው ቀድሞ የነበሩ ባህላዊ የፍቅር

[120] ለምሳሌ የከንፈር ወዳጅ ባህል አፈጻጸም በአሁኑ ዘመን እየተለወጠ መምጣቱን መረጃ አቀበዮች ሲገልጹ፡- “በድሮ ዘመን የግብረሥጋ ግንኙነት ወደ መፈጸም አይሸጋገሩም ምክንያቱም በባህሉ መሠረት የከንፈር ወደጆች ወሲብ ከፈጸሙ በባህሉ **ነውር** በመሆኑ ውግዘት ይድርስባቸዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ዘመን ይህ ነውር ቀርቶ የከንፈር ወዳጅነቱ ከላይም ከታችም እየሆነ መጥቷል።” (መረጃ አቀባዮች አቶ ሰይፉ መልካ እና አቶ ጉዲሣ አቤቤ፣ ህዳር 27 ቀን 2007ዓ.ም.)።

[121] በከተማ አከባቢ የሚገኙ ወጣቶች የወሲብ ፊልሞችን በማየት በከፍተኛ ደረጃ ለኤድስ የተጋለጡ ናቸው (Amanuel 2007፡ 67)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በኤትዮጵያ ቴሌቪዥን አዲስ ሙግት ፕሮግራም ላይ የተሰጠው አስተያየት ወጣቶች ወሲብ ቀስቃሽ የሆኑ ፊልሞችን በማየትና በዚህም የተነሳ ልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነቶችን በመፈጸም ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የተጋለጡ መሆናቸውን ይጠቁማል።

[122] (Lisa et al, 2006 እና Susser Ida, 2009)።

ግንኙነቶች እየተቀየሩ መምጣታቸው ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት መባባስ ምክንያት የሆኑ ናቸው።

ጥናቱም እንደሚያመለክተው በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቂ መሆናቸውን የሚያሳዩ ቢሆኑም ለችግሩ ይበልጥ የተጋለጡት ወጣቶች መሆናቸውን እና የቫይረሱም ሥርጭት በከተማ እንደሚበዛ የሚያረጋግጡ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከከተማ ሴትኛ አዳሪዎች ጋር የሚፈጸመው የግብረ-ስጋ ግንኙነት ለቫይረሱ የሚያጋልጡ መሆናቸውን የሚገልጹ አመለካከቶችም በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። ከዚሁ አኳያ ሥነቃል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉድለቶች በማሳየት እና በማስተማር ረገድ ጉልህ ድርሻ እንዳለው በትንታኔው ውስጥ በሰፊው ተገልጿል።

የሥነቃልን የማስተማር ሚና አስመልክቶ የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች እምቅ በሆነ ትርጉማቸው መልዕክት የማስተላለፍ ሚናቸው የጎላ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ። ስለሆነም በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት እነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች የቱለማን ኦሮሞ በትኩረት እና ሌሎች ማህበረሰቦችን በአጠቃላይ የማስተማር፣ የመለወጥና የተበላሸ ባህሪይን የማስተካከል ፋይዳ አላቸው። በሌላ መልኩ ወሲባዊ ፍላጎትን በማነሳሳት ለልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚዳርጉ እና ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የማጋለጥ ሚና የሚጨወቱም አሉ። እነዚህንም ቢሆን የሚያስከትሉትን ጉዳት በማሳየት ለማስተመሪያነት መጠቀም ይቻላል። የሥነቃል ፋይዳን አስመልክተው የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባር እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ውጤታማ መሆናቸውን Bascom, (1954)ያብራራል።

ከዚሁ አንጻር ከመስክ የተገኙት የሥነቃል ዓይነቶች ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በተለይም ወጣቶች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የሚያስተምሩ እንዳሉ በጥናቱ ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶች በተፈጥሮአቸው ለኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጡ አይደሉም። ይሁን እንጂ በአንድ በኩል የቀድሞ ባህላዊ ትርጉማቸውን በመሳታቸው ለበሽታው የሚያጋልጡ ወይም የቫይረሱን ሥርጭት የሚያባብሱ ሆነዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ የቱለማ ኦሮሞ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በልዩ ልዩ መልኩ በፈጠራቸው ግንኙነቶች ቀድሞ የነበሩት ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች በመለወጣቸው የሥነቃል

ዓይነቶችም ይህንኑ ለውጥ ተከትለው ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭት መባባስ ምክንያት ሆነዋል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን በሚመለከት ባህልን በደፈናው ማውገዝ ሳይሆን ባህልን የሚጻረሩ **ነውር** ተግባራት የፈጠሩትን ችግሮች መለየት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የቱለማ ኦሮሞ ለውጡን ተከትለው የተከሰቱትን ችግሮች በሥነቃል የመግለጽ የደባረ ባህል ያለው በመሆኑ መፍትሔዎቻቸውም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ የሥነቃል ዓይነቶችም እንዲሁ በራሳቸው ቫይረሱን የሚያስፋፉ ሳይሆኑ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን ተንተርሰው ወሲባዊ ፍላጎቶችን በማነሳሳት በተዘዋዋሪ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚያጋልጡ ናቸው። በሌላ መልኩ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን ኢላማ በማድረግ የቫይረሱን ሥርጭት በምክር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የሚከላከሉ የሥነቃል ዓይነቶች ሚናቸው የጎላ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። በመሆኑም ማህበረሰቡ የኤች አይ ቪ/ ኤድስን አደገኛነት አውቀው እና ተረድተው በሥነቃል አማካይነት የመነጋገሪያ አጀንዳ አድርገዋል። ከዚሁ አንጻር የሥነቃል ዓይነቶቹ በማህበራዊ፣ ሐይማኖታዊ እና ባህላዊ ሥነ-ሥርዓቶች (ከበራዎች) ላይ መነገራቸውና መከወናቸው እንደ በጎ ተግባር የሚታዩ ናቸው።

በመሆኑም የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በጤና እና በማህበራዊ ጉዳዮች መካከል ያለውን ቁርኝት አስተሳስረው ለማስተማር እነዚህ በጎ ሁኔታዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ሰፊ ውይይት ለማድረግ እንደ መግቢያ በር የሚያገለግሉ ናቸው። ይህም አዲስ ለመፍጠር ሳይሆን ቀድሞውኑ ማህበረሰቡ ውስጥ የነበረውን በሥነቃል የመነጋገር ጉዳይን የበለጠ ለማጠናከር የሚያመች ነው።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ለቀረቡት የምርምር ጥያቄዎች የጥናቱ ውጤት ምላሽ ሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የጥናቱን ዓላማ በተመለከተ ጥናቱ ባተኮረበት አካባቢ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው ኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዳይስፋፋ የሚከላከሉ ወይም እንዲስፋፋ የሚያደርጉ የሥነቃል ዓይነቶችን በመተንተን ለችግሮቹ መፍትሔ ከመፈለጉ አኳያ ጥናቱ ተሳክቷል የሚል እምነት አለኝ። ይህንኑ መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የጥናቱን ይሁንታ እንደሚከተለው እንመለከታለን።


ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ
ሥነቃል
ባህላዊ የፍቅር
ግንኙነቶች
ከንፈር ወዳጅ
ውሽማ
ሲገባ
እሬ
ጋብቻ

ሞዴል 1፡- የጥናቱ ማጠቃለያ ሞዴል[123]

የሞዳሌ 1 ማብራሪያ



ሦስቱ የእንቁላል ቅርጽ ያላቸው ምስልች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን፣ ጋብቻ እና ኤች አይ/ቪ/ ኤዴስን የሚመለከቱ ናቸው። በእንቁላል የተመሰለበት ምክንያት ልክ እንቁላል አስኳል እንዳለው ሁሉ በእያንዳንዳቸውም ውስጥ የየራሳቸው ጉዳ

አላቸው። ይኸውም፡- በኤች ኣይ ቪ/ ኤዴስ ውስጥ **መድኃኒት የሌለው በሽታ** መኖሩን፣

በጋብቻና ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ **ወሲባዊ ጉዳይ** መኖሩን ያሳያል።



በሦስቱ የእንቁላል ቅርጽ መሀከል የሚገኘው ሦስት ጎን ቅርጽ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙ ቶች፣

ስለ ጋብቻ እና ኤች ስለ አይ ቪ/ኤዴስ የሚነገሩ **የሥነቃል ዓይነቶች** መኖራቸውን ያሳ

ይህም ሥነቃል በማ/ሰቡ ውስጥ ድብቅ የሆኑ ወሲባዊ ጉዳዮችን ይፋ የሚያደርግና **የጥናቱም መሪ ቃል** መሆኑን ያመለክታል።



ከኤች ኣይ ቪ ወደ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ጋብቻ የሚያመለክቱ ሁለቱ ወፍ ም

ቀስቶች ቫይረሱ ወደ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ጋብቻ መሠራጨቱን የሚ ልጹ

ሥነቃልችን ያመለክታሉ።



ይህ ቀስት **ኤች አይ ቪ** ከባህላዊ የፍቅር ግንኙቶች ወደ ጋብቻ እንዲሁም ከ

ባህላዊ የፍቅርግንኙቶች መሠራጨቱን የሚገልጹ **የሥነቃል ዓይነቶችን** ያመለ ታል።



---

[123] የእ ርጾቹ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ፣ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ጋብቻ ይወክላሉ። ቀስቶቹ የኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭትን የሚያመለክቱ ሲሆን ላይ የሚገኘው ባለ ሦስት ጎን ቅርጽ በአዎንታዊ እና አሉታዊ መልኩ የሚነገሩ እና የሚከወኑ የሥነቃል ዓይነቶች መኖራቸውን የሚያ ። ከዚሁ አኳያ ሥነቃል የዚህ ጥናት መሪ ቃል ነው። የእያንዳንዱ ዝርዝር ማብራሪያ በሚቀጥለው ገፅ ላይ ቀርበዋል

ከሥነቃል ወደ ኤች ኣይ ቪ/ ኤዴስ የሚያመለክተው ወፍራም ቀስት **ሰዎች** **ራሳቸውን**

ከቫይረሱ እንዲከላከሉ የሚረዱ የሥነቃሌል ዓይነቶች መኖራቸውን ያሳያል።

በወፍራሙ ቀስት ላይ የታጋደመው ቀጭኑ ቀስት ደግሞ **ወሲባዊ ፍላጎትን** **በማነሳሳት**

ሰዎችን ለኤች ኣይ ቪ/ ኤዴስ የሚያጋልጡ ሥነቃልች መኖራቸውን ያመለክታል



ከሥነቃል ወደ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች የሚያመለክት ወፍራም ቀስት ባ

የፍቅር ግንኙነቶችን **የሚያሞግሱ** ሲሆኑ፣ በላዩ የተጋደመው ቀጭን ቀስት ደግ

ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶችን **የሚያወግዙ የሥነቃል ዓይነቶችን** ያመለክታል።

ከሥነቃል ወዳ ጋብቻ የሚያመለክተው ወፍራም ቀስት ከጋብቻ ውጭ ሚፈጸሙትን

የግብረ-ስጋ ግንኙነት **የሚያወግዝ** ሲሆን በላዩ ላይ የሚገኘው ቀጭን ቀስት ደግም

ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸሙ የግብረ-ስጋ ግንኙነትን **የሚያበረታቱ የሥነቃል ዓይነቶችን** ያመለክታል።

8.2 ይሁንታ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ከመረጃዎች ትንተና ውጤት በመነሳት የጥናቱን ማጠቃለያ መሠረት ያደረጉ የይሁንታ ሀሳቦችን ዝርዝር ያካተተ ነው። ከዚሁ አኳያ በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች የቫይረሱን ሥርጭት ከመከላከሉ እና ከመቆጣጠሩ አንጻር ለወደፊቱ መከናወን በሚገቧቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል። ከዚሁ አንጻር በጥናቱ ውስጥ በትንተና ሒደት ጎልተው የወጡ ሀሳቦች ለወደፊት ተግባራዊ ቢሆኑ ኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ በሰው ልጅ ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት ለመከላካል ብሎም ለመቆጣጠር ይቻላል። በመሆኑም ቀጥለው በተዘረዘሩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ቢደረግባቸው መልካም ነው።

1. የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚገልጹ የሥነቃል እውቀት መሰብሰብና ማጥናት፣ የጥናቱ ውጤቶችን መልሶ ለማህበረሰቡ ማስተማሪያነት እንዲውሉ

በማድረጉ ረገድ የሚደረገው እንቅስቃሴ መበረታታት አለበት። ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጥናቱ የዳሰሳቸው የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ እሴቶች ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ አኳያ ይፋ ወጥተዋል። በዚህ ጥናት ውስጥ ይዘታዊ ትንተኔ የተደረገባቸው ባህላዊ የፍቅር ግንኙቶችን የሚገልጹ የሥነቃል ዓይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በልዩ ልዩ መልኩ የሚታዩ ጉድለቶችን በማረም የማስተማር አገልግሎት እንዲሰጡ በባህልና ቱሪዝም፣ በጤና እና ትምህርት ዘርፍ ተግባራዊ ቢደረጉ ጥሩ ውጤት ያስገኛሉ።

2. የብልግናን አስከፊነት በግልጽ ማውራቱ **ነውር** አይደለም። **ነውሩ** ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ባፈነገጡ **ነውር** ድርጊቶች ውስጥ መሳተፉ ነው። በጥናቱም ውስጥ ጎልቶ የወጣው የማህበረሰቡ ባህል የማይቀበለው **ነውር** የሆኑ ወሲባዊ ተግባራት ናቸው። በሥነቃል ዓይነቶችም በብዛት የተነገረውና በክዋኔዎቹም የተገለጹት በእነዚህ ተግባራት ዙሪያ ነው። ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚፈጸመው ወሲባዊ ድርጊቶች ዙሪያ ያለውን ችግር ለመፍታት የሚቻለው በችግሮቹ ላይ ግልጽ ውይይት ማድረግ ሲቻል ነው። እንደዚህ ዓይነት ድርጊቶችን ይፋ የማውጣት አቅም ያለው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ሥነቃል መሆኑ ጥናቱ አሳይቷል። ስለዚህ እነዚህን የሥነቃል ዓይነቶች መሠረት በማድረግ ወጣቱ ትውልድ በወሲባዊ ድርጊቶች ላይ በግልጽ መወያየት ይኖርበታል። በመሆኑም የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣቶች እና ሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሠሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የሥነቃል ዓይነቶች በመጠቀም በማስተማር ወገኖቻቸውን የማዳን ተግባር ቢያከናውኑ መልካም ነው።

3. በዚህ ጥናት ውስጥ እንደተገለጸው ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሰዎች ላይ ያደረሰው ጉዳት እና እያደረሰ ያለው ችግር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። የቫይረሱ ሥርጭት ወሬም አንዳንዴ እየሞቀ አንዳንዴ እየቀዘቀዘ መሠረታዊ መፍትሔ ግን ባለመገኘቱ በማህበረሰቡ ላይ እያሰደረ ያለው የመንፈስ ጭንቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ጥናቱ ያመለክታል። ከዚሁ አኳያ ጥናቱ የተከናወነበት ማህበረሰብ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጎኑ በጉዳዩ ላይ እየተነጋገሩበት ይገኛል። ይህንንም በሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ-በዓላት እንዲሁም በሌሎቹም ልዩ ልዩ መቼቶች የውስጥ ስሜቱን

በሥነቃሉ እየገለጸ ይገኛል። በመሆኑም የእነዚህ የሥነቃል ዓይነቶች ሥነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ መፍትሔያቸው እና ትዕምርታዊ ጠቀሜታቸው ታይተው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ወጣቶች እና ሴቶች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ ኤድስ እንዲከላከሉ በጤና ዘርፍ ትምህርት ሊሰጥበት ይገባል። በመሆኑም ሰዎች ራሳቸውን ከኤች ኣይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት ትምህርት የሚሰጡ የሥቃል ዓይነቶች ተመርጠው በትምህርቱ ዘርፍ በቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ውስጥ ቢካተቱ እና በኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የወጣቱን ትውልድ ግንዛቤ ማደበሪያነት እንዲውል ቢደረግ የተሻለ ነው።

4. በፌዴራልም ይሁን በክልል መስተዳድር የባህል፣ የጤና እና የትምህርት ፖሊሲዎችን ሲዘጋጅ ከባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች ጋር ተያይዘው ስለ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩ እና በሚከወኑ ባህላዊ እውቀት ላይ ጥናት ቢደረግ መልካም ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት፣ በሥነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርት ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የቤተሰብ መምሪያ የመሳሰሉት ለሚያከናውኑ ተግባራት እነኚህን ባህላዊ ዘዴዎች ቢጠቀሙ መልካም ነው።

5. የቱለማ ኦሮሞ ባህል በውስጡ ታምቆ የሚገኙትን ኢኮኖሞያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮቹን በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ገጽታቸው በዘፈኖች የሚገልጻባቸው ቦታዎች በአብዛኛው በየዓመቱ በሚያከብራቸው ባህላዊ እና ሓይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ላይ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል። ለዚህም እንቁጣጣሽ፣ እሬቻ እና ጥምቀት ጉልህ ሥፍራ ይይዛሉ። በእነዚህ ክብረ-በዓላት ላይ በአብዛኛው የሚዘፈኑት ዘፈኖች ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶቹን የሚመለከቱ ሲሆኑ ከእነዚሁ ጋር ተያይዘው ኤች ኣይ ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ በርካታ ዘፈኖች ስለመዘፈናቸው በጥናቱ የተገኙት መረጃዎች ይገልጻሉ። በመሆኑም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በተለይም በባህልና ቱሪዝም ቢሮ እነዚህ ተግባራት እንዲጠናከሩ ቢደረግና ለዚህም በሕዝብ ግንኙነት በኩል ከአሁን ቀደሙ በበለጠ ሰፊ ሽፋን ቢኖረው መልካም ነው።

6. በኦሮሞ ባህል አረጋውያን ሰፊ ተሰሚነት አላቸው። በተለይም አገርን የሚጎዳ ሁኔታዎች በአጋጠሙ ጊዜ መፍትሔዎቻቸውን ከባህል አኳያ በመፈለጉ ረገድ ጉልህ ሚና የሚጨወቱ ናቸው። በመሆኑም ለልዩ ልዩ ጉዳዮች በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ ዕድል ቢሰጣቸውና ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በመከላከሉና በመቆጣጠሩ ረገድ ኅብረተሰቡን ቢመክሩ ጥሩ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ።

ዋቢዎች

መኮንን ብሩ፤ (1981)፤ "በመናገሻ አውራጃ በአደኣ በርጋ ወረዳ በገዳ ሥርዓት የሚዘፈኑ

የኦሮሞ ዘፈኖች ይዘታዊ ጥናት" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የቀረበ፤ አአዩ: የመጀመሪያ ድግሪ ማሚያ፤ ያልታተመ።

ሙሉቀን ኡመር፤ (1997)፤ "በጊዲኦ አከባቢ ከኤች አይ ቪ ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ሥነቃሎች

ይዘት ትንተና፤" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ:

የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ።

ሙሉጌታ ነጋሣ፤ (1997)፤ "በአደአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር፤"

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ:

የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ።

ሱሉልታ ከተማ አስተዳደር፤ (2006)፤ "የሱሉልታ ከተማ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ

ፕሮፋይል"፤ ሱሉልታ፤ ሰሉልታ ከተማ አስተዳደር።

ስንቅነሽ አጣለ፤ (1997)፤ ሙስና፣ ስደትና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ከ1990 እስከ 1996 ዓ.ም.

በታተሙ ልቦለዶች፤ "ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የቀረበ፤ አአዩ:የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ።

ባቃሮ ቢያንሣ (ተርጓሚ)፤ (1985)፤ *[የገዳ ሚልባ - ኦሮሚያ]* አዲስ አበባ።

ብርሃኑ ገበየሁ (1995)፤ *የአማርኛ ሥነግጥም፤* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ መስፍን (ተርጓሚ)፤ (2000)፤ *ኤድስ እና እኛ፤* አዲስ አበባ: ጸጋ ክርስቲያን

መጻሕፍት ማዕከል።

ታቦር ዋሚ፤ (2006)፤ *የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች፤* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ

ማተሚያ ድርጅት።

ታደሰ ዓለሙ፤ (1974)፤ "የሰላሌ ኦሮሞ የፍቅርና የጋብቻ ዘፈኖች፤" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና

ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ያልታተመ።

ኃይለማርያም አብዲሣ፤ (2006)፤ *ቀልድ እና ቁም ነገር፤ የመጀመሪያ እትም፤* አዲስ አበባ።

ነብዩ ተድላ፤ (1993)፤ "ሬድዮ ፋና ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ የሰጠው ሽፋን፤" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: የሁለተኛ ድግሪ ማሚያያልታተመ።

አበባየሁ ደምሴ፤ (1974)፣ "የኦሮሞ ገዳና ዲቺሣ ዘፈን ግጥሞች በየረርና ገረዩ አውራጃ፤" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: የመጀመሪያ ድግሪ ማሚያ፤ ያልታተመ።

አብዮት ኩምሳ፤ (1992)፤ "ሲ.ቪ.ኤም. ከኢትዮጵያ ሬድዮ ጋር በመተባበር ከ1987 - 1990 ዓ.ም. በዝሙት አዳሪዎች እና ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ያቀረባቸው ጭውውቶች፤"

ለትያትርና ሥነ-ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: የሁለተኛ ድግሪ ማሚያ፤

ያልታተመ።

ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል፤ (1993)፤ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አዲስ አበባ: አርቲስትክ ማተሚያ ቤት።

ኤርሚያስ ሥዩም ፤ (2006)፤ *ሰዓት እላፊ 2 ከጨለማ ወደ ብርሃን፤ አራተኛ ዕትም፤* ዮርዳኖስ ሥዩም ሚዲያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር።

________፤ (2006)፣ *ሰዓት እላፊ 3 የመጀመሪያ ዕትም፤* ዮርዳኖስ ሥዩም ሚዲያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርር።

ኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፤ *የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤* ፊንፊኔ፤ ኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፤ 1998 ።

ዘሪሁን አስፋው፤ (1992)፤ *የስነጽሁፍ መሰረታዊያን፤* ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ያዴሣ ቶሎሣ ወዬሣ፤ (2007)፣ *መሠረታዊ የጥናትና ምርምር ዘዴዎች፤* (በተግባራዊ

ምሳሌዎችና አስረጅዎች የተደገፈ)።

ይርጋ ደበበ፤ (ተርጓሚ)፤ (2002)፤ *የፍቅርና ወሲብ ቀልዶች፤* ቁጥር 1።

ደረጀ ተሰማ፤ (1998)፤ "በቢሾፍቱ ከተማ የእሬቻ በዓል አከባበር ሥነቃላዊ ይዘት ትንተና።"

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: የመጀመሪያ ድግሪ

ማሟያ፤ ያልታተመ።

ዳንኤል ክብረት፤ (2006)፤ *የሁለት ሐውልቶች ወግ እና ሌሎች፤* (7ኛ ዕትም)፤ አግዮስ

አዲስ አበባ: ኅትመት እና ጠቅላላ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር።

ድሪቢ ደምሴ ቦኩ፤ (2007)፤ *የኦሮሞ ማንነት ታሪክ፤* ፍንፍኔ።

ጀቤሳ ዲልቦ፤ (1995)፤ "ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ አስመልክተው በሬድዮ ፋና የኦሮምኛ አዝናኝና

አስተማሪ ተከታታይ ዲራማዎች፤" ለትያትርና ሥነ-ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበ፤

አአዩ: የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ።

ጌታቸው ኃይሌ፤ (1997)፤ *የአባ በሕርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች*

ጋራ፤ አዲስ አበባ።

ጥላሁን ተሊላ፤ (2007)፣ "የቱለማ ኦሮሞ "መርሣ" ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት፤"

ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: ለዶክትርና

ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ።

ፈቃደ አዘዘ፤ (1991)፤ *የሥነቃል መመሪያ፤* አዲስ አበባ፤ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ

የኅልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም።

________፤ (1996)፤ *ሰሚ ያጡ ድምፆች*፣ አዲስ አበባ።

ፍትህ ቶላ፤ (2007)፤ *ዎናው ነገር ጤና*፤ አዲስ አበባ።

Ababa Margaa. (2007). “Qaacccessa Qabiyyee Sirba Gadaa Oromoo Tuulamaa.” Yunvarsiitii Addis Ababa, Kolleejjii Barnootaa. Mana Baruumsa Eebba Boodaa Finfinnee. Digrii 2ffaa. Kan Hin maxxafamni.

Alksander, F. (1988). *Myths and Traditions Concerning the Origin of Oromo People.* In Africa Bulletin. No. 35. Page 59-65. Poland: Warszawa University.

Almaayyoo Hayilee. (1999). *Sirna Gadaa: Siyaasa Oromoo Tulamaa.* Finfinnee: Biiroo Aadaa fi Tuurizimii Oromiyaa.

Amanuel Taferi. (2007). “The Influence of Exposure to Pornography among The Youth in Addis Ababa.” Under Graduate Studies. AAu: Unpublished BA Thesis.

Asefa Tefera Dibaba. (2004). *Theorizing the Present: Towards a Sociology Of Literature, Jarso Waqo’s Poetry*. Addis Ababa: Beranna Publishing.

Austin, B. (1994). *Understanding Oral Literature*. Nairobi University Press.

Banks, J.A. Banks,C.A. McGee.(eds).(2001). *Multicultural Education: Issues And Prespectives (4th ed).* New York: John Wiley and Sons.

Bascom, W. (1954).*Four Functions of Folklore*. Journal of American Folklore. Vol. 67. No. 266.

Bauman, R. (1977). *Verbal Art as Performance*. Newbury House: Rowley.

______ (1983). "The Field Study of Folklore in Context," in Hand Book of American Folklore. Bloomington.

______ (ed.)(1992). *Folklore, Cultural Performances and Popular* Entertainment. Oxford: Oxford University Press.

Bayleyegn Tasew. (2009). *Metaphors of Peace and Violence in the Folklore Discourse of South Western Ethiopia:A Comparative Study*. Amsterdam: VU University Press.

Bajigaa Takkaa Bunee. (2008). ''Aadaa Saala Oromoo Godina Shawaa Kaabaa (Salaalee), Aanaa Barrakk.'' Mana Barumsa Yunivarsiitii Ebba Boodaa Addis Ababaa: Qo'annoo Digrii Lammaaffaa Kan Hin maxxaffamni.

Ben-Amos, D. (1975a). *Folklore in Africa Society Research in Africa Litertaure.*

Ben-Amos, D. (1979). *Toward definition of Folklore in context*. The Journal of American Folklore, Vol. 84,No.331.

_____. (1993). *Theorizing Folklore: Towards New Perspective on the Politics of Culture*.

____. (2006). *Folklore in Context*. Nordic journal of African Studies. NewDelhi: Vol.15.No.3. South Asia Publishers.

Ben-sly, R. and Brooking, J. (2009). *Community Health Education Methods: A Practical Guide.* Canada: Jones and Bartlett Publishers.

Berger Peter and Luckmann. (1966). *The Social Construction of Reality.* United States of America.

Best Jhon, & Jems V. Kahn. (1993). *Research in Education* (7th ed.) New Delhi: Printice Hall of India Private Limited Press.

BezuAyehu Ayele. (2009). "Vulnerabiltyof Woman to HIV/AIDS: The Lived" Experience of Woman Living with HIV/AIDS in Fche Town", North Shewa Zone of Oromia National Reginal State Addis Ababa. Graduate Studies. AAu: Unpublished MA Thesis.

Bodenstien, M. & Gisela, W. (2005). *Teaching about HIV and AIDS.*Malaysia: Macmillan Publishers Limited.

Brooks, G.j. and Furstenberg, F.F. (1989). *Adolescent Sexual Behavior.* American psychologist.

Brunvad, V. (1979). *Reading American Folklore.*

CDC. (2013). CDC Fact sheet: Incidence, Prevalence, and Cost of Sexually Transmited Infections in the United States. www.cdc.gov/std.Februry,2013.

CDC. (2014). CDC Fact sheet: Reported STDs In the United States. 2014 National Data for Chamydia, Gonorrhea, and Syphilis. www.cdc.gov/std.November,20135.

Creswell,J.W. (2007). *Qualitative Inquiry Research Design: Choosing Among Five Approaches.* (2nd ed.)Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications,Inc.

Crowley,D.j. (1982). *The Erotic, The Pornographic and The Vulgar in Africa*

Arts. UCLA. Jams Coleman: African Studies Center.

CSA. (2011). *Ethiopia Demographic Health survey*. Perliminary Report. A.A.

Desta Desalegn. (2015). "A Fuctional Study of Tulama Oromo Oral Prose Narratives." School of Graduate Studies. AAu: Unpublished PhD Thesis.

Dirribii Damissee Bokkuu. (2009). *Ilaalcha Oromoo.* Barroo Aadaa, Seenaa fi Amantaa Oromoo. Finfinnee. Mana maxxansaa D.G.

Dorson, R.M. (1963). Current Folklore Theories: Current Anthropology, Vl. 4, No. 1. (Feb., 1963), pp. 93-112. Stable URL; http:// www.jstor/stable/2739820. Accessed 17/02/2008 11:12

________. (1972). *Concept Folklore and Folk life Studies: An Introduction. Chicago:* Chicago University press.

Dundes, A. (1965). *The Study of Folklore*. Englewood: N.J. prentice Hall Inc.

____.(1980). *Interpreting Folklore*. Bloomington: Indian University Press.

____. (1989). *Folklore Matters*:The Psychoanalytic Study of the Grimm's tales. USA Knoxville: The University of Tennessee Press.

____. (2004). "Folkloristics in the Twenty - First Century" (AFS Invited Presidential Plenary Address). *Journal of American Folklore.* Vol. 118, No. 470, pp.2005.

Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, Laurence A, Basirico. (1993). *Sociology: An Introduction* (4th ed.) New York: Harper Collins College Pubilisher.

Egbe, D. (2000). *Mastering English Usage and Communication Skills*. Lagos: Tisons Limited Press.

Emana Beyene. (2015). “Historical Documantation and Thematic Analisis of Waaqeeffanna Religion and Songs among Tulama Oromo.” School of Graduate Studies. AAu: Unpublished PhD Thesis.

Ember, C. R. and Ember, M. (2003).*Men and Women in the World’s Cultures. Encyclopedia of Sex and Gender:* Volume I and II.United State of America: Springer Science + Business Media, Inc.

Ephraim, T. G. (2011). *Exploring Shona Proverbial Moral Teaching in Face of HIV/AIDS.* journal Sustainable of Development in Africa. Vol.13, No2. Pennsylvania: Great Zimbabwe University.

Ethiopian Public Health Institute. (2014). H*IV Related Estimates and Projections for Ethiopia.* Addis Ababa: FederalMinistry of Health.

Fayeradnd, P. (1998). *Farewell to Reason*. London: Verso Press.

